መስከረም

Maskeram

STANFORD LIBRARIES

▲ የሃሣብ [illegible] ቁጥጥር

▲ የዘመናችን የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የውጭ ፖሊሲ

▲ የባሔራዊ ኢኮኖሚ ግንዛቤና የኋላቀር አገሮች ዕውነታ

▲ ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ

▲ ሽብር ፈጣሪነት—የኢምፔሪያሊዝም ዓይነተኛ መሣሪያ

DT
371
M469
1976

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ 4 ቁጥር 15
መስከረም 1976

Digitized by Google

Digitized by Google

ET4116760P
9

መስከረም

ቅጽ 4 ቁጥር 15
መስከረም 1976

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ማ ው ጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገፅ 3
- የሐሳብ ሥርጭት ቁጥጥር 13
  —ተስፋዬ ሸዋዬ
- የዘመናችን የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የውጭ ፖሊሲ
  —አንዳንድ ነጥቦች 21
  —አበበ ወርቁ
- የብሔራዊ ኢኮኖሚ ግንዛቤና የኋላቀር አገሮች ዕውነታ 44
  —ከበደ ገ/መድኅን
- ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ 59
  —ጌታቸው ርበሌ
- ሽብር ፈጣሪነት—የኢምፔርያሊዝም ዓይነተኛ መሣሪያ· 72
  ወልዴ ዮሐንስ ወርቅነህ

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ
ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

አድራሻ
የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

Digitized by Google

ያለ አብዮታዊ ንድፈሐሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም!

Digitized by Google

የዝግጅት ገጽ

የማሌ ፓርቲ–አማራጭ የማይገኝለት የትግል መሣሪያ

የወቅታችን የታሪክ ገስጋሴ እጅግ በጣም የተፋጠነ ነው ። ጭቁናችና ምዝብርቻ ለእውነተኛ ፍትሕ ፣ ለነፃነት ፣ ለእኩልነትና ለወል ብልጽግና የተወሳሰበና የተፋፋመ ትግል በማድረግ ላይ ናቸው ። የተያያዝነው የታሪክ ምዕራፍ የሰው ልጆች ከካፒታሊዝም ወደሶሻሊዝም ፣ ከጭቆናና ብዝበዛ ሥርዓት ወደአዲስ የእውነተኛ ነፃነትና እኩልነት ሥርዓት የሚተላለፉበት ወቅት መሆኑ በተግባር ከተከሰተ በርካታ ዓመታት ሆኖታል ።

በኢምፔሪያሊዝምና በሶሻሊዝም መካከል የሚካሔደው የሞት የሽረት ፉልሚያ ከተቀጣጠለና ይፋ ከወጣ ከገማሽ ምዕት ዓመት በላይ የሆነ ጊዜ አልፏል። በዛሬው ጊዜ ይህ ፍልሚያ እጅግ ከላቀ ደረጃ ላይ ደርሶ ይገኛል ። በኢምፔሪያሊዝም የበላይነት ይመራ የነበረው የበዝባዦችና የጨቋኞች ጐራ ከታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት ወዲህ የምዝበራ መስኩ እንዳይጠብበት ፣ የሚያጋብሰው ትርፍ እንዳይቀንስበት ፣ የያዘውን ላለመልቀቅ የመከላከል ፣ የማፈግፈግ ፣ የመወራጨት ትግል ውስጥ ገብቷል ። በዚህ አንፃር የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ሰንደቅ ከፍ አድርገው የሚያውለበልቡት ሶሻሊስትና ተራማጅ ኃይላት ድልን በድል ላይ እየደረቡ የማጥቃትና ወደፊት የመገፋት ትግልን በማፋፋም ላይ ይገኛሉ ።

በዛሬው ወቅት በብዙ መቶ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ምዝብሮችና ጭቁናች ከተራማጅ ኃይሎች ጋር በመደጋገፍ በበዝባዥና ጨቋኝ መደቦች ላይ የሚያካሔዱት ትግል በውስብስብነቱና በመራራነቱ ወደላቀ ደረጃ ላይ ደርሶአል። የአገርና የዘር ፣ የቋንቋና ሃይማኖት ፣ የቀለምና የባህል ወዘተ ... ልዩነት ሳይገድባቸውና ሳይከለክላቸው ፣ ለአንድ ዓላማ ትከሻ ለትከሻ ተደጋግፈው ክንዳቸውን አስተባብረው ከመደብ ጠላቶቻቸው ጋር በርዕዮተዓለም ፣ በፖለቲካ ፣ በትጥቅ ወዘተ ... ውጣ ውረድ የተመላበት መራራ ትግል እያካሔዱ ነው ። በዚህ ፍልሚያ ውስጥ በየሰዓቱ ፣ በየቀኑ በብዙ መቶና ሺ የሚቆጠር ሕይወት ይረገፋል ፤ ለረሃብና ለበሽታ ፣ ለስደትና ለመንከራተት ፣ በአንድ ቃል ለሥቃይና ለሰቆቃ የሚዳረጉት ቁጥር በአያሌ ሚሊዮን የሚቆጠር ነው።

በ1917 * ባንዲት አገር ማለትም በሶቭየት ኅብረት የተመሠረተው የሶሻሊዝም ጎራ ዛሬ ከአርባ በመቶ በላይ የሆነውን የዓለም ሕዝብ ያቀፈና በቀላሉ የማይበገር ኃይል ሆኗል ። በልዩ ልዩ ደረጃና አቀጣጫ ለሐቀኛ ደሞክራሲና ለሶሻሊዝም የሚዋደቁትን ሕዝቦች የተመለከትን እንደሆነ ይህ ግምት እጅግ በጣም ከፍተኛና አብዛኛውን የዓለም ሠርቶአደር ሕዝብ እንደሚያጠቃልል አይጠረጠርም ።

ሶሻሊዝም ዛሬ ትልቅ የማይበገር ታዳጊ ኃይል በመሆን በኢምፔሪያሊዝም የሚመራውን የጨቋኞችና የበዝባዦች ጎራ በማርበድበድ ላይ ለመገኘት የበቃው እንዲ

---

* በዚህ መጽሄት ውስጥ በሚገኙት ጽሑፎች የተመለከቱት የዘመን አቆጣጠሮች በተለይ ካልተጠቀሱ በስተቀር እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው ።

Digitized by Google

ያው በቀላሉ አይደለም ። የጭቁኖችና የምዝብሮች የአያሌ ምዕተ ዓመታት ትግልና መስዋዕትነት ሊሠምርና ፍሬ ሊሰጥ የቻለው የማሌ ሳይንስ ባስታጠቃቸው ሳይንሳዊ ስልትና በማሌ ፓርቲ አማካይነት ባገኙት ብርቱ የትግል መሣሪያ መሆኑ እዚህ ላይ ደህና ተደርጎ መጤን አለበት ።

ሌኒን የማሌ ፓርቲ ለጭቁኖችና ለምዝብሮች ፍቱን የሆነና አማራጭ የሌለው የድል መሣሪያ መሆኑን ሲያመለክት «የአብዮታውያንን ድርጅት ካገኘን ሩሲያን እንገለባብጣታለን ።» * በማለት ገልጾታል ። የመጀመሪያዋንና ታላቋን የሶሻሊስት አገር ማለትም ሶቭየት ኅብረትን በማስገኘት ለሶሻሊዝም መስፋፋትና አሁን ከደረሰበት የላቀ የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ ግንባር ቀደሙንና የአዝማችነቱን ሚና የተጫወተው አዲሱ ዓይነት የሌኒኒስት ፓርቲ እንደሆነ የታወቀ ነው ። ይህም የፖለቲካ ድርጅት በማሌ ንድፈ ሐሳብ የታጠቀና ከብረት በጠነከረ ዲስፕሊን የሚመራ የቦልሼቪክ ዓይነት የትግል ድርጅት ነው ።

ከማርክስና ከኤንግልስ መሠረተ ሐሳብ በመነሣት በሌኒን ከፍተኛ አስተዋጽኦ የተገነባው የመጀመሪያው የቦልሼቪክ ፓርቲ ፣ በዛሩ ግዛት ውስጥ ይጨቆኑና ይበዘበዙ የነበሩትን ወዝአደሮችና ገበሬዎች ነፃ ከማውጣቱና ሰው በሰው የማይበዘበዝበትን የአዲስ ኅብረተሰብ ወራሾች ከማድረጉም በላይ ፣ በዚሁ አምሳል በየአገሩ የወዝአደር ፓርቲዎች እንዲመሠረቱና ከራሉቹ የድል ባለቤቶች እንዲሆኑ በማድረግ በኩል የላቀ ሚና ተጫውቷል ፤ በመጫወትም ላይ ይገኛል ።

የዚህ ዓይነት ማለትም የቦልሼቪክ ዓይነት የወዝአደሩ ፓርቲ በውስብስብና ረዥም መራራ ትግል ውስጥ በማለፍ አድኃሪ የጭቆናና የብዝበዛ ሥርዓትን በመገርሰስ የሠራተኛውን ሕዝብ የበላይ ገዥነት በመመሥረት ብቻ አይቆምም ። ከዚህ ለጥቆ የሚመጣውን ቀለበሳን የማክሸፍና የረዥሙን የግንባታ ትግልም በድል አድራጊነት የሚወጣ መሆኑን በሶሻሊዝም ግንባታ ዛሬ ከላቀ ደረጃ ላይ ከደረሱት ሶሻሊስት አገሮች ልምድ የምንገነዘበው ሐቅ ነው ። ሶቭየት ኅብረት እንደተመሠረተች ከ14 የማያንሱ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ከውስጥ አድኃርያን ጋር በመተባበር ያካሄዱትን የቀለበሳ ጦርነት በድል አድራጊነት ለመወጣት የተቻለው በቦልሼቪክ ፓርቲ አደራጅነት ፣ አስተባባሪነት ፣ አቀናጅነትና ግንባር ቀደም መሪነት እንደሆነ የታወቀ ነው ። የሶቭየት ኅብረት ሕዝብ በልዩ ልዩ መልክ የተካሄደበትን ቡርቦራ ፣ አሻጥር ፣ የኢኮኖሚ ማዕቀብና ሌሎችም ተፅዕኖዎችን አክሽፎ በዓለም ላይ አቻ የሌለውን የፋሽዝም ጦርነት በከፍተኛ መስዋዕትነት ድል መትቶ የግንባታውን ምዕራፍ ወደላቀ ደረጃ ለማድረስ የቻለው በሐቀኛና ቆራጥ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች የተገነባ የቦልሼቪክ ፓርቲ ስለአለው መሆኑ የሶቭየት ኅብረት ሕዝብ የትግል ታሪክ በሕያውነት የሚመሰክረው ሐቅ ነው ።

በዛሬው ወቅት የጭቁኖችና የምዝብሮች አብዮቶች ነባራዊ ሁኔታዎች ሲሟሉ፣ ኢምፔሪያሊዝምና አድኃሪ የገዥ መደቦች ባልጠበቁበት ወይም ከፍተኛ ትኩረት ባላረጉበት ወቅትና የኃይል ሚዛንም ወደ ተራማጆች በሚያዘነብልበት ልዩና አጋጣሚ ሁኔታ ሊቀጣጠሉና ድልን ሊቀዳጁ የሚችሉ መሆኑ የታወቀ ነው ። ሆኖም ውስብስቡንና መራራውን ትግል አልፎ አዲስ በፍትሕ ፣ በእኩልነት ፣ በነፃነትና በወል

---

* ሌኒን ፣ ስብስብ ሥራዎች ፣ ቅጽ 5 ፣ ገጽ 467

ብልጽግና ላይ የተመሠረተ ኅብረተሰብ ለመገንባት የቦልሼቪክ ዓይነት ፓርቲ የማይታለፍ ወይም የማይዘለል ገደታ ነው ። በሐቀኛና ቀራጥ አብዮታውያን የተገነባ የቦልሼቪክ ዓይነት ፓርቲ በሌለበት ሁኔታ ሶሻሊዝም ሊገነባ አይችልም ። የወቅታችን የታሪክ ሐቅ ይህ ነው ። አያሌ ቦገ ብለው የተጻፉት ፣ በልዩ ልዩ ሁኔታዎች የተቀለበሱ አብዮቶች ከላይ የተባለውን ሐቅ ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩ ናቸው ።

ከዚህ አጠቃላይ አባባልና መንደርደሪያ አለፍ በማለት ስለወዝአደሩ ትግል ፣ ስለፓርቲው ወይም ስለትግል ድርጅቱ አነሳስና ዕድገት ፣ ስለሚያካሂዳቸው አብዮቶች ልዩ ባሕርያት ወዘተ ...ዓበይትና ንዑሀ የሆኑትን ቁምነገሮች አጠር ባለመንገድም ቢሆን መዳሰስ ተገቢ ይመስላል ።

የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መሥራቾች ፣ ማርክስና ኢንግልስ የኅብረተሰብን አመጣጥ ፣ ዕድገትና ለውጥ በማጥናትና በመመርመር ከደረሱባቸው መደምደሚያዎች ውስጥ አንዱ ፣ ከጥንታዊ የጋርዮሽ ስርዓት ወዲህ ያለው የሰው ልጅ ታሪክ የመደብ ትግል ታሪክ መሆኑን ነው ። ይህ የመደብ ትግል ታሪክ የምርት መገልገያዎችና ምርቱም ጭምር የግል መሆናቸው ቀርቶ የኅብረተሰቡ የወል ወይም ማኅበራዊ በመሆን «ከያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደፍላጐቱ» የሚለው ኮሚኒስታዊ መርሕ ተግባራዊ እስከሚሆንበት ድረስ በልዩ ልዩ መልክና ደረጃ ይቀጥላል ።

ኅብረተሰብ በመደብ ከተከፋፈለበት ጊዜ ጀምሮ ጭቁናችና ምዝበርች ባንድ በኩል በመሆን ከበዝባዦችና ጨቋኞች ጋር ያልተቋረጠና ውስብስብ የሆነ ትግል ሲያካሔዱ የቆዩ ቢሆንም ፣ በዝባዥና ተበዝባዥ ፣ ጨቋኝና ተጨቋኝ ፊት ለፊት መፋጠጥና ኅብረተሰብ ገልጽ በሆነ መንገድ ሁለት ላይ መከፈል የጀመረው ከካፒታሊስት ስልተ ምርት መምጣት ጋር ነው ። ካፒታሊዝም በንግድና በአነስተኛ ኢንዱስትሪ መልክ ብቅ ማለት የጀመረው በ16ኛው ምዕተ ዓመት በሆላንድ ቢሆንም ፣ ከዚያ ቀደም ብሎ በፊውዳሊዝም ማኅፀን ውስጥ ከ13ኛው ምዕተ ዓመት አንሥቶ ቅድመ ሁኔታዎችን ሲያመቻች ቆይቷል ። በሸቀጥ ምርትና በንግድ መስፋፋት ቁጥራቸው ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ የመጣ ገበሬዎችና የእጅ ባለሙያዎች ከምርት ማከናወኛ መሣሪያቸውና ከመሬታቸው እየተወገዱና እየተላቀቁ የሥራ ኃይላቸውን እየሸጡ እንዲተዳደሩ ተገደዱ ። በሌላ በኩል ደግሞ በዚሁ ሂደት ከፍያለ ሀብት በጥቂቶች እጅ መከማቸት ጀመረ ። የከበርቲው መንግሥትም ከባድ ሕጎችን በማወጅ ልዩ ልዩ ታክስና ግብር በሠርተአደሮችና ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ላይ በመጫን ፣ ሥራ ፈቶችን ከባድ ቅጣት በመቅጣትና ረዥም የሥራ ሰዓት እንዲሠሩ በማድረግ ፣ ለሀብታሞችና ለከበርቲዎች የሚጠቀሙ መሠረተ ልማቶችን በማስፋፋትና የተለያዩ ድጋፎችን በመስጠት ለካፒታሊዝም ዕድገትና መዳበር በቀላሉ የማይገመት አስተዋጽኦ አድርጓል ።

የወዝአደሩ መደብ መከሰት ከካፒታሊዝም ጋር የተያያዘ የዚህ ስልተ ምርት አካልና ውጤት የመሆኑን ያህል ዕድገቱና መስፋፋቱም ከዚሁ ተነጥሎ ሊታይ አይችልም ። በእንግሊዝ ከ18ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ በአሜሪካና በሌሎች የአውሮፓ አገሮች ከ19ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ፣ በኢንዱስትሪ አብዮት አማካይነት የተንሰራፋው ካፒታሊዝም ወዝአደሩ «መደብ በራሱ» መሆኑ ቀርቶ «መደብ ለራሱ» በመሆን እንዲቆም ያደረገበት ፣ ማለትም ተበዝባዥና ተጨቋኝ መደብ መሆኑን እየተገነዘበ ለመምጣት የቻለበት ወቅት ነው ። በካፒታሊስቱ መደብ የሚደርስበትን ብዝበዛና ጭቆናም በግልና በተናጠል ብቻ ሳይሆን በኅብረት እንደመደብ ሆና መቋቋምና

መታገል ጀመረ ። ታላቁ የወዝአደር ፈላስፋና መሪ ካርል ማርክስ በታዋቂ ሥራው በካፒታል ውስጥ ይኸንን ሁኔታ ፣ «የካፒታል ክምችት እያደገ ሲሔድ ፣ የሠራተኛው መደብ ንቃተ ሕሊናና የመደብ ትግሉም ያድጋል፡ » * በማለት ሁለቱም የተያያዙ መሆናቸውን አሳይቷል ።

በሌላ በኩል ሌኒን የትግሉን ባሕሪና አቀጣጫ ሲያብራራ ፣ «እያንዳንዱ ወዝ አደር የመላው ወዝአደር መደብ አካል መሆኑን ሲገነዘብ ፣ ለካፒታሊዝም በቀጥታ በግ ለሰብ አሠሪዎችና በመንግሥት ባለሥልጣናች ላይ የሚያካሒደው ትግል በመላው የቡርዧ መደብና መንግሥት ላይ የተቃጣ ትግል መሆኑን ሲረዳ ያንጊዜ ፣ ትግሉ የመደብ ትግል ይሆናል፡» ** በማለት በትክክል አስቀምጦታል ።

ወዝአደሩ ከእጅ ወደአፍ የሆነችውን የሥቃይ ምንዳ ለማስጨመር በቀን እስከ 16 እና 18 ሰዓት ይደርስ የነበረውን የሥራ ጊዜ ለማስቀነስ ፣ ተስማሚ ያልሆነው ንና አደገኛ የነበረውን የሥራ ሁኔታና አካባቢ ለማሻሻል ፣ በማኅበር የመደራጀትና ሌሎችም ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በማስመልከት ከባድና መራራ ትግል አካሂዷል ። በዚህም ሂደት በመረዳጃና በሙያ ማኅበር በመደራጀት የተጀመረው ረዥም ፀረ ብዝ በዛና ፀረ ጭቆና ትግል ቀስ በቀስ ወደፖለቲካ ትግልና ወደፖለቲካ ድርጅት መመ ሥረት ሊያመራ ቻለ ።

ሌኒን የወዝአደሩን የፖለቲካ ትግል ባሕርይና ሂደት አስመልክቶ ሲናገር ፣ «የመደብ ትግሉ እያደገ የሚሔድና ዘላቂ የሚሆነው በፖለቲካ ክልል ውስጥ ስላለ ብቻ አይደለም ። ...የመደብ ትግሉን የተሟላና አገር አቀፍ አድርገን የምንወስደው በፖለቲካ ክልል ውስጥ ስላለ ብቻ ሳይሆን ፣ ቁልፍ የፖለቲካ ጥያቄ የሆነውን የመን ግሥት ሥልጣን ጥያቄ የተመለከተ እንደሆነ ነው፡» *** በማለት አብራርቶ ነበር ።

በመጀመሪያ የቡርዧው መደብ ተቀጥላ ፣ ከዚያም በንዑስ ከበርቴው አመራር ሥር በመሆን ይታገል የነበረው የወዝአደር መደብ ፣ የራሱ የሆነ የፖለቲካ ድርጅት አቋቁሞ ካልታገለ በስተቀር ፣ ራሱንና ሌሎችንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ነፃ የማው ጣትና ብዝበዛና ጭቆና የሌለበት ኅብረተሰብ ለመገንባት የማይችል መሆኑን ማርክስ ስና ኤንግልስ በቀመሩት የሳይንሳዊ ኮሚኒዝም ንድፈሐሳብ ውስጥ ከማብራራታቸ ውም በላይ ወደተግባርም በመተርጎም ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

«ወዝአደሩ አስፈላጊ የሆነውን ኃይል በመሰብሰብ በወሳኙ የትግል ወቅት በአ ሸናፊነት ሊወጣ የሚችለው ፣ የመደብ ንቃት ያለው ፣ ከሌሎች ፓርቲዎች ሁሉ የተለየና ከነሱ ጋር በተፃራሪነት የቆመ ፣ የራሱ የሆነ ፓርቲ ሲመሠርት ብቻ ነው፡» **** በማለት ማርክስና ኤንግልስ ወዝደሩ የራሱ የሆነ ፓርቲ እንደሚያስፈልገው ቀደም ብለው አስገንዝበው ነበር ። ይኸንንም ተግባራዊ ለማድረግ ዓለም አቀፍ የወዝአደሮችና የታጋይ ኮሚኒስቶች ድርጅቶችን የመሠረቱ ሲሆን ፣ እነሱም ኮሚኒስት ሊግ ፣ አንደኛው ኢንተርናሽናልና ሁለተኛው ኢንተርናሽናል በመባል የሚታወቁት ናቸው ።

---

* ካርል ማርክስ ፡ ካፒታል ፡ (ሞስኮ 1965) ፡ ቅጽ 1 ፡ ገጽ 653

** ሌኒን ፡ ስብስብ ሥራዎች ፡ ቅጽ 4 ፡ ገጽ 215

*** ሌኒን ፡ ስብስብ ሥራዎች ፡ ቅጽ 19 ፡ ገጽ 97—98

**** ካርል ማርክስና ፍሬድሪክ ኤንግልስ ፡ ምርጥ ደብዳቤዎች ፡ ገጽ 386

Digitized by Google

ማርክስና ኢንግልስ የድርጅትን መሣሪያነት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በማጤን ወዝአደሩን በዓለምአቀፍ ደረጃ ለማሰባሰብና ለማስተባበር ያደረጉት ትግል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ ቢሆንም ፣ ንዑስ ከበርቴዎችና ሌሎችም ወዝአደር ያልሆኑ ከኅብረተሰቡ ልዩ ልዩ ክፍሎች የመጡ ቡድኖችና ግለሰቦች ሠርገው በመግባትና በመቀላቀል የወዝአደሩን የሙያና የፖለቲካ ድርጅቶች አመራር ሊይዙና ውዥንብር ሊፈጥሩ ቻሉ ። በተለይም ሁለተኛው ኢንተርናሽናል በአድርባዮች አመራር ሥር በመውደቁ፣ የወዝአደሩ ትግል አቅጣጫውን መሳቱን በተጨባጭ ካደረገው ሳይንሳዊ ትንተና የተገነዘበው ፣ የማርክስና የኢንግልስ ግንባር ቀደም ደቀመዝሙር የሆነው ሌኒን አድርባዮች ካቋቋሟቸው ሶሻል ደሞክራቲክ ፓርቲዎች የተለየ አብዮታዊ ፓርቲ መሠረተ።

በሌኒን የተመሠረተው አዲሱ ዓይነት አብዮታዊ የወዝአደር ፓርቲ መሠረታዊ ባሕርያት ፦1/ በቆራጥና በሐቀኛ ማርክሲስቶች የተገነባ ፣ 2/ የሠራተኛው መደብ የተደራጀና የላቀ አካል ፣ 3/ በዓላማና በተግባር አንድነት ላይ የተገነባ ፣ 4/ ከሰፊው ሠርተአደር ሕዝብ ጋር የተሳሰረና የተለየ ጥቅምና ዓላማ የሌለው ፣ 5/ በወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት የጸና እምነት ያለው ፣ 6/ በአሠራሩ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን ተግባራዊ የሚያደርግ ፣ 7/ አንድ ወጥ የሆነና ሠራተኛውን መደብ በሙሉ የሚወክል ፣ እንደብረት በጠነከረ ዲስፕሊን የሚመራ መሆኑ ናቸው ። እነዚህ ባሕርያት ናቸው የቦልሼቪክ ፓርቲ የመጀመሪያውን ሶሻሊስት አገር ለመመሥረትና ከኢምፔሪያሊስቶችና ከአድኃርያን የቀልበሳ ወረራና ቡርቦራ ለመከላከልና የአዲሱን ኅብረተሰብ ግንባታ ከላቀ ደረጃ ላይ ለማድረስ ያስቻሉት ።

የሶቭየት ኅብረት መመሥረትና ከኢምፔሪያሊዝምና ከአድኃርት ወረራ፣ ከቀልበሳና ቡርቦራ ሙከራ በድል አድራጊነት መውጣት ፣ በሶሻሊዝም ግንባታ ወደፊት መግፋት፣ ምዝብሮችንና ጭቁናችን ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ አድኃርት የሆነውን፣ ለዲሞክራሲና ለሶሻሊዝም የሚያደርጉትን ትግል አጠናክሮታል፤ አፋፍሞታል ። ይህ አዲስ ክስተት የዘመናችን ዓይነተኛ እንቅስቃሴ ለሆነው ለማኅበራዊ አብዮት መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል ።

በመሠረቱ ካንድ ሥርዓተ ማኅበር ወደሌላውና ከፍተኛው ሥርዓተ ማኅበር የተደረገውና የሚደረገው ለውጥ ወይም ሽግግር በልዩ ልዩ ሁኔታና መልክ በብዙኃን ተሳትፎና ድጋፍ ወይም ተቀባይነት የሚከናወን ነው ። የአብዮቶች አነሳስና ሂደት እንደሚያሳየው የነበረን ወይም ያለን በዝባዥና ጨቋኝ ሥርዓት ለመገርሰስና ለመለወጥ የአብዛኛውን ሕዝብ ድጋፍና ተቀባይነት ማግኘት ያስፈልጋል።የቡርዧው መደብ ፊውዳሊዝምን ሲያስወግድ ፣ «ነፃነት ፣ እኩልነት ፣ ወንድማማችነት ፣» በሚለው መፈክር የወዝአደሩን ፣ የገበሬውን ፣ የአብዛኛውን ሠርተአደር ሕዝብ ተሳትፎና ድጋፍ ለማግኘት ችሎ ነበር ። ይሁንና ከጥቂት ጊዜ በኋላ የትግሉ ፍሬ የባለ ሀብቱና የከበርቴው እንጂ ጭ[illegible]ችና ምዝብሮች ግን ከቀንበራቸው አለመላቀቃቸው ይፋ ሆነ ። በቡርዧው መፈክር ሥር አንድ በዝባዥና ጨቋኝ ሥርዓት በሌላ ጨቋኝና በዝባዥ ሥርዓት ተተካ እንጂ የብዙኃኑ ሠርተአደር ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ መሠረታዊ ለውጥ አላሳየም፤ ሊያሳይም አይችልም ።

የወቅታችን ማኅበራዊ አብዮት ከቀድሞዎቹ አንፃር ሲታይ የዓይነት ለውጥ አለው ። ጭቁኖችና ምዝብሮች ድጋፍ ሰጭ ወይም ተቀባይ ብቻ ሳይሆኑ ቀጥታ ተሳታፊና ወሳኝ ገቢራዊ ሚና የሚጫወቱ መሆናቸው ካለፈው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ጀምሮ

Digitized by Google

በልዩ ልዩ የዓለም ክፍሎችና አገሮች የተካሔዱትና በመካሔድ ላይ ያሉት አብዮታዊ እንቅስቃሴዎች በተጨባጭ የሚያረጋግጡት ነው ። እነዚህ ለዲሞክራሲ ፣ ለነፃነት ፣ ለሶሻሊዝም የሚካሄዱት አብዮቶች የመጨረሻና ዘላቂ ዓላማቸው በአብዛኛው ፣ ሰው በሰው የማይበዘበዝበትን ፣ እውነተኛ ፍትሕ ፣ እኩልነትና ማኅበራዊ ብልጽግና የሰፈነበትን ኅብረተሰብ ለመገንባት መሆኑ የጊዜያችን የሕዝቦች የትግል ታሪክ የሚመሰክረው ነው ። ጭቁናችና ምዝብሮች እንደዚሁም ተራማጅ የኅብረተሰብ ክፍሎች በእነዚህ አብዮታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በግንባር ቀደምትነት የሚሳተፉና ከፍተኛ መስዋዕትነት የሚከፍሉትም መደብ አልባ ኅብረተሰብ ለመመሥረት እንደሆነ ግልጽ ነው ።

የሶሻሊስት አብዮት ከሌሎቹ አብዮቶች ጋር ሲነፃፀር ሥር ነቀልና መሠረታዊ ለውጥን የሚያመጣ ፣ የግል ንብረትን በወል ወይም በማኅበራዊ ይዞታ የሚተካና ለሰው ልጅ እውነተኛውን ነፃነትና እኩልነት የሚያጐናጽፍ ነው ።

ማርክስና ኤንግልስ ከዛሬ መቶ ሠላሳ ዓመታት በፊት በዝነኛው ሥራቸው «የጀርመን ርዕዮተ ዓለም» በተሰኘው መጽሐፋቸው አዲሱ አብዮት ከሌሎች ቀድመው ከነበሩት አብዮቶች እንደት እንደሚለይ ሲገልጹ ፣ «የእስካሁኑ አብዮቶች ሁሉ የክንዋኔን ስልት ሳይለኩ ፣ ያተኮሩት በክንዋኔ አደላደል ፤ አዲስ ሥራን ለሌሎች ሰዎች በማከፋፈል ላይ ነበር ። የኮሚኒስት አብዮት ግን በነበረው የክንዋኔ ስልት ላይ የተሰነዘረ ፣ የግል ንብረትንና የመደብ አገዛዝን ጨርሶ የሚያወድም ይሆናል ፤ ምክንያቱም ይህ የሚከናወነው በኅብረተሰቡ ዘንድ እንደመደብ በማይቆጠርና ተቀባይነት በሌለው መደብ ፣ ራሱ የመደቦች ፣ የብሔረሰቦች ወዘተ ...ዝቅጠት ተደርጎ በሚቆጠረው የኅብረተሰብ ክፍል በመሆኑ ነው ፤» * ብለው ነበር ።

በካፒታሊስት ሥርዓት ቡርዧው ወዝአደሩን ከምርት መገልገያዎች ጋር በማቀናጀት ተረፈ እሴትን ያስፈጥረዋል ፤ በዚህም የግል ሀብት ይዞታውን ያስፋፋበታል ፤ መልሶም ወዝአደሩን የበለጠ ይበዘብዝበታል ። ወዝአደሩ ከዚህ ለመውጣት ወይም ለመዳን የግል ሀብትን ማጥፋት ወይም የወል ማድረግ ይኖርበታል ። ይኸንን ለማድረግ ደግሞ መደቦችን ፣ የራሱንም መደብ ጨምር ፣ ማጥፋትና አዲስ መደብ አልባ ኅብረተሰብ መመሥረት አለበት ። በዚህም ሂደት ራሱንና ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችን ነፃ ያወጣል ። ማርክስና ኤንግልስም በሰፊው ጥናትና ምርመራቸው የደረሱበት መደምደሚያ ፣ ማለትም የወዝአደሩ ተልዕኮ ብለው ያስቀመጡትም ይህንኑ ሐቅ ነው ።

የወዝአደሩ ተልዕኮ ይሳካ ዘንድ መራራና ውስብስብ ትግል መካሔድን ይጠይቃል ። በዝባዡና ጨቋኝ መደቦችን ታግሎና ደምስሶ የወዝአደሩን የበላይ ገዥነት መመሥረት ያስፈልጋል ፤ የአድኃርያንና የኢምፔሪያሊዝምን ወረራና ልዩ ልዩ መሠሪ ደባዎች መቋቋምና ማክሸፍ ግድታ ነው ። ከዚህም በላይ ረዥሙንና በውጣ ውረድ የተመላውን የግንባታ ምዕራፍ ከዳር ማድረስ ይጠይቃል ። ወዝአደሩ ይህንን ሁሉ ለማከናወን የሚችለው በሐቀኛና ቀራጥ አብዮታዊያን የተገነባው በአዲሱ አይነት የማሌ ፓርቲው አዝማችነትና መሪነት ብቻ ነው ።

---

* ካርል ማርክስና ፍሬደሪክ ኤንግልስ፣ የጀርመን ርዕዮተዓለም ፣ ሞስኮ ፣ ገጽ 85-86

Digitized by Google

ከፍ ሲል እንደተመለከተው ከካፒታሊዝም ወደሶሻሊዝም ብሎም ኮሚኒዝም የሚደረገውን ሽግግር የማከናወን ታሪካዊ ተልዕኮ የወደቀው በሠራተኛው መደብ ላይ ቢሆንም ፣ ይህ በምርት ክንዋኔ ውስጥ ከፍተኛውንና ወሳኙን ሥፍራ የያዘው መደብ ግደታውን ሊወጣ የሚችለው ሌሎችን ጭቁን የኅብረተሰብ ክፍሎች ለማስተባበርና ለማሰለፍ የቻለና የማሌን ፓርቲ ሐቀኛና ሳይንሳዊ አመራር ያገኘ እንደሆነ ብቻ ነው። ይህ የወቅታችን የሕዝቦች ትግል ታሪክ በተጨባጭና በማያጠራጥር አኳኋን ያረጋገጠው ነው ። ፓርቲው ሠራተኛውን መደብ ከሥር ጀምር የመደብ ንቃተ ሕሊናውን በማዳበርና በማሳደግ በልዩ ልዩ መልክና ደረጃ በማደራጀትና በውስብስቡ ትግል ውስጥ አሳልፎ ወደ ሥልጣን ባለቤትነት ያደርሰዋል ፤ ከዚያም የአድኃርያንን ጥቃት እየተከታተለና እያከሸፈ የግንባታውን ተግባር እንዲያከናውን አስፈላጊውን አመራር ይሰጠዋል ።

ሌኒን ይኸንን የወዝአደሩን መደብ ፓርቲ ወሳኝ የሆነ ሚና ሲገልፅ ፣ ያለ ፓርቲው « ወዝአደሩ ሊነቃ ፣ ለመደብ ትግል ሊበቃ አይችልም ፤ ያለዚህ ድርጅት የወዝአደሩ መደብ ንቅናቄ ውጤት አልባ ይሆናል ፤ በታሪክ ውስጥ አንድም መደብ እንኳን ንቅናቄውን ሊያደራጁለትና ሊመሩለት የሚችሉ የራሱ የሆኑ የፖለቲካ መሪዎችና ተወካዮች ሳያፈራ ሥልጣን ሊጨብጥ የቻለ የለም ፤ » * ብሉ ነበር ።

የወዝአደሩ መደብ ፓርቲ ተግባራት አያሌና ውስብስብ ናቸው ። ፓርቲው ከሥር ጀምር ደረጃ በደረጃ በተከታታይና ያለማቋረጥ በማሌ ሳይንስ መሠረት ይገነባል ፤ ይህንንም የሚያከናውነው በሠራተኛው መደብና በውስብስቡ ትግል ውስጥ ስለሚሆን ቀላል ነገር አይደለም ። የሠራተኛውን መደብ በማንቃትና በማደራጀት ሳይንሳዊውን ስትራቴጂና ታክቲክ በመቀየስ በመራራውና በውስብስቡ ትግል ውስጥ ዘልቆ የወዝአደሩን የበላይ ገዥነት በማቋቋም ረዥሙን የግንባታ ምዕራፍ ይያያዛል። የአድኃርያንን የቀልበሳ ሤራ እየመታና እያከሸፈ አዲሱን እውነተኛ ፍትሕ ፣ እኩልነት ፣ ነፃነትና ብልፅግና የሰፈነበትን ኅብረተሰብ ግንባታ ያራምዳል ፤ በሶሻሊዝም አልፎ የመደብ አልባውን ኅብረተሰብ ሕልውና ያረጋግጣል ። እነዚህ ተግባራት ከባድና አያሌ መስዋዕትነት የሚጠይቁ ፣ በረዥም ወቀቶችና ከውስብስብና መራራ ውጣ ውረዶች በኋላ ሊደረስባቸው የሚችል መሆናቸውን ቀደም ብለው የሶሻሊዝምን ግንባታ ከጀመሩት አገሮች ልምድና ታሪክ ለመገንዘብ ይቻላል ። የእነዚህ አገሮችና በአጠቃላይም የዘመናችን የሠራተኛው መደብ የትግል ታሪክ እንደሚያስረዳን እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ተግባራት ሊከናወኑና ከግባቸው ሊደርሱ የሚችሉት በማሌ ሳይንስ አጥብቀ በታጠቀና በቀራጥ ማርክሲስት ሌኒኒስት አብዮተኞች በተገነባ አዲሱ አይነት የማሌ ፓርቲ አመራር ብቻ ነው ።

ይህንኑ በማስመልከት የሌኒን የፓርቲ ንድፈሐሳብ የሚያስገነዝበው « ሥልጣን ለመያዝና መላውን ሰፊ ሕዝብ ወደሶሻሊዝም ሊመራ የሚችለውን ፣ አዲሱን ሥርዓት ሊቀይስና ሊያደራጅ የሚችለውን ፣ የጭቁን ሕዝቦች አስተማሪና መሪ የሆነውን የወዝአደሩን ግንባር ቀደም (ፓርቲውን) ማርክሲዝም የሚያስተምረው ፣ የሰፊ

---

* ሌኒን ፣ ስብስብ ሥራዎች ፣ ቅጽ 4 ፣ ገጽ 370

Digitized by Google

ውን ሕዝብ ሕይወት ያለ ቡርዧውና ቡርዧውን በመፃረር እንዲያደራጅ ነው ።» ከዚህ በመነሣት ነው ሌኒን «የግንባር ቀደም ተዋጊነት ሚናውን ሊያሟላ የሚችለው ፓርቲው በአብዮታዊ ንድፈ ሐሳብ የታጠቀ እንደሆነ ብቻ ነው ፤» * በማለት ለማሊ ፓርቲ የአመራር ብቃት የማሊ ሳይንስ ግንዛቤ ወሳኝ መሆኑን አበክሮ ያስገነዘበው ።

ካፒታሊዝም ሙሉ በሙሉ ባልተስፋፉባቸው አገሮች በካፒታሊስት የዕድገት ደረጃ ሳይታለፍ ወደሶሻሊዝም ለመሸጋገር የሚቻል መሆኑን ከማርክስና ከኤንግልስ አስተሳሰብ በመነሣት በስፋት ያብራራው ሌኒን ነው ። ሌኒን በቅድመ ካፒታሊስት የዕድገት ደረጃ የሚገኙ ሕዝቦች የሶሻሊስት አገሮችን ሠራተኞችና የካፒታሊስት አገሮችን ወዝአደሮችና ተራማጅ ኃይሎች ድጋፍና ርዳታ ካገኙ ፥ ካፒታሊዝምን በመዝለል ወደሶሻሊዝም ሊያልፉ እንደሚችሉ በ1921 በሁለተኛው የኮሚኒስት ኢንተርናሽናል ጉባኤ ላይ ባቀረበው በኩረ ሐሳብ እንደሚከተለው አስቀምጦታል፦

> «አሁን በአርነት ጉዳና ላይና ከጦርነቱ (1ኛው የኢምፔሪያሊስት ጦርነት) በኋላ ርምጃ በማሳየት ላይ በሚገኙት ኋላቀር አገሮች የካፒታሊስት የኢኮኖሚ ዕድገት ጉዳና የማይዘለል ነው የሚለውን አባባል እንደተከከለኛ ልንቀበለው ይገባል? በአሉታ መልሰነዋል ። አሸናፊው አብዮታዊ ወዝአደር በእነዚህ ዘንድ የተቀነባበረ የፕሮፓጋንዳ ሥራ ካከናወነ ፥ የሶቭየት መንግሥታት ባላቸው አቅም ከረዷቸው ፤ በዚህ ሁኔታ ኋላቀር ሕዝቦች የግድ በካፒታሊስት የዕድገት ደረጃ ማለፍ አለባቸው የሚለው አስተሳሰብ ስሕተት ይሆናል ። ራሳቸውን የቻሉ ታጋዮችና የፓርቲ ድርጅቶችን በቀኝ ግዛቶችና በኋላቀር አገሮች ማቋቋም ብቻ ሳይሆን ፥ ተሉ የገበሬዎች ሶቭየቶች ከቅድመ ካፒታሊስት ሁኔታዎች ጋር በተገናዘበ ሁኔታ እንዲደራጁ ፕሮፓጋንዳ ማካሔድ ብቻ ሳይሆን ፥ ይልቁንም ኮሚኒስት ኢንተርናሽናል በተገቢ ንድፈ ሐሳባዊ መሠረት ላይ የተገነባ ፤ በዳበሩት አገሮች ወዝአደሮች ርዳታ ፥ ኋላቀር አገሮች በካፒታሊስት ሥርዓት ሳያልፉ ወደ ሶቭየት ሥርዓት ለመሔድ እንደሚችሉ ሐሳብ ማቅረብ ይኖርበታል ። በተወሰነ የዕድገት ምዕራፍ በማለፍ ወደ ኮሚኒዝም ለመሸጋገር ይችላሉ ።» **

የዚህ የሌኒን ንድፈሐሳብ ትክክለኛነት ዛሬ በተግባር ተረጋግጧል ። ብዙኛው ኋላቀርና የእርሻ አገር የነበሩ ከሶቭየት ኅብረት ጋር ዘጠኝ የአውሮፓ አገሮች የዳበረ ሶሻሊዝምን በመገንባት ላይ የሚገኙ ሲሆን ፥ በእስያ ሰባት ፥ በላቲን አሜሪካ ሁለት ፥ በአፍሪካ ከአሥር በላይ የሆኑ የቀድሞ ቀኝ ግዛትና ጥገኛ አገሮች ደግሞ በሶሻሊዝም የዕድገት ፈለግ በልዩ ልዩ ደረጃዎች ላይ ይገኛሉ ። እነዚህም አገሮች ያቀፉት የሕዝብ ቁጥር ከዓለም ሕዝብ ከሃምሳ በመቶ የማያንስ ሲሆን ፤ በኢምፔሪያሊስትና ታዳጊ አገሮች ለዲሞክራሲና ለሶሻሊዝም በመዋደቅ ላይ የሚገኙት ሕዝቦች ቁጥር እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው ።

ከሐያኛው ምዕተ ዓመት መባቻ ጀምሮ ወደኢምፔሪያሊዝም የዕድገት ደረጃ የተሸጋገረው ካፒታሊዝም ፥ የምዝብርችንና የጭቁኖችን የነፃነትና የእኩልነት ትግል ለመግታትና ይዞታውን ላለመልቀቅ ከፍተኛ የሆነ ፀረ-አብዮት ትግል እያካሔደ ነው ። ካፒታሊዝም አምራቹን የኅብረተሰብ ክፍል በመጀመሪያ ደረጃም ወዝአደሩን በመበዝበዝ ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ ፥ ከአንድ መቶ ዓመት በፊት ለሰባ ሁለት ቀናት ያህል የወዝአደሩን የበላይ ገዥነት ለመመሥረት የሳይንሳዊ ኮሚኒ

---

* ሌኒን ፥ ቀደም ሲል ከተጠቀሰው

** ሌኒን ፥ ምርጥ ሥራዎች ፥ ቅጽ 3 ፥ ሞስኮ ፥ 1977 ገጽ ፥ 408

Digitized by Google

ዝምን ንድፈ ሐሳብ ተግባራዊነት ያረጋገጠውን የፓሪስ ኮሙን በደም ያጥለቀለቀውን ያህል የሩስያን ታላቁን የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት ለመደምሰስ ከየአቅጣጫውና ከየማዕዘኑ ወረራ በማካሔድ በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎችን ሕይወት አጥፍቷል። ዛሬም ቢሆን ሶሻሊስት አገሮችን መተናኮሉንና መጻረሩን ከቶውንም አላቆመም። ባሁኑ ወቅት ከሶቭየት ኅብረት ጋር ለጦርነት የሚያደርገው ፍጥጫና ተራማጅ አገሮችን በሚመለከት የሚያካሔደው ፀረ አብዮት ደባ፣ ኢምፔሪያሊዝም የጭቀናንና የብዝበዛን ሥርዓት መልሶ ለመገንባት ለሚያደርገው ፍርጋጣ ጉልህ ማስረጃ ሆና ሊቀርብ ይችላል።

ኢምፔሪያሊዝምና በእርሱ የሚመራው የአድኅርት ኀራ ከጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት ወዲህ ከገባበት የቀውስ አዘቅት ውስጥ ለመውጣት በሚያደርገው መፈራገጥ በልዩ ልዩ የዓለም ክፍሎችና አገሮች ቀጥታና የእጅ አዙር ጦርነቶችን አካሂዷል፤ እያካሔደም ይገኛል። ባሁኑ ጊዜ በማዕከላዊ አሜሪካ ማለትም በኒካራጓና በኤልሳልቫዶር በገፍ መሣሪያና ገንዘብ በመስጠት «አማካሪዎቹን» በመላክና የአድኃሪ ገዥ መደቦችን ወታደሮች በማሠልጠን ከፍተኛ ጭፍጨፋና እልቂት በመፈጸም ላይ ይገኛል። በሶሻሊዝም ፈለግ ዕድገታቸውን በመገንባት ላይ ያሉትን እንደ ኢትዮጵያ ያሉትን ተራማጅ አገሮች ፈጣን ጣልቃ ገብ ጦር በማዘጋጀትና በአካባቢያቸው ያሉትን አድኃሪ መንግሥታት በመሣሪያነት በመጠቀም አቀጣጫቸውን ለማስለወጥና ዕድገታቸውን ለማሰናከል የተለያዩ መሠሪ ድርጊቶችን እየፈጸመ ነው።

ኢምፔሪያሊዝምና አድኅርት በተራማጅና ሶሻሊስት አገሮች ላይ የሚፈጽሙትን ደባ ለመቋቋምና ለመምታት የሚቻለው በማሌ ፓርቲ መሪነት ሰፊው ሠርቶአደር ሕዝብ እንደ አንድ ሰው ሆኖ ሲነሣ መሆኑን የወቅታችን የትግል ታሪክ ቁልጭ አድርጎ ያስረዳል። ሰፊው ሠርቶአደር ሕዝብ እንደአቀሙና እንደሁኔታው በፀረ ሕዝብ ኃይላት የሚሰነዘርበትን ወረራ፣ ደባ፣ ቡርቦራና ሌሎችም ፀረ አብዮት ድርጊቶች ነቅቶ መጠባበቅና መከላከል አማራጭ የሌለው ገደታው መሆን ይኖርበታል። ይህ ዓቢይ ተግባር ለዘለቄታው ሊከናወን ወይም ሊሟላ የሚችለው በቀራጥና ሐቀኛ አብዮታውያን በተገነባ አብዮታዊ ፓርቲ ብቻ መሆኑን በሶሻሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም፣ በአድኅርትና በተራማጅ ኃይላት መካከል የተካሔደውና በመካሔድ ላይ የሚገኘው የዘመናችን የትግል ታሪክ በተጨባጭ የሚያረጋግጠው እውነት ነው።

የኢትዮጵያ አብዮት ዘጠነኛ ዓመቱን በሚያከብርበት በአሁኑ ወቅት ይህ ሐቅ ከምንጊዜውም ይበልጥ ጉልቶ ይታያል። ምክንያቱም ይኸ የጀመርነው ዓመት በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ ለአብዮታዊት እናት አገር ብሎም ለሶሺያሊዝም ልዕልና የተዋደቁ አብዮተኞች ሲመኙት የነበረውን፣ አሁንም ለአብዮቱ አሸናፊነት ያለማወላወል የቆሙ ኃይሎች የሚታገሉለትን፣ ዓለምአቀፋዊ አጋርቻችን የሆኑት የኮሚኒስትና የሠራተኛ ፓርቲዎች እንዲሁም ተራማጅ ኃይሎች በሙሉ በጉጉት የሚጠብቁትን ያልተበረዘና ጠንካራ የሆነ የማሌ ፓርቲ ለመመሥረት አስፈላጊው ዝግጅት የሚጠናቀቅበት ዓመት በመሆኑ ነው።

Digitized by Google

ከዚህ ለንጻር በመጋቢት ወር 1975 በተካሄደው የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ስድስተኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ባቀረቡት ማዕከላዊ ሪፖርት ውስጥ፣ የፓርቲውን መዳረሻ ለስተኛና የመጨረሻ ምዕራፍ ተግባር በማስመልከት ሲናገሩ፣ የበፊቱን ለሠራር እንዳለ መቀጠል ሳይሆን ይልቁንም የኢሠፓአኮን ታሪካዊ ተልዕኮ ማጠናቀቅ፣ ይኸውም ኢሠፓአኮ ይዞ የተነሳውን ፓርቲ የማደራጀት መሠረታዊ ዓላማ በተያያዝነው የፓርቲ የመጨረሻ መዳረሻ ምዕራፍ ውስጥ እውን ማድረግ የወቅቱ ዓቢይ ተግባር መሆን እንዳለበት ገልጸዋል።

ጓድ ሊቀ መንበር በዚሁ ማዕከላዊ ሪፖርት ላይ በፓርቲው መዳረሻ ለስተኛና የመቢረሻ ምዕራፍ ወቅት የተወጠኑ ለያሌ ወሳኝ ተግባራትን በማሳካቱ ሂደት ለጠንካራ የማሌ ፓርቲ ምስረታ የቆሙ ኃይሎችን ሚና በማስመልከት ሲያብራሩ፣ «በየተሰማሩበት መስክ መመሪያን በሚያረካ ሁኔታ ተግባራዊ ከማድረግም ባሻገር፣ በግልም ሆነ በወል፣ በእራስ ለነሳሽነት ጭምር አጥፍ ድርብ ውጤት ለማስገኘት ወደር በሌለው ቁርጠኝነት መነሳሳት ከአብዮቱ ወገኖች ሁሉ የሚጠበቅ ነው።» በማለት ለሰጡት መመሪያ ሙሉ ለሙሉ ተፈፃሚ መሆን ለሁንም በበለጠ የጥንካሬ መንፈስ እንሥራ፣ እንራመድ።

Digitized by Google

የሐሳብ ሥርጭት ቁጥጥር

ተስፋዬ ሸዋዬ

በመደብ በተከፋፈለ ስርዓተ ማኅበር ውስጥ ተፃራሪ መደቦች የየራሳቸውን ጥቅም ለማስከበር ትግል ያካሂዳሉ ። ከዚህም የተነሳ ስልጣን የያዘው መደብ በሌላው ላይ የበላይነትን ለማገኘት በሚያስችሉት ስልቶች ሁሉ እንደየሁኔታው ይጠቀማል ። የስልቶቹም ደረጃ የፕሮፓጋንዳና የሀሳብ ስርጭትን ከመግታት (ከመቆጣጠር) እስከ ጦር መሣሪያ መዘዛ ይደርሳል ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በአንድ መደብ ተቀባይነት የሌለው ሀሳብ በጽሑፍ ፣ በስዕል ፣ በቅርጽም ሆነ ተመሳሳይነት ባለው በሌላ መልክ እንዳይሰራጭ ወይም እንዳይገለጽ ስለሚደረገው የሀሳብ ስርጭት ቁጥጥር ለማየት እንሞክራለን ።

የሀሳብ ስርጭትን መቆጣጠር በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ እንደሌለ ፣ ሁሉ እንደፈለገው የሚጽፍ ፣ ሁሉ እንደፈለገው የሚናገር ፣ ሁሉ የፈለገውን ሀሳብ ባመቸው ዘዴ ለማሰራጨት የሚችል እንደሆነ ይወራል ። በሌላ አገላለጽ ለሐሳብ ስርጭት ምንም ገደብ እንደማይበጅለት ይነገራል ። ይህ እንዴት እውነት ሊሆን ይችላል ? ብዙ ዝርዝር ውስጥ ሳንገባ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ጋዜጦች ፣ ማተሚያ ቤቶች ፣ አሳታሚ ድርጅቶች ፣ የመገናኛ ዘዴዎች ፣ አከፋፋዮች በማን ባለቤትነት ስር ናቸው ? ሠርቶአደሩ በእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ተሰማርቶ ጉልበቱን ከመሸጥ አልፎ የመደብ ጠላቱን ለመታገያ ሳውላቸው ቢል ማን እሺ ይለዋል ? ለመሆኑ ሠርቶአደሩ ቢጽፍስ በምን ያሳትማል ? ማን ያሰራጭለታል ? ለእዚህ የሚያበቃው ትምህርትስ መች አግኝቶ ? እነዚህ ጥያቄዎች ሲነሱ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ያለው ነፃነት ሁሉን ያቀፈ ይምሰል እንጂ ነፃነቱን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል ሁኔታ ባለመኖሩ ነፃነቱ የወረቀት ላይ ነፃነት ነው ። ሌኒን እንዳረጋገጠው «ቡርዧው የጽሑፍ ነፃነት ማለት ሀብታሞች እንዲጽፉ ካፒ

Digitized by Google

ታሊስቶች ደግሞ ጋዜጦችን በእጃቸው እን
ዲያደርጉ የሚያስችል ነፃነት ማለት
ነው ። »[1]

በካፒታሊስቱ መደብ አስተሳሰብና አሠ
ራር « ነፃ የሐሳብ ስርጭት » ሲባል የበዝ
ባዡ መደብ አባላት በነፃነት ስም የብዙሀ
ኑን መብት አግደው የራሳቸውን የጥቂት
ወገኖች መብት የሚያስከብሩበት አፈጻጸም
ነው ። ይህንኑ በሚመለከት ሌኒን ስለ ሀሳብ
ስርጭት ሲናገር የሚከተለውን ብሏል ።

ካፒታሊስቶች « ነፃነት » የሚለውን ቃል
ምንጊዜም የተጠቀሙበት የሀብታሞች የበ
ለጠ ሀብታም መሆን ማለት እንደሆነ፣ ለሠ
ራተኞች ደግሞ እስከ ዕለተ ሞት መራብ
ማለት እንደሆነ አድርገው ነው ። በካፒታ
ሊስት አባባል የጽሑፍ ነፃነት ማለት ሀብታ
ሞች ጋዜጦችን የመደለል ነፃነት እንዳላቸው
ሀብታቸውን «የሕዝብ፣ አስተሳሰብ፣ አስተያ
የት» የሚሉትን ለማመንጨያና ለመፍጠ
ሪያ የማዋል ነፃነት አላቸው ማለት ነው ።...
ትክክለኛው ነፃነትና እኩልነት የሚገኘው
ኮሚኒስቶች በሚገነቡት ሥርዓት ውስጥ፣
ማለትም በሌሎች ወዝ ሀብት የማጋበስ ዕድል
በሌለበት ፣ ጋዜጣን በቀጥታም ሆነ በተዘ
ዋዋሪ መንገድ በገንዘብ ኃይል ሥር የማድ
ረግ ነባራዊ ሁኔታዎች በሌሉበትና ሕዝባዊ
የማተሚያ ድርጅቶችንና የሕዝብ የወረቀት
ክምችትን በእኩልነት የመጠቀም ዕድል
ማግኘትና ተግባራዊ ማድረግ በሚቻልበት
ሥርዓት ውስጥ ነው ።[2]

በገብር ሊታይ የማይችል ፣ እንዲታይም
ሁኔታዎች በማይፈቅዱበት ሁኔታ «ነፃነት
ለሁሉም » የሚለው የካፒታሊስት አገሮች
ነፃነት ከንቱ ማወናበጃ ነው ። በግልጽ እን
ደሚታየውና እንደሚታወቀው ደግሞ በሶ
ሻሊስት አገሮች ያለው ነፃነት የሰፊው
ሕዝብ ብቻ ነው ። የመደብ ጥቅምን የሚያ
ስጠብቀው ኃይል - መንግሥት የምንለው-
እስካስፈለገ ድረስ በየትም ሆነ የት የሚጠ
በቀው መብት ፣ ያለው ነፃነት ስልጣን ላይ
ያለው መደብ ነፃነት ነው ፤ በካፒታሊስቱ
መንግሥት የካፒታሊስቱ መደብ ፣ በሶ
ሻሊስቱ መንግሥት ደግሞ የሠራተኛ

መደብ ። ይህ ገሀድና ግዙፍ ሀቅ ሲሆን
ካፒታሊስቶቹ ግን ይህንን ለማድበስበስ
ይጥራሉ ። ከመደብ ጥቅም ውጭ ነፃነት ፣
ከመደብ ጥቅም ውጭ እኩልነት ፣ ከመደብ
ጥቅም ውጭ ወንድማማችነት እንዳለ
ለማሳመን በተለያየ ዘዴ ይሞክራሉ ። በተግ
ባር የሚታየው ግን ሳይንሱ የገለጸው
ሀቅ ነው ። በአለንበት የታሪክ ወቅት መደብ
አልባ የሆነ ነፃነት የለም ።

ይህም በመሆኑ እስካሁን የታዩት የሠ
ርቶ አደሩን ልእልና ለማስከበር የተካሄዱት
አብዮቶች በዝባዥ መደቦችን እንበርክከው
የሀሳብ ስርጭት ነፃነትን ለሠርቶአደሩ ሲያ
ጐናጽፉ በአንፃሩ የበዝባዥ መደቦችን የሀ
ሳብ ስርጭት ነፃነት ማገዳቸውን ይገልፃሉ።
ታላቁ የጥቅምት አብዮት በፈነዳ ሰሞን ሌኒን
የሚከተለውን ገልጾ ነበር ፣

ለሠራተኛውና ለገበሬው መንግሥት የጽ
ሑፍ ነፃነት ማለት ጋዜጦችን ከካፒታሊስ
ቶች ጭቀና ነፃ ማውጣትና የወረቀት ፋብሪ
ካዎችንና ማተሚያ ቤቶችን በሕዝብ ይዞታ
ሥር ማድረግ ነው ። ...ቀደም ሲል ሥል
ጣን ብንወስድ የቡርዧውን ጋዜጣ እና
ግዳለን ብለን ነበር ። የእነዚህ ጋዜጦች
መኖር እንዲቀጥል ማድረግ ማለት ሶሻ
ሊስት መሆንን ማቆም ማለት ነው ። የቡ
ርዧ ጋዜጦች ይኑሩ (ይቀጥሉ) የሚሉ
ወገኖች ወደ ሶሻሊዝም በከፍተኛ ፍጥነት
በመጓዝ ላይ መሆናችንን መገንዘብ ያቃታ
ቸው ናቸው ። . . . ቡርዧው እንዲሳለቀ
ብን ዕድል ልንሰጠው አንችልም ።[3]

የካፒታሊስቱን መሳለቅም ሆነ ሌላ ፀረ-
አብዮት ተግባር ሙሉ በሙሉ ተቋቁሞ የእ
ውነተኛ ነፃነት መገኛ ሥርዓት (ሶሻሊዝም)
ለመገንባት ዋነኛና አስፈላጊ የሆነው የአ
መራር ዘይቤ የወዝ አደሩ የበላይ ገዥነት
መሆኑንም ሌኒን በሚገባ አስረድቷል ።
የወዝአደሩ የበላይ ገዥነትም የቡርዧውን
አምባገነንነት የሚተካ ነው ። የጥቂት ሀብ
ታሞች መብትና ነፃነት ይከበር የሚለ
ውን የበዝባዦችን የመሰብሰብና የመ
ጻፍ ነፃነት በሰፊው ሕዝብ የመሰብሰብና
የመጻፍ ነፃነት የሚተካ ነው ። በአጠቃላይ
አነጋገር የወዝአደሩ የበላይ ገዥነትም የቡ

ርሂውን መንግሥት በሠርቶአደሩ መንግሥት የሚተካ ነው ። ብሉም መንግሥት የተባለው ክስተት እያደር የሚከስምበትን ብቸኛ መንገድ የሚያመቻች ነው ። [4]

መንግሥት በባሕርዩ የኅብረተሰብ በመደብ መከፋፈል ያስከተለው የመጨቆኛ መማሪያ ነው ።[5] ይህ የመንግሥት ባህሪይ ደግሞ ለሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ተከታዮች እንግዳ ነገር ስላይደለ ማርክስና ኤንግልስ «ኮሚኒስቶች አላማቸውን በይፋ ፣ በአደባባይ መግለጽ አለባቸው» ሲሉ የቡርዧው መንግሥት ፈርሶ የሚተካው መንግሥት ሊኖረው ስለሚችለው በዝባዦችን የመጨቆን ባሕሪይ አስረድተዋል ።[6] የመንግሥት ዓይነተኛ ባህሪይ በሥልጣን ላይ ያለውን መደብ መብት አስከባሪ መሆኑ የተረጋገጠ ሆኖ የቡርዧ መንግሥታት ሀቁን በመካድ ለሁሉም መደብ ነፃ የሀሳብ ስርጭት እንፈቅዳለን ይላሉ ። ከዚህም አልፈው ለነፃ የሀሳብ ስርጭትም እንታገላለን ይላሉ ። ይህንንም ከብዙዎቹ የቡርዧ መንግሥታት ጽሑፎችና መግለጫዎች መታዘብ ይቻላል ።

መንግሥት የመደብ ጥቅም ማስከበሪያ መሳሪያ ሲሆን አንዱም የጥቅም ማስከበሪያ ስልት የተፃራሪ መደብን የሀሳብ ስርጭት መቆጣጠር ነው ። የሀሳብ ስርጭትን የመቆጣጠሩ ስልትም ከአገር ወደ አገር ከስርዓተ ማኅበር ስርዓተ ማኅበር ይለያያል። በመጀመሪያ የካፒታሊስቱን ስርዓት የሀሳብ ስርጭትን የመቆጣጠሪያ ስልት እንመልከት ። ለዚህም ጉልህ ምሳሌ የሚሆነን አሜሪካ ነው ። በአሜሪካ ነፃ የሀሳብ ስርጭት ፣ ቁጥጥር የማይደረገበት የሀሳብ ስርጭት አለ ፤ ጽሑፎችም ከመታተማቸው በፊት ቁጥጥር አይደረገባቸውም ይባላል። እንዲያውም የመጀመሪያው የአሜሪካ ሕገ መንግሥት «ምክር ቤቱ የሀሳብ ስርጭትን ነፃነት የሚያግድ ሕግ ማውጣት አይቻለውም » ይላል ። ይሁን እንጂ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ፣ ጽሑፎችን በአሳታሚነት የሚቀበሉ ፣ ተቀብለውም በቀጠሩዋቸው አዘጋጆች የሚያስገመግሙ ፣ ተቀባይነት እንዳላቸው አረጋግጠው የሚያትሙ፤ ካተሙም በኋላ የሚያሰራጩ ድርጅቶች በግል ይዞታ ሥር ያሉ በመሆናቸው ነፃነቱ የይስሙላ ነፃነት ነው ። ፀሐፊው በግሉ ሊያሳትም ስለማይችል ለአሳታሚ ድርጅት ያቀርባል ። ያ አሳታሚ ድርጅት ደግሞ ጽሑፉ ዋጋ ይገኝበታል ወይስ አይገኝበትም ? የድርጅቱን ስም ያጎድፋል ወይስ የበለጠ ደንበኛ ይስብልኛል ? ጥቅሜን ያስከብራል ? ወይስ ይነካል ? የሚሉትንና ሌሎችንም ጥያቄዎች መሠረት አድርጎ ለዚሁ በተመደቡ አዘጋጆች ጽሑፉን ያስመረምራል ።

ይህ ምርመራ በማንኛውም ጊዜ ቢሆን የግል ሀብት ይዞታ ሕልውና መጠበቁን ያረጋግጣል ። ለዚህም ማስረጃው የትምህርት ቤት መጻሕፍትን በሚመለከት «ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ስለሩሲያ ኮሚኒዝም ፣ ማርክሲዝም ወይም ሶሻሊዝም ደጋፊ ተብለው የሚተረጎሙ አስተሳሰቦችና ከተጠርጣሪ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት አላቸው የሚባሉ የመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች » መሆናቸው ነው ።[7] ስለዚህም የሀሳብ ስርጭት ቅድመ ቁጥጥር አይደረግበትም ሲባል የመንግሥት አካል የሆነ የተለየ ድርጅት አይቆጣጠርም ለማለት ካልሆነ በስተቀር፣ከመታተሙ በፊት ቁጥጥር ይደረጋል ማለት ነው ። ከዚህም አልፎ በተደረገ የሀሳብ ስርጭት ተጎድቻለሁ ባይ ከተነሳ ደግሞ በጉዳዩ ተጠያቂ የሆነውን አካል ለመክሰስ መብት እንዳለው ይታወቃል ።[8]

እንግዲህ ከዚህ በላይ ካለው አሠራር ለመገንዘብ እንደሚቻለው ካፒታሊስት አገሮች የፈለጉትን ይበሉ እንጂ የሀሳብ ስርጭት ቁጥጥር ማድረጋቸው እውቅ ነው ። ዋናዎቹም ተቆጣጣሪዎች በሞኖፖል የተያዙት አሳታሚና አከፋፋይ ድርጅቶች ናቸው።እነዚሁ በግል ሞኖፖሊስቶች የተያዙ አሳታሚና አከፋፋይ ድርጅቶች የጽሑፎችን

Digitized by Google

ሕትመትና ስርጭት በሚመለከት ረገድ የወሳኝነት ሚና አላቸው ። [9] ስለዚህም የሚታተመውም ሆነ የሚሠራጨው ጉዳይ ሥልጣን ላይ ያለውን መደብ ሕልውና እንዳይነካ ነቅተው ይጠብቃሉ ማለት ነው ። እርግጥ በአመራር ላይ ያሉትን ቡድኖች የሚነቅፉ የሚመስሉ ወይም ስርዓቱን የሚነኩ የሚመስሉ ጽሑፎች ታትመው ይወጣሉ ። እነዚህም በአጠቃላይ ሲታዩ ሙሉ ነፃነት ያለ ያስመስላሉ ። ይሁን እንጂ እነዚህን መሰል ጽሑፎች መውጣታቸው በገዥ መደብ አባላት መካከል ባለ የገንዘብ ሽሚያና የስልጣን ሽኩቻ ምክንያት እንጂ የሥርዓቱን መሠረት እንዲያናጉ አይደለም። ብዛታቸውም ቢሆን ከሌሎች ሥርዓቱን ከሚያወድሱ ጽሑፎችና ዝግጅቶች ጋር ሲነፃፀር እጅግ በጣም ያነሰ ነው ።

ይህ ደግሞ በዓይነትም በቁጥርም ነው ። የሕትመትና የስርጭት ጉዳይ በግል ባለሀብቶች እጅ በመሆኑ ከላይ የተጠቀሰውን የዓይነትና የመጠን መበላለጥ በሚገባ ይጠብቁታል ። ስርዓቱ የሚቀበለውን በተለያየ መልክና ስያሜ ያቀርቡታል። ቁጥሩን አብዝተው ዋጋውን አሳንሰው በገፍ እንዲሰራጭ ያደርጉታል ። ለስርጭቱም የተጠናከረ የቅስቀሳ ድጋፍ ይሰጡታል ። በአንፃሩም ስርዓቱን የሚነካ የሚመስለውን ጽሑፍ ለተለያየ የማታለያ ምክንያት ሲሉ ቢያትሙትም ቁጥሩ እንዲያንስ ፣ ዋጋው እንዲበዛና ስርጭቱ ውሱን እንዲሆን ያደርጋሉ ። ቅጥረኛ ተቺዎቻቸውም በሚቻላቸው መንገድ ሁሉ እንዲያራክሱት ያደርጋሉ ። «ቤተ መጻሕፍትም አንዳንድ መጻሕፍትን ለመቀበል አሻፈረኝ ይላሉ፤ ወይም ተጠቃሚዎች መጻሕፍቱን እንደልብ እንዳያገኙዋቸው ያደርጋሉ ። » [10] ይህ አሠራር ከሌላውም ጋር ተዳምሮ ያ ጽሑፍ እንዲቀጭ ወይም እንዲታፈን ይሆናል ።

በካፒታሊስት ሥርዓት ከላይ የተጠቀሱት አድራጎቶች የሚፈጸሙት ሥርዓቱን በቀጥታ ይነካሉ ወይም ይገራረሉ በሚባሉት ጽሑፎች ላይ ብቻ አይደለም ። የሥነ ጽሑፍና የሳይንሳዊ ምርምር ይዘታቸውና ደረጃቸው ከፍ ያለ መጻሕፍትም ቢሆኑ ብዙኀኑ አንባቢ እጅ ገብተው እውቀት እንዳያስጨብጡና አእምሮ እንዳያበለጽጉ ቁጥራቸውን አሳንሰው ፣ ዋጋቸውን አብዝተው ያትማሉ ። በአንፃሩ የብዙኀኑን አስተሳሰብ የሚያደነዝዙ ፣ ጭቁኖች የወቅቱን ግፍና በደል ይበልጥ ተገንዝበው ለተሻለ ማኅበራዊ ኑሮ እንዳይታገሉ አስተሳሰባቸውን የሚያዛቡ የውንብድና ፣ የፍትወተ ሥጋ ፣ የፌዝና የመሳሰሉትን ጉዳዮች የሚያንፀባርቁ ጽሑፎችን በገፍ በማተም እጅግ አነስተኛና ማንም ሊገዛ በሚችለው ዋጋ ያቀርባሉ ። [11]

እስካሁን የተገለፀው በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ለሚታተሙና ለሚሠራጩ ሲሆን ከውጪ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡትም ላይ ቢሆን ያለው እገዳ ተመሳሳይ ነው ። ለምሳሌ በ1962 የአሜሪካ ምክር ቤት ያወጣው ሕግ ማንኛቸውንም በፖስታ ቤት በኩል የሚላክ ጽሑፍ የገንዘብ ሚኒስትሩ የኰሚኒስት ፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ ነው ብሎ የሚገምት ከሆነ ፖስታ ቤቱ እንዲይዝና የተላከለት ሰው የጠየቀ እንደሆነ ብቻ እንደሚለቀቅለት ለተቀባዩ እንዲገለጽለት የሚል ነበር ። [12] ኰሚኒዝምን እንደ ዓይነተኛ ጠላት በሚፈራ ስርዓት ውስጥ የተላከውን ጽሑፍ እፈልገዋለሁ ብሎ ቀርቦ ተከራክሮ መቀበል በኋላ የሚያስከትለውን ውጤት ሁሉም ስለሚያውቀው ወደኋላ እንደሚል መገመት አያዳግትም ። ይህንን ከላይ የጠቀስነውን በካፒታሊስት አገሮች በብዛት (በይበልጥ) የሚሠራበትን የሀሳብ ስርጭት ቁጥጥር ፣ የሕትመትንና የስርጭትን መስክ በግል ባለሀብትነት በያዙ ወገኖች ፣ አንደኛው የካፒታሊስት ሀሳብ ስርጭት ቁጥጥር ዘዴ ልንለው እንችላለን ።

ሁለተኛው ፣ የካፒታሊስቱን የእድገት ፈለግ በሚከተሉ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ በሰፈነባቸው አገሮች ውስጥ የሃሳብ ስርጭትን

Digitized by Google

የሚቆጣጠር የመንግሥት አካል የሆነ ተቆጣጣሪ ጽሕፈት ቤት ያለበት ሁኔታ ነው ። በነኝህ ዓይነት አገሮች ማንኛውም ጽሑፍ ከመታተሙ በፊት ለተቆጣጣሪው ጽሕፈት ቤት ይቀርባል ። እዚያም ለጽሕፈት ቤቱ በተሰጠ መመሪያ መሠረት ያ የቀረበ ጽሑፍ በጽሑፉ ይዘት ልዩ ሙያ በሌላቸው ሰዎች ይመረመራል ። ለመገመት እንደሚቻለው ያ ተቆጣጣሪ ጽሕፈት ቤት የሚሰጠው መመሪያም ሆነ የሚቋቋምበት ዓላማ ያለውን መንግሥት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚቃወም ፣ የሚያጥላላ ፣ የሚነቅፍ ወይም የሚነካ የሚመስል ጉዳይን እንዳይታተም መከልከል ነው ። በዚህ ረገድ የተቆጣጣሪው ጽሕፈት ቤት አንድ ጽሑፍ ቀርቦለት ይመለከታል ። የቀረበው ጉዳይ ያለውን መንግሥት ደጋፊ ወይም ያለውን መንግሥት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የማይነካ የሆነ እንደሆነ እንዲታተም ይፈቀዳል ። የቀረበውን ጽሑፍ በዝርዝር የመመልከቱም ጉዳይ እንደደራሲው ማንነት ሊጠነከርና ሊቀል እንደሚችልም ለመገመት ይቻላል ። ይህም ማለት ደራሲው የሥርዓቱ ወይም የመንግሥቱ አካል ወይም ደጋፊ መሆኑ ከታወቀ ቁጥጥሩ ይላላል ። ደራሲው የስርዓቱ ተቃዋሚ ከሆነ ደግሞ ቁጥጥሩ ያይላል ። ይኸ ሁኔታ በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ በግልጽ ይሠራበት እንደነበር የታወቀ ነው ።

በዚያ ዓይነት አሠራር ለተቆጣጣሪው ጽሕፈት ቤት የቀረበ ጽሑፍ አልፎ አልፎ ተቃዋሚ ወይም ነቃፊ የሚመስሉ ነጥቦችን የያዘ ከሆነ እነዚህ አጠራጣሪ ነጥቦች ፈጽሞ እንዲሠረዙ ወይም በሌላ እንዲተኩ ተቆጣጣሪው እርማትና ትዕዛዝ ይሰጣል ። የማረሙም መሠረታዊ ዓላማ መንግሥትን ይነኩ ይሆናል ተብለው የሚገመቱ ነጥቦችን ለማስወገድ ብቻ እንጂ የቀረበውን ነገር አስተካክሎ የተሻለ ጠቀሜታ እንዲኖረው አይደለም ። ምክንያቱም ቀደም ሲል እንደተጠቆመው ተቆጣጣሪዎቹ ለሥራው ሲመደቡ ላለው መንግሥት ታማኝ መሆናቸው እንጂ የሙያ ብቃታቸው ከቁጥር ስለማይገባ በቀረበው ጽሑፍ ይዘት አንፃር የሚያበረክቱት እምብዛም ነው ።

የቀረበው ጽሑፍ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያለውን መንግሥት የሚቃወም ከመሰለ ግን ከመታተም ፈጽሞ ይከለከላል ። የመከልከሉ ሁኔታ እስከምን ምክንያት እንደሚሻ « እንኳን በግልጥ ማውራቱ ቀርቶ ያለምንም ተንኮል ይጻፍ የነበረውሁሉ እየተተረጐመ (ምናልባት እንዲህ ማለቱ ይሆናል) የሚባልበት ጊዜ ነበር» [13] ከሚለው አስተያየት መገመት ይቻላል ። ደራስያን ከተቆጣጣሪው አካል ጋር በሚያደርጉት የድብብቆሽ ፍልሚያ የማምለጫ ዘዴ እየፈጠሩ ለማሳተም ቢችሉም ዘዴው የቋንቋ አጠቃቀማቸውንና የሀሳብ ግልጽነታቸውን እያዳከመው እንደሄደ ይገመታል ።

በቅድመ-አብዮት ኢትዮጵያ

.. . በቁንቁ ድቀትና በሐሳብ አገላለጽ ድነዘ ትልቁን ድርሻ የያዙት ጋዜጦችና ጋዜጠኞች ነበሩ . . . ለምሳሌ በጋዜጣ አገላለጽ አንዱ እርምጃ ቃል ኩደታ (ዛሬ መፈንቅለ መንግሥት ተብሏል) ነበር ። በእንደዚህ ያለ አገር መንግሥት ተገለበጠ ማለት ፈጽሞ አይሞከርም ። አንዱ መንገድ ጥቂት ሰንብቶ . . . አዲስ መንግሥት ተቋቋመ ብሎ ማውራት ነው ። የፊተኛው የት እንደደረሰ ግን አይነገርም ። ወዲያውኑ ከተቻለ ሊላው የአገላለጽ መንገድ ባንድ በተወሰነ . . . አገር የአስተዳደር ባለሥልጣኖች ተለውጠው አዲሶች ተተኩ ይሆናል።ሊላው ለመግለጽ አስቸጋሪ የነበረው መስከ ኅብረተሰብአዊነትን በተለይም የሠራተኛ ማኅበርን ንቅናቄ ወይም እንቅስቃሴ የሚመለከት ነው ። የሠራተኞች ማኅበር መቋቋም በሕግ የተፈቀደ ቢሆንም የሠራተኞች ማኅበር አሠሪው ወይም ሊላ ወገን የወሰደውን እርምጃ 'ተቃወሙ' ለማለት ፣ በተወሰደው እርምጃ 'አቤቱታ አሰሙ' ወይም 'ስሞታ አቀረቡ' ነበር የሚባለው ። ብዙ ጊዜ አገላለጹ ከመሠረታዊ ትክክለኛ ድርጊት ወጥቶ ፍጹም ሊላ መልክ ይይዛል ። [14]

Digitized by Google

በወዲያም በወዲህ ተብሎ አንድ ጽሑፍ ሊታተም ቢችል እንኳ ጽሑፉ አደባባይ ከወጣ በኋላ የሥርዓቱ ደጋፊዎች በሚያደርጉት የትርጉም ስንጠቃ መልእክቱ «ተቃዋሚ» መስሎ ከተገመተ ጽሁፉ ተሰብስቦ እንዲቃጠል ወይም ከገበያ እንዲጠፋ ይደረግ ነበር ። እነዚህ አፈጻጸሞች በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ እጅግ የጎሉ ቢሆኑም ለማስታወስ ያህል የአቶ አቤ ጉበኛን አልወለድም እና ምልክአም ሰይፈ ነበልባልን መጥቀስ ይቻላል ። ይህ ሁሉ ይደረግ የነበረው በ1948 ወጥቶ በመስከረም 2/1967 የሰፊው ሕዝብ አብዮት በሻረው ሕገ መንግሥት አንቀጽ 41 ላይ «የንግግርና የጋዜጣ ነፃነት የተፈቀደ» መሆኑ በይፋ ሰፍሮ ነው ።

ሦስተኛው የሀሳብ ስርጭትን የመቆጣጠሪያ ዘዴ ሕዝባዊ የሆነው ነው ። ይህም በመሠረቱ የሚታየው የሶሻሊስትን ሥርዓት በሚከተሉ አገሮች ዘንድ ነው ። ሕዝባዊ የሆነው የሀሳብ ስርጭትን የመቆጣጠሪያ ዘዴ መለኪያ የሚያደርገው የሰፊውን ሕዝብ መብትና ጥቅም ፣ የሰፊውን ሕዝብ ዓላማና ግብ ነው ። ስለዚህም የሰፊውን ሕዝብ መብትና ጥቅም ፣ የሰፊውን ሕዝብ ዓላማና ግብ የሚያራምደውን ፣ የሚያግዘውን ፣ የሚንከባከበውን ሀሳብ ሁሉ እንዲሰራጭ ይደግፋል ፤ ያበረታታል ። በአንፃሩ የሰፊውን ሕዝብ መብትና ጥቅም፣ የሰፊውን ሕዝብ ዓላማና ግብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያደናቅፈውን ፣ የሚጐዳውን ፣ የሚነካውን ሀሳብ ሁሉ እንዳይሰራጭ ያግዳል ፤ ይታገላል ።

ሰፊው ሕዝብ ይህንን ተግባር የሚያከናውንበትም ዓይነተኛ መሣሪያ መደራጀቱ ነው ። የመደራጀቱም ዓይነተኛ ዓላማ የመደብ ጠላቱን በተጠናከረ ኃይል ለመደምሰስና መብቱንና ጥቅሙን ለማስከበር ነው ። አደረጃጀቱም በፈርጅ በፈርጁ እንደሆነ ይታወቃል ። በሠራተኛ ማኅበር ፣ በገበሬ ማኅበር ፣ በከተማ ነዋሪዎች ማኅበር፣ በሴቶች ማኅበር ፣ በወጣቶች ማኅበር ፣ በሙያ ማኅበርና በመሳሰሉት ይደራጃል ። የሙያ ማኅበር የተባለው ዘርዘር ተደርጐ ቢጻፍ ፣ የመምህራንን ፣ የደራስያንን ፣ የሰዓሊያንን ፣ የሙዚቀኞችንና ሌሎችንም እንደሚያቅፍ ለመገመት ይቻላል ።

እነዚህ ልዩ ልዩ ሕዝባዊ ድርጅቶች የተመሰረቱበት ዓይነተኛ ዓላማ የሰፊውን ሕዝብ የመደብ ትግል ለማገዝ በመሆኑ ማንኛቸውንም ተግራሪ ወገን እንደየሁኔታው ይቆጣጠራሉ ። በተለይ የሀሳብ ሥርጭትና ምንጭ በይበልጥ የሚመለከታቸው የሙያ ማኅበሮች በየዘርፋቸው የሚቀርቡትን ወይም የሚደርሱትን ጽሑፎች ፣ ሙዚቃዎች ፣ ስዕሎች ፣ ቅርጻ ቅርጾችና የመሳሰሉት ማኅበሮች ለተቋቋሙባቸው ዓላማዎች ተገቢ መሆናቸውን በንቃት ይከታተላሉ ። ከሰፊው ሕዝብ ወገን የቆመ ባለሙያ ሙያውን ለሰፊው ሕዝብ በተሟላ ሁኔታ አጋዥ ለማድረግ የሚችለው ከማኅበሮቹ በአንዱ ሲታቀፍ መሆኑን ያውቃል ። ስለዚህም እንደ የሙያው የአንዱ ማ ኅ በ ር አ ባ ል ይሆናል ። የማኅበሩ አባል በመሆኑም በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም የበለጠ ለመታነጽ ፣ በሙያው የበለጠ እውቀት ለማግኘት ይቻለዋል ። ስለዚህም ለስርጭት የሚያቀርባቸው ጉዳዮች የሕዝብ ወገንነቱን የሚያጠናክሩና የሚመሰክሩ እንዲሆኑ ያላሰለሰ ጥረትና ዝግጅት ያደርጋል ።

በሶሻሊስትና የሶሻሊስቱን የእድገት ፈለግ በሚከተሉ አገሮች ይህ ሕዝባዊ የሀሳብ ስርጭት ቁጥጥር በስፋት የ ሚ ታ ይ ነው ። በመሠረቱ ቁጥጥሩ የሚያተኩረው የደራሲዎችንና የመሳሰሉትን ባለሙያዎች ርዕዮተዓለማዊ ጥንካሬ በማረጋገጡ ላይ ነው ። ባለሙያዎቹም የሕዝብ ወገንነታቸው እንዲጠናከርና የመንሸራተት አዝማሚያ እንዳይኖርባቸው ልዩ ልዩ ኮርሶችና ሴሚናሮች እንዲዘጋጁላቸው ጥረት ይደረጋል።ዋናው የቁጥጥሩ መሠረተ ሀሳብ ይህ ነው ።

በተጨማሪ የሕዝብ ወገን የሆኑ ፀሐፊዎች ፣ ሰአሊዎች ፣ ቀራጮች ፣ ዜማ አው

Digitized by Google

ቃዎችና የመሳሰሉት የሚያቀርቡት ዝግጅት ጥራትና ጥልቀት ኖሮት ለሕዝብ እንዲደርስ አስፈላጊውን ምክርና አስተያየት የሚሰጥ ተቆጣጣሪ የመንግሥት አካል ይመደባል ። በዚህ ተቆጣጣሪ አካል ውስጥ ተመድበው የሚሠሩትም በልዩ ልዩ የሙያ መስክ የጠለቀ እውቀት ያላቸው ፥ የርዕዮተ ዓለም ጥንካሬአቸው ከፍተኛ የሆኑ ናቸው። ተቆጣጣሪው አካል መሠረተ ዓላማው የሕዝቡ ወገን በሆነ ባለሙያ የተፃፈ ፥ የተሳለ፥ የተቀረፀ ፥ የተዜመ ሁሉ ለሕዝቡ እንዲደርስ ስለሆነ ምክሩም አስተያየቱም ይህንኑ ይይዛል ። ለኪነጥበብና ለሳይንስ መዳበር ሶሻሊዝም አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር እንደ መሆኑ ፥ ይኸን ስርዓት በሚከተሉ አገሮች የተቆጣጣሪው አካል ተግባር ከዚህ አንፃር ይቀየሳል ።

በሶሺያሊዝም የሰፊውን ሕዝብ ልዩ ልዩ ድርጅቶች የሚያስተባብርና በበላይነትም የሚመራ የሠራተኛው መደብ ፓርቲ ነው። ለሠራተኛው ፓርቲ እነዚህ ልዩ ልዩ ድርጅቶች የሠራተኛ ማኅበራት ፥ የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት ፥ የወጣቶች ማኅበራት ፥ የሴቶች ማኅበራት ፥ የሙያ ማኅበራት ፥ አብዮታዊው ጦር ፥ ወዘተ - - - ከሰፊው ሕዝብ ጋር የመዋሀጃ የደም ስሮች ናቸው።[15] በእነዚህ ሰፊው ሕዝብ በየፈርጁ በተደራጀባቸው አካላት አማካይነት ፓርቲው አዲስ ለሚገነባው ኅብረተሰብ አመራር ይሰጣል ። የሠራተኛው ፓርቲ « የሠራተኛው መደብ ማርክሳዊ አካል የሆነ ፥ ስለ ኅብረተሰቡ ሕይወት ፥ ስለእድገቱ ሕግጋትና ስለመደብ ትግሉ ሕግጋት በሚገባ ያወቀ በዚህም ምክንያት ሠራተኛውን መደብ ለመምራትና የመደብ ትግሉንም ትክክለኛ አቅጣጫ ለማስያዝ የሚችል ነው ። » [16]

በታሪክ ይህን መሰል ተልዕኮ ያለው አካል አመራሩ ፍጹም ተቀባይነት ሊኖረው የቻለው የመንግሥት ሥልጣን በመጨበጡ ሳይሆን አባላቱ ከሠራተኛው መካከል በማንኛቸውም ለሰው ልጅ አለኝታ በሆነ ተግባርና ሥነ ምግባር ብቃትና ዝግጅት ያላቸው በመሆናቸው ነው ። ሌኒን እንዳለው የፓርቲው አባላት ከሠራተኛው መኸል ግምባር ቀደምና በርዕዮተዓለም ጥንካሬአቸው ምርጥ የሆኑት ናቸው ። ስለዚህም ቀደም ሲል የተጠቀሱት የሰፊው ሕዝብ ልዩ ልዩ ማኅበሮች የሀሳብ ስርጭትን ለመቆጣጠር ዓይነተኛ ናቸው ሲባል የመቆጣጠሪያውን ስልትና መመሪያ የሚያገኙት ከፓርቲያቸው መሆኑ መታወስ አለበት ።

ሶሻሊዝም ወደ ኮሚኒዝም ስርዓተ ማኅበር ማለፊያ የሽግግር ምዕራፍ ነው ። በዚህም የሽግግር ምዕራፍ ውስጥ ካለፈው ስርዓት የሚወረሱ ለመጥፋት ጊዜ የሚወስዱ አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ ። ከእነዚህም ውስጥ አንዱ የአስተሳሰብና የአሠራር ጉዳይ ነው ። ሌኒን እንዳለው «የካፒታሊስቶችን እምቢተኝነት በየፈርጁ መቋቋም አለብን፤ በጦርና በፖለቲካ መስኮች ብቻ ሳይሆን ጠንካራና ስር የሰደደ በሆነው በአስተሳሰብና በአሰራርም መስክ ። » [17] የአስተሳሰብ ጉዳይ ደግሞ በይበልጥ የሚያይለው ቀድሞ በዝባዥ መደቦች የግል አድርገው በሞኖፖል በያዙት በሕትመትና በስርጭት መስክ ነው ። ይህንኑ በማጤን ሌኒን የሚከተለውን ብሎ ነበር ፥

ስነጽሁፍ በማንኛቸውም ረገድና የግደታ ከሌሎች ጉዳዮችም ጋር ተያይዞ የፓርቲ ተግባር መሆን አለበት ። ጋዜጦች የልዩልዩ ፓርቲ አካላት ልሳናች መሆን አለባቸው ። ፀሐፊዎች በማንኛውም ረገድ የእነዚህ አካላት አባላት መሆን አለባቸው ። መጻሕፍት አሳታሚዎችና አከፋፋይ ድርጅቶች ፥ የመጻሕፍት መደብሮችና የንባብ ቤቶች ፥ ቤተመጻሕፍትና ሌሎችም ተመሳሳይ ድርጅቶች ሁሉ በፓርቲ ቁጥጥር ሥር መዋል አለባቸው ። የተደራጀው ሶሻሊስታዊ ሠራተኛ ይህንን ሁሉ ሥራ መከታተል ፥ መላ አሰራሩን መቆጣጠርና ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ምንም ሳይቀር የሠራተኛውን ሕያው ዓላማ እንዲያገኝ ማድረግ ... አለበት ። [18]

Digitized by Google

ስለዚህ በሽግግር ወቅት ሊኖር የሚገባው የሀሳብ ስርጭት ቁጥጥር የበዝባዦችን የፖለቲካ ሥልጣን የሚነጥቅ ፣ የሰፊውን ሕዝብ የፖለቲካ ሥልጣን ግን የሚያዳብር ነው ። በዚህ አፈጻጸሙ የሀሳብ ስርጭት ቁጥጥር በተወሰነ ወቅት (ወደ ሶሺያሊዝም በሚደረግ የሽግግር ወቅት) አብዮታዊ ባህርይ አለው ማለት ነው ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. *V. I. Lenin,* Collected Works, *Vol.* 26, *Progress Publishers, Moscow,* 1974, *p.* 283.
2. *Lenin,* Collected Works, *Vol.* 28, *p.* 461.
3. *Lenin,* Collected Works, *Vol.* 26, *pp.* 283-285.
4. *Ibid., p.* 371.
5. *Marx and Engles,* Selected Works, *Vol.* 3, *Progress Publishers, Moscow* 1973, *p.* 328.
6. *Marx and Engles "The Communist Manifesto," in Selected Works.* Vol. 1, *Progress, Publishers, Moscow,* 1973, pp. 108-137.
7. Encyclopaedia Britannica, *Vol.* 5, 1970, *p.* 166 *A.*
8. *Ronald Dworkin, "Is the Press Losing the First Amendment?", in the New York Review of Books,* Vol. *XXVII, No.* 19, *December* 4, 1980, *pp.* 49-57.
9. Great Soviet Encyclopaedia, Vol. 10, 1976, *p.* 568.
10. Encyclopaedia Britannnica, *Vol.* 5, *p.* 166 *A.*
11. Great Soviet Encyclopaedia, Vol. 10, *p.* 568.
    Encyclopaedia Britannica, *p.* 165.
12. Encyclopaedia Britannica, *Vol.* 5, *p.* 166 *B.*

13 ጳውሎስ ኞኞ ፣ «ኑዛዜ»፣ <u>አዲስ ዘመን</u> መጋቢት 22 ፣ 1966

14 <u>አዲስ ዘመን ፣</u> «አብዮትና የቋንቋ እድገት » ፣ መስከረም 3 ፣ 1968

15. *Joseph Stalin,* Collected Works, *Vol.* 5, *Foreign Languages Publishing House,* Moscow, 1953, pp. 200-209.
16. History of the Communist Party (Bolsheviks), *International Publishers, N. Y.,* 1930, *p.* 46.
17. *Lenin,* Collected Works, *Vol.* 31, *p.* 370.
18. *Lenin,* Collected Works, *Vol.* 10, *p.* 46.

Digitized by Google

የዘመናችን የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የውጭ ፖሊሲ

—አንዳንድ ነጥቦች

አበበ ወርቁ

ግዛት ማስፋፋት ፣ ሌላውን አገር በፖለ
ቲካ መጨቆን ፣ በኢኮኖሚ መበዝበዝ፣ በሚ
ሊታሪ መጉሸም ፣ ወይም ለመጉሸም መሞ
ከር፣ጣልቃ ገብነትና የመሳሰሉት ድርጊቶች
የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የቆዩ የውጭ
ፖሊሲ ባህርያት ናቸው ። በተለይም ከ1970
ዎቹ መጨረሻ ጀምር ሥር እየሰደደ የሄደ
ውና በመሄድ ላይ ያለው የአሜሪካ ጦረኝነ
ትና የጣልቃ ገብነት ፖሊሲ ለሰው ልጅ ደህ
ንነት በአጠቃላይ፣በተለይ ደግሞ ለምዝብር
ሕዝቦችና ነፃነት ለተጠሙ ጭቁኖች እጅግ
አሳሳቢ ሆኗል ። ዛሬ በዓለም ላይ የኒኩሌር
ጦርነት ዳመና እያንዣበበ ነው ፤ ዛሬ ለነፃ
ነታቸው የሚዋጉ ጭቁን ሕዝቦች ከመቼ
ውም ጊዜ የበለጠ የአሜሪካ የሚሊታሪ ቴክ
ኖሎጂ በአፈራቸው መጫሪያዎች በሊባኖስ፣
በደቡባዊ አፍሪካ ፣ በኤልሳልቫዶርና በሌሎ
ችም ቦታዎች እየተጨፈጨፉ ነው ። በአጠ
ቃላይ ኢምፔሪያሊዝም የገጠመውን ሽን
ፈት ለመቋቋም ኢሰባዊ ድርጊቶችን እየፈ
ጸመ ነው ።

ያለንበት ጊዜ በሌላ ገጽታው ከመቼ
ውም የበለጠ ጭቁኖች በትግላቸው ሶሻሊ
ዝምን ለመገንባት የሚታገሉበት ፣ ለተሟላ
ነፃነት የመረረ ትግል የሚያካሂዱበት ወቅት
ነው።ይህ የነፃነት ትግል እድገት የኢምፔሪያ
ሊዝምን የግዛት ስፋት እያጠበበው፣የሚያጋ
ብሰውን ትርፍና የብዝበዛ መጠን ከዕለት
ወደ ዕለት ዋስትና እያሳጣው፣በአንዳንድ
አገሮችም የሽንፈት ማቅ እያከናነበው ስለ
ሆነ ኢምፔሪያሊዝም ሽንፈቱን ላለመቀ
በል ወደ ከፋ ጦረኝነት ፣ ወደ ላቀ ጣልቃ ገብ
ነት ተሸጋግሯል። ከ1970ዎቹ መባቻ ጀምሮ
በዓለም ፖለቲካ ከሞላ ጐደል የሰፈነው «የዴ
ታንት» አየር በአሜሪካ የጣልቃ ገብነት
ፖሊሲ ደፍርሷል ። ሁለተኛው ቀዝቃዛ ጦር
ነት ተጀምሯል ማለት ይቻላል ። ለዚሁ ቀን

ደኛና ዋነኛ መንስኤ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም መሆኑ ሁኔታውን በትክክል ለሚከታተሉ ሰዎች ሁሉ ስውር አይደለም ።

በ1970ዎቹ ማክተሚያ ላይ የዓለም የፖለቲካ አየር በካርተር አስተዳደር ይመራ በነበረው የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የጦረኝነት አዝማሚያ ተመረዘ ። በጥር ወር 1980 ሬጋን የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆኖ በትረ መንግሥቱን ሲጨብጥ በካርተር የተወጠነውን የገጠጠ የፀረ ሰላም ፖሊሲ መከተልን የበለጠ አተኮረበት።ይህ ፖሊሲ በመሠረቱ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች በአገራቸውም ሆነ በውጭ የገጠማቸው ችግር ነፀብራቅ ነው። ይህን በበለጠ ለመረዳት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት እስከ ዛሬ ያለውን የአሜሪካንንና የውጭ ፖሊሲ (የዘመናችን የአሜሪካ ፖሊሲ እየተባለ የሚጠራውን) ታሪክ መሠረታዊ አዝማሚያዎችንና ለምንስ እነዚህን መሠረታዊ አዝማሚያዎች እንደያዘ ታሪካዊ መረጃዎችን መመርመርና መረዳት ተገቢ ነው ። ይህን ለማድረግ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግስት ጀምር ለምን የተዝታዛውን « ጦርነት » ፖሊሲ ተከተለ ? ከዚያም ቀጥሎ ለ25 ዓመታት ያሀል የተከተለውን የቀዝቃዛ ጦርነት ፖሊሲ ትቶ ለምን በ1970ዎቹ መገቢያ ላይ የውጥረት ቅነሳን (የዴታንት) ፖሊሲ መከተል ጀመረ ? በ1970ዎቹ መዝጊያ ላይስ ለምን ወደ ቀዝቃዛው ጦርነት ተመለሰ ? የአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ በአሁኑ ጊዜ ምን ዓይነት አቅጣጫ እየያዘ ነው? ለሚሉትና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መልሶች ማግኘት አስፈላጊ ስለሆነ ይህ ጽሑፍ እነኝህን ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት ያደርጋል ።

የጽሑፉ የመጀመሪያው ክፍል ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግስት እስከ 1970ዎቹ መባቻ ድረስ የነበረውን የአሜሪካንን የውጭ ፖሊሲ ባህሪ ማለትም የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምን የቀዝቃዛ ጦርነት ፖሊሲ አነሳስን ፣ ውድቀትንና በውጥረት ቅነሳ ፖሊሲ መተካትን ይመለከታል።ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከ1970ዎቹ አጋማሽ ጀምር የአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ባህርያትን ያትታል ። በዚህም ክፍል በ1970ዎቹ ማክተሚያ ላይ የአሜሪካ መንግሥት የውጭ ፖሊሲ ለምን ከውጥረት ቅነሳ ፖሊሲ እንደገና ወደ ቀዝቃዛው ጦርነት ፖሊሲ እንዳዘነበለና ምንስ አቅጣጫ በመያዝ ላይ እንደሆነ ለመገምገም ይሞከራል ።

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የቀዘቀዘው ጦርነት ፖሊሲ አነሳስና ውድቀት

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ኃይለኛና የዓለምን ፖለቲካ ብቸኛ ተቆጣጣሪ መስሎ የታየው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግስት ነበር ። በወቅቱ ሌሎች ቀንደኛ የኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ማለትም ፣ እንግሊዝ ፣ ፈረንሣይ ፣ ጀርመን ፣ ጣሊያንና ጃፓን ባካሄዱት ጦርነት ክፉኛ ተዳክመው ስለነበረ ለአሜሪካ አመች ሁኔታ ተፈጠረ ። በዚህ ወቅት አሜሪካ በኢንዱስትሪ ምርት፣ በውጭ መዋዕለንዋይ ፣ በውጭ ንግድና በገንዘብ ኃይሏ መሪ የኢምፔሪያሊስት አገር ሆነች። ብሔራዊ ገንዘቧም (ዶላር) በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት አገኘ ። በአጭሩ የአሜሪካን ዘመን (American Century) ተጀመረ ።

የተወዳዳሪዎቿ መዳከም አሜሪካ በውጭ ፖሊሲዋ በሁለት ዋና ዋና ተግባራት ላይ እንድታተኩር አስገደዳት ። አንደኛው ተግባር አሜሪካ የካፒታሊስቱን ዓለም በበላይነት የመምራትና ከሚገጥመውም ሕዝባዊ ትግል መከላከል ነበር ። የሕዝባዊ አብዮት ድል ማድረግና የሶሻሊዝም መስፋፋት ለዓለም አቀፍ ካፒታሊዝምም ሆነ ለራሱ ለአሜሪካ የገዥ መደብ አደጋ ሆነ ። በመሆኑም የካፒታሊስቱ ሥርዓት ሕልውና እንዲጠበቅ የአሜሪካ መንግሥት የተዳከሙትን ሌሎች ዋና ዋና የካፒታሊስት አገሮች በማስተባበር ጭምር አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ ነበረበት።ሁለተኛው ተግባር የአሜሪካንን ሞኖፖሊስቶች ጥቅም ማስጠበቅ ነበረ ። የሌሎች ካፒታሊስት አገ

ሮች መሳሪያ ለአሜሪካ ሞኖፖሊስቶች የበለጠ የንግድ ተጠና ፣ የበለጠ ትርፍ ለማግኘት አመች ሁኔታ ፈጠረ ። ይህን አመች ሁኔታ ለመጠቀም የአሜሪካ መንግሥት መሪዎች የአገራቸውን የሞኖፖሊስቶች ጥቅም ሊያስከብር የሚችል የውጭ ፖሊሲ መከተል ከፊታቸው የተደቀነ ተግባር ሆነ ። ስለሆነም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግስት ጀምሮ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ሁለቱን ተግባራት በአንድ ላይ አጣምሮ በማካሄድ ወደ ከፍተኛ የፖለቲካና የኢኮኖሚ መስፋፋት ፣ ወደየኢምፔሪያሊስቶች መሪነት ተሸጋገረ ።[1] ሆኖም ይህ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የኢኮኖሚና የፖለቲካ መስፋፋት በውስጡ የራሱን ችግር ይዞ መምጣቱ አልቀረም ።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ውስጥ ተጠናክሮ የወጣውና በአንዳንድ የአውሮፓ አገሮች በመገንባት ላይ የነበረው ሶሻሊዝም ለአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም እጅግ አስፈሪ ነበር ። በካፒታሊስት አገሮች ይካሄድ የነበረው ፀረ ካፒታሊዝም ትግልና በ«ሦስተኛው ዓለም» በመቀጣጠል ላይ የነበረው ፀረ—ኢምፔሪያሊስት እንቅስቃሴም እንዲሁ በአሜሪካ በመመራት ላይ ያለውን ኢምፔሪያሊዝምን አደጋ ላይ የሚጥል ነበር ። ስለሆነም የአሜሪካ መሪዎች በውጭ ፖሊሲያቸው መስክ የገጠማቸውን የሶሻሊዝም መጠናከር፣የፀረ ካፒታሊዝምና የነፃነት እንቅስቃሴዎች ትግል መጋፋት ያስከተለባቸውን «ችግር» በሚመለከት መከተል የሚገባቸው የውጭ ፖሊሲ ምን ዓይነት ባሕርይ እንደሚኖረውና የካፓታሊሲቱን ዓለም ሕልውናና የአሜሪካ ሞኖፖሊስቶችን ጥቅም ለማስከበር እንዴት መታገል እንዳለባቸው መወሰን ነበረባቸው።

ይህ በውጭ ፖሊሲ በኩል የታየው ችግር ከ1945—1946 በአሜሪካ መሪዎች ዘንድ ከፍተኛ መከፋፈልንና አለመግባባትን ከፈጠሩ ችግሮች አንዱ ነው ። በወቅቱ የሪፓብሊካን ፓርቲ መሪዎች የነበሩት እነ ሮበርት ታፍትና አርተር ቫንደንበርግ አሜሪካ ሶሻሊዝምን በጥብቅ መቃወም አለበት የሚል አቋም ያዙ ።[2] ይሁን እንጂ በጊዜው የነኝህን የቀኝ አክራሪዎች ፖሊሲ የሚቃወሙ ሌሎች የአሜሪካ የገዥ መደብ አባላት ለምሳሌ፣ በአስተዳደሩ ውስጥ የነበረው ሄንሪ ዋለስና በሕግ መወሰኛው ምክር ቤት የነበረው ክላውድ ሬፐር እና በመሳሰሉት የሚመራውና የተራማጆችም ጠንካራ ድጋፍ የነበረው ቡድን ለጊዜውም ቢሆን የአሜሪካ መንግሥት የውጭ ፖሊሲ ወደቀኝ ተስፈንጥሮ እንዳይሄድ ገቱት ።[3]

የአሜሪካ መንግሥት በውጭ ፖሊሲው ከቀኝ አክራሪነት መገታት በጣም ጊዜያዊ ነበር ። በሀገሪቱ በጠቅላላው የበላይነት እየያዘ የመጣው የቀኝ አክራሪዎች ፖለቲካና ርዕዮተዓለም ነበር ። ይህ ሐቅ በ1946 በተካሄደው የምክር ቤት አባላት ምርጫ ላይ ገልጾ ወጣ ። በዚህ ምርጫ የሪፓብሊካንን ፓርቲ የሚመራው የቀኝ አክራሪ ቡድን «ከ1930 ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ በሕግ መወሰኛው ምክር ቤት አብዛኛውን መቀመጫ አገኘ ፤ ከ1928 ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ሁለቱንም ምክር ቤቶች (የሕግ መወሰኛውንና የሕግ መምሪያ ምክር ቤቶች) ለመቆጣጠር ቻለ ። የሕግ መምሪያውን ምክር ቤት የሪፓብሊካኑ ፓርቲ ለመቆጣጠር የቻለው በምክር ቤት ውስጥ ከነበሩት ቀኝ አክራሪ ከሆኑት ከዲሞክራቲክ ፓርቲ አባላት ጋር በማበር ነው ።[4] ይህን የበላይነት ከተጎናጸፉ በኋላ የአሜሪካ ቀኝ አክራሪዎች በሀገሪቱም ውስጥ ሆነ በውጭ ፖሊሲ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ የነፃነት እንቅስቃሴ ለማፈን በአመዛኙ በቀጥታ በኃይል መጠቀም ጀመሩ ።

በሀገር ውስጥ የሠራተኛውን እንቅስቃሴ ለማፈን ሰኔ 23 ፣ 1947 ሕግ ወጣ ። ይህ ሕግ እጅግ በጣም በቀኝ አክራሪነቱ በታወቀው በታፍት ሃርትሌይ ስም በመሰየም «የታፍት ሃርትሌይ ሕግ» በመባል ይታወቃል ። ሕጉ የሚመለከተው የአሠሪንና የሠራተኛን ግንኙነት ሲሆን ፣ የአሜሪካ የሠራተኞች ማኅበራት በረጅም ትግላቸው የተጎናፀፉቸውን ልዩ ልዩ መብቶች ፣ ለምሳሌ የሥራ ማቆም

አድማን መብት የሚያጠብ ፣ ሠርቶ አደሮች ለሚደግፉት የፖለቲካ ፓርቲ የገንዘብ ድጋፍ መስጠት መብታቸውን የሚነፍግ ፣ ተፅዕኖ የሌለበት የአሠሪንና የሠራተኛን ድርድር የሚሽር ነበር ። ሪቻርድ ሞሪስ የሚባለው አሜሪካዊ ፀሐፊ እንዳለው ይህን አዋጅ የሠራተኛ መሪዎች «የባርነት ሕግ» የሚል ስም ሰጥተውታል ።[5]

ሕጉ የወጣው የሕግ መምሪያውና የሕግ መወሰኛው ምክር ቤት አባላት ስምምነት በጊዜው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበረውን የሃሪ ትሩማንን ተቃውሞ በማክሸፉ ነው ። የሪፓብሊካኑ ፓርቲ አባላትና በምክር ቤቱ የሰፈነው የቀኝ አክራሪነት ፖሊሲ እየተጠናከረ ሲመጣ የዲሞክራቲክ ፓርቲ አባል የነበረው ፕሬዚዳንት ትሩማንም ከዕለት ወደ ዕለት ከነኝህ የቀኝ አክራሪዎች ጋር የበለጠ እያበረ መጣ ። ፕሬዚዳንት ትሩማን በመጀመሪያ ጊዜ የምክር ቤቱ የቀኝ አክራሪዎች አውጥተዋቸው የነበሩትን 62 አድሃሪ ሕጎች የተቃወመ ቢሆንም « ከመንግሥቱ መዋቅር ውስጥ ታማኝ ያልሆኑ ግለሰቦችን መመንጠር» በሚል ሽፋን ኮሚኒስቶችንና ተራማጆችን በማስታየቱ ዘመቻ ግንባር ቀደም አስፈጻሚ ሆነ ። መጋቢት 22 ፣ 1947 ትሩማን ለዚሁ ምንጠራ ተፈጻሚነት ትዕዛዝ አስተላለፈ ፤ በዚሁ ትዕዛዝ መሠረትም አሥራ ሁለት የአሜሪካ ኮሚኒስት ፓርቲ መሪዎች ለፍርድ ቀረቡ ።[6] የቀኝ አክራሪዎች የበለጠ የፀረ ሕዝብ ሥራቸውን አስፋፉት ፤ የኮሚኒዝም አደጋ ያሰጋናል እያሉ በመቀስቀስ የሕዝቡን አስተያየትና ሃሣብ ለራሳቸው ፖሊሲ አመች እንዲሆን አርገው ለመቅረጽ ሞከሩ። ለምሳሌ በአገሪቱ ፖለቲካ የቀኝ አክራሪዎች በጣም ከመጠናከራቸውና የመንግሥቱን ሥልጣን በአመዛኙ ከመቆጣጠራቸው በፊት ፣ በ1946 የተሰበሰበው የሕዝብ አስተያየት እንደሚጠቁመው ከአሜሪካ ሕዝብ 3% ብቻ አዲስ ጦርነት መነሣቱ የማይቀር ነው ብሎ ያመነ ሲሆን ፣ በ1948 ግን ይህ ቁጥር 32% ደረሰ ። በሌላ አነጋገር የቀኝ አክራሪዎች ሕዝቡን ለአድሃሪ ጦርነት አነሳሱት ፣ አዘጋጁት ማለት ነው ። በተጨማሪም የአሜሪካ መሪዎች የሃሣብ ነፃነትን የበለጠ ገደቡ ፤ የሀገሪቷን ኮሚኒስቶች እያደኑ ማሰቃየትን ተያያዙት ። ብሔራዊ ጥቅማችንን ከውጭ አደጋና ከኮሚኒስቶች ለመከላከል በሚል ሰበብ የፀረ ሕዝብ ሥራቸውን አስፋፉት ።[7]

የአሜሪካ መንግሥት የውስጥ ፖሊሲ ብቻ ሳይሆን የውጭ ፖሊሲውም በ1947 የበለጠ ወደ ቀኝ አክራሪነትና ጦረኝነት ተሸጋገረ ። በዚህ ዓመት «በኮርፖሬሽኖች፣ በወታደራዊ ባለሥልጣኖች ፣ በውጭ ፖሊሲ የጥናት ማዕከሎች ፣ በዋና ዋና ጋዜጦችና ተደማጭነት ባላቸው ግለሰቦች በዋሽንግተን ይብላሉ የነበሩ ብዙ የኢምፔሪያሊስት ሃሣቦች» ተግባራዊነት እንዲያገኙ ልዩ ልዩ የውጭ ፖሊሲ እርምጃዎች ተወሰዱ፤የውጭ ፖሊሲ መመሪያዎችም ወጡ። በዚሁ ዓመት ጆርጅ ማርሻል የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እንዲሆን ተመረጠ። ይህ ሰው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በፀረ ፋሽስት ግንባር ከተሰለፉት ኃይላት መካከል የታወቀ የሚሊታሪ ስልተኛና የግንባሩ ዕዝ ሊቀመንበር ነበር ። የሱ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ቦታ መመረጥ በአሜሪካ ፖሊሲ ውስጥ «የጦር መኮንኖችና ዲፕሎማቶች አንድ የሚያደርጋቸው አካል አስገኘላቸው ፤ ለሚሊታሪ ቡድኖችም አዲስ ሚና እንዲኖራቸው በር ከፈተላቸው ። የውጭ ፖሊሲ የሚሊታሪ (በአመዛኙ በኃይል ላይ የተመሠረተ ማለቱ ይሻላል) ፖሊሲ ሆነ ፤ ይህም በይፋ በወጣ የመንግሥት መመሪያ ተብራራ ።»[8]

የአሜሪካ የቀኝ አክራሪዎች በዚህ ዓይነት በሀገሪቱ የውስጥ አመራር የበላይነትን ይዘው ፀረ ሕዝብ ሥራቸውን ሲያካሂዱና ለውጭ ጣልቃ ገብነት ዝግጁ ሆነው ሳለ በልዩ ልዩ ሥፍራዎች በተለይም በአውሮፓና በእስያ የሠርቶ አደሮችና የሌሎች የጭቁን ሕዝቦች ትግል ሥር እየሰደደና የኢም

Digitized by Google

ፔሪያሊዝምን የጭቆና ሰንሰለት እያሰለሰለው መጣ፡፡በዚህ ወቅት የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ፖሊሲ ይህን ሕዝባዊ ትግል ማከሸፍ ዓይነተኛ ተግባሩ ሆነ ። ትግሉን ለማፈን የአሜሪካ ዶላር በአውሮፓ ዘመተ ፣ የወታደራዊ ስምምነቶች ተፈረሙ ፣ የጦር ሰፈሮች በብዙ ቦታዎችና አገሮች ተመሠረቱ ። የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች የገጠማቸውን ሕዝባዊ ትግል ሁሉ በጠመንጃ አፈሙዝ ለመቋቋም መረጡ ። ኮሚኒዝም እንዳይስፋፋ «ለማገድ» ከተቻለም ከምድረ ገጽ «ለማጥፋት» ዘመቻ ተቀየሰ ። ዓለም በውጥረት ውስጥ ወደቀች ። ይህ የተዘጋጃው ጦርነት ወቅት ፖሊሲ መሆኑ ነው ። ፖሊሲውን የነደፈው በጊዜው የአሜሪካንን መንግሥት የሚመራው የትሩማን አስተዳደር ነበር ። ይህ ፖሊሲ በትሩማን ዶክትሪን ፣ በማርሻል ፕሮግራምና ፖይንት ፎር ፕሮግራም በይበልጥ ተዘርዝሯል ። እነኚህን መመሪያዎች ከዋና ጉዳል በዝርዝር እንመለከታቸዋለን ።

የትሩማን መመሪያ

የትሩማን መመሪያ መጋቢት 12 ፣ 1947 ወጣ ። በወቅቱ በግሪክና በቱርክ ከፍተኛ ሕዝባዊ ትግል ተቀጣጥሎ ነበር ። ቀደም ሲል በአካባቢው የሕዝባዊ ትግልን በማፈን ከፍተኛ ትብብር ያደርግ የነበረው የእንግሊዝ መንግሥትም በሕዝባዊ ትግል የተወጠሩትን የግሪክንና የቱርክ ገዥዎችን ለመርዳት የማይችል መሆኑን ለአሜሪካ መንግሥት ሪፖርት አቀረበ።[9] ፕሬዚዳንት ትሩማን እንዳለው «ግሪክ እርዳታ» ልትጠይቀው የምትችለው ሌላ አገር አልነበረም ። በዚህ ንግግሩ እንደተጠቀሰው ትሩማን የግሪክ መንግሥት በሕዝብ አመጽ ከተገለበጠ የትግሉ ወላፈን ለግሪክ ጉረቤቶችም ይደርሳቸዋል ብሎ መፍራቱን አልሸሸገም ። በእሱ እምነት « በታጠቁ አናሳን እጅ ግሪክ ከወደቀች ተፅዕኖው ለዚችው አገር ጉረቤት በሆነችው በቱርክ ላይ የተፋጠነና ከባድ ይሆናል ... በተጨማሪም የግሪክ ነፃ መንግሥት (በጊዜው የነበረውን አድሃሪውን የግሪክ መንግሥት ማለቱ ነው) መደምሰስ በአውሮፓ ባሉ ሕዝቦች ላይ ተፅዕኖ አለው ። » ለዚሁ ሁሉ « መፍትሔ » የሚሆነው የተቀሰቀሰውን ትግል ለማፈን የሚያስችለው የአሜሪካ የኢኮኖሚና የሚሊታሪ እርዳታ መሆኑን ትሩማን በማመኑ ይህንኑ «መፍትሔ» ለመስጠት ከመጋቢት 1947 ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 1948 ድረስ የአሜሪካ መንግሥት «ለግሪክና ለቱርክ 400,000,000 ዶላር እርዳታ እንዲሰጥና የአሜሪካ ሲቪሎችና የሚሊታሪ ባለሙያዎች ወደ እነኝህ አገሮች እንዲሄዱ እንዲፈቀድ ኮንግሬሱን ጠየቀ ።[10] ከዚህ ከትሩማን አነጋገር ለመረዳት እንደሚቻለው የትሩማን መመሪያ በባህሪው ሕዝባዊ ትግልና አብዮታዊ እንቅስቃሴን ለማከሸፍ አቅም ያነሳቸውን አድኃሪ መንግሥታትን ለመርዳት በሌሎች አገሮች ጉዳይ የአሜሪካ ወታደራዊና ኢኮኖሚ ጣልቃ ገብነት ነው ።

የማርሻል ፕላንና የሰሜን ቃል ኪዳን ድርጅት

የካፒታሊዝምን ሥርዓት ከውድቀት ለማዳን የትሩማን መመሪያ ንድፍ ብቻ በቂ አልነበረም ። በምዕራብ አውሮፓ የሕዝብ አመጽ በአንዳንድ አገሮች ተቀስቅሶና በአንዳንዶቹም በተለይ በፈረንሳይና በኢጣሊያ ኮሚኒስቶች ሥልጣን ለመያዝ ተቃርበው ስለነበር[11] በአሜሪካ በኩል ይህ ጉዳይ ከፍተኛ ስጋትን አስከትሎ ነበር ። ስጋቱም « የማርሻል ፕላንን » አስከተለ ። ፕላኑ የተሰየመው በጥር ወር 1947 የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እንዲሆን በተመረጠው በጄኔራል ጆርጅ ማርሻል ስም ነበር። ጆርጅ ማርሻል ሰኔ 5 ፣ 1947 በሃርቫርድ

Digitized by Google

ዩኒቨርስቲ ባደረገው ንግግር በጦርነት የፈራረሰውን የአውሮፓን ኢኮኖሚ መልሶ በአሜሪካ እርዳታ መገንባት እንደሚያስፈልግ አሳሰበ ፡፡ የዚህም ፖሊሲ ዓላማ «ነፃ ተቋሞች (የካፒታሊዝምን ማለቱ ነው) ሊጠበቁ የሚችሉበት የፖለቲካና የማኅበራዊ ሁኔታዎችን መፍጠር» እንደሆነ አስገነዘበ ፡፡ [12] በተጨማሪም የምዕራቡን ካፒታሊዝም ከውድቀት ለማዳን በወታደራዊ መስክም ዝግጅት ለማድረግ መጋቢት 4 ፣ 1949 የሰሜን አትላንቲክ የቃል ኪዳን ድርጅት (NATO) በአሜሪካ መሪነት ተቋቋመ ፡፡

ፖይንት ፎር ፕሮግራም

ኋላቀር አገሮችም ከኢምፔሪያሊዝም ወጥመድ እንዳያመልጡ ፣ ነፃ ብሔራዊ ኢኮኖሚ እንዳይገነቡ ፣ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ሌላ ፕሮግራም ነደፈ ፡፡ ይህም ፖይንት ፎር ፕሮግራም እየተባለ የሚጠራው ነበር ፡፡ ይህ ፕሮግራም በይፋ የቀረበው ፕሬዚዳንት ትሩማን ሰኔ 24 ፣ 1949 ባደረገው ንግግር ነው ፡፡ ፕሮግራሙ የአሜሪካንን የቴክኒክ ዕርዳታና የግል መዋዕለንዋይ ወደ ታዳጊ አገሮች መስፋፋት እንዳለበት ይጠቁማል ፡፡ የትሩማን ፍራቻ የታዳጊ አገር ሕዝቦች በአሜሪካ «ካልተረዱ» የሶሻሊስት የእድገት ጎዳናን ይመርጣሉ የሚል ነው ፡፡ [13] ስለሆነም ታዳጊ አገሮች ወደ ሶሻሊስት የዕድገት ጎዳና እንዳያመሩ ለማደናቀፍ የአሜሪካ መንግሥት በኢኮኖሚ እርዳታ ለማዘናጋት ቆርጦ ተነሳ ፡፡ የፖይንት ፎር ፕሮግራም ዓላማም ይኸው ነበር ፡፡

የፖይንት ፎር ፕሮግራም እውነተኛ ዓላማ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአፍሪካ በኢስያና በላቲን አሜሪካ የነበሩ የቀድሞ ቅኝ ግዛቶችን ለየት ባለ ዘዴ በመጠቀም በአሜሪካ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ቀንበር ሥር ማስገባት ነው ፡፡ ለዚህም ነው «ፖይንት ፎር በኋላቀር አገሮች የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የበላይነት ማስጨበጫ መሣሪያ...» ነው የሚባለው ፡፡ [14] በፖይንት ፎር ፕሮግራም አማካይነት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ መልክ እያገኘ የመጣው የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ መሠረቱን ጣለ ፡፡ የአሜሪካ ገዥዎች እውነተኛ የብዝበዛ ዓላማቸውን በአንዳንድ የነፃነት መፈክሮች ለምሳሌ (እንደ ሁኔታው) አርገውን የቅኝ አገዛዝ በማውገዝና . . . ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር የተላቀቁትን ሕዝቦች የነፃነትን መብት ለይስሙላ በማወቅ ... የአሜሪካንን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ አስፋፉ ፡፡

ሶሻሊዝምን የመገደብ ፖሊሲ

በአውሮፓም ሆነ በታዳጊ አገሮች የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ዓላማ የካፒታሊዝምን እድሜ ለማራዘም ፣ ሶሻሊዝምንና የነፃነት እንቅስቃሴዎችን እውነተኛ የአርነት ትግል መግታት ነበር ፡፡ በመሆኑም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ውስጥ የጦር ወዳጃቸው በነበረችው በሶቭየት ኅብረት ላይ ጠንካራ እርምጃ ለመውሰድ ወሰኑ ፡፡ ፕሬዚዳንት ትሩማን በጊዜው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለነበረው ለባርንስ ጥር 5 ፣ 1946 በፃፈው ደብዳቤ «ሩሲያ እንደ ብረት የጠነከረ ክንድና ጠንካራ አነጋገር ካልገደባት በስተቀር ሌላ ጦርነት እየተጠነሰሰ ነው» ካለ በኋላ በደብዳቤው መጨረሻ «ሶቭዬትን እሹሩሩ ማለት እጅ እጅ ብሎኛል» ብሏል ፡፡ [16] ትሩማን ይህን ደብዳቤ የጻፈበት ምክንያት የአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ በደብዳቤው ላይ በሰፈረው ፅንሰሃሳብ አንፃር እንዲቀየስ ነበር ፡፡ ይህ ድርጊት በወቅቱ ለሶቭዬትና ለአሜሪካ የበለጠ መራራቅ እንደመንደርደሪያ ነጥብ ይቆጠራል ፡፡

የሶቭዬት ኅብረትና የአሜሪካ ግንኙነት በ1947 የባሰ ተበላሸ ፡፡ ለመጀመሪያም ጊዜ ሶሻሊዝምን የመገደብ ንድፈሃሳብ (ኮንቴይንመንት ቲዎሪ) ተቀነባበረ ፡፡ ንድፈሃሳቡን ያቀረበው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መ/ቤት ባልደረባ የነበረው ጆርጅ ኬናን ነው ፡፡ ኬናን «ሶቭየት ኅብረትን በሚመለከት ማንኛውም የአሜሪካ ፖሊሲ የረጅም ፣ ትዕግስተኛና የሩሲያን የመስፋፋት

Digitized by Google

አዝማሚያዎች የሚገድብ ጠንካራና ቀራጥነት የተሞላበት መሆን አለበት» በማለት አስገነዘበ ።[17] ኬናን በዚህ ዓይነት ተፅዕኖ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ሶሻሊዝምን ከዓለም ለማስወገድ የሚቻል መሆኑን ተነበየ። የዚህ ግለሰብ አቋም በመንግሥት ደረጃ ተቀባይነት አግኝቶና ተብራርቶም በሥራ መዋል ጀመረ ።

በአሜሪካ መሪዎች አስተያየት የሶሻሊዝም በፖላንድ ፣ በምሥራቅ ጀርመን፣ በቼኮዝሎቫኪያ መመስረትና በኢራን፣ በግሪክና በመሳሰሉት አገሮች የነፃነት እንቅስቃሴዎች ትግል መለኮስ የሶቭዬት ኅብረት «መስፋፋት» ነው ። ይህም በመሆኑ አሜሪካ ከሶቭዬት ኅብረት ጋር መልካም ግንኙነት ሊኖራት አልቻለችም ባይ ናቸው ።[18] የአሜሪካ መንግሥት መሪዎች ለዚህ «መስፋፋት» መገደቢያ ይሆኑናል ብለው ያመኑባቸውን ልዩ ልዩ ተጨማሪ እርምጃዎች ወሰዱ ። ለምሳሌ በግሪክና በቱርክ የውስጥ ጉዳዮች የአሜሪካ በተለየ መንገድ ጣልቃ መግባት ፣ በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አስተባባሪነት በሰሜንና ደቡብ አሜሪካ ያሉ መንግሥታት (ካናዳን ሳይጨምር) መስከረም 2 ፣ 1947 የሪዮ ስምምነት በመባል የሚታወቀውን የርስ በርስ መረዳዳት ስምምነት መፈረም ፣ በአውሮፓ የኢኮኖሚ እርዳታና የሚሊታሪ ስምምነት (የሰሜን አትላንቲክ ቃል ኪዳን መጋቢት 4 ፣ 1949) ማድረግና ፀረ ሶሻሊስት ኃይላትን ማጠናከር በከፊል የዚሁ «ሶሻሊዝምን ለመገደብ» ከሚለው ዓላማ የመነጩ እርምጃዎች ናቸው ። የሪዮ ስምምነት የወታደራዊ ስምምነት ግዴታ ያለበትንና አሜሪካ በታሪኳ ውስጥ በሰላም ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ የወታደራዊ ግዴታ የገባችበት ስምምነት ነው ።[19] የሰሜን አትላንቲክ የቃል ኪዳን ድርጅት ስምምነትም አሜሪካ በሰላም ወቅት ከምዕራብ አውሮፓ መንግሥታት ጋር የጦር ስምምነት ስታደርግ የመጀመሪያው ነው ።[20]

በአጠቃላይ እላይ እንደተጠቀሰው የእነኚህ ስምምነቶች አንዱ ዓላማ የሶሻሊዝምን መመሥረት ማፈን ነው ። የሶሻሊዝም መስፋፋት ደግሞ የታሪክ እድገት ውጤት ነውና ሊገታ የሚችል ነገር አይደለም ። ስለሆነም የምሥራቅ አውሮፓ ሕዝብ የሶሻሊዝምን መንገድ ተከተለ። በእስያ የቻይና ሕዝብ በፀረ ኢምፔሪያሊዝም ትግሉ ድል አድርጎ ቀይ ባንዲራ አውለበለበ ። በዚህ ሕዝባዊ ድል የተደናገጡ የአሜሪካ ገዥዎችም በኮሪያ የተቀሰቀሰውን ሕዝባዊ ትግል ለማደናቀፍና የኢምፔሪያሊዝምን ጥቅም ለማስከበር በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታ ምክር ቤት ውሣኔ ሽፋን እጃቸውን አስገቡ ። ይህንኑ ውሣኔ መሠረት በማድረግ ትሩማን ሰኔ 27 ፣ 1950 ባደረገው ንግግር «የአሜሪካ የአየርና የባህር ኃይላት ፣ ለኮሪያ መንግሥት ሽፋንና ድጋፍ እንዲሰጡ» ማዘዙን አሳወቀ። በዚህ ንግግሩ ትሩማን በፊሊፒንስ ፣ በኢንዶቻይና (በቬትናም ጭምር) ፈረንሣይንና አጋሮቿን አሜሪካ እንድትረዳ ያዘዘ መሆኑን ገልጿል ።[21]

የቀዝቃዛው ጦርነት መባባስ

ሕዝባዊ ትግል በልዩ ልዩ ሀገሮች ሲፋፋም የአሜሪካ መንግሥት መሪዎችም የበለጠ የቀኝ አክራሪነታቸውን እያባባሱት ሄዱ ። በጊዜው በአሜሪካ የፖለቲካ አስተሳሰብ ተስሚነትንና በብሔራዊ ሸንጐው በ1946 በተደረገው ምርጫ የበላይነትን ይዘው የነበሩት የሪፐብሊካን ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎቻቸው በ1952 በተደረገው ምርጫ ተጨማሪ ድል አገኙ ። በዚህ ምርጫ የሪፐብሊካኑ ፓርቲ ከ1928 ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ በሁለቱም ምክር ቤቶች የበላይነትን ያዘ ። ፕሬዚዳንቱም የዚሁ ፓርቲ አባል የነበረው ጄኔራል አይዘንሃወር ሆነ ።[22]

በዚህ ምርጫ የሪፐብሊካኑ ፓርቲ አክራሪ መሪዎች በመንግሥት መዋቅር ውስጥ የበላይነትን እንደያዙ ዩናይትድ ስቴትስ ከሶቪየት ኅብረት ጋር ፈጽሞ ለመጣጣም የማትችል መሆኗን ፣ ሶሻሊዝምን እንዳይስፋፋ መገደብ ሳይሆን ማጥፋት የሚያስፈልግ መሆኑን አመኑበት ። ይህንኑ በሚመለከት የዚሁ ፓርቲ የውጭ ፖሊሲ ቃል አቀ

Digitized by Google

ባይ የነበረውና በኋላም የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሆነው ጆን ፎስተር ዱላስ ለአሜሪካ የሕግ መወሰኛ ምክርቤት የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ባደረገው ንግግር፡«የዓለም ሕዝብ አንድ ሶስተኛው በሶቪዬት ኮሚኒዝም ሥር ሆኖ እንዲሁም (የሶቪየት ኮሚኒዝም) ግዛቱን ለማስፋት እየሞከረ እስካለ ድረስ ሰላም ልናገኝ ወይም ደስታ ያለው ዓለም ሊኖረን ፈጽሞ አይችልም» አለ ። ቀጥሎም አመች በሆነ ጊዜ ሁሉ በመጠቀም ሶሻሊዝም የሰፈነባቸውን አካባቢዎች «ነፃ» ማውጣት እንዳለባቸው አስገነዘበ ።[23] የዚህ ግለሰብ አቋም የጠቅላላ የአሜሪካ መንግሥት የውጭ ፖሊሲ መመሪያ ሆኖ የቀዝቃዛው ጦርነት እሳት የበለጠ እንዲነድ ይራገብ ጀመር ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዱላስ ጥር 12 ፡ 1954 ባደረገው ንግግር በማንኛውም አሳሳቢ ነው በምትለው ቦታ አሜሪካ ባሳት ኃይሏና በመረጠችው ዓይነት መሣሪያ የምትጠቀም መሆን ግልጽ አደረገ።[24] በጊዜው የአሜሪካ መንግሥት መሪዎች አቶሚክ ቦምብ በጃቸው ነበረና (የመጀመሪያው የተሳካ የሃይድሮጂን ቦምብ ሙከራ መጋቢት 1፡ 1954 ተካሂዷል) የዱላስ ዛቻ ሶሻሊዝምን ሆነ የነፃነት እንቅስቃሴዎችን «ለማውደም» የአሜሪካ መንግሥት ቦምቡን ለመጠቀም የከጀለ መሆኑን ያመለክታል። በእርግጥ በፕሬዚዳንት አይዘንሃወር አስተዳደር ጊዜ አሜሪካ የውጭ ጥቅሟን ለማስከበር የአውቶሚክ ቦምብ ለመጠቀም ዝግጁ እንደነበረች ፕሬዚዳንቱ በኋላ በይፋ ተናግሯል።[25] የዱለስ ንግግር የቀዝቃዛው ጦርነትን ከከፍተኛ ነጥብ ያደረሰው እንደሆነም ይታመናል ።

የአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣኖች ሶሻሊዝምን «ለማውደም» ባወጡት ፖሊሲ ሊቀጥሉበት አልቻሉም ። ምክንያቱም አንደኛ፡ሶቪየት ኅብረትም የኑክሌር መሣሪያ ባለቤት ለመሆን ስለቻለችና ሌሎችም ሶሻሊስት አገሮች እየተጠናከሩ ስለመጡ ከነሱ ጋር አጠቃላይ ጦርነት መቀስቀስና ማካሄድ እራስን ማጥፋት የሚያስከትል መሆኑ ግልጽ በመሆኑ ነው ። ሁለተኛ ፡ የታዳጊ አገሮች የፀረ ቅኝ አገዛዝ እንቅስቃሴም እየተስፋፋ በመሄድ ላይ ነበር ። ሶስተኛ ፡ የአሜሪካ ወዳጆችም ዱለስ በወጠነው መሠረት ቀዝቃዛው ጦርነትን ማካሄድና የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን የፀረ ሶሻሊዝም ጥሪ ሙሉ ለሙሉ ለመቀበል ዝግጁ አልነበሩም። አራተኛ ፡ ዱለስ በጥር 2 ፡ 1955 ባደረገው ንግግር በአለው መሣሪያ ሁሉ ተጠቅመን ሶሻሊዝምን እናወድማለን ማለቱ በአሜሪካና በሶቪየት ኅብረት መካከል የኑክሌር ጦርነት ሊቀሰቅስ መቻሉን ይፋ ስላደረገውና ይህም ሃሳብ በአሜሪካ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ስለአልነበረው ሕዝቡን ለማረጋጋት ከዚህ የአክራሪነት ፖሊሲ ማፈግፈግ ግዴታ ስለነበረ ነው ።[26]

ሐምሌ 21 ፡ 1955 በጄኔቫ በአራቱ ኃያላን መንግሥታት መካከል ይካሄድ ለነበረው ስብሰባ ጄኔራል አይዘንሃወር ስለጦር መሣሪያ ቅነሣ ሃሣብ አቀረበ ። የቀረበው ሃሣብ በጊዜው የተሰሩት መሣሪያዎች አደገኛ መሆናቸውን ሲጠቁም «በቅርብ ዓመታት የተሠሩት መሣሪያዎች» ተፋላሚ ወታደሮችን ብቻ ሳይሆን ቤቶችን ፡ እንዱስትሪዎችንና ሕይወትን እጅግ ብዙ ጊዜ (እስከ አሁን ከታወቀው) ወይም እስከ አሁን ከታሰበው በላይ ሊያጠፉ የሚችሉ ናቸው» የሚል ነበር። ሁለተኛ ፡ የጦር መሣሪያን መቀነስ ፡ «ለምን እንደሚጠቅም ሲጠቁም ፡ ሀ/ የጦር መሣሪያ ቅነሣ የሁሉንም አገሮች ሰላም ለመጠበቅና ፀጥታን ለማስከበር የተሻለ ዘዴ ሊሆን እንደሚችል ፡ ለ/ «በየቦታው በሕዝብ ዘንድ የሚታየውን የጦርነት ፍራቻ» እንደሚያስወግድ ፡ ሐ/በሕዝቡ ላይ የተጫነውን ወታደራዊ ወጪ ሊቀንስ የሚችልና የማንኛውም አገር ሕዝብ «የኑሮ ደረጃ ከፍ እንደሚያደርግ ፡ የተሻለ ምግብ ፡ ልብስ ፡ መጠለያ ፡ ከፍተኛ ትምህርትና የላቀ የኑሮ ደስታ» ሊያስገኝለት የሚችል መሆኑን አመልክቷል ።

Digitized by Google

ስለሆነም በሁኔታዎች አስገዳጅነት የአሜሪካ መሪዎች የግዴታ በቀጥታ ከሶሻሊስት አገሮች ጋር ጦርነት እናውጃለን ወይም በዱለስ አነጋገር ሶሻሊዝም «እስካለ ድረስ ሰላም ልናገኝ ወይንም ደስታ ያለው ዓለም ሊኖር ፈጽሞ አይችልም» ከሚል አቋም ከሶሻሊዝም ጋር ጦርነት «ብናካሄድ ያጠፉናል»፤ ከሶሻሊስት መንግሥት ጋር መደራደሩ «ለሕዝባችን» ይጠቅማል ወዘተ … ወደሚለት ወይንም ቢያንስ ቢያንስ ሶሻሊዝምን «ለማጥፋት» ከሚለው ይፋ የጀብደኝነትና የጦርነት ፖሊሲያቸው መቆጠብ እንዳለባቸው ተገነዘቡ ።

በአይዘንሃወር ቀርቦ የነበረው የጦር መሣሪያ ትነሳ ስምምነት ሊቀጥል አልቻለም ። በአሜሪካ መሪዎች አስተያየት ለዚህም ምክንያቶች የሆኑት የሶቪየት ኅብረት የሕዋው ቴክኖሎጂ ከፍ ማለትና ስፖትኒክ የምትባለውን የጠፈር መንኩራኩር በ1957 በተሳካ ሁኔታ ወደ ህዋው ለማምጠቅ የመጀመሪያ አገር ለመሆን መቻሏ፣ ሶቪየት ኅብረት በሚሳይል መሣሪያ በልጣናለች የሚል የአሜሪካ መሪዎች ፍራቻ፣ የሁለተኛው የበርሊን ቀውስ (1960)፣ በኩባና በኮንጎ አብዮት መቀጣጠል፣ የግብጽ ነፃነት ትግል ሥር መስደድና የናስርም ከሶቪየት ኅብረት ጋር ወዳጅ መሆንና የመሳሰሉት ድርጊቶች ናቸው ።[28]

በአሜሪካ መሪዎች አስተያየት በየአገሮች (በግብጽ ጭምር) የሚካሄደው የነፃነት እንቅስቃሴ መንስኤው የኮሚኒዝም ወይንም የሶቪየት ኅብረት «ሴራ» ነው ። በመሆኑም ከሶቭየት ኅብረትም ሆነ ከሌሎች ከሶሻሊስት አገሮች ጋር ሊኖር የሚገባው መልካም ግንኙነት በታዳጊ አገሮች አብዮት መካሄድ ይደናቀፋል ባይ ናቸው ። ያ ጊዜ ደግሞ በብዙ ኋላቀር አገሮች የአርነት ትግል በመፋፋም ላይ የነበረበትና አሜሪካም ትግሉን ለማፈን የበኩሏን ጥረት የምታደርግበት ወቅት ነበር ። ለምሳሌ በመስከረም 1954 አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሣይ፣ አውስትራሊያና አራት የእስያ አህጉር አገሮች ያሉበት የደቡብ ምስራቅ እስያ ስምምነት በመባል የሚታወቀው ወታደራዊ ስምምነት ተፈረመ ። በዚያው ወቅት የአሜሪካ መንግሥት በሕዝባዊ ቻይናና በጓቴማላም የውስጥ ጣልቃ መግባቱን እንደቀጠለ ነበር ።[29] በግብጽ ተቀስቅሶ በነበረው ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግልና ግብጽ የሲዊዝ ቦይን በራሷ ለመቆጣጠር ያደረገችውን ጥረት አስመልክቶ መጋቢት 9፣ 1957 አሜሪካ በመካከለኛው ምሥራቅ የምትከተለውን የጣልቃ ገብነት ፖሊሲ ይፋ አወጣች። ይህ ፖሊሲ የአይዘንሃወር መመሪያ (ዶክትሪን) የሚል ስም ተሰጥቶታል ። በዚህ ፖሊሲ መሠረት የሶቪየት ኅብረት «ጣልቃ ገብነት»፣ የኮሚኒዝምን መስፋፋት «ለመከላከል» በሚል ሰበብ አሜሪካ ለማንኛውም አፍቃሪ—አሜሪካ (የአሜሪካ ደጋፊ) የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች የሚሊታሪና የኢኮኖሚ እርዳታ ለመስጠት ቃል ገባች። ለዚሁ ወጪ በ1957 የበጀት ዓመት 200,000,000 የአሜሪካ ዶላር ተመደበ ። በዚያው መመሪያው በወጣበት ዓመትም በዮርዳኖስ ሰላም ለማስከበር በሚል ስም ስድስተኛውን የአሜሪካ የባህር ኃይል ወደ መካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ ላከች ። በሚቀጥለውም ዓመት በሊባኖስ ጦሯን ጣልቃ አስገባች ።[30]

በአጠቃላይ ሲታይ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግስት ጀምሮ ተጠናክሮ የታየውን ሶሻሊዝምንና የአርነት እንቅስቃሴን እንዲሁም በለሙት ካፒታሊስት አገሮች በመቀጣጠል ላይ የነበረውን ሕዝባዊ ትግል ለማፈንና የካፒታሊዝምን እድሜ ለማራዘም የአሜሪካ የቀኝ አክራሪዎች ልዩ ልዩ የውጭ ፖሊሲ መመሪያዎችን አወጡ፤ ከሌሎች አድኃሪ መንግሥታት ጋር ስምምነቶች ተፈራረሙ ። በሌላ ከነጋገር በድምራቸውና በመስተጋብራቸው ሲታዩ እነኝህ የአሜሪካ ፖሊሲዎችና ስምምነቶች በሙሉ የሶሻሊ

Digitized by Google



በጦር መሳሪያ ኃይል መጠቀም አሜሪካ የውጭ ፖሊሲውን ለማስፈፀም የሚጠቀምበት ዓይነተኛ ዘዴ ነው ።

(ከ « *News Week* » መጽሔት የተገኘ)

ዝምን ዕድገት ለመግታት ፣ ከተቻለም ለመ ደምሰስ ፣ በታዳጊ አገሮች ሕዝባዊ ትግልን ለማከሸፍና የኢምፔሪያሊዝምን ጥቅም ለማ ስከበር የታለሙ ነበሩ ።

ለዓላማዎቹ ግብ መምታት የአሜሪካ መንግ ሥት መሪዎች በጦር ኃይል በተለይም በሰ ውም ሆነ በንብረት ላይ ከፍተኛ አደጋ ሊ ያደርስ የሚችለውን የአቶሚክ ቦምብ ለመ ጠቀም ዝግጁ መሆናቸውን በተለያዩ አጋ ጣሚዎች ይሰነዝሯቸው ከነበሩት ዛቻዎች መገንዘብ ይቻላል ። በመሆኑም የአሜሪካ መንግሥት በአመዛኙ በጣልቃ ገብነትና በጦርነት ላይ መተማመን የውጭ ፖሊ ሲው ዓይነተኛ ገጽታ ሆነ ። ለዚህም በኮርያ፣ በቬትናምና በኮንጐ ያደረጋቸው ጦርነቶች ግልጽ መረጃዎች ናቸው።ይህ በጦረኛነት ላይ የተመሠረተ የአሜሪካ የኢምፔሪያሊዝም የውጭ ፖሊሲ እስከ 1960 ዎቹ ዓመታት መጨረሻ ድረስ የዓለምን ፖለቲካ በከባድ ውጥረት ውስጥ እንዲወድቅ አደረገው ። ይህ ወቅት የቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት በመባል የሚታወቀው ነው ። የቀዝቃዛው ጦርነት አሜሪካና ሌሎች ኢምፔሪያሊስት አገሮች ከሶሻሊስት አገሮች ጋር ሆነ ከነፃነት እንቅ ስቃሴዎች ጋር ያላቸውን ቅራኔ ፣ ግጭት ወይም አለመግባባት በሰላማዊ መንገድና በውይይት ሳይሆን በአብዛኛው በጦርነት ለመፈታት ፣ ዓለምን የካፒታሊዝም ትርፍ ማጋበሻ ለማድረግ የጣሩበት ፣ የኢምፔሪያ ሊዝምን የብዝበዛ ተቃዋሚዎች ሁሉ በጦ ርነት እናንበረክካለን ብለው ተስፋ ያደረ ጉበትና ይህንኑም ተስፋቸውን በተግባር ለመተርጐም የተነሱበት ወቅት ነበር። ይህ ወቅት የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የሕዝ ቦችን የነፃነት ትግል ለማፈን በየአገሩ ጣልቃ የገባበት ፣ በዓለም ዙሪያ የጦር ሰፈሮችን በብዛት የመሠረተበት ወቅት ነው ። በሌላ በኩል ይኸው ወቅት በዛ ያሉ ኋላቀር አገ ሮች በዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ላይ ባካሄዱት ትግል ብሔራዊ ነፃነታቸውን የተ ጐናፀፉበት ፣ በዓለማችን ሶሻሊዝም በኢ ኮኖሚ አቋሙና በወታደራዊ ኃይሉ የተጠ ናከረበትና በብዙ የዓለም ምዝብር ሕዝቦ ች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘበት ወቅት ነበር ።

የቀዝቃዛው ጦርነት ፖሊሲ ውድቀት

በ1940ዎቹ መግባደጃ ላይ በዩናይትድ ስቴትስ ገዥ መደቦች መሪነት የተቀየሰው የቀዝቃዛው ጦርነት ፖሊሲ በ1960 ዎቹ መ ጨረሻ ላይ ግቡን ሊመታ የማይችልና የማ ያዋጣ ፖሊሲ መሆኑ ለአብዛኞቹ ለዚህ ፖሊሲ አራማጅ ለሆኑት ኃይላት ግልጽ ሆነ ። ለዚህ ፖሊሲ ውድቀት ሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ ። 1/ የሶ ሻሊስቱ ማኅበረሰብ በቀዝቃዛው ጦርነት ፖሊሲ የማይሸነፍ መሆኑን አረጋገጠ። በቀ ዝቃዛው ጦርነት ፖሊሲ ውጥን መሠረት ይደመሰሳል የተባለው የሶሻሊስት ስርዓት እንኳን ሊደመሰስ ቀርቶ የበለጠ ተጠናከረ። ሶሻሊዝም በኢምፔሪያሊዝም የሚሰነዘርበ ትን ጥቃት (ወታደራዊ ሆነ ሌላ ዓይነት ጥ ቃት) ሊቋቋም የሚችል መሆኑን በተግባር አሳየ ። 2ኛ/ የነፃነት እንቅስቃሴዎች ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል ድል ተጐናጸፈ። እነ ዚህ እንቅስቃሴዎች በቆራጥ ትግላቸው ኢም ፔሪያሊስቶችን ድል እያደረጉ ብዙዎቹ ብሔራዊ ነፃነታቸውን ተጐናጸፉ ፤ በትግላ ቸውም የበለጠ የገፉት (ቬትናም ፣ ኩባ ፣ ቻይና ፣ ሰሜን ኮሪያ ወዘተ...) በቀዝቃዛው ጦርነት ፖሊሲ ይጠፋል ወይንም እንዳይስ ፋፋ ይታገዳል የተባለውን ሶሻሊዝምን ለመ ገንባት ባካሄዱት መራራ ትግላቸው ባለድል ሆኑ ። 3ኛ/ የአሜሪካ የውስጥ ሁኔታ ለቀዝ ቃዛው ጦርነትና ለጣልቃ ገብነት ፖሊሲ መ ቀጠል አመች አልሆነም ። በወቅቱ የአሜሪካ የቅኝ አክራሪዎች ይከተሉ ት የነበረውን የቀዝቃዛውን ጦርነት ፖሊሲ (ማለትም ወ ታደራዊ ጠብ አጫሪነትና የቀጥታ ወታደ ራዊ ጣልቃ ገብነት ፣ በመንግሥታትና በሀ ገሮች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ሁሉ በአመዛኙ በኃይል ለመፍታት መዘጋ

Digitized by Google

ጀትን) መለወጥን አስፈላጊና የግዴታ የሚያ
ደርጉ ልዩ ልዩ የውስጥ ችግሮች ተከሰቱ ።
ለምሳሌ የአሜሪካ ሠራተኛ መደብና ሌሎ
ችም የኅብረተሰብ ክፍሎች ተቃውሞ ፥ ስር
የሰደዱ ማኅበራዊ፥ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ
ችግሮች ተፋፋሙ። እነዚህና የሌሎችም የዓ
ለም አቀፍ ሁኔታዎች ኢምፔሪያሊዝምን
እንዲያፈገፍግ ፥ በአንዳንድ ቦታም ፈጽሞ
እንዲሸነፍ ፥ በአጠቃላይ የተወሰነ የውጭ
ፖሊሲ ለውጥ እንዲያደርግ ፥ ከሶሻሊስት
አገሮች ጋር የነበረውን በቀዝቃዛው ጦርነት
ላይ የተመሠረተውን ፖሊሲ እንዲያለዝብ፥
በኋላቀር አገሮች የውስጥ ጉዳይ የሚያደርገ
ውን ጣልቃ ገብነትና የመሳሰሉትን አክራሪ
የውጭ ፖሊሲ አቋሞቹን እንዲለውጥ አስገ
ደዱት ። በሌላ አነጋገር በ1960 ዎቹ መጨ
ረሻ የነበረው የኃይል ሚዛን በጊዜው ሰፍና
ለነበረው የቀዝቃዛው ጦርነት ፖሊሲ መቀ
ጠል አመች አልነበረም ። የዓለም ፖለቲካ
ሚዛን ወደ ሰላም ኃይሎች ያጋደለና የኢም
ፔሪያሊስቶችን የጦረኝነት ፖሊሲ የሚያ
ናጋ ፥ በተለይም የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝ
ምን ጭልጥ ያለ የቀኝ አክራሪነት የውጭ
ፖሊሲ የግድ የሚያስለውጥ ነበር ። የቀዝ
ቃዛው ጦርነት ፖሊሲ በዴታንት ፖሊሲ
ሊቀየር የቻለባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች
ባጭሩ የተጠቀሱ ቢሆንም ፥ ከዚህ ቀጥሎ
እነዚህኑ ምክንያቶች በዝርዝር ለመመል
ከት እንሞክራለን ።

የሶሻሊዝም መጠናከር

ቀዝቃዛው ጦርነት ሲጀመር የአሜ
ሪካ ኢምፔሪያሊስቶች የአውቶሚክ ቦንብ
ብቸኛ ባለቤት ነበሩ ። ይህ ሊቀጥል አል
ቻለም ። የሶቭዬት ኅብረት የቴክኖሎጂ
እድገት በ1940 ዎቹ መጨረሻ ይህችን አገር
የአቶሚክ መሣሪያ ባለቤት አደረጋት ።
በሌላም የሚሊታሪ ቴክኖሎጂ ሶቭዬት
ኅብረት ከአሜሪካ የማታንስ መሆኑ እያደር
ተከሰተ ። በኢኮኖሚ ግንባታም መስክ
የተገኘው ከፍተኛ እድገት ሶሻሊዝም
ከኢምፔሪያሊዝም ይልቅ ያልተዛባና የማ
ያቋርጥ የኤኮኖሚ እድገት በማስገኘት የሠ
ርቶ አደሩን ቁሳዊና ሕሊናዊ ፍላጎት የሚ
ያረካና ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ የቆመ መሆ
ኑን አስመሰከረ ። በአሜሪካ ኢምፔሪያሊ
ዝም ቀንደኛ መሪነት በሶሻሊስት አገሮች
ላይ ተጥሎ የነበረው የኢኮኖሚ ማዕቀብ
ሊቀጥል አልቻለም ። ከነኝህ አገሮች ጋር
የንግድ ልውውጥ ቢያደርጉ የሚጠቅ
ማቸው መሆኑን የተረዱ የምዕራብ አው
ሮፓ ካፒታሊስት መንግሥታት ከሶሻ
ሊስት አገሮች ጋር የኢኮኖሚ ግንኙ
ነት መፍጠር ጀመሩ ። ስለሆነም ኢም
ፔሪያሊስቶች እናጠፋዋለን ካሉት ከሶሻሊ
ስት ሥርዓት ጋር በሰላም አብሮ ለመኖር
የግዴታ ወደ ፈቃደኛነት ተሸጋገሩ ። የሶሻ
ሊስት ሥርዓት ድል አድራጊነት በአጠቃ
ላይ በኢምፔሪያሊስቶች ፥ በተለይም በአሜ
ሪካ ኢምፔሪያሊስቶች የውጭ ፖሊሲ ላይ
ምን ያህል ተፅዕና እንዳደረገና የውጭ ፖሊ
ሲያቸውን እንዳስለወጣቸው ከሚቀጥለው
ንዑስ ርዕስ በበለጠ መገንዘብ ይቻላል ።

የሌሎች ኢምፔሪያሊስት አገሮች ከቀዝቃዛው ጦርነት ማፈግፈግ

የምዕራብ አውሮፓ ኢምፔሪያሊስት
መንግሥታት በአሜሪካ የሚውጠነጠነው
የቀዝቃዛው ጦርነት ፖሊሲ የማያዋጣቸው
መሆኑን እያደር ተገነዘቡት ። የፈረንሣይ
ፕሬዚዳንት የነበረው ጀኔራል ደጐል ከሶ
ሻሊስት አገሮች ጋር ተቻችሎ መኖር
የሚያስፈልግ መሆኑን ቀደም ብሎ ከተ
ረዱት ከምዕራብ አውሮፓ አገሮች መሪ
ዎች አንዱ ነበሩ ። ደጐል ከሶሻሊስት
አገሮች ጋር በሰላም ተቻችሎ የመኖርን
አስፈላጊነት ሲገልፁ «አለበለዚያ የሰ
ውን ልጅ ሌላ የሚያድነው ነገር የለም»
ብለው ነበር።[31] ደጐል ይህን ያሉት በ1960
ነበር ። በዚሁ ዓመት በጊዜው የእንግሊዝ
ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረው ሃሮልድ ማክ
ሚላንም «ሁላችንም (ካፒታሊስቶችና ሶሻ
ሊስቶች) አብሮ መኖርን መማር አለብን፤...
ወደድንም ጠላንም አብረን የምንኖርበትን
መንገድ መፈለግ አለብን ፤ ጐን ለጐን የም

Digitized by Google

ንኖርበትን አንድ መፍትሔ ማግኘት አለብን»[32] በማለት ከሶሻሊስቱ ዓለም ተቻችሎ በሰላም አብሮ የመኖርን አስፈላጊነት አስገነዘበ ።

የምዕራብ አውሮፓ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ከሶሻሊስት አገሮች ጋር በሰላም አብሮ ለመኖር ፈቃደኝነት ማሳየትና በዚህም መሠረት ግንኙነታቸውን ማሻሻላቸው አሜሪካ በግንባር ቀደምነት ትመራው የነበረው የቀዝቃዛው ጦርነት ፖሊሲ ላይ የቀጥታም ሆነ የተዘዋዋሪ ተፅዕኖ ነበረው ። የምዕራብ አውሮፓ ኢምፔሪያሊስት አገሮች ከሶሻሊስትአገሮች ጋር ግንኙነታቸውን እያጠናከሩ መሆናቸውን የተረዱ የዋሽንግተን መሪዎች እነሱም ከሶሻሊስት አገሮች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማሻሻልን መምረጥ ግዴታ ሆነባቸው ። ይህንኑ ምርጫ አሜሪካ መከተል ያለባት መሆኑ አሜሪካዊ የምክር ቤት አባል ፍራንክ ቸርች እንደሚከተለው ገልጾት ነበር ፤

ለመሳተፍ ፈቃደኛ ሆነን ካልተሳተፍን እኛን ትተው እነሱ (የአውሮፓ የካፒታሊስት መሪዎች—ፀሐፊው) ግንኙነታቸውን ያሻሽላሉ ። ይህ ከሆነ እኛ በአውሮፓ ውስጥ ተሳታፊዎች ሳንሆን በአፋጣኝ ተመልካቾች እንሆናለን ። ዩናይትድ ስቴትስ ወዳጆችዋ ከሶሻሊስት አገሮች ጋር ማድረግ የፈለጉትን ግንኙነት መምራት አለባት ። ግን እኛ ለመምራት መረጥንም አልመረጥንም የአውሮፓ ወዳጆቻችን ቢያንስ በአውሮፓ ውስጥ ቀዝቃዛው ጦርነት አብቅቷል በሚል እምነት ...ግንኙነታቸውን ለማሻሻል መጣራቸውን ይቀጥላሉ ።[33]

በመሠረቱ ለአሜሪካ መሪዎች አንዱ የኃይል ምንጭ ከምዕራብ አውሮፓ የካፒታሊስት መሪዎች ጋር በተቻለ መጠን ማበርና ከሞላ ጐደልም ቢሆን አንድ አቋም መውሰድ ነው ። ብቻቸውን በፀረ—ሶቪዬትና በቀዝቃዛው ጦርነት ፖሊሲያቸው ቢገፉበት ሊያዳግታቸው እንደሚችልና ከአውሮፓ ሰላም «ፈላጊዎች» ጋር ማበር ያለባቸው መሆኑን በሁኔታዎች አስገዳጅነት የተረዱት ይመስላል ። ይህ ብቻም ሳይሆን የአሜሪካ የውስጥ ሁኔታም ለቀዝቃዛው ጦርነት ፖሊሲ አመች አልነበረም ።

የአሜሪካ የውስጥ ሁኔታ

ብዙ ተመራማሪዎች አሜሪካ በ1960ዎቹ መጨረሻና በ1970ዎቹ ዓመታት መጀመሪያ ላይ የገጠሟትን ችግሮች ከፍተኛነት ሲገልጹ ፤ ይህች አገር ከ1929—1933 ከታየው ታላቅ የኢኮኖሚ ቀውስ ወዲህ(በአንዳንዶቹ አስተሳሰብ እንዲያውም በ1860ዎቹ ከተደረገው የርስ በርስ ጦርነት ችግር ወዲህ) እንደዚህ ከባድና አሳሳቢ የውስጥ ችግሮች ገጥሟት አያውቅም ይላሉ ።[34] ከነዚህ ዋና ዋና የውስጥ ችግሮች ፤ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ችግሮች ለምሳሌ የዋጋ መናር ፤ ሥራ አጥነት እየበዛ መሄድ ፤ የአሜሪካ ሕዝብ በአስተዳደሩ ላይ ያለው እምነት መናጋት፣ የአንዳንድ ሞኖፖሊስት ቡድኖች የቀዝቃዛ ጦርነት ፖሊሲን አለመደገፍና የነዚህ ሞኖፖስት ቡድኖች ወኪሎች የአሜሪካን የውጭ ፖሊሲ አመራር ለመቆጣጠር መቻላቸው ይገኙበታል ።

የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ችግሮች

በአሜሪካ እየተስፋፋ የመጣውን ድኅነት ለመቋቋም የሚያስችል ሕግ ነሐሴ 20 ፤ 1964 ወጥቶ ነበር ።[35] ይሁን እንጂ የካፒታሊዝም ባህሪ አንዱ መገለጫ በሀብታሞች ጐን የድሃዎች መኖር ነውና ችግሩ ሊወገድ አልቻለም ። እንዲያውም በ1960ዎቹ መጨረሻ ድኅነትና ሌሎችም ማኅበራዊ ችግሮች የበለጠ ተባብሰው በብዙ የአሜሪካ ከተሞች ለሕዝብ አመጽ መንስኤ ሆኑ ። በ1967 አያሌ የአሜሪካ ከተሞችን የሕዝብ አመጽ አጥለቅቀለቃቸው ። የአመጹን መንስኤ ለማጥናት የተቋቋመው ኮሚቴ መጋቢት 1 ፤ 1968 ባቀረበው ሪፖርት ፤ አሜሪካ

ውያን የገጠማቸውን መራራ ችግር ሲገ ልጹ የ1968 የክረምት ወራት የነጮችና የጥቁሮች ግጭት በሕዝቡ ዘንድ ፍራ ቻንና ግራ መጋባትን የፈጠረበት መሆ ኑን አመልክቶ « ማንኛውም አሜሪካዊ፣ ነጭም ሆነ ጥቁር በዋና ዋና ከተሞ ቻችን ከማያቋርጠው የማኅበራዊና የኢኮ ኖሚ ማሸቀልቀል ሊያመልጥ አይችልም» ብሏል ። ይህ ሪፖርት በሀገሪቱ ውስጥ የተ ስፋፋውንም የሥራ አጥ መጠን በዝርዝር ለማቅረብ ሞክሯል ።[36] እላይ እንደተጠቀ ሰው ለነኝህ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግ ሮች ዋነኛ መንስኤ የካፒታሊዝም የኢኮ ኖሚ ቀውስ ቢሆንም ከፍተኛ የሆነ የሀገሪቷ ብሔራዊ ሀብት ለመሣሪያ አሽቅድድምና በየቦታው ለሚደረግ (ጦርነት በተለይም ለቬ ትናም ጦርነት) የሚባክነው ገንዘብ ችግሩን እንዳባባሰው ለብዙ አሜሪካውያን ግልጽ ነበር ። ስለሆነም የአሜሪካ መሪዎች ከዚህ መሰል የብሔራዊ ሀብት ማባከን እንዲቆ ጠቡ በሕዝቡ ተጽዕኖ ተደረገባቸው ። አን ዳንድ የገዥው መደብ አባላትም የሀብት ማባከኑ ፖሊሲ መቀጠልና የሕዝቡም የው ስጥ ተቃውሞ ሥር እየሰደደ መሄድ ሕልው ናቸውን አደጋ ላይ የሚጥለው መሆኑን በመ ረዳታቸው የአሜሪካ መንግሥት ከውጭ ጣልቃ ገብነት እንዲቆጠብና በቅድሚያ «በብሔራዊ ጥቅም» ማለትም ሀገሪቷ በገጠማት የውስጥ ችግር ላይ እንዲያተ ኩር ማሳሰባቸው አልቀረም ።

የሕዝብ እምነት «መናጋት»

በ1960ዎቹ ማክተሚያ ላይ በግልጽ መታ የት እንደጀመረው የአሜሪካ « የበላይነት ያለው» የአኗኗር ዘይቤ እየተባለ ይናፈስ የነ በረውም ስብከት ከሥሩ ተናጋ ። በአሜ ሪካ ሥራ አጥ በዛ፣ ወንጀል ተበራከተ፣ የብዙ አሜሪካውያን የኑሮ ሁኔታ እያሽቆለቆለ መጣ ። በአጠቃላይ የማኅበራዊ ሆነ የኢኮኖ ሚ ሁኔታ ለጭቁን አሜሪካውያን እጅግ አስ ቸጋሪ ሆነ። ሰፊው ሕዝብ ለልዩ ልዩ ችግሮ ች ተዳረገ ። ይህም በመሆኑ የአሜሪካ የአኗ ኗር ዘይቤ ሌሎች አገሮች እንዲከተሉት የሚ ጋብዝ ሳይሆን በራሱም አገር ተቀባይነት እ ያጣ መሄድ ጀመረ። ይህ «የላቀ» ነው እየተ ባለ የሚነገርለት የኑሮ ዘዴ ደግሞ የአሜሪካ ገዥዎች በሌላው አገር ጣልቃ ሲገቡ «የኛን መልካም የአኗኗር ዘዴ ለማስተዋወቅ ነው» የሚለውን ሰበባቸውን ያዳከመባቸው መሆኑ ግልጽ እየሆነ መጣ ፤ የእምነት ክስረት ደረሰ ።[37] አንድ የተስፋፊነት ፖሊሲ መሸ ፈኛ መነመነ ማለት ነው ። ስለአሜሪካ የፖ ለቲካና ማኅበራዊ ችግሮች ጠለቅ ያለ ዕው ቀት አለው የሚባለው ፕሮፌሰር አንድሪው ሃከር <u>የአሜሪካን ዘመን ማለቂ</u> በሚል ርዕስ ይህንን በአሜሪካ ፖሊሲ ላይ የደ ረሰ የእምነት ክስረት በሚመለከት ሲጽፍ « ብዙ አሜሪካውያን እድለኛ በመሆና ቸው ካፒታሊዝምን ፣ ክርስቲያንነትን ወይንም የአሜሪካ ሕገ መንግሥትን በዓለም ማሠራጨት አለብን ብለው አያምኑም ። እንዲያውም በአሁኑ ጊዜ የሀገራችን የኑሮ ዓይነት በሌላው አገር የሚመኙት እንዳይ ደለ ብዙ ሰዎች በእርግጥ እየተገነዘቡ ነው» ብሎ ነበር ።[38]

የአንዳንድ የሞኖፖል ቡድኖች የቀዝ ቃዛው ጦርነት ፖሊሲን አለመደገፍ

የአሜሪካ የውስጥ ኢኮኖሚ መናጋት ለብዙ የአሜሪካ የገዥ መደብ አባላት የመስፋፋት ዓላማና የሀገሪቷን አቅም ከማጋነን እንዲ ቆጠቡ ፣ በዓለም ዙሪያ ለነፃነት እንቅስቃሴ ዎች ማፈኛ ከሚረጩት ሀብት እንዲታገ ሱና የአሜሪካንን የውስጥ ችግር እንዲፈቱ ያስገደዳቸው ይመስላል ። ይህን አስመልክቶ የአይ.ቢ.ኤም ኩባንያ ፕሬዚዳንት ቶማስ ጂ. ዋትሰን ለአሜሪካ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ሰኔ 3 ፣ 1970 ባደረገው ንግግር እንደ ሚከተለው ብሎ ነበር ፣

ከጥቂት ዓመታት በፊት ብዙ ሰዎች የአ ሚሪካ የራሷ የውስጥ ኢኮኖሚ ብዝሆም ሳያ ናጋ በማናቸውም የዓለም አካባቢዎች የሚነሱ የኮሚኒስት እንቅስቃሴዎችን ለመ

Digitized by Google

ገደብና ፀረ—ኮሚኒስት እንቅስቃሴዎችን
ለመደገፍ ትችላለች ብለው ያስቡ ነበር ።
ይህ አስተሳሰብ ትክክል አለመሆኑ ግልጽ
ነው። በአስተሳሰቡ የንግድ ሰዎች (ካፒ
ታሊስቶችን ማለቱ ነው) ከፍተኛ ጥን
ቃቄ እያደረጉና ስለወደፊቱም እያሰቡበት
ነው።[39]

የሚዳስ ኢንተርናሽናል ኮርፖሬሽን ፕሬ
ዚዳንት ጐርደን ቤርማንም በ1970 ይህንኑ
ጉዳይ በማስመልከት ሲናገር ፣ «በእጃችን
ያለው ውድ ነገር ሁሉ አደጋ ላይ ወድቆ
እያለ ሊደርስ ይችላል ለሚባል አደጋ ያለ
ንን ንብረት ከትክክለኛ አጠቃቀም ውጪ
ማጥፋትና ትርፍ ለሌለው ነገር ሀብትን ማባ
ከን የለብንም »[40] ብሎ ነበር ። በተጨማ
ሪም በአንድ ወቅት የአሜሪካ ባንክ ሊቀመን
በር የነበረው ሊዮ ቢ. ሉንድቦርድ የአሜ
ሪካ ገዥዎች የማይጠቅማቸውን ጦርነት
ከማካሄድ እንዲቆጠቡና ለመስፋፋት ከፈ
ለጉ በኢኮኖሚው መስክ አጥቂ መሆን እን
ዳለባቸው በማስመልከት ሲናገር ፣ «ለማት
ረፍ ከፈለጋችሁ ኃይላችሁን ለጥቅመቢስ
ጦርነት አታባክኑ፤ ከሁለተኛው የዓለም ጦር
ነት ወዲህ የጃፓንና የጀርመንን (ምዕራብ
ጀርመንን—ፀሐፊ) ምሣሌነት ተከትላችሁ
ኢኮኖሚያዊ አጥቂ ሁኑ »[41] በማለት አሳ
ስቦ ነበር ። የጃፓንና የምዕራብ ጀርመን ሞና
ፖሊስቶች የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ካደ
ረሰባቸው ጥፋት በአጭር ጊዜ አገግመውና
በኢኮኖሚ ተጠናክረው በልዩ ልዩ የኢኮ
ኖሚ መስኮች የአሜሪካ ተወዳዳሪ ሆነው
በመገኘታቸው የአሜሪካ ሞኖፖሊስቶች
ለምን እንደነሱ አያደርጉም ባይ ነው ሉን
ድቦርድ ። በርግጥም ይህ አቋም የብዙ የአ
ሜሪካ ሞኖፖሊስቶች አቋም እንደነበር
ሪቻርድ ጂ ባርኔት የተባለ አሜሪካዊ ምሁር
«ገበያን ለማስፋፋትና ጥሬ ሀብትን ለማግ
ኘት ከዕለት ወደ ዕለት እነሱ (ሀብታሞች)
ከሚሊታሪ ኃይል ይልቅ የኢኮኖሚ ኃይል
በጣም የበለጠ ተግባራዊ መሣሪያ መሆኑን
እየተገነዘቡ ነው»[42] በማለት ጽፏል ።

የሪቻርድ ጂ. ባርኔት አቋም ለአሜሪካ
ኢምፔሪያሊስቶች ያዋጣል ወይስ አያዋ
ጣም የሚለውን አንስቶ መዘርዘሩ የዚህ
ጽሑፍ ዓላማ አይደለም ። እዚህ ላይ ዋናው
ነጥብ አንዳንድ የአሜሪካ የሞኖፖል ቡር
ዧዎች በአሜሪካ የገዥው መደብ ጋሻ
ጃግሬዎች የሆኑት የመንግሥት ባለሥል
ጣናት በሚከተሉት የጣልቃ ገብነት ፖሊሲ
ምክንያት የኤኮኖሚ ጥቅማቸው ስለተነካ
ባቸው ከተወዳዳሪዎቻቸው ሌሎች የኢም
ፔሪያሊስት አገሮች (በተለይም ከምዕራብ
ጀርመንና ከጃፓን) ለመወዳደር የኢኮኖሚ
ኃይላቸውን ስለቀነሰባቸው በግልፅ መቃ
ወም መጀመራቸው ነው ። ይህም ተቃው
ሟቸው አሜሪካ በወቅቱ ይከተል የነበረ
ውን የጠብ አጫሪነት የውጭ ፖሊሲ እን
ዲቀንስና ከሶሻሊስት አገሮች ጋር ተቻችሎ
በሰላም አብሮ እንዲኖር አስተዋጽኦ ሊያደ
ርግ መቻሉ ግልጽ ነው ። በርግጥም
ይህ አቋም ቀስ በቀስ በአሜሪካ ዲፕሎማቶ
ችና የፖለቲካ መሪዎች መንፀባረቁ አል
ቀረም ።

የቀዝቃዛው ጦርነት ፖሊሲ ተቃዋሚ ዎች አመራር መያዛቸው

የአሜሪካ ታዋቂ ዲፕሎማት ጆርጅ ኬናን
በ1964 ባሳተመው መጽሐፍ ውስጥ «የም
ዕራቡ ዓለም ከኮሚኒስቱ ዓለም ጋር ለሚና
ረው ግንኙነት በሰላም አብሮ የመኖርን
ጥያቄ ከመቀበል በስተቀር ሌላ አማራጭ
የለውም» ብሎ ነበር ።[43] ይህ ሰው ኮሚኒ
ዝምን ለመዋጋት የቀዝቃዛው ጦርነትን
ፖሊሲ ከነደፉት የአሜሪካ የፖለቲካ ሰዎች
አንዱ እንደነበረ እላይ ተጠቅሷል። ከሁለተ
ኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ ለመጀመሪያ
ጊዜ ከሶሻሊስት አገሮች ጋር አሜሪካ በሰ
ላም አብሮ መኖር አለባት የሚለውን መርህ
ኦፊሴላዊ በሆነ መንገድ የተቀበለና በግል
ጽም ያብራራው በ1960ዎቹ የመጀመሪያ
ዓመታት ላይ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበ
ረው ኬኔዲ ነው።

ኬኔዲ ሰኔ 10 ፣ 1963 ባደረገው ንግግር
የዘመኑ ቴክኖሎጂ ባፈራቸው የጦር መሣ
ሪያዎች ጦርነት ማካሄድ ትልቅ ጥፋት የሚ

Digitized by Google

ያስከትል መሆኑን ፣ ለብዙ ሰውና ለሚመጣውም ትውልድ ጭምር የኒኩሌር ጦርነት ጉጂ መሆኑን አስገነዘበ ።[44] ኬኔዲ የዓለም ጦርነት ቢነሣ ሶቭየት ኅብረትና አሜሪካ ከማናቸውም አገሮች የበለጠ ጦርነቱ ጥፋት የሚደርስባቸው መሆኑን ሲያስገነዝብ ፣ «የገነባነው ሁሉ ፣ የለፋንበት ሁሉ፣ በመጀመሪያዎቹ 24ሰዓቶች ይወድማሉ»ብሏል።[45] ይህ ብቻ አይደለም ፣ ኬኔዲ ቀዝቃዛው ጦርነት ሶቭየት ኅብረትን ብቻ ሳይሆን አሜሪካንም ጭምር የሚጎዳ መሆኑን በማስመልከት ሲናገር ፤—

> ለብዙ አገሮች—ለዚች አገር ወዳጆችም ጭምር—ጫናና አደጋዎችን ባስከተለው በቀዝቃዛው ጦርነት ጊዜ እንኳንየኛ ሁለቱ አገሮች (አሜሪካና ሶቭዩት ኅብረት—ጸሐፊው) እጅግ ከፍተኛውን ችግር እየተቀበሉ ነው ። ምክንያቱም ሁለታችንም መሀይምነትን፣ ድህነትንና በሽታን ለመዋጋት ብናውለው የሚሻለውን ከፍተኛ ገንዘብ ለጦር መሣሪያ እናውላለን» [46] ብሎ ነበር ።

ኬኔዲ እነኝህንና የመሳሰሉትን ችግሮች በመጥቀስ የአሜሪካ ጥቅም ጭምር በቀዝቃዛው ጦርነት ፣ በመሣሪያ እሽቅድድም የተጎዳች መሆኑን ዘርዝሮ «በማይፈለጉ ሰዎች ላይ የኛን ሥርዓት ልንጭንባቸው አንፈልግም፤ በዓለም ላይ ካለው ከማንኛውም አገር ጋር በሰላም ለመወዳደር ፈቃደኛና የምንችልም ነን» በማለት ተናግሯል ። [47]

በተጨማሪም ኬኔዲ «በእስያ ፣ በአፍሪካና በላቲን አሜሪካ የሚካሄዱት አብዮታዊ ንቅናቄዎች» የመስከብ ማደፋፈር ነው «የሚለውን ተራና ተጨባጭነት የሌለውን አተረጓጐም ለማሻሻል ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ የመጀመሪያው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት» እንደነበርም ይነገራል ።[48]

እዚህ ላይ መታወስ ካለበት ነገር አንዱ ኬኔዲ ሙሉ ለሙሉ ለሰላም የቆመና የኢምፔሪያሊዝም ጥቅም አራማጅ አልነበረም ለማለት አይደለም ። በመሠረቱ ኬኔዲ የአሜሪካ ሞኖፖሊስቶች ጥቅም አስከባሪ እንደነበር አጠራጣሪ አይደለም ። ነገር ግን ከእዚህ አቋሙ ልንገነዘበው የሚገባው ይህ ሰው በአመራሩ ከሞላ ጎደል ጊዜው የሚጠይቀውን ያሟላ ፣ አሜሪካ የምትከተለው ፖሊሲ ቢያንስ ለአሜሪካ መንግሥትና ይህ መንግሥት ለቆመላቸው ሞኖፖሊስቶች ለራሳቸው እንኳን ጉጂ ሊሆን መቻሉን መገንዘቡ ነበር ። ይሁንና ከሶሻሊስት አገሮች ጋር በሰላም አብሮ የመኖርና የዴታንት ፖሊሲን በመቀበል የአሜሪካ መንግሥትን ወክሉ ከሶቭዬት ኅብረት ጋር ስምምነት የተዋዋለው በ1969 የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆኖ በትረ ሥልጣን የያዘው ሪቻርድ ኒክሰን ነበር ።

የኒክሰን አስተዳደርና ከሶሻሊስት አገሮች ጋር በሰላም አብሮ የመኖር ፖሊሲ

የኒክሰን አስተዳደር ሲጀመር የቀዝቃዛው ጦርነት ፖሊሲን የሚቃወሙ የአሜሪካ የሞኖፖል ቡድኖች በሀገሪቷ የውጪ ፖሊሲ ቅየሳ የበላይነትን ያዙ ። ኒክሰን በ 1969 የአሜሪካ ፕሬዚዳንት እንደሆነ «ከሶቭዬት ኅብረትና ከሌሎች ሶሻሊስት አገሮች ጋር አሜሪካ የሚኖራት ግንኙነት በድርድር፣ በውይይት ላይ የተመሠረተ እንዲሆንና የግጭት ወቅት ማብቃት እንዳለበት»አሳሰበ ። [49] ኒክሰን የኒኩሌር የጦር መሣሪያ ባለቤት ከሆነችው ከሶቭዬት ኅብረት ጋር ጦርነት ማካሄድ በአሜሪካ መንግሥት ዘንድ ጨርሶ ጉጂ መሆኑን የተገነዘበ ይመስላል ።

የኒክሰን አስተዳደር በ1969 መጨረሻ አካባቢ የጦር መሣሪያን በሚመለከት ከሶቭዬት ኅብረት ጋር ውይይት ጀመረ ። የኒክሰን የሰላም እርምጃ የአሜሪካ መሪዎች በሰላም አብሮ መኖርን በበለጠ የተገነዘቡ መሆኑን የሚገልጽና በብዙ ሰላም ወዳድ ሕዝቦችም ዘንድ የተደገፈ ነበር ። የቀዝቃዛው ጦርነት ቀስቃሾችና አራማጆች ከነበሩት አንዱ የነበረው ኒክሰን ከግንቦት 22 እስከ 30 ፣ 1973 በመስኮብ በመገኘት ከሶቭዬት

Digitized by Google

ኅብረት መሪዎች ጋር ውይይት አደረገ ። ውይይቱ ሁለት መሠረታዊ ስምምነቶችን አስገኘ ። አንደኛ ፥ በሶቭዬት ኅብረትና በአሜሪካ መካከል የሚኖረው ግንኙነት የሚመሠረትበት ስምምነት በግልጽ ተዘረዘረ። ሁለተኛ ፥ የጦር መሣሪያን ለመግታት ስምምነትና በሁለቱም ወገኖች በኩል ጉዳዩን የሚከታተሉ ጊዜያዊ ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ተስማሙ ።[50]

የኒክሰንን የሰላም ፖሊሲ የሚቃወሙ የአሜሪካ የሞኖፖል ቡድኖችና ባለሥልጣኖች ባይጠፉም ደጋፊዎችም ነበሩት ። ከኒክሰን ፖሊሲ ደጋፊዎች መካከል በመጀመሪያ የብሔራዊ ደኅንነትን በሚመለከት የኒክሰን አማካሪ የነበረውና በ1973 መጨረሻ ወራት አካባቢ ጀምር የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረው ሄነሪ ኪሲንጀር፥ ኤድዋርድ ኬኔዲና የሕግ መወሰኛው ምክር ቤት አባል የነበረው ዊሊያም ፉልብራይት ይገኙበታል ። ኪሲንጀር የውጥረት ቅነሳ ፖሊሲ ስር ሰዶ በነበረበት ወቅት ፥ በ1975 በአውሮፓ ለአሜሪካ አምባሳደሮች ባደረገው ንግግር «ሶቭዬት ኅብረት እንደታላቅ ኃይል እየሆነች በመምጣቷ በጋራ አብር መኖር ተፈርዶብናል ። ውጥረት ቅነሳ ... ማንም ይሆን ማንም ፥ የትኛውንም የአሜሪካንን ፕሬዚዳንት የገጠመው ጉዳይ ነው » ብሏል ።[51] በአጠቃላይ የኒክሰን አመራር ከሶሻሊስት አገሮች ጋር በሰላም አብር ወደ መኖር ፖሊሲ በመሸጋገር በዩናይትድ ስቴትስና በሶቭዬት ኅብረት መንግሥታት መካከል የነበረው የቀዝቃዛ ጦርነት ፖሊሲ በውጥረት ቅነሳ ፖሊሲ (በዴታንት) ተተካ።

የአርነት እንቅስቃሴ ትግል ድል አድራጊነት

ኒክሰን የአሜሪካ የውጭ ፖሊሲን የለወጠው አሜሪካ ከሶሻሊስት አገሮች ጋር የነበራትን ግንኙነት በሚመለከት ብቻ አልነበረም ፤ የኋላቀር አገሮችንም በሚመለከት የውጭ ፖሊሲ ለውጥ አድርጐ ነበር ። ቀደም ብሉ እንደተጠቀሰው ለለውጡ ዋና ምክንያት በዓለም የፖለቲካ መድረክ የኃይል አሰላለፍ ለኢምፔሪያሊስቶች የጠብ አጫሪነትና የአምባገነንነት ፖሊሲ አመቺ ባለመሆኑ ነው ። የሶሻሊስት አገሮች ድል እያደረጉ በልዩ ልዩ መስኮች ለምሳሌ በኢኮኖሚ ፥ በፖለቲካ፥በሚሊታሪና በርዕዮተዓለም በመጠናከራቸው ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር ለመላቀቅ ለሚታገሉ ኃይሎች የሚሰጡት የማቴሪያል እርዳታና የትግል አርአያነታቸው ጭቁን ሕዝቦች ለአርነት ፥ አገሮች ለነፃነት ለሚያደርጉት ትግል ከፍተኛ ግፊት ሰጠሙ ። ይህን ሕዝባዊ ትግል ኢምፔሪያሊስቶች ሊቋቋሙት ስላልቻሉ እንደትግሉ ደረጃ የብዝበዛ ዘዴያቸውን ለመለወጥ፥የነፃነት ትግሉ አየል ባለባቸው አገሮች ደግሞ ጭራሹን ጓዛቸውን ጠቅልለው መውጣት ግድ ሆነባቸው። በአጠቃላይ በ1960ዎቹ ዓመታት መጨረሻ ላይ የጣልቃ ገብነትና የጦረኝነት ፖሊሲ ጨርሶ የማያዋጣ መሆኑ ለብዙ ለአሜሪካና የምዕራብ አውሮፓ ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት መሪዎች ግልጽ እየሆነ መጣ ።

የምዕራብ አውሮፓ ኢምፔሪያሊስቶች የነፃነት ትግል ቋያ ከተቀጣጠለበት «ከሶስተኛው ዓለም» ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንደ ራሳቸው ጥንካሬና እንደገጠማቸው ሕዝባዊ የትግል ደረጃ ፖሊሲያቸውን እያስተካከሉ ብዝበዛቸውን መቀጠል ያለባቸው መሆኑን ከአሜሪካ መሪዎች ቀደም ብለው የተገነዘቡ ይመስላል ። በዚህ አንፃር የነሱ ማፈግፈግ ወይንም መዳከም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የአሜሪካ መዳከም ነውና አሜሪካንን እንዳሳሰባት ይገመታል ። በተለይ የእንግሊዝና የፈረንሣይ መሪዎች «የሶስተኛውን ዓለም» ሕዝባዊ ትግል በጠመንጃ አፈሙዝ በግንባር በመግጠም ሊወጡት የማይችሉት ተግባር መሆኑን አምነዋል ። ጠቅላይ ሚኒስትር ሃሮልድ ማክሚላን የካቲት 3፥ 1960 አድርጐት በነበረው ንግግር በአፍሪካ ስለነበረው ብሔራዊ ንቃትና ስለትግሉ ያለውን ፍራቻ በሚመለከት «በአህጉሩ (በአፍሪካ) የለውጥ ንፋስ እየነፈሰ ነው— እኛ

Digitized by Google

ወደድንም ጠላንም ይህ የብሔራዊ ንቃት እድገት ፖለቲካዊ ሃቅ ነው ። ሁላችንም እንደሃቅ መቀበል አለብን ። ብሔራዊ ፖሊሲያችን ሊቀበለው ይገባል። ... ይህን ማድረግ ካልቻልን ግን በምስራቅና በምዕራብ (በሶሻሊዝምና በካፒታሊዝም) መካከል ያለውን አስተማማኝ ያልሆነ ሚዛን አደጋ ላይ እንጥለዋለን ብዬ ከልብ አምናለሁ » [52] ብሎ ነበር ። ፕሬዚዳንት ደጐልም ፈረንሣይ በአልጀሪያ ሕዝብ የነፃነት ትግል በደረሰባት የፖለቲካና የሚሊታሪ ቀውስ ውስጥ ተዘፍቃ በነበረችበት ጊዜ የፈረንሣይ ባለሥልጣናት የቅኝ ግዛት አስተሳሰባቸውን እንዲለውጡና ከአልጀሪያ ጋር ያላቸው ግንኙነት በአዲስ መልክ እንዲቀጥል እንዲያደርጉ በማስገንዘብ ታህሣሥ 9 ፣ 1960 ባደረጉት ንግግር ላይ

ፈረንሣይ ከአልጀሪያ ጋር ያላት ግንኙነት መቀጠል አለበት ፤ ግን ይህ ግንኙነት ትናንት ይካሄድበት በነበረበት ሁኔታ መካሄድ እንደማይቻል ግልጽ ነው። ለመጹና ከሱ ጋር የተገናኙት ነገሮች ሁሉ በአዲስ ዓለም ውስጥ፣ እኔ ወጣት በነበርኩ ጊዜ ከማውቀው ዓይነት ዓለም የተለየ ዓለም ውስጥ እየተካሄዱ ነው ። ዓለምን ከአድማስ አድማስ በማጥለቅለቅ ላይ ያለ የነፃ መውጣት እንቅስቃሴ እውን ነው ፤ [53]

ብለው እንደ ነበር የሚታወስ ነው ። የፈረንሣይ መሪዎች የፈሩትን የአልጀሪያን ሕዝባዊ ትግል ድል አድራጊነት በ1961 ተቀብለው አልጀሪያን ለቀው ለመውጣት ተገደዱ ።

የአውሮፓ ኢምፔሪያሊስቶች ለብሔራዊ ነፃነት በሚካሄዱ ትግሎች መሸነፍና ማፈግፈግ ለአሜሪካ መሪዎች መዳከምን፣ ለነፃነት እንቅስቃሴዎችና ለሶሻሊዝም መጠናከርን አስከተለ ። በአጠቃላይ ሲታይ የዓለም ፖለቲካ የኃይል ሚዛን ለአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች አመች አልሆነም ። ሮበርት ኬኔዲ እስያንና አውሮፓን ጐብኝቶ ያገኘውን አስተያየት አቀነባብሮ በ1962 ባሳተመው መጽሐፉ ውስጥ የካፒታሊስት ሥርዓት ብዙ ሕዝብ እየጠላው መሆኑ ሲገለጽ ፣ ካፒታሊዝም «ለምስራቁ ዓለም ጠያፍ ቃል ሆኗል» ብሏል ። [54] ይህም በካፒታሊዝም ላይ የሚሰነዘር ጥላቻ የሚገለጸው በስነልቡናዊ ጥላቻ ፣ በትጥቅ ፣ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ትግል ወዘተ ... ከፍ ሲልም በአብዮትና በሕዝባዊ አመጽ መልክ ነው። ግንቦት 9 ፣1966 ሮበርት ኬኔዲ አሜሪካ በላቲን አሜሪካ አገሮች የገጠማትን ሕዝባዊ ትግል በሚመለከት የነበረውን ፍራቻ ሲገልጽ ፣ «ለውጥ ይኖራል ፤ አብዮት እየመጣ ነው ፤ ይህም አብዮት ብልህ ከሆንን ሰላማዊ የሚሆን ፣ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ካደረግን ለዘብተኛ የሚሆን ፣ እድለኛ ከሆንን የሚሳካ ግን ወደድንም ጠላንም የሚመጣ አብዮት ነው» [55] ብሎ ነበር ። ይህ ወቅት አሜሪካ በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የሚበዘብዙት የላቲን አሜሪካ አገሮች የሕዝባዊ ትግል ሥር እየሰደደ የነበረበት ወቅት ነበር ።

ታዲያ የአሜሪካ መሪዎች ትግሉን ለማክሸፍ የተጠቀሙበት መሣሪያ መጠነኛ የጥገና ለውጥ ማምጣት ነበር ። የአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ደጋፊና በወቅቱ የቬንዙዌላ ፕሬዚዳንት የነበረው እንዳለው «ሀብታሞችን ለማዳን ድሆችን መርዳት አለብን»[56] የሚለው አቀራረብ የጊዜው የአሜሪካ መንግሥት የውጭ ፖሊሲ አንዱ መመሪያ ነበር ማለት ይቻላል ። እርዳታው ነፃነቱን ለሕዝብ ለማጐናፀፍ ሳይሆን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ወጥመድ ውስጥ ለማቆየት ማዘናጊያ ነበር ።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ለመገንዘብ እንደሚቻለው በ1950ዎቹ ማክተሚያ እና በ1960ዎቹ ውስጥ አንዳንድ የአሜሪካና የምዕራብ አውሮፓ መንግሥታት የውጭ ፖሊሲ ኃላፊዎች በጠመንጃ አፈሙዝ የነፃነት እንቅስቃሴን እስከ መጨረሻው ማፈን የማይችል መሆኑን ተገንዝበ

Digitized by Google

ውት እንደነበር ነው ። ብዝበዛቸው መል
ኩን ቀይሮ እንዲቀጥል ከፈለጉ የተወሰነ
ደረጃም ቢሆን ማፈግፈግ እንዳለባቸው ግ
ልጽ ነበር ። የምዕራብ አውሮፓ ኢምፔሪያ
ሊስቶች እያፈገፈጉና አዲስ ዘዴ እየፈለጉ
ሳለ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች ግትር
ብለው የፖሊሲ ለውጥ ሳያደርጉ ቢቀጥሉ
ደግሞ እንደማያዋጣቸው ተገነዘቡት። ስለ
ሆነም እንደነ እንግሊዝና ፈረንሣይ መሪ
ዎች ሁሉ «ችግሩ» የገባቸው የአሜሪካ መሪ
ዎች ይህን የማፈግፈግ ዘዴ በመንግሥታዊ
ፖሊሲ ደረጃ መቀበል ነበረባቸው ። ይህ
ማፈግፈግ በኒክሰን አስተዳደር ጊዜ በተግ
ባር መታየት ጀመረ ።

የኒክሰን ፖሊሲና የአርነት ንቅናቄዎች

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች የብሔራዊ አር
ነት ትግልን በጠመንጃ ለመቋቋም ምን
ያህል እንደሚያዳግት በበለጠ የተከሰተላ
ቸው በቬትናም ባደረጉት ጦርነት ነበር ።
የፈረንሣይ ኢምፔሪያሊዝም በቬትናም
ሰፊ ሕዝብ ቆራጥ የአርነት ትግል ድል ተ
መቶ ከቬትናም እንዲወጣ ሲገደድ ፀረ ኢም
ፔሪያሊስት ትግሉ ግቡን እንዳይመታ ለማ
ገድ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በቬትናም
የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገባ ።

የቬትናምን ሕዝብ የነፃነት ትግል ማዕ
በል ለመግታት የአሜሪካ ወታደሮች በቬት
ናም ሰፊ ሕዝብ ላይ የመርዝ ጋዝ ፣ የቦንብ
ውርጅብኝና ይህ ነው የማይባል ኢሰብአዊ
ድርጊቶችን ፈጸሙ ። ከዚህም በተጨማሪ
ቬትናሞችን እርስ በርስ ለማፋጀት ሕዝባዊ
ትግሉን ለማኮላሸት ሞከሩ ። ይህ ሙከራ
ትግሉን ሊያከሽፈው አልቻለም ። እንዲያው
ም ጦርነቱ ወደ ሌሎች አገሮች ተዛምቶ በ19
70ና በ1971 የአሜሪካ ወታደሮች ካምቦዲያን
(ካምፑቺያን) እና ላኦስን በተከታታይ ወረሩ።
በ1972 የአሜሪካ የአየር ኃይል በሰሜን ቬት
ናም ላይ የቦንብ ድብደባውን አስፋፋው ።
ያም ሆኖ የቬትናምን ሕዝብ ቆራጥ የነፃነት
ትግል ለማፈን የሚችል ኃይል ባለመኖሩ
የአሜካሪን ኢምፔሪያሊዝም የውርደት ግ
ቁን ተከናንቦ ቬትናምን ለቆ ለመውጣት
ተገደደ ። ይህ የሆነው በኒክሰን አስተዳደር
ወቅት ሲሆን ፣ በሌላ አካባቢ የቬትናም ዓይ
ነት ሕዝባዊ ትግል ቢነሳ ፣ ይኸን ዓይነት
ትግል ለማፈን የሚያስችል የኒክሰን መመ
ሪያ ተብሎ የሚጠራ ፖሊሲ ተቀይሶ
ነበር ።

የኒክሰን መመሪያ የተወጠነው በ1969
ነበር ። በአሜሪካ በፕሪንስተን ዩኒቨርሲቲ
ዓለም አቀፍ ግንኙነት ፕሮፌሰር ፣ ሪቻርድ
ፎክ ይህን ማስመልከት እንደጻፈው በኒክ
ሰን መመሪያ መሠረት አሜሪካ በቬትናም
ውስጥ እንዳደረገችው የሕዝብ ትግል የገጠ
መውን አድሃሪ መንግሥት በቀጥታ የአሜ
ሪካንን ወታደሮች አሰልፎ በመዋጋት መር
ዳት ሳይሆን ፣ ከፍተኛ የወታደራዊ እርዳታ
በመስጠትና ሕዝባዊ ትግሉን ለመቋቋም
ከዚያው «ችግሩ» ካለበት አገር ወታደሮችን
ማሰልጠን እንዲሆን ፣ «አስፈላጊም ከሆነ
ከአሜሪካ አየር ኃይልና ባህር ኃይል» ተጨ
ማሪ ድጋፍ እንዲሰጥ ታቀደ ። በዚህ ግለ
ሰብ አስተያየት ይህ የኒክሰን ፖሊሲ «አሜ
ሪካ ከሦስተኛው ዓለም» ወዳጆቿ ጋር ሊኖ
ራት የሚችለው የግንኙነት መልክ ምን
መምሰል እንዳለበት የሚቀርጽ ነበር።[57]

የውጥረት ቅነሳ ፖሊሲ መስፈን

በ1970ዎቹ መግቢያ ላይ በአጠቃላይ
ሲታይ የአሜሪካ መሪዎች ከሶሻሊስት አገ
ሮች ጋር ባላቸው ግንኙነት ከቀዝቃዛው
ጦርነት ወደ የውጥረት ቅነሳ ፖሊሲ የተ
ሸጋገሩበትና ከኋላቀር አገሮች ጋር ባላቸው
ግንኙነት ከቀጥታ ጣልቃ ገብነት ከምላ
ጉደል የተቆጠቡበት ወቅት ነበር ። ይህም
በመሆኑ ቀደም ሲል በዓለም የፖለቲካ መ
ድረክ የበላይነትን ይዞ የነበረው የኢምፔ
ሪያሊስቶች የቀዝቃዛው ጦርነትና የቀጥታ
ጣልቃ ገብነት ፖሊሲ ሥፍራውን ለውጥ
ረት ቅነሳ ፖሊሲ ለቀቀ ።

የውጥረት ቅነሳ ፖሊሲ በኬኔዲና በኒክ
ሰን ቋርነት ፣ በእነሱ ለሰው ልጅ «አሳቢ

Digitized by Google

ነት» የመነጨ ማይሆን በመሠረቱ ከሶሻሊዝም የማይቀር እድገት ፣ በለሙት ካፒታሊስት አገሮች የፀረ ሞኖፖሊስቶች ትግልና ተቃውሞ ፣ ከአርነት ንቅናቄ ጥንካሬና ድል አድራጊነት ፣ ከዓለም የሰላም ኃይሎች ግፊትና ከመሳሰሉት የመነጨ ለመሆኑ ከላይ የቀረቡት መረጃዎች ይጠቁማሉ። ኢምፔሪያሊስቶች አቅማቸው መቀነሱና እየተዳከሙ መምጣታቸው ሐቅ በመሆኑ «የምንናርበትን ዘዴ እንፈልግ» በማለት ነው የፖሊሲያቸውን መልክ የለወጡት ።

በየካቲት ወር 1972 ፕሬዚዳንት ሪቻርድ ኒክሰን ለአሜሪካ ብሔራዊ ሸንጎ ዘገባ ባቀረበበት ወቅት ፣ በጊዜው ስለታዩት ለውጦች ሲያትት ፣ ከነኝህ ለውጦች አንዱ ነገር «በስትራቴጂ ጥንካሬ አንፃር አከራካሪ የነበረው የአሜሪካ የበላይነት ማክተሙ» እንደሆነ ጠቁሟል ።[58] ከኒክሰን በፊት የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበረው ሊንደን ጆንሰን የዘመናችን የዓለም ሁኔታ ለአሜሪካ መሪዎች ወይም በአጠቃላይ ለአሜሪካ የገዥ መደብ አባላት የፈተና ጊዜና ለነሱ ጥቅም የማይበጅ ፣ በጣም አደገኛ መሆኑን በጥር ወር 1967 ለሀገሪቱ ብሔራዊ ሸንጎ ባደረገው ንግግር ሲገልጽ ፣ «የፈተና ጊዜ ነው–አዎ። የሽግግር ጊዜም ነው ። ሽግግሩም አንዳንዴ አዝጋሚ ፣ አንዳንዴ ተፈላጊ ያልሆነ፣ በአብዛኛው በጣም አሰቃይና ሁልጊዜ በጣም አደገኛ ነው »[59] ብሎ ነበር ። በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የመረጃና የምርምር ክፍል ዲሬክተር ቶማስ ኤል ሁግሄስ በጥር ወር 1967 «የላዩ ወደታች በሆነበት ዓለም ፖሊሲ ማውጣት» በሚል ርዕስ በጻፈው ጽሑፉ የዓለም አቀፍ ሁኔታ በአጠቃላይ የአሜሪካ መሪዎች የፈለጉትን የውጭ ፖሊሲ ለማራመድ እንዳላስቻላቸውና ወደማይፈልጉበት አቅጣጫ እየገፉቸው መሆኑን ሲገልጽ ፣ « የምንናረው የማይሆኑ አግራሞችን ያለማቋረጥ በሚያቀርብልን ዘመን ነው ። እነኝህ አግራሞች እንዳቸውም ልንሄድበት ወደ ምንፈልግበት አቅጣጫ የሚወስዱን አይመስሉም » ብሏል ።[60]

በአጠቃላይ እስከ አሁን ከቀረቡት ነጥቦች ለመገንዘብ እንደሚቻለው 1960ዎቹና በ1970ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት ላይ በዓለም አቀፍ የፖለቲካ መድረክ የታዩት ለውጦች የአሜሪካ የቀዝቃዛው ጦርነት ፖሊሲ መለወጥን የግድ አስፈላጊ አደረጉት። ከነዚህም ለውጦች የሶሻሊስት አገሮች በኢኮኖሚ ፣ በፖለቲካና በወታደራዊ አቅማቸው መጠናከር ፣ የተቀነባበረ የሰላም ፖሊሲ መከተልና ከካፒታሊስት አገሮች ጋር በሰላም አብሮ ለመኖር ዝግጁ መሆናቸውን ያለማቋረጥ መግለፃቸው ፣ የነፃነት እንቅስቃሴዎች በየቦታው ነፃነታቸውን መጎናፀፋቸው ፣ በአንዳንድ ቦታም ድል በማድረግና የሶሻሊስት የእድገት ጉዳናን መከተል ወዘተ ... የአሜሪካ አጋሮች የሆኑ ዋና ዋና የካፒታሊስት አገሮች ለምሳሌ ምዕራብ ጀርመን ፣ ፈረንሣይ ፣ ጣሊያንና እንግሊዝ የቀዝቃዛው ጦርነት ፖሊሲን በመተው ከሶሻሊስት አገሮች ጋር ጤናማና መልካም ግንኙነት መመሥረት ፣ የአሜሪካ ብሔራዊ ኢኮኖሚ የአሜሪካ መንግሥት በሚያራምደው የመሣሪያ እሽቅድምድም ምክንያት ተደጋጋሚ ቀውስ ውስጥ መግባት ፣ የአሜሪካ ሕዝብ የአሜሪካ መንግሥት የሚከተለውን የጦርነት ፖሊሲ መቃወም ፣ በዚሁ ወቅት አገሪቷ መጠነኛ የፖሊሲ ለውጥ ማድረግ ያለባት መሆኑን የሚያምኑ የአንዳንድ የሞኖፖል ቡድኖችና የፖለቲካ ወኪሎቻቸው በአሜሪካ መንግሥት የውጭ ፖሊሲ አቀያየስ የበላይነት መያዛቸው ይገኙበታል ። በነኝህ ለውጦች የተነሣ የአሜሪካ መሪዎች እናጠፋቸዋለን ካሏቸው ከሶሻሊስት አገሮች ጋር መደራደርንና በሰላም አብሮ መኖርን የግድ ለመምረጥ ተገደዱ ። የነፃነት እንቅስቃሴዎችንም ለማፈን በየቦታው ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ሁልጊዜ የማያዋጣና ከፍተኛ ችግር ላይ ሊጥላቸው የሚችል መሆኑ ፣ ሽንፈትን ሊያስከትል የሚችል መሆኑን በተለይም ከቬትናም ጦርነት ተማሩ ። ስለሆነም የነፃነት እንቅስቃ

Digitized by Google

ፊዎችንም ለማፈን በአመዛኙ በጣልቃ ገብነት ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ለምሳሌ፣ የአካባቢ አድኃሪ መንግሥታትን ለወረራ በማደፋፈርና የውስጥ ፀረ አብዮት ኃይሎችን በመደገፍ ሕዝባዊ እንቅስቃሴን ለማፈን አዲስ የውጭ ፖሊሲ ዘዴ ተቀየሰ ። ይኸም በ1969 የወጣው የኒክሰን መመሪያ የሚባለው ፖሊሲ መሆኑ ነው ።

እነኚህ እርምጃዎች በአሜሪካ መሪዎች በመወሰዳቸው ምክንያት የቀዝቃዛው ጦርነትና የቀጥታ ጣልቃ ገብነት ፖሊሲ በሰላም አብሮ ለመኖር ፖሊሲ ቦታውን ሊለቅ ቻለ ። በሰላም አብሮ የመኖር ፖሊሲ ከ1917 የሩስያ አብዮት ጀምሮ የሶቭየት ኅብረት ፣ በኋላም በተለይም ከ1945 ጀምሮ የተመሠረቱት ሌሎች ሶሻሊስት መንግሥታትና በአሁኑ ጊዜ የዓለምአቀፍ ፖለቲካ በደረሰበት የእድገት ደረጃ ብዙ ሰላም ወዳድ መንግሥታት የሚከተሉት የውጭ ፖሊሲ መርህ ነው ። በሰላም አብሮ የመኖር መርህ «በሀገሮች መካከል ያለ አለመግባባት በኃይል ፣ በጦርነት ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ መፈታት አለበት» የሚል ዲሞክራሲያዊ ፖሊሲ ነው ። ይህን ፖሊሲ መቀበል ማለት በዓለም ውስጥ በቀዝቃዛው ጦርነት ምክንያት ሰፍና የነበረውን ውጥረት መቀነስ ፣ የተለያዩ የሶሲዮ ፖለቲካ ሥርዓት በሚከተሉ ሀገሮች መካከል ጠቃሚ በሆኑ በጋራ ጉዳዮች ላይ ለምሳሌ በኢኮኖሚ ፣ በንግድ፣ በሳይንስ፣ በቴክኒክና በባህል መስኮች መተባበር ማለት ነው ።

የውጥረት ቅነሳ ማለት በመንግሥታት መካከል በቀዝቃዛው ጦርነት ላይ ተመስርቶ የነበረ ግንኙነትን በማስወገድ ወደ «ተረጋጋ ግንኙነት መሸጋገር ማለት ነው ። » የውጥረት ቅነሳ ማለት በሀገሮች መካከል የሚነሱ «የሚያከራክሩ ነገሮችን በኃይልና በማስፈራራት ... ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ ፣ በጋራ ማስወገድ ማለት ነው ። የውጥረት ቅነሳ ማለት የተወሰነ መተማመንና የርስ በርስ ጥቅም ግንኙነት መፍጠር ማለት ነው ።»[61] ይህ በ1970ዎቹ መግቢያ ላይ የተጀመረው የውጥረት ቅነሳ ፖሊሲ በቅርቡ በሬጋን አስተዳደር ያገጠጠ የጦረኝነትና የጠባብ አሜሪካነት ፖሊሲ መደፍረስ እስከጀመረበት ጊዜ ድረስ የተለያዩ የሶሲዮ ፖለቲካ ሥርዓት በሚከተሉ አገሮች መካከል የጋራ ጥቅሞችን መሠረት በማድረግ መልካም ግንኙነትን በመፍጠር ለዓለም ሰላም መጠበቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. *N. Sivachyov and E. Yazkov,* History of USA Since World War I (*Moscow: Progress Publishers,* 1976), *p.* 211. *See also Harry Magdoff,* Imperialism: From the Colonial Age to the Present (*New York: Monthly Review Press,* 1978), *p.* 204.
2. *N. Sivachyov and E. Yazkov, pp.* 212-213. *See also A. Kirsanov,* USA and Western Europe (*Moscow: Progress Publishers,* 1975), *pp.* 26-27.
3. *N.Sivachyov and E. Yazkov,* p. 215.
4. *Ibid.,* 250.
5. U.S. Statutes at Large *Vol. LXI. part* 1 *pp.* 136-162 (1947) *Richard B. Morris, ed.,* Significant Documents In United States History *Vol. II,* 1983-1968 (*New York. Van Nostrand Reinhold Company,* 1969), *p.* 165. *See also N. Sivachyov and E. Yazkov, pp* 205-206.
6. *N. Sivachyov and E. Yazkov,* p. 209.
7. Ibid.
8. Ibid., *p.* 217.
9. Ibid.
10. Congressional Record *Vol. XCII* (*March* 12, 1947) *in Richard B. Morris,* pp. 159-161.

Digitized by Google

11. *See Roy C. Macridis, ed.,* Foreign *Policy In World Politics 5th rev. ed., (New Delhi: Prestice-Hall of India Private Limited,* 1979), pp. 305 351.

12. New York Times, *June* 6, 1947, *in Richard B. Morris,* p. 164.

13. 81st Congress, 1st Session. House Document No. 240 *in Richard B. Morris,* pp. 180-181.

14. *N. Sivachyo and E. Yazkov, p.* 240.

15. Ibid., *p.* 239.

16. Ibid., pp. 213-214.

17. Ibid., *p.* 219.

18. *See Robert Osgood, "The Revitaliztion of Cold War"* Foreign Affairs, *Vol.* 60, *No.* 3, 1981, *p.* 466.

19. *N. Sivachyov and E. Yazkov,* p. 219.

20. Ibid., *p.* 240.

21. The New York Times, *June* 28, 1950, *in Richard B. Morris,* pp. 185-186.

22. *N. Sivachyov and E. Yazkov, p.* 246.

23. Ibid., *p.* 247.

24. Ibid., *pp.* 249-250.

25. *Monthly Review, Editorial, Sept.* 1982.

26. *See N. Sivachyov and E. Yazkov, pp.* 250-251.

27. *The New York Tims,* July 22, 1955, in *Richard B. Morris, p.* 195.

28. *Robert Osgood, p.* 466.

29. *See* Declaration on Indo-China, U.S. State Dept. American Foreign Policy 1950-1955; Basic Documents. Publications 6446, 1 pp. 912-917, *in Richard B. Morris. N. Sivachyov and E. Yazkov,* p. 251.

30. U.S. Statute at Large, *Vol. LXXI,* pp.634-638 (1967) *in Richard B. Morris,* pp. 200 201.

31. Le Monde, April 21, 1960 quoted by D. Tomashevsky, *Lenin's Ideas and Modern International Relations* (Moscow: Progress Publishers, 1974), p. 184.

32. *The Time,* April 23, 1960 quoted by D. Tomashevsky, p. 184.

33. *Foreign Affairs,* Oct. 1966, pp. 54-55 quoted by O. Bykov, V. Razmerov and D. Tomashevsky, *Priorities of Soviet Foreign Policy Toda*). (Moscow: Progress Publishers, 1981), p. 100.

34. G. Arbatov, "A New Stage in Soviet American Relations", *Social Sciences* No. 1, 1974 p, 15.

35. See *.U.S. Statutes at Large,* Vol. LXXVIII, pp. 508-513 (1964) in *Richard B. Morris,* pp. 269-276.

36. *Report of the National Advisory Commission on Civil Disorders.* (New York, Bantam Books, Inc., 1968 in Richard B. Morris, pp. 307-315.

37. Georgi Arbatov, p. 15.

38. Andrew Hacker, *The End of American Era* (New York, 1970), pp. 220-221 qu°ted by Georgi Arbatov, p. 15.

39. *Congressional Record,* June 3, 1970 p. 8208 quoted by Georgi Arbatov, p. 16.

40. "Impact of the War in Southeast Asia on Us Economy" *Hearing Before the Commitee On Foreign Relations US Senate* 91*st Congress,* Washington, 1970, p. 86 quoted by Georgi Arbaov, p. 16.

41. *Ibid.*

42. Richard J. Barnet, *Roots of War* (New York) 1972, p. 227, quoted by G. Arbatov, p. 16.

43. George F. Kennan, *On Dealing with Communist World,* (New York, 1964) quoted by D. Tomeshevsky, pp. 184-185.

44. *United States Arms Control and Disarmament Agency,* Publication, No. 17, June 1963 in Richard B. Morris, p. 248.

45. *Ibid.,* p. 249.

46. *Ibid.,* pp. 249-250.

Digitized by Google

47. *Ibid.*, p. 250.

48. N. Sivachyov and E. Yazkov, p. 329.

49. *Ibid.*, p. 402.

50. *Ibid.*, pp. 411-412.

51. *International Herald Tribune*, April 12, 1976 as cited in International Affairs, No. 12, Dec. 1982, p. 86.

52. Quoted in Jack Woddis, *Introduction to Neo-Colonialism* (New York: International Publishers, 1976), pp. 52 53.

53. *Ibid.*, p. 53.

54. Robert F.Kennedy, *Just Friends and Brave Enemies* (New York: 1962, p. 118 quoted by Georgi Arbatov, *The War of Ideas In Contemporary International Relations* (Moscow: Progress Publishers, 1973), p. 112.

55. Jack Woddis, p. 106.

56. *Ibid.*, p. 105.

57. Richard Falk, "Iran and American Geopolitics in the Gulf", *Horn of Africa*, Vol. 2, No. 2, April/June 1979, p. 63.

58. *The Department of State Bulletin*, March 13, 1972 p. 314 quoted in D. Tomashevsky, p. 191.

59. *The Department of State Bulletin*, Jan. 30, 1967, p. 163, quoted in Tomashevsky pp. 12-13.

60. *Foreign Affairs*, Vol. 45, Jan. 1967, No. 2, p. 208 quoted by D. Tomashevsky, p. 14.

61. Leonid Brezhnev's answers to quesions by *"Times"* Magazine quoted in *New Times*, No. 4, Jan. 1920, p. 5.

Digitized by Google

የብሔራዊ ኢኮኖሚ ግንዛቤና የኋላቀር አገሮች ዕውነታ

ከበደ ገ/መድህን

ኢምፔሪያሊዝም የአምባገነንነትና የመስፋፋት ፖሊሲን በመከተል በታዳጊ አገሮች ላይ የሚፈጽመው ግፍ በቀላሉ የሚታይ አይደለም ። ከዚህም ተጽዕና ለመላቀቅ ብዙ ተራማጅ አገሮች የሶሻሊስት የዕድገት ጐዳና ቢመርጡም ቀደም ሲል የቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ተክሎ የሄደውን መርዝ ለመንቀል እጅግ ውስብስብና ከባድ ትግል ማካሄድ ይጠይቃቸዋል ።

በአሁኑ ወቅት ተራማጅ ታዳጊ አገሮች ለብሔራዊ ኢኮኖሚያቸው ነጻነት የሚያደርጉት ትግል እየተፋፋመ መጥቷል ።ይህም ኋላቀር የሆነውን የምርት ግንኙነት በማስወገድ ነጻ የሆነ ብሔራዊ ኢኮኖሚ በመገንባት ከኢኮኖሚ ጥገኝነት ለመላቀቅ ያላቸውን ፍላጐት ያንፀባርቃል ።

እንደሚታወቀው « ብሔራዊ ኢኮኖሚ» ኢኮኖሚ ከሚለው አጠቃላይ ጽንሰ ሐሳብ የመነጨ ነው ። ኢኮኖሚ የተባለው ቃልም የመጣው «oikonomos» ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም « oikos ».ማለት የቤት ውስጥ ንብረት አስተዳደር እና «nomos » ደግሞ ሕግ ማለት ነው ። በዚህ መሠረት ኦይኮኖሞስ (oik nomos) ማለት የቤት ውስጥ ንብረት የማስተዳደር ሕግ ማለት ነው ።

ኢኮኖሚን ከሰዎች ማህበራዊ ኑሮ ውጪ ማሰብ አይቻልም ። ኢኮኖሚ የሰዎች ማህበራዊ ኑሮ አንዱ ገጽታ በመሆኑ ሰዎች የጋራ ኑሮአቸውን ለማሳደግና ለመለወጥ በሚያደርጉት ጥረት ከፍተኛውን ሚና ይጫወታል። የኅብረተሰብንም የዕድገት አቅጣጫ የሚወስነው የሰዎች የማምረት ተግባር ነው የሚባለውም ከዚሁ የተነሳ ነው ።

የሰው ልጅ በማምረት ተግባር ላይ ከተሰማራበት ጊዜ አንስቶ የኅብረተሰብ ዕድገት በተለያዩ የሶሺዮ ኢኮኖሚ ሥርዓቶች አማካይነት ሲንፀባረቅ ቆይቷል ። ሆኖም ብሔራዊ ኢኮኖሚ መከሰት የጀመረው ከተወሰነ የኅብረተሰብ የዕድገት ደረጃ በኋላ

Digitized by Google

መሆኑ አይካድም ። ብሔራዊ ኢኮኖሚ የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በሁሉም ሥርዓተ ማህበሮች ውስጥ የታየ አይደለም ። ብሔራዊ ኢኮኖሚ በቅጡ መከሰት የጀመረው በተለይ የኅብረተሰብ ዕድገት ከፊውዳሊዝም ወደ ካፒታሊዝም በተሸጋገረበት ወቅት ላይ ሲሆን፣ ለዚህም ያበቁት በአንድ በኩል የኢኮኖሚ ምክንያቶች ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ የፖለቲካ ምክንያቶች ናቸው ። ከኢኮኖሚ ምክንያቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ፣ የሀገር ውስጥ ገበያ መስፋፋት ፣ የምርት ኃይሎች ዕድገት ፣ የማህበራዊ የሥራ ክፍፍል መዳበርና የሸቀጥ ልውውጥ መስፋፋት ይገኙበታል ። ከፖለቲካዊ ምክንያቶች መካከል ደግሞ የማዕከላዊ መንግሥት መቋቋምና የቡርዧው አብዮት መካሄድ ይገኙበታል ። በአጠቃላይ የአንድ ኅብረተሰብ በብሔር ደረጃ ማደግ ብሔራዊ ኢኮኖሚ በጉልህ እንዲታይ የረዳ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የብሔር መከሰት ራሱ የማኅበራዊ ዕድገት ውጤት ነው ለማለት ይቻላል ።

ብሔራዊ ኢኮኖሚ የሚለው ግንዛቤ አንድ ብሔር ሕልውናውን የሚጠብቅበትና በራሱ የተፈጥሮ ሀብት ላይ ያለውን መብትና የአጠቃቀም ሕግ አጠቃሎ የያዘ ከመሆኑም በላይ ፣ ከኢምፔሪያሊስት የኢኮኖሚ ተፅዕኖ የሚከላከልበት ዋናው መሣሪያ ሆኖ ይገኛል ። ከዚህ አጠቃላይ ግንዛቤ በመነሳት በኋላ ቀር አገሮች ውስጥ ሰፍኖ የሚገኘው የኋላ ቀርነት ክስተት ምንጭ ሲጤን፣ ከሞላ ጎደል የሚከተለውን ይመስላል ።

ኋላቀርነት የብሔራዊ ኢኮኖሚ መፋለስ ውጤት ነው ።

በዓለም ላይ ብዙዎች አገሮች በኋላቀርነት ደረጃ እንዲቀሩና ጥቂቶች በዕድገት መጥቀው ሕንዲገኙ ያደረጉ ምክንያቶችን በሚመለከት የተለያዩ አመለካከቶች ከተለያዩ የኢኮኖሚ ተመራማሪዎችና የፖለቲካ ሰዎች ይሰነዘራሉ ።

ይህን ጉዳይ በማስመልከት ከቡርዧ የኢኮኖሚ ተመራማሪዎች የሚሰነዘረው አመለካከት ኋላቀርነት ከኢምፔሪያሊዝም የቅኝና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም የሚል ነው ። በዚህ መሠረት የቡርዧ የኢኮኖሚ ተመራማሪዎች ኋላቀርነት በዓለም ላይ የተፈጥሮ ሀብቶች በእኩልና በተመሳሳይ ሁኔታ ያለመሰራጨት ውጤት ነው በማለት ያቀርባሉ ።[1] ዳሩ ግን ይህ አመለካከት እውነትነት የሌለው መሆኑን መረዳት የሚያዳግት አይደለም ። ለምሳሌ ዛየርንና ጃፓንን በማነጻጸር ከዚህ አንጻር የሚታየውን ሁኔታ ስናጤን የሚከተለውን ለመገምገም ይቻላል ። ዛየር በተፈጥሮ ሀብት የበለፀገች አገር ስትሆን ጃፓን ግን ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት እጥረት ስለአላት ከውጭ በምታስመጣቸው የጥሬ ዕቃዎች ላይ ያላት ጥገኝነት የኢኮኖሚዋ ልዩ ባህሪ ነው ። ዛየር ምንም እንኳን በተፈጥሮ ሀብት የበለጸገች ብትሆንም ቀደም ሲል በቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ውስጥ ወድቃ የነበረችና ዛሬም ቢሆን ከእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ያላመለጠች በመሆኗ ኋላቀር ከሆኑ አገሮች መካከል አንዷ ናት ። በአንጻሩ ጃፓን ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሁሉ የተፈጥሮ ሀብት እጥረት ቢኖርባትም እንኳ በዓለም ላይ በኢኮኖሚ ረገድ የሦስተኛነትን ቦታ ይዛ ትገኛለች ። ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለው ለኋላቀርነት መንስኤው ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ናቸው የሚለው አመለካከት ጨርሶ ከእውነት የራቀ መሆኑን ነው ። ምክንያቱም ለኋላቀርነት መንስኤ የሆነው ተፈጥሮአዊ ምክንያት ቢሆን ኖሮ የሁለቱ አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ተጻራሪ መልክ ባልያዘም ነበር ።

አንድ አሜሪካዊ የኢኮኖሚ ተመራማሪ ኋላቀርነት የታዳጊ አገሮች መሬት ለም ካለመሆኑ ፣ ለዕድገታቸው የሚያስፈልጋቸው ክምችት ስለሌላቸው ፣ ብሔራዊ ኢኮኖሚያቸውን የሚመራ መሪ ኃይል የሌላቸው በመሆኑ የተከሰተ ነው በማለት አስተያየቱን ሰንዝሯል ።[2] በዚህ ግለሰብ አመለካከት

Digitized by Google

ለኋላቀርነት መንስኤ የሆኑት ውስጣዊ ምክንያቶች (Internal Factors) ብቻ ሲሆኑ እነዚህም ምክንያቶች ከኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛና ተፅዕኖ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የላቸውም ። ኢምፔሪያሊዝም በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓቱ አማካይነት ብዙዎቹን ኋላቀር አገሮች በቁጥጥሩ ሥር በማድረግ በተፈጥሮ ሀብቶቻቸው ላይ የወሳኝነት ሚና እያለው በየአገሮቹ የኢኮኖሚ፣የፖለቲካና የማህበራዊ ጉዳዮች ውስጥ ፈላጭ ቆራጭ በሆነበት በአሁኑ ወቅት የኋላቀርነት መንስኤ ውስጣዊ ምክንያቶች ብቻ ናቸው የሚለው አመለካከት ትክክለኛ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም ።

ኋላቀርነት ከኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም በማለት የሚከራከሩ ብዙዎች ናቸው። ለምሳሌ አሜሪካዊው የኢኮኖሚ ተመራማሪ ቤንጃሚን ጂ. ኮኸን ኋላቀር አገሮች ለእድገታቸው አመች ሁኔታ የተፈጠረው ከበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ጋር የፋይናንስና የንግድ ግንኙነት ሲጀምሩ ነው በማለት ያቀረበውን ኢሳይንሳዊ አመለካከት መጥቀስ ይቻላል ።[3] በዚህ ገለሰብ አመለካከት ኢምፔሪያሊዝም ለኋላቀርነት ክስተት ታሪካዊ ኃላፊነት የለበትም ማለት ነው ። እንዲሁም ደግሞ እንደእነ አርተር ሊዊስ ፣ ሮስቶው እና ሳሙኤልሰን ያሉት የቡርዧ ኢኮኖሚ ተመራማሪዎች ኋላቀርነትን ሲገልጹ ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ያለውን ግንኙነት ማንሳት ፍጹም አይሹም ። እንዲያውም ኋላቀርነትን እንደማህበራዊ ክስተት ብቻ አርገው ያቀርቡታል ። በተለያዩ አገሮች መካከል የዕድገት ደረጃ ልዩነትን ሲያብራሩ ዕድገትን ቶሎ በመጀመርና ዘግይቶ ከመጀመር የተነሳ የተከሰተ ነው በማለት ያትታሉ ። በዚህም አመለካከታቸው ለብዙዎች አገሮች ኋላቀርነት የካፒታሊዝምና የቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ምክንያት መሆናቸውን ከታሪክ ፊት ለመሸሸግ ይሞክራሉ ።[4]

በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ የቡርዧ የኢኮኖሚ ተመራማሪዎች እንኳ ሳይቀሩ የዓለምአቀፍ የካፒታሊስት የሥራ ክፍፍል ዓለምን በድሀና በሀብታም አገሮች መክፈሉ በእኩልነት ላይ ላልተመሠረተ ግንኙነት መንስኤ መሆኑን ያምናሉ።የዚህ አመለካከት አፍላቂ ከሆኑት መካከል አሜሪካዊው ሬቻርድ ተብር ይገኝበታል።[5] በኋላቀር አገሮች ውስጥ የሚገኙ ብዙ የኢኮኖሚ ተመራማሪዎችና የፖለቲካ ሰዎች ኋላቀርነት የኢምፔሪያሊዝም ብዝበዛና ተፅዕኖ ውጤት መሆኑን ለማጋለጥ ከፍተኛ የንድፈ ሐሳብ ትግል በማድረግ ላይ ይገኛሉ።በዚህም መሠረት የላቲን አሜሪካው የኢኮኖሚ ተመራማሪ አንድሬ ጉንደር ፍራንክ ኋላቀርነት በአንድ በኩል በአሁኑ ጊዜ ኋላቀር አገሮች ተብለው በሚጠሩ፣ ቀድሞ በቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ሥር ወድቀው በነበሩትና አሁን በበለፀጉት የካፒታሊስት አገሮች መካከል በብዝበዛና በተፅዕኖ ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ውጤት ነው ሲል ገልጾታል ።[6]

የታሪካዊ ቁስአካልነት አመለካከት ያላቸው የኢኮኖሚ ተመራማሪዎች ኋላቀርነትን ሲገልጹ የቅኝ አገዛዝ ሥርዓት በሦስት አቅጣጫ የተጫወተውን ሚና ሳያነሱ አያልፉም ። በዚሁ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ ቅኝ አገዛዝ ዓለምን በድሀና በሀብታም አገሮች መክፈሉን ፣ በቅኝ አገዛዝ ቀንበር ሥር ወድቀው በነበሩት አገሮች ውስጥ የተፈጠረው ተረፈ እሴት ወደቅኝ ገዥ አገሮች ይሸጋገር እንደነበርና ይህ ሁኔታም በኋላቀር አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ እንቅፋት መፍጠሩን ፣ በሁለተኛ ደረጃ የቅኝ አገዛዝ ሥርዓት በኋላቀር አገሮች ውስጥ የተዛባ ኢኮኖሚ እንዲፈጠር ማድረጉ፣ብሎም ከዕድገታቸው ጋር በማይጣጣም የምርትና የሥራ ክፍፍል እንዲሰማሩ ማስገደዱና በዚህ ሁኔታም ቢጠቀም ውህደት የሌለው ኢኮኖሚ እንዲመሠርቱ ያ[illegible]ቸው መሆኑን ፣ በሦስተኛ ደረጃ የቅኝ አገዛዝ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት በብዝበዛና በተፅዕኖ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያሳያሉ ። ከዚህም በመነሳት ኋላቀርነት የካፒታሊስቱ ዓለም አቀፍ የሥራ

Digitized by Google

ከፍፍል ውጪት መሆኑን ይገልጻሉ ።

በዓለም ላይ የሰሰት ፖለቲካ ኃይሎች መከሰት ማለትም የዓለም የሶሻሊስት ሥርዓት መገንባት ፣ የብሔራዊ አርነት ትግል መፋፋምና በበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የሠራተኛው መደብ ለዲሞክራሲና ለሰላም የሚያደርገው ትግል እየተስፋፋ መምጣት ኋላቀር አገሮች ብሔራዊ ነጻነታቸውን እንዲጐናፀፉ ረድቷቸዋል ። ዳሩ ግን የፖለቲካ ነጻነታቸውን ባገኙ ማግስት የኢኮኖሚ ነጻነታቸውን አልተጐናፀፉም ። በዚህ ረገድ ከ1960 ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያለውን የኋላቀር አገሮችን የኢኮኖሚ ሁኔታ ስንገመግም የምናገኘው የሚከተለውን አስከፊና አሳሳቢ ሁኔታ ነው ፦

— ለዕድገታቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርግ የሚችለው የተፈጥሮ ሀብታቸው ተዘርፏል ፤ በመዘረፍም ላይ ይገኛል፤

— ከቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ፍላጐት አንጻር የተዘረጉት የኢኮኖሚ መዋቅሮች ነጻ ለሆነ የብሔራዊ እድገት የሚያመቹ ሁነው አልተገኙም ፤

— የባህልና የትምህርት ደረጃቸው በቅኝ አገዛዝ ሥርዓት በተፈፀመው ደባ ምክንያት እጅግ ኋላቀር ሆኖ ይገኛል ፤

— የብዙዎቹ ኋላቀር አገሮች የፋይናንስ አቋም ኢምፔሪያሊዝም ንግድን ፣ኢንቬስትመንትን ፣ የቴክኖሎጂ ስርጭትን አስታኮ በሚያካሂደው ከፍተኛ ብዝበዛ ሳቢያ በማጧጠጥ ላይ ያለ በመሆኑ ለእድገታቸው አስፈላጊ የሆነው ክምችት ሊገኝ አልቻለም ።

ኋላቀር አገሮች ብሔራዊ ነጻነታቸውን ካገኙ ከሃያና ከዚያ በላይ ከሆኑ ዓመታት በኋላ የኢኮኖሚ ሁኔታቸው ይህን ዓይነት መልክ መያዙ ከታሪካዊ አቀራረብ አንጻር ለኋላቀርነት ተቀዳሚ የሚሆነው ውጫዊ ምክንያት መሆኑ አያጠራጥርም ።

በእርግጥ በአሁኑ ወቅት የኋላቀርነት ክስተት የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ውጤት መሆኑ ቢታወቅም የዚህ ክስተት ብቸኛ ምክንያት ውጫዊ (External Factors) ነው ለማለትም አያስደፍርም ። እንደሚታወቀው የብሔራዊ ነፃነት ጉዳይ ለማናቸውም አገር የሕልውና ጥያቄ በመሆኑ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉ የተለያዩ መደቦች ምንም እንኳን የመደብ ቅራኔ ቢኖራቸውም ፣ ይህንን ለጊዜው ወደኋላ በመተው አንድ ግንባር በመፍጠር የሚታገሉለት ዓላማ ነው ። የብሔራዊ ነፃነት ከተገኘ በኋላ ግን በጥቅም ረገድ ተጠቃሚ የሚሆነው የፖለቲካ ሥልጣን የያዘው አንዱ የኅብረተሰብ መደብ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ የሀገራችንን ሁኔታ እንኳ ወደኋላ መለስ ብለን ብንቃኝ በአባቶቻችን ከፍተኛ መስዋዕትነት ተጠብቆ የቆየው ብሔራዊ ነፃነታችን የፖለቲካ ሥልጣን በፊውዶ ቡርዧው መንግሥት እጅ በመውደቁ በዚሁ መሣሪያነት በመጠቀም ይኸው አድኃሪ አገዛዝ በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ላይ ያደረሰውን ግፍና መከራ ማስታወሱ በቂ ይሆናል ።

ኢምፔሪያሊዝም ኋላቀር አገሮች ያገኙትን የብሔራዊ ነፃነት ለኢኮኖሚ ነፃነታቸው ትግል መሣሪያ እንዳያደርጉት ለፖለቲካ ነፃነት የተሳሳተ ግንዛቤ በመስጠት ከትግል ለማዘናጋት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። በዚሁ መሠረት ሃንስ ኮኸን የተባለው የኢኮኖሚ ተመራማሪ የኋላቀር አገሮች ነፃነት በፖለቲካ ነፃነት የሚያበቃ ነው በማለት የቅኝ አገዛዝን ውስብስብ ባህሪ ወደ ፖለቲካ ተፅዕኖ ብቻ ዝቅ ለማድረግ ይሞክራል ።[7] ከእንዲህ ዓይነቱ ግንዛቤም በመነሳት የፖለቲካ ነፃነት በኢምፔሪያሊዝም ላይ ያለን ጥገኝነት ፈጽሞ ያስወግዳል ነው ወደሚል የተሳሳተ አመለካከት ሊያመራ ይችላል ። ብዙ ኋላቀር አገሮችም በዚህ የተሳሳተ አመለካከት በመደለል የፖለቲካ ነፃነታቸውን ከተጐናጸፉ በኋላ የቅኝ አገዛዝ ቅሪትን ለማስወገድ ተገቢውን እርምጃ አልወሰዱም ። እንደሚታወቀው አብዛኞቹ ኋላቀር አገሮች ከቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ጋር ተጣምሮ የቆየውን የቅድመ ካፒታሊስት የምርት ግንኙነት ለማ

Digitized by Google

ስወገድ አልሞከሩም ፤ ብቃት ያለው የብሔራዊ ኢኮኖሚ የቁጥጥር ስልት አልቀመሩም። የብሔራዊ ኢኮኖሚያቸው መዋቅር ለካፒታሊዝም ብዝበዛ አመቺ እንዲሆን ታስቦ የተዘረጋ መሆኑ እየታወቀ መሠረታዊ ለውጥ አላደረጉም ። በብሔራዊ ኢኮኖሚ ሕይወት ውስጥ የመንግሥት ተሳትፎ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል ። ይህም ሁኔታ አብዛኞቹ ኋላ ቀር አገሮች የፖለቲካ ነፃነታቸውን ለኢኮኖሚ ነፃነታቸው እንደትግል መሣሪያነት በመጠቀም አንፃር ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆኑን ያንፀባርቃል ። ከዚህም የተነሳ ውስጣዊ ምክንያቶች ለኋላቀርነት ክስተት መቀጠል ተጨማሪ ምክንያቶች ሊሆኑ ችለዋል ።

ኢምፔሪያሊዝም መጀመሪያውኑ የጨነቀው ኋላቀር አገሮች የፖለቲካ ነፃነታቸውን መጐናፀፋቸው ሳይሆን ከበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ተፅዕኖ ነፃ የሆነ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ለማቋቋም መሞከራቸው ነው ። ምክንያቱም ኋላቀር አገሮች ነፃ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ካቋቋሙ ከኢምፔሪያሊዝም ጥገኛነት በመላቀቅ የፖለቲካ ነፃነታቸውን የተሟላ ነፃነት የሚያደርጉት መሆኑ የሚያጠራጥር ስለማይሆን ነው ። ይህንኑ ለመቋቋም ኢምፔሪያሊዝም ኋላቀር አገሮች ብሔራዊ ነፃነታቸውን ባገኙበት ዋዜማ የትግል ስልቱ ያተኮረው እነዚህ አገሮች ነፃና ጠንካራ ብሔራዊ ኢኮኖሚ እንዳያቋቁሙ ፤ በአንፃሩ ደግሞ የእርሱ አፈቀላጤዎች የፖለቲካ ሥልጣን እንዲጨብጡና ጥገኛ የሆነ መንግሥት እንዲመሰረት ማድረግ ነበር ። በዚህ ረገድ የነበረውን ስጋት ካስወገደ በኋላ የብዙዎችን ኋላቀር አገሮች የፖለቲካ ነፃነት ባንዲራ ከማውለብለብ ነፃነት እንዳያልፍ አድርጎታል ።

ኢምፔሪያሊዝም ይኸን ሥውር ደባ ለመሸፈንና በኋላቀር አገሮች ውስጥ ተስፋፍቶ የነበረውን ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል ለማፈን የነዚህን አገሮች ሕዝቦች ብሔራዊ ፍላጐትና ምኞት በመጠኑም ቢሆን እንዲሟላ « በማሰብ » ቅድመ ካፒታሊስት ይዞታ ተንሰራፍቶ ይገኝባቸው በነበሩ አንዳንድ አገሮች ውስጥ በቡርዧው ፈለግ የመሬት ይዞታ ለውጥ እንዲደረግ ገፋፍቷል ። ይህ አድራጐቱ በእርግጥ ለነዚህ አገሮች በመቆርቆር ሳይሆን ከትግል በማዘናጋት ሰላማዊ በሆነ መንገድ ከቀጥታ ቅኝ አገዛዝ ወደ እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ እንዲሸጋገሩ ለማድረግ ነው ። ኢምፔሪያሊዝም ይኸው ዓላማው በአብዛኛው ተሳክቶለት በኋላቀር አገሮችና በበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች መካከል ያለው ግንኙነት በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ተፅዕኖ ክልል ሥር እንዲወድቅ ለማድረግ ችሏል ።

የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ በኢምፔሪያሊስት አገሮችና ቀድሞ በቅኝ ግዛትነት ይዟዋቸው በነበሩት አገሮች መካከል የነበረውን ግንኙነት ለወጥ ባለ መንገድ ለማቆየት፣ ካፒታሊዝም በዓለም ላይ ያለውን ቦታ ጠብቆ እንዲቆይ ለማድረግ ፣ የብሔራዊ አርነት ትግልን ለመግታት ፣ ከኋላቀር አገሮች የሚካበተውን ትርፍ ከፍ ለማድረግና በነዚህ አገሮች ውስጥ የኢምፔሪያሊዝምን የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካ ፣ የወታደራዊ ጥቅም ይበልጥ በማጠናከር ካፒታሊዝም ከገባበት አጠቃላይ ቀውስ ለመወጣት ፣ ሀገሮች ለሶሻሊዝም የሚያደረጉትን ትግል ለመግታት ኢምፔሪያሊዝም የሚጠቀምበት ብቸኛ አማራጭ ነው ።[8] በአጭሩ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ኋላቀር አገሮችን በበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ላይ ጥገኛ ለማድረግ የተቀየሰ የኢምፔሪያሊዝም የብዝበዛ ዘይቤ ነው ። ስለሆነም ኋላቀር አገሮች የፖለቲካ ነፃነትን ግንዛቤ ከኢምፔሪያሊዝም የቀጥታ ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት በማላቀቅ « ነፃ » መንግሥት ለማቋቋም ወደ አወጁት አዋጅ ዝቅ በማድረግ ሳይወሰኑ ለፖለቲካ ነፃነታቸው አስተማማኝ የሆነ መሠረት መጣል ይኖርባቸዋል ።

በመሠረቱ ብሔራዊ ነፃነት ከሁለት አንፃር መታየት እንዳለበት መገንዘብ አያዳግትም ። እነርሱም ፖለቲካና ኢኮኖሚ ናቸው። የፖለቲካው አንፃር ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር

Digitized by Google

በመላቀቅ ነፃ መንግሥትን መመስረትና ብሔራዊ ሕልውናውን መጠበቅ መቻሏን ሲያመለክት ፣ የኢኮኖሚው ገፀታ ደግሞ ፖለቲካውንና ኢኮኖሚውን በማቀናጀት ነፃ በሆነ ሁኔታ ብሔራዊ ኢኮኖሚው የሚመራበትን መንገድ የመምረጥ ፣ በራስ ሀገር የተፈጥሮ ሀብት ላይ ብቸኛ ባለቤት የመሆንና የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም የማስጠበቅ ችሎታን የሚያንፀባርቅ ነው ።

በዓለም ላይ በዘመናችን የሚታዩት ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ክስተቶች የቅኝ አገዛዝ የዘመናዊ ቅርጹ ገጽታዎች መሆናቸውን ካለመገንዘብ የተነሳ ስለተለያዩ አገሮች የዕድገት ልዩነት የተሳሳተ አመለካከት ላይ ለመድረስ ይቻላል ። ስለሆነም ኢምፔሪያሊዝም ዛሬም ቢሆን በቀጥታ ሳይሆን ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ፣በግልጽ ሳይሆን ረቂቅ በሆነ ዘዴ በቅርቡ ነፃ የወጡትን አገሮች ጥገኛ በማድረግ መበዝበዝ መቀጠሉን መረዳት ያሻል ።

በዘመናችን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ስርዓት ኋላቀር አገሮችን በሚመለከት የቀየሰው መሠረታዊ ስትራቴጂ እነዚህን አገሮች ጥገኛ ማድረግ ነው ። [9] በዚሁ ሁኔታ በኋላቀር አገሮች ላይ የሚፈጸመው ደባ እንዳይታወቅበት የጥገኝነትና የኢኮኖሚ መደጋገፍ ግንዛቤን አንድ ለማስመሰል በአፈቀላጤዎቹ አማካይነት ከፍተኛ የሆነ የንድፈሐሳብ ትግል ያካሂዳል ። የዓለም ኢኮኖሚ ተጨባጭ ዕውነታ ግን የኢኮኖሚ ጥገኝነትና የኢኮኖሚ መደጋገፍ የተለያዩ መሆናቸውን በግልጽ ያሳያል ። በዚህ መሠረት የኢኮኖሚ ጥገኝነት ጠንካራው በደካማው ላይ ተፅዕኖ በማድረግ የሚፈጥረውን ግንኙነት ያንጸባርቃል። እንዲህ ዓይነቱ ግንኙነትም የካፒታሊስቱ ዓለምአቀፍ የሥራ ክፍፍል አንዱ ገጽታ ነው ። ኢምፔሪያሊዝም በጥገኝነትና በመደጋገፍ ባህሪ መካከል ልዩነት የሌለ በማስመሰል የሚነዛው ፕሮፖጋንዳ በኋላቀር አገሮች ላይ ለሚፈጸመው ደባ ሽፋን ለመስጠት ነው ። በግልጽ እንደሚታየው ኋላቀር አገሮች በቴክኖሎጂ ፣ በንግድ ፣ በፋይናንስ ወዘተ - - - ረገድ በበለፀጉት ካፒታሊስት አገሮች ላይ ያላቸው ጥገኝነት ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ብዝበዛ አጋልጧቸው ይገኛል ።

የቴክኖሎጂ ጥገኝነት

በዓለም የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ ዓለም አቀፍ ሞኖፖሊዎች ለኋላቀር አገሮች አዳዲስ የምርት መገልገያዎችንና ቴክኖሎጂዎችን በማቅረብ ረገድ የመጀመሪያውን ቦታ ይዘው ይገኛሉ ። በዚህ መስክ ያላቸውን የበላይነት በመጠቀም በቅርቡ ነፃነታቸውን የተጐናፀፉትን አገሮች በቀላሉ የኢምፔሪያሊስት አገሮች ጥገኞች እንዲሆኑ አድርገዋቸዋል ።

የሃርቨርድ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር የሆነው ጂ ናይ ጁንየር ኋላቀር አገሮችን በቴክኖሎጂ መስክ የኢምፔሪያሊዝም ጥገኛ የማድረጉን « ጠቃሚነት » ሲገልጽ ፣ « ወደ ታዳጊ አገሮች የሚላኩት ቴክኖሎጂዎች ከተጨባጭ የዕድገት ፍላጐታቸው ጋር የሚጣጣም ስለአልሆነ በካፒታሊስቱ ዓለም ላይ ያላቸውን ጥገኝነት ይበልጥ ለማጠናከር ይረዳል ፣ የኢኮኖሚ ፖሊሲያቸውንም ለማናጋት ያስችላል ፣ የሕዝቡም የሸመታ ልምድ እንደበለፀጉት ካፒታሊስት አገሮች እንዲሆን ያደርጋል » ሲል መጻፉ ይታወሳል ። [10]

ኢምፔሪያሊስት አገሮች ኋላቀር አገሮችን በቴክኖሎጂ ጥገኛ ከሚያደርጉበት መንገድ አንዱ ከነዚህ አገሮች ምሁራንን መዝረፍ ነው ። ከኋላ ቀር አገሮች ወደ በለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች የሚኰበልሉት ምሁራን በነዚህ አገሮች ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ላይ ከብዙ አቅጣጫ ጉዳትን ያስከትላሉ ። ኋላቀር አገሮች

Digitized by Google

በሚኩበልሉባቸው ምሁራን ሳቢያ የሰለጠነ የሰው ኃይል ስለሚያንሳቸው ይህንኑ ችግር ለመወጣት ሲሉ ከበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ለሚያስመጧቸው ኤክስፐርቶች የሚከፍሉት ደሞዝ ከፍተኛ በመሆኑ ብዙ ወጭ አውጥተው ያስተማሯቸውን ምሁራን በማጣት በአንድ በኩል ከፍተኛ ኪሳራ ላይ ሲወድቁ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከውጭ በከፍተኛ ክፍያ ለሚያስመጧቸው ምሁራን የሚያወጡት ወጭ በሁለት በኩል እንዲጐዱ አድርጓቸዋል ።

የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ከኋላቀር አገሮች በሚኩበልሉ ምሁራን በመጠቀም የሚያገኙትን ገቢ ለአብነት ያህል ከዚህ ቀጥሎ ለማቅረብ ይሞከራል ።

በ1970 አሜሪካ ከኋላቀር አገሮች ኩብልለው በሄዱ ምሁራን በመጠቀም ያገኘችው የተጣራ ገቢ [11]

	የኩበለሉ ምሁራን ቁጥር	ከአንድ ምሁር የሚገኝ የተጣራ ገቢ (በሺ የአሜሪካን ዶላር)	አጠቃላይ የተጣራ ገቢ (በሺ የአሜሪካ ዶላር)
የሶሻል ሳይንስ እስፔሻሊስቶች	471	230	108,330
የተፈጥሮ ሳይንስ እስፔሻሊስቶች	2,154	235	506,190
ኢንጂነሮች	6,400	253	1,619,200
የሕክምና ሰዎች	2.211	616	1,428,306
ጠቅላላ ድምር	11,236		3,662,026

ከአሃዛዊ መረጃው መረዳት እንደሚቻለው አሜሪካ ከታዳጊ አገሮች ምሁራንን በመዝረፍ የምታካብተው ትርፍ ከፍተኛ መሆኑን ነው ። አሜሪካ በ1970 ለኋላቀር አገሮች ከሰጠችው 3.1 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር እርዳታ ጋር ሲነፃፀር ከኩበለሉ ምሁራን ያገኘችው ልቆ እንደሚገኝ መረዳት ይቻላል ። በተጨማሪም አሜሪካ ከኩበለሉ ምሁራን ያገኘችው ገቢ ለምርምርና ለጥናት ከምታወጣው ወጪ 14% ይሆናል ። ለከፍተኛ ትምህርት ከምታደርገው ወጪ ደግሞ 39 በመቶውን ያህላል ።[12] በአጠቃላይ አነጋገር ኋላቀር አገሮች በሳይንስና በቴክኖሎጂ የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮችን እየረዱ ናቸው ማለት ነው ።

ታዳጊ አገሮች በምሁራን ኩብለላ የሚደርስባቸው ጉዳት ይህ ብቻ አይደለም ። ምሁራንንም ለማፍራት የሚያወጡት ወጪ ሳይሸፈን መቅረቱ ሌላው የጉዳታቸውም ምንጭ ነው ። ይህንንም በግልጽ ለመገንዘብ እንዲቻል የሕንድን ምሳሌ ከዚህ በታች ለማቅረብ ይሞከራል ።

Digitized by Google

ሕንድ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምሁራንን ለማሰልጠን የምታወጣው ወጪና የኩበለሉ ምሁራን የሚያስከትሉት ኪሣራ [13]

	ለአንድ ምሁር የሚወጣው ወጪ (በአሜሪካ ዶላር)	የኩበለሉ ምሁራን ቁጥር	በዓመት የሚደርሰው ኪሣራ (በአሜሪካ ዶላር)
ኢንጂነሮች	40,009	307.8	1,231,477
የተፈጥሮ ሳይንስ እስፔሻሊስቶች	2,151	119.4	256,829.4
የሶሻል ሳይንስ እስፔሻሊስቶች	2,151	7.6	16,347.6
የሕክምና ሰዎች	4,009	50.2	201,251.8
በዲፕሎማ ደረጃ የሚገኙ እስፔሻሊስቶች	877	32.8	28,765.6

ከዚህ አሃዛዊ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ሕንድ በሚኩበልሉ ምሁራን ሳቢያ የሚደርስባት ኪሣራ ከፍተኛ መሆኑን ነው። የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች በተመሳሳይ መልክ ከመላ ኋላቀር አገሮች የሚዘርፉት የሰለጠነ የሰው ኃይል የነዚህ አገሮችን ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ሕይወት እያቀጨጨ ከመሄዱም ሌላ በበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮችና በኋላቀር አገሮች መካከል የሳይንስ ሰዎችን በሚመለከት ያለው ልዩነት ከፍተኛ እየሆነ እንዲሄድ በማድረግ ላይ ነው። በዚህ መሠረት ከዓለም ሳይንቲስቶች 90 በመቶ የሚሰሩት በበለጸጉ ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ሲሆን ፣ በዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች ለ10 ሺህ ነዋሪዎች የሚደርሰው የኢንጂነሮችና ሳይንቲስቶች ቁጥር 112፣ በላቲን አሜሪካ 69፣ በእስያ 22 በአፍሪካ ውስጥ ደግሞ 5.8 ነው። [14]

የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች በሳይንስ ምርምርና ጥናት ባላቸው የበላይነት የተነሣ የምርምሩና የጥናቱን ውጤት የመጠቀሙን መብት ለኋላቀር አገሮች በመሸጥ ከፍተኛ ትርፍ ያጋብሱበታል። በሌላ በኩል ደግሞ አስመስሎ የመስራት መብት (Patent) መሸጥ በአዳዲስ ገበያ ውስጥ እንዲገቡ ስለሚረዳቸው የውጭ ንግዳቸውን የሚያስፋፉበት መሰረታዊ ዘዴ አድርገው ይጠቀሙበታል። ከዚህም ሌላ በብሔራዊ ካፒታል በተገነቡ የኢኮኖሚ ድርጅቶች ውስጥ የካፒታል ድርሻ እንዲኖራቸው ስለሚያደርግ ቀስ በቀስ እነዚህን ድርጅቶች በቀላሉ በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ ይችላሉ። በአጠቃላይ አስመስሎ የመሥራት ፈቃድና መብትን መሸጥ ኢምፔሪያሊስቶች በቴክኖሎጂ ሥርጭት ሰበብ ከፍተኛ ትርፍ የሚያጋብሱበት መስክ ነው።

ከድንበር ዘለል ኩባንያዎች ወደ ኋላቀር አገሮች የሚደረገው የቴክኖሎጂ «ስርጭት» የሚከናወነው በተለያዩ ሁኔታዎች ነው። እነሱም ኋላቀር አገሮች ከዓለም አቀፍ ሞኖፖሊዎች ቴክኖሎጂዎች እንዲገዙ በማድረግ በድንበር ዘለል ኩባንያዎች የግል ካፒታል ኢንቬስትመንት በመጠቀምና የውጭ ኤክስፐርቶችን ወደኋላቀር አገሮች በመላክና ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው አስመስሎ የመሥራት መብትን በመሸጥ ነው።

ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በኋላቀር አገሮች ውስጥ የሚያውሉትን የካፒታል ኢንቬ

Digitized by Google

ስትመንት እንዲያስፋፉ የረዳቸው ከዚህ ቀደም ሲል ያካሄዱት የማኔጅመንት አብዮት በመባል የሚታወቀው ነው ። የማኔጅመንት አብዮት ዓላማ በኋላቀር አገሮች ውስጥ የሚገኙት በዝባዥ መደቦች በየአገሮቻቸው የኢኮኖሚ ሕይወት ውስጥ በድንበር ዘለል ኩባንያዎች መስፋፋት ላይ ጥላቻ እንዳይኖራቸው ለማድረግ ነው ።

ኢምፔሪያሊስት አገሮች በኋላቀር አገሮች ውስጥ የሚያውሉት መዋዕለ ንዋይ የእነዚህን አገሮች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በቀላሉ በቁጥጥር ሥር ለማዋልና ኢምፔሪያሊስት አገሮች በሚያካሂዱት የርስ በርስ ውድድር ተወዳዳሪ የሆኑትን ለመከላከል ስለሚያስችል በከፍተኛ ሁኔታ ሲጠቀሙበት ቆይተዋል ፤ እየተጠቀሙበትም ነው ። በዚሁ መሠረት በዓለምአቀፍ ሞኖፖል ኩባንያዎች አማካይነት በዓመት በኋላቀር አገሮች ውስጥ ለመዋዕለ ንዋይ ሥራ የሚውለው የገንዘብ መጠን 8 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚደርስ ሲሆን ፣ በመዋዕለ ንዋዩ ሳቢያ ደግሞ በትርፍና በሌላ መልክ የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ከኋላቀር አገሮች የሚያገኙት ገቢ 25 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር እንደሚደርስ ይገመታል ።[15] ለምሳሌ የአሜሪካ ዓለምአቀፍ ኩባንያዎች በ1978 ከውጭ የመዋዕለ ንዋይ ሥራ 24 ቢሊዮን ዶላር ትርፍ አግኝተዋል ። ይህም በ1970 ካገኙት ጋር ሲነፃፀር በሶስት እጅ ይበልጣል ። ከመዋዕለ ንዋይ የሚገኙት የትርፍ መጣኔም በበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ 14% ሲሆን በታዳጊ አገሮች ውስጥ ደግሞ 65.7% ነው ።[16] በአጠቃላይ ከተጠቀሱት አኀዛዊ መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው ኢምፔሪሊያስቶች በኋላቀር አገሮች ውስጥ ለመዋዕለ ንዋይ ሥራ የሚያውሉት ገንዘብ ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ብዝበዛቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ነው ።



እርዳታ — የአሜሪካ ዓይነት
("Horizon" ከተሰኘ የጀ. ዲ. ሪፐብሊክ መጽሔት የተወሰደ)

Digitized by Google

ቀደም ሲል እንደቀረበው ታላላቅ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ገበያቸውን ከሚያስፋፉበት ዘዴ አንዱ የኋላቀር አገሮችን ሕዝቦች የሸመታ ልምድ እንደበለፀጉት ካፒታሊስት አገሮች እንዲሆን በማድረግ ነው። በኋላቀር አገሮች ያለው ምርታማነት ከበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ጋር ሲነፃፀር እጅግ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ የኋቀር አገሮች የሸመታ ልምድ ግን ኢምፔሪያሊዝም ባሳደረባቸው የባህል ተጽዕኖ የተነሳ ከምርታማነታቸው ጋር ጨርሶ የማይጣጣም ነው ። በዚህ አድራጎቱ ኢምፔሪያሊዝም የሚፈልገው ውጤት የኋላቀር አገሮችን ሕዝቦች ከማምረት ተግባር በማዘናጋት የገበያ ጥገኛ ለማድረግ ነው ። ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በዚህ መልክ ለገበያቸው አመቺ ሁኔታ ከፈጠሩ በኋላ የፍጆታ ዕቃዎችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎችን በኋላቀር አገሮች ውስጥ ማስፋፋት ይጀምራሉ ። ከዚህም በላይ የኋላቀር አገሮች ኢኮኖሚ እጅግ በጣም ውስን በሆኑ ምርቶች ላይ እንዲመሠረት በማድረግ የውጭ ምንዛሬ ክምችት ምንጫቸው በዓለም አቀፍ የካፒታሊስት ገበያ ፍላጎት ላይ እንዲወሰን ያደርጋሉ ። የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ኋላቀር አገሮች የጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች ሆነው እንዲቀሩ ስለሚፈልጉ በቂ የጥሬ ዕቃ ሀብት እንኳን ባላቸው ኋላቀር አገሮች ውስጥ ከባድ ኢንዱስትሪዎች እንዳይቋቋሙ እንቅፋት ይፈጥራሉ ። በዚህም ምክንያት የነዚህ አገሮች ብሔራዊ ነፃነት ጠንካራ መሠረት ሊኖረው አልቻለም ።

የንግድ ጥገኝነት

ባለንበት ዘመን የዓለም የንግድ ግንኙነት የሚከናወንበት ስልት የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች በዕድገት ኋላቀር የሆኑትን አገሮች በቀላሉ እንደ በዘብዙዋቸው የሚያደርግ በመሆኑ ለኋላቀርነት መቀጠል አንዱ ምክንያት ሆኖአል። በዓለምአቀፍ ደረጃ በካፒታሊስት ዓለምአቀፍ የሥራ ክፍፍል ላይ የተመሰረተው የወጪና የገቢ ንግዳቸው ዘርፍ ብሔራዊ ኢኮኖሚያቸውን በበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ብሔራዊ ኢኮኖሚ ላይ በከፍተኛ ደረጃ ጥገኛ እንዲሆን አድርጓል። በጥሬ ዕቃዎች ምርት ላይ ያተኰረው የውጪ ንግዳቸው ገበያ በበለጸጉ ካፒታሊስት አገሮች ገበያ ላይ ጥገኛ ነው ። ለምሳሌ ከኋላቀር አገሮች 94 በመቶ የነዳጅ ዘይት 45 በመቶ ብረታ ብረት፣ 57 በመቶ መዳብ፣ 12 በመቶ ቆርቆሮ፣ 55 በመቶ ቦክሳይት እንዲሁም ሌሎች የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃዎች የሚገዙት በኢምፔሪያሊስት አገሮች ነው ።[17]

በወጪ ንግድ ረገድ በ1976 በታዳጊ አገሮች መካከል የ58,086 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የንግድ ልውውጥ የተከናወነ ሲሆን ይኸም ከዓለም አቀፍ የንግድ ልውውጥ 22.8 በመቶ ድርሻ ነበረው ። ይኸ መጠን በ1978 ወደ 73,342 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ያደገ ሲሆን የመቶኛ ድርሻው በዚያው መጠን ወደ 24.4 በመቶ አድጎ ነበር ። በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ በኋላቀር አገሮችና በበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች መካከል የተከናወነው የንግድ ልውውጥ 181,755 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲሆን የዚህ ልውውጥ ድርሻ ከመቶኛ 71.2 ነበር ። በ1978 ደግሞ ወደ 212,501 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከፍ ያለ ሲሆን ይኸም ከመቶ ሲሰላ 70.6 በመቶ መሆኑ ነው ። በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በኋላቀር አገሮችና በሶሻሊስት አገሮች መካከል የተከናወነው የንግድ ልውውጥ 10,625 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲሆን ከመቶ ሲሰላ 4.2 በመቶ ነው ። በ1978 ልውውጡ ወደ 12,855 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ያደገ ሲሆን የዚህ ልውውጥ ድርሻ ከመቶ ወደ 4.3 ከፍ ብሏል ።[18] ኋላቀር አገሮች በበለፀጉት ካፒታሊስት አገሮች ላይ በውጪ ንግድ ረገድ ጥገኞች እንደሆኑ ከቀረቡት አኀዛዊ መረጃዎች በመነሳት መረዳት ይቻላል ። ከዚህ ጥገኝነት ለመላቀቅ ኋላቀር አገሮች እርስ በእርስ የሚያደርጉትን የንግድ ልውውጥ ማዳበርና የሶሻሊስት ዓለምአቀፍ ገበያ ከፈጠረው ጠቃሚ ሁኔታ መጠቀም መቻል ይኖርባቸዋል ።

Digitized by Google

ኋላቀር አገሮች በበለፀጉት ካፒታሊስት አገሮች ላይ በገቢ ንግድ መስክ ያላቸውን ጥገኝነት በተመሳሳይ ሁኔታ ማቅረብ ይቻላል ። በ1978 በኋላቀር አገሮች መካከል የተደረገው የገቢ ንግድ ልውውጥ 73,342 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲሆን ፥ ድርሻው ከመቶ 24.2 ነበር ። በተመሳሳይ ጊዜ በኋላቀር አገሮችና በበለጸጉት ካፒታሊስት አገሮች መካከል የተከናወነው የገቢ ንግድ ልውውጥ 207,219 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲሆን ይኸም 68.3 በመቶ መሆኑ ነው። በኋላቀር አገሮችና በሶሻሊስት አገሮች መካከል ደግሞ በዚሁ ጊዜ ውስጥ የ12,909ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የንግድ ልውውጥ የተደረገ ሲሆን ድርሻው 7.5 በመቶ ብቻ መሆኑ ነው ።[19] ቀደም ሲል እንደተገለጸው ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ለኋላቀር አገሮች ልዩ ልዩ መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂዎችን በማቅረብ ረገድ የመጀመሪያውን ቦታ ይዘዋል ። በዚህም ምክንያት በገቢ ንግድ ረገድ እነዚህ አገሮች የኢምፔሪያሊስት አገሮች ጥገኞች እንዲሆኑ አድርገዋቸዋል ። ኋላቀር አገሮች ተመሳሳይ መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂዎችን ከሶሻሊስት አገሮች ለማግኘት ቢችሉም ይህንን ዕድል በሚገባ የተጠቀሙበት አይመስሉም ። ዳሩ ግን በገቢ ንግድ መስክ በኢምፔሪያሊስት አገሮች ላይ ያላቸውን ጥገኝነት ለመቀነስ የሶሻሊስቱ ዓለምአቀፍ ገበያ አማራጫቸው እንደሆነ መገንዘብ ይኖርባቸዋል ።

አብዛኞቹ ኋላቀር አገሮች በበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ላይ በወጪና በገቢ ንግድ ጥገኞች በመሆናቸው 70 በመቶ ያህል የሚሆነውን የወጪ ንግዳቸውን ገቢ የሚያገኙት ከእነሱ ነው ፤ 4 በመቶ ደግሞ ከሶሻሊስት አገሮች ነው ። በገቢ ንግድ በኩል ደግሞ ከዓለም ገበያ ለሚገዙት የተለያዩ ዕቃዎች የሚከፍሉት 67 በመቶ ለካፒታሊስት አገሮች ሲሆን 26 በመቶ በመካከላቸው ላለው የንግድ ልውውጥ 7 በመቶ ለሶሻሊስት አገሮች ነው ።[20]

በጥሬ ዕቃዎች ላይ የተመሰረተው የወጪ ንግዳቸው በአብዛኛው በዓለምአቀፍ የካፒታሊስት ገበያ ሥር የሚወድቅ በመሆኑ በ1978 ዓለም አቀፍ ሞኖፖል ኩባንያዎች ከኋላቀር አገሮች የ30 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ጥሬ ዕቃዎች በመግዛትና በ200 ቢሊዮን በመሸጥ የ170 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ትርፍ ሊያገኙ ችለዋል ።[21] ይህም የሚያሳየው ኋላቀር አገሮች ውስን በሆኑ የወጪ ምርቶቻቸው ላይ እንኳ የበላይነት የሌላቸውና ትክክለኛ ዋጋም የማያገኙ መሆናቸውን ነው ።

እንደሚታወቀው በአብዛኞቹ ኋላቀር አገሮች ውስጥ ዓለምአቀፍ ሞኖፖል ኩባንያዎች የሚያቋቁሟቸው ፋብሪካዎች አንድን ምርት በራሳቸው ሙሉ በሙሉ ጨርሰው መሥራት የሚችሉ አይደሉም ። ስለሆነም ተመሳሳይ በሆኑና በበለጸጉ ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ በሚገኙ ፋብሪካዎች ላይ ጥገኞች ናቸው ። በእንዲህ ዓይነት መልክ የሚቋቋሙ የኢኮኖሚ ተቋሞች በዋጋ ሽግግር (Transfer of Price) ረገድ ለሚፈጸም ብዝበዛ አመች ይሆናሉ ። ማለትም ኋላቀር አገሮች እንደነዚህ ላሉ ፋብሪካዎቻቸው የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ ዕቃዎች ከበለጸጉ ካፒታሊስት አገሮች ሲገዙ ፥ የሚገዙት በገበያ ዋጋ ሳይሆን በፋብሪካዎቹ መካከል (ማለትም በዋናው ፋብሪካና በቅርንጫፎች መካከል) ባለው ዋጋ (Intrafirm Price) ነው ። ይህ ዋጋ ደግሞ እንደየአገሮቹ የግብር ፥ የታክስና የቀረጥ ፖሊሲ የውጭ ኩባንያዎች ባመቻቸው ሁኔታ ከፍና ዝቅ በማድረግ ከፍተኛ ገቢ የሚያጋብሱበት ነው ። ይህ እንግዲህ ከገቢ ንግድ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሚታይ ሲሆን ፥ በወጪ ንግድ በኩልም በእንዲህ ዓይነቱ ግንኙነት ሳቢያ ኋላቀር አገሮች ከፍተኛ ብዝበዛ ይደርስባቸዋል ። ይኸውም ቀደም ሲል እንደተገለጸው በኋላቀር አገሮች የተመሠረቱት ፋብሪካዎች አንድን ምርት ሙሉ በሙሉ የማምረት አቅም ስለሌላቸው ፥ ያመረቱትን ምርት

Digitized by Google

በበለጸጉ ካፒታሊስት አገሮች ለሚገኙ ሌሎች ፋብሪካዎች መሸጥ ይኖርባቸዋል ። እንደሚታወቀው ኋላቀር አገሮች ዋጋ ተቀባይ እንጂ ወሳኝ ስለአልሆኑ የበለጸጉ ካፒታሊስት አገሮች በሚወስኑት ርካሽ ዋጋ ለመሸጥ ይገደዳሉ ። ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በኋላቀር አገሮች ካዋሉት መዋዕለ ንዋይ የሚያገኙትትንና ወደ ውጭ የሚያግዙት ከፍተኛ የሆነ ትርፍ ከዚህ ሁኔታ ጋር ሲዳመር ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በኋላቀር አገሮች ላይ የሚያካሂደውን ብዝበዛ ስፋት ለመገንዘብ ያስችላል ።

በኋላቀር አገሮች ላይ ተንሰራፍቶ የሚታየው የኋላቀርነት ክስተት እንዲባባስ ከረዱ ምክንያቶች መካከል አንዱ በጥሬ ዕቃዎች ዋጋና በኢንዱስትሪ ዕቃዎች ዋጋ መካከል ተመዛዛኝነት ያለመኖሩ ሌላው ነው ። ለምሳሌ ከ1963—76 ባለው ጊዜ ውስጥ የጥሬ ዕቃዎች ዋጋ በ183 በመቶ ሲያድግ የኢንዱስትሪ ምርቶች ዋጋ ግን በ573 በመቶ አድጉ ነበር ። ከዚህም በተጨማሪ በ1973—75 እንደታየው ሁሉ የካፒታሊስቱ ዓለም በገጠመው የኤኰኖሚ ቀውስ ሳቢያ የበለጸጉ ካፒታሊስት አገሮች ከኋላቀር አገሮች ጋር ያላቸው የገቢ ንግድ ግንኙነት ሊቀዘቅዝ የሚችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል።በሌላ በኩል ደግሞ ኋላቀር አገሮች ለኢኮኖሚና ለማኅበራዊ ኑሮአቸው ዕድገት የሚያስፈልጉ የምርት መገልገያዎችንና የፍጆታ ዕቃዎችን ማስገባት ስለሚገደዱ የገቢ ንግዳቸው ያድጋል ። በዚህ መልክ በገቢና በወጪ ንግዳቸው መካከል በሚከሰተው ተፃራሪ ዕድገት ሳቢያ ኋላቀር አገሮች የንግድና የክፍያ ሚዛን ጉድለት ይገጥማቸዋል ። ይህም ሁኔታ ለኢምፔሪያሊስት አገሮች አዲስ የብዝበዛ ስልት ቀዳዳ ይከፍታል ።

የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ለኋላቀር አገሮች የሚሰጡት ዕርዳታ ሌላው የኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የመበዝበዣ ስልት ነው ። ለምሳሌ የአሜሪካ ዕርዳታ የውጭ ፖሊሲዋ አካል ነው ። የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች የተፈጠረባቸውን የተትረፈረፈ ምርት ቀውስ የሚወጡት በኋላቀር አገሮች ብዝበዛ ነው ። ብዙውን ጊዜ ለኋላቀር አገሮች ዕርዳታ በሚሰጡበት ጊዜ በዕርዳታው ገንዘብ ከበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ገበያ በውድ ዋጋ ዕቃ እንዲገዙ ያደርጓቸዋል ። በሌላ በኩል ደግሞ የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ለነዚህ አገሮች የሚሰጡት ዕርዳታ ከፖለቲካና ወታደራዊ ሁኔታዎች ጋር የተያያዘ ስለሆነ ለኋላቀር አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት እምብዛም አስተዋጽኦ አያደርግም ። የኢምፔሪያሊስት አገሮች ዕርዳታ የኢምፔሪያሊዝም ጥገኛ የሆኑ አገሮች በውስጥ የሚነሱባቸውን ማኅበራዊ ቅራኔዎች ለማፈን ተራማጅ መንግሥታትን ለማናጋትና ኮሚኒዝምን ለመገደብ ሥራ ላይ የሚውል እንጂ እምብዛም ከኋላቀር አገሮች ብሔራዊ ኤኮኖሚ ዕድገት ጋር የተያያዘ አይደለም ።

ኋላቀር አገሮች በኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት አማካይነት የሚደርስባቸውን የኢኮኖሚ ብዝበዛ ለመቋቋም የውጭ ኩባንያዎችንና የኢኮኖሚ ተቋሞችን በቁጥጥር ሥር ማዋል ሲጀምሩ የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ስልታቸውን በመለወጥ የፋይናንስ ካፒታልን ወደነዚህ አገሮች መላክ ጀመሩ ። ይኸውም ሁኔታ ታዳጊ አገሮችን በፋይናንስ ረገድ በቀላሉ ጥገኞች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል ። ለምሳሌ በ1982 የታዳጊ አገሮች የውጭ ዕዳ 626 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር መድረሱ ይህንኑ የሚያንፀባርቅ ነው ።[22]

የዓለምአቀፍ የሞኖፖል ኩባንያዎች በመላው ዓለም መስፋፋት የዓለምን የኤኮኖሚ እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር አስችሏቸዋል ። በአሁኑ ጊዜ እነዚህ ዓለምአቀፍ ሞኖፖሊዎች 50,000 ቅርንጫፎች በመላው ዓለም ያሏቸው በመሆኑ በተለያዩ ዘዴዎችና ስልቶች የአብዛኞቹን የኋላቀር አገሮች ኤኮኖሚ የበለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች ጥገኛ እንዲሆን ለማድረግ ችለዋል ። በዚህም የተነሳ ዓመታዊ ገበያቸው ከ100 ቢሊዮን የአሜ

Digitized by Google

ሪካ ዶላር በላይ የሆኑ ድንበር ዘለል ኩባንያ ዎች ቁጥር በየጊዜው በመጨመር ላይ ይገ ኛል ። [23]

ከቀጥታ ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት የተላቀቁ በቅርቡ ነፃነታቸውን የተጐናፀፉት ኋላቀር አገሮች ምንም እንኳን በተለዩ ውስጣዊና ዓለምአቀፋዊ ምክንያቶች የተነሳ የተለያዩ ባህሪያትን የያዙ ቢሆንም ፣ በዚያው መጠን ደግሞ የወል የሆኑ ገጽታዎች አሏቸው። የመ ጀመሪያው የወል ገጽታቸው ከበለፀጉ ካፒ ታሊስት አገሮች ጋር ሲነፃፀር የምርት ኃይ ሎች ዕድገት በዝቅተኛ ደረጃ መገኘት፣ እን ዲሁም በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስክ ኋላቀር መሆናቸውን ሲያንፀባርቅ፣ ሁለተኛው የወል ገጽታቸው ደግሞ ውስጣዊ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍላቸው ዝቅተኛ መሆኑ ፣ በተለያዩ የኤ ኮኖሚ ዘርፎች መካከል ተደጋጋፊነት አለ መኖር ወይም ተደጋጋፊነቱ ዝቅተኛ መሆን በአጠቃላይ የተዛባ የኤኮኖሚ መዋቅር መኖ ርን የሚያሳይ ነው ።

በሶስተኛ ደረጃ የሚታየው የኋላቀር አገ ሮች የወል ገጽታ የምርት ርባታቸው የተ ለየ ባህሪ ያለው መሆኑ ነው ። በምርት ዕር ባታው ሂደት ውስጥ ውጫዊ ምክንያቶች ወሳኝ ሚና ከመጫወታቸው የተነሳ የበ ለፀጉ ካፒታሊስት አገሮች የቴክኖሎጂ ፣ የገንዘብ ፣ የንግድና የፋይናንስ ወዘተ . . . ጥገኞች መሆናቸውን የሚያንፀባርቅ ነው ።

በአራተኛ ደረጃ ደግሞ የሚታየው የኋላ ቀር አገሮች የወል ገጽታ የሕዝቦቻቸው የኑሮ ደረጃ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘት ነው ። በዓለም የምግብ ድርጅት (FAO) መረጃ መሠረት ከአፍሪካ ሕዝብ 30 በመ ቶው፣ ከእስያ ሕዝብ 1/4ኛው በረሀብ ይሰ ቃያል።በረሀብ ከሚቸገሩት መካከል 40 በመ ቶው ሕፃናት ናቸው። በዓለም የጤና ድርጅት መረጃ መሠረት በሩቅ ምሥራቅ አገሮች 100,000 ህፃናት በየዓመቱ በቫይታሚን «ኤ»እጥረት ምክንያት የዓይን ብርሃናቸውን ያጣሉ ። [24] 300 ሚሊዮን ያህል ደግሞ የአ ካል ዕድገታቸው የተገታ ነው።ኋላቀር አገ ሮች ውስጥ በ1970 750,000,000 ማይማን የነበሩ ሲሆን በ1985 ይህ ቁጥር ወደ820 ሚሊዮን ከፍ እንደሚል ይገመታል ። [25]

አምስተኛው የኋላቀር አገሮች የወል ገጽታ ዛሬ አብዛኞቹ ኋላቀር አገሮች የቅኝ አገዛዝ ቅሪትን በማስወገድ ብሔራዊ ኤኮ ኖሚያቸውን ነፃ በሆነ መንገድ ለመገንባት የሚያደርጉት ጥረት ነው ። በዚህም መሠ ረት ለብሔራዊ ኤኮኖሚ ነፃነታቸው አስ ተማማኝ መሠረት ለመስጠት ፣ የኤኮኖሚ እድገታቸውን ለማፋጠን፣ዘመናዊ የሆኑ የኤ ኮኖሚ ዘርፎችን በመመስረት የሕዝቦቻቸ ውን የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ ።

በተለይ ለማኅበራዊ ዕድገት የቆሙ ተራ ማጅ ኃይሎች ሁሉ ኢምፔሪያሊዝም ዛሬ ድንበር ዘለል የሞኖፖል ኩባንያዎቹን በማ ስፋፋት ኋላቀር አገሮችን በብዝበዛው ጥላ ሥር ለማቆየት የሚያደርገውን ጥረት በፅኑ በመታገል ላይ ይገኛሉ ። በዚህም ረገድ ብዙ ተራማጅ የሆኑ ኋላቀር አገሮችና የሶሻ ሊስት አገሮች በጋራ የፖለቲካና የኤኮኖሚ መድረኮች ላይ ትግላቸውን ከማስተባበራ ቸውም በላይ በርዕዮተዓለም በኩልም የሚ ያደርጉት ትግል የኢምፔሪያሊዝምን ኢሰ ብአዊነት በዓለም ሰፊ ሕዝብ ፊት ክፉኛ እያጋለጠው በመምጣት ላይ ይገኛል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ኋላቀር አገሮች የመ ረጡትን የዕድገት ጐዳና የመከተል መብታ ቸውንና የዕድገታቸው ፈር ቀያሽ ራሳቸው መሆናቸውን በተግባር እያስመሰከሩ በመ ሄድ ላይ ይገኛሉ ። በዚህም መሠረት ብሔ ራዊ ነፃነታቸውን ሊያረጋግጥ በሚችል የዕ ድገት ጐዳና እየተጓዙ በዓለም አቀፍ ደረጃ

Digitized by Google

የሶሻሊስቱን ዓለም የሥራ ክፍፍል ለማጠናከር የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ናቸው ።

እስከአሁን በመጠኑም ቢሆን በኋላቀር አገሮች ውስጥ የኋላቀርነት ሂደት ከፖለቲካ ነፃነት በኋላ ለምን እንደቀጠለና እነዚህ አገሮች ለብሔራዊ የኢኮኖሚ ነፃነት መታገል ለምን እንዳስፈለጋቸው ለማሳየት ተሞክሯል ። በዚህ አጋጣሚ ግን ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ሌላ ጉዳይ ቢኖር ፣ ለብሔራዊ የኢኮኖሚ ነፃነት የሚደረገው ትግል ጥንቃቄ የሚያስፈልገው መሆኑ ነው ። ለብሔራዊ የኢኮኖሚ ነፃነት የሚደረግ ትግል በቅድሚያ የዓለም ኢኮኖሚ ነባራዊ ሁኔታዎችን ማጤንን ይጠይቃል ። ይህ ነጥብ ሊጠቀስ የቻለው ካለበቂ ምክንያት አይደለም። በዚህ መሠረታዊ ሀሳብ ግንዛቤ እማካይነት አንድ አገር ለብሔራዊ የኢኮኖሚ ነፃነት የሚያደርገውን የትግል ስትራቴጂና ታክቲክ በመቀየስ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው በመገመት ነው ። ይህንን መሠረተ ሀሳብ ካለመገንዘብ የተነሳ ብዙ የኋላቀር አገሮች የኢኮኖሚ ተመራማሪዎች እንደሚሉት የብሔራዊ ኢኮኖሚ ነፃነት ያለ ምንም ትግል ከዓለምአቀፍ የካፒታሊስቱ የሥራ ክፍፍል መላቀቅ ይቻላል ወደሚል የተሳሳተ አዝማሚያ ሊያደርስ ይቻላል ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሌላ ሊጠቀስ የሚገባውና እንደየአገሩ ተጨባጭ ሁኔታ ተጨባጭ መልስ የሚጠይቀውም ነፃና ጠንካራ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ለመመሥረት ለየትኛው የኢኮኖሚ ዘርፍ (ዘርፎች) ቅድሚያ መስጠት አለበት የሚለው ጥያቄ ነው ።

በመጨረሻም ለብሔራዊ የኢኮኖሚ ነፃነት ከሚታገሉ አገሮች ልምድ የሚከተሉትን መሠረተ ሀሳቦች በማጠቃለል ለማቅረብ ይቻላል ። እነሱም ፦

— አሁን በያዝነው ወቅት በኢኮኖሚው ረገድ ሥር ሰዶ ከሚገኘው የዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍልና እየተስፋፋ ከመጣው የተለያዩ ብሔራዊ ኢኮኖሚዎች ተደጋጋፊነት አንፃር ፣ የኢኮኖሚ ነፃነት ሲባል ሙሉ በሙሉ እራስን ከመቻል አንፃር ብቻ ሊታይ እንደማይችል መገንዘብ ፣

— ብሔራዊ የኢኮኖሚ ነፃነትን በዓለም ገበያ ላይ ከሚፈጥሩት ክስተቶች ነጥሎ መመልከት ስለማይቻል እነዚህን ክስተቶች አስቀድሞ በማጤን ተፅዕኖአቸውን በተቻለ መጠን መከላከል ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነጥብ መሆኑን ማጤን ፣

— ብሔራዊ የኢኮኖሚ ነፃነት በጋራ ስምምነቶች መሠረት ከሚፈጠር የኢኮኖሚ መተሳሰርና የግንኙነት ግዳጆች ውጪ መሆንን የሚያመለክት ሳይሆን ፣ ከአንድ አገር ሰፊ ሕዝብ መሠረታዊ ጥቅም ጋር የሚቃረኑትን አዝማሚያዎች ሁሉ በፅኑ መዋጋትና ማስወገድን የሚመለከት መሆኑን መገንዘብ ያሻል ።

ከዚህ አጠቃላይ መሠረተሃሳብ መገንዘብ እንደሚቻለው የብሔራዊ ኢኮኖሚ ነፃነት ማለት አንድ ብሔራዊ ኢኮኖሚን ከዓለም ኢኮኖሚ መነጠል ማለት አይደለም ። ለብሔራዊ የኢኮኖሚ ነፃነት የሚካሄድ ትግ ካፒታሊዝም በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ያለውን ከፍተኛ ቦታ በማሳጣት በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት መመሥረት የሚያስችል መሆን አለበት ። ከዚህም የተነሳ የኢኮኖሚ ነፃነትን እንደተፈለገው በአንድ አገር ወይንም በተወሰኑ ጥቂት አገሮች ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ ለመግለጽ አይቻልም ። የኢኮኖሚ ነፃነት ግንዛቤ የአንድ ሀገር ሕዝብ ጥረት ለዕድገት ወሳኝነት ያለው መሆኑንና ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ግንኙነት ግን ለዚህ ጥረት ድጋፍ ሰጭና አጋዥ መሆኑን መገንዘብን ያጠቃልላል ። ስለሆነም የአንድ አገር ሰፊ ሕዝብ ለብሔራዊ ነፃነቱ የሚያደርገው ትግል ነፃና ጠንካራ ፣ የዳበረ ኢኮኖሚ ለመገንባት ከሚያካሂደው ትግል ጋር የተቆራኘ መሆኑን በመረዳት ትግሉን ማፋፋምና በዓለምአቀፍ ደረጃም ይህንን ዓላማውን ከሚደግፉለት ሶሻሊስትና ተራማጅ አገሮች ጋር በፅኑ መሠረት ላይ የተገነባ ትብብርና ግንኙነት ማዳበር የግድ አስፈላጊ ይሆናል ማለት ነው ።

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻ

1. J.R. Hicks, *Essays in World Economy* (Oxford: Chardon Press, 1954), p. 30.
2. W. Brand, *The Struggle For Higher Standard of Living,* (New York: Free Press of Glencoe, 1956), p. 26.
3. B. J. Cohen: *The Question on Imperialism, The Poltical Economy of Dominance and Dependence,* (New York: Macmillan Press, 1976), p. 230.
4. W. A. Lewis, *The Theory of Economic Growth, (Homewood*: Harper and Rover, 1955), p. 46.
5. R. W. Tucker, *The Radical Left and American Foreign Policy,* (New York: Hopkins Press, 1971), p. 143.
6. A. G. Frank, *Underdevelopment cr Revolution* (New York: Monthly Review Press, 1969), p. 3 and 11.
7. R. Strausz, *The Idea of Colonialism,* (London: Atlantic Books, 1968), p. 4.
8. Vasily Vakmrushev, *Neocolonialism Methods and Manoeuvre,* (Moscow: Progress Publishers, 1973), p. 47.
9. Clive Y. Thomas, *Dependence and Transformation to Socialism,* (New York: Monthly Review Press, 1974), p. 14.
10. J. Nye Jr, *Multinatinal Corporation in World Politics,* Vol. 53, No. 1, (New York: 1976), p. 170.
11. Ion Rosu Hamzescu,*Training National Personnel in the Developing Countries,* (Criovia, 1978), p. 85; (Rumanian ed.).
12. *Ibid.*
13. *Ibid.*, p. 88.
14. Gerry Helleiner, *The Role of Multi-National Corporations in The Less Developing Countries,* (New York: Monthly Review Press, 1975), p. 165.
15. *The African Communist,* No. 88, First Quarter 1982, p. 58.
16. *Ibid.*, p. 59.
17. *International Affairs,* No. 3, 1983, p. 31.
18. *Hand Book of International Trade and Development Statistics;* (New York: 1980), p. 2 and 3.
19. *Ibid.*
20. *Ibid.*, p.3.
21. *International Affairs,* No. 3, 1983, p. 21.
22. *Ibid.*, No. 5, 1983, p. 62.
23. *Ibid.*, No. 3, 1983, p. 22.
24. Dr. Sorica Sava, *Ways and Strategies of Eradicating Underdevelopment,* (Bucharest: 1979), p. 35. (Rumanian ed.).
25. *Ibid.*, p. 38.

Digitized by Google

ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ

ጌታቸው ርበሌ

መንግሥታት እንደ ሀገር ውስጥ ፖሊሲ ሁሉ በውጭውም ዓለም የሚያራምዱት ፖሊሲ አላቸው። እንደ ማንኛውም ክስተት የመንግሥታት የውጭ ፖሊሲ ከቀላል ወደ ውስብስብነት እያደገ መጥቷል ። በጥንታዊቷ ግሪክ ፣ ሮምና በመካከለኛው ዘመን የአውሮፓ ፊውዳል መንግሥታት ያራምዱት የነበረው የውጭ ፖሊሲ የዛሬዎቹ ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ከሚያራምዱት በውስብስብነቱም ሆነ በዕድገት ደረጃው በጣም ይለያል ። ይሁንና ሁሉንም የሚገናኛቸው አንድ የጋራ ባሕርይ ፣ ከመደብ ኅብረተሰብ መፈጠር ጀምሮ በትርፊ ከመለያየታቸው ባሻገር ፣ የብዝበዛን ሥርዓት በተለያየ መልኩ የሚያጠናክሩና ለዓላማዎቹ ተገባራዊነት የሚያገለግሉ የበዝባዥ መደቦች የውጭ ፖሊሲ መሆናቸው ነው ። ብዝበዛ በሠፈነበት ስልተ ምርትና የበዝባዥ መደቦች የበላይ ገዥነት በገነነበት ኅብረተሰብ በሀገር ውስጥም ይሁን በውጭ የሚኖረው ፖሊሲ ከሠርቶ አደሩ ሕዝብ መሠረታዊ ጥቅም ጋር ይጻረራል ። የውጭ ፖሊሲን ከተወሰነ ስልተ ምርትና በሥልጣን ላይ ካለው መደብ ጥቅም ውጭ በትክክል መረዳት አይቻልም ።

የገዥ መደቦች የውጭ ፖሊሲ ከውስጥ ፖሊሲ ጋር ምንገዜም ይያያዛል ። በመሠረቱ ሁለቱም ፖሊሲዎች በሥልጣን ላይ ያለውን መደብ ጥቅም ለማስከበር የሚቀየሱና ለዚህ መደብ ጥቅም የቆሙ ናቸው ።

ይሁንና የመደብ ትግል በዓለምአቀፍ ግንኙነት የሚገለጸው ከሀገር ውስጥ ለየት ባለ ትርፊ በመሆኑ በሀገር ውስጥ የምርት መገልገያ መሣሪያዎች ባለቤት በሆኑትና ባልሆኑት ፣ ጨቋኝና ተጨቋኝ መደቦች መካከል ያለው ዓይነት ቀጥተኛ ትግል በውጭ ፖሊሲ ውስጥ በቀጥታ አይንጸባረቅም ። የውጭን ፖሊሲ የሚያራምዱት መደቦች ተራማጅም ይሁኑ አድኃሪ በየሀገሩ በሥልጣን ላይ ያሉ ናቸው ። ስለሆነም ምንም እንኳን በዓለም አቀፍና በብሔራዊ ምክንያቶች የውጭና የውስጥ ፖሊሲ በትርፊ ቢለያዩም

Digitized by Google



የኢምፔሪያሊዝም ጦረኝነት በሰላም ወዳድ ኃይሎች የተቀነባበረ ትግል ይገታል ።
(« ሶሺያሊዝም ፣ ንድፈሃሳብና ተግባር » ከተሰኘ የሶቭዮት ሕብረት መጽሔት የተገኘ)

በይዘት አንድነት አላቸው፡፡የቡርዧውን መ
ደብ የውጭ ፖሊሲ መርሆዎች ብዝበዛንና
ጭቆናን ለማራመድ ካለው ዓላማ ነጥሎ
ማየት ትክክል አይሆንም ፡፡ የሠራተኛው
መደብም የውጭ ፖሊሲ ሠርቶ አደሮች
የበለጸገ ኑሮ እንዲኖሩ ካለው ዓላማ ጋር
ይጣጣማል ፡፡ ይህም በመሆኑ ዲያሌክቲ
ካዊ አንድነት ያላቸውን ሁለቱን ፖሊሲ
ዎች ምንም ግንኙነት እንደሌላቸው በመቁ
ጠር ነጣጥሎ ማቅረብ በጣም የተሳሳተ አቀ
ራረብ ይሆናል ፡፡ [1]

አርጌው ስልተምርት በአዲስ ሲለወጥ
የውጭ ፖሊሲም መሠረታዊ ለውጥ ያሳ
ያል ፡፡ ማርክስና ኤንግልስ የውጭ ፖሊሲን
በዓይነት መለወጥን ከወዝአደሩ አብዮትና
ከሶሻሊስት ኅብረተሰብ መመሥረት ጋር
በቀጥታ አያይዘውታል ፡፡ በኮሚኒስት ማኒ
ፌስቶ ውስጥ የሰው በሰው መበዝበዝ
ሲቀር የአንዱም ሀገር በሌላው ሀገር መበ
ዝበዝ ይቀራል ፤ የመደብ ልዩነትና ቅራኔ
ሲጠፉ ፣ በሀገሮች መካከል ያለውም ጥላቻ
ይጠፋል ያሉት ይኸንኑ ለማመልከት
ነበር ፡፡ [2]

የማርክስና የኤንግልስን አስተምህሮ በመ
ከተል ሶሻሊዝምን የገነቡና በመገንባት
ላይ የሚገኙ ሀገሮች የሚያራምዱት ሌኒ
ናዊ የውጭ ፖሊሲ በ20ኛው ምዕት ዓመት
ታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት ድል
ሲያደርግ ለመጀመሪያ ጊዜ በሌኒን መሪ
ነት በሶቭዬት ሩሲያ ተግባራዊ የሆነ
ፖሊሲ ነው ፡፡ ርዕዮተዓለማዊና ንድፈ ሃሳ
ባዊ መሠረቱ በማርክሳዊ ሌኒናዊ አስ
ተምህሮ ላይ የተገነባው ሌኒናዊ የውጭ
ፖሊሲ በዓከም ፣ በብሔራዊ ደረጃና በመ
ደቦች መካከል ያለውን ግንኙነትና የኃ
ይል አሠላለፍ በመገምገም ፣ በተወሰነ ታሪ
ካዊ ዘመን የሚታየውን ልዩ ሁኔታ በመገን
ዘብ በዓለም ላይ አዲስ የተፈጠሩትን ለው
ጦችና አዳዲስ ነባራዊ ሁኔታዎችን በመረ
ዳት ፣ የኅብረተሰብ ዕድገት ሕገጋት ዕውቀ
ትን በመጠቀም ፣ ለልዩ ልዩ የዓለም አቀፍ
ችግሮች ተጨባጭ መፍትሔዎችን የሚያቀ
ርብ ፖሊሲ ነው ፡፡

ሠራተኛው መደብ በዓላማውና በግቦቹ
ከቡርዧው መደብ ፖሊሲ ጋር የማይገናኝ፥
ነፃ የሆነ የራሱ የውጭ ፖሊሲ ያስፈልጉ
ታል ፡፡ ሰብአዊነት የሠፈነበት ዓለም ለማነ
ጽ ዓለም አቀፋዊ ትግሉ የሚሠምረው በው
ጭ ፖሊሲም በኩል የቡርዧውን ፖሊሲና
ዲፕሎማሲ በመታገል የራሱ ፖሊሲ በአሸ
ናፊነት እንዲወጣ ሲያደርግ ነው ፡፡ ገና በ19
ነኛው ምዕት ዓመት ካርል ማርክስ የዓ
ለም ሠራተኞችን ማኅበር ሲመሠርት ባደ
ረገው የመክፈቻ ንግግር የሠራተኛው መደ
ብ በአስቸኳይ የራሱ የሆነ ዓለም አቀፍ
ፖሊሲ እንዲኖረው በማስገንዘብ በዚህ
አኳያ የሠራተኛውን መደብ ግዴታ አመል
ክቷል ፡፡ ሠርቶአደሮች የዓለምን ፖለቲካ
ምስጢር ማወቅ የየመንግሥታቸውን የዲ
ፕሎማቲክ ድርጊቶች መከታተልና በሚቻ
ላቸው ሁሉ የበዝባዥ መደቦችን የዲፕሎማ
ቲክ ድርጊቶችን መታገል ይኖርባቸዋል ፡፡
የመደብ ጥቅማቸውን ለሚጠበቀው የውጭ
ፖሊሲ የሚያደርጉት ትግል ለተሟላ ነፃነታ
ቸው ከሚያደርጉት ትግል ጋር በጥብቅ
የተቆራኘ ነው ፡፡ [3]

ከዚህ መሠረታዊ ሃሳብ በመነሳት በማ
ናቸውም ወቅት በሠራተኛው መደብ ጥቅም
ላይ የተመሠረተው ወገናዊነት ያለው መደ
ባዊ የሆነው ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ በባሕር
ይው ሳይንሳዊና አብዮታዊ ነው ፡፡ ይህ
አብዮታዊ ባሕርይ የሠራተኛው መደብ
ካለው ታሪካዊ ተልዕኮ ይመነጫል ፡፡ በመ
ሠረቱ የሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ ተግባ
ሮች በዓለም ደረጃ የሶሻሊዝምን ድሎች
መጠበቅ፥ የኢምፔሪያሊዝምን ወረራና ሴራ
መቋቋም ፣ ለሶሻሊዝምና ለኮሚኒዝም አመ
ች የሆኑ ውጫዊ ሁኔታዎችን ማመቻቸት
ነው ፡፡ በአንድ ሀገር ውስጥ ሕልውና ያገኘ
ውን የሠርቶአደሮች መንግሥት መንከባ
ከብ በዚህ ሀገር ውስጥ ለሚገኘው ሠርቶ

Digitized by Google

አደር ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ኮሚኒስት
ንቅናቄ እጅግ በጣም አስፈላጊ ይሆናል ።
ከዚህ አቋም በመነሳት በ1918 ሌኒን በሶ
ቭዬት ሩስያ በቦልሼቪክ ፓርቲ ውስጥ በተ
ነሣ ክርክር የተለያየ አቋም በሚንጸባረቅ
በት ወቅት ለውጭ ፖሊሲ ጉዳዮች መፍ
ትሔ ማግኘት በሩስያ የተጀመረውን የሶሻ
ሊስት አብዮት ከማጠናከር አኳያ መታየት
እንዳለበት ተናግሯል ። [4]

ለዚህ የሌኒን አባባል ተጨባጭ ትርጉም
የሚሰጠው ማርክሳዊ የውጭ ፖሊሲ የኮ
ሚኒዝምን መርሆች በመከተል አብዮታዊ
ዓላማዎችን ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር አገ
ናዝቦ የሚያራምድ የዓለም አብዮታዊ ኃይሎ
ችን የሚያስተባብር መሣሪያም በመሆኑ
በባሕርይው ፍጹም ዓለምአቀፋዊ ነው ።

በታሪክ ውስጥ በዝባዥ መደቦች ጥቅ
ማቸውን ለማስጠበቅ ካካሄድዋቸውና ከሚ
ያካሂዱዋቸው አድኃሪ ጦርነቶች ሠርቶ
አደሮች የሚተርፋቸው እልቂትና ሰቆቃ
ብቻ ነው ። የሠርቶአደሮች ዓላማ የኢኮ
ኖሚ ድህነትና የፖለቲካ ጭቆና የነገ
ሠበት ፣ የጦርነት ፣ የዕልቂትና የሰቆቃ ዓለ
ም ሳይሆን ዓለም አቀፋዊ መርሁ ሰላም የሆ
ነበት የበለጸገና እኩልነት የሰፈነበት አዲስ
ዓለም መመሥረት ነው ። [5] ለዚህ ዓይነት
ዓለም ዕውን መሆን የዓለም ሠርቶአደሮች
ጦርነትን እንዲቃወሙና ለሰላም እንዲታ
ገሉ ማነሳሳት በሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ ከፍ
ተኛውን ቦታ ይይዛል። «ሁሉንም ነገር ለሰ
ው ሲባል ፣ ሁሉንም ነገር ለሰው » የሚለ
ውን መፈክር በማራመድ ለሰላም የቆመ
በመሆኑ ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ በባሕርይ
ው ሰብአዊነት ያለው የሰላም ፖሊሲ ነው።
ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በ1917 በተካ
ሄደው ታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮ
ት የተመሠረተው የሶቭዬት መንግሥት
ለሰላም መስፈን የወሰደው ተጨባጭ ርም
ጃ ነው ።

በቀድሞው ሩስያ የሠራተኞችና ገበሬዎ
ች መንግሥት በተመሠረተ ማግሥት በወጣ
ው «የሰላም አዋጅ» ውስጥ እንደተገለጸው
በውጭ ፖሊሲ አኳያ ከተወሰዱት ርምጃ
ዎች አንዱ በወቅቱ ዓለምን ለመቀራመት
ኢምፔሪያሊስቶች በጫሩት በአንደኛው
የዓለም ጦርነት ውስጥ ይማገዱ ለነበሩት
ሕዝቦችና በጦርነቱ ይሳተፉ ለነበሩ መንግሥ
ታት ትክክለኛና ዲሞክራሲያዊ የሆነ አስ
ቸኳይ የሰላም ውይይት እንዲደረግ ጥሪ ማቅ
ረብ ነበር ። [6] እዚህ ላይ ትልቁ ቁምነገር ሌኒ
ናዊ የውጭ ፖሊሲ ተግባራዊመሆን ከጀመረ
በት ጊዜ አንስቶ የሰላም ፖሊሲ በማራመድ
ላይ የተመሠረተ ለሕዝቦች ዕልቂትና ባር
ነት የሚደረገው ጦርነት በሰው ልጅ ላይ የሚ
ፈጸም እጅግ ከፍተኛ ወንጀል መሆኑን በማስ
ገንዘብ ለትክክለኛና ዲሞክራሲያዊ ሰላም
ለትግል ሠርቶአደሮችን በማነሳሳት፣ በተለይ
ም ደግሞ ጦርነትን ለመደምሰስ፣ ብዝበዛንና
ባርነትን ለማስወገድ በሚደረገው አጠቃላ
ይ ካለምአቀፍ ትግል ውስጥ የግንባር ቀደም
ትነት ሚና በመጫወት ለዕድገትና ለሶሻሊ
ዝም የላቀ አስተዋጽኦ ማበረከቱ ነው ። [7]
በዚህ መሠረት በጊዜው ይካሄድ ‹በነበረው
የአንደኛው የዓለም ጦርነት የእንግሊዝ ፣ የፈ
ረንሳይና የጀርመን ሠራተኞች በሁለተኛው
ኢንተርናሽናል አድርባይ መሪዎች ማንአህ
ሎኝነት ተበክለው ስለነበር የሰላሙ አዋጅ
በተለይ ለተጠቀሱት የሶስቱ ሀገሮች ሠርቶ
አደሮች ልዩ ጥሪ አድርጓል ። [8] ይህ
የሰላም አዋጅ በአንድ በኩል ለሰላም
እንዲታገሉ በጦርነቱ ተካፋይ ለነበሩ መን
ግሥታትና ሕዝቦች ጥሪ ሲያቀርብ በሌላ
በኩል ከፍተኛ የንቃትና የድርጅት ደረጃ
ላይ የደረሱ የዓለም ሠርቶአደሮች ለሰ
ላም የሚቻላቸውን ሁሉ እንዲያደርጉ አስ
ተምሯል ። ከዚህ መረዳት የሚቻለው የዓ
ለም ሠርቶአደሮች ሳይተባበሩ ጦርነትን
መግታት ፣ ማጥፋትና ሰላምን መጠበቅ የማ
ይቻል መሆኑን ነው ። እንዲሁም የሰላም

Digitized by Google

ሙሉ ዋስትና የሚረጋገጠው በሠርቶ አደሮች አንድነት ጦርነትን ማጥፋት ሲቻል መሆኑ ነው ። ይህንን ሐቅ ሲያስገነዝብ ግርክስ «የሁሉም ሀገር ሠርቶ አደሮች አንድነት በመጨረሻ ላይ ጦርነትን ያጠፋል» ብሏል።[9]

በዛሬው የዓለም ሁኔታ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ አብዮት ግምጋሚ የተነሳ የዓለም ጦርነት ቢቀሰቀስ አሸናፊም ተሸናፊም አይኖርም። ስለሆነም አጠቃላይ የሰውን ልጅ ዘር ከምድርገጽ ሊያጠፋ የሚችል ጦርነትን ለመግታትና ለዓለም ሰላምና ደህንነት መጠበቅ መታገል ከምንገዜውም ይበልጥ አስፈላጊ ሆኗል ። ከዚህ አንፃር የሠራተኛው መደብ ብሔራዊ የመደብ ፍላጐት ካጠቃላይ የማኅበራዊ ዕድገት ፍላጐት ጋር መጣመር ብቻ ሳይሆን በሁለቱ መካከል ያለው መተሳሰር እየጐላ መጥቷል ። ሌኒን በእነዚህ ፍላጐቶች መካከል ያለውን መተሳሰር ሲያብራራ ፣ «ከማርክሲዝም መሠረተ ሀሳቦች አኳያ የማኅበራዊ ዕድገት ፍላጐቶች ከመዝአደሩ ፍላጐቶች በላይ ናቸው ። የሠራተኛው መደብ እንቅስቃሴ ፍላጐቶች በአጠቃላይ ከተለያዩ የሠራተኛ ክፍሎች ወይም ከተለያዩ የእንቅስቃሴው ደረጃዎች በላይ ናቸው » [10] በማለት አስገንዝቧል ።

በአጭሩ ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ ሰብአዊነትን የሚያራምድ የሰላም ፖሊሲ ነው ። በዝባዥ መደቦችን ከፖለቲካ ሥልጣናቸው በማስወገድ የሠርቶአደሩን ሕዝብ ጥቅም የሚወክል መንግሥት የሚያራምደው ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ ዲሞክራሲያዊ ነው ። ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ በዓለምና በሀገር አቀፍ ደረጃ የሠርቶ አደሮችን ጥቅም በመጻረር ለዝርፊያ ፣ ለብጥብጥና ለተጽዕኖ ፣ የሌሎችን ግዛት ለመቁረስ የሚያካሂደው የምስጢር ዲፕሎማሲ አይኖርም ። ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ ጉዳዮችን ከሕዝብ በመሸሸግ ፣ ሕዝብን በማገለል ነገሮችን በምስጢር በመያዝ አያምንም ። ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ ሕዝብ በፖለቲካ ሲነቃ ፣ ሁሉን ነገር ሲያውቅ ፣ በሁሉም ነገር ሀሳብ መስጠትና ሁሉንም ነገር በንቃት ማድረግ ሲችል የመንግሥት የውጭ ፖሊሲ ጠንካራ ይሆናል የሚል አቋም አለው ።[11] ከዚህ ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ አቋም በመነሳት ሠርቶ አደሩ ህዝብ የውጭ ፖሊሲ ጉዳዮችን ከሠርቶ አደሩ ሕዝብ በመደበቅ በውጭ ፖሊሲ ጉዳዮች የሠርቶ አደሮችን ተሳትፎ አያስወግድም ። በተቃራኒው ተሳትፎአቸው እንዲበረታታና እንዲስፋፋ ያደርጋል ። በሌላ በኩል ከሌሎች ሀገሮች ጋር ለዝርፊያ ፣ ለብጥብጥና ለግዛት መስፋፋት ስምምነቶችን በምስጢር መፈራረም ለሌኒኒስት የውጭ ፖሊሲ ባዕድ ነው ። ይህን ዓላማ መሠረት በማድረግ ካፒታሊስቶችና የመሬት ከበርቴዎች ቀደም ሲል የተፈራረሙትን በዕኩልነት ላይ ያልተመሠረቱና ባርነትን የሚጋብዙ ስምምነቶችን ያፈርሳል ። ለዚህም በሌኒን የተመራው የሶቭዬት መንግሥት የሩሲያ የዘውድ አገዛዝና የቡርዧው መንግሥት የጐረቤት ሀገሮችን ለመዝረፍና ቁጥጥር ሥር ለማዋል የተፈራረመውን የምስጢር ስምምነቶች ለመላው ሩስያ ሕዝብና ለዓለም ሕዝብ በማጋለጥ ማፍረሱ እንደምሳሌ ሊቀርብ ይችላል ። ይህን ዲሞክራሲያዊ ሌኒናዊ የሆነ የውጭ ፖሊሲ ገጽታ በ1917 በሌኒን የተነደፈው የሰላም አዋጅ ሲያትት ፣ «መንግሥት በምስጢር የሚካሄደውን ዲፕሎማሲ ያስወግዳል ፣ በበኩሉም ማንኛውንም የሰላም ድርድሮችን በግልጽ መላው ሕዝብም በሚያውቀው መንገድ ለማካሔድ ያለውን ቁርጥ ሐሳብ ይገልጻል » [12] ይላል ።

የሌኒኒስት የውጭ ፖሊሲ ዲሞክራሲያዊ ገጽታ በጦርነትና በሰላም ጉዳዮች ሠርቶአደሮች ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆን በመርዳትም ይገለጻል።የጦርነትና የሰላም ጉዳይ ለመንግሥታት የሚተው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በማናቸውም ማኅበራዊ ሥርዓት ውስጥ የሚገኙትን ሕዝቦች ጥቅም የሚነካ በመሆኑ በቀጥታ የሕዝቦችን ተሳትፎ ይጠይቃል ። ይህን በሚገባ የተገነዘበው የሶቭዬት ሩስያ መንግሥት በውጭ ፖሊሲ ለመንግሥታትና ለሕዝቦች

Digitized by Google

ብጋራ ጥሪውን ሲያቀርብ ፣ በተለይ ደግሞ የጦርነት መወገድንና የሰላም መረጋጋትን በሚመለከት ሕዝቦች ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በጥብቅ አስገንዝቧል ። [13]

በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የብሔሮች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠልና የራስን ነፃ መንግሥት የመመሥረት መብት የቅኝ ግዛት ሕዝቦችንም የሚያቅፍ ጥያቄ ሆኗል ። አብዮታውያን የብሔሮችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት በመርህ ሲቀበሉ እንደአመቺነቱ በተግባር እንዲተረጉም ከሠርቶአደሩ ሕዝብ ጥቅም አኳያ ይመረምራሉ ። ማርክሳዊ ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ በቅኝ አገዛዝ የባርነት ቀንበር ሥር የሚማቅቁ ሕዝቦች የቅኝ አገዛዝን ሥርዓት በማስወገድ የራሳቸውን ነፃ መንግሥታት እንዲመሠርቱ ያለማወላወል በተጨባጭ ይደግፋል ። ይህ ፖሊሲ የሌሎች አገሮች ግዛቶችን በወረራ መያዝን ፣ በመንግሥታት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባትን ፣ የሁሉንም ሀገሮች የግዛት አንድነትንና ብሔራዊ ሕልውና መድፈርን በጥብቅ ይቃወማል ።

በማርክስና ኤንግልስ መሠረታዊ የሳይንሳዊ ኮሚኒዝም መርሆች ላይ የተገነባውና በሌኒን የተቀመረው የሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ በወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነትና በሰላም አብሮ መኖር መርሆች ላይ የተመሠረተ ነው ። እነዚህን ሁለቱን የሌኒኒስት የውጭ ፖሊሲ ዋና ዋና መርሆዎች በመጠኑም ቢሆን ለየብቻ መዳሰስ ጠቃሚ ይሆናል ።

ወዛደራዊ ዓለምአቀፋዊነት

የሠራተኛው መደብ እንቅስቃሴ በባሕርይው ዓለምአቀፋዊ ነው ። ፍሬድሪክ ኤንግልስ በዓለም ፖለቲካ የሠራተኛው መደብ ፍላጐት ተመሳሳይ የሚሆንበትን ምክንያት ሲገልፅ ፣ «በሥራ ኃይልና በካፒታል መካከል ያሉት ግንኙነቶች በየትም ቦታ ተመሳሳይ ስለሆኑና በተበዝባዥ መደቦች ላይ የበዝባዥ መደቦች የፖለቲካ የበላይነት በየትም ቦታ ስለሚኖር ፣ የወዝ አደሩ ፖሊሲ መርሆች ግቦች በየትም ቦታ ተመሳሳይ ይሆናሉ ! » ብሎ ነበር ። [14]

ካፒታል ዓለምአቀፋዊ በመሆኑ ሠርቶአደሮች በአንድነት እንዲታገሉት ነባራዊው ሁኔታ ያስገድዳቸዋል ። በአንድነት ከመታገል ውጭ ግን ተበታትነው በከንቱ የሚያደርጉት መፍጨርጨር አይሳካም ። ይህን አስመልክቶ ሌኒን በማያሻማ አኳኋን ሲገልጽ ፣ « የሁሉም ሀገር ሠራተኞች ለነፃነታቸው የሚካሄዱት ትግል የሚሳካው ሠራተኞች በአንድነት ዓለም አቀፍ ካፒታልን ሲታገሉ ብቻ ነው » [15] ማለቱ ይታወሳል ።

በተጨማሪ ከኢምፔሪያሊዝም የጭቆና ቀንበር ለመላቀቅ የሚታገሉ ሕዝቦች ትግላቸው ዓለምአቀፋዊ ባሕርይ አለው ። ስለዚህ የዛሬው ዓለምአቀፍ ትግል በካፒታሊስት ሀገሮች ውስጥ ከሚገኙ ተራማጅ ኃይሎችና ኢምፔሪያሊዝምን በልዩ ልዩ ቅርጽ ከሚታገሉ ጭቁን ሕዝቦች ጋር መተባበርን ጠይቋል ። ሌኒኒስት የውጭ ፖሊሲ ይህንን በተግባር ያራምዳል ። ሌኒን ይህንኑ ሲያረጋግጥ « የወዝ አደሩ የውጭ ፖሊሲ በሁሉም ኢምፔሪያሊስቶች ላይ በዳበሩ ሀገሮች ካሉ አብዮታውያንና ከሁሉም ተጨቋኝ ብሔሮች ጋር አንድነት መፍጠር ነው » ብሏል ። [16]

በዓለም ላይ ተስፋፍቶ የሚገኘው የኮሚኒስት እንቅስቃሴና ሌሎችም የዚሁ እንቅስቃሴ አካል የሆኑ የአርነት ትግሎች ከሶ

ሻሊስት ሀገሮች ጋር ባንድ ላይ የአጠቃላይ የዓለም አብዮታዊ ሂደት ኃይሎች ናቸው ። ፀረ ኢምፔሪያሊስት አቋም ያላቸው ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ከዓለምአቀፍ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ተነጥለው መታየት እንደሌለባቸውና በዓለም አቀፍ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ላይ አቋም ሲወስድ ከዚህ ሐቅ መነሳት አስፈላጊ መሆኑን ሌኒኒዝም ያስገነዝባል ። የሶሻሊስት አብዮት መታየት ያለበት በእያንዳንዱ ሀገር ውስጥ ያሉ ሠርቶአደሮች ቡርዧውን ከሥልጣን ለማስወገድ ከሚያደርጉት ትግል አኳያ ብቻ ሳይሆን በኢምፔሪያሊዝም የተጨቆኑ ግዛቶችና ሀገሮች ፣ ጥገኛ ሀገሮች በመላ በዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ላይ ከሚያደርጉት ትግል አኳያም ነው ።[17] በዓለምአቀፍ ደረጃ ዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝምን የመታገሉ ትክክለኛ ፖሊሲ የሠርቶአደሩ ሕዝብ የበላይነት ከተረጋገጠባቸው ሶሻሊስት ሀገሮች ጋር መተባበርን አጥብቆ ይጠይቃል ። የብሔራዊ አርነት አብዮት በማካሄድ ላይ የሚገኙ ሕዝቦች ለአብዮታቸው ዘላቂነትና ድል ማድረግ ብቸኛው ዓለም አቀፍ ፖሊሲ ከዓለም ተራማጅ ኃይሎች ጋር በአጠቃላይና የሠርቶ አደሮች የበላይ ገዥነት ከተረጋገጠባቸው መንግሥታት ጋር በተለይ ግንኙነትንና ትብብርን በቀጥታ ማዳበር ይሆናል ። ሌኒን ይህንን አስመልክቶ ኅዳር 22/1919 በምሥራቅ ሕዝቦች የመላ ሩስያ ኮሚኒስት ድርጅቶች ሁለተኛው ጉባኤ ላይ የሚከተለውን ብሎ ነበር ፤ «በዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ላይ የሚካሄደው የምሥራቅ ሕዝቦች አብዮታዊ እንቅስቃሴ በሚገባ ሊያድግ የሚችለው . . . ከሶቬየት ኅብረት ሪፐብሊክ አብዮታዊ ትግል ጋር በቀጥታ በመተባበር ብቻ ነው ።»[18]

ከሶሻሊስት መንግሥታት ፣ በካፒታሊስት ሀገሮች ካሉ ተራማጅ ሃይሎች ፣ ቅኝ አገዛዝና ኢምፔሪያሊዝምን ከሚታገሉ ጭቁን ሕዝቦች ጋር በተግባር መተባበር በሌላ በኩል አብዮታዊ ዓላማዎችን በማራመድ ረገድ ከካፒታሊስቶችና ከመሬት ከበርቴዎች ፖሊሲ ጋር መቆራረጥን የግድ ያደርገዋል ። ይልቁንም ደግሞ አብዮት ለሚያካሂድ ሀገር አብዮቱን ለመጠበቅ አድሃሪ ሃይሎች ከሚያራምዱት የውጭ ፖሊሲ ጋር ያለ ማወላወል ትግል ማካሄድ ያሻል ።[19] ከዚህ ውጭ የሌኒኒስት የውጭ ፖሊሲ አራምዳለሁ ማለት ተምኔታዊነት ይሆናል ።

ዛሬ ወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ዳብር በሶሻሊስት መንግሥታት መካከል ላለው ግንኙነት የሚያገለግል ፖሊሲም ሆኗል ። ወዝአደራዊ አለምአቀፋዊነትን መሠረት በማድረግ በኤኮኖሚ ፣ በፖለቲካ ሥርዓትና በሚመሩበት ርዕዮተዓለም የጋራ አንድነት ባላቸው ሶሻሊስት መንግሥታት መካከል የሚኖረው ግንኙነት በሚከተሉት ዲሞክራቲክ መርሆች ላይ የተመሠረተ ነው ፤

— የእያንዳንዱ ሶሻሊስት ማኅበረሰብ አካል እኩልነትና ነፃነት ፣

— የግዛት አንድነት ፣ ብሔራዊ ነፃነትና ብሔራዊ ሕልውናን ማክበር ፣

— በሌላው የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት ፣

— የጋራ ጠቀሜታ ያለውን ትብብር ማራመድ ፣

— ወንድማዊ የጋራ ተራድኦ ማድረግ ፣

— የሶሻሊስት ሀገሮች መጠናከርና አንድነት ፣

በሶሻሊስት መንግሥታት መካከል ያሉ ግንኙነቶች በሶሻሊስት ዓለም አቀፋዊነት መርሀ መሠረት በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ሶሻሊስት መንግሥታት መካከል በስምምነቶች መፈራረም ቅርፅ ሊከሰት ይችላል ። ለምሳሌ የወዳጅነትና ትብብር ስምምነቶች እንዲሁም ለእያንዳንዱ ሶሻሊስት ሀገር የሶሻሊስት ኅብረተሰብ ግንባታ መሳካትና በጋራም ለሶሻሊስት ሀገሮች በሶሻሊዝምና

Digitized by Google

በኮሚኒዝም ጉዳና ወደፊት መገስገስ እንዲያገዝ የጋራ የኢኮኖሚ ተራድኦ ድርጅትን የማቋቋም ቅርፅም ሊይዝ ይችላል ። የሶሻሊዝምን ድሎች ለመጠበቅና የኢምፔሪያሊዝምን ወረራ ለመግታት በወታደራዊ በኩል የጋራ የመከላከያ ኃይልን የማደራጀት ቅርጽም ሊይዝ ይችላል ። በተጨማሪ፣ ወቅታዊ የሆኑ አሳሳቢ የዓለም ጉዳዮች ላይ ለዓለም አብዮታዊ ሂደት በሚያመች ሁኔታ የውጭ ፖሊሲ አቋሞችን የመውሰድ ቅርፅም ሊይዝ ይችላል ።

በውጭ ፖሊሲ ወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት በተግባር ሲተረጎም የሚጠይቃቸው ሁለት አበይትና የማይነጣጠሉ ጉዳዮች አሉ ። እነርሱም « አንደኛ ፣ በማንኛውም ሀገር ውስጥ የወዝአደሩ ፍላጎቶች በመላው ዓለም ደረጃ ላለው የወዝአደሩ ትግል ፍላጎቶች ተገዥ መሆንና ሁለተኛ ፣ በቡርዧ ላይ ድልን ያገኘው ሀገር ዓለም አቀፍ ካፒታልን ለመጣል ከፍተኛ ብሔራዊ መስዋዕትነት ለማድረግ መቻልና ፈቃደኛ መሆን ናቸው ። » [20]

በእርግጥ ብሔራዊ መሥዋዕትነት ማድረግ ብሔራዊ ጥቅምን መዘንጋት አይሆንም ። የሠርቶ አደሮች ብሔራዊ ጥቅም የሚጠበቀው ዓለምአቀፋዊ ጥቅማቸው እስከ ተጠበቀ ድረስ ይሆናል ። ለሠራተኛው መደብ በብሔራዊ ጥቅምና በዓለም አቀፋዊ ጥቅም መካከል ልዩነቶች ቢኖሩም ፣ ሁለቱ የሚጻረሩ ሳይሆኑ የሚደጋገፉ ፣ የአንዱ ጥቅም በትክክል መጠበቅ የሌላውን ጥቅም ማሟላት የሚጠይቅ ነው ። ሁለቱንም በሚገባ አቀናጅቶ ተግባራዊ ማድረጉ ዓለም አቀፋዊም ሀገር ወዳድም ያደርጋል ። ይህ ደግሞ ለአንድ ሀገር ሠርቶ አደሮች ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሠርቶአደሮች ብልጽግናና ነፃነት ሙሉ ኃላፊነት መሸከምን ያመለክታል ። የኮሚኒስቶችን ኃላፊነት በማስመልከት በ1969 ሞስኮ ውስጥ የተካሄደው የዓለም ኮሚኒስቶችና ሠራተኛ ፓርቲዎች ስብሰባ ያጠናቀረው ሰነድ የሚከተለውን አስፍሯል ።

> እያንዳንዱ ኮሚኒስት ፓርቲ በድርጊቱ ለራሱ ሠራተኛ መደብና ሕዝብ ኃላፊ እንደሆነ ሁሉ ለዓለም አቀፍ ሠራተኛ መደብም ኃላፊ ነው ። የእያንዳንዱ ኮሚኒስትና ሠራተኛ ፓርቲ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ግደታዎች የማይነጣጠሉ ናቸው ። ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ሀገር ወዳዶችም ፣ ዓለም አቀፋውያንም ናቸው ። እነርሱ ብሔራዊ ጠባብነትንና ብሔራዊ ጥቅሞችን መካድ ወይም ዝቅ ማድረግና ለአምባገነንነት መጣርን ይቃወማሉ ። [21]

እዚህ ላይ ትልቁ ነገር በውጭ ፖሊሲ በብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ጥቅሞች መካከል ያለውን ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት በሚገባ በማጤን ከዓለም አብዮታዊ ኃይሎች ጋር አንድነትን አጠናክር በዓለም አብዮታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተገቢውን ሚና መጫወት መቻል ነው ።

በሰላም አብሮ መኖር

ከጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት ወዲህ ተግባራዊ በመሆን ላይ የሚገኘው በሰላም አብሮ የመኖር ሌኒናዊ ፖሊሲ በየጊዜው ተቀባይነትና ተሰሚነት እያገኘ መጥቷል ። በተባበሩት መንግሥታት ፣ በገለልተኛ ሀገሮች ንቅናቄና በሌሎች ትላልቅ ዓለም አቀፍ ዶክሜንቶች ውስጥ መንግሥታት በሰላም አብረው እንዲኖሩና እንዲተባበሩ የሠፈሩት አንቀጾች ይህንኑ የሚያመለክቱ ናቸው ። በሰላም አብሮ የመኖር ሌኒናዊ ፖሊሲ የዘመናችን መሠረታዊ ቅራኔ ማለትም በሶሻሊዝምና በካፒታሊዝም መካከል ያለው ቅራኔና ከቅራኔውም የሚመነጨው ትግል የሚፈታው በወታደራዊ ገፅታው ሳይሆን በፖለቲካዊ፣ በርዕዮተዓለማዊና በኢኮኖሚያዊ የትግል መስኮች ነው ከሚል አስተሳሰብ የሚነሳ ነው ። ይህ ፖሊሲ የተለያዩ ሶሲዮ ፖለቲካዊ ሥርዓቶች ውስጥ በሚገኙ ሀገሮች መካከል የጦርነት አለመኖርን ብቻ

Digitized by Google

የሚያመለክት ሳይሆን ፣ የተለያዩ ፖለቲካዊ ሥርዓቶችን የሚከተሉ ሀገሮች ሊተባበሩና ትብብሩም ፍሬያማ ሊሆን እንደሚችል ያስገነዝባል ።

በሰላም አብሮ የመኖር ሌኒኒስት የውጭ ፖሊሲ ለመጀመሪያ ጊዜ በሌኒን በሚመራው የሶቭዬት መንግሥት ተግባራዊ ቢሆንም ፣ በሰላም አብሮ የመኖር መርህን ጽንሰ ሐሳብ በሚመለከት ከጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት አስቀድሞ በሌኒን በሚገባ ተብራርቷል ። በዚህ ጥያቄ ላይ የሌኒን ንድፈ ሃሳባዊ ትንታኔ የተመሠረተው በኢምፔሪያሊዝምና በሶሻሊስት አብዮት ንድፈ ሃሳባዊ ትንታኔ ላይ ነበር ።

ማርክስና ኤንግልስ በቅድመ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ዘመን በመኖራቸው ስለ ሶሻሊስት አብዮት የነበራቸው አስተሳሰብ ከወቅቱ የዓለም ሁኔታ ጋር የሚገናዘብና ትክክለኛ ነበር ። በዚሁ መሠረት በ1846 «የኮሚኒዝም መርሆች » በሚለው ጽሑፍ የሶሻሊስት አብዮትን አስመልክቶ ኤንግልስ የሶሻሊስት አብዮት በአንድ ሀገር ብቻ ሳይሆን በሰለጠኑ ሀገሮች ሁሉ ቢያንስ በእንግሊዝ ፣ በአሜሪካ ፣ በፈረንሳይና በጀርመን በአንድ ጊዜ እንደሚሳካ ጽፎአል ። [22] ይሁንና በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም የካፒታሊዝምን ያልተመጣጠነ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ዕድገት በጥልቀት የመረመረው ሌኒን በማርክሲዝም መሠረታዊ መርሆች ላይ በመመሥረት የሶሻሊስትን አብዮት ንድፈ ሃሳብ አዳበረ ። ሶሻሊስት አብዮት ድልን የሚቀዳጀው ማርክስና ኤንግልስ ካሰቡት ለየት ባለ ሁኔታ እንደሆነ አስረዳ ። ለመጀመሪያ ጊዜ በ1915 « ስለተባበረው አውሮፓ መፈክር » በሚለው ጽሑፉ « ያልተመጣጠነ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ዕድገት የካፒታሊዝም ፍጹም ሕግ ነው ። ስለዚህ በመጀመሪያ ሶሻሊዝም በጥቂት ወይም በአንድ ሀገር እንኳን ሊሳካ ይችላል » በማለት አብራርቷል ። [23]

በተከታታይ በጻፋቸው ሌሎች ጽሑፎችም ውስጥ ለምሳሌ በ1916 «የወዝአደሩ አብዮት የሚሊታሪ ፕሮግራም » በሚለው ጽሑፉም የሶሻሊስት አብዮትን ድል መቀዳጀት አስመልክቶ በካፒታሊስት የሸቀጥ ምርት ሥርዓት ያልተመጣጠነ የካፒታሊዝም ዕድገት መቀጠሉን በማስመልከት « ሶሻሊዝም በሁሉም ሀገሮች ድልን በተመሳሳይ ጊዜ ሊቀዳጅ አይችልም ። በመጀመሪያ በአንድ ወይም በጥቂት ሀገሮች ድልን ሲቀዳጅ ሌሎች ለተወሰነ ጊዜ ቡርዧ ወይም ቅድመ ቡርዧ ሆነው ይቆያሉ ፣ » [24] ሲል ጽፏል ።

የሌኒን የሶሻሊስት አብዮት ንድፈ ሃሳብ ለሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ አስፈላጊና ጠቃሚ ትንተናዎችን ለመስጠት አስችሏል ። በንድፈሃሳቡ ላይ በመመሥረት የሚከተሉትን ነጥቦች በቀጥታ ለመደምደም ተችሏል ።

1. ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም በሚደረገው ታሪካዊ የሽግግር ዘመን
   ሀ. ሶሻሊስት ሥርዓትን የሚከተሉ፣
   ለ. የቡርዧ ሥርዓትን የሚከተሉና
   ሐ. የቅድመ ካፒታሊስት ሥርዓት የሰፈነባቸው ሀገሮች ለተወሰነ ወቅትም ቢሆን ለጐን ይኖራሉ።በዚህ ታሪካዊየሽግግር ዘመን ከመደቦችና ከመንግሥታት ፍላጐትና ውሳኔ ውጭ የተለያየ ሶሲዮ ፖለቲካዊ ሥርዓት በሚከተሉ ሀገሮች መካከል የጋድ ዓለም አቀፋዊ ግንኙነት ይመሠረታል ። ይህ ነባራዊና የማይቀር ነው ።
2. ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም በሚደረገው ታሪካዊ የሽግግር ዘመን የተለያየ ማኅበራዊ ሥርዓት በሚከተሉ ሀገሮች መካከል በኢኮኖሚ መሠረት ፣ በፖለቲካ ሥርዓትና በሚመሩበት ርዕዮተ ዓለም እንዲሁም በሌሎች መስኮች ልዩነቶች መኖራቸው አይቀርም።

Digitized by Google

ይሁንና እነዚህ ልዩነቶች እያሉ የተለያየ ማኅበራዊ ሥርዓት የሚከተሉ ሀገሮች በሰላም አብረው መኖር ይችላሉ። በሰላም አብሮ የመኖር ሌኒናዊ ፖሊሲ በመንግሥታት መካከል ውዝግቦች ሊኖሩ እንደሚችሉ አይክድም ። በተለይ ዛሬ የኑክሌር ጦርነት አደጋ በሚያንዣብበት ወቅትና ጦርነቱ የሰው ልጅ ሕልውናን አደጋ ላይ የሚጥል ስለሆነ በመንግሥታት መካከል በሰላም አብሮ የመኖር ፖሊሲ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ አስፈላጊነቱ ግልጽ ነው ። ስለሆነም በካፒታሊስትና በሶሻሊስት መንግሥታት መካከል አለመግባባት ቢኖርም በጦርነት የሚፈታ አይደለም ።

የተለያየ ሶሲዮ ፖለቲካዊ ሥርዓቶችን በሚከተሉ ሀገሮች መካከል በሰላም አብሮ የመኖር ሌኒናዊ ፖሊሲ መከተል የሚያቅፉቸው እርምጃዎች ፣

— በመንግሥታት መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት በስምምነት ፣ በሰላማዊ መንገድ መጠቀምን እንጂ በጦርነት አለመጠቀምን ፣

— ትልቅም ይሁን ትንሽ የሀገሮችን ብሔራዊ ሕልውና፣ እኩልነት፣ የግዛት አንድነት ማክበርን ፣

— በሌሎች ሀገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባትን ፣ የሕዝቦችን የማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊና የፖለቲካ ሥርዓትን የመምረጥ ነፃነት ማክበርን ፣ በመንግሥታት መካከል የኢኮኖሚና የባህል ግንኙነቶችና ትብብሮች እንዲዳብሩ ማድረግን ፣

— የጦር መሣሪያ እሽቅድድም ማቆምና አጠቃላይ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ማድረግን ናቸው ።

በሀገሮች መካከል ለሚኖረው ጤናማና ዲሞክራሲያዊ ለሆነ ዓለምአቀፍ ግንኙነት መዳበር ለሁሉም ሀገሮች የጋራ ጥቅም መጠበቅ ትኩረት መስጠትን ይጠይቃል ። ይህን ተግባራዊ በሚያደርገው በሰላም አብሮ መኖር ፖሊሲ ውስጥ ምን ዓይነት ስምምነቶች ተቀባይነት እንዳላቸውና ምንስ ዓይነት ስምምነቶች ተቀባይነት እንደሌላቸው ሌኒን በሚገባ ለይቶ ተናግሯል ። ይህን አስመልክቶ በጥቅምት አብዮት ማግሥት ሌኒን « በዝርፊያ ፣ በብጥብጥ ላይ የተመሠረቱትን አንቀጾች እንቃወማለን ፤ ነገር ግን የመልካም ጉርብትና ግንኙነቶችንና ሁሉንም የኢኮኖሚ ስምምነቶች የያዙትን አንቀጾች እንቀበላለን ፤ እነዚህን ልንቃወም አንችልም » ሲል ጽፏል ። [25]

ለመልካም ጉርብትና መጠናከር አዳዲስ ስምምነቶችንም መፈራረም አለ ። በዚህ መሠረት የሶቭዬት ሩስያ መንግሥት የዛሩ አገዛዝና የቡርዧው መንግሥት የተፈራረሙትን አድሃሪ ስምምነቶች ካፈረሰ በኋላ በ1921 ከሞንጎሊያ ፣ ከአፍጋኒስታን ፣ ከኢራንና ከቱርክ ጋር አዲስ ስምምነቶችን ተፈራርሟል ። የመልካም ጉርብትናንና ግንኙነትን የሚያጠናክር ፖሊሲ ማራመድ በተለያዩ ሶሲዮ ፖለቲካዊ ሥርዓቶች ውስጥ ለሚገኙ ሕዝቦች የጋራ ፍላጐት ይጠቅማል ። በሌላ በኩል የተለያዩ ማኅበራዊ ሥርዓቶች በሚከተሉ ሀገሮች መካከል የኢኮኖሚ ግንኙነቶች መኖር ከዓለም የኢኮኖሚ ግንኙነት የሚመነጭ ነው ። ይልቁንም ደግሞ ከሳይንስና ከቴክኖሎጂ አብዮት ወደፊት መገሥገሥ የተነሣ በሀገሮች መካከል በኢኮኖሚየ መተሳሰሩ ሂደት እየተወሳሰበና ከፍ እያለ መጥቷል ።

ካፒታሊስት ሀገሮች ከሶሻሊስት ሀገሮች ጋር እንዲቀራረቡ የሚያደርጋቸው ኃይል ተጨባጭነቱ ጉልህ ሆኗል ። ይህ ኃይል የዓለም የኢኮኖሚ ግንኙነት ሲሆን ከመንግሥታትና ከመደቦች ፍላጐትና ውሳኔ ውጭ በሰላም አብሮ መኖርን አስፈላጊ ያደርገዋል ። ሌኒን ካፒታሊስት ሀገሮች ለምን

Digitized by Google

ከሶቭዬት ሩሲያ ጋር እንዲቀራረቡ እንደ ሚገደዱ ሲገልጽ ፣ « እኛን ከሚጠሉ መን ግሥታት መደቦች ፍላጐትና ውሳኔዎች የበለጠ ትልቅ የሆነ ኃይል አለ ፤ ይህ ኃይል ከእኛ ጋር እንዲገናኙ የሚያስገድዳቸው የዓለም አጠቃላይ የኢኮኖሚ ግንኙነት ነው » ። [26] ብሎ ነበር ።

በሰላም አብሮ መኖሩ ጠቀሚታው ሶሻሊ ዝምን ለሚገነቡ ሀገሮች ብቻ አይደለም ። ሶሻሊስት ላልሆኑት ሀገሮች ጭምር ይጠቅ ማል። ሶቭዬት ሩሲያ ከካፒታሊስት ሀገሮች ጋር የንግድ ግንኙነት ልታዳብር እንደምት ችልና ይህም ለሶቭዬት መንግሥት ብቻ ሳይ ሆን ለካፒታሊስት ሀገሮችም ጭምር ጠቀ ሚታ እንዳለው ለተጠየቀው ጥያቄ ሌኒን መልስ ሲሰጥ የሚከተለውን ብሎ ነበር፤«የእ ኛን መሰል የሶሻሊስት ሀገር ከካፒታሊስት ሀገሮች ጋር ላልተወሰነ ጊዜ የንግድ ግንኙነ ቶች የማያደርግባቸው ምክንያቶች አይታዩ ኝም። የካፒታሊስቶችን ባቡሮች እና የእርሻ መሣሪያዎች መውሰድ ለእኛ ጠቃሚ ነው ። እነርሱስ ቢሆኑ የእኛን ስንዴ ፣ ተልባና ፕላቲኒም ቢወስዱ ምን አለበት ? » [27]

ሶሻሊዝም የዓለምን ሕዝቦች አስተሳሰብ ስቦ ማራኪነቱ እየገነነ የሚሄደው በጦር ነት ሶሻሊስት ያልሆኑ ሀገሮች ሶሻሊዝ ምን እንዲከተሉ በማስገደድ አይደለም ። ወይም ከውጭ በመግፋት አብዮት በሌሎች ሀገሮች ውስጥ እንዲፈነዳ በማድረግ አይ ሆንም ። ይህ ለማርክሲዝም ሌኒኒዝም ባዕድ ነው ፤ ከኅብረተሰብ ዕድገት ነባራዊ ሕግ ጋት ጋር ይቃረናልና ። ሕዝባዊ አብዮት በማንኛውም ሀገር ውስጣዊና ውጫዊ አመች ሁኔታዎች ሲኖሩ የሚቀሰቀስ እንጂ እንደሸቀጥ ወደ ውጭ ተልኮ በሀገሮች ላይ የሚጫን አይደለም ። በሶሻሊዝምና በካ ፒታሊዝም መካከል ሰላማዊ የኢኰኖሚ ውድድር በማካሄድ ሶሻሊስት ባልሆኑ አገ ሮች ውስጥ ለሚገኙ ሕዝቦች የሶሻሊዝምን የበላይነትና ሰብአዊነት ፣ የወደፊቱም ዓለም

በእርግጥ የሠርቶአደሮች መሆኑን ለማረጋ ገጥ የሚቻለው ሶሻሊዝም በተግባር በሚያ ሳየው አርአያነት ነው ። ይህንኑ በሚመለ ከት ሌኒን ሲጽፍ፣«እኛ ይበልጥ ጠንካራ እን ደምንሆን እናረጋግጣለን ፤ በእርግጥ ይህ ተግባር ከባድ ነው ፤ ይሁንና . . . ሶሻሊ ዝም የአርአያነት ኃይል አለው ። በኃይል መጠቀም የሚሠራው የቀድሞ ሥልጣና ቸውን እንደገና ለመመለስ ለሚሹት ነው። የኃይል ጠቃሚነቱ እዚህ ላይ አብቅቷል ። ከዚህ በኋላ የሚሠሩት ማሳመንና አርአያ ነት ብቻ ይሆናሉ ። የኮሚኒዝምን ታላቅ ነት በተግባር በአርአያነት ማሳየት አለብን፤» ብሏል ። [28]

የሶሻሊዝም ግንባታ መሠረታዊ ዓላማ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ መስኮችን በሶሻሊዝም መሠረት ላይ በማደራጀት የሕ ዝቦችን ቁሳዊና ባህላዊ ፍላጐቶችን ማሟ ላት ነው ። ሌኒን በ1919 በሩሲያ ኮሚኒስት ፓርቲ ስምንተኛው ኮንግሬስ የውጭ ፖሊሲን በሚመለከት ባቀረበው የውሳኔ ረቂቅ ላይ ፣ የሩሲያ ሶሻሊስት ፌዴሬ ቲቭ ሶቭዬት ሪፐብሊክ ከሁሉም ሕዝ ቦች ጋር በሰላም ለመኖርና በሶቭዬት ሥርዓት አቅጣጫ ምርትን ፣ ትራንስፖር ትንና የመንግሥትን ጉዳዮች ለመምራት ሁሉንም ጥረቶችዋን ለውስጥ ዕድገት ለማ ዋል ትሻለች ብሎ ነበር ። [29] ሶሻሊዝምን የመገንባት ሂደት የሚፋጠነውና ጥንካሬ ውም በዚያው ልክ የሚጨምረው ሰላም ኖሮ በሰላማዊ ሁኔታ የግንባታን ትግል ማጧጧፍ ሲቻል መሆኑን ሌኒን ሲናገር « ሰላም የሰፈነበት እያንዳንዱ ወር አሥር ጊዜ ያጠናክረናል » ብሎ ነበር ። [30]

ለሶሻሊዝም ሰላማዊና አመች የዕድገት ሁ ኔታ ለማስገኘት በሰላም አብሮ የመኖር ፖ ሊሲ በሥራ ሃይልና በካፒታል፣በሠራተኛው

Digitized by Google

መደብና በቡርዧው መደብ ፣ በሶሻሊዝምና በካፒታሊዝም መካከል ያለውን ቅራኔ እያድበሰበሰም ። ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር ሥር ለመላቀቅ ሕዝቦች የሚያቀጣጥሉትን የነፃነት ችቦ ያቀጣጥለዋል እንጂ አያጠፋውም ። ይህ ፖሊሲ ከወዝ አደራዊ ዓለም አቀፋዊነት ጋር ዲያሌክቲካዊ አንድነት ስላለው የሶሻሊስት ርዕዮተዓለምን ከቡርዧው ርዕዮተዓለም ጋር አያስታርቅም ። ምንም ኃይል ደግሞ ሊያስታርቃቸው አይችልም ። ያለው ብቸኛ ምርጫ የሶሻሊስት ወይም የቡርዧ ርዕዮተዓለም በመሆኑ በማናቸውም መንገድ የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለምን ማዳከም የቡርዧውን ርዕዮተ ዓለም ማጠናከር ማለት ነው ።

እርግጥ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መርሆች እንደተጠበቁ ሆነው ሶሻሊስት ሥርዓት ከማይከተሉ ሀገሮች ጋር መግባባትና መተባበር ይችላል ። ከዚህ አንጻር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በፀረ ሂትለር ግንባር ለተወሰነ ግብ የሶቭዬት ኅብረትና የኢምፔሪያሊስት ሀገሮች ትብብር በቂ ምስክር ይሆናል ። በሰላም አብሮ የመኖር ፖሊሲ የዓለምን የሰላም ኃይሎች ለማስተባበርና ለማንቀሳቀስ አመች ሁኔታ የሚፈጥር ፖሊሲ ነው ።

ፀአጠቃላይ ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ ግርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተዓለምን መመሪያው ያደረገ የሶሻሊስት መንግሥት የሚከተለው የውጭ ፖሊሲ ነው ። ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ በሰፊው ሕዝብ ታሪክ ሠሪነትና ዛሬ በዓለም ፖለቲካ የሚታየው የሰላም መደፍረስና የኢምፔሪያሊዝም በተለይም የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ጠብ አጫሪነትና ጣልቃ ገብነት ሊወገድ የሚችለው ለሰላም የቆሙ ኃይሎች ሁሉ በሚያካሄዱት የተቀነባበረ ትግል መሆኑን ያምናል ። ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ በሠርቶ አደሮች በስተጀርባ የሚካሄድ የውጭ ፖሊሲ ሴራዎችን ያጋልጣል ። የዲፕሎማሲ ሴራዎችን ምዝብር ሕዝቦች እንዲረዱና እንዲታገሉት ጥሪ ያደርጋል ። ሕዝቦች ለነፃነታቸው እንዲታገሉ አመች ሁኔታ ለመፍጠር ዘዴውንና ስልቱን ይቀይሳል ። በዚህም ባሕሪው ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ ዲሞክራሲያዊ ነው ።

ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም አስተምህሮን መመሪያ ያደረገና ለተሟላ ማኅበራዊ ዕድገት መፋጠን ፣ ለምዝብሮች ነፃ መውጣት ፣ ብዝበዛና ጭቆና የሌለበት አዲስ የኅብረተሰብ ሥርዓት ለመመሥረት አመች የሆኑ የውጭ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ነው ። ስለሆነም ይህ ፖሊሲ አብዮታዊ ነው ። ይህ ፖሊሲ በጠቅላላው በዓለም ውስጥ ለወዝአደሩና ለወዝ አደሩ አጋሮች የቆመ በመሆኑ ዓለም አቀፋዊና ወገናዊ ነው ። ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ የሚወስዳቸው እርምጃዎች፣የሚያወጣቸው የውጭ ፖሊሲ ዕቅዶች ነባራዊ የኅብረተሰብ ሕግጋትን፣ የዓለም የኃይል አሰላለፍንና ሕሊናዊ ሁኔታዎችን በትክክል በመረዳት ላይ የተመሠረቱና ከስሜታዊ የውጭ ፖሊሲ አወጣጥ ነፃ ስለሆኑ ሳይንሳዊ ናቸው ።

ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ ዛሬ ያለንበት ዘመን ከቅድመ ካፒታሊዝምና ከካፒታሊዝም የኅብረተሰብ የእድገት ደረጃዎች ወደ ሶሻሊስት ሥርዓት ሽግግር የሚደረግበት ዘመን መሆኑን በትክክል በመረዳት በካፒታሊስትና በሶሻሊስት ሀገሮች እንዲሁም በአጠቃላይ በመንግሥታት መካከል ያሉ ግንኙነቶች በሰላም አብሮ በመኖር መርህ ላይ የተመሠረቱ እንዲሆኑ ይጥራል ። ለዚህም መርህ ተፈጻሚነት ይታገላል ።

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻ

1 ቪ. አይ. ሌኒን፣ስብስብ ሥራዎች ፣ ቅፅ 25 ፣ ገጽ 85

2 ካርል ማርክስና ፍሬዲሪክ ኤንግልስ ምርጥ ሥራዎች፣በሶስት ቅጾች፣ቅጽ 1፣ ገጽ 125

3 የዓለም አቀፍ ጀኔራል ካውንስል 1864-1866 ቃለጉባኤዎች፣ሞስኮ 1973 ገጽ ፣ 287

4 ቪ. አይ. ሌኒን ስብስብ ሥራዎች ቅጽ ፣ 26 ፣ ገጽ 445

5 ካርል ማርክስና ፍሬዲሪክ ኤንግልስ ፣ ገጽ 125

6 ቪ.አይ.ሌኒን፣ ምርጥ ሥራዎች፣በሶስት ቅጾች ፣ ቅጽ 2 ፣ ገጽ 419

7 ከላይ የተጠቀሰው

8 ከላይ የተጠቀሰው

9 ካርል ማርክስና ፍሬዲሪክ ኤንግልስ ፣ ምርጥ ሥራዎች ፣ በሶስት ቅጾች ፣ ቅጽ 2 ፣ ገጽ 193

10 ቪ.አይ. ሌኒን፣ስብስብ ሥራዎች ፣ ቅጽ 4 ፣ ገጽ 236

11 ቪ.አይ. ሌኒን፣ምርጥ ሥራዎች ፣ ቅጽ 2 ፣ ገጽ 424

12 ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 420—421

13 ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 422

14 የአንደኛው ዓለም አቀፍ ጀኔራል ካውንስል 1870—1871 ቃለ ጉባኤ ዎች ፣ ሞስኮ 1966 ፣ ገጽ 321

15 ቪ.አይ. ሌኒን፣ስብስብ ሥራዎች፣ቅጽ 2 ፣ ገጽ 109

16 ቪ.አይ. ሌኒን፣ስብስብ ሥራዎች፣ ቅጽ 25 ፣ ገጽ 87

17 ቪ.አይ. ሌኒን ምርጥ ሥራዎች ቅጽ 3 ፣ ገጽ 248 ፡

18 ቪ.አይ. ሌኒን፣ስብስብ ሥራዎች ፣ ቅጽ 32 ፣ ገጽ 482

19 ቪ.አይ. ሌኒን፣ስብስብ ሥራዎች፣ ቅጽ 25 ፣ ገጽ 363

20 ቪ.አይ. ሌኒን፣ስብስብ ሥራዎች፣ ቅጽ 31 ፣ ገጽ 148

21 የዓለም አቀፍ ኮሚኒስትና ሠራተኞች ፓርቲዎች ስብሰባ ፣ ሞስኮ 1969 ፣ ፕራግ ፣ ገጽ 37

22 ካርል ማርክስና ፍሬዴሪክ ኤንግልስ፣ ምርጥ ሥራዎች፣ቅጽ 1 ፣ ገጽ 91—92

23 ቪ. አይ. ሌኒን ፣ ምርጥ ሥራዎች ፣ ቅጽ 1 ፣ ገጽ 631

24 ከላይ የተጠቀሰው ፣ ገጽ 741—742

25 ቪ.አይ. ሌኒን ፣ ምርጥ ሥራዎች፣ ቅጽ 29 ገጽ 420—221

26 ቪ.አይ. ሌኒን፣ስብስብ ሥራዎች፣ ቅጽ 33 ፣ ገጽ 155

27 ሌኒን ፣ በሰላም ተቻችሎ ስለመኖር ፣ ሞስኮ ፣ የሮግሬስ አሳታሚዎች 1979 ፣ ገጽ 80

28 ቪ.አይ.ሌኒን ፣ ስብስብ ሥራዎች፣ቅጽ 31፣ ገጽ 256—457

29 ቪ.አይ. ሌኒን ፣ ምርጥ ሥራዎች፣ቅጽ 3 ፣ ገጽ 251

30 ቪ.አይ. ሌኒን፣ስብስብ ሥራዎች፣ቅጽ 31 ፣ ገጽ 169

Digitized by Google

ሽብር ፈጣሪነት —

የኢምፔሪያሊዝም ዓይነተኛ መሣሪያ

ወልደ ዮሐንስ ወርቅነህ

ካለፉት 36 ዓመታት ወዲህ በምዕራብ አ
ውሮፓ መንግሥታት መካከል የይፋ ጦርነት
ተካሂዶ አያውቅም። ይሁን እንጂ ኅብረተሰቡ
በረጅም የዕድገት ዘመኑ ያከማቻቸው የሥ
ልጣኔ ቅርሶች በየጊዜው በሽብር ፈጣሪዎች
እየወደሙ ሲሆን ፥ ሕዝቡም የካፒታሊዝም
ሥርዓት በፈጠረው ውጥረት የተነሣ የዕለት
ተዕለት ኑሮው አስጊ ሁኔታ ላይ ወድቋል ።

በካፒታሊስቱ ዓለም ያለውን ሁኔታ ስን
መለከት በየጊዜው በሚነሱ ጦርነቶች ሳቢያ
ደም ሲፈስና ሰላም ሲደፈርስ ይታያል ።
ለዚህ ሰላም መጥፋትና በየቀኑ ለሚደረግ
ብጥብጥ ተጠያቂው ሽብር ፈጣሪ የሆነው
ኢምፔሪያሊዝም ነው ። ኢምፔሪያሊዝም
ለዚህ ተወዳዳሪ የሌለው አረመኔያዊ ተግ
ባር የውጭ ፖሊሲ መሣሪያው አድርጐ የሚ
ገለገለው በሽብር ፈጣሪነት ነው ።

ሽብር ፈጣሪነት ካፒታሊዝም ከወለዳ
ቸው ማኅበራዊ ቅራኔዎችና ኢኮኖሚያዊ
ቀውሶች ጋራ የተቆራኘ ነው ። ሽብር ፈጣ
ሪነት ለወደፊቱ አዲስ ሥርዓት የሚገነቡ
ዜጐችን ማኅበራዊ ሕይወት የሚያደፈርስና
በሰው ልጆች ጥፋት ላይ የተመሠረተ የኢ
ምፔሪያሊስት ፖሊሲ ነው ። ኢምፔሪያሊ
ዝም ይህን የኅብረተሰብ ሰላም አደፍራሽ
የሆነውን ፖሊሲ በመከተል ፥ በተለይም
ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ትግል በሚካሄድባ
ቸው አካባቢዎች ሲመቻቸው በይፋ ፥ ሳይመ
ቻቸው በእጅ አዙር ስርጎ በመግባት እያሌ
ደባዎችን ሲፈጽም ቆይቷል ። በየቦታው
ሕዝባዊ አብዮት ፈንድቶ ፀረ—ኢምፔሪያ
ሊስት አቋም ያለው መንግሥት ሲመሠረት፥
እንደነዚህ ያሉ መንግሥታትን ለማናጋት
ሽብር ከመንዛት የተቆጠበበት ጊዜ የለም።
ባጭሩ አሁን በያዝነው ታሪካዊ ወቅት ኢም
ፔሪያሊዝም በየአካባቢው የታሪክን እድ
ገት በመጋፋት ላይ ይገኛል ። ኢምፔሪ
ያሊስቶች ባገር ውስጥ ፖሊሲያቸው የተ

Digitized by Google

ሊያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን መጨቆንና መበዝበዝን ፥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ በጦር መሣሪያ ኃይል ብጥብጥ ማስነሳትና የአገሮችን ብሔራዊ ሕልውና ደፍሮ ጠብ መጫርን ተቀዳሚ ተግባራቸው አድርገው ተያይዘውታል ። [1] የካፒታሊስት መንግሥታት አድኃሪ ፖሊሲያቸውን የሚያራምዱት አመጽን በማስነሳትና ሽብርን በመፍጠር ነው ።

ቀደም ሲል የፖለቲካ ሽብር ፈጣሪነት ከማኅበራዊና ከብሔር ጭቆና ጋር የተቆራኘ ነበር ። በተያያዝነው ዘመን ግን ሽብር ፈጣሪነት የኢምፔሪያሊዝም ዓይነተኛ የፖለቲካ አመጽና የፖሊሲ መሣሪያ ሆኗል። ኢምፔሪያሊዝምም በዚህ መሠሪ ተግባሩ የፖለቲካ ግድያንና ጠለፋን ያካሂዳል ። ከዚህም ሌላ ተራማጅ የፖለቲካ ፓርቲዎችንና ድርጅቶችን ሥራ ማደናቀፍ ፥ ንብረትን መዝረፍና ማቃጠል ፥ በየቦታው ግጭትን መፍጠር ወዘተ . . . ሌላው ድርጊቱ ሆኗል ።

ዛሬ በዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም አማካይነት የሚካሄደው ሽብር ፈጣሪነት በዓለምአቀፍ ደረጃ ውጥረትንና ጭንቀትን እያባባሰ መጥቷል ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የፖለቲካ ነፃነታቸውን የተጎናፀፉ ሕዝቦችና አገሮች የተያያዙት አዲስ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት የመገንባት ጥረት የኢምፔሪያሊስቶችን ዓይን ደም እንዲለብስ ያደረገ ሲሆን ፥ በዚሁ ሳቢያ ኢምፔሪያሊስቶች አዲስ ዓለምአቀፍ ስትራቴጂ ቀይሰው የነዚህን አገሮች ዕድገት ለመገደብ ተነሳስተዋል ።

ሌኒን ሽብር ፈጣሪነት የኅብረተሰብ ዕድገት መሰናክል መሆኑን በማስገንዘብ ሽብር ፈጣሪዎች የሰፊውን ሕዝብ ታሪክ ሠሪነት የማያውቁ ፥ ትግሉን ለማስተባበር የማይችሉና ራሳቸውን ከሰፊው ሕዝብ ያገለሉ ግለሰቦች ወይንም የቡርዧው መደብ ለራሱ መሠሪ ተግባር ሲል የሚያሰማራቸው ቅጥረኞች እንደሆኑ በትክክል ጠቁሟል ።[2] ይሁን እንጂ ለሞኖፖል ካፒታሊዝም ሕልውና የቆሙ የቡርዧ የፖለቲካ ሳይንስ ተቺዎችና የመገናኛ ዘዴዎቻቸው ኢምፔሪያሊዝም ለሽብር ፈጣሪነት ተግባር መቆሙን ለመሸፋፈን ይሞክራሉ ።

ኢምፔሪያሊዝም ከራሱ ክልል ውጭ ቀደም ብሎ ይጨቁናቸውና ይመዘብራቸው የነበሩ አገሮች መራራ መስዋዕትነትን ከፍለው የፖለቲካ ነፃነታቸውን ለመጎናፀፍ ሲታገሉ ዝም ብሎ አይመለከትም ፤ በዓለም ሥርነቀል ለውጥ እንዲካሄድም አይፈቅድም ። ይህንን መሠረታዊ ለውጥ ለመቅጨት ይህ ነው የማይባል ደባ ሲሠራ ይታያል ። ፍሬድሪክ ኤንግልስ የቡርዧውን ሽብር ፈጣሪነት ውስጣዊ ይዘት ሲያብራራ፥ «ሽብር ፈጣሪዎች ራሳቸው በሽብርና በፍራቻ የተሞሉ ሲሆኑ ፥ ሽብር ፈጠራ ደግሞ በፍርሃት የተጠቃው የቡርዧው መደብ የራሱን ሕልውና ለመጠበቅ ሲል የሚፈጽመው አስከፊ ድርጊት ነው »[3] በማለት የተናገረው ይኸንኑ ያረጋግጣል ።

የቡርዧ አፈቀላጤዎች አብዮታዊ እንቅስቃሴ የሚያራምዱ አብዮታውያን ኃይሎችን ሀቅን በማዛባት « ሽብር» ፈጣሪዎች ይሏቸዋል ። ነገር ግን ቀደም ካለ ጊዜ አንስቶ የአድሀሮት ኃይላትና መንግሥታት የታሪክን ዕድገት በመካድ ለአዲስ ማኅበራዊ ለውጥና ለተስተካከለ ኅብረተሰብ አደረጃጀት የሚታገሉትን ሁሉ አመፀኞች ፥ ረብሸኞችና ሽብርተኞች በማለት ይተናኰሷቸው እንደነበር ታሪክ ራሱ ማስረጃ ነው። በሕዝባዊ አብዮት ድል የተመታውና ሥልጣኑን የተቀማው የሩሲያ የቡርዧ መደብ አባላት ቦልሼቢኮችን « ሽብርተኞች » ናቸው በማለት አስተጋብተው ነበር ። እያደር ግን ቦልሼቢኮች ሳይሆኑ ቡርዧው ራሱ ሽብር ፈጣሪ መሆኑ ታሪክ በይፋ ሊመሰከረ ቻለ ። ቀደም ብለው የቅኝ ግዛት የነበራቸውና በኋላ ግን የቅኝ ግዛታቸው አድማስ የጠበበባቸው ኢምፔሪያሊስቶች «ሽብር» ለሚለው ቃል የተዛባ ትርጉም በመስጠት ለነፃነታቸው የሚታገሉ

Digitized by Google

በላቲን አሜሪካ ፣ በአፍሪካና በእስያ ያሉ የብሔራዊ አርነት ንቅናቄዎችንና ሌሎች ለብሔራዊ ነፃነታቸው የሚታገሉ ሕዝቦችን ሽብር ፈጣሪዎች ይሏቸዋል ። ምዝብር ሕዝቦች ኢምፔሪያሊዝም ከዘረጋው የብዝበዛ ሰንሰለት ተላቀው ማኅበራዊ ኑሯቸውን ለመገንባት ብዝበዛና ጭቆና የሌለበትን ሥርዓት ለመመሥረት የሚያካሂዱቸው ጦርነቶችና አብዮቶች ከሽብር ፈጣሪነት ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም ።

ዛሬ አንዳንድ የኢምፔሪያሊስት አገሮች መሪዎች ሽብር ፈጣሪነት ፖሊሲያቸው መሆኑን በይፋ መናገር የሚያሳፍር ሁኖ አላገኙትም ። ለምሳሌ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬጋን ባንድ ወቅት ይሽንኑ በሚመለከት ሲናገር ሽብር ፈጣሪነት «በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት ለአሜሪካ አዲስ ዙር ጣልቃ ገብነት የተቀየሰ ሌላ የዘመኑ የፀረኮሚዩኒዝም መገለጫ ነው »[4] ማለቱ ሽብር ፈጣሪነት የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ዓይነተኛ የውጭ የፖሊሲ መሣሪያ እንደሆነ ያመለክታል ።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መሠረታዊ ዓላማ የሰው ልጅ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ መብት እንዲከበር ፣ ሁሉም አገሮች ብሔራዊ ነፃነታቸውን እንዲጎናፀፉና በዓለም ሰላም እንዲሰፍን ነው ። ይሁን እንጂ ዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በተቃራኒው ሽብር በመፍጠር ፣ በሌሎች አገሮች የውስጥ ጉዳይ በቀጥታ ጣልቃ በመግባት ወይንም አምባገነን መንግሥታትን በስውር በመመሥረት ወይንም ቅጥረኛ ወታደሮችን (Mercenaries) ወደ ሌሎች አገሮች አሠርጎ በማስገባት ፀረ ኢምፔሪያሊዝም አቋም ያላቸውን መንግሥታት ማናወጥና ተራማጅ የመንግሥታት መሪዎችን ማስገደል የጊዜው ተግባሩ ሆኖአል ።

ሽብር ፈጣሪነት የኢፔሪያሊዝም የአክራሪነት ፖሊሲ ነው ። በዚህ የሽብር ፈጣሪነት ተግባር የመካከለኛውና የትላልቅ ቡርዧ መደብ አባላት በይፋና በስውር ይሳተፉሉ። በተለይም በትላልቅ ከተሞች አካባቢ ሌሎች ማኅበራዊ ክፍሎችም በዚህ የሽብር ፈጠራ ተግባር ተሰልፈው ይገኛሉ ። እነዚህ ማኅበራዊ ክፍሎች የካፒታሊስቱ ሥርዓት ባመጣባቸው ማኅበራዊ ጭቆና ሰብዓዊ ክብራቸው ተዋርዶ ከፍርሃት፣ ከመንፈስ ጭንቀትና ተስፋ ከመቁረጥ የተነሣ ለወንጀል ድርጊት ራሳቸውን አጋልጠው እንዲሰጡ የተገደዱ ናቸው ። በዚህ አስከፊ ተግባር ላይ የተሰማሩ ሁሉ በሰፊው ሕዝብ ሃያልነት ቅንጣት ያህል እምነት የሌላቸው ናቸው ።

ሽብር ፈጣሪነት በማኅበራዊ መሠረቱ ፣ በድርጅታዊ ባህሪው ፣ በማኅበራዊ ሥነልቦናና በርዕዮተዓለሙ ከፋሽዝም ጋር የተማሠረ ሲሆን በማንኛውም መልኩ ፀረ ኮሚዩኒዝም፣ ፀረ ዲሞክራሲና ባጠቃላይም የሰፊውን ሕዝብ መሠረታዊ ፍላጐት የሚጻረር ነው ። በዚህም የተነሣ ከተራማጁ ኅብረተሰብ ክፍል ጋራ በተጻራሪነት ቆሞ ይገኛል።

ቀንደኞቹ የኢምፔሪያሊስት አገሮችና በነዚሁ አገሮች ውስጥ በስውር የሚንቀሳቀሱ የሽብር ፈጣሪዎች ድርጅቶች በበለጠ በመመሳጠር ሰላምን ሲያደፈርሱና የበርካታ ሰዎችን ሕይወት ሲያጠፉ ኖረዋል ። ዛሬም በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የሚገኙ ከተሞች በገድያ ፣ በገድያ ሙከራ ፣ በቦምብ ፍንዳታና በየመንገዱ ላይ በሚካሄድ ሽብር ተናውጠዋል ፤ የብዙ ሰዎች ሕይወትም ዋስትና አጥቷል ።

ሽብር ፈጣሪነት የኢምፔሪያሊስቱን ዓለም የማይለቅ በሽታ ነው ። ሲ.አይ.ኤ. በመባል የሚታወቀው የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የስለላ ድርጅት ከነዚህ የኅብረተሰቡን ፀጥታ ከሚያደፈርሱ ቡድኖች ጋር በመተባበርና በመመሳጠር ይሠራል ። በዚሁ የስለላ ድርጅት አቀናጅነትና መሪነት ከ1969 እስከ 1979 ባለው ጊዜ ውስጥ በተለያዩ አገሮች በርካታ ሰዎች ሽብር ፈጣሪዎች ባካሄዱት ገድያ ሕይወታቸውን አጥተዋል ።

Digitized by Google

በ1979 ብቻ ሽብር ፈጣሪዎች በ58 አገሮች ወንጀል መፈጸማቸውን ኒውዮርክ ታይምስ የተባለው የአሜሪካ ጋዜጣ አረጋግጧል ።[5] የዓለምአቀፍ ሽብር ፈጣሪዎች ጥናት ኢንስቲትዩት (Institute for studies International Terrorism) የሚባለውም ተቋም በየጊዜው በዓለም ዙሪያ የሚፈጸሙትን ወንጀሎች ይመዘግባል ። በዚሁ መሠረት በካፒታሊስቱ ዓለም ከ1970—78 መካከል 5529 ጊዜያት ሽብር ፈጣሪዎች አደጋ መጣላቸውን የመዘገበ ሲሆን የኢጣሊያ ኮሚዩኒስት ፓርቲም በበኩሉ ጥር 7 ቀን 1980 ያወጣው መግለጫ እንደሚያመለክተው ከ1977—79 በኢጣሊያ ብቻ 6639 ጊዜያት አደጋ መጣሉን ገልጿል ። በተጠቀሰው ጊዜ በሮም ከተማ ብቻ 748 ጊዜያት የወንጀል ድርጊት ተፈጽሟል ። በ1980 በዚችው ከተማ መሽገው ከነበሩ አያሌ ሽብር ፈጣሪዎች መካከል 557 ሽብር ፈጣሪዎች ሲያዙ 36 የሽብር ፈጣሪዎች የማሰልጠኛ ማዕከሎችም በቁጥጥር ሥር ውለዋል ።[6] ሆኖም ዛሬ የኢጣሊያ ከተሞች ከሽብር ፈጣሪዎች ጸድተዋል ማለት አይደለም ።

በካፒታሊስቱ ሥርዓት ለወዝአደሩ መደብና ለሌሎችም ጭቁን ሕዝቦች ጥቅም የቆሙ አያሌ ታጋዮች የኢምፔሪያሊዝም የጥፋት መልዕክተኞች በሆኑት ሽብር ፈጣሪዎች በየጊዜው ተገድለዋል ። ከነዚህም መካከል ባንደኛው የዓለም ጦርነት መባቻ ላይ የተገደለው የፈረንሣይ ሶሻሊስት ፓርቲ መሪ ዧን ጆረስ ፣ በ1918 የተገደሉት የሶቪየት መሪዎች ሞይሲይ ዩሪትስኪና ሞሲይ ቮሎዳሪስኪ ፣ በ1919 የተገደሉት የጀርመን ኮሚዩኒስት ፓርቲ መሪዎች ካርል ሊብክነሽት ፣ ሮዛ ለግዛምበርግና ጃን ታይዝካ ፣ በ1944 የተገደለው የጀርመን ኮሚዩኒስት ፓርቲ መሪ እርነስት ታልማን ፣ በ1973 የተገደለው የቺሊ መሪ ሳልቫዶር አየንዴ ከምናስታውሳቸው ጥቂቶቹ ናቸው ።[7]

ሽብር ፈጣሪነት የኢምፔሪያሊዝም የፖሊሲ መግሪያ በመሆን በየአካባቢው እየተስፋፋ መጥቷል ። በአፍሪካ ሽብር ፈጣሪው የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ፣ በላቲን አሜሪካ የቺሊው የፒኖቼ ፋሽስታዊ መንግሥት፣ በመካከለኛው ምሥራቅም የጽዮናዊት እሥራኤል አድኃሪ መንግሥትና መሰሎቻቸው ለዚህ ዓይነተኛ ማስረጃ ናቸው ። የነዚህ ጥገኛ መንግሥታት ሕልውናም ከኢምፔሪያሊዝም ጋር የተሳሰረ እንደሆነ የሚያጠያይቅ አይደለም ።

ይሁንና በአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የሚመራው የሽብር ፈጣሪነት ድርጊት ዕርታኑን በመውጣት ላይ ነው ። ጆን ማርክስ በመባል የሚታወቀው አንድ የአሜሪካ «የብሔራዊ ፀጥታ ጥናት ማዕከል» አባል ይሸንን አስመልክቶ ሲናገር «አሜሪካ ላለፉት 35 ዓመታት ሽብር ፈጣሪነትን ቋሚ የውጭ ፖሊሲ መግሪያ አድርጎ ተጠቅሞበታል»[8] ብሏል ። ይህም የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ከኢምፔሪያሊዝም የጭቆና አገዛዝ ተላቀው አዲስ ኅብረተሰብን በሚገነቡ አገሮች ላይ ምን ዓይነት ፖሊሲ እንደሚከተል በግልጽ የሚያስረዳ ነው ።

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ከ2ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በተለያዩ አካባቢዎች ሽብር መፍጠርን ተቀዳሚ ዓላማው አድርጎ ቆይቷል ። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ በብዙ ሥፍራዎች የቅኝ አገዛዝ ዘመንና ዕድሜ እያጠረ መሄዱን በመገንዘብ የፖለቲካ ነፃነት በተጎናፀፉ አገሮች ውስጥ ማኅበራዊ ዕድገትን ለማደናቀፍ ወጥመዱን መዘርጋት ጀመረ ። ለምሳሌ በ1946 (በፊሊፒንስ እና በ)1957 በፓራጓይ የተቀጣጠለውን ሕዝባዊ ንቅናቄ ለማፈን ያደረገው ጥረት፣ በ1948 ቅጥረኛ ወታደሮችን በመላክ በኩባ ታሪክ የተቀጣጠለውን ሕዝባዊ አብዮት ማጨናገፉ ፣ በ1950 የፖርታሪኩን ሕዝባዊ የአርነት እንቅስቃሴ መቅጨቱ ከዚሁ ፖሊሲ የመነጩ ድርጊቶች ናቸው ። ከዚህም ሌላ በ1950 እና በ1953 ዓመታት መካከል በኮሪያ ብዙ ሕዝቦችን መጨፍጨፉ፣ በ1953 አድኃሪውን የኢራኑን ሻህ ወደ ሥልጣን ለመመለስ መፈንቅለ መንግሥት ማካሄዱ

Digitized by Google

ከኢራን በኋላ በጓቲማላ ፣ በታይላንድ፣ በላ
ኦስ ፣ በኩንጐ ፣ በፓናማ ፣ በዶሚንካን ሬፑ
ብሊክና በሌሎችም አገሮች በሲ.አይ.ኤ.
ወኪሎች አቀነባባሪነትና በቅጥረኛ ወታደ
ሮች ዕርዳታ የተራማጅ መንግሥታትን
ፀጥታ ለማወክ የተፈጸሙ ደባዎች ከአስከፊ
ድርጊቶቹ መካከል ጥቂቶቹ ናቸው ። ከላይ
በተጠቀሱት አገሮች ውስጥ ተራማጅ መን
ግሥታትን አውርዶ በነሱ ምትክ አድኃሪ የአ
ምባገነን መንግሥታትን መሥርቷል። ብሩኪ
ንግ ኢንስቲትዩት በመባል የሚታወቀው
አንድ የአሜሪካ የጥናት ኢንስቲትዩት እን
ዳመለከተው አሜሪካ በ1945 እና በ1975
መካከል የውጭ ተልዕኮውን ለመወጣት
215 ጊዜያት በወታደራዊ ኃይል መጠቀ
ሙን ገልጧል ። [9] ይህም የአሜሪካ ኢም
ፔሪያሊዝም በዓለም ላይሰላም እንዳይና
ርና ሕዝባዊ ሥርዓት እንዳይሰፍን የሚ
ፈጽመው ድርጊት ሲሆን ፣ የውጭ ፖሊሲ
ውን ተግባራዊ ለማድረግ በተጠናከረ ወታ
ደራዊ ኃይል በመጠቀምና የስለላ ተግባር
በማካሄድ የነፃ መንግሥታትን ሕልውና
በተደጋጋሚ መድፈሩን ድርጊቱ ያስረዳል።
ለዚህ ተልዕኮ የሚሰማሩ ሽብር ፈጣሪዎች
ሁሉ ድርጊታቸው በተጨባጭ ሲገመገም
ከአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ፖሊሲ ውጭ
የሚሠሩ አይደሉም ።

የሬጋን አስተዳደር በሰላማዊ ሕዝብ ላይ
ሽብር ለማካሄድ ቀደም ሲል ከመሠረተው
ሽብር ፈጣሪ ፈጣን ጣልቃ ገብ ጦር ጎን በያ
ዝነው የአውሮፓውያን ዓመት ጥር 1 ቀን
1983 የዓለም ሕዝብን ሰላም የሚነሳበት
አንድ ሌላ ተጨማሪ ጦር መሥርቷል። ይህም
«ሴንትራል ኰማንድ»(ማዕከላዊ ዕዝ) በመ
ባል የሚታወቀው ነው ። ይህ ዕዝ በከፍተኛ
የአሜሪካ መኰንኖች የሚመራ ሲሆን የዋ
ሽንግተን ዓለም አቀፍ ሽብር ፈጣሪነት ባህ
ርይ ዋና መከሰቻ ነው ። ዕዙ ለአሜሪካ ጥ
ቅም ሲባል ማንኛውንም ተግባር ይፈጽ
ማል ። ከመጀመሪያው የፈጣን ጣልቃ ገብ
ጦር ቀጥሎ የተመሠረተው ይኸው ዕዝ እስከ
250,000 የሚደርሱ የጦር ኃይል አባላት
ሲኖሩት ፣ የኋላቀር አገሮችን የተፈጥሮ ሀ
ብት በመዝረፍ ላይ የተሰማሩ ድንበር ዘለል
ኩባንያዎችን የሚጠብቅና በተለይም ከፍ
ተኛ የዘይት ክምችት ባላቸው አገሮች ላይ
የሚያተኩር ነው ። ከዚህ ተግባሩ ሌላ ከፈ
ጣን ጣልቃ ገብ ጦር ጋር ተደርቦ በደቡብ
ምሥራቅ እስያ ፣ በምሥራቅ አፍሪካና በመ
ካከለኛ ምሥራቅ ጭምር ይሰራል ። ይህ ዕዝ
በሰላም ጊዜ በአሜሪካ ከፍተኛ መኰንኖች
መሪነት ለጦርነት ዕቅድ ያወጣል ፣ ወታደ
ራዊ ፕሮግራሞችን በማቀነባበርና በመቆ
ጣጠር ይሠራል ። [10]

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ዓለምአቀፍ
ሽብርን በማስፋፋት ዓለምአቀፍ ግንኙነትን
ለማሻከር በጣልቃ ገብ ጦርና በሴንትራል
ኰማንድ ብቻ አይጠቀምም ።በየጊዜው የሚ
ሰራቸውን የተራቀቁ የጦር መሣሪያዎች ዓይ
ነትና ብዛት ከማሳደጉና ለዓለም ሰላም ጠንቅ
የሆነ የሚሊታሪ ቴክኖሎጂን ከማስፋፋቱም
በላይ ዓለምን ለመሰለልና አድፍጦም እርስ
በርስ ለማተረማመስ ሲ.አይ.ኤን ከመሠረ
ተበት ከ1947 አንስቶ በዚህ የስለላ ድርጅት
አማካይነት የዓለምን ሰላም ሲያደፈርስ ቆይ
ቷል ። አንድ የአሜሪካ ዜናና የዓለም ሪፖ
ርት የተባለ ዘገባ ስለዚሁ ድርጊት ሲገልጽ
አሜሪካ ከ1961—76 ባሉት ዓመታት መካ
ከል ከ900 ጊዜያት በላይ ስውር ብጥብጥን
አቀነባብሮ በግለሰቦችና በተራማጅ መንግ
ሥታት ላይ ስለላ አካሂዷል።የፖለቲካ ብጥ
ብጦችንም አቀነባብሯል። በዚህ ፀረ ሰላም
ድርጅት አማካይነት በርካታ ፀረ ኢምፔሪ
ያሊስት አቋም ያላቸው የመንግሥት መሪ
ዎች ግድያ ተፈጽሞባቸዋል ። [11]

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ይህንን ስውር
ደባ በመፈጸም ብቻ አልተወሰነም ። የተለ
ያየ የሽብር ፈጣሪነት ገጽታው ዛሬ በላቲን
አሜሪካ በግልጽ እየታየ ነው ። የላቲን አሜ
ሪካ የተፈጥሮ ሀብት በስፔን የቅኝ አገዛዝ
ሥር ለረጂም ዘመናት ሲበዘበዝና ሕዝቡም
ሲጨቆን እንደቆየ የሚታወስ ነው ። ቅኝ

Digitized by Google

ገዥዋ ስፔን ላቲን አሜሪካ ውስጥ ከቆየች
ባቸው ብዙ ዘመናት መካከል ለ200 ዓመት
ያህል የተጠናከረ ዝርፊያ ስታካሂድ ቆይታ
ለች ። [12] ስፔን ላቲን አሜሪካን ለቃ ከወ
ጣች በኋላ ዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም
በተለይም የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ይህ
ንን አህጉር የብዝበዛ ክልሉ ለማድረግ ታ
ጥቆ ተነሳ ። በ1950 እና በ1957 ዓመታት
መካከል ዩናይትድ ስቴትስ ቀደም ብሎ በላ
ቲን አሜሪካ ለዘረፋ ከላከው ካፒታል ሌላ
3,921 ዐቢሊዮን ዶላር በሥራ ላይ በማዋል
ትርፉ ከካፒታሉ ሦስት እጥፍ የሆነውን
12,819 ቢሊዮን ዶላር ወደ አገሩ ወስዷል።
የአሜሪካ ባለሥልጣኖችም ቢሆኑ በላቲን
አሜሪካና በሌሎች አገሮች ለዘረፋ ተግባር
የተሰማሩ ድንበር ዘለል ኩርፖሬሽኖቻቸው
መጠኑ እጅግ ከፍተኛ የሆነውን ትርፍ እን
ደሚያጋብሱ በይፋ ይናገራሉ ። ለምሳሌ
ፕሬዚዳንት ኬኔዲ በ1960 ስለዚሁ ሲናገር
ባልበለፀጉ አገሮች 200,000,000 ዶላር
በሥራ ላይ ውሎ 1,300,000,000 ትርፍ
ወደ ዩናይትድ ስቴትስ መግባቱን አልደበ
ቀም ። ዛሬም ቢሆን ከዚህ ይበልጥ በተጠ
ናከረ መልኩ ዘረፋ የሚካሄድበት ክልል
ለመሆኑ ብዙ መረጃዎች ይጠቁማሉ ። [13]
የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በዚህ አህጉር
ሕልውና ውስጥ በኢኮኖሚ ዘረፋና በፖለ
ቲካ ጣልቃ ለመግባት የተገደደበት ራሱን
የቻለ ታሪካዊ መንስኤ አለው ።

በአውሮፓ መንግሥታት ላይ የደረሰው
የኃይል ሚዛን መለዋወጥ ፣ በተለይም የስ
ፔን ቅኝ አገዛዝ እየተዳከመ መምጣት ለአ
ሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም መደራጀት አስተ
ዋጽኦ አድርጓል ። ይሁን እንጂ የስፔን አህ
ጉሩን ለቆ መውጣት ለላቲን አሜሪካ ሕዝ
ቦች እውነተኛ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ነፃ
ነት ለመቀዳጀት እንዲችሉ አላደረገም ።
በስፔን ቅኝ ገዥዎች ፈንታ በመላው ዓለም
የብዝበዛ እውታራቸውን የዘረጉት የአሜሪ
ካና የአውሮፓ ኢምፔሪያሊስቶች የራሳቸ
ውን ጥቅም የሚያስከብሩ ፍጹም አድኃሪ
የገዥ መደብ አባላትን ተኩባቸው ።

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ላቲን አሜሪ
ካንን በራሱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ተጽዕኖ
አውታር ሥር ማድረግ የጀመረው ዛሬ አይ
ደለም ፤ ቀደም ብሎ 5ኛው የአሜሪካ ፕሬ
ዚዳንት ጀምስ ሞንሮ በቀየሰው ዶክትሪን
መሠረት ነው ። በወቅቱ የአሜሪካ ኢም
ፔሪያሊዝም የውጭ መመሪያ አድርጐ ያወ
ጣው « ሞንሮ ዶክትሪን » « የአሜሪካ
አገሮች ባገኙትና በሚጠብቁ ነፃ ሁናቴ ፣
ወደፊት ለማንም የአውሮፓ ኃይል ቅኝ ተ
ገዥ የማይሆኑ ናቸው» ሲል ሞንሮ ካወጣው
ፖሊሲ የመነጨ ነው ። [14] የዚህ አባባል
መሠረተ ዓላማ የባህር ማዶ ቅኝ ገዥዎችን
ጣልቃ ገብነትና ወረራን ከአትላንቲክና ከፓ
ስፊክ ውቅያኖሶች በመለስ ለመከላከል የተ
ደረገ ነበር ። ግቡ ግን ባካባቢው የአሜሪካ
ንን ተጽዕኖ ለማጠናከር ተብሎ የተቀየሰ
ነው ። እያደርም የላቲን አሜሪካ መርቶ አደ
ሮች የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የሚፈጽ
ምባቸውን ብዝበዛ ለመከላከል እንዳይነሱ
የማፈኛ መሣሪያ ሆኖ ቀረበ ። የዚሁ የሞ
ንሮ ዶክትሪን (መመሪያ) ተመሥርቶ በ1948
ካራካስ ላይ የተሰበሰበው የፓን አሜሪካ
ጉባዔ ያወጣው መግለጫ «በአሜሪካ ያለው
የፖለቲካ ድርጅት በዓለም አቀፍ የኮሚዩ
ኒስት ንቅናቄ ቁጥጥር ሥር ከሆነና የዓለም
አቀፍ ኮሚዩኒስት ንቅናቄ ወደዚህ ክፍለ
አህጉር ሰርጎ ከገባ የአሜሪካ አገሮችን ነፃ
ነትና የግዛት አንድነት አደጋ ላይ የሚጥል
ስለሆነ አሜሪካ ይኸንኑ የመከላከል መ
ብት አላት » [15] የሚለው መግለጫና ው
ሳኔ ዛሬ የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች የሚያካሂ
ዱትን ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል ለመም
ታት የታቀደ መሆኑን ያስረዳል ።

የሞንሮ ዶክትሪን የላቲን አሜሪካን አህ
ጉር ለብዝበዛ እንደሚዳርግ የተገነዘበው
ሲሞን ቦሊቫር ይህ ዶክትሪን ከወጣ ከ3 ዓ
መት በኋላ በ1826 የፓናማ ኮንግሬስን መሥ
ርቶ የአህጉሩን ሠርቶ አደር የትግል አንድ
ነት በመመሥረት ትግል ጀመረ ። ይሁን
እንጂ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ዓላማ
ውን የሚቃረን ድርጅት ሲቋቋም ቶሎ መመ

Digitized by Google

ልከቱ ስላላዋጣው ከአድኃሪ የገዥ መደብ አባላት ጋራ መመሳጠር ጀመረ ። ይኸንኑ ትግል ለማጨናገፍና አካባቢውን በይበልጥ ለመቆጣጠር እንዲቻል ከ2ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የ «ማካርቲዝም» እና የ «ቀዝቃዛው ጦርነት» ጥላውን በአህጉሩ ላይ ዘርግቶ የነፃነት ትግሎችን ማጨናገፉን ተያያዘው ። በ20ኛው ምዕተ ዓመት መግቢያ ላይ በላቲን አሜሪካ ለአሜሪካ ካፒታል ምቹ የብዝበዛ ሁኔታ ለመፍጠርና የሠርቶ አደሩን ትግል ለማጨናገፍ የሩዝቤልት «ትልቁ በትር» በመባል የሚታወቀው ፖሊሲ ተዘረጋ ። የሩዝቤልት ትልቁ በትር ዓላማ የካሪቢያንን ክልል የኢምፔሪያሊስት አሜሪካ ደሴት ለማድረግ የተቀነባበረ ነበር ። በዚሁ መሠረት የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በአህጉሩ ከወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ሌላ የፖለቲካ ቁጥጥርም እያደረገ ተራማጅ ኃይሎችን መጫን ጀመረ ።

ከ2ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአካባቢው ጠንካራ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል በመካሄድ ላይ እንዳለ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በቀዝቃዛ ጦርነት አማካይነት «ማካርቲዝም» የሚለውን አዲስ ፖሊሲ ቀየሰ ። ከዚሁ ጋር «የፓን አሜሪካ መከላከያ ጁንታ) (Pan American Defence Junta) በመባል የሚታወቀውን ፀረ ተራማጅ ኃይሎች ድርጅት በፔንታጉን አቀነባባሪነት መሠረተ ። ይህ የመከላከያ ጁንታ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎችን የሚያሳድድ ፣ ሲመዘበር በኖረው የአህጉሩ ሕዝብ ላይ ሽብር የሚያካሂድና ሽብር ፈጣሪዎችንም የሚያሰለጥን ነው ። ጁንታው ሕዝባዊ አብዮቶች በተቀሰቀሱበት አካባቢም እየገባ ጸረ አብዮት ድርጊት ያከናውናል ። ለምሳሌ በ1961 የኪዩባን አብዮት ለመቀልበስ የተሞከረው ሴራ ሲከሽፍ ፣ ከ4 ዓመት በኋላ በ1965 40,000 ሠራዊት አሰልፎ የዶሚኒካን ሪፑብሊክን በይፋ በመውረር የመንግሥት ግልበጣ አካሂዶ የራሱን ጥገኛ መንግሥት ለመመሥረት በቅቷል ። [16]

የላቲን አሜሪካ አህጉር በሶሻሊዝም ጎዳና መጓዝ መያያዙን የተገነዘበው የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም አድሀርት ኃይላትን በብዛት ለማፍራት እንዲችል በቋሚነት የስልጠና ማዕከል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ አገኘው ። ለዚህ ተግባር ፀረ ኮሚዩኒዝም አቋም ያላቸውን ግለሰቦች መልምሎ ማሠልጠን የቅድሚያ ተግባሩ ሆነ ። በዚሁ መሠረት በ1974 በካናል ዞን በተቋቋመው ልዩ የማሠልጠኛ ተቋም 70,000 የላቲን አሜሪካ ወታደራዊ መኮንኖች ተራማጅ ኃይሎችን እንዴት እንደሚያጠቁና እንደሚያሰቃዩ አሠልጥኗቸዋል ። በተለይም 150 የላቲን አሜሪካ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ከጠቅላይ ጦር አዛዥ እስከ ካቢኔ አባላት ድረስ በዚህ ተቋም የሰለጠኑ ሲሆን እነዚህ ምልምሎች ዛሬ በአህጉሩ የተለያዩ የገድያ ቡድኖችን በማደራጀትና አመራርም በመስጠት ሽብር ሲፈጥሩ ይታያሉ ። [17]

የኢምፔሪያሊስቱ ዓለም ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ላቲን አሜሪካን በፋይናንስ ካፒታላቸው ማጥለቅለቃቸውንና አህጉሩንም የኢምፔሪያሊስቶች ባዛር ማድረጋቸውን የተገነዘበው ሕዝብ ዛሬ ለኢኮኖሚና ለፖለቲካ ትግል ቆርጦ ተነስቷል ። የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምም ይህንን ሕዝባዊ አመጽ ለመግታት በታጋዮችና በሰፊው ሕዝብ ላይ ሽብር መፍጠሩን ተያይዞታል ። ይህንን መሠሪ ተግባር እንዲያቀነባብር ሲ·አይ·ኤ· ግንባር ቀደም ሚና ተሰጥቶታል ። በሥልጣን ላይ ያሉ ጥገኛ መንግሥታትም በአህጉሩ በመካሄድ ላይ ያለውን ሕዝባዊ አብዮት ለመቅጨት ከሲ·አይ·ኤ· ጋራ ማበራቸው በገሃድ እየታየ ነው ። ይሁን እንጂ በአንዳንድ አገሮች በመካሄድ ላይ ያለው ሕዝባዊ አመጽ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የመሰሎቹን የብዝበዛ ክልል የሚያጠብ ሆኖ በመገኘቱ ልዩ የአፈና ቡድኖችን ከማሠልጠኑ ጎን ወታደራዊ ዕርዳታውንም ከመቼውም የበለጠ እያጠናከረ ነው ። ለምሳሌ በኤልሳልቫዶር ፣ በቺሊና በሌሎችም አካባ

Digitized by Google

ቢዎች በመካሄድ ላይ ያለውን ሕዝባዊ አመጽ የሚያኮላሹ ልዩ ልዩ ወታደራዊ ዕርዳታዎችን ከመስጠቱም ሌላ ልዩ የአፈና ቡድኖችንም በተጨማሪ ያሰለጥናል ። ከ1950 79 መካከል ባሉት ዓመታት 1,971 የኤልሳልቫዶር ከፍተኛ መኰንኖችን ሲያሰለጥን ከ1957-79 በተጨማሪ 4ሺ ልዩ ፖሊስ በመባል የሚታወቁ የጸጥታ ሠራተኞችን አሠልጥኗቸዋል ። [14] እነዚህም በአሁኑ ወቅት የኤልሳልቫዶር ታጋዮችን በመጨፍጨፍና በማሰቃየት ላይ ተሰማርተው የኢምፔሪያሊዝምን ፖሊሲ በተግባር በማራመድ ላይ ይገኛሉ ።

እልቂት እንዴት እንደሚፈጽሙና የነፃነት ታጋዮችን እንዴት እንደሚያድኑ ትምህርት ተሰጥቷቸዋል ። [19] የዚሁ የስልጠና ውጤት ዛሬ በሰፊው የላቲን አሜሪካ ሕዝብ ላይ በተግባር እየተፈጸመ ነው ። እንደ ምሳሌ ከሚጠቀሱት መካከል ኤልሳልቫዶር ካሏት 4,354,000 ሕዝቦች መካከል ከ0.3% በላይ የሚሆኑት በነዚህ ቅጥረኞችና በተባባሪዎቻቸው ማለታቸው ነው ። [20]

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በላቲን አሜሪካ የሚያካሄደው ጭፍጨፋ በተግባር ከተከሰተባቸው አካባቢዎች አንዱ ቺሊ ነው ። በቺሊ የአየንዴ መንግሥት እንዲገለበጥና



የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ሽብር፡ ፈጠራ በላቲን አሜሪካ
(« ሶሻሊዝም ንድፈ ሃሳብና ተግባር » ከተባለው የሶቪየት ህብረት መጽሔት የተወሰደ)

ዛሬ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ሽብር ፈጣሪዎችን የሚመለምለውና የሚያሰለጥነው በማእከላዊ አሜሪካ ብቻ አይደለም ። በ150 የአሜሪካ ጦር ሠፈሮች ከተለያዩ የካፒታሊስት አገሮች የተውጣጡ «ታማኝ ሽብር ፈጣሪዎችን» በማሠልጠን ላይ ይገኛል ። በነዚህ የጦር ሠፈሮች የሰለጠኑ 200,000 ምልምሎች ሲኖሩ እነሱም በኮሚዩኒስቶችና በሌሎች ታጋዮች ላይ አሰቃቂ

ያሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ጥገኛ መንግሥት እንዲመሠረት ተደርጓል ። ይሽንኑ ፋሽስታዊ መንግሥት ለማጠናከር ባንድ ወቅት የአሜሪካ የአገር አስተዳደር ሚኒስቴር ሲናገር «ጥቅማችንን የሚጻረር ድርጊት ዝም ብለን ለመመልከት ትእግስት እንደሌለንና የዚህ ዓይነቱ ትዕግስት ጊዜ ያለፈበት መሆኑን ዛሬ ወዳጆቻችን ጥርጣሬ እንዲገባቸው አያስፈልግም ። የወዳጆቻችን ፍላጐት እኛ

Digitized by Google

ስትራተጂያዊ አካባቢዎችን እንድንይዝ ነው» [21] ብሉ ነበር። ይህ ዛሬ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በላቲን አሜሪካ የሚካሄደውን የሸብር ፈጠራ ተግባር በግልጽ ያሳያል።

ዛሬ በላቲን አሜሪካ በመቀጣጠል ላይ ያለው ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና ተገኛ መንግሥታትን ጭምር ስጋት ላይ ጥሏቸዋል። ይኸንኑ ስጋት በይፋ ከገለጹት መካከል አንዱ ሄንሪ ኪሲንጀር ነው። ኪሲንጀር በ1970 የአየንዴ መንግሥት ሥልጣን እንደያዘ «40 ኮሚቴ» የሚባለውን ፀረ ኮሚዩኒስት ኮሚቴ አጽቁሞ የአየንዴን መንግሥት እንዲገለብጡ መመሪያ በሰጠበት ወቅት «የሕዝቡን ኃላፊነት በመዘንጋት ዛሬ ቺሊ ወደ ኮሚዩኒዝም ስትጓዝ ቆመን የምንመለከትበት ምክንያት የለም»[22] በማለት የተናገረው ያሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል በሚካሄድበት ሁሉ ገብቶ ሽብር ከመፍጠር እንደማይቆጠብ ያመለክታል። በዚሁ ፀረ አብዮት ትንብር መሠረት በቺሊ የተቀጣጠለውን ሕዝባዊ አመጽ ለመቅጨት ሲ.አይ.ኤ. ከያቅጣጫው ፀረ አየንዴ ቡድኖችን በማደራጀት ሥራውን ጀመረ። ለዚህ ተግባር የ8 ሚሊዮን ዶላር (በኢት.ብር 16 ሚሊዮን በላይ) ወጪ በመመደብ ሴራ መጠንሰስ ተጀመረ። በዚሁ መሠረት የአየንዴን መንግሥት ለመገልበጥ 14 ጊዜ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ተደርጐ በመጨረሻ አየንዴ ሲገደል በዚሁ ብጥብጥ 30,000 ሕዝብ አልቋ፣ 200,000 ወደ እስር ቤት ተግዞ፣ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆን ሕዝብ ወደ ጐረቤት አገሮች ለመሰደድ በቅቷል።[23] ፀረ ሕዝብ ኃይሎችም በተቀነባበረ ትግል አየንዴንና ይከተለው የነበረውን የቺሊ ሰፊ ሕዝብ ለሦስት ዓመታት ያህል በመፈታተን አዳከመው የፋሽስት ሥርዓታቸውን መሠረቱ። ከገልበጣውም በኋላ በኮሚዩኒስቶቹ ላይ ሽብር የሚያካሂደውንና የኢምፔሪያሊስት አሜሪካ የጡት ልጅ የሆነው ፒኖቼን በሥልጣን ላይ አስቀመጡ። ከዚህ በኋላ በቺሊ ተራማጅ ኃይሎች ላይ በተፈጸመው ጭፍጨፋ እጅግ ደስ የተሰኘው ኒክሰን «ከፍተኛ የገንዘብ ወጪ በማድረግ የአንድን መንግሥት ስም ለማጉደፍም ሆነ ለማስገልበጥ እንደሚቻል በቺሊ የተደረገው ሙከራ ትምህርት ሰጥቶናል»[24] ብሉ የተናገረው አሜሪካ ሽብር ፈጣሪነትን የፖሊሲው መመሪያ ማድረጉን ያስገነዝበናል። በቺሌ ሕዝባዊ አብዮት ከተቀለበሰበት ጊዜ አንስቶ አብዮታውያን ኃይሎችን የሚያሳድዱና በሲ.አይ.ኤ. አቀነባባሪነት የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችም በመጽጽም ላይ ይገኛሉ። ለምሳሌ በ1979 ወደ ጡረታ ተገልለው ከነበሩ ሠራተኞች መካከል 100,000 ሰዎችን በመመልመል «የነጭ ጦረኞች ኅብረት» (White Warriors Union) የሚባለውን ድርጅት መሠረቱ። ከዚያም ሌላ «የፀረ ኮሚዩኒስት ጦር ኃይሎች አርነትና (The anti-Communist Armed Forces of Liberation) «የፀረ ኮሚዩኒስት ስውር ሠራዊት» (Secret anti-Communist Army) በመባል የሚታወቁትንና ሌሎች በርካታ ስውር የሸብር ፈጣሪ ድርጅቶችን መሥርተው ሕዝቡን እያስጨፈጨፉ ናቸው። የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ነፃነትና የተረጋጋ ማኅበራዊ ኑሮ የጠማውን የላቲን አሜሪካን ሰፊ ሕዝብ ለኋላቀርነት፣ ለእርዛትና ለሰቆቃ በመዳረግ የሚፈጽመው ወንጀል እጅግ የሚዘገንን ነው። እንደዚህ ዓነቶቹ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም መሠሪ ደባዎች በእሲያና በአፍሪካም ጭምር ተዛምተው ዛሬ በየአህጉሩ ለማኅበራዊ ዕድገት ከፍተኛ መሰናክል በመፍጠር ላይ ናቸው።

ለምሳሌ በአፍሪካ አህጉር የሚካሄደው የአርነት ትግል ለመፈታተን ሲ.አይ.ኤ ቢጂንግ በሚባል ስውር ድርጅት አማካይነት ተራማጅ መንግሥታት ላይ የሚያምፁ ፀረ ማርክሲስት ቡድኖችን ይመለምላል። የአንጐላን መንግሥት የሚታወሙት የነሆልደን ሮቤርቶና ዮናስ ሳቪምቢ ቡድ

ችን እንዲሁም የአብዮታዊት ኢትዮጵያን ፀጥታ ለማደፍረስና አንድነቷን ለማናጋት የሚፍጨረጨረው ፀረ ማርክሲስት የገንጣይ ወንበዴዎች ቡድን የዚሁ ትንብር ውጤቶች ናቸው ። እነዚህ አድኃሪ ቡድኖችና የሚገፋፉውና ለሚያካሂዱትም የውንብድ ተግባር አስፈላጊውን ድጋፍ የሚሰጠ ራሱ ሲ.አ.ይ.ኤ. ነው ። [25]

ሆልደን ሮቤርቶ «የአንጎላ ሕዝብ ኮሚዩኒዝምን እንደሚቃወም ምንም አያጠራጥርም» [26] ብሎ መናገሩ የሲ.አይ.ኤ. መልክተኛ መሆኑን በገሃድ ያሳያል ። ዛሬ ይኸው ከሃዲ ሰውር የነበረውን ተልዕኮውን በይፋ ተግባራዊ በማድረግ ከዘረኛው የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ጋር በመሆን ከደቡባዊ የአፍሪካ ክልል ያካባቢ አገሮችን ፀጥታ ሲያደፈርስ ይታያል ። ከዚህም ሌላ ሆልደን ሮቤርቶ የአንጎላን አብዮት ለመቀልበስ ከካፒታሊስት ከተሞች የመጡ የቦዘኔ ጥርቃምዎችን መልምሎ ወደ አብዮታዊት አንጎላ ከወሰዳቸው ቅጥረኞች መካከል አንዱ ከሆልደን ሮቤርቶ ያልተለየ ቃል ተናግሯል ። ይኸው ቅጥረኛ ለምን ወደ አፍሪካ እንደመጣ ሲናገር «ብዕል የሌለኝ የቅጥር ወታደር ነኝ ! — በሕይወት ዘመኔ ሁሉ ለዚ ድርጊት የተሰማራሁና የምወደውም ነኝ ። ይሁን እንጂ አፀያፊ ጦርነት ነው ። አንዳንዶቻችን ግን በቅጥረኛነት ተግባር ለመሰማራት ተገደናል ። እንደሚሰማኝ ኮሚዩኒዝም ለጥቁር አፍሪካ ጥሩ አይደለም ። [27] በማለት የተናገረው የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ፖሊሲ አራማጅ መሆኑን ያመለክታል ።

በአፍሪካ አህጉር ውስጥ ሽብር በመፍጠር የታወቀውና የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ተቀጥያ የሆነው የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ነው ። የደቡብ አፍሪካ ሽብር ፈጣሪ መንግሥት የሽብር ፈጠራ ሥራ ከጀመረ ጊዜው ሰንበት ብሏል ። ለሽብር ፈጠራ ድርጊት የሚጠቀመው በብሮደርቦንድ (Broeder-bond) የአፈናና የግድያ ቡድን አማካይነት ሲሆን ይህም ከጀርመን ናዚዎች አጽም ጋር የረጅም ዘመን ግንኙነት ያለውና ለደቡብ አፍሪካ ጥቂት ነጮች አምባገነንነት የቆመ ዓይነተኛ የሽብር ፈጣሪዎች ድርጅት ነው ። ብሮደርቦንድ ዛሬ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ « በሀቡዕ » ከሚንቀሳቀሰው ዊት ኮማንዶ (Wit Commando) ከሚባለው ሽብር ፈጣሪ ድርጅት ጋር ይሠራል ። የነዚህ የጋራ መፈክር ደቡብ አፍሪካን ከኮሚዩኒዝምና ከሊበራሊዝም እናድን ("Save South Africa from Liberalism and Communism") በሚል ፀረ ኮሚዩኒዝም ዓላማ ላይ የተመሠረተና የጋራ ዓላማቸውም ፀረ አፓርታይድ አቋም ያላቸውን ግለሰቦች መግደል ወይንም ማስገደል ነው። በዚሁ መሠረት በዘር ልዩነት ላይ የተመሠረተውን የሽብር ፈጣሪውን መንግሥት ፖሊሲ ተግባራዊ በማድረግ ዛሬ በጥቁር አፍሪካውያን ላይ የሚደረገውን ጭፍጨፋ በግንባር ቀደምትነት እየመሩ ናቸው ። ብሮደርቦንድ ከደቡብ አፍሪካ ውጭ « በምዕራብ አውሮፓ የዓለም አቀፍ ጥቁር ሽብር ፈጣሪዎች ("Black International Terrorist in Western Europe") ከሚባለው የሽብር ፈጣሪዎች ድርጅት ጋራ የብዙ ዘመን ግንኙነት አለው። አንድ የዩናይትድ ስቴትስ የጠበቆች ኮሚሽን የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ከሽብር ፈጣሪው የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ጋራ ያለውን ግንኙነትና ባጠቃላይም በአፍሪካ አህጉር ላይ ያለውን የፖሊሲ አቋም ሲገልጽ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ከአሜሪካና ከምዕራብ አውሮፓ ነፍስ ገዳዮችን (ቅጥረኞችን) በማሰባሰብና በመላክ ሰብአዊ መብትን እንደሚጻረር በግልጽ አብራርቷል ። [28]

በአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝምና በተባባሪዎቹ አድሀርት ኃይላት የሚመራው የሽብር ፈጠራ ተግባር በግልጽ ከሚካሄድባቸው ቀጠናዎች መካከል አንዱ መካከለኛው ምሥራቅ ነው ። የመካከለኛው ምሥራቅ ሕዝብ ለረጅም ዘመን በኢምፔሪያሊስቶች የብዝበዛ መዋቅር ውስጥ ገብቶ ከመበዝበዙም

Digitized by Google

ሌላ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የተፋት መል
ዕክተኛ በሆንችው በጽዮናዊት እስራኤል
ሰላሙ ከደፈረሰበት ጊዜው ስንበት ብሏል።
ለጽዮናዊት እስራኤል በመካከለኛው ምሥ
ራቅ በኃይል ለመስፋፋት መሠረታዊ ምክ
ንያቶች ከሆኑት መካከል አንዱ የአሜሪካ ኢ
ምፔሪያሊዝም የሚሰጣት የማቴሪያልና የሞ
ራልድጋፍ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም።
በመሆኑም ጽዮናዊት እስራኤል በአሜሪካ
ኢምፔሪያሊዝም ድጋፍ ሰጪነት የ « ታላቋ
እስራኤልን » ግዛት ለመመስረት እንድት
ችል በአካባቢው ሕዝብ ላይ በተለይም ለዚህ
ተግባሯ እንቅፋት ሆና ባገኘችው በፍልስጥ
ኤም ሕዝብ ላይ ጭፍጨፋን ታካሂዳለች።

ሪካ ኢምፔሪያሊዝም በመካከለኛው ምሥ
ራቅ የሚካሄደውን ማንኛውንም ፀረ ኢም
ፔሪያሊስት ትግል ለመግታት እንደጽዮና
ዊት እስራኤል ባሉ ጥገኛ መንግሥታት
መጠቀም ከተያያዛቸው ስትራቴጂያዊ
አሠራሮች መካከል አንዱ እንደሆነ ያስ
ረዳል ። ከዚህም ሌላ በመካከለኛው ምሥ
ራቅ የኢምፔሪያሊዝም ሕልውና እንዲ
ጠበቅ እንደ ጽዮናዊት እስራኤል ላሉ የኢ
ምፔሪያሊስት ተቀጥላ መንግሥታት የጦር
መሣሪያን ማቀበልና አርነት ወዳዶችን ማስ
ጨረስ ከተያያዛቸው መሰሪ ደባዎች መካ
ከል ጥቂቶቹ ናቸው። ይህ ደግሞ በእስራኤል
ብቻ ሳይወሰን በአፍሪካም እንደ ፕሪቶሪያ

የእሥራኤል ሽብር ፈጣሪነት በአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ሲደገፍ
«ሆሪዞን» ከተባለ የጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፓብሊክ መጽሔት የተወሰደ ።

በቅርቡ በፍልስጥኤምና በሊባኖስ ዜጎች
ላይ የፈጸመችው አሰቃቂ እልቂት ለዚህ
ጉልህ ማስረጃ ነው ። ለፈጸመችው እል
ቂት ከዓለም አካባቢ ውግዘት ሲሰነዘርባት፣
የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ምንም ዓይነት
የማውገዝ ድምጽ አላሰማም። ይህም የአሜ

ሽብር ፈጣሪ መንግሥት ያሉትን በመሣሪ
ያነት መጠቀምንም ይጨምራል ። ዛሬ ጽዮ
ናዊት እስራኤልና ሽብር ፈጣሪው የደቡብ
አፍሪካ መንግሥት በመካከላቸው የቅርብ
ግንኙነት ፈጥረው ይገኛሉ ። እነዚህ ሽብር
ፈጣሪ መንግሥታት ጦር መሣሪያ ከሚያቀ

Digitized by Google

ብኋቸው ኢምፔሪያሊስት አገሮች ጋራ ጠንካራ ወታደራዊ ግንኙነት አላቸው ። ከወታደራዊ ግንኙነት ሌላ ዛሬ የኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ጦር መሣሪያ ፋብሪካዎች በአገሮቻቸው አቋቁመውላቸው ዘመናዊ መሣሪያ ጭምር እንዲያመርቱ አድርገዋቸዋል። ከዚህም ባሻገር ዛሬ በጉልህ እንደሚታየው ሽብር ፈጣሪው የፐሪቶሪያ መንግሥትና ጽዮናዊት እስራኤል የጉረቤት አገሮችን ፀጥታ በማደፍረስ ፣ ሽብር በመፍጠር ፣ አርነት ወዳዶችን በማሳደድ ፣ በፀረ ኮሚዩኒዝም አቋም ፣ በዘር ልዩነት የሚያምኑና የኢምፔሪያሊስቱ ተቀጥላ መንግሥታት ሲሆኑ ፣ ሕልውናቸውም ከኢምፔሪያሊስቶች በተለይም ከአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ሕልውና ጋር የተሳሰረ ነው ።

የኢምፔሪያሊስቱ ዓለም ዛሬ በየቦታው የሚያሳየው የጠብ አጫሪነት ባህርይ ፣ የሽብር ፈጣራ ተግባር ፣ የሌሎች አገሮች የግዛት ሕልውናን አለማክበርና ጀብደኝነት የተሞላበትን ጣልቃገብነት ነው ። ይህ በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ የኢምፔሪያሊስቱ ካምፕ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰላም እንዳይረጋጋና ሕዝቦችም ማኅበራዊ ብልጽግናና ዕድገትን እንዳይጐናፀፉ ያለውን አድኅሪ ዓላማ ያስረዳል ። ይኸ የኢምፔሪያሊዝም የጦረኛነትና የሽብር ፈጣሪነት ፖሊሲ ከካፒታሊዝም ሥርዓት የሚመነጭ ውስጣዊ ባህሪው ነው ።

በካፒታሊስቱ ዓለም ለሽብር ፈጣሪነት ተግባር ከሚያገለግሉ ማኅበራዊ ክፍሎች መካከል ብዙ ወጣቶች ይገኙበታል ። የኢምፔሪያ ሊስቱ ዓለም የአመራረት ዘይቤ ሥርዓተ አልባነትን የተከተለ በመሆኑ የቴክኖሎጂ መስፋፋት የወጣቱን የሥራ ማግኘት ዕድል አጣቧል ። ለዚህም ጉልህ ማረጋገጫ በ1970 አጋማሽ ላይ በፈረንሳይ 45.8% ፣ በኢጣሊያ 32.7% ፣ በእንግሊዝ 30% ፣ በቤልጅግ ከ30% በላይ፣ በዴንማርክ 47.2 ፣ በሆላንድ 37.6% ፣ በፌዴራል ጀርመን 28.4% ወጣቶች ሥራ አጥ መሆናቸው ነው ። በ1980 በአውሮፓ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የወጣት ሥራ አጦች ብዛት 40% ሲደርስ የነዚሁ አማካይ ዕድሜም ከ25 ዓመት በታች ነበር ። በዚሁ ማኅበረሰብ ከልል በያመቱ ትምህርታቸውን ከሚያጠናቅቁ 5 ሚሊዮን ወጣቶች መካከል አንድ ሚሊዮን ወጣቶች ሥራ በማጣት የኅብረተሰብ ሸክም ይሆናሉ ።

ወጣቱ የወደፊት አገር ተረካቢና ገንቢም ነው ። በመሆኑም ባፍላ ጉልበቱ መጠቀምና የሥራ ምርታማነቱን ማሳደግ እንዲችል ማድረግ ተቀዳሚነት ያለው ተግባር ነው ።ይሁን እንጂ በዘመናችን የወጣቱን አገር ገንቢነትና የወደፊት አገር ተረካቢነት በሚመለከት በተለይም በካፒታሊስቱ ዓለም ትኩረት አልተሰጠውም ። ዛሬ ያለውን የወጣቶች ብዛት በሚመለከት ረገድ ዕድሜያቸው ከ25 ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶች የዓለምን ሕዝብ ቁጥር ግማሽ ይሆናሉ ተብሉ ይገመታል ።በአንዳንድ አገሮች ከመቶ 60% እና 70% ሲደርስ ፣ ይህ ቁጥር በ1990 ገደማ ማለትም ከ7 ዓመት በኋላ 4,000 ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል ። ዛሬ በአውሮፓ ብቻ 250 ሚሊዮን ወጣቶች ሲኖሩ ይህ የወጣቶች ቁጥር ከፍተኛ ዕድገት ማሳየት ከሥራ አጥነት ጋር ተዳምሮ በያዝነው ምዕተ ዓመት ማብቂያ ላይ የካፒታሊስቱን ዓለም ከፍተኛ ችግር ላይ እንደሚጥለው አይጠረጠርም ።[29]

እነዚህ የኅብረተሰብ አባላት የካፒታሊዝም ሥርዓት በፈጠራቸው ቀውሶች ሳቢያ የሥራ ዕድል አጥተው በድህነትና ተስፋ በመቁረጥ በሰቀቀንና በሐዘን ይኖራሉ ። በካፒታሊስቱ ዓለም በሥራ ማጣት የተነሳ የቤተሰብ ጥገኛ ሆነው የወደፊቱ ዓለም ኑሮ የጨለመባቸው ወጣቶች በርካታ ናቸው ። በዚሁ የተነሣ ወጣቱ ለማኅበራዊ ኑሮ ያለው አመለካከት በጣም ዝቅተኛ ነው ። ለምሳሌ በእንግሊዝ አገር በያመቱ ከሚወለዱት ሕፃናት ይልቅ የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር እየበዛ ነው ። በፌዴራል ጀርመን በያመቱ ከ6,000 በላይ የሚሆኑ ወጣቶች ራሳቸውን ሲገ

Digitized by Google

ድሉ ፣ 10,000 ደግሞ ራስን የመግደል
ሙከራ ይፈጽማሉ ። በግሪክ ከ13 እስከ
20 ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚገ
ኙት ወጣቶች መካከል 60% የሚሆኑት
የመድኃኒት ሱሰኛ ሆነዋል ። በአሜሪካ
ከ20 እስከ 25 ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ
ካሉት ወጣቶች የሚሞቱት ቁጥር በያመቱ
እየጨመረ ነው ።[30]

ይህ ማኅበራዊ ችግር በተያያዝነው ምዕተ
አጋማሽ ላይ በካፒታሊስት ዓለም ያሉ ወጣ
ቶችን ለሽብር ፈጣሪዎች ድርጅት እንዲጋ
ለጡ አድርጓቸዋል ። ለዚህ ተግባር እንዲጋ
ለጡ የተገደዱበትም ምክንያት በተፈጥሮ
አመፅን ለማካሄድ ፈልገው ሳይሆን ከቁጥ
ጥራቸው ውጭ በሆነ ማኅበራዊና ኢኮኖ
ሚያዊ ችግር የተነሳ ትዕግሥታቸውን ስለ
ጨረሱ ነው ። ይህንን የኅብረተሰብ ትኩስ
ኃይል ባመቺ ሁኔታ መገኘት የተገነዘቡ
የሽብር ፈጣሪ ድርጅቶች አጋጣሚውን
በመጠቀም ወጣቱን ለራሳቸው ዓላማ ማስ
ለፍን ሥራዬ ብለው ተያይዘውታል ። ለም
ሳሌ በኢጣሊያ « ብላክ ኦርደርና» « የሞ
ሶሎኒ ድርጊት ፈጣሪ ቡድን» በእንግሊዝ
«የእንግሊዝም ንቅናቄና ብሔራዊ ግንባር ፣
በአሜሪካ ኩ ኩሉክስ ክላን እና « ወጣት
አሜሪካውያን ለነፃነት» ፣ «በጃፓን ሬንጉ
ሲኪገን » ፣ በፈረንሳይ « ላ አክሲዮን » ፣
በፌዴራል ጀርመን «ራፍ ሮቴ አርሚ ፍራ
ክሽን» (Raf-Rote-Arme-Fraktion) ተብ
ለው የተቋቋሙት የሽብር ፈጣሪዎች ድር
ጅቶች ወጣቱን የኢምፔሪያሊዝም የውጭ
ፖሊሲ አራማጅ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።[31]

ዛሬ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በአሜ
ሪካ ግዛት ሰላም እንዲሰፈንና ምንም የሽብር
ፈጣሪ ድርጅቶች እንደሌሉ በማስመሰል
ያናፍሳል ። ሐቁ ግን የተጠናከረና ራሳቸው
የአሜሪካ ባለሥልጣኖች ጭምር አባል የሆ
ኑበት ድርጅት በአሜሪካ ግዛት በይፋ ሽብር
በመፍጠር ላይ መገኘቱ ነው ። በአሜሪካ
ግዛት የረጅም ዘመን ዕድሜ ካላቸው የሽብር
ፈጣሪ ድርጅቶች መካከል ኩክሉክስ ክላን
(Ku Kluks Klan "KKK") በመባል የሚ
ታወቀው ድርጅት ሲሆን ዛሬ በዘመናዊ
ትጥቅ የተደራጁ 50,000 አባላት አሉት ።

በአሜሪካ ግዛት ሜሪላንድ ያለውን የዚህ
ድርጅት መሪ በ1970 አንድ የሶሻሊስት
አገር የዜና ወኪል ላቀረበለት ጥያቄ ሲመ
ልስ ጥቁሮች ወደ አፍሪካ ለመመለስ ፈቃ
ደኛ ሆነው ስላልተገኙ እነሱ የሚጠፉ
በት የጉጣ ጦርነት እንደሚካሄድና ተመ
ሳሳይ እልቂትም በአይሁዶችና በኮሚኒስ
ቶች ላይ እንደሚፈጸም በግልጽ ተናገሯል።
ቀጥሎም አባላቱ ሥልጣናን እንዴት እንደ
ሚያገኙ ተጠይቆ ሲመልስ ፣ የአሜሪካ መን
ግሥት ወታደሮች (በቂ ሥልጣና ያገኙ)
በምስጢር አባል ሆነው እንደሚያገለግሉና
በቬትናም ጦርነት ተካፋይ የነበሩ ወታደር
ችም እንዳሉበት ተናግሯል ። ከዚህም ሌላ
ይኸው ድርጅት በየቀኑ አባላትን በመመ
ልመልና ዘመናዊ መሣሪያን በማከማቸት
በኩልም ከፍተኛ እንቅስቃሴ እንደሚያደ
ርግ አልደበቀም ። የድርጅቱን አባላት ሁኔታ
በሚመለከት ረገድም ሲጠየቅ ከተራ ሠራ
ተኛ እስከ ፖለቲካ መሪዎች ፣ ነጋዴዎች ፣
ተማሪዎች ፣ ጠበቆች ፣ ዶክተሮችና የወህኒ
ቤት አስተዳዳሪዎች ያሉበት መሆኑን ጠቁሞ
የስም ዝርዝር ግን በምስጢር እንደሚያዝ
ገልጿል ።

ኩ ክሉክስ ክላን በ1866 የሂትለር ፓርቲ
(ናዚ ፓርቲ) በምድረ ጀርመን ከመመሥ
ረቱ በፊት የተመሠረተ ፣ ጥቁሮችን አሳድዶ
በማሰቃየትና በመግደል ላይ ያተኮረ የዘረኛ
ነጮች ድርጅት ነው ። በዚህ ተግባሩ በብዙ
ጥቁር አሜሪካውያን ላይ ግድያን ፈጽሟል።
እያደረም ብዙ ተቃውሞ ቢሰነዘርበትም
ጨርሶ ሊጠፋ አልቻለም ። በመሆኑም በየ
ቀኑ እየተጠናከረ መጥቶ በአንድ ወቅት
200 ጥቁሮችን በአሰቃቂ ሁኔታ በቢላዋ ሲያ
ርዳቸው ፣ በ1980 ላይ የ3,000 አይሁዶችን
መቃብር በማፈራረስ ግፍ አድራጊነቱን
በይፋ አጋልጧል ።

ኩ ክሉክስ ክላን ዛሬ ዘረኝነትን መሠረት
አድርጐ ከሚያካሂደው ሽብር ፈጠራ ጐን

Digitized by Google

ፀረ ኮሚኒዝም ከፍ በማለት « ከአሜሪካ
ሪካ ናዚ ፓርቲ » ጋር ተባብሮ በመሥራት
ላይ ይገኛል ። ከዚህም ሌላ አባላቱን በአሜ
ሪካ የጦር ኃይል ውስጥ አሠርጐ እያስገባም
ይሠራል ። የአባላቱን ቁጥር ለመጨመርም
በየቀኑ ወጣቶችን በመቀስቀስ ይመለምላል።
ባቋቋመው ልዩ የማሠልጠኛ ሥፍራ ከ10
እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ወጣቶች
በመመልመል ስለ ድርጅቱ ዓላማና ስለጦር
መሣሪያ አጠቃቀም ያስተምራቸዋል ። ቢል
ዊልክሰን የሚባለው የዚሁ ድርጅት ተቀ
ዳሚ መሪ ስለ ድርጅቱ መሠረታዊ ዓላማ
ሲናገር « ጠመንጃችን ጥንቸልን የምናድ
ንበት ሳይሆን የሰውን ልጅ የምናጠፋበት
ነው » በማለት በይፋ ለሽብር ፈጠራ መቆ
ሙን በገሀድ ያሳያል ። አንዳንድ የአሜሪካ
ፕሬዚዳንቶችም ቢሆኑ ይህ የሽብር ፈጣሪ
ድርጅት በአሜሪካ ግዛት በሽብር ፈጠራ
መሰማራቱን በይፋ ቢያውቁም በድርጊቱ
ላይ የተቃውሞ ቃል አለማሰማታቸውም
በስውር የሚደግፉት መሆኑን ያመለክታል።

ከኩ ክሉክስ ክላን ቀጥሎ በአሜሪካ ውስጥ
ሌላ የጆን ቢርች ኅብረተሰብ (The John
Birch Society) የሚባለው ከ100,000 አባ
ላት በላይ ያሉት የቀኝ አክራሪ ድርጅት
አለ ። በአባላት ብዛት ከኩ ክሉክስ ክላን
ከመብለጡም ሌላ በዚህ ድርጅት ውስጥ የአ
ገሪቱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖችም አሉበት ።
የጆን ቢርች ኅብረተሰብ መሠረተ ዓላማ ከሽ
ብር ፈጠራ ተግባር ጐን በአሜሪካ ውስጥ
ቀውጢ ቀን ቢመጣ ጭልጥ ያለ ቀኝ አክ
ራሪ አቋም ያላቸውን ግለሰቦች በሥል
ጣን ላይ ለማስቀመጥ የሚሠራ ድርጅት
ነው ።[32]

የኢምፔሪያሊስቱ ዓለም ሽብርን ለማስ
ፋፋት የሚጠቀመው በወጣቱ ኃይልና በስ
ውር በሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ብቻ አይደ
ለም ። በካፒታሊስት አገሮች የቴክኖሎጂ
መስፋፋት የወጣቱን የሥራ ዕድል እንዳጣ
በበ ሁሉ ብዙ ሠራተኞችንም ከሥራ ፈንቅ
ሏቸዋል ። ይህ የሠራተኞች ከሥራ መባረ
ርና ሠራተኞቹ በማሺን የመተካት አዝማ
ሚያ የካፒታሊዝምን አጠቃላይ ቀውስ ቢያ
መለክትም በዚሁ መዘዝ ከሥራ የተፈናቀ
ሉት አንዳንድ ሠራተኞች ለሽብር ፈጣሪ
ነት በተቋቋሙ ድርጅቶች ውስጥ በመግ
ባት ለኢምፔሪያሊዝም ፖሊሲ መልዕክተኛ
ሆነው እንዲሠሩ አስገድዷቸዋል ። በብዙ
የካፒታሊስት አገሮች ያሉ ቦዘኔዎች ለወረ
ራና ለሽብር ፈጠራ ተልዕኮ በመገዛት ከራ
ሳቸው ድንበር ውጭ በመሄድ ሥርነቀል አብ
ዮት በሚያካሂዱ አገሮች ላይ አመጽና
ሽብር የሚያካሂዱ መሆናቸው የታወቀ ነው።
በአገር ውስጥም ቢሆን ዛሬ ብዙዎቹ የካፒ
ታሊስቱ ዓለም ከተሞች በሽብር ፈጣሪዎች
እየተናወጡ ናቸው ።

ዛሬ በተለይም በአሜሪካ ከተሞች የዝር
ፊያ ፥ የግድያና የረቂቅ ወንጀሎች ማየል
ብዙ ሕዝብ ከቤቱ ተወስና እንዲኖር ወይ
ንም በቡድን እንዲንቀሳቀስ አስገድዶታል።
ባሁኑ ጊዜ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ
በመፈጸም ላይ ያለው የወንጀል ድርጊት
በያመቱ ከሚወለደው የሕዝብ ቁጥር ብዛት
በመብለጥ ላይ ይገኛል ። ለምሳሌ በያመቱ
የሕዝብ ብዛት በ14% ሲጨምር የወን
ጀል ድርጊቶች ግን ከዚህ የላቀ ነው ።
ባለፉት10 ዓመታት በአሜሪካ ከተሞች
አካባቢ የኑሮ ዋስትና በመጥፋቱ የከተማ
ኑሮ አስተማማኝ ባለመሆኑ ፥ የሕዝብ ብዛት
በአንድ ሚሊዮን እየቀነሰ መጥቷል ። በከ
ተሞች ክልል በየቀኑ የሚፈጸሙት የወን
ጀል ድርጊቶች ከፍተኛ በመሆናቸው እሥር
ቤቶችም ከመቼውም የበለጠ ተጣብበው
ይገኛሉ ። ዛሬ በአሜሪካ ውስጥ ከሩብ ሚሊ
የን ሕዝብ በላይ በወንጀል ድርጊት ታስ
ሯል ።

የአሜሪካ የፌዴራል ምርመራ ቢሮ
(FBI)ዛሬ በአሜሪካ ስላለው የፀጥታ ሁኔታ
ሲናገር ከ10 ዓመታት ወዲህ ወንጀል በ55%
መጨመሩን ገልጿል ።በ1980 23,044 ሰዎች
ግድያ ፥ በ82,088 ሴቶችን የመደፈር ወን
ጀል ፥ 654,054 ድብደባና 11 ሚሊዮን ዝር
ፍያ ተካሂዷል ። ዛሬም ቢሆን በየ23 ደቂቃ
አንድ ግድያ ፥ በየስድስት ደቂቃ ሴትን አስ
ገድዶ የመድፈር ወንጀል ፥ በየ58ቱ ሰኮንድ
በመሣሪያ በማስፈራራት የሚፈጸም ዝር

ሬያ ፣ በየ33 ሰከንድ የመኪና ስርቆት ይፈ
ጸማል ። የአሜሪካ ባለሥልጣኖች የወንጀሉ
መንስኤ ከሆኑት መካከል ሱስ የሚያስይዙ
እፅዋት እንደሆኑ ቢያውቁም በአደገኛ እጾች
ላይጥብቅ እርምጃ እንዲወሰድ ለማድረግ አል
ተዘጋጁም ። ከዚህም ሌላ ዛሬ ዩናይትድ ስቴ
ትስ ሱስ የሚያስይዙ መድሐኒቶችና እፅዋት
የሚገበዩበት መናኸሪያ ሆኗል ። በሚሊዮን
የሚቆጠሩ ዜጎች በኮኬይን ፣ በሄርይን፣በማ
ሪዮዋናና በኤል. ኤስ. ዲና በሌሎችም ሰው
ነት ላይ አደጋ በሚፈጥሩ ዕፅዋት እየተጠ
ቀሙ ነው።የዚህን የሞኖፖል ንግድ የሚያካ
ሂደውን ማፊያ የተባለው የዘራፊዎችና የወ
ርበሎች ድርጅት ነው ። ማፊያ የዚህን የዕፅ
ንግድ በሚያደናቅፉ ግለሰቦች (ድርጅቶች)
ላይ ከአፈና ጀምሮ እስከ ግድያ ድረስ በመፈ
ጸም የፈለገውን ለማድረግ የሚችልና ምንም
ቁጥጥር የማይደረግበት ፣ በአደረጃጀቱና በገ
ንዘብ ኃይል ዛሬ በዓለም ውስጥ አሉ ከሚ
ባሉ ከ500 ትላልቅ ኩባንያዎች የሚበልጥ
ነው ። ይኸው ድርጅት ከታዋቂ የፖለቲካ
ሰዎች ፣ ከፖሊሶችና ከትላልቅ ነጋዴዎች
ጋራ ግንኙነት ሲኖረው ፣ በርካታ የአውሮ
ፕላን ማረፊያዎች ፣ ወደቦች ፣ የከባድ መኪና
መናኸሪያዎችና የአነስተኛ ትራንስፖርት
ዘርፎችን ይቆጣጠራል ። ከሚያካሂደው የን
ግድ ትርፍም ከፊሉ ወደ መድህንና ወደተደ
ራጁ የወንጀል ድርጅቶች ይተላለፋል ።[33]

የዚህ ዓይነት ማኅበራዊ ምስቅልቅልነት
የሚታየው በአሜሪካ ብቻ ሳይሆን በሌሎ
ችም የካፒታሊስት አገሮችም ጭምር ነው።
በእንግሊዝ አገር ያለው ማኅበራዊ ሁኔታ
በአሜሪካ ውስጥ ከተፈጸመ ካለው የወን
ጀል ድርጊት ጋራ ተመሳሳይነት አለው ።
በዚሁ አገር በ1981 የወንጀል መጠን 10%
በላይ ሲያድግ ከ3 ሚሊዮን በላይ የወንጀል
ድርጊት ተፈጽሟል ። የአገሪቱ ፖሊስ እን
ደመዘገበው በ1981 ፣ 557 ሰዎች በወንጀለ
ኞች ተገድለዋል ። 19,000 ሴቶች ላይ የመ
ደፈር ወንጀል ተፈጽሞባቸዋል ። ዛሬ ከ
1,900 በላይ የሆኑ በትጥቅ የተደራጁ ዘራፊ
ዎች የከተማውን ፀጥታ በማወክ ላይ ይገ
ኛሉ ። የአደገኛ ዕፅ በብዙ ወንጀለኞች እጅ
መግባት ሁኔታውን የከፋ አድርጎታል ።
የእንግሊዝ መንግሥትም ይህን ሁኔታ ለመ
ቆጣጠር ስላቃተው በብዙ ሚሊዮን ፓው
ንድ የሚቆጠር ወጪ በመመደብ ሕዝቡ
ራሱን በራሱ እንዲከላከል ጥሪ አስተላል
ፏል ። ባወጣው መግለጫ መሠረትም ወን
ጀሉን በቁጥጥር ሥር ለማዋል እንዲቻል
የተራቀቀ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎችን
ለመሥራት የሚችሉ 60 ታዋቂ ኩባንያዎች
መጽጽግቸውንም ገልጿል ። ከዚህም ሌላ
የእንግሊዝ ፖሊስ አርጊቶች ከቀኑ ከአሥር
ሰዓት በኋላ ከቤታቸው እንዳይወጡ ፣ በማ
ንኛውም ጊዜ የእጅ ቦርሳ እንዳይዙና ብቻ
ቸውን እንዳይሄዱ አስጠንቅቋል ። በትላ
ልቅ ከተሞች አደጋ ሲፈጠር የማስደንገጫ
መሣሪያ (ፖሊሶችን የሚጠራ መሣሪያ) ቢሠ
ራም ወንጀለኞቹ በቀላሉ የሚለማመዱት
ስለሆነ በዚህ በኩል ያለው ቁጥጥር እምብ
ዛም ተግባራዊ አልሆነም ። ለመከላከያነት
ይረዳሉ ተብለው የተለያዩ መጻሕፍት ቢታ
ተሙም ውድ ከመሆናቸውም የተነሳ ለወ
ንጀል የተጋለጠው የኅብረተሰቡ ክፍል ሊገ
ዛቸው አልቻለም ። ዛሬ በለንደን ከተማ
ከ30,000 በላይ የሚሆኑ መኖሪያ ቤት የሌ
ላቸው ወጣቶች መኖር በአጠቃላይ በእንግ
ሊዝ አገር 3,224,715 በውል የተመዘገበ
ሥራ አጥ መኖሩ ከሽብር ፈጠራ ተግባር መስ
ፋፋት ጋር የተዛመደ መሆኑ ግልጽ ነው ።[34]
የታቸር አስተዳደርም ምስቅልቅሉ የወጣ
ውን ይህን ሥርዓት ለመሸፋፈን የፕሮፓጋ
ንዳ ዘመቻ ቢያካሂድም ሁኔታው ከቁጥጥሯ
ውጭ በመሆን ላይ ነው ። ይህ ሁኔታ በአሜ
ሪካና በእንግሊዝ ብቻ ሳይወሰን በሌሎች
የካፒታሊስት አገሮችም በተመሳሳይ ሁኔታ
እየተከሰተ ነው ። ለምሳሌ በ1975 በጃፓን
ከ234,304 እና በኢጣሊያ ከ2 ሚሊዮን በ
ላይ ወንጀሎች ተፈጽመዋል ።[35] ይሁንና
ኢምፔሪያሊዝም ይህንኑ ትርምስ የሞላበ
ትን ሥርዓት በሚመለከት የዓለምን ሕዝብ
አስተያየት ለመለወጥ የሚያካሂደውን የፕ

Digitized by Google

ሮፓጋንዳ ዘመቻ ከተደኖው ይበልጥ በከፍተኛ ደረጃ ተያይዞታል ።

ዛሬ ፀረ—ኰሚኒስት ፕሮፓጋንዳ የኢምፔሪያሊስት ፖሊሲ ዓይነተኛ መሣሪያ ከመሆኑም ሌላ እጅግ አስፈላጊ ከሆኑ የሽብር ፈጠራ መሣሪያዎች መካከል አንዱ ነው ። የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የተራቀቁ የመገናኛ ዘዴዎች ሲኖሩት በእነዚህ አማካይነት ፀረ ኮሚኒዝም ዘመቻ በማካሄድ የዓለምን ሕዝብ አስተያየት መበከልና ሥነ ልቦናዊ (Psychological Warefare) ጦርነት ማካሄድ አንዱ ተግባሩ ነው ። ዛሬ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በ111 አገሮች ከ301 በላይ የፕሮፓጋንዳ ማዕከሎች ሲኖሩት በእነዚሀ ሥፍራዎች 1,200 አሜሪካውያንና ከ5,300 የውጭ ዜጎች በላይ በዚሁ ሥራ እንዲሠማሩ አድርጓል ። በ120 አገሮች ከ223 በላይ መጻሕፍት ቤቶችና ንባብ ቤቶች ሲኖሩት በእነዚሁ ውስጥ በየዓመቱ 350 ሚሊዮን ሕዝብ ይስተናገዳል ። በየሳምንቱ በ47 ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሚታተሙ 400,000 በራሪ ወረቀቶችና ፓምፍሌቶች ተዘጋጅተው ወደ 115 አገሮች ይላካሉ ። በየዓመቱ ከ799 በላይ ልዩ ልዩ መጻሕፍት ታትሞ ከ6,000,000 ቅጂ በላይ ያሠራጫል ። በአሜሪካ ድጋፍ ሰጪነት በ 2,082 ቴሌቢዥን ጣቢያዎች አማካይነት የቴሌቢዥን ፕሮግራም ወደ 94 አገሮች ይተላለፋል ።«የአሜሪካ ድምጽ» በመባል የሚታወቀው ራዲዮ ጣቢያ በአሜሪካ ግዛት ውስጥ 41 የማስተላለፊያ ጣቢያዎች ሲኖሩት ፣ ከአሜሪካ ውጭ ደግሞ 61 ጣቢያዎች አሉት ። በሳምንት 845 የራዲዮ ሰዓት ዝግጅቶችን ሲያስተላልፉ ለዚሁም በ38 ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ይጠቀማል ። በዓለምአቀፍ ደረጃም በየቀኑ የሚሰራጨው የአሜሪካ ራዲዮ ዝግጅት ከ25 ሚሊዮን በላይ አድማጮች አሉት ። ከዚሁም በተጨማሪ የአሜሪካ ወታደራዊ ተቋም ከአሜሪካ ውጭ 250 የራዲዮና 34 የቴሌቪዥን ጣቢያዎች አሉት ። እነዚህ ሁሉ ዋንኛ ፀረ—ኮሚኒስት ፕሮፓጋንዳ ማሰራጫት ነው ።[36]

የኢምፔሪያሊስት አገሮች የሚያካሂዱትን ፀረ ኮሚኒዝም ቅስቀሳና ሽብር ፈጣሪነት ዕድሜያቸውን ለማራዘምና የዓለም ሕዝቦችን አብዮታዊ እንቅስቃሴ ለመግታት የሚጠቀሙበት መሣሪያ ነው ። ፀረ ኮሚኒዝም ፕሮፓጋንዳ እና ሽብር ፈጠራቸው አስፈላጊነቱና ታዳጊነቱ ያበቃለትን የቡርዧው መደብ የበላይ ገዥነት ለማቆየት ኢምፔሪያሊዝምና አድኅሮት ኃይላት የሚጠቀሙበትን ዓይነተኛ የፖሊሲ መሣሪያ እየሆነ መጥቷል ። በዚህ የፀረ ኮሚኒስት የትግል ስልታቸው አማካይነትም ሶሻሊዝምንና የኰሚኒስት ፓርቲዎችን በማንቋሸሽ የሶሻሊስትን ሥርዓት ባልገነቡ አገሮች ዘንድ ሶሻሊዝም እንዲጠላ ማድረግ አንዱ ተግባራቸው ሆኗል ። ከዚህም ሌላ የግንባር ቀደም ማሌ ፓርቲዎችን ርዕዮተዓለማዊና ድርጅታዊ አንድነት ለማናጋት ለከላሾችና ለበራዦች ድጋፍ በመስጠትና በማስተባበር ኮሚኒስት ፓርቲዎች በከላሽነት እንዲበከሉ ደባ ሲሰሩ ኖረዋል ። ይሁን እንጂ የሶሻሊዝምን ግስጋሴ ለማቆም አያሌ ቢሊዮን ዶላር በማፍሰስ የፕሮፓጋንዳ ወናፍ በዓለም ዙሪያ ለማሠራጨት ብዙ ቢሞክሩና ሽብርን ቢፈጥሩም ያሰቡት ሊሳካላቸው አልቻለም ። ኢምፔሪያሊዝም በውስጡ ያዘላቸው ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ቀውሶች እያመረቀዙ መሄዳቸውና ይህም ሂደት የኢምፔሪያሊዝምን ሽንፈት ማስከተሉ የታሪክ ሕግ በመሆኑ ፣ ኢምፔሪያሊዝም በፖሊሲ ደረጃ የሚያራምደው ሽብር ፈጣሪነት አላፊ ጠፊ ከመሆን አያድነውም ።

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻ

1. *International Affairs*: A Monthly Journal of Political Analysis, No. 4, April 1982, p. 46.
2. V. I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 30, 30, p. 181.
3. *Marx and Engles Selected Correspondence*, (Moscow: Progress Publishers, 1975), pp. 233-234.
4. International Affairs p. 47.
5. Henry Ernest, *Stop Terrorism* (Moscow: Novosty Press Agency, 1982), p. 6.
6. *Ibid.*, p. 9.
7. *Ibid.*, p. 49.
8. International Affairs, p. 48.
9. *Ibid.*, p. 49.
10. New Dawn, No. 2 /147/, 1983, p. 41.
11. International Affairs, p. 52.
12. Eduardo Galeano, *Open Veins of Latin America*: Five Centuries of the Pillage of the Continent, Monthly Review Press, New York, 1973, p. 33.
13. *Ibid.*, pp. 246-47.
14. Great Soviet Encyclopaedia Volume, 16, (MacMillan, Inc. New York 1977) p. 533.
15. CISCAC, Committee in Solidarity with Central America and the Carib bean, *El Salvador*: A Dossier, Sydney 1981, pp. 31-32.
16. *Ibid.*, 30.
17. *Ibid.*, 31.
18. *Ibid.*, 32.
19. *Ibid.*, p. 56.
20. *Monthly Review*: An Independent Socialist Magazine, Vol. 32, No. 11, 1981, New York, pp. 8-9.
21. CISCAC, Publications. p. 39.
22. Joseph Fickes and Stephen Orlofsky, *The CIA and the Security Debate*: 1971-1975, Facts on File Inc., New York, 1975, p. 10.
23. *Monthly Review*, p. 10.
24. The CIA and the Security Debate, p. 10.
25. International Affairs, p. 53.
26. Cheris Depster, Dave Tomkins and Michael Parry, *Fire Power*, *Transworld* Publishers Ltd., London, 1978, p. 119.
27. *Ibid.*, p. 298.
28. Henry Ernest, p. 106-107.
29. *Ibid.*, pp. 18-19.
30. *Ibid.*, p. 24.
31. *Ibid.*, pp. 59, 141.
32. *Ibid.*, pp. 97-100.
33. "Wholesale Crime" *Granma, Havanna*, Feb. 20, 1983, p. 8. See also New Times, 1982, No. 44, p. 24.
34. "The Chamber of Horrors" *Granma*, Havanna, March 13, 1983, p. 8.
35. Henry Ernest, p. 55.
36. Georgi Arbatov, *The War of Ideas in Contemporary International Relations* (Moscow: Progress Publishers, 1973), pp. 208-209, 211.

Digitized by Google

Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

Digitized by Google

መስከረም

HOOVER INSTITUTION NOV 1985

▲ የኢትዮጵያ አብዮትና የሴቶች ጥያቄ

▲ የዘመኑ ዓለምአቀፍ ህግ መሠረታዊ መርሆዎች

▲ ቢሮክራሲና ህዝባዊ አስተዳደር

▲ ሕግ በሽግግር ወቅት

▲ የጋብቻ ጽንሰሐሳብ ግንዛቤ–አጠቃላይ ነጥቦች

ም መጽሔት

ጽ 4 ቁጥር

ኃቢት 1976

17

Digitized by Google

መስከረም

ቅጽ 4 ቁጥር 17
መጋቢት 1976

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ማ ው ጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገፅ 3
- የኢትዮጵያ አብዮትና የሴቶች ጥያቄ 7
  — ጥሩወርቅ ዋቀዮ
- የዘመኑ ዓለምአቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች 29
  — ግርማቸው መኮንን
- ቢሮክራሲና ሕዝባዊ አስተዳደር 50
  — ወልደ ዮሐንስ ወርቅነህ
- ሕግ በሽግግር ወቅት 62
  — ሣህሉ ወ/ጊዮርጊስ
- የጋብቻ ጽንሰሐሳብ ገንዛቤ-አጠቃላይ ነጥቦች 74
  — ኢሳይያስ ደምሴ

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

አድራሻ
የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

Digitized by Google

ያለ አብዮታዊ ንድፈሐሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም!

Digitized by Google

የዝግጅት ገፅ

አዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት

የፖለቲካ ሥርዓት ውስብስብ ግንኙነቶች ያሉት ፥ በኅብረተሰብ ውስጥ የፖለቲካ መዋቅርን ፥ የተለያዩ ሕዝባዊ ድርጅቶች በተቋቋሙባቸው ስርዓተ ማህበሮች ደግም እነዚህን ድርጅቶች ጭምር በአንድ የፖለቲካ ሥልጣን ሰንሰለት ለሚከሉ የሚያንቀሳቀስ ነው ። በመሆኑም የፖለቲካ ሥርዓት የልዩ ልዩ ፖለቲካ አካሎች ፥ ማኅበራዊ ተቋሞችና ድርጅቶች በነዚህም መካከል የሚገኙ ግንኙነቶች፥ እንዲሁም የፖለቲካ ባህልና ግንዛቤ ድምር ውጤት ነው ።

የፖለቲካ ሥርዓት በአንድ ኅብረተሰብ ሶሲዮ ኢኮኖሚ ታህታይ መዋቅር ላይ የሚገነባ ፥ የኅብረተሰብ ላዕላይ መዋቅርን የሚሸፍን ነው ። በኅብረተሰብ የዕድገት ታሪክ ውስጥ የፖለቲካ ሥርዓት ከዝቅተኛ ደረጃ ተነስቶ ወደ ከፍተኛና ውስብስብ ወደሆነ ደረጃ የደረሰ ነው ። በባሪያ አሳዳሪውና በፊውዳሉ ኅብረተሰብ የፖለቲካ ሥርዓት በመንግሥት ውስጥ የተዋቀሩ ሕጋዊ ተቋሞችንና ከመንግሥት ጋር ተወራራሽ የሆነ የጥቅም ግንኙነት የነበራቸውን የእምነት ተቋሞች ያጠቃልል ነበር ። በነዚህ ሁለት ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ ዛሬ በሚታወቀው ቅርፅና ይዘት የፖለቲካ ፓርቲዎች ያልነበሩ ቢሆኑም የመደቦችን ጥቅም የሚወክሉ ልዩ ልዩ ድርጅቶች እንደነበሩ የተረጋገጠ ነው ። በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ግን የፖለቲካ ሥርዓቱ ከመንግሥት በተጨማሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ፥ ማኅበራትንና ሌሎችንም የሙያና « ሕዝባውያን » ድርጅቶችን ያጠቃልለ ሊሆን በቅቷል ። በነዚህ ብዝበዛና ጭቆና በሰፈነባቸው ሥርዓተ ማኅበሮች ሁሉ የኅብረተሰብ የፖለቲካ አደረጃጀት (የፖለቲካ ሥርዓቱ) በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ተጻራሪ መደቦችን ጠባይና ፍላጐት የሚያንጸባርቅ ነው ።

ከላይ ለመጠቆም እንደተሞከረው ፥ ከቅድመ ካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበሮች ይልቅ የፖለቲካ ሥርዓት ከፍተኛ ዕድገትና ውስብስብነት ያሳየው በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ነው ። በካፒታሊስቱ ሥርዓት ውስጥ የመደብ ብዝበዛን የማጥፋት ታሪካዊ ኃላፊነት የወደቀበት የወዝአደሩ መደብ ሕልውና ማግኘት ፥ በዚህ ሥርዓት ውስጥ ወዝአደሩ በቡርዧው መደብ ላይ የሚያካሂደው የመደብ ትግል ስፋትና ጥልቀት እያገኘ መሄድ ፥ በተለይም በዚህ የመደብ ትግል ውስጥ የተለያዩ የመደብ የፖለቲካ ድርጅቶችና ፓርቲዎች መከሰት የፖለቲካ ሥርዓቱ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ የሰፋና የተወሳሰበ እንዲሆን አድርጉታል ።

በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ የወዝአደሩ መደብ በሚያካሂደው ትግልና በትግሉም በሚያስመዘግበው ድል ለማካይነት እንደሁኔታው በፓርቲው ለማካይነትም ሆነ ወይም የሚወክለው ፓርቲ በሌለበት ሁኔታ በሙያ ማኅበሩ ለማካይነት በቡርዧው የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ የተወሰነ ተሳትፎ እንዲኖረው ቢደረግም ፥ የቡርዧው የፖለቲካ ሥርዓት በመሠረቱ የቡርዧውን መደብ ጥቅም ማስከበሪያና የበላይነቱንም ማረጋገጫ ከመሆን አይዘልም ።

በቡርዧው የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ያሉት የተለያዩ አካላት ሁሉም የዓላማና የተግባር አንድነት ያላቸው ባለመሆናቸው ሥርዓቱ በቅራኔ የተወጠረ ነው ። በዚሁ የፖለቲካ ሥርዓት

Digitized by Google

ውስጥ በአንድ በኩል ለወዝአደሩ መደብና ለሌሎችም ሠርቶአደሮች ጊዜያዊም ሆነ ዘለቄታዊ ጥቅም መከበር የቆሙ ማኅበራዊ ኃይሎች ማለትም ፓርቲዎችና የሙያ ማኅበራት ሲኖሩ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የወዝአደሩ መደብ ጥቅም መከበር የነሱ መደብ ጥቅም መጓደል የሚሆንባቸው ፣ በመሆኑም ለቡርዧው መደብ ጥቅም መከበር የቆሙ የቡርዧው መንግሥት ፣ በቀርፅ የተለያዩ የቡርዧ ፓርቲዎችና «ሕዝባዊ» ድርጅቶች ፣ «ቢጫ» ወይም ጠጋኝ የሠራተኛ ማኅበራትና የፖለቲካ ዓላማ ያላቸው የተለያዩ ድርጅቶች ይገኛሉ ። የካፒታሊስት ሥርዓት ብዝበዛ የሰፈነበት ሥርዓት እንደመሆኑ ፣ የኅብረተሰቡ የፖለቲካ አደረጃጀት ተጻራሪ የሆኑ ቅራኔዎችን የሚያንጸባርቅ ነው ። በአጭሩ በካፒታሊስቱ ኅብረተሰብ የፖለቲካ አደረጃጀት ውስጥ ጉልቶ የሚታየው የቡርዧው መደብ አምባገነንነትና ይህንንም አምባገነንነት በተግባር የሚተረጉሙት የቡርዧው መንግሥት ፣ የቡርዧው መደብ ፓርቲዎችና የወዝአደሩን መደብ ጥቅም ለቡርዧው መደብ የሸጠና ጠጋኝ የሆነ የሠራተኛ ማኅበራት እንቅስቃሴ ነው ።

በአንጻሩ አዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት በመባል የሚታወቀው የሶሺያሊስት ኅብረተሰብ የፖለቲካ ሥርዓት ነው ። የሶሻያሊስት የፖለቲካ ሥርዓት ለሶሺያሊዝም በሚደረግ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ተወልዶ እየጐለመሰ ፣ እያደገና እየተጠናከረ የሚሄድ ነው ። የሶሺያሊስት የፖለቲካ ሥርዓት በሠራተኛው መደብ ግንባር ቀደም የማሌ ፓርቲ መሪነት ፣ በቅድመ ሶሺያሊስት የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ዋንኛውን ወሳኙን ቦታ ይዞ የሚገኘውን ፣ አድኃሪ ተልዕኮ ያለውን የበዝባዥ መደቦች መንግሥት በማፈራረስ የፖለቲካ ሥልጣንን በመጨበጥ የሚከሰት ሲሆን ፣ በዚህም የፖለቲካ ሥልጣን መሣሪያነት ሰፊውን ሠርቶአደር ሕዝብ አንቅቶና አደራጅቶ ለጠንካራ ኢኮኖሚ ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ እድገት መገኘት የሚመራና የሚያንቀሳቅስ ነው ።

የሶሻሊስት የፖለቲካ ሥርዓት አካላት የማሌ ፓርቲ ፣ በተለያየ ቅርጹ የሚከሰት የወዝአደሩ የበላይ ገዥነት መንግሥት ፣ ሕዝባዊ ድርጅቶችና የሙያ ማኅበራት ናቸው ። የሶሺያሊስት የፖለቲካ ሥርዓት እምብርትና የሥርዓቱ መሪ አካል የሠራተኛው መደብ ግንባር ቀደም የማርክሲስት ሌኒንስት ፓርቲ ሲሆን ፣ በዚህ ዓይነት ፓርቲ የሚመራው የሶሺያሊስት መንግሥትም በሶሺያሊስት የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ሰፊና ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ።

በሶሺያሊስት የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ የግንባር ቀደሙ ፓርቲ ሚና ለሌሎች የፖለቲካ ሥርዓቱ አካላት ርዕዮተዓለማዊ ፣ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ አመራር መስጠት ሲሆን ፣ የመንግሥት ተግባሮች ደግሞ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ባህላዊ ፣ ትምህርታዊ ሥራዎችን ማከናወን ፣ በዚህ ሂደት ውስጥ አዲሱን ሰው ማነፅ ፣ ሶሺያሊስት ሕጋዊነትንና ሶሺያሊስት ንብረትን መጠበቅና መንከባከብ ፣ ሀገርንና አብዮትን ከጥቃት ለመከላከል ጠንካራ የመከላከያ ኃይል መገንባት ፣ በሰላም አብሮ የመኖር ፖሊሲን ተግባራዊ ማድረግና በዓለምአቀፍ ግንኙነት ዘርፍ ለዚህ ፖሊሲ ተግባራዊነት መታገልን የሚያጠቃልሉ ናቸው ። የሶሺያሊስት መንግሥት ተግባራት ከሶሺያሊስት ግንባታ ሂደት ዕድገትና መወሳሰብ ጋር እያደጉና እየተወሳሰቡ የሚሄዱ ናቸው ።

በሥራ ዘርፍ ፣ በሙያ ፣ በጾታ ፣ በዕድሜ ፣ በመኖሪያ ክልል ወዘተ . . . የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያቀፉ የብዙኃን ድርጅቶች በሶሺያሊስት የፖለቲካ ሥርዓት አካልነታቸው በዚህ ሥርዓት ውስጥ የበኩላቸውን ሚና ይጫወታሉ ። እነዚህ የብዙኃን ድርጅቶች የአባሎቻቸውን የጋራ ፍላጐት ለማሟላት የቆሙ ቢሆንም ፣ በሶሻያሊስት ግንባታ ሂደት ውስጥ የአባሎቻቸው ፍላጐት የሠርቶአደሩ ሕዝብ ድምር ፍላጐት አካል በመሆኑ ዓላማ

Digitized by Google

ቸው የሚደገፍ እንጂ የሚጻረር አይሆንም ። የፖለቲካ ድርጅቶች ባይሆኑም ፣ በሕዝብና በፓርቲ መካከል እንደ ድልድይ ሁነው የሚያገለግሉ ከመሆናቸውም በላይ ሰራው ሠርቶ አደር ሕዝብ በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ለሚያደርገው ተሳትፎ አመቺ መድረክ በመሆን የሚያገለግሉ በመሆናቸው እንቅስቃሴያቸው ከፖለቲካ ውጭ አይደለም ። ከፓርቲና ከመንግሥት ፍላጎት ውጭ የተለየ የፖለቲካ ፍላጎት ስለሌላቸው እንቅስቃሴያቸው ከፓርቲ ፖሊሲና ከመንግሥት መመሪያ ውጭ ሊሆን አይችልም ፤ በመሆኑም ነፃነታቸው አንጻራዊ ነው ።

በአዲሱ / የሶሺያሊስት / የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ያሉ የተለያዩ አካላት የዓለማ አንድነት ቢኖራቸውም በተቋምነታቸው ፣ ባሰባሰቧቸው ኃይሎች ፣ በሶሺያሊስት ግንባታው ውስጥ በሚኖራቸው ሚና ይለያያሉ ።

የሶሺያሊስት የፖለቲካ ሥርዓት እምብርት የማሌ ፓርቲ እንደመሆኑ ፣ የተቀሩት የፖለቲካ ሥርዓቱ አካላት ማለትም መንግሥት ፣ ሕዝባዊ ድርጅቶችና የሙያ ማኅበራት የሚደራጁትና ርዕዮተዓለማዊና ፖለቲካዊ አመራር የሚያገኙት በፓርቲው ነው ። ፓርቲው አጠቃላይ መስመር ይነድፋል ፤ በሁሉም ዘርፍ የዕድገት ፖሊሲ ይቀይሳል ። መንግሥት የፓርቲ የፖለቲካ መሣሪያ በመሆኑ በፓርቲው የተቀየሱ ፖሊሲዎችን በተግባር ያስፈጽማል ። ሕዝባዊ ድርጅቶችና የሙያ ማኅበራት ብዙኀን ሠርቶአደሮችን በማስተባበር የፓርቲ ፖሊሲዎችን ንና በፓርቲው ፖሊሲ ላይ ተመስርተው የተቀየሱ የመንግሥት መመሪያዎችንና ትእዛዞችን ተግባራዊ በማድረግ ለመንግሥት እገዛ ያደርጋሉ ።

ፓርቲው ለመንግሥትና ለሕዝባውያን ድርጅቶች አመራር የሚሰጠው አጠቃላይ ፖሊሲዎችን በመቀየስና በመከታተል ፣ በነዚህ አካሎች ውስጥ መዋቅሩን በመዘርጋትና ብቁ የሆኑ አባላቱን በየደረጃው በመመደብ ፣ የመንግሥትንም ሆነ የሕዝባዊ ድርጅቶችን አሠራር በውስጣቸው ባሉ አባላቱ አማካይነት በቀርብ በመከታተል ፣ በአመራርና በአሠራራቸው ላይ የሚከሰቱ ችግሮች እንዲወገዱ በማድረገና በአጠቃላይ አሠራራቸውን በማቃናት እንጂ በሥራ አፈጻጸም ሂደት ውስጥ እነሱን በቀጥታ በመተካት አይደለም ።

የሶሺያሊስቱን የዕድገት ፈለግ በመምረጥ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን በማካሄድ ላይ የሚገኙ አገሮች የዘለቄታ ዓላማቸው ሶሺያሊዝምን መገንባት እንደመሆኑ ፣ ለሶሺያሊዝም ግንባታ ቅድመ ሁኔታ የሆነውን የማቴሪያልና የቴክኒክ መሠረት ለመጣል ከሚያካሂዱት ትግል በተጨማሪ ፣ የሶሻሊዝምን ላዕላይ መዋቅር ማለትም አዲሱን የፖለቲካ ሥርዓት ለማደራጀት ውስብስብና መራራ የሆነ ትግል ማካሄድ ይኖርባቸዋል ።

በእነዚህ አገሮች ያሉና የሚቋቋሙ በይዘት አብዮታዊ ዲሞክራቲክ የሆኑ ግንባር ቀደም ፓርቲዎች በሂደት ወደተሟላ ማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲነት የሚያድጉ ናቸው ። በተጓዳኝ በእነዚሁ አገሮች የሚቋቋሙ የመላ ሠርቶአደሮችን ዲሞክራሲያዊ የበላይ ገዥነት የሚያንፀባርቁ አብዮታዊ ዲሞክራቲክ መንግሥታትም የወዝአደሩን የበላይ ገዥነት ወደሚያረጋግጥ ሶሻሊስት መንግሥትነት የሚያድጉ ናቸው ። በመሆኑም በነዚህ አገሮች ውስጥ የሚገነባው የፖለቲካ ሥርዓት በሂደት ወደተሟላና የተዋሃደ ሶሻሊስት የፖለቲካ ሥርዓትነት የሚያድግ ፣ የሽግግር ጠባይ ያለው ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት ነው ።

Digitized by Google

በሀገራችንም ውስጥ የአብዮቱ ግንባር ቀደም መሪ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ መመሥረት፥ አዲስ በመገንባት ላይ ለሚገኘው ሕዝባዊ የፖለቲካ ሥርዓት አማራጭ የማይገኝለትን የፓርቲ አመራር የሚያስገኝ ከመሆኑም በላይ፥ በፓርቲው መሪነት የሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መንግሥት መቋቋም፥ እየተጠናከሩ በመሄድ ላይ ከሚገኙት ሕዝባዊ ማኅበራትና ድርጅቶች ጋር ተዳምሮ በመገንባት ላይ የሚገኘውን አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት የተሟላ ያደረገዋል።

እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ ውስጥ ከአብዮቱ ፍንዳታ ጀምሮ ለሀቀኛ ግንባር ቀደም ፓርቲ መቋቋምና ለሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መመሥረት፥ በአጠቃላይ ፍትሕና እኩልነት ለሰፈነበት አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት መገንባት እጅግ መራራና ውስብስብ የሆነ ትግል የተካሄደ ከመሆኑም በላይ፥ ትግሉ ከፍተኛ መስዋዕትነትን ጠይቋል።

የውስጥም ሆኑ የውጭ አድኀርት ኃይሎች በዚች አገር ውስጥ አዲስ ሕዝባዊ የፖለቲካ ሥርዓት መመሥረት ማለት ግብዓተ መሬታቸው መከናወኑ መሆኑን በሚገባ ይገነዘባሉ። ስለዚህም ማናቸውንም ገንቢ ጥረታችንን ለማሰናከል እስከመጨረሻው እንደማይዘናጉ መታወቅ አለበት። አሁንም ሳያቋርጡ የሚያውጠነጥኑት ሤራና የሚፈፅሙት ደባ ለዚህ ጥረታቸው ቋሚ ምስክር ነው። ስለዚህ የአብዮቱ ወገኖች የሆን ሁሉ በአንድ በኩል የግንባታ ትግላችንን ከመቼውም ይልቅ እያጣደፍን በሌላ በኩል ደግሞ የፀረ አብዮትን ሤራ ነቅቶ መጠበቅና ማናቸውንም አፍራሽ ድርጊታቸውን መቋቋምና ማክሸፍ የሚጠበቅብን ብሔራዊ ኃላፊነትና አብዮታዊ ግዴታ ነው።

Digitized by Google

የኢትዮጵያ አብዮትና የሴቶች ጥያቄ

ሶሻሊስት ኅብረተሰብ የመገንባት ተግባራችን ተጀመረ ለማለት የምንችለው የሴቶች ሙሉ እኩልነት ተጎናጽፈው አዲሱን ሥራችንን ከተቃቅን፣ ጥጋ ቢስ ከሆነና ምርታማ ካልሆነ ሥራ አላቀን ነፃ ከሆኑ ሴቶች ጋር በአንድነት ስናካሂድ ብቻ ነው ። ይህ ብቻውን በጣም ብዙ ዓመት ይፈጅብናል ።[1]

ሌኒን

ጥሩወርቅ ጥቀቁ

ኅብረተሰብ በመደብ ከተከፋፈለበት ጊዜ አንሥቶ እስከዛሬ በብዝበዛ ላይ የተመሠረተ የምርት ግንኙነት በሰፈነባቸው ኅብረተሰቦች ሁሉ የሰው ልጆች መብት ሲረገጥ ኖሯል ። ጥቂት የገዥ መደቦች በብዙኃኑ ተበዝባዥ መደብ ሕይወት ላይ ሲወስኑ ቆይተዋል። የገዥ መደብ አባላት ጥቅማቸውን የሚያራምዱ አሠራሮችንና ሰልቶችን በመቀየስ የመደባቸውን ፍላጎት የሚያንጸባርቅ ሕግ ደንግገው ፣ ደንብ አውጥተው ፣ ኃይላቸውን አጠናክረው በበላይነትና በድሎት ኖረዋል። በአንፃሩ የተበዝባዥ መደብ አባላት የሆኑ ብዙኃን መብታቸው ተገፎ፣ ሰብአዊነታቸው ተረግጦ ብዙ የመከራና የጭንቀት ኑሮ አሳልፈዋል ። ጭቁኑ ሕዝብ ችግሩን ለማስወገድ በጠላቶቹ ላይ እጁን እያነሣ ፣ እያመጸና በዚህም ዓመጹ ለብዝበዛውና ለጭቆናው መሠረት የሆነውን የምርት ግንኙነት በማስወገድ አዲስና የላቀ ኅብረተሰብ መሥርቷል ። ይኸው ትግል ዛሬም የበለጠ ተፋፍሞ በመካሔድ ላይ ነው ።

በኢትዮጵያም ለረጅም ጊዜ በተካሔዱት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሁሉ የኅብረተሰቡ አካል የሆኑት ሴቶች ፣ ባመቻቸውና በተገኘው መድረክ በመጠቀም የበኩላቸውን የትግል ድርሻ አበርክተዋል ። ለዚህ ነው ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በአኢሴማ ፩ኛ ጉባኤ ላይ ሲናገሩ ፣ «ሴቶች በአድኃሪው ሥርዓት መብታቸው ተረግጦ በሥቃይ ይኑሩ እንጂ ፣ አስፈላጊ በነበረበት ጊዜ ሁሉ ለእናት ሀገራቸው አንድነት መሥዋዕትነት ከመክፈል ወደኋላ ያሉበት ጊዜ የለም ። ሰፊው ሕዝብ ባካሔዳቸው ቁርጠኛ ጸረ—ቅኝ አገዛዝና ጸረ—ወራሪ ኃይላት ትግል ውስጥ ሴቶች የከፈሉት መሥዋዕትነት በረዥሙ ታሪካችን ውስጥ ጉልህ ምዕራፍ ይዞ የሚገኝ ነው »[2] ያሉት ።

የመደቦች መከሰት ያስከተለው የፍትሕ መዛባት ለሴቶችም መብት መገፈፍ ዋናውና

Digitized by Google

መሠረታዊ ምክንያት ነበር ። የተበዝባዥ መደብ አባላት የሆኑት ሴቶች የመደብ አጋራቸው ከሆነው ወንድ ልዩ የሚያደርጋቸው አንዱ ነገር ፣ ሊባስ ብዝበዛና በደል የተጋለጡ መሆናቸው ነው ። ሴቶች በወንዶች ላይ የሚጫነውን መደባዊ የጭቆና ቀምበር እኩል ተሸካሚዎች ከመሆናቸው በተጨማሪ በጾታቸው ምክንያት ከገዥው መደብ ብቻ ሳይሆን በራሳቸው መደብ አባላት ጭምር ዳግመኛ በደል ይፈጸምባቸዋል ። የመደብ ተፅዕኖው ነጸብራቅ የሆነው የጾታ በደል አልፎ ተርፎ የገዥ መደብ አባላት የሆኑትን ሴቶችም አልማራቸውም ።እነሱ የሚበሉት ፣ የሚለብሱትና የሚኖሩበት ሁኔታ የተሟላ ሆኖ ሳለ በሴትነታቸው ምክንያት በገዥው መደብ አባላት ከመገልገያ ዕቃና ልጅ ከሚያመርት ማሽን በተለየ ሁኔታ ስለማይታዩ ፣ መሠረታዊ ሰብአዊ መብታቸው የተረገጠ ነው ።

ይህ በሴቶች ጾታ ላይ የሚፈጸመው በደል በሁለቱም መደቦች ውስጥ ለሚገኙት ሴቶች የጋራ ችግር በመሆኑ በጋራ ሊያስልፋቸውና ሊያታግላቸው የሚችል ጉዳይ ነው ። ሆኖም የመደብ ጥቅም ማስጠበቅ ቅድሚያ የሚሰጠው በመሆኑ ያላቸው የጋራ ችግር ለተወሰነ ጊዜ በጋራ ሊያመሳስላቸውና ሊያስልፋቸው ቢችልም የመደብ ፍልሚያው ሲከሰት ሁሉም ለቆሙለት መደብ እንደሚሰለፉ ግልጽ ነው ።

የሴቶች የመብት ጥያቄ የረጅም ጊዜ ዕድሜ ያለው ሲሆን ፣ ብዙ አዋቂዎችንና ተመራማሪዎችን ያከራከረና ያወያየ ፣ ችግሩ እጅግ የተወሳሰበና በቀላሉ መፍትሔ ሊገኝለት ያልቻለ ነው ። ጥያቄውን የበለጠ ውስብስብ ሊያደርገው የሚችለው ሴቶች በኅብረተሰቡ ውስጥ እጅግ ክቡር የሆኑ ተፈላጊ ተግባሮች እያከናወኑ በአንፃሩ በጾታቸው ላይ የሚፈጸመው ከባድ በደል ካለባቸው ኃላፊነትና ግዴታ ጋር ሲታይ ምንጊዜም አብሮ የማይሔድና የማይጣጣም መሆኑ ነው ።

ለምሳሌ ሴ ቶ ች ክቡር የሆነውን የመውለድ ተግባር የሚያከናውኑ ናቸው ። ይህ ተግባር በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚፈለግና የኅብረተሰቡ ህልውና እንዲቀጥል ለማድረግ የግዴታ መከናወን ያለበት ተግባር ነው።ከዚህም በቀር እስከዛሬ በዓለም ላይ ከፍተኛ ተግባር የሚያከናውኑ ፣ አከናውነውም ያለፉ አንጋፋ ፈላስፋዎች ፣ ታላላቅ ጀግኖች ፣ ሳይንቲስቶች ፣ ወዘተ --- የመጀመሪያ ትምህርታቸውን የቀሰሙት ፣ የመብላትን ፣ የመራመድን ፣ የመናገርን ፣ ልምምድ ያገኙት ሰብአዊ ፍቅርና እንክብካቤን የተማሩት ከእናቶቻቸው ነው። በሥነልቡና አዋቂዎች እንደሚነገረው በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት ሕፃናት የሚያገኙት ትምህርት በሕይወታቸው ሙሉ ተፅዕኖ ይኖረዋል ይላሉ ። እነዚህ የመጀመሪያ ጥቂት ዓመታት እናት ልጇን በቅርብ ሆና የምትከታተልበት ፣ ጡቷን አጥብታ ፣ ጤንነታቸውን ተንከባክባ፣ አብልታ፣ አቅፋ ፣ ራሷን በድላ ፣ በአስተሳሰብና በጠባይ የወደፊት ዕድላቸውን የምትቀይስበት ወቅት ነው። እናት ለልጅዋ የምትሰጠው ትምህርትም ሆነ በሕፃኑ ላይ የምታሳድረው ስሜት በሕፃኑ የወደፊት ሕይወት ላይ ተፅዕኖ ማድረጉ የማይቀር ነው ። ይህን ከፍተኛ የእናትነት ተግባር የምትወጣ ሴት በተቃራኒው የእናትነት ተግባሯ ይንኳሰሳል ፤ የዜግነት መብቷ ይገፈፋል ፤ ሰብአዊ ክብሯ ይረገጣል ።

ሴት የወደፊቱን ኅብረተሰብ ገንቢ ትውልድ ከማፍራት በተጨማሪ ቤተሰቡን ባጠቃላይ የመንከባከብ ኃላፊነት አለባት ። ብዝበዛ በሠፈነበት ሥርዓት ለኅብረተሰቡ ብሎም ለሰው ልጅ አጠቃላይ ህልውና መሠረት የሆነውን ቤተሰብ መግባ ፣ በቤት ውስጥ ያለውን ከባድ የሥራ ሸክም ያለ ዕረፍት አጠናቃ ፣ የሚስትነት ተግባሯን የምታከናውነው ሴት ለዚህ ክቡድ ኃላፊነቷ ስታገኝ የኖረችው ወሮ

Digitized by Google

ታ ወይም ምስቅና ሳይሆን መናቅንና የዝቅተ
ኛነትን ቦታ ነው ።

ሴት በቤት ውስጥ የምትሠራው ሥራ
በጣም አድካሚ ይሁን እንጂ ምርታማ አይ
ደለም ። በቤት ውስጥ ያለአግባብ ለብዙ ጊዜ
የሚጠፋው የሴት ጉልበት ፣ ግማሹ ያህል
እንኳን ውጤት ባለው የኅብረተሰቡ የሥራ
መስክ ላይ ቢውል ለሀገር ኢኮኖሚና ለ
ራሷም የባህልና የአእምሮ እድገት ምን ያ
ህል ውጤት ሊያስገኝ እንደሚችል መገመት
ይቻላል ።

ለዘመናት በሴቶች ላይ ሲፈራረቁ የቆዩት
እነዚህ አስከፊ ሁኔታዎች በየሥልተ ምርቱ
በቅርጽ ለውጥ እያሳዩ የመጡ ቢሆንም በይ
ዘት ግን ሳይቀየሩ በመኖራቸው በኅብረተሰቡ
ውስጥ ሴቶች በሁለተኛ ዜጋነት እንዲታዩ ፣
ያላቸው ተሳትፎና ተሰሚነት እንዲቀዘቅዝ ፣
በአካልም ሆነ በአእምሮ እንዳይጐለምሱ ታግ
ደው ኖረዋል ። ይህ ችግር መኖሩን የሚክድ
ወገን ባይኖርም ችግሩን መረዳት ብቻ በቂ
ሳይሆን ዋናው ቁምነገር ለችግሩ መፍትሔ
መሻትና ተግባራዊ ውጤት ለማሳየት መቻል
ነው ።

«የሴቶች አርነት» በሚል መርህ ሥር ተሰ
ልፈው በሴቶች ላይ የተጫነውን ተፅዕኖ ለመ
ፍታት የተሳተፉ አያሌ ናቸው ። ሆኖም ይኽ
ነፃነት እንዴት ሊገኝ ይችላል ? ለሚለው
ጥያቄ የሚሰጡት መልስ የተለያየ ነው።በሶ
ሻሊስትና በካፒታሊስቱ ዓለም የጥያቄው
ምላሽ ወይም የችግሩ መፍትሔ የተለያየ ግብ
ያለው ነው ። በሶሻሊስትና በካፒታሊስት ርዕ
ዮተ ዓለሞችና የፖለቲካ አመለካከቶች መሠ
ረታዊ ልዩነት እንዳለ ሁሉ ፣ የሴቶችንም ነፃ
ነት በሚመለከትም ልዩነት አለ ። የካፒታሊ
ስቱን ርዕዮተ ዓለም የሚከተሉ የሴቶች «የአ
ርነት» ንቅናቄ እምነት ለሴቶች ጭቆና መሠ
ረቱ የካፒታሊስቱ ወይንም ሌላ ብዝበዛ የሰ
ፈነበት ሥርዓት ሳይሆን ወንዶች ናቸው የሚ
ል ነው ። በነሱ አስተያየት የሴቶች ጥያቄ በዚ
ያው በካፒታሊስት ሥርዓት ማኅበር ውስጥ
ወንዶችን ለይቶ በመታገል ሊፈታ ይችላል።
የዚህ አመለካከት ተከታዮች አስተሳሰብ
መሠረት ወንዶችን መታገል ፣ ወንዶች
የሚያደርጉትን ሁሉ ለማድረግ መሞከር ራሱ
እንደግብ የሚቆጠር ጉዳይ ነው ። የዚህ ዓይ
ነቱ የሴቶች «ነፃነት» ንቅናቄ እንስታዊነት
(Femini m) ተብሎ የሚጠራ ሲሆን
ተከታዮቹም እንስታውያን ይባላሉ ።

እንስታዊነት በመባል የሚታወቀው የቡ
ርዧ ሴቶች እንቅስቃሴ በካፒታሊስት አገሮች
ውስጥ ከ17ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛው
አጋማሽ ጀምሮ ሲካሔድ የቆየ እንቅስቃሴ
ነው ። ዛሬም ቅርጹንና ስሙን በመቀያየር በ
ፍተኛ ደረጃ በመካሔድ ላይ ያለና አልፎ አል
ፎ አንዳንድ ለውጦችን ያስገኘ ቢሆንም፣በነ
ዚህ የረጅም ጊዜ የትግል ዓመታት ውስጥ
ለሴቶች ያስገኘው መሠረታዊ ለውጥ የለም።

የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መሥራቾች ከመጀ
መሪያ እንሥቶ የሴቶችን ጥያቄ ያስተናገዱት
ወይም የተመለከቱት የሶሻሊዝም ንድፈ ሐ
ሳብ አንድ አካል አድርገው ነው ። የሳይንሳዊ
ሶሻሊዝም የመጀመሪያ ፕሮግራም በሆነው
በኮሚኒስት ማኒፌስቶ ላይ «የዓለም ሠራተ
ኞች ተባበሩ» በማለት የተደረገው ጥሪ ከወ
ንድ የመደብ ወንድሞቻቸው በባሰ ሁ ኔ ታ
ሲበዘበዙና ሲሠቃዩ ለኖሩት የሠራተኛ መደ
ብ ሴቶች ጭምር የተደረገ ጥሪ ነበር ።

ሶሻሊስቶች የሴቶችን የመብት ጥያቄ ከኅ
ብረተሰቡ ማኅበራዊ ጥያቄዎች መካከል እን
ደአንዱ በመቁጠር ፣ ካጠቃላይ የኅብረተሰቡ
ችግር ጋር አብሮ የሚፈታ እንጂ ከዚያ ውጭ
መታየት እንደሌለበት ደጋግመው አስገንዝ
በዋል ። ሌድዋን እንዳሉት «የሴቶች ነፃነት
ከብሔራዊ ነፃነትና ከሠራተኛው መደብ ነፃ
ነት ጋር ተያይዞ መታየት አለበት ። አገሪቱና
ሠራተኛው መደብ ነፃ ካልወጡ ሴቶች ነፃ
ሊሆኑ አይችሉም ። በሌላ በኩል ሴቶች ነፃ
ካልሆኑና በሀገራቸው ግንባታ ሊሳተፉ ካል

Digitized by Google

ቻሉ አገሪቱም ሆነ ሠራተኛው መደብ ሙሉ ነፃነት ሊጎናጸፉ አይችሉም ። በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ሴቶች ገና በጥገኝነት ያሉና ነፃነታቸውን ያላገኙ ከሆነ ኅብረተሰቡ ሠልጥኗል ወይም ተራምዷል ለማለት አይቻልም። ሴቶች በሀገራቸው ውስጥ የሚኖራቸው የመብት ደረጃ የኅብረተሰቡ እድገትና ሥልጣኔ መለኪያ ነው። ምክንያቱም ባለፈው ሥርዓት ከፍተኛየፍርድ መዛባት የደረሰባቸው እነርሱ በመሆናቸው ነው ።»[3] በአጠቃላይ ነፃ ባልወጣ ኅብረተሰብ ውስጥ ሴቶች የተሟላ ነፃነት አላቸው ለማለት አይቻልም ።

ማርክሳዊ ሌኒናዊ ርዕዮተዓለም ማለትም ሳይንሳዊ ርዕዮተ ዓለም መመሪያቸው የሆነ የሠራተኛው መደብ ሴቶች ለጾታቸው ነፃነት የሚያደርጉት ትግል ፣ በሠራተኛው መደብ ላይ የወደቀውን ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ለማስወገድ የሚያደርገው ትግል አካል አድርገው የሚመለከቱት ስለሆን ፣ የጾታ ትግላቸውን የሠራተኛውን ትግል ወደፊት የማራመጃ መሣሪያ አድርገው ይቆጥሩታል ።

በከባድና መራራ ትግል ሶሻሊዝምን ገንብተው ዛሬ በከፍተኛ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙት ሶሻሊስት አገሮች ውስጥ ለሴቶች ጥያቄ አያሌ ጠንካራ መሠረቶች ተጥለዋል ። ከኅብረተሰቡ ጥያቄዎች ጋር ጎን ለጎን የሴቶች ጥያቄ መፍትሔ እያገኘ ዛሬ ከየትኛውም የዓለም አካባቢ በሶሻሊስት ሀገሮች ውስጥ የሴቶች የእኩልነት መብት በተግባር ተተርጉሞ ፣ ሴቶችም በተጎናፀፉት ድል በመጠቀም ያላቸውን ችሎታና ዕውቀት በተሟላ ሁኔታ ለኅብረተሰቡ ሲያበረክቱ ማየት በአርአያነቱ የጭቁን ሴቶች ትግል በተስፋ የተሞላ እንዲሆን የሚያደርግ ነው ።

የሴቶች ጥያቄ መልስ አገኘ ለማለት የሚቻለው ሴቶች በተሠማሩበት የሥራ መስክ ኃላፊነታቸውን በብቃት ሊወጡ ሲችሉ ፣ የእናትነት ተግባራቸውን ያለ ምንም ችግር ለማከናወን ሲበቁ ፣ የኅብረተሰቡ እኩል ዜጋ ለመሆንና ባጠቃላይ የማኅበራዊና የኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴያቸውን ከናትነትና ከቤተሰብ ኃላፊነት ተግባራቸው ጋር አጣምረው ለማከናወን አመቺ ሁኔታ ሊፈጠርላቸው ሲችል ነው ። ለዚህ ተግባራዊ ምላሽ የሚሰጠው ፣ የሰው በሰው መበዝበዝ የሌለበት ፣ የሕዝቡ መሠረታዊ ፍላጎቶች የተሟሉበት ፣ ፍትሕ የሠፈነበት ኅብረተሰብ ሲመሠረት ብቻ ነው ። ለዚህም ነው መፈክራችን «መፍትሔው ሶሻሊዝም ነው» የሚል መሆን ያለበት ።

የኢትዮጵያ ሴቶች በቅድመ አብዮት

በሀገራችን የነበረው የፊውዳሉ ስልተምርት እጅግ ኋላቀር በሆኑ የምርት መገልገያዎች የሚጠቀም፣በእርሻ ኢኮኖሚ ላይ የተመሠረተና የኅብረተሰቡ የማኅበራዊና የባህል ደረጃም እጅግ ዝቅ ያለ ነበር ። ፊውዳላዊ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ከ90 በመቶ በላይ ሕዝብ በማይምነት የሚማቅቅበት ፣ የኢኮኖሚው መሠረት የሆነው ጭቁን የገበሬ መደብ ከመጠን በላይ ጉልበቱ የሚበዘበዝበት ፣ እሱ ብቻ ሳይሆን መላ ቤተሰቡ በፊውዳል የመሬት ከበርቴዎች ቤት በአሽከርነትና በግርድና የሚመዘበርበት ኅብረተሰብ ነበር ።

የባህል የእድገት ደረጃው ዝቅተኛ በመሆኑ የፊውዳል ኅብረተሰብ አስተሳሰብና አመለካከት በዚሁ መጠን በጣም ዝቅተኛና ኋላቀር ነው ። እንደሚታወቀው የፊውዳል ኅብረተሰብ የሰውን በሰው መበዝበዝ ጽኑ እምነቱ ያደረገ ፣ የሚሠራን ሰው የሚያንኳስስ ፣ የማይሠራ ወይም ሳይሠራ የሚበላውን « የጨዋ ልጅ» የሚል ስያሜ የሚሰጥ ፣ ኅብረተሰብን በዘር ፣ በጎሣ ፣ በመንደር ፣ በጾታ ፣ በሃይማኖት በመለ ያየት ለአገዛዝ እንዲያመቸው ከፋፍሎ ለማስተዳደር የሚሞክር ፣ ማይምነት ፣ እርዛት ፣ ኢሰብአዊነት የሠፈነበት ኅብረ ተሰብ ነው ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ፣ ሁኔታ በተለይ በሴቶች ላይ ያለው አመለካከት በጣም አድኃሪና ሰብአዊነት የጎደለው ነው ።

በፊውዳል ኢትዮጵያ ሴቶች ከሌላው ጭ
ቁን ሕዝብ ሁሉ እጅግ በባሰ ሁኔታ ተመቃይ
ተዋል ። የፊውዳል ኢትዮጵያ ሴቶች በባህል
ተፅዕኖ የማተቁ ፣ ከማኅበራዊ ኑሮ እንቅስቃሴ
የተገለሉ ፣ በኢኮኖሚ የወንድ ጥገኛ ሆነው
የኖሩ ናቸው ። ሴቶች ገና በለጋ ዕድሜያቸው
በቤተሰብ ውስጥ ከሚፈጸምባቸው ያልተዳ
ደገ በደል በተጨማሪ ፣ ዓቅመ ሔዋን ሳይ
ደርሱ እየተዳሩና ይህ ያለወቅቱ የሚፈጸም
ጋብቻም በወደፊት ኑሮአቸውና በጤንነታ
ቸው ላይ ከፍተኛ ቀውስ ሊያስከትል ኖሯል።
በፊውዳላዊ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ በግና
ልብኝነትና በወንድ ትምክህተኝነት ተከት
ኩቶ ያደገው ወንድ በሚስት ላይ የሚፈጸ
መው የተለያየ ኢሰብአዊ ድርጊት ወንጀል
መሆኑ ቀርቶ እንደመልካም ሥራ ፣ እንደ
ወንድነት መገለጫና እንደጉብዝና እየተቆ
ጠረለት ጉሽ ሊባል ኖሯል ። ለምሳሌ ሚስ
ት መደብደብ በጣም አስጸያፊና ሰብአዊነ
ትን የሚጻረር የኋላቀርነት መገለጫ ዋና
ምልክት መሆኑ ቀርቶ ፣ ድርጊቱን በቀላሉ
በመቁጠር እንደፍቅር መገለጫ እንደ ወን
ድነት ማረጋገጫ መታየቱ የፊውዳል አመ
ለካከት ዓይነተኛ መገለጫ ነው ።

በቤተሰብ ውስጥ የሴቶች ኃላፊነትና የሚ
ደርስባቸው ጭቆናም በጣም ከባድ ነው ።
የቤት ውስጥ ሥራ የሚከናወነው ኋላቀር
በሆነ መሣሪያ ፣ ከጋርዮሽ ስልተምርት
ጊዜ ባልተሻለ ያሠራር ዘዴ ነው ። በቤት
ውስጥ ለፍጆታ የሚቀርበው ሁሉ ብዙ
የሴቶችን ጊዜ ከመፍጀቱም ሌላ እጅግ
አድካሚና ጉልበታቸውን ጨራሽ ፣ ጤን
ነታቸውን አቃዋሽ ነው ። ከዚህ ኃላፊ
ነት በተደራቢ ልጅን ዘጠኝ ወር አርግዞ ወ
ልዶና ተንከባክቦ ማሳደግ ፣ ከዚህም ባለፈ
ባልን በግብርና ሥራ ላይ መርዳት ፣ ቤተ
ሰቡን ባጠቃላይ መግቦ ፣ ተንከባክቦ አብቃ
ቅቶ ማስተዳደር የዘወትር የሴቶች ተግባር
ነው ። በዚህ አጋጣሚ ሴቶች ከዚህ ሁኔታ
የሚያገኙት የማስተዳደር ልምድም በቀላሉ

የሚገመት አይደለም ። በቅርብ ካሉ ጉረቤ
ቶቹዋ ጋር ካልሆነ በቀር ሴት ከኅብረተሰቡ
ጋር ለመቀላቀልና ለመገናኘት ዕድል ስለ
ሌላት አስተሳሰቧ ውሱን ፣ አመለካከቷ ጠ
ባብ ፣ በራሷ የማትተማመን ፣ የጥገኝነት ስ
ሜት የሚያጠቃት እንድትሆን ሁኔታው
ያስገድዳታል ። መላ ዕድሜዋን ሰብአዊ መ
ብቷ ሳይጠበቅ ፣ ከኤኮኖሚ ተጽዕኖ ሳትላ
ቀቅ ፣ ወጣቷ በለጋ ዕድሜዋ ሰውነቷ በሥ
ራ ብዛት ፣ በጤንነት ዕጦት ደቅቆና ገርጅፎ
አእምሮዋ ላሸቆ ገና ለአማካይ የዕድሜ ወሰ
ን እንኳ ሳትደርስ የምትቀጨዋ የፊውዳል
ኢትዮጵያ ሴት እንደደካማ የምትቆጠር ሳ
ትሆን ጠንካራ ፣ የምትናቅ ሳይሆን የምት
ከበር መሆን ነበረባት ።

በፊውዳላዊ ኢትዮጵያ የሴቶች የመማር
ዕድልም እንደዚሁ በጣም የመነመነ ነበር ።
ለመማር ዕድል ያገኙት እጅግ ጥቂት ወጣት
ሴቶች ትምህርታቸውን አቋርጠው ሳይወዱ
በግድ ይዳራሉ ፤ ወይም ያቋርጣሉ ። በዚህና
በሌሎችም ምክንያቶች ከአንደኛ ደረጃ
ወደ ሁለተኛ ደረጃ የሴቶች ቁጥር ከግ
ማሽ በታች እያሽቆለቆለ ይሔዳል ፤ በጣት
የሚቆጠሩ ወደ ከፍተኛ ተቋሞች ይገባሉ ።
ሴቶች የሚሰማሩበት የትምህርትም ሆነ የ
ሥራ መስክ አብዛኛው የሚያተኩረው በአ
ገልግሎት ሰጭ ፣ በማኅበራዊ ጉዳይና በመሳ
ሰሉት አካባቢ ሲሆን ፣ በዚሁ መጠን የሚ
ሰማሩባቸው የሥራ መስኮችም በጣም ጠባ
ብና ውሱን ነበሩ ።

በዚህ ምክንያት በቅድመ አብዮት ኢት
ዮጵያ አብዛኛው የሴት ኃይል ያልሰለጠነና
በሥራ ላይ ለማሰማራት ዕድል ያላገኘ በመ
ሆኑ ፣ በተለይ በከተማዎች አካባቢ ብዙ ሴ
ቶች ሕይወታቸውን የሚገፉት በቤት ሠራ
ተኝነት ፣ በሞግዚትነት ፣ ከዚያ የተረፉትም
በሴትኛ አዳሪነት መስክ ተሰማርተው ነበር ።
ጥቂት በቢሮና በፋብሪካ ውስጥ ለመቀጠር
የቻሉት ሴቶች ለሥራ አመች ሁኔታ አልነ
በራቸውም ። የሠራተኛውን መብት የሚ
ደግፍ ደንብ ባለመኖሩ ለእኩል ሥራ እኩል

Digitized by Google

ክፍያ የሚለው የሰው ልጅ መሠረታዊ
መብት ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም ።
በተለይ በፋብሪካ ውስጥ የሚሠሩ ሴቶች
ሁኔታ ከማንኛውም የበለጠ አስቃቂ ነበር።
ለኩል ሥራ የተለያየ ክፍያ ብቻ ሳይሆን
በቂ የወሊድ ፈቃድ፣የሥራ ዋስትና ጥምር
አለመኖር በቤት ውስጥ ያለባቸውን የናትነ
ት ኃላፊነትና የፋብሪካውን ሥራ አቀናጅተ
ው ሊሠሩ የሚችሉበት ሁኔታ አልነበረም ።

በፊውዳሉ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ከ90
በመቶ በላይ በግብርና አካባቢ የተሰማሩት
ሴቶች በአብዛኛው የጭሰኛው ወይም የጭ
ቁን ገበሬው ሚስት ወይም ሴት ልጆች ሲ
ሆኑ ፣ በእርሻው ላይ የሚያበረክቱት የራሳ
ቸው የሆነ ከፍተኛ ድርሻ ነበር ። ሆኖም ይህ
ተሳትፎ በኅብረተሰቡ ዘንድ ታዋቂነት ስለ
ሌለው ፣ በእርሻውም ላይ አስተዋጽኦ እን
ዳደረጉ አያስቆጥራቸውም ። የነርሱ ልዩ
ተግባር ሆኖ የሚቆጠረው በቤት ውስጥ የ
ሚሰጡት ግልጋሎት ብቻ ነው ። ከዚህም
በተደራቢ ጭቁን ሴቶች በመሬት ከበርቴ
ው ቤት የሚሰጡት የነፃ ጉልበት አገልግ
ሎት በጣም ብዙ ነው ። እህል መፍጨት
ጠላ መጥመቅ ፣ ውሀ መቅዳት ፣ እንጨት
መስበር ፣ ጥቂቶቹ ሲሆኑ ፣ ከዚህ በተረፈ
የመሬት ከበርቴውን ሥጋዊ ፍላጐት ለማ
ርካት ግዳጅ የሚደረግባቸውም ብዙዎች ና
ቸው ።

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው
በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ሴቶች በሕፃ
ንነት ዕድሜያቸው በቤተሰባቸው ውስጥ
ጥምር ተጽዕኖና አድልዎ ይፈጸምባቸዋል።
ይህም የሚሆነው የወደፊት ኑሮአቸውን
ለማዘጋጀት ሲባል ነው ። ታታሪ ባለሙያ ፣
ባሏን ቀና ብላ የማታይ ፣ እንግዷን የደፋች
ከቤት የማትወጣ ሴት ማዘጋጀት ቤተሰቡ
ከኅብረተሰቡ የሚደርስበትን ወቀሳ ለመቋ
ቋም የሚያከናውነው ተግባር ነበር ።ከቤት
ውስጥ የሥቃይ ኑሮ ወደ ባሰ ሁኔታ መሸ
ጋገሯን በደንብ የምትረዳው ለጋ ወጣት የ
ሙርጓ ዕለት በመደሰት ፈንታ ምርር ብላ ታ
ለቅሳለች ።«ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ»ለሷ
ተገቢ አባባል አይደለም ። ሳታውቀው የገ
ባችበት ቤትና ያገባችው ባል እንደአጋጣሚ
ከተስማማት ዕድለኛ ናት ፤ ካልሆነም የወ
ደፊቱ ኑሮዋ ለባሰ ችግር የተጋለጠ ነው ።

ከፊውዳሉ ሥርዓት ቅሪቶች መካከል ያ
ተረፍነውና ዛሬም ገና ያልተወጣነው የሴ
ትኛ አዳሪነት አስከፊ ገጽታ ባብዛኛው የሚ
መነጨው ካልተስተካከለ የትዳርና የኑሮ
ሁኔታ ነው ።ኑሮ ሳይመቻቸው ፣ ችግር ሲበ
ዛባቸው ፣ ትዳር ሲፈርስ ፣ አካባቢን ጥሎ
በመሸሽ ራቅ ወዳለ ቦታ ሔዶ ሊታወቁ በ
ማይችሉበት ከተማ ውስጥ ገብቶ መኖር የ
ብዙ ሴቶች የችግር መወጫ ዘዴ ሆኖ ቆይ
ቷል ። ከተማ ውስጥ ከተገባ በኋላ የሥራ
አማራጭ ውሱን በመሆኑ በስፋት የሚገኘ
ውን አማራጭ በመውሰድ እንደገና ለባሰ ች
ግር ፣ ለባሰ ኑሮ ቀውስና አስከፊ ሁኔታ ይዳ
ረጋሉ ። በሀገራችን ሴትኛ አዳሪነት ባብዛ
ኛው ከዚህ ዓይነቱ የኑሮ ቀውስ የሚመነጭ
ነው ። ሴቶቻችን ባብዛኛው ሴትኛ አዳሪነ
ትን የሚጠሉትና የሚያፍሩበት ስለሆነ ለተ
ሻለ ኑሮና ሥራ በቀላሉ የሚለውጡት መስ
ክ ነው ።

በሌላ በኩል የተለያዩ ብሔረሰቦች ባለ
ጸጋ በሆነችው ሀገራችን ውስጥ የብሔረሰቡ
ባህልና ወግ ሴቶችን በሚመለከት ወደፊት
ታሪክ ሊያሰባስባቸውና ሊያጠናቅራቸው
የሚገባ ብዙ አሳዛኝና አስገራሚ ሁኔታዎች
አሉ ። በሁሉም ብሔረሰቦቻችን ዘንድ በቤ
ተሰብ ፣ በጋብቻ ፣ በወሊድ ፣ በአጠቃላይ
አኗኗር በሴቶች ላይ ጭካኔ የተሞላበት ኢ
ሰብአዊ በደል ሲፈጸም ይታያል ። ከቦታ
ቦታ አድራጐቱ በቅርጹ የተለያየ ቢመስል
ም በይዘት ሁሉም ተመሳሳይ ነው ።

ለምሳሌ በከፋና በጊሚራ አካባቢ ፣
በወለጋ አንዳንድ አካባቢዎች ፣ በኢ
ሉባቦር ሸኮች በመባል በሚታወቁት
ማህበረሰቦች ዘንድ ሴት የወር አበባዋ በ
መጣ ቁጥር እንደርኩስ ስለምትቆጠር ፣

Digitized by Google

ከቤት ውጭ የመቆየት ግዴታ አለባት ። እንዲሁም የክርስትና ሃይማኖት በሚከተሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች አካባቢ የወር አበባዋ የመጣበትና አራስ ሴት እንደርኩስ ስለሚቆጠሩ ወደ ቤተ እምልኮ አካባቢ እንዲጠጉ አይፈቀድም ፤ የተጠጋቸውም ሰው እንደርኩስ ይቆጠራል ።

በጋሙጎፋ ክፍለ ሀገር በኮንሶ ብሔረሰብና በከፋ ክፍለ ሀገር በጊሚራ አውራጃ ባሉ ብሔረሰቦች አንዲት ሴት የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ የሚያስፈልጓትን ነገሮች በመያዝ ከቤት መውጣት አለባት ። ራቅ ብላ ከወንዝ ዳር በተሰራች ጐጆ ውስጥ እስክትወልድ ድረስ ብቻዋን ትቀመጣለች ። ብቻዋን አምጣና ተገላግላ «ጣጣዋን» ከጨረሰች በኋላ ቆየት ብላ ወደ ቤቷ ትመለሳለች ። ይህ ሁሉ ሲሆን ዞር ብሉ የሚያያት ሰው የለም ። በዚህ ሁኔታ የስንት እናቶችና የስንት ሕፃናት ሕይወት ያለአግባብ እንደተቀጨ ቤቱ ይቁጠረው ። ይህ ባህል ዛሬም ሙሉ በሙሉ አልተወገደም ።

በአንዳንድ ብሔረሰቦች አካባቢ ደግሞ ሕፃን ሴቶች በአስቃቂ ሁኔታ ብልታቸው እንዲሰፋና ሲዳሩ ደግሞ እንዲተረተር በማድረግ ፣ ለመናገር እንኳን የሚዘገንን ኢሰብአዊ ተግባር ይከናወናል ።

በብዙ ብሔረሰቦች ውስጥ ሴቲቱ ወጥታ ወርዳ ደክማ ያዘጋጀችውን ምግብ ከባሏ ጋር አብራ በሥነ ሥርዓት የመመገብ መብት እንኳን የላትም ። ለምሳሌ በኢሉባቦር ክፍለ ሀገር ባሉ አንዳንድ ብሔረሰቦች ውስጥ ለባሏ ያዘጋጀችውን ምግብ ስታቀርብለት ዓይኑን እንዳታይ አንገቷን ደፍታ ፣ በእንብርክኳ ሔዳ ካቀረበች በኋላ ፣ በእንብርክኳ ትመለሳለች ።

በአብዛኛው ብሔረሰቦች ውስጥ ሴቶች ልጆች የሚዳሩት በሕፃንነት ዕድሜያቸው ነው ። በሰሜን ክፍላተ ሀገር ከዘጠኝ ዓመት ጀምሮ መዳር የተለመደ አሠራር ነው።አንዳንድ ጊዜም ገና በናቶቻቸው ማኅጸን ውስጥ ሆነው ለጋብቻ ውል የሚቀርቡ ሕፃናት አሉ ።

በዚህ ላይ ለቁንጅና እየተባለ ሰውነት በመተኮስ ፣ ከንፈር በመቅደድ ፣ ገላ በመተልተል ፣ ጥርስ በመንቀል ፣ ወዘተ - - - ውብ ሰውነታቸውን በኋላ ቀር ባህላዊ አመለካከት የሚጐዱ ብዙዎች ናቸው ።

ከላይ የተጠቀሱት እጅግ በጣም ጥቂት ምሳሌዎች ለማንሳት ያህል ቀረቡ እንጂ ዝርዝር ውስጥ ከተገባ እንደነዚህ ያሉ በሴቶች ላይ በየዕለቱ በየቦታው የሚፈጸሙ ኋላቀር ፣ ለጤንነት ጐጂ የሆኑ ድርጊቶችና አድጎሪ አሠራሮች አያሌ ናቸው ።

በፊውዳሉ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ውስጥ እነዚህ ኋላቀር ድርጊቶች በኅብረተሰቡ ውስጥ እንዲሰርጹ ፣ ባህል ሆነው እንዲለመዱና በሥራ እንዲተረጐሙ የሚያግዙ የፊውዳሉ መንግሥት ደንቦችና ሕጐች ሴቶችን በሚመለከት ያዘሉት ፍሬ ሐሳብ ይሆኑ የሚደገፉ ናቸው ። የነበሩት ፍርድ ቤቶች ፣ የሃይማኖት ተቋሞች ፣ ወዘተ - - - ይሆኑ የሴቶችን የበታችነትና ተገዥነት የሚያስፋፉና የሚያራምዱ ነበሩ ። ይህ የገዥ መደቦች ፍላጐት በተለያየ መልኩ ተጽዕና እንዲያደርግ በመደረጉ ፣ ባጠቃላይ በኅብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት አግኝቶ ፣ እንደ ሀገር ባህልና ልምድ ተቆጥሮ የዘወትር አሠራር ሆኖ በተግባር ሲተረጐም ዘመናት ተቆጥረዋል ።

ሁኔታው ይህ ሆኖ ሳለ ይኸው ከባድ የኅብረተሰብ ተጽዕኖ በላያቸው ላይ መጫን ሳያንበረክካቸውና ተስፋም ሳያስቆርጣቸው ሴቶች ለኅብረተሰቡ ማኅበራዊ ኑሮ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ እንቅስቃሴ የራሳቸውን ድርሻ ሲያበረክቱ ቆይተዋል ።

ለኅብረተሰብ መሠረት የሆነውን ቤተሰብ ከመንከባከብ ፣ ሊሠራና ሀገሩን ሊገነባ የሚችል ሰው ከማዘጋጀት ባሻገር በየወቅቱ የእናት ሀገርን ዳር ድንበር ለመተናኮል የመጡትን ፣ ቅኝ ግዛት ለማስፋፋት ከባ

Digitized by Google

ሕር ማዶ የመጡትን ጠላቶች በጀግንነት ተፋልመው ሕይወታቸውን ሰውተው ከተ ከላከሉት አኩሪ ጀግና አባቶች መካከል ጀ ግና እናቶችም ይገኛሉ ። የሠራዊቱን ስንቅ በመሰነቅ፣ በጦር ሜዳ በጀግንነት እን ዲሰለፍ ከቤት ጀምሮ በማበረታታት፣ ከመ ሀል ሆነው በደጀንነት በመጠባበቅ፣ ከዚህ ም አልፎ በጦር ሜዳው ፍልሚያ ላይ ተሰል ፈው፣ ቁስለኞችን እያከሙ፣ እየደገፉና ከጠላት እየተዋጉ ሰፊውን ሕዝብ ለድል ካበቁት መካከል በምሳሌነት የሚጠቀሱ የአያሌ ሴቶች ታሪክ ባብዛኛው ገና በመዝ ገብ ላይ አልሰፈረም ።

ባንድ ወቅት አንዲት በሁለተኛው የዓ ለም ጦርነት በአውሮፕላን ተዋጊነት ከፍ ተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉና የሶቭየት የጀግና ሜዳይ ተሸላሚ የሆኑ አዛውንት ሴት በአ ንድ የሞስኮ ፋብሪካ ውስጥ ዓለም አቀፍ የሴ ቶችን ቀን ምክንያት በማድረግ ንግግር ሲያ ደርጉ በአጋጣሚ በስብሰባው ላይ ተገኝተው ለነበሩ ኢትዮጵያውያት ያቀረቡት ጥያቄ ነበር ። ይኸውም በሁለተኛው ዓለም ጦር ነት ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በሚወጋ በት ወቅት አንድ ቀን በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከጠላት ጋር ከፍተኛ የተፋፋመ ው ጊያ፣ ትንቅንቅ፣ የቤት ቃጠሎ፣ የደም መ ፍሰስ ነበር ። በዚያን ወቅት በዚያ ከባድ ፍ ልሚያ ውስጥ አንዲት ሴት የኢትዮጵያን ባንዲራ ከፍ አድርጋ እያውለበለበች ከአ ንድ ቤት ጣሪያ ላይ ወጥታ ባንዲራውን በ ሚታይበት ቦታ ላይ ተከለች ። ይህች ሴት ስሟ ማን ይባላል ? » የሚል ነበር ። ወደ ፊት አብዮታችን እውነተኛውን የሰፊውን ሕዝብ ታሪክ ከውስጥም ከውጭም ካፈ ታ ሪክም ከያለበት እያሰባሰበ ዕውን ሲያደር ገው የእኝህም ጀግና ሴት ስምና የሌሎችም ሴቶች እጅግ አኩሪ የጀግንነት ታሪክ ይገ ለጽ ይሆናል ።

የአብዮታችን ፍንዳታ ያስገኛቸው ድሎ ችና የሴቶች ሁኔታ

በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ሰፊው ህዝብ ለምዝበራ በመጋለጥ ረጅም የምሬት ጊዜ አሳልፏል ። የፊውዳል የምርት ግንኙነት እያደር እየተዳከመ ካፒታሊዝም በመ ጠኑም ቢሆን እያቆጠቆጠ መሔድ ኋላቀ ሩን የፊውዳል አገዛዝ ይበልጥ እያጋለጠው ሲሔድ ባንጻሩ በጋብቻና በጥቅም ከፊውዳ ሎች ጋር በቅርብ በመተሳሰር ብቅ ብቅ ማለ ት የጀመረው የቡርዧ መደብ የኅብረተሰቡን ኑሮ ለማሻሻል ያደረገው ጉልህ እንቅስቃሴ ባለመኖሩና ሊኖርም ባለመቻሉ ከቀን ወደ ቀን የሰፊው ሕዝብ ኑሮ እየተባባሰ መሔዱ አልቀረም ። ይህ ጭቆናና ብዝበዛ በ1966 በተጀመረው የአብዮታችን ሂደት ውስጥ ደረጃ በደረጃ መወገድ ጀመረ ።

ከአብዮቱ ፍንዳታ ማግስት ጀምሮ የኅብረ ተሰቡን ጥያቄዎች የሚመልሱ አያሌ ርምጃ ዎች በተከታታይ ተወስደዋል። ከነዚህም መ ካከል መሠረታዊውና ትልቁ መሬትን የሕ ዝብ ሀብት ያደረገው አዋጅ ሲሆን፣ ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጀው የዕ ድገት በኅብረት ዘመቻም ታውጆ በሥራ ላይ ዋለ ።እነዚህና በተከታታይ አብዮቱ የወሰ ዳቸው አያሌ አብዮታዊ ርምጃዎች ሁሉ የኅ ብረተ ሰቡን ጥያቄ ባጠቃላይ የሴቶችንም ጥያቄ ጭምር ሳይነኩ ያለፉበት ጊዜ የለም ።

የካቲት 25 ቀን 1967 የመሬት አዋጅ ቁ· 31/1967 በተ. ቁ· 1 « ጾታ ሳይለይ ማንኛውም ለማረስ ፈቃደኛ የሆነ ሰው ለራ ሱና ለቤተሰቡ ኑሮ የሆነ የገጠር መሬት በይ

Digitized by Google

ዞታ ያገኛል» ይላል ። ተ.ቁ. 3 «ማንኛውም እራሽ ሌላ ሰው በመቅጠር ለማረስ አይችልም ፤ ሆኖም ሌላ በቂ መተዳደሪያ የሌላት ሴት ወይም ባለይዞታ ሲሞት ፤ ሲታመም ወይም ሲያረጅ ሚስቱ ወይም ባልየው ወይም አካለ መጠን ያልደረሱ ልጆቹ ሠራተኛ በመቅጠር ለማረስ ይችላሉ» በማለት ሴቶችን የአዋጁ ተጠቃሚና ተሳታፊ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል ።

የመሬቱ ባለቤት ለመሆን የበቃው ገበሬ በተበጣጠሰ መሬት ላይ በየራሱ ከማረስ ይልቅ ኃይሉን አስተባብር መሣሪያውን አቀናጅቶ በኅብረት እንዲያመርት ገበሬውን በማስተማርና በመቀስቀስ በተደረገው ጥረት በየወቅቱ ቀስ በቀስ እያበቡ የመጡት የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ፤ በእርሻ ላይ ለተመሠረተው የሀገራችን ኤኮኖሚ አስተማማኝ የዕድገት መሠረቶች ናቸው ። በዚህ አኳያ ለአብዮታዊት ኢትዮጵያ ሴቶችም የእኩልነት ጥያቄ ዋናው መፍቻ ቁልፍ ይኸው በመሆኑ ለዚህ ዘርፍ የተሰጠው ትኩረት እጅግ ወሳኝ ውጤት ይኖረዋል ። ምክንያቱም በሀገራችንም ሆነ በሌላው ሀገር የሴቶች ጥያቄ ዘላቂ መፍትሔ የሚያገኘው በገጠርም ሆነ በከተማ የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ሲስፋፋና የምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ሲወገድ ነው ። የሴቶች ነፃነት ማግኘት ከሶሻሊዝም ግንባታ ጋር የተያያዘ መሆኑን አስመልክቶ ሌኒን ሲጽፍ ፤ «እስከ ዛሬ ድረስ የሴቶች መብት ከባሮች ጋር የሚያነጻፅር ነበር ፤ ሴቶች የቤት ሥራ በሚነባቸው ቀንበር ሲዳሸቁ ኖረዋል ። ከዚህ ሊያድናቸው የሚችለው ሶሻሊዝም ብቻ ነው ። ሴቶች ፍጹም ነፃነታቸውን የሚቀዳጁት ከአነስተኛ የግል እርሻ ተላቅቀው ወደማኅበራዊ እርሻና ወደማኅበራዊ የመሬት ይዞታ ሊሸጋገሩ ሲችሉ ነው» [4] ብሏል ።

በሀገራችን ዛሬ ባሉት የገበሬ አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ውስጥ ያለው የሴቶች ተሳትፎ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ባሉ

ጣኝ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው ። በሌላ በኩል ለመሳተፍ ዕድል ያገኙት ጥቂቶቹ ደግሞ የማኅበራቱን ጠቃሚነትና የእኩልነት መገለጫ መድረኮች መሆናቸውን በተግባር እያዩት ነው ። በሸዋ ክፍለ ሀገር በመናገሻ አውራጃ በዓለም ገና ወረዳ በሚገኘው በዳለቲ ነውሶ የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር ከ232 አባላት ውስጥ 93 ሴት አባላት ያሉት ሲሆን የዚሁ ማኅበር አባል የሆኑት ጓድ ራዲያ መታፈሪያ ባንድ ወቅት አስተያየት ሲሰጡ «ባለቤቴ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ምንም ዓይነት ቋሚ የመተዳደሪያ ገቢ ስላልነበረኝ ልጆቼን የማሳደግ ኃላፊነት በጣም ከባድ ሸክም ሆኖብኝ ነበር ። በቀበሌያችን ይህ የኅብረት ሥራ ማኅበር ሲቋቋም ለችግሬ መፍትሔ ለማግኘት በአባልነት ለመመዝገብ በቅቻለሁ ። በመጀመሪያ እንዲያው ሰው ያደረገውን ልሞክር ብዬ ነው እንጂ እስከዚህም ተስፋ ጥዬበት አልነበረም ። ከዓመት ወደ ዓመት ግን ብዙ ለውጥ አይቻለሁ ። የማኅበሩ አባል ከሆንኩ ወዲህ ያቅሜን ያህል ሠርቼ የልፋቴን ዋጋ ስለማገኝ እኔና ልጆቼ የኑሮ ዋስትና አግኝተናል ። በማኅበሩ ውስጥ እያንዳንዱ አባል የሚችለውን ያህል ሠርቶ በሥራው መጠን ስለሚከፈል እኛም በሴትነታችን የሚደርስብን ተጽዕኖ የለም ። እስካሁን በሬ ጠምዶ ከማረስ በስተቀር በአብዛኛው የሥራ መስክ ከወንድሞቻችን ጐን ተሰልፈን የምንችለውን ያህል እንሠራለን» [5] ብለው ነበር ። ይህ አባባል በብዙ የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባል ሴቶች ዘንድ ተደጋግሞ የሚጠቀስ ሲሆን ፤ የገበሬዎች የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር በገጠሪቷ ኢትዮጵያ ለሶሻሊስት ኤኮኖሚ መሠረትና የሴቶች መብት ማስከበሪያ ለመሆን ከተጨባጭ ማስረጃዎች መሀል አንዱ ነው ።

በከተሞችም ቢሆን እያሌ የሴቶችን ጥያቄ የሚመልሱ እርምጃዎች እየተወሰዱ ነው ። ኅዳር 21 ቀን 1968 የወጣው የሠራተኛው ጉዳይ አዋጅ ምዕራፍ 5 አንቀጽ 39

Digitized by Google

ተ··ቁ ፪ ላይ «ማንኛውም ነፍሰጡር ሠራተኛ 45 ቀን መደዳውን ደመወዝ የሚከፈልበት የወሊድ ፈቃድ ይሰጣታል» ይላል ። በዚሁ አዋጅ መሠረት ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ እንዲከፈል ፣ ነፍሰጡር ሴቶች በማታ ፈረቃ እንዳይሠሩ ፣ ከከባድ ሥራ ወደ ቀላል ሥራ እንዲዛዋወሩ መብት ሰጥቷል ። ይህ ሠራተኛ ሴቶችን በሚመለከት የተሰጠው ትኩረት በተለይ በፋብሪካ ብዙ ሲሰቃዩ ለኖሩ ሴት ወዝአደሮች ከፍተኛ ለውጥ ያስገኘ ነው ።

የአብዮታችንን አቅጣጫና ዓላማ ግልጽ ባደረገው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ ፣ በክፍል 2 ቁጥር 6 «በሃይማኖቶችና እንዲሁም በጾታዎች መካከል ምንም ዓይነት አድልዎ አይደረግም ። ማንኛውምዜጋ በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ጉዳዮች ለሚኖረው ሚና በጾታና በሃይማኖት ሳቢያ ምንም ልዩነት አይደረግም » ይላል ።

ከዚህ በላይ የተመለከቱት ለምሣሌ ያህል በዋና ዋና አዋጆች ላይ የተጠቀሱትን ለማስታወስ ብቻ ተነሡ እንጂ ለኅብረተሰቡ ደህንነት ፣ ለኢኮኖሚና ለማኅበራዊ ኑሮ እድገት ሲባል አብዮታችን በየወቅቱና በየፈርጁ የወሰዳቸው ርምጃዎችና መመሪያዎች ሁሉ የሴቶችን ተሳትፎ የሚጋብዙና የሴቶች አስተዋጽኦም ያልተለያቸው መሆኑ ግልጽ ነው ። የነዚህ መመሪያዎች በየጊዜው መውጣት ቀደም ሲል የነበሩትን አድኃሪ ሕጎችና ደንቦች ደረጃ በደረጃ በመሻርና በመተካት ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ ሊያደርግ ችሏል ።

አብዮቱ በአጠቃላይ በወሰዳቸው እርምጃዎች ሴቶችን በሚመለከት ካነሳቸው ጉዳዮች ሌላ በተለይ ሴቶችን የሚመለከቱ ርምጃዎችም በየወቅቱ ተወስደዋል ።

የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ሴቶች መደራጀት

በአብዮቱ ፍንዳታ ማግስት ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ የሴቶችን በአብዮቱ አካባቢ መሰባሰብ አስፈላጊነት በመረዳት ፣ በየሥራ መስኩ የሚገኙ ሴቶችን በማሰባሰብና ትምህርት በመስጠት የወደፊት የሴቶችን ማኅበር መሠረት የሚጥል አካል እንዲፈጠር በነበረው ፍላጐት አንድ « የሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴ» የተባለ ኮሚቴ በማቋቋም የሴቶች ጥያቄን አቅጣጫ የሚያስይዝና ሴቶችን በቀጥታ የአብዮቱ ተሳታፊዎች ለማድረግ የሚያስችል መድረክ ለመክፈት ብዙ ጥረት አድርጓል ። ብዙም ሳይቆይ በኮሚቴው አባላት መካከል ሰርገው የገቡ የለየላቸው ጸረ ሕዝብ አባላት የኮሚቴውን ዓላማ አቅጣጫ ለማስለወጥና ኮሚቴውንም የጸረ አብዮት መድረክ ለማድረግ ሲያካሂዱ የነበረው ቅስቀሳና ሲወስዱ የነበረው እርምጃ በኮሚቴው ውስጥ ከነበሩ የአብዮቱ ወገኖች ጋር ከፍተኛ ፍልሚያ እንዲደረግ ሁኔታው አስገድዶ ነበር ። በኮሚቴው ውስጥ የነበረው እንቅስቃሴ ከኮሚቴው ውጭም በመንጸባረቅ ፣ በተለይ በሠራተኛ ሴቶች አካባቢ ብዙ ውዥንብር እንዲፈጠር ምክንያት ሆኖ ነበር ። ይህን አደገኛ አዝማሚያ አብዮቱ በወቅቱ ሊቆጣጠረው በመቻሉ ሥር ሳይሰድ ቶሎ ሊቀጭ ችሏል ።

ግንቦት 1968 የሕዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ጽ/ቤትን ያቋቋመው አዋጅ ሲወጣ በውስጡ የሴቶች ክፍል በመክፈት ሴቶችን በአብዮቱ አካባቢ ለማሰባሰብ ሌላ ጥረት መደረጉ ይታወሳል ። በዚህ ክፍል አማካይነት ሴቶችን በማንቃትና በማደራጀት ፣ የሴቶችን ጥያቄ ትክክለኛ አቅጣጫ ለማሳወቅ ፣ የነበረውን ጸረ ሕዝብ እንቅስቃሴ ለመቅጨትና ሴቶች በአብዮቱ ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና ግልጽ ለማድረግ፣ በየቦታው የሴቶች ማኅበራትን ጥንስሶች በመ

Digitized by Google



የኢአሴማ ሁለተኛ መደበኛ ጉባኤ

መሥረት ሴቶችን በድርጅት አካባቢ ለማ ሰባሰብ ጥረት ተደረገ ።

የሴቶች ማኅበራት በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በየክፍላተ ሀገር በገጠርና በከተማ እየተስፋፉ ፣ የየራሳቸውን መመሪያና ደንብ በመንደፍ በገጠር በገበሬ ማኅበራት ፣ በከ ተማም በከተማ ነዋሪዎች ማኅበር ድጋፍ ማበብ ጀመሩ ። ሴቶችም በማኅበራቱ አማ ካይነት ተሣትፎአቸውን በማስተባበር በሀ ገሪቱ ኤኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና በሀገር መከ ላከል ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለማድረግ ቻሉ ።

በ1972 ኅብረተሰቡን ለግንባር ቀደም የፓርቲ አመራር ለማብቃት ፣ የኅብረተሰ ቡን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በተቀነባበረ መልክ ለመምራት ፣ የተቋቋመው ኢሠፓ አኮ ባዘጋጀው መመሪያና ፕሮግራም ሕዝ ባዊ ድርጅቶችን በአዲስ መልክ ለማጠና ከር የወሰደው ርምጃ የሴቶች እንቅስቃሴ ይበልጥ የተቀነባበረ አሠራር እንዲኖረው አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል ። በኢሠፓአኮ የድ ርጅት መምሪያ ሥር የተዋቀረው የሴቶች ጉዳይ ክፍል ለሴቶች ጥያቄ ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ፣ የሴቶችን አጠቃላይ ሁኔታ እያ ጠናና እየተከታተለ የመፍትሔ ሀሳብ እን ዲያቀርብ ፣ በሀገሪቱ ኤኮኖሚያዊ ፣ ማኅበ ራዊና ባሕላዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የሴቶች ተሣትፎና አስተዋጽኦ ከፍ እንዲል አመች ስልቶችን ለመቀየስ ኃላፊነት ተሰጥቶት ተቋቋመ ።

ይህንን መሠረት በማድረግ ኢሠፓአኮ ራሱን ካደራጀ በኋላ እንቅስቃሴውን ሲጀ ምር ቅድሚያ ትኩረት የሰጠው የሴቶችንና የወጣቶችን ማኅበር በማጠናከር ላይ ስለ ነበር ፣ ለዚሁ አስፈላጊ የሆኑትን ዝግጅ ቶች ካጠናቀቀ በኋላ በኢትዮጵያ ሴቶች ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያ የሆነው የአብ ዮታዊት ኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበር (አኢ ሴማ) አንደኛ ጠ/ጉባዔ 1972 ተጠርቶ ሕ ጋዊ ሰውነትም አግኝቶ ሀገር አቀፍ ማኅበር ሊመሠረት ቢቃ ።

ነሐሴ 16 ቀን 1975 2ኛ ጉባዔውን በመ ጥራት እራሱን እንደገና ያጠናከረውና ሴ ቶች የእናትነት ተግባራቸውን በተመቻቸ ሁኔታ እንዲያከናውኑ ፣ከዚህ ጐን ለጐን የሠ ራተኛነት ግዴታቸውን በሚገባ አሟልተው እንዲገኙና የእኩል ዜጋነት መብታቸው መጠበቅ የረጅም ጊዜ ዓላማው የሆነው አኢሴማ በአሁኑ ወቅት በ20,421 መሠረ ታዊ ማኅበራት ተዋቅሮ 5,127,614 አባላት ያ ሉ ት ማኅበር ሊሆን በቅቷል ። የሀገሪ ቱን አስተዳደር ክልል መሠረት በማድረግ ማኅበሩ በወረዳ ፣ በአውራጃና በክፍለ ሀገር ብሎም በሀገር አቀፍ የተዋቀረ ሲሆን ሴቶ ችን በአጠቃላይ በሚኖሩበት አካባቢና ሠራ ተኛ ሴቶችን በተለይ በመሥሪያ ቤታቸው አካባቢ ያሰባስባል ።

ከመሠረታዊ ማኅበር አንስቶ እስከ ሀገር አቀፍ ድረስ በጠቅላላው ከ255,000 በላ የአመራር አባላት ተመርጠው በየደረጃው የማኅበሩን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ ከፍ ተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ ። ከነዚህ አመራር አባላት መካከል በሀገር አቀፍና በክፍለ ሀገር ደረጃ ተመርጠው ማኅበሩን በቋሚነት የሚያገለግሉ 100 አባላት ሲኖሩ በማኅበሩ ተቀጥረው አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችና በትርፍ ጊዜያቸው ዕውቀ ታቸውን የሚያካፍሉ ጓዶችም ይገኙበታል።

ኢሠፓአኮ የሴቶችን ማኅበርና እንቅስ ቃሴያቸውን ለመርዳት በየጊዜው በሚሰ ጠው ድርጅታዊና ርዕዮተዓለማዊ አመራር የአብዮታዊት ኢትዮጵያን ሴቶች የወደፊት የትግል አቅጣጫ ቀይሷል ፤ ለጥያቄውም መፍትሔ ሊያስገኙ የሚችሉ አመች ሁኔ ታዎች ለማዘጋጀት ጥረት አድርጓል ።

ከላይ ባጭሩ የተጠቀሱትና ሴቶችን ለማ ንቃትና ለማደራጀት ፣ በአብዮቱ የተደረጉ ት ጥረቶች በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም ። የነዚህ ጥረቶች ውጤት ዛሬ ሴቶች በበለጠ በነቃ ተሣትፎ ለመብታቸው እንዲታገሉና አብዮታቸውን እንዲንከባከቡ አመች ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል ።

Digitized by Google



ሴቶች አብዮቱ የፈጠረላቸውን አመቺ ሁኔታ በመጠቀም በፖለቲካ ዘርፍም ንቁ ተሳትፍ ያደርጋሉ

ሴቶች በኢኮኖሚ ግንባታ መስክ

Digitized by Google

የሴቶች ተሳትፎ ከፍ ማለት

የሴቶች ሁኔታ በቅድመና በድህረ አብዮት ኢትዮጵያ ትልቅ ልዩነት አለው ። በዓለም ዙሪያ በምሣሌነት የሚጠቀሰውን የአብዮታችን ውጤት የሆነውን የመሠረተ ትምህርት ሁኔታ ስንመለከት ፣ የሴቶች ተሣትፎ በከፍተኛ ደረጃ የሚታይበት መስክ ሲሆን ፣ የሴቶችን ጥያቄ ለመፍታት በሚደረገው ውስብስብ የትግል ሂደት ውስጥ ትልቅ እርምጃ ነው ። በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ «የሴት ትምህርት፣ተምራ የት ልትደርስ»በሚለው አድሃሪ ፈሊጥ ዕድሉ ተነፍጓቸው የኖሩ ሴቶች ዛሬ አብዮቱ ያስገኘላቸውን ድል በሚገባ ለመጠቀም ካላቸው ፍላጐት የተነሳ ትምህርቱን አጥብቀው የያዙት መሆናቸው በተግባር እየታየ ነው ። ከመጀመሪያው የመሠረተ ትምህርት ዙር ጀምሮ እስከ ዛሬ ሴቶች በመማር ብቻ ሳይሆን በማስተማርም ከፍተኛ ተሣትፎ አሳይተዋል ፤ አሁንም በማሳየት ላይ ናቸው ። ከ1ኛ እስከ 8ኛ ዙር ብቻ በማስተማር ተግባር የተሣተፉ ሴቶች ቁጥር 173,863 ሲሆን ይህም ከጠቅላላው ተሣታፊ 17.7 በመቶ ይሆናል። ከዚህ በላይ በነዚህ ዙሮች በመማር የተሳተፉና ፈተና ያለፉ 4,086,415 ሲሆኑ ይህም ከጠቅላላው ተሣታፊ ጋር ሲወዳደር 48.9 በመቶ ነበር ። ይህ እጅግ የሚያበረታታ ውጤት ነው ። በመሠረተ ትምህርት ብቻ ሳይሆን በድህረ መሠረተ ትምህርት በመቀጠል የ8ኛውን ርዙ መልቀቂያ ፈተና ሳይቀር የወሰዱና ያለፉ ሲኖሩ ፣ ሴቶች በብዛትና በስሜት ትምህርቱን ሲከታተሉ ማየቱ አብዮታችን የሴቶችን ጥያቄ ለመመለስ የወሰደው እርምጃ ምን ያህል ውጤታማ እየሆነ መምጣቱን ያስገነዝበናል ።

በመደበኛ ትምህርትም በማስተማርም ሆነ በመማር የሴቶች ተሣትፎ እያደገ መጥቷል ። በ1965 ከ1--12ኛ ክፍል 283,771 የነበረው የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከጠቅላላው 30.7 ከመቶ ሲሆን፣ ይህ ቁጥር በ1974 ወደ 1,018,600 ወይም ወደ 36.7 ከመቶ ከፍ ብሏል ።

በየሥራ ዘርፉና በየማምረቻ ተቋም የሚሠሩ ሴቶች በትክክል ቁጥራቸውን ለማስፈር ያለው መረጃ በቂ ባይሆንም ፣ በመኢሠማ ሥር የተደራጁት ሴቶች ቁጥር24%፣ በመንግሥት መ/ቤት በሥራ የተሰማሩ 16.6.% እንደሚሆኑ ይገመታል ። በሌላ በኩል ብዙው አምራች የሰው ኃይል በተሰማራበት በገጠሩ አካባቢ በመኢገማ ሥር የተደራጁ ሴቶች ብዛት 12.7% ሲሆን በገበሬ አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሥር የተደራጁ ሴቶች 7.5% ብቻ እንደሆኑ ይገመታል ።

የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት መስፋፋትና መጠናከር መሠረቱን በመጣል ላይ ለሚገኘው የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ዋልታ እንደመሆኑ የነዚህ ማኅበራት መስፋፋት ለሴቶች እኩልነት እውን መሆን ወሳኝ ነው ። ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ ዛሬ በማበብ ላይ ባሉት ያምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ውስጥ የሴቶች ቁጥር በሚፈለገው መጠን እያደገ አለመምጣት የሚያሳስብ ጉዳይ ስለሆነ ብዙ ሥራ ሊሠራበት የሚገባ አካባቢ ነው ። በአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር ውስጥ በአባልነት የሚመዘገቡ የቤተሰብ ኃላፊዎች መሆናቸውን መመሪያው ስለሚገልጽና በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የቤተሰብ ኃላፊዎች ወንዶች ወይም ባሎች ስለሆኑ ይህም ለችግሩ አስተዋጽኦ ያደረገ ዓቢይ ምክንያት ነው ።

ሴቶች በየሙያ ማኅበራቱ ውስጥ በአባልነት ከመሳተፍ ባሻገር በአመራር አባልነትም ተመርጠው አገልግሎት ይሰጣሉ ። በመኢገማ ውስጥ 1,913 የአመራር አባላት ሲገኙ፣በመኢሠማ ውስጥ 5,362 ሴቶች አመራር በመስጠት ላይ ናቸው ። ከዚህ በተረፈ በከነማ ፣ በአኢወማ ፣ በአብዮት ጥበቃ ፣ በውይይት ክበብ ውስጥ የሴቶች ተሣትፎ በየጊዜው እያደገ በመምጣት ላይ ነው ።

Digitized by Google

ሴቶች አብዮትንና ሀገርን ከጥቃት ለመከላከል ከፍተኛ ወታደራዊ ተሳትፎ ያደርጋሉ ።

የሴቶች ተሳትፎ የወደፊቱ አቅጣጫ

ሴቶቻችን ዛሬ ባሉበት የዕድገት ደረጃ በጥቂት የአብዮት ዓመታት ውስጥ ያገኙት ፖለቲካዊም ሆነ ማኅበራዊ ንቃት በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። በየማኅበሮቻቸው አማካይነት ከሚያገኙት ትምህርት ሌላ በየ አካባቢያቸው ካሉት ሕዝባዊ ድርጅቶችና አብዮታዊ ተቋሞች ፣ ከሁሉም በላይ በሕ ይወታቸውና በኑሮአቸው ላይ አብዮቱ ያስ ከተለው ለውጥ ራሱ እንደ ትልቅ ተግባ ራዊ ትምህርት ተቆጥሮ ፣ የሴቶችን የእኩ ልነት ጥያቄ ፣ በውስጥ የጠላትንና የወዳጅን አሰላለፍ በመጠኑም ቢሆን ዛሬ ያልተረዳች ሴት አለች ለማለት አያስደፍርም ። ሆኖም አሁንም የሴቶችን መብት ተግባራዊ ለማ ድረግ በርካታ ችግሮች አሉ ።

ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው የፊውዳል ልማድና ወግ መሠረት ኅብረተሰቡ ስለሴ ቶች ያለውን አመለካከት ወይም ሴቶች ራሳቸውም ስለራሳቸው ያላቸውን ዝቅተ ኛነት አመለካከት ዛሬ ተወጥተዋል ፣ ለማ ለት በጣም አስቸጋሪ ነው ። በኢኮኖ ሚና በፖለቲካ መስክ ለረዥም ጊዜ ስር ሰዶ የኖረው የፊውዳል ስልተምርት በኅብ ረተሰቡ ውስጥ የተወው አስተሳሰብና አመ ለካከት በቀላሉ የምንገላገለው አይደለም።ይህ አስተሳሰብባ የሚቀየረው በአጠቃላይ የባ ሕል ዕድገት ሲሆን ተግባራዊም የሚሆነው ብዙ የፓርቲ የርእዮተዓለምና የፕሮፓጋንዳ ሥራ ለረዥም ጊዜና በማያሰልስ ሁኔታ በሕዝቡ ውስጥ በተጠናከረ መልክ መሠ ራት ሲችል ነው ።

ቀድሞ የነበረው ኋላቀር አሠራርና አስ ተሳሰብ ዛሬም በብዙ አካባቢ የሴቶቻችንን ኑሮ አስቸጋሪ እያደረገው ነው ። ትምክህ ተኛ ወንዶችም በሴቶች ላይ የሚፈጽሙት አስጸያፊ ተግባር ፣ ሴቶችን በሁለተኛ ደረ ጃነት የመመልከት ልምድ ፣ ሴቶችን ከመ ርዳትና ከማገዝ ይልቅ በሁኔታቸው መሳ ለቅ፣ የሴቶችን የእኩልነት ጥያቄ አውቆ የተጣመመ ትርጉም የመስጠትን መሰል ድርጊቶች ዛሬም ያሉ ችግሮች ናቸው ።

አሁንም ካለንበት ኋላቀርነት የተነሳ የሴ ቶች የቤት ውስጥ የሥራ ሁኔታ አልተሻሻ ለም። ቀሴች ዛሬም በቤት ውስጥ ሥራቸውን የሚያከናውኑት ኋላቀርና አድካሚ በሆኑ መሣ ሪያዎችነው። ልጆቻቸውን በመዋዕለ ሕፃናት የማስገባት እድል የሚገጥማቸው የእናቶች ቁጥርም እጅግ አነስተኛ ነው ። በእርግጥ ከአ ብዮቱ በፊት የነበሩት መዋዕለ ሕፃናት ቁጥር 77 ሲሆን ከአብዮቱ በኋላ የተሠሩት ደግሞ በጠቅላላ 630 ናቸው።ከአብዮታችን ፍንዳታ በኋላ የተቋቋሙት መዋዕለ ሕፃናት በተለይ ከዚህ በፊት ዕድሉን ለተነፈጉት የኅብረተ ሰብ ክፍሎች ግልጋሎት የሚሰጡ ከመሆ ናቸውም ሌላ የቁጥራቸው መጨመር ባለ ፈው የፊውዳል ዘመን ከነበሩት በጣም ከፍ ተኛ ዕድገት እያሳየ ነው ። ይህም ሆኖ ዛሬ ያሉት ጥቂት መዋዕለ ሕፃናት በከ ተሞች አካባቢ የተቋቋሙ ሲሆን ፣ እነዚህም ቢሆኑ እጅግ በጣም ያነሱ ናቸው ።

ሴቶች ያለባቸው የቤት ውስጥ የረጅም ጊዜ ሥራ ፣ ልጆች የማሳደግ ተግባር ጭምር ብዙውን ጊዜያቸውን ስለሚሻሙ ይህንን ኃላፊነታቸውን ተወጥተው በሌላ የሥራ መስክ ለመሠማራት የቻሉትም የሚጠበቅ ባቸውን ውጤት በተሟላ ሁኔታ ለማከና ወን ችግር ይገጥማቸዋል ።

ዛሬ የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበ ራቸውን በሀገር አቀፍ ደረጃ አዋቅረው እን ቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛሉ ።ይህ ሴቶችን በተደራጀ መልክ ለማስተባበር የሚያስች ላቸውና በብዙ ትግል የተገኘው መድረክ ከላይ የተጠቀሱትን ሥር የሰደዱ ችግሮች በመፍታትም ሆነ ለወደፊቱ ትግል እጅግ ውስብስብና ወሣኝ እርምጃዎችን ለመው ሰድ ዓይነተኛ መሣሪያ የሆነና ሊሆንም የ ሚገባው ነው ። በአባላቱ ብቻ ሳይሆን ጠቅ ላላ የኢትዮጵያን ሴቶች ለማንቀሳቀስ ኃላ ፊነት የተጣለበት በመሆኑ ማኅበሩን ከማ

Digitized by Google

ወኖከር ጉን ለጉን ሊያራምዱቸው የሚገባ ብዙ ሥራዎች ይጠብቁታል ፡፡

ሴቶች በእናትነታቸው የወደፊቱን ትውልድ በማዘጋጀት ፣ ጤናማና የታነፀ ኅብረተሰብ ለማበርከት ልጆች ወልደው ተንከባክበው ማሳደግ የሚጠበቅባቸው ክቡር ተግባር ነው ፡፡ በሚስትነታቸው በመተሳሰብና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ጋብቻ መሥርተው ለባላቸው አጋዥና ድጋፍ ሆነው በጋራ ጥሩ ቤተሰብ የመመሥረት ኃላፊነት አለባቸው፡፡በዜግነታቸው በሀገሪቱ ፖለቲካዊ ሕይወት ውስጥ የእኩልነት መብት አግኝተው በመንግሥት መዋቅርና በሌሎችም ተቋሞች ውስጥ የመምረጥ ፣ የመመረጥ ፣ በኃላፊነት ቦታ ላይ የመመደብና ለኅብረተሰቡ ግልጋሎት የመስጠት መብትና ግዴታ አለባቸው፡፡

በሠራተኛነታቸው በርካታ ማኅበራዊና ባሕላዊ ተግባሮች አሉባቸው ፡፡ የኅብረተሰቡን ልዩ ልዩ ማኅበራዊ ችግሮች በመፍታት ፣ ምርት በማሳደግ ፣ ብቁና ታታሪ ሠራተኛ በመሆን የተጣለባቸውን ኃላፊነት በተሳካ ሁኔታ መወጣት ይጠበቅባቸዋል ፡፡

የኢሴማ ዋና ተግባርና ኃላፊነት የሚሆነው ከፓርቲውና ከመንግሥት ሙሉ ድጋፍ እያገኘ ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባሮች ሴቶች በተሟላ ሁኔታ እንዲወጡ ማገዝና ማዘጋጀት ነው ፡፡ ሴቶች እነዚህን ተግባራት በተሟላ ሁኔታ ሊያከናውኑ ከቻሉ ማለትም ሴቶች የእናትነት ፣ የሚስትነት ፣ የዜግነትና የሠራተኛነት ተግባራቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲወጡ አመች ሁኔታ ሊፈጠርላቸው ከቻለ ፣ የሴቶች ጥያቄ ተግባራዊ ምላሽ አገኘ ማለት ነው ፡፡

ሴቶች የእናትነትና ሌሎችም ተግባሮቻቸውን በሚገባ እንዲያከናውኑ በቅድሚያ የሴቶች የቤት ውስጥ የሥራ ሸክም መቃለል አለበት

ለብዙ ዘመን የሴቶች ቦታ በማጀት ውስጥ እንዲወሰን የተደረገ በመሆኑ ፣ ሴቶች በኅብረተሰቡ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ንቁ ተሣትፎ እንዳያደርጉ ታፍነው ቆይተዋል ፡፡ ሴቶች አሰልቺና አድካሚ ለሆነ ፣ ከዚህም በላይ ምርታማነት ለሌለው ከባድ ኃላፊነት ተዳርገው ኖረዋል ፡፡ ይህንን ሁኔታ ለማሻሻል ተገቢው እርምጃ ካሁኑ ሊወሰድ ካልቻለ ለሌላው ተሳትፎአቸው ሁሉ እንቅፋት ሊሆን የሚችል ነው ፡፡ ይህንን ሁኔታ በሚመለከት ሌኒን ያለውን እንጥቀስ ፤ «ምንም እንኳን ነፃነት የሚያውጁት ሕጎች የወጡና የጸደቁ ቢሆንም ፣ ሴቶች የቤት ውስጥ ባሪያ መሆናቸው አሁንም አልተወገደም። ዛሬም ጥቃቅን የቤት ውስጥ ሥራዎች አንቀው እንደያዟቸው ፣ እንዳሰለቿቸውና እንዳዋረዱዋቸው ነው ፡፡ እነዚህ ሥራዎች ሴቶችን ከማድቤትና ከሕፃናት ጋር አብረው በማያያዝ የጉልበት ኃይላቸውን አስከፊ ከሆነ ፣ ከማይረባ ጥቃቅንና አእምሮ በሚያቀረቅዝ ፣ ራስ በሚያዞር ፣ ቅስም በሚሰብር ውጣ ውረድ እንዲያባክኑ አስገድዷቸዋል። እውነተኛ የሴቶች አርነት ማለትም ኮሚኒዝም የሚመሠረተው በዚህ ዝቅተኛ በሆነ የቤት ውስጥ ኢኮኖሚ ላይ ሰፊ ትግል ሲደረግ ነው . . . ወይም ደግሞ ነገሩን በተሻለ ሁኔታ ለማቅረብ ፣ ይህ የቤት ውስጥ ኢኮኖሚ አጠቃላይ በሆነ ፣ ብዙውን እቅድ በሚይዝ ሁኔታ ወደ ከፍተኛ ሶሻሊስት ኢኮኖሚ ሲለወጥ ብቻ ነው ፡፡»[6] ይህ ግልጽ አባባል ማብራሪያ የሚያሻው አይደለም ፡፡

በኛ ተጨባጭ ሁኔታ ያለንበት የኢኮኖሚ ሁኔታ በፈቀደው መጠን በዚህ ላይ ካሁኑ ርምጃ መውሰድ መጀመር አለበት። ኋላቀር የቤት ሥራ ፣ ኋላቀር የማብሰያና የአመጋገብ ባሕል ሁሉ ለውጥ የሚያሻው ጉዳይ ነው ፡፡ በግብርና ሚ/ር ሥር ያለው የኑሮ ዘዴ ክፍል ከኢሴማ ጋር በመተባበር ከ 1973—1975 ብቻ እንኳን 29,531 ገበሬ ሴቶችን በገጠር የኑሮ ዘዴ ፣ በሕፃናት አስተዳደግና በቤት አያያዝ አሠልጥኗል ፡፡ ከነዚህ ሠልጣኞች ውስጥ ምንያህሉ እርግጥ የተማሩትን በተግባር እየተረጐሙት

Digitized by Google

ነው የሚለው የቅርብ ክትትል ሊደረግበት የሚገባ ጉዳይ ነው ። በትላልቅ ከተሞቻችን በአ/አበባ ጭምር በቁም ምድጃ የሚጠቀሙ ሴቶች ቁጥር ምን ያህል ይሆን ? በግምት ለመናገር እጅግ አነስተኛ ነው ።

በገጠር አካባቢ በዛ ያሉ የአኢሴማ አካላት ገንዘብ እያዋጡ የእህል ወፍጮ ለመግዛት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው ። ይህም ለገጠሯ ሴት ምን ያህል ሥራ ሊያቃልልና ጊዜ ሊቆጥብ እንደሚችል መገመት አያዳግትም ። ውሀ ለመቅዳት እንስራ በጀርባዋ አዝላ ለረጅም ጊዜ የምትጓዘው፣ እንጨት ሰብራ ለቤቷ ወይም ለገበያ ለማቅረብ ለብዙ ሰዓት ወገቧ የሚጐብጠው ፣ እንጀራ ለመጋገርና ወጥ ለመሥራት በእሳትና በጭስ ላይ የምትንቃቃው ሴት ሁኔታ እንዲሻሻል ባለው አቅም በመንግሥት በኩልም ሆነ በህዝባዊ ድርጅቶች ጥረቱ ይበልጥ መዳበር አለበት ።

የቤት ውስጥ መሣሪያዎች ፣ እንጀራ መጋገሪያው ፣ ወጥ መሥሪያው ፣ እህል መፍጫው ፣ መፍተያው ፣ ውሀ መቅጃው ፣ እንጨት ማምጫው ፣ ወዘተ ... በተሻሻለ መንገድ ተለውጠው የሚሠሩበትን ፣ ከተሰሩም በኋላ ሊዳረሱና በጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉበትን ሁኔታ በመከታተልና በማጥናት ማገዝ ያስፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪ በቤት ውስጥ የሚዘጋጁት እንጀራ ፣ ሽሮው ፣ በርበሬው ፣ ቅመማ ቅመሙ የቤት ሥራ መሆናቸው ቀርቶ በኢንዱስትሪ በስፋትና በብዛት ሊዳረሱ በሚችሉበት መልክ እንዲዘጋጁ ለማድረግ መጣርና ሴቶችም ለውጡን ተቀብለው በሥራ እንዲተረጉሙት በማኅበራቸው በኩል ማስተባበር ልናልፈው የማይገባ ግዴታ ነው። በዚህ ዓይነት ማኅበራዊ ምርት እንዲዳብር በምናደርገው ሂደት ውስጥ ነው ችግሩን እያቃለልን ልንሄድ የምንችለው ።

ሌላው የልጆችን ሁኔታ የሚመለከት ነው ። እናቶች በእርግዝናም ጊዜ ሆነ ከወለዱ በኋላ የራሳቸውንና የልጆቻቸውን ጤንነት ለመጠበቅ ፣ ከበሽታ ለመከላከል ፣ ክትባት በወቅቱ ለመውሰድ የሚያስችላቸውን ትምህርት በስፋት በመስጠት ፣ በወሊድ ጊዜ የሚደርሰውንና ዛሬም ያልተወገደውን ችግር ለመፍታት በመካሄድ ላይ ያለው የልምድ አዋላጆችን ሳይንሣዊ ትምህርት ተሀድሶ እያገኙ በብዛት እንዲሰራጩ ማድረግና በማኅበሩና በመንግሥት ትብብር የማዋለጃ ክሊኒኮችን ባለ አቅም ይበልጥ ማስፋፋት ያስፈልጋል ። የተወለዱትን ሕፃናት በአካባቢው ያለውን ምግብ በተመጣጠነ መንገድ እንዲመገቡ ፣ በመልካም ሥነ ምግባር ማሳደግን እንዲያውቁ ትምህርት በስፋትና በተከታታይ መስጠት ያስፈልጋል። ሴቶች በእናትነታቸው አዲሲቱን ኢትዮጵያ የሚገነቡና ለሰው ልጅ እኩልነት የሚታገሉ ዜጐች ማፍራት የሚጠበቅባቸው ቢሆንም ፣ በጣም ብዙ ሕፃናት በተከታታይ ወይንም በላይ በላዩ እየተወለዱ የአስተዳደግ ችግር እንዳይገጥማቸው ፣ በዚህ በኩል ምክር ሊያገኙ የሚችሉበት መድረክ በማህበሩና በመንግሥት ትብብር በየቦታው መፈጠር አለበት ።

ሴቶች የቤተሰብ ኃላፊነት ተግባራቸውን እንዲወጡ ማስቻል

የሚስትነትና የቤተሰብ ኃላፊነት ተግባርን ከናትነት ተግባር ጋር አጣምሮ ማየት ይቻላል። እዚህ ላይ ለማንሳት የተፈለገው ሴቶች ቤተሰብን ተንከባክበው የመያዝ ሃላፊነት ቢኖርባቸውም ይህ ተግባር የነሱ ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን የወንዱም እንደሆነ ለማስገንዘብ ነው ።

የሴቶች ነፃነት ሶሻሊስት ቤተሰብን ከመመሥረት ጋር በቅርብ የተያያዘ ነው ። ይህ ዓይነቱ ቤተሰብ ደግሞ ሊኖር የሚችለው በእኩልነት ፣ በመፈቃቀድና በመተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ነው ። ይህ ከግል ሀብት መክሰምና ከአስተሳሰብም መለወጥ ጋር አብሮ የሚመጣ ሲሆን በሕግም መደገፍ ይኖርበታል ። ዛሬ ባለንበት ሁኔታ የቀ

Digitized by Google

ድሞ የፊውዳሎች ሕግ በጋብቻ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያደርግ በመሆኑ፣የጋብቻው ሁኔታ በባሪያና በባሪያ አሳዳሪ መካከል እንዳለ ግንኙነት የሚቆጠር ዓይነት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም ። ባል ሚስቱን ለመጨቆን የሚያስችለው አድኃሪ ሕጋዊ መብቱ መወገድ አለበት ። ዛሬም ባል የቤተሰብ ኃላፊ ነው የሚሉ ሕጎች መለወጥ አለባቸው ። በአሮጌው ህግ ፍቺን መወሰን የሚችለው ባል ብቻ ነው ፤ አንዲት ሴት ባል ሳታገባ ልጅ ብትወልድ በአያሌ የኅብረተሰባችን ክፍሎች የተጠላች ወይም የተናቀች ትሆናለች ። አንዳንዴም በዚህ ዓይነት ሕፃናትን ያፈሩ ሴቶች ኢሰብአዊ ድርጊት ይፈጸምባቸዋል ፣ . . . ብዙ መዘርዘር ይቻላል ። እነዚህ ሁኔታዎች የቤተሰብ ሕግ በአስቸኳይ እንዲወጣና ከሌሎች ሕጎች ጋር ተገናዝቦ በተግባር እንዲተረጐም ለማድረግ የተጀመረውን ጥረት በቶሎ ተግባራዊ እንድናደርግ የሚገፋፉን ነው።ሕጉ ከወጣ በኋላም ለተግባራዊነቱ ከኢኢሴማ ፣ ከሌሎች ሕዝባዊ ድርጅቶችና ከመንግሥት ጭምር ከፍተኛ ጥረትን ይጠይቃል ። ይህ ከሆነ አሁን የሚታየውን ችግር ደረጃ በደረጃ እየፈታው ለመሄዱ እርግጠኞች መሆን እንችላለን ።

ሴቶች የሠራተኛነት መብታቸውንና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማገዝ

ሴቶች መሥራት የሚፈልጉት ወይም መሥራት የሚያስፈልጋቸው ገንዘብ ለማግኘት ወይም ለደመወዝ ብቻ ሳይሆን፣የኅብረተሰቡ ጠቃሚ አካል አድርገው ራሳቸውን እንዲቆጥሩ ስለሚያስችላቸው ፣ የአመለካከትና አስተሳሰብ አድማሳቸውን ከፍ ለማድረግ ስለሚረዳቸው ነው ።

በተለምዶ የሴቶች የሥራ መስክ ተብለው በሚታወቁት ጠባብ መስኮች ለመሠማራት የተገደዱት ጥቂት ሴቶች ችሎታውና እውቀቱ ሳይኖራቸው ቀርቶ ሳይሆን ፣ ሴቶችን ዝቅ አድርጐ የመመልከት የኅብረተሰብ ግፊት ስለነበረ ነው ። ከዚህ የችግር ማጥ ውስጥ ሴቶች እንዲወጡና በተለያዩ መስኮች ተሰማርተው አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ለማስቻል በተለይ በመንግሥት በኩል ብዙ ጥረት ያስፈልጋል ። በትምህርት ራሳቸውን እንዲያሻሽሉ የተለያዩ ኮርሶችን ለሴቶች በማዘጋጀት ፣ በየትምህርትና በየማሰልጠኛ መስክ የሴቶች ኮታ በመያዝ ፣ እንዲገቡም በመገፋፋትና በማበረታታት ጥቂት ሴቶችን ለማሳመንና ለማውጣት ከተቻለ እነሱን በምሣሌነት በማየት የሌሎች ሴቶች ቁጥር በፍጥነት እየተበራከተ ይሄዳል ። ይህ አሠራር በአብዮታቸው የመጀመሪያ ዓመታት ውስጥ በሶሻሊስት አገሮች የተሞከረና ብዙ ውጤትም ያስገኘ ነው ።

ሴቶች በተለያዩ የሥራ መስኮች በሚሳተፉበት ጊዜ የሚወሰድ ጥንቃቄ አለ ። ይኸውም የሚሠሩት ሥራ ከሴትነታቸው ጋር የማይፃረር የእናትነት ግዴታቸውን የማያስናክል ፣ ጤንነታቸውን የማይጐዳና አቅማቸውን የሚገምት መሆኑን ማረጋገጥ ነው ። ሌኒን እንዳለው ፣ «... ሴቶች ከወንዶች እኩል ናቸው ማለት ሴቶችን በማምረት ሂደት በሚሠሩበት ሥራ መጠን ፣ ሥራው በሚወስደው ጊዜ በሥራ ሁኔታዎች ወዘተ ... ሁሉ ከወንዶች ጋር እኩል ይሰለፉ ማለት አይደለም ።» [7] ሌኒን በተለመው መሠረት የሶቭየት ሕግ ሴቶች በመሬት ከርስ ውስጥ በሚከናወኑ ሥራዎች ፣ በኬሚካል ኢንዱስትሪዎችና በመሳሰሉት በከባድና ለጤና ተስማሚ ባልሆኑ ሥራዎች እንዳይሳተፉ ያግዳል ።

በአብዮታዊት ኢትዮጵያ በፋብሪካ ውስጥ የሚሠሩ ሴቶች ከአቅማቸው በላይ በሆኑ በከባድ ማሺኖች ላይ እንዳይሠሩ ፣ በእርግዝና ወራት ከከባድ ሥራ ወደቀላል ሥራ እንዲዛወሩ ፣ ከወሊድ በፊትና ከወለዱም በኋላ በቂ የወሊድ እረፍት እንዲያገኙ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ አሁን የተጀመረው ጥረት በተጠናከረና በተሻሻለ ሁኔታ መቀጠል

Digitized by Google

አለበት ። በሕግ ላይ የሚሰፍሩ ጉዳዮች ተገባራዊ ለመሆናቸው በቅርብ የሚከታተሉ የሠራተኛ ሴቶች ኮሚቴዎች በየሥራ መስኩ መቋቋማቸው ብዙ አስተዋጽኦ አለው ። ከዚህም በቀር ሴቶች በተሰማሩበት የሥራ መስክ ትጉህ ሠራተኛ እንዲሆኑ በጥራትና በብዛት እንዲያመርቱ ርስ በርሳቸው እንዲወዳደሩ ማድረግ የሠራተኛ ሴቶች ኮሚቴ ከሌሎች አብዮታዊ ተቋሞች ጋር በመተባበር ሊያከናውኑት የሚገባ ተግባር ነው ።

ካርል ማርክስ ካፒታል በተሰኘው ዝነኛ መጽሐፉ ውስጥ «ሴቶችን በሥራ ማሰማራት (መቅጠር) ለከፍተኛ የቤተሰብ ዓይነትና በጾታዎች መካከል ለሚኖረው ግንኙነት አዲስ የኤኮኖሚ መሠረት ይፈጥራል !» እንዳለው ይህ ሁኔታ ፣ በሀገራችን ተገባራዊ እንዲሆን ከመንግሥትና ከማኅበሩ ከፍተኛ ጥረት ይጠበቃል ።

ሴቶች በኅብረተሰቡ ውስጥ የዜግነት መብታቸው በእኩልነት ላይ መመሥረት አለበት ፤

«እኔ እንደሚገባኝ ለጥያቄው (ለሴቶች ጥያቄ) ፍጹማዊ ምላሽ መስጠት ማለት በሕግ ፊት ሴቶችንና ወንዶችን እኩል ማድረግ ብቻ ሳይሆን ፣ ... ኤኮኖሚያዊና ቁሳዊ ነፃነታቸውን አእምሮአዊ ዕድገታቸውን ጭምር መለወጥን ይጠይቃል»[8] ሲል አገስት ቤበል ከዛሬ105 ዓመት በፊት የጻፈው ዛሬም ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባ እውነት ነው። ሴቶችን በሕግ ፊት እኩል ማድረግ ብቻ በቂ አይደለም ። ቁም ነገሩ ሕጉ በተግባር ተተርጉሞ የኅብረተሰቡን ሕይወት ሊለውጥ ሲችል ነው ። የሴቶች የአገሪቱ ዜጋ መሆን በስሜት ዝም ብሎ የሚታወቅ ወይም ግልጽ የሆነ ነገር ቢመስልም ኅብረተሰቡ በሴቶች ላይ ያለው ዝቅተኛ አመለካከት እስካልተለወጠ ድረስና ተገቢውን ክብር እስካልሰጣቸው ድረስ እንደ ሁለተኛ ደረጃ ዜጋ መቆጠራቸው አልቀረም ። ይህን ሁኔታ ለመለወጥ ጊዜ መውሰዱ ባይካድም ሴቶች በተለያዩ የሥራ መስኮች ሲሳተፉ ፣ ውጤታማ ሥራ እያከናወኑ ሲታዩ በዚህ ሂደት ውስጥ የኅብረተሰቡ አስተሳሰብም እየተቀየረ ይሄዳል ።

ሴቶች በሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ በአባልነትም ሆነ በአመራር የሚያደርጉት ተሳትፎ በየጊዜው እያደገ መምጣቱን ቀደም ሲል ተመልክተናል ። በዚህ ሳይወሰኑ በመንግሥት ተቋሞችና በማምረቻ ድርጅቶችም ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ ይበልጥ መጠናከር አለበት ። ሌኒን ሲጽፍ ሴቶች «በአስተዳደር ሥራውስጥ መሳተፋቸው ፈጥነው እንዲማሩ፣ ከወንዶችም እኩል እንዲሆኑ ያስችላቸዋል ። ስለዚህ ኮሚኒስት የሆኑትንም የፓርቲ አካል ያልሆኑትንም ብዙ ሴት ሠራተኞች ለሶቬየት አባልነት ምረጡ» በማለት መመሪያ መስጠቱ ሴቶችን በአመራር ላይ እንዲቀመጡ የማድረግን አስፈላጊነት ለማጠናከር ነው። ሴቶች ከአስተዳደጋቸው አንስቶ ኃላፊነት የመቀበል ልምድ ያላቸውና የተሰጣቸውንም ኃላፊነት ለመወጣት በብዙ ጥረት የሚያደርጉ በመሆናቸው ብዙ ውጤታማ ሥራ ሊያከናውኑ ይችላሉ ። ብዙ ሴቶችን ከያሉበት በማምረቻ ተቋሞች በመንግሥትና በሕዝባዊ ተቋሞች ውስጥ በኃላፊነት ቦታ ላይ ለመመደብ ሙከራ ማድረግና በዚሁ አኳያ ሌሎችንም እያዘጋጁ መሄድ ዛሬ ከኢሠፓአኮ ነገም ከሚመሠረተው ፓርቲያችንና ከአብዮታዊ መንግሥት ይበልጥ በተጠናከረ መልክ የሚጠበቅ ተግባር ነው ።

ሌሎች ተግባሮች

አኢሴማ በሴቶች ይበልጥ ተሰሚነት ለማግኘት የሚያስችሉ ሥራዎች ማከናወን አለበት። በተለያዩ ደረጃ ላይ የሚገኙትን ሴቶች እንደጠባያቸው ፣ እንደፍላጐታቸው ለማቅረብና ለማኅበሩ የሚጠቀሙበትን እነሱም ከማኅበሩ የሚጠቀሙበትን ስልት መቀየስ አለበት ።

Digitized by Google

ማኅበሩ ሥራ አጥነትን ለመቀነስ በተለይም ሴተኛ አዳሪነትን ለማጥፋት ከሚመለከታቸው መንግሥት መ/ቤቶችና ተቋሞች ጋር በመተባበር ፣ አብሮ በማቀድ ጭምር በማኅበራዊ ምርትና እንቅስቃሴ ውስጥ በንቃት የሚሳተፉበት ዘዴ መቀየስ አለበት። የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ትላልቅ ተቋሞችን በየቦታው በማቋቋም የሴቶችን ሙያ ለማዳበር ከዚህ ጐን የማኅበሩን የገቢ መጠን ለማሳደግ ፣ በዚህም ሂደት የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች ለማስወገድ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅበታል ።

ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ፣ ሕዝባዊ ድርጅቶች ጋር ትብብር በመጠየቅ የሕፃናት መዋያዎች የሚያስፋፉበትን ፣ ሰፋፊ የባልትና የኅብረት ሱቆች የሚቋቋሙበትን ፣ መመገቢያ ሥፍራዎችና መዝናኛዎች የሚስፋፉበትን ፣ ባጠቃላይ የሴቶች የሥራ ሸክም የሚያቃልልበትንና አምራች ዜጋ ሊሆኑ የሚችሉበትን መንገድ ሁሉ በእቅድ ይዞ ደረጃ በደረጃ ለማከናወን የማኅበሩ መዋቅር አመች ነው ።

እናት አገርንና አብዮትን መንከባከብ ደግሞ ከሁሉ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ በመሆኑ አኢሴማ አባላቱን ለዚህ ክቡር ዓላማ ለማሰለፍ በሚሰጠው መመሪያ ሁሉ በላቀ ሁኔታ ለማሳተፍና ለማዘጋጀት መቻል አለበት ። የዘማች ቤተሰቦችን በመንከባከብና በፕሮግራም ቋሚ የሆነ ድጋፍ በማድረግ የጀመረውን ሥራ በይበልጥ ማጠናከር ያስፈልጋል ።

እስከሁን ድረስ ለመዘርዘር የተሞከሩትን እንቅስቃሴዎች በመምራትና በማስተባበር በኩል በቅርቡ ሕልውናውን ከሚያገኘው ግምባር ቀደም ፓርቲያችን ብዙ ይጠበቃል ። በዚህ መስክ ከተቀዳሚ ተግባሮቹ መካከል ሴት ካድሬዎችን በብዛት ማፍራት አንዱ ነው ። በኢሠፓአኮ ማ/ኮሚቴ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ሴቶችን በሚመለከት ከተላለፉት ውሳኔዎች አንዱ ፣ «የሴቶችን የተለያዩ ችግሮች ለመፍታት የተደራጀ ተሳትፎአቸውን ለማጠናከር በአጭር ጊዜ ውስጥ የሴት ካድሬዎች በብዛት በማሰልጠንና በማሰማራት የሴቶችን ሁኔታ ለማሻሻል የሚደረገውን ጥረት ይበልጥ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል የሴት ካድሬዎች የሚሰለጥኑበት አመች ሁኔታ እንዲፈጠር ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ ጥረት እንዲያደርጉ [10] » የሚል ነው ። ከሕዝቡ ውስጥ ወጥተው ወደ ሕዝቡ የሚመለሱ ካድሬዎችን በብዛት ማፍራት የምንሰራውን ሥራ ባፋጣኝ ተግባራዊ ለማድረግ ዓይነተኛ ዘዴ ነው ።

ሴቶችን ለማሰባሰብ የተቀነባበረ የርዕዮተዓለምና የፕሮፖጋንዳ ሥራ ማካሄድና ንቃተ ኅሊናቸውንና የኑሮ ሁኔታቸውን የሚመጥንና የሚስማማ የፕሮፖጋንዳ ሥራ መቀየስ ለነገ ፡ ማይባል ተግባር ነው ። በራሳቸው አካባቢ ቻ ሳይቀር ሴላውንም ኅብረተሰብ ለመሳብ ለማሰባሰብ ሴቶች ከፍተኛ ኃይልና ችሎታ አላቸው ። በዚህ አንፃር ጥረቱ ጥቂት ሴ ፣ ችን ሳይሆን ብዙሀንን በፖለቲካ ውስጥ እ ዲሳተፉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ሊሆን ይገባል ። «የፓርቲ አባላት ያልሆኑትንና የፖለቲካ ንቃታቸው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሴት ሠራተኞችን (በፖለቲካ ውስጥ) እንዲሳተፉ ማድረግ ያስፈልጋል ። እንደዚህ ሲሆን የሶቭየት ኃይል ለሠራተኛ ሴቶች የነቃ ተሳትፎ ስፊ መስክ ይከፍታል ፣ » [11] በማለት ሌኒን ሴቶችን በፖለቲካ ውስጥ ማሳተፍ አማራጭ የሌለው መሆኑን ገልጿል ።

የሚመሠረተው ግንባር ቀደም ፓርቲያችን የሴቶች ጥያቄ ትክክለኛ ምላሽ እንዲያገኝ በሚያደርገው ጥረት ፣ መንግሥታዊ ድርጅቶች፣ ሌሎች ሕዝባዊ ድርጅቶችና ኅብረተሰቡ በአጠቃላይ ለጥያቄው ትክክለኛ ግንዛቤ አግኝተው ፣ በተቀነባበረ መልክ ተግባራዊ ሥራ እንዲሰሩ ሁሉም ኃላፊነት

Digitized by Google

ያለባቸው መሆኑን በተደጋጋሚ በማስረዳት ፣ ግልጽም በማድረግ ፣ የሴቶች ችግር የሚፈታው በኅብረተሰቡ ሙሉ ተሳትፎ መሆኑን ማስጨበጥ አንዱ ተግባሩ ነው ።

ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም ባንድ ወቅት ሲናገሩ ፣ « ... ለሠርቶ አደሩ የዘለቄታ ነፃነት መታገል ለሴቶች ነፃነት መታገልን የግድ የሚያጠቃልል ነውና የሴቶችን ጥያቄ ችል ብሎ ለአብዮቱ ጉዳዮች ቆሚያለሁ ማለት የአብዮቱን ተልዕኮ በሚገባ አለመገንዘብ ነው ። በዚህ በኩል አብዮቱ የጣለብንን ኃላፊነት ለመወጣት መሠረታዊው ምላሽ የሴቶች በኢኮኖሚው ውስጥ በስፋት መሳተፍ እንደመሆኑ ፣ እድገታችንን ለማፋጠንና የሥራ መስካችንን ለማስፋፋት ፣ ከመንግሥትና ከመላው ሰፊ ሕዝብ ያልተቋጠበ ጥረት ይጠይቃል »[12] ያሉት ለአብዮታውያን ሁሉ ቋሚ መመሪያችን ሊሆን ይገባል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 30 (Mocow: Progress Publishers, 1965) p. 43.
2. ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም በኢሠፓኮ አንደኛ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ያደረጉት የመክፈቻ ንግግር ፣ ነሐሴ 1972
3. Le Duan, *Selected Writings* (Foreign Languages Publishing House: Hanoi, 1977), p. 376.
4. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 28, (Moscow: Progress Publishers, 1965) p. 181
5. አዲስ ሕይወት ፣ (ኢሴማ) ማ/ኮ ጽ/ቤት ቅጽ 2 ፣ ቁ. 5 ፣ ገጽ 24
6. ሴቶች በየሥርዓቱ ማኅበሩ ፣ አዲስ አበባ (ኩራዝ አሳታሚዎች ትርጉም ፣ 1973 ገጽ 89
7. V.I. Lenin, *On The Emancipation of Women* (Moscow: Progress Publishers, 1977), p. 71.
8. August Babel, *Women and Socialism*, (London: International Library of Social Sciences, 1885), Vol., 1, pp. 4-5
9. ሴቶች በየሥርዓቱ ማኅበሩ ፣ ገጽ 98
10. የኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች ፣ የካቲት 1975
11. V.I. Lenin, *Collected Works*, Vol. 30, (Moscow: Progress Publishers, 1965), p. 44.
12. ጓድ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም በኢሠፓኮ አንደኛ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ያደረጉት የመክፈቻ ንግግር ፣ ነሐሴ 1972 ፣ አዲስ አበባ

Digitized by Google

የዘመኑ ዓለምአቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች

ገርማቸው መኮንን

በኅብረተሰብ ሳይንስ መንግሥትና ሕግ
የታሪክ ክስተቶች መሆናቸው የተረጋገጠ
ሲሆን፣የቡርዧ ምሁራን እንደሚሉት አመ
ጣጣቸውም እንዱ ቀደሞ የመጣና ሌላ
ውን የፈጠረው ሳይሆን ፤ ተያይዘውና ተወ
ሳስበው ከግል ሀብትና ከኅብረተሰብ በመ
ደብ መከፋፈል ጋር ብቅ ያሉ ናቸው ። ኅብ
ረተሰብ ከአንድ ሥርዓተ ማኅበር ወደሌላ
ሥርዓተ ማኅበር እያደገ ሲሄድ ፤ የመንግሥ
ሥትና የሕግ ቅርጽ እየተለዋወጠ ፤ ይዘታ
ቸውና ተግባራቸውም ከእያንዳንዱ የገዥ
መደብ ፍላጐት አንፃር ሲዋቀርና ሲቀረጽ
ቆይቷል ። የዓሊም አቀፍ ሕግም አመጣጥና
ዕድገት ከኅብረተሰብ ዕድገት በተለይም
ከመንግሥታት ብቅ ብቅ ማለት ጋር የተያ
ያዘ ሆና ይገኛል ። በነባራዊና ማኅበራዊ
ሁኔታዎች አስገዳጅነት በመንግሥታት
መካከል የኢኮኖሚ ፤ የባህልና የሌሎችም
ግንኙነቶች መፈጠርና እየዳበሩ መሄድ፣በመ
ካከላቸው የተዘረጉትና እየተስፋፉ የመጡ
ትን እነኝህን ግንኙነቶች የሚገዛ ዓሊም
አቀፍ ሕግን አስፈላጊ ሊያደርገው ችሏል ።

መንግሥታት የሚቀይሷቸው የውጭ
ፖሊሲዎች የውጭ ግንኙነታቸውን የሚ
መሩ የመሆናቸውን ያህል እነኝህ ፖሊሲ
ዎች በዓሊም አቀፍ ሕግ ክልል ውስጥ የሚን
ቀሳቀሱ ፤ ከዓሊም አቀፍ ሕግ ጋር የጠበቀ
ግንኙነት ያላቸውና በመጨረሻም በነሂሁ
ዓሊም አቀፍ ሕግ የሚወሰኑና የሚገዙ
ናቸው ።

ዓለም አቀፍ ሕግ እንደማናቸውም ማኅ
በራዊ ክስተት ከኅብረተሰብ ዕድገት ጋር
ቅርጹና ይዘቱን እንደሚያገለግለው መደብ
እየለወጠ መጥቷል ። ለምሳሌ ፤ ጥንታዊ
ሮማና ግሪክ ዓሊም አቀፍ ግንኙነታቸውን
የሚመሩባቸው ፖሊሲዎች እንደነበሯቸው
የታወቀ ሲሆን ፤ ዓላማቸው የባሪያ አሳዳሪ
ዎችን ጥቅም ማስጠበቅና መንከባከብ
ነበር ። በአጠቃላይ በጊዜው የነበረው የእነ
ዚህን ባሪያ አሳዳሪ መንግሥታት ግንኙነት

Digitized by Google

ይገዛ የነበረው ዓለም አቀፍ ሕግ የገዥ መደቦችን ጥቅም የሚያስጠብቅና በይዘቱና በቅርጹ የእነሱን የበላይነት ከማንጸባረቅ የሚያልፍ አልነበረም ።

በፊውዳሊዝም ፣ በተለይም በክርስቲያን አውሮፓ ሃይማኖት የበላይነትን የያዘው መደብ ርዕዮተዓለም መሠረት ሲሆን ፣ በኅብረተሰቡ ባህላዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ስነልቡናዊ ወዘተ . . .እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ነበረው ። መካከለኛው ዘመን እየተባለ በሚጠራው ፊውዳሊዝም በሰፈነበት ወቅት የክርስትና ሃይማኖት በአውሮፓ ልዩ ልዩ መንግሥታት መካከል የነበረውን ግንኙነት በበላይነት በመምራት በነበረው ዓለም አቀፍ ሕግ ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ ያደርግ ነበር። ስለሆነም የሮማው ጳጳስ ራሱን እንደእግዚአብሔር እንደራሴ በመቁጠር የፊውዳል የገዥ መደቦችን ጥቅም በበላይነት ያስከብርና ይንከባከብ ነበር ።

የፈረንሳይ የቡርዧው አብዮት በ18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ገደማ ፊውዳሊዝምን ከደመሰሰና የቡርዧውን የበላይነት ከመሠረተ ወዲህ በቡርዧ ዓለም አቀፍ ግንኙነት ውስጥ « የሥልጣኔ መንግሥታት እኩልነትና ነፃነት ፣ በሌላው መንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት ፣ ወዘተ. . . » የሚሉ መሠረታዊ የዓለም አቀፍ ሕግ መርሆዎች ብቅ ማለት ጀመሩ ። በዘመነ ካፒታሊዝም የተከሰተው የዓለም አቀፍ ሕግ የቡርዧውን መደብ ጥቅም በማስጠበቅና በመከላከል ረገድ ግልጥ ያለ አቋም ያዘ ። የዚህ ሕግ ተፈጻሚነትና ተግባራዊነት « በሠለጠኑ » መንግሥታት መካከል ብቻ ሲሆን፣ በአጠቃላይ ሕጉ በወቅቱ የነበሩትን የትላልቅ የብሔራዊ ቡርዧዎች መብትና ጥቅም የሚያስከብር ነበር ። በሌላ በኩል ግን አብዛኛውቹ የእስያ ፣ የላቲን አሜሪካና የአፍሪካ አገሮች « አረመኔዎች ፣ ያልሠለጠኑ ፣ ወዘተ » በመባል ለቅኝ ግዛትነት ተዳርገዋል ።

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም የሰው ልጅ የአመለካከት አድማስን በማስፋት አዳዲስ አመለካከትና አስተሳሰብ እንዲቀረጽ ሳይንሳዊ መንገድ በመክፈቱ የቡርዧ ምሁራንን ሃሳባዊ የሆነ የሕግ ፍልስፍናን ኢሳይንሳዊነት በማጋለጥ የሕግን አመጣጥና የዕድገት እቅጣጫ በትክክል ሊያመለክት ችሏል ። ማርክሲዝም ሌኒኒዝም በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ የነበረውንና ያለውን ዓለም አቀፍ ሕግ መደባዊና ማኅበራዊ ይዘት በሚገባ በመተንተን ምንጩን፣ መሠረቱን ፣ አገልግሎቱን ፣ ተግባሩን ፣ ወዘተ... ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ አብራርቷል ። የካፒታሊዝምን ጠፊነት በቦታውም የሶሻሊዝምን ተተኪነትና ሕልውና ያረጋገጠ ታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት ዓለም አቀፍ ሕግን በሚመለከት አዳዲስ ጽንሰ ሃሳቦችን በማፍለቅ በሕዝቦችና በመንግሥታት መካከል ዲሞክራሲ ፣ እኩልነት ፣ ፍትሕ ፣ ነፃነት ፣ ወዘተ እንዲሰፍን ያደረገው አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ።

የታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት በሕዝብና በመንግሥታት መካከል ያለውን ግንኙነት በኃይል እንፃር የሚመለከተውንና ጦርነትን የማስፋፋት አዝማሚያ ያለውን በካፒታሊዝም የተቀረጸውን ዓለም አቀፍ ሕግ መሠረታዊ በሆነ መንገድ በመለወጥ የተለያዩ የፖለቲካና የማኅበራዊ ሥርዓቶችን በሚከተሉ መንግሥታትና ሕዝቦች መካከል ፣ በሰላም አብሮ በመኖር መርህ ለመተካት ያደረገው ትግል ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው ። እንዲሁም ለአዲሱ ዓለም አቀፍ ግንኙነት መሠረት ሊሆኑ የሚችሉ አዳዲስ መርሆዎችን የሶቭዬት መንግሥት በጥቅምት 26 ቀን 1917* በሰላሙ አዋጁ ከማውጣቱም በተጨማሪ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በሕዝቦችና በመንግሥታት መካከል በኢምፔሪያሊስቶች ሳቢያ በየአካባቢው የሚካሄደው ጦርነት አክትሞ ፣ ሕዝቦች ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ወደ ሆነው ዓለም አቀፍ ሥር

* በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተመለከቱት የዘመን አቆጣጠሮች እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ናቸው ።

Digitized by Google

ዓት ለመሸጋገር ይችሉ ዘንድ ለዓለም ተራ ማጅ ኃይሎች ጥሪ አቅርቧል ። በተጨማ ሪም በሶሻሊዝም ጉራ መጠናከር በመንግ ሥታት መካከል ለሚፈጠረው ዓለም አቀፍ ግንኙነትና ለዓለም ሰላም ማስከበሪያ የሚ ያገለግሉ መርሆዎች ፈልቀዋል ፤ እየፈለ ቁም ነው ።

1. የዓለምአቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርሆች ልዩ ባሕርይና አቀራረብ

የመሠረታዊ መርሆዎች ልዩ ባሕርይ

መሠረታዊ የዓለም አቀፍ ሕግ መርሆ ዎች የሚባሉት በመሠረቱ በመንግሥታት መካከል የሚፈጠሩትን ግንኙነቶች ለመ ምራት ሁለንተናዊና አጠቃላይ ተቀባይነት ያገኙ ግዕዛን (Norms) ናቸው ። እነ ዚህ መርሆዎች ከሌሎች የዓለም አቀፍ ሕግ ዘርፎች ግዕዛን ተለይተው የሚታወቁና ለዓ ለም አቀፍ ሕግም እንደ አስኳል ወይም እንደመሠረት የሚገለግሉ ናቸው ። ሌሎች የዓለም አቀፍ ሕግ ዘርፎች ከመሠረታዊ መርሆዎች ጋር ራሳቸውን ማጣጣም ይኖ ርባቸዋል ፤ ይህንን ካላደረጉ በአብዛኞቹ መንግሥታት ዘንድ ተቀባይነት አይኖራቸ ውም ። በሌላ አነጋገር የዓለም አቀፍ ሕግ ልዩ ልዩ ሕጐችና ደንቦች እነዚህን መሠረ ታዊ መርሆዎች የሚፃረሩ ከሆነ ሁለንተ ናዊ ተቀባይነት አይኖራቸውም ። ለምሳሌ የመንግሥታትን ሕጋዊ እኩልነት መርህ የማይቀበል መንግሥት ከሌሎች ጋር ፋይዳ (ረብ) ያለው ግንኙነት ሊፈጥር አይችልም ። ባብዛኛው የዘመኑ የዓለም አቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች በባሪያ አሳዳሪና በፊ ውዳል ሥርዓቶች ዘንድ አይታወቁም ነበር፤ ሊከሰቱና ሊስፋፉ የቻሉት በቡርዧው ሥርዓትና በኋላም በሶሻሊዝም ነው ። የቡ ርዧው አብዮት የእኩልነትና የነፃነትን አርማ አንግቦ በተነሳበት ጊዜ በዓለም አቀፍ ግንኙነት መስክ የሚከተሉትን መር ሆዎች ማስተጋባት ጀምሮ እንደነበር ይታ ወሳል ።

—የመንግሥታት ሕጋዊ (በሕግ ፊት) እኩልነት ፤

—የአንድ ሀገር ልዕልና (ሥልጣነ መን ግሥት) አለመገሰስ ፤

—በሀገሮች (መንግሥታት) የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት ፤

እነዚህ መርሆዎች « የሠለጠኑ » የመባል ስያሜ ያገኙትን የቡርዧ መንግሥታትን ግንኙነት የሚመለከቱ እንጂ ሌሎችን በተ ለይም ከአውሮፓና አሜሪካ ውጭ የነበሩ ትን ሕዝቦችና መንግሥታት የሚመለከቱ አልነበሩም ። በእስያ በአፍሪካና በላቲን አሜሪካ የሚገኙት መንግሥታት « ያልሠ ለጠኑ» ፤ አረመኔ የሚል ቅጽል ተሰጥቷቸ ው ስለነበር በእነዚህ መርሆች አልተሸፈ ኑም ።

በዛሬው ጊዜ ታላቁ የሩስያ የጥቅምት ሶሺያሊስት አብዮት በቀደደው ፈር የሶሻ ሊስት አገሮች ፤ ተራማጅ መንግሥታትና ሰላም ወዳድ ሕዝቦች በአደረጉት መራራ ትግል ለሁለቱ የተለያዩ ሥርዓቶች (ሶሻ ሊዝምና ካፒታሊዝም) የጋራ የሆኑ አዳ ዲስ የዘመኑ ዓለም አቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች ሁለንተናዊ ተቀባይነት እን ዲያገኙ ተደርጓል ።

—በሰላም አብሮ መኖር ፤

—ግጭቶችንና አለመግባባቶችን በሰላ ማዊ መንገድ መፍታት ፤

—የሕዝቦችን የራስን ዕድል በራስ መወ ሰንና የሰብአዊ መብቶች መከበር ፤

እነዚህ ቀደም ብለው በተቀረጹት የቡር ዧው የዓለም አቀፍ ሕግ መርሆች ላይ በመ ጨመር የዘመኑን የዓለም አቀፍ ሕግ አድ ሰውና አጠናክረው ይገኛሉ ። የሶሻ ሊስትና ተራማጅ ኃይሎች አስተዋጽኦ የሆኑ አዲስ መርሆች በዲሞክራሲያዊ መን ፈሳቸው በፀረ ጦረኝነትና ለሰላም ባላ ቸው አቋም በቡርዧው ሥርዓት የተከሰ

Digitized by Google

ቱትን መርሆች ይዘት አሻሽለውና ለውጠው ይገኛሉ ።

በዓለም አቀፍ ሕግ የዕድገት ሂደት የመሠረታዊ መርሆች ጠቀሜታና ተቀባይነት በየጊዜው እያደገና እየዳበረ መጥቷል ። የመሠረታዊ መርሆች እየዳበሩና እየተጠናከሩ መምጣት ለብሔራዊ ነፃነት ፥ ለዲሞክራሲ ፥ ለፍትህ ፥ ለእኩልነትና ለሶሻሊዝም በቀላሉ የማይገመት አስተዋጽኦ አድርጓል። የዘመኑ ዓለም አቀፍ ሕግ ለብሔራዊ ነፃነት ንቅናቄዎች ፥ ቅኝ አገዛዝን ፥ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን ፥ ኢምፔሪያሊዝምን ለሚዋጉ ሕዝቦች ሕጋዊ ድጋፍ ከመስጠቱም በላይ ትግላቸው ትክክለኛ መሆኑንም የሚያረጋግጥላቸው ዓይነተኛ. መሣሪያ ሆኗል ። በሌላ በኩል የእነዚህ መንግሥታትና ሕዝቦች ትግል መሠረታዊ መርሆች በማስፋፋትና በማጠናከር በኩል ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ። ይህንን በማስመልከት ?ታወቁት የሶቭዬት ኅብረት የዓለም አቀፍ ሕግ ተመራማሪ ዲ· ቪ· ሌቪን በትክክል እንዳስቀመጡት « የሰላም ወዳድና የዲሞክራቲክ ኃይሎች ለሰላምና ለነፃነት የሚያደርጉት ትግል ዓለም አቀፍ ሕግን ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዲሸጋገርና ልዩ ልዩ አሳሳቢ ጉዳዮችን ከመሠረታዊ መርሆች አንፃር መመርመር እንዲቻል አድርጓል ።»[1]

የመሠረታዊ መርሆች አቀማመጥና አቀራረብ ፡

የዓለም አቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርሆች በልዩ ልዩ ሰነዶች አማካይነት ተቀባይነት ማግኘታቸው ተረጋግጧል ። በሁለትና በብዙ መንግሥታት መካከል ከተከናወኑት ውሎችና ስምምነቶች ባሻገር በርካታ መግለጫዎች መኖራቸው ቢታወቅም ዋናዎቹ ማኅደሮች የሚከተሉት ናቸው፥የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር ፥ የተባበሩት መንግሥታት ጠ/ጉባኤ በ1970 ያወጣው የዓለም አቀፍ ሕግ መግለጫ ፥ የ1975 የሄልስንኪ መግለጫ ፥ (Helsinki Final Act) አብዛኞቹና ዓበይት የሆኑት የወቅታችን ዓለም አቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርሆች በእነዚህ ሠነዶች ውስጥ ተጠቃልለው ይገኛሉ ። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር ጸድቀው በሁለቱ ሠነዶች ተቀባይነታቸው የተጠናከረው ሰባቱ የዓለም አቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርሆች ከዚህ ቀጥለው የተመለከቱት ናቸው ።

—አለማስፈራራት ወይም በኃይል አለመጠቀም (በኃይል መጠቀምን ወይም ማስፈራራትን ማስወገድ) ፥

—ያለመግባባትንና ግጭትን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ፥

—በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባት ፥

—ሕጋዊ እኩልነትና የሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ መወሰን ፥

—የመንግሥታት ልዕልና አለመገሰስ ፥

—የመንግሥታት ትብብር ፥

—የቻርተሩን ግዴታ በቅን መንፈስ ተግባራዊ ማድረግ ።

ከዚህም በላይ በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ውስጥ የጸደቁትን የዓለም አቀፍ ሕግ መርሆች የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ በ1970 በአወጣው መሠረታዊ የዓለም አቀፍ ሕግ መርሆች መግለጫ ይበልጥ አጠናክሯቸዋል ። በተጨማሪም በሄልስንኪው መግለጫ ውስጥ ከላይ የተዘረዘሩት ሰባቱ መርሆች በሚገባ ዳብረው ከመውጣታቸውም በላይ ሦስት ተጨማሪ መርሆች ተቀባይነትን አግኝተዋል ። እነርሱም የግዛት አንድነት መከበር ፥ የሌላውን አገር ድንበር አለመጣስና ፥ የሰውን ልጅ ሰብአዊ መብቶች ማክበር ናቸው ።

Digitized by Google

እላይ ከተዘረዘሩት መሠረታዊ መርሆች በተጨማሪ የዘመኑ የዓለም አቀፍ ሕግ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ፣ የጋራ ጸጥታ መረጋገጥና በዓለም አቀፍ ሕግ ፊት የመንግሥታት ኃላፊነት የሚሉ መርሆዎችን ያቀፈ ነው ።

ከፍ ብለው የተመለከቱትን መሠረታዊ መርሆች ከይዘታቸው ፣ ከታሪካዊና ከፖለቲካዊ ባሕሪያቸው አኳያ ከፋፍሎ ለመተንተን ቢቻልም ፣ እዚህ ላይ ለማየት የሚሞከረው ከተግባራቸው አንፃር ነው ። የዓለም አቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርሆችን ከፋፍለን ስናጠና በሰላም አብሮ የመኖር መርህ ልዩ ቦታና ግምት ሊሰጠው እንደሚገባ ለመገንዘብ አያስቸግርም ። ይህ መርህ ሌሎች መርሆችን ሁሉ ሊያጠቃልልና ሊያቅፍ ፣ ለእነሱም ተግባራዊነት ተስማሚ ሁኔታውችን ሊፈጥር የሚችል መሆኑ በግልጽ ይታያል ። በመሆኑም ይህ መርህ የዓለምአቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርሆችን ይዘት ተግባርና የወደፊት የዕድገት አቅጣጫን ሊወስን የሚችል ነው ።

ብዙዎቹ የጊዜያችን የዓለም አቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርሆች የሚያተኩሩት በሰላም ጥበቃ ፣ ጦርነትን በማስወገድና ጠቀሜታ ባለው ትብብር ላይ እንደመሆኑ የተዛመዱና ርስበርሳቸው የሚደጋገፉ ናቸው ። ስለሆነም እንደሚከተለው አሰባስቦ በቅደም ተከተል ለመመልከት ይቻላል ።

ሀ· <u>የዓለምአቀፍን ሰላምና ጸጥታ የሚመለከትቱ መርሆች</u>

—ወረራን አለመፈጸም ፣
—በኃይል አለመጠቀም ወይም አለማስፈራራት ፣
—አለመግባባትን ፣ ግጭትን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ፣
—የጦር መሣሪያን መቀነስ ፣
—በዓለም አቀፍ ሕግ ፊት የመንግሥታት ተጠያቂ መሆን ።

ለ· <u>የመንግሥታትን ትብብር የሚያራምዱ መርሆች</u>

— የመንግሥታትን ልዕልና አለመገሰስ ፣
— የግዛት አንድነትን ማክበርና ድንበርን አለመጣስ ፣
— በአንድ አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባት ፣
— የመንግሥታት ትብብርን ማዳበር ፣
— ግዴታን በቅን መንፈስ ተግባራዊ ማድረግ ።

ሐ· <u>የብሔሮችንና የሰውን ልጅ መብቶች የሚመለከቱ መርሆች</u>

—የሕዝቦችንና የብሔሮች የራስን ዕድል የመወሰን መብት ማወቅ
—የሰው ልጅ ሰብአዊ መብቶችን ማክበር

2. ዓበይት መርሆዎች

<u>በሰላም አብሮ መኖር አጠቃላይ የሆነ የዓለም አቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርህ</u>

በሰላም አብሮ የመኖር መርህ ሁለንተናዊ ተቀባይነትን ያገኘ ከመሆኑም በላይ በዘመኑ የዓለም አቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርሆች ሥርዓት ውስጥ እንደመሠረት በመሆን የሚያገለግል ነው ። በሰላም አብሮ የመኖርን መርህ ጽንሰ ሐሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ ያብራራው ታላቁ ሌኒን ሲሆን ፣ የሶቭዬት መንግሥት በ1917 ባወጣው የሰላም መግለጫ አማካይነት ይህን መርህ በተግባር ላይ አውሎታል ።

በሰላም አብሮ የመኖር መርህ አስፈላጊ የሆነው የተለያዩ ሶስዮ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቶችን የሚከተሉ አገሮችና መንግሥታት በመኖራቸው ነው ። ካፒታሊስት በሆኑ አገሮችና በሶሻሊስት አገሮች መካከል በሰላም አብሮ መኖር አማራጭ የሌለው ጉዳይ

Digitized by Google

ነው ። ሰላማዊ በሆነ መንገድ የሰዎችን ኑሮ በማሻሻልና በማሳደግ ፣ መሠረታዊ ፍላጐቶችን በማሟላት ፣ ሳይንስንና ቴክኖሎጂን በማዳበርና ምርትን በመጠንና በብዛት እንደዚሁም በዓይነት በማሳደግ የበለጠ ተቀባይነት ለማግኘት በሚደረገው ውድድር ከሁለቱ አንደኛው ሥርዓት አሸንፎ እስኪወጣ ድረስ በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም መካከል በሰላም አብሮ ጐን ለጐን ከመኖር በስተቀር ሌላ አማራጭ የለም ።

ይሁንና ኢምፔሪያሊስት አገሮች የሶሻሊዝምን ሕልውና እንደዚሁ በቀላሉና በአንድ ጊዜ አልተቀበሉትም ። ጣልቃ ገብ ወረራውና የኢኮኖሚ ማዕቀቡ ከከሸፈባቸው በኋላ የካፒታሊስት አገሮች የሶቭየት ኅብረትን መንግሥት ነፃነትና ሕልውና አምነው በመቀበል በኢኮኖሚ ፣ በፖለቲካ ፣ በባህልና በዲፕሎማሲ መስኮች ግንኙነት ሲፈጥሩ፣ ይህ መርህ በመንግሥታት ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት በቃ ። የተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቶች በሚከተሉ አገሮች መካከል የሚደረገው ዓለም አቀፍ ግንኙነት በዚህ መርህ መመራት ጀመረ ። የፋሽዝምን ወረራ ለመቋቋምና ድል ለመምታት በሶቭየት ኅብረትና በዋናዎቹ ካፒታሊስት መንግሥታት መካከል የተደረገው ትብብርና የተፈጠረው ግንባር በሰላም አብሮ የመኖርን መርህ ይበልጥ ሊያዳብረውና ተግባራዊነቱንም ሊያጠናክረው ችሏል ።

በሰላም አብሮ የመኖር መርህ ሕጋዊ ባሕርይ ተቀባይነት እየተጠናከረና ሥር እየሰደደ የሔደው የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ከጸደቀ በኋላ ሲሆን ምንም እንኳ «በሰላም አብሮ መኖር» በሚል ሐረግ በቻርተሩ ላይ ባይቀረጽም ፣ የመርሁ ጠቅላላ መንፈስ በቻርተሩ መግቢያ አንቀጽ «መቻቻልን ተግባራዊ ለማድረግ መለማመድና ፣ በመልካም ጉርብትና በሰላም አብሮ መኖር»[2] በሚል መልክ ሰፍሯል። የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር አንቀጽ 1 በሰላም አብሮ የመኖር መርህን መንፈስ ለአባል መንግሥታት ሲያሳስብ «የዓለም አቀፍን ሰላምና ደህንነት መጠበቅ ፣ በመንግሥታት መካከል መልካም የወዳጅነት ግንኙነትን ማዳበር ፣ ዓለም አቀፍ ችግሮችን በኢኮኖሚ በማኅበራዊ ኑሮ ፣ በባህል ወዘተ ... እንጻር ለመፍታት በመንግሥታት መካከል ዓለም አቀፍ ትብብርን ማጠናከር »[3] በሚሉ ሐረጐች እንዲንጸባረቅ ተደርጓል ።

በሰላም አብሮ የመኖር መርህ በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ውስጥ በጸደቁት ዲሞክራሲያዊ መርሆዎች ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንደሚከተለው ተንጸባርቀዋል ።

— የመንግሥታት ሕጋዊ እኩልነት ፤

— የአንድ ሀገር ልዕልናና የግዛት አንድነት አለመገሰስ ወይም አለመደፈር ፣

— አለመግባባትን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ፣

— በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባት ፣

— ወረራን ያለመፈጸም ፣

— ዓለምአቀፍ ግዴታን ማክበር ።

እነዚህ የመንግሥታትን ሕጋዊ እኩልነት የሚያንጸባርቁ ዲሞክራሲያዊ መርሆዎች በሰላም አብሮ የመኖር መርህ ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው ። በተጨማሪም ይኸው መርህ «በአገሮች መካከል ሰላማዊና የመልካም ጉርብትና ግንኙነት» በሚል ስያሜ ፣ የተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ባወጣው የዓለም አቀፍ ሕግ መርሆዎች መግለጫ»[4] በቁጥር 2625 እና በ1975 የሄልስንኪው መግለጫ ላይ ተቀባይነትና ድጋፍ አግኝቷል ። እንዲሁም በሰላም አብሮ የመኖር መርህ በ1955 የተካሔደው የባንዱንግ ጉባኤ (ኮንፈረንስ) ባወጣው መግለጫና በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተር እንዲሁም በሌሎች ዓለምአቀፍና አኅጉራዊ ስምምነቶችና መግለጫዎች ላይ ሰፍሮ ይገኛል ።

በሰላም አብሮ የመኖር መርህ ፣ የዓለምን

Digitized by Google

ሰላምና ጸጥታ ለመጠበቅና ለማስከበር የሚ
ያገለግል ዓይነተኛ መሣሪያ እንደመሆኑ
በዓለምአቀፍ ግንኙነት ሊያጋጥሙ የሚች
ሉትን ማንኛውንም ችግሮች ለመከላከልና
ለማቃለል የሚያስችል ነው ። አገሮችና መ
ንግሥታት ይኸንን መርህ አጥብቀው እስከ
ተከተሉ ድረስ ግንኙነታቸው ሊሰምር ይች
ላል ፤ ሆኖም ኢምፔሪያሊስት አገሮች የሚ
መኩትና የሚመሩት በኃይል በመሆኑ ከፊ
ታቸው በተደቀነው የሶሻሊስትና የተራማ
ጅ ኃይሎች ኅብረት መርሁን በአፍ ቢቀበ
ሉትም በተግባር ግን እየጣሱት የዓለምን
ሰላም ከባድ ችግር ላይ ከመጣል አልተቆ
ጠቡም ። በአንጻሩ ተራማጅ ኃይሎችና በማ
ርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲዎች የሚመሩት
ሶሻሊስት አገሮች በፕሮግራማቸውና በጉባ
ኤዎቻቸው ውሳኔዎች ላይ ለዚህ መርህ ተገ
ዥነታቸውን ሳያረጋግጡና ለተግባራዊነ
ቱም ቃል ኪዳናቸውን ሳያድሱ ያለፉበት
ጊዜ የለም ።

የዓለምን ሰላምና ጸጥታ ለማስከበር የሚያገለግሉ መሠረታዊ መርሆች

ወረራን ያለመፈጸም መርህ

ከታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት በ
ፊት በወቅቱ በነበረው የዓለም አቀፍ ሕግ
በሌሎች አገሮች ላይ ወረራ ያለመፈጸም ወ
ይም ከወረራ የመታቀብ መርህ አይታወ
ቅም ነበር ። ወረራ የአለመፈጸም መርህ ለ
መጀመሪያ ጊዜ በሕጋዊ ሰነድነት የሰፈረው
በ1917 በሶቭየት መንግሥት የሰላም አ
ዋጅ ላይ ነበር ። የሰላም አዋጁ የወረራ ጦር
ነት በሰው ልጅ ላይ የሚቃጣ ታላቅ ወን
ጀል መሆኑን ሲያረጋግጥ ፥ በአንጻሩ ግን
የቡርዧው የዓለም አቀፍ ሕግ በመንግሥ
ታት መካከል ሊፈጠር የሚችለውን አለመ
ግባባት በጦርነት መንገድ መፍታትን አይ
ከለክልም ነበር ።

ወረራን ያለመፈጸም መርህ በዘመኑ የዓ
ለም አቀፍ ሕግ ተቀባይነት እስከአገኘ ድ
ረስ ፥ ሶሻሊስት አገሮች ሰላም ወዳድና ተራ
ማጅ ኃይሎችና መንግሥታት ከፍተኛ ትግ
ል አካሂደዋል ። ወረራ ያለመፈጸም መርህ
በዓለም አቀፍ ሕጋዊ ሰነድ እንዲታወቅ የሶ
ቭየት ኅብረት መንግሥት ከፍተኛ ጥረት
አድርጓል ። እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦር
ነት ድረስ ሶቭየት ኅብረት ወረራ ያለመፈ
ጸምን መርህ ከተለያዩ መንግሥታት ጋር
ባደረገችው ስምምነቶች ያጸደቀች ሲሆን፥
ከጦርነቱ በኋላ ይኸው መርህ በተባበሩት
መንግሥታት ቻርተር ላይ እንደ ዓለም አቀ
አቀፍ ሕግ መርህ ሆኖ እንዲጸድቅ ያላሰለሰ
ጥረት አድርጋለች ። ይህ መርህ በቻርተሩ
ውስጥ የሠፈረው በኃይል መጠቀምን ወይ
ንም ማስፈራራትን ማገድ» [5] በሚለው መ
ርህ ውስጥ ተጠቃሎ ነው ። በኃይል መጠቀ
ምን ወይንም ማስፈራራትን የማገድ መርህ
በብዙ ጥናቶች እንደተረጋገጠው ወረራን
ካለመፈጸም መርህ ጋር የተዛመደና ተመሳ
ሳይነትም ያለው ነው ። በመሆኑም በመሠረ
ቱ ሁለቱም አንድ ናቸው ለማለት ይቻላል ።
ወረራ ሲባል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አ
ንድ መንግሥት የሌላውን ነፃ መንግሥት
ድንበር መጣስ ፥ ብሔራዊ አንድነቱን መጻ
ረር ፥ በኃይል ማስፈራራትና የመሳሰሉትን
ማድረግን ያጠቃልላል ።

የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር አንቀጽ
2/4 መንግሥታት በግንኙነታቸው መታቀብ
ከአለባቸው ነገሮች ውስጥ ፥ «በዓለም አቀፍ
ግን ኙነታቸው አባል አገሮች በማንኛውም
ሀገር የግዛት አንድነትና የፖለቲካ ነፃነት ላይ
በኃይል ከመጠቀምና ከማስፈራራት ወይንም
ከተባበሩት መንግሥታት ተግባር ጋር የማ
ይጣጣሙ ሁኔታዎችን ከመፈጸም መቆጠብ
አለባቸው» [6] የሚለው ይገኝበታል ። ይህ
መርህ በ1970 በተባበሩት መንግሥታት የዓ
ለም አቀፍ ሕግ መግለጫና በ1975 የሄል
ስንኪ የአውሮፓ የጸጥታና የትብብር ስብ
ሰባ የመጨረሻ መግለጫ ላይ ሰፊ ሕጋዊ
ግንዛቤ አግኝቷል ። የ1970ው የተባበ
ሩት መንግሥታት መግለጫ እንደሚለው

Digitized by Google

«አንዳንዱ መንግሥት በኃይል ከማስፈራራት ፣ የሌላውን ሀገር ድንበር በኃይል ከመጣስ ፣ ዓለም አቀፍ አለመግባባትን ለመፍታት በኃይል አለመጠቀም » [7] በማለት ያሳስባል ።

እያንዳንዱ መንግሥት በኃይል በማስፈራራትን ወይንም በኃይል ያለመጠቀምን መርህ ተግባራዊ ለማድረግ ፣

ሀ/ ዓለምአቀፍ የድንበር መሥመር ክልሎችን ከመጣስ መቆጠብ ፤

ለ/ በተደራጀ መልክ ሕገወጥ ኃይልን ፣ የታጠቁ ወንበዴዎችን ፣ ቅጥረኛ ወታደሮችን ወዘተ . . . በሌላ አገር ግዛት አሰርጎ አለማስማራት ፣

ሐ/ በሌላው ሀገር ውስጥ ወንበዴዎችንና ሽብር ፈጣሪዎችን ከማሰልጠን ፣ ከማስረግና ከመርዳት መቆጠብ አለበት ።

እነዚህንና የመሳሰሉትን መሠረታዊ ነጥቦች መንግሥታት በዓለም አቀፍ ግንኙነታቸው ልዩ ትኩረት እንዲያደርጉባቸው የዘመኑ ዓለም አቀፍ ሕግ ያስገነዝባል ።

የ1970ው የተባበሩት መንግሥታት የዓለም አቀፍ ሕግ መግለጫ በኃይል በመጠቀም ወይንም በኃይል በማስፈራራት የአንድን ሀገር ግዛት የጦርነት አውድማ ማድረግና በጊዜያዊነት እንኳ ቢሆን መያዝ ሕገወጥ ድርጊት እንደሆነ ያስረዳል ። በመግለጫው መሠረት በኃይል መጠቀም ወይንም ማስፈራራት የወረራ ጦርነትን ሊያስከትል የሚችል ወንጀል በመሆኑ መንግሥታት በዓለም አቀፍ ሕግ ፊት ኃላፊነት እንዳለባቸው ያረጋግጣል ።

በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር የጦርነት ፕሮፓጋንዳን የሚያግድ ምንም ዓይነት አንቀጽ የለም ። ይሁን እንጂ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ በ1947 የጦርነት ፕሮፓጋንዳን የሚያግድ ወይንም ሕገወጥ ድርጊት መሆኑን የሚያረጋግጥ ውሳኔ አስተላልፏል ። ሶሻሊስት ሀገሮች ሰላምን ለመንከባከብና ለመጠበቅ የጦርነት ፕሮፓጋንዳን የሚያግድ ሕረግ በብሔራዊ ሕገ መንግሥታቸው አስፍረዋል ። በእነዚህ ሀገሮች የጦርነት ፕሮፓጋንዳ የታገደ ብቻ ሳይሆን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግም የሚያስቀጣ መሆኑን አውጀዋል።

የዓለም አቀፍን ሰላምና ጸጥታ ለመጠበቅና ለማጠናከር የመንግሥታት በዓለም አቀፍ ሕግ ፊት ተጠያቂ መሆን አስፈላጊ ነገር ነው። ይሁንና ይህ መርህ በመሠረቱና በወረቀት ላይ በመንግሥታት ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘ ቢሆንም ተግባራዊነቱ ግን አወዛጋቢና አስቸጋሪም ነው ። የመንግሥታት ልዕልና (ሥልጣነ መንግሥት) ከሕግ በላይ ነው በሚለው የቡርዣ ዘይቤና በተለይም ኢምፔሪያሊስቶች የሚመሩት በኃይል በመሆኑ ይህ መርህ ዘወትር እንደተጣሰ ነው ። ይሁንና የዓለም ሰላምና ጸጥታ ለሰው ልጅ ሕልውናና ደኅንነት መሠረታዊ ጉዳይ ስለሆነ ተራማጅ ኃይሎችና ሶሻሊስት መንግሥታት ለእነዚሁ መርሆዎች ተግባራዊነት ያላሰለሰ ትግል በማድረግ ላይ ናቸው ።

ወረራ፣የንጹሐንን ደም በከንቱ በማፍሰስና ኢሰብአዊ ድርጊት በመፈጸም የሚካሔድ ሕገወጥ ተግባር እንደመሆኑ ወራሪና ተወራሪ መንግሥትን የሚያገናዝብ ሰፊና ጥልቀት ያለው ትርጉምና እንዲሁም ትክክለኛ የሕግ ግንዛቤ እንዲሰጠው ያስፈልጋል ። በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ላይ ወረራ ፣ ወራሪና ተወራሪ ለሚሉት ቃላት ሕጋዊ ግንዛቤና ትርጉም ለመስጠት የረዥም ጊዜ ጥረት ቢደረግም ፣ በኢምፔሪያሊዝም መሰናክልነት እስከአሁን ስምምነት ላይ ለመድረስ አልተቻለም ። ሆኖም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት 29ኛ ልዩ ጠቅላላ ጉባኤ በወረራ ላይ በ1974 ውሳኔ ለማሳለፍ ችሏል ።

<u>ዓለምአቀፍ ያለመግባባትን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት መርህ</u>

መንግሥታት ርስ በርሳቸው በሚያደርጉ

Digitized by Google

ቸው ግንኙነቶች አንዱ በሌላው ኪሣራ የበለጠ ጥቅም ለማግኘት ወይም አንዱ በሌላው ላይ ተጽዕኖ በማድረግ ለራሱ ወይም ለሌሎች ሦስተኛ ወገኖች የተለያዩ ጥቅሞችን ለማስገኘት ሙከራ ሲያደርጉ በመካከላቸው አለመግባባት ወይም ግጭት ይፈጥራል ፤ አለመግባባቶች ውለው ሲያድሩ መፍትሄ ሳይገኝላቸው ሲቀርና መከረር ሲመጣ ወደ ግጭት ይደርሳሉ ። በትንሽ ወይም በቀላል ሊጀመር የሚችለው ግጭት እያደገና ሥር እየሰደደ ሲሔድ ወደ ጦርነት ሊያመራ ይችላል ። አለመግባባትና ግጭ የተያያዙ ሲሆኑ በመካከላቸው ያለው ልዩነት የመከረርና የደረጃ ልዩነት ነው ። ሁለቱም የዓለም ሰላም ጠንቅ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው ።

አለመግባባትንና ግጭትን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት መርህ ከታወቁት የዓለም አቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች አንዱ እንዲሆን ታላቋ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮትና የሶቭየት ኅብረት የውጪ ፖሊሲ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል ። ባሁኑም ወቅት ቢሆን ሶሻሊስት አገሮችና ተራማጅ መንግሥታት ዓለም አቀፍ አለመግባባቶችና ግጭቶች በኃይልና በጦርነት ሳይሆን ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲፈቱ ፣ መንግሥታት ሁሉ ይኸንን መርህ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ያላቋረጠ ትግል እያካሔዱ ነው ።

መንግሥታት የዓለምን ሰላምና ፀጥታ ላለማናጋት ዓለም አቀፍ አለመግባባትንና በመካከላቸው የሚፈጠሩ ግጭቶችን ሰላማዊ በሆነ መንገድ የመፍታት ግዴታ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር በአንቀጽ 2/3 ደንግጓል ። «የዓለም ሰላምና ፀጥታ እንዲሁም ፍትሕ አደጋ ላይ እንዳይወድቁ ለመጠበቅ አባል ሀገሮች ዓለም አቀፍ ግጭትን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ይኖርባቸዋል » ፣ በማለት ቻርተሩ ግዴታውን ቁልጭ አድርጎ አስቀምጧል ። አለመግባባትንና ግጭትን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት መርህና በኃይል አለመጠቀም ወይንም በኃይል ያለማስፈራራት መርህ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች መሆናቸው በግልጽ የሚታይ ነው ። በሰላማዊ መንገድ ዓለም አቀፍ አለመግባባትን መፍታት ማለት በኃይል አለመጠቀም ፣ አለማስፈራራት ማለት ነው ። አለመግባባቶችና ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ ከተፈቱ በኃይል መጠቀምና ማስፈራራት ሥፍራ አይኖራቸውም ።

አለመግባባትንና ግጭትን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት መርህ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር ከመጽደቁም በላይ በ1970ው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና የ1975 የሄልሲንኪው የመጨረሻው ሰነድ በተከታታይ ተጠናክሮ እናገኘዋለን ። ይሁንና መርሁን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት አሁንም ከፍተኛ መሰናክል መሆናቸው አልቀረም ፤ በአንጻሩ ግን ሶሻሊስትና ተራማጅ መንግሥታት ለመርሁ መከበርና ተግባራዊነት የሚያደርጉት ትግል እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው ።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር የዓለምን ሰላምና ፀጥታ ለመጠበቅ መንግሥታት ወረራ ከመፈጸም እንዲቆጠቡ መጠንቀቅ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፍ አለመግባባትንና ግጭትንም የዓለም አቀፍ ሕግንና ፍትህን መሠረት በማድረግ በሰላማዊ መንገድ መፍታት እንደሚገባ ያሳስባል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አንቀጽ 33 አለመግባባትን በሰላማዊ መንገድ መፍታት እንደሚያስፈልግ ገልጾ ፣ በጉዳዩ አግባብ ያላቸው ወገኖች የዓለም ሰላምና ጸጥታ ሥጋት ላይ ሳይወድቅ እንዲቀጥል ችግሩን ለመፍታት በተለያዩ ዘዴዎች መጠቀም እንደሚገባቸው ያመለክታል።እነዚህም ዘዴዎች ዲፕሎማሲያዊ ድርድር ፣ በጠረጴዛ ዙሪያ ንግግርና ሐሳብ በመለዋወጥ ፣ በሽምግልና ፣ በግልግል ፣ በዕርቅ ፣ በዳኝነት ፣ ወዘተ . . . ችግሩን ለመፍታት ጥረት

Digitized by Google

ማድረግ ናቸው ። እነዚህ ዘዴዎች ወይም መንገዶች የተወሳሰቡና ጊዜ የሚፈጁ ቢሆንም ፣ የዓለም ሰላም እንዳይናጋና ዕልቂት እንዳይከተል ለማድረግ ሌላ አማራጭ የለም ።

የጦር መሣሪያ ቅነሳ መርህ

በዓለም አቀፍ ሕግ መርሆዎች ውስጥ አዳዲስ ተራማጅ መርሆዎችን በመፍጠር የዓለም ሰላምና ፀጥታን ለመጠበቅ የሚደረገው ጥረት እንደቀጠለ ነው ። በዚህ አንፃር ለሚደረገው ጥረት የጦር መሣሪያ ቅነሳ መርህ እንደ ምሳሌ የሚጠቀስ ነው ። የጦር መሣሪያ እሽቅድምድምን መግታትና ያለውንም መቀነስ ለሰላምና ለዕድገት አስፈላጊ ነው ። አብዛኞቹ የዓለም መንግሥታት የመሣሪያ ክምችትን ፣ አዳዲስ መሣሪያዎችን በመፍጠር የሚደረገውን እሽቅድምድም ጉዳትነትና አደገኛነት ከተገነዘቡት ውለው አድረዋል ። ፍጹምና አጠቃላይ ጦር መሣሪያ ቅነሳን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረጉ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ የሶቭየት ኅብረት ኮሚኒስት ፓርቲ በፕሮግራሙ ላይ «በዓለም ኅብረተሰብ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ሥር ፍጹምና አጠቃላይ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ማድረግ ለሰላም ዋስትና ነው» [9] በማለት አረጋግጦታል ። ሶሻሊስትና ተራማጅ ሀገሮች ለጦር መሣሪያ ቅነሳ ባደረጉት ብርቱ ጥረት ይህ መርህ ተቀባይነት ለማግኘት በቅቷል ።

በዓለም መንግሥታት ማኅበር አማካኝነት በ1925 የጦር መሣሪያን ቅነሳ በሚመለከት ዓለምአቀፍ ጉባኤ ለማካሔድ ዝግጅት ተደርጐ ፣ በ1932 የመሣሪያ ቅነሳ አስፈላጊነት ጉዳይ ላይ የሚወያይ ዓለምአቀፍ ጉባኤ ተካሂዶ ነበር ። ይሁን እንጂ የኢምፔሪያሊስት ሀገሮች የመሣሪያን ብዛት መወሰን ላይ በጐ አመለካከት ሊያሳዩ ባለመቻላቸው የጉባኤው ሥራ ውጤታማ ሳይሆን ቀርቷል ። ሞኖፖሊስቶች የጦር መሣሪያን እሽቅድምድም የተመለከቱት ከትርፍ ምንጭነቱ አኳያ ብቻ ሳይሆን ፣ በራሳቸው ሀገርና በቅኝ ግዛትነት በሚያስተዳድሯቸው ሀገሮች ላይ ያላቸውን የበላይነት ካለማጣት አንጻር ጭምር ስለነበር፣ሐሳቡን ለመቀበልና ተግባራዊ ለማድረግ የተደረገውን ጥረት ሁሉ ሊያከሽፉት ችለዋል።

በዘመኑ ዓለምአቀፍ ሕግ መንግሥታት የራሳቸው የጦር ኃይል እንዳይኖራቸው የሚያግድ ድንጋጌ ሊኖር አይችልም ። የራሳቸውን ጦር ኃይሎች ማቋቋምና ማደራጀት በውስጥ ጉዳያቸው ውስጥ የሚጠቃለል ስለሆነና በልዕልናቸውም የፈለጉትን ለማድረግ የሚችሉ የበላይ የሌላቸው በመሆኑ በመሠረቱ ማንም ሊያግዳቸው ወይም ሊከለክላቸው አይችልም ። የተባበሩት መንግሥታት ቻርተርም መንግሥታት ትጥቅ እንዲፈቱ ወይንም እንዲታጠቁ የሚጠይቅ ምንም ዓይነት አንቀጽ የለውም ። ቻርተሩ ለተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የመሣሪያ ቅነሳን በሚመለከት የሰጠው ሥልጣን በአንቀጽ 11 የተመለከተው ሲሆን ፣ በዚህም ጠቅላላ ጉባኤው ዓለምአቀፍ ሰላምና ጸጥታን ከመጠበቅ አኳያ የመሣሪያ ቅነሳን የሚገዙ ሕጐችና ደንቦችን ጨምሮ የትብብር መርህ ጉዳዮችን ለማየት ይችላል ። እነዚህን መርሆዎች በማስመልከት ለአባል አገሮችም ሆነ ለጸጥታው ምክር ቤት ወይም ለሁለቱም ሐሳብ ሊያቀርብ ይችላል ። በቻርተሩ አንቀጽ 26 ይህንኑ ኃለፊነት ለጸጥታው ምክር ቤት ሰጥቷል ። «ጸጥታው ም/ቤት በቻርተሩ አንቀጽ 47 መሠረት በሚሊተሪ ባልደረቦች ኮሚቴ ረዳትነት የጦር መሣሪያን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት የሚገነባበትን ዕቅድ በተባበሩት መንግሥታት አባል ሀገሮች ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ የማድረግ ኃላፊነት አለበት » [10] በማለት ደንግጓል ።

በታኅሣሥ 14 ቀን 1946 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ «አጠቃላይ የጦር መሣሪያዎችና የጦር ኃይሎ

Digitized by Google

ችን ቁጥር በተቻለ ፍጥነት የመቀነሱን አስፈላጊነት ይገነዘባል »[11] በማለት በቻርተሩ የተሰጠውን ተግባር አስታውሷል ። በዚህ ጉዳይ ላይ ጠቅላላው ጉባኤ ካሳለፋቸው ተከታታይ ውሳኔዎች መካከል በቁጥር 808 (IX) ኅዳር 4 ቀን ፣ 1954 የተላለፈው የጦር መሣሪያ ቅነሳ ስምምነትን ይዘት «የማናቸውም የጦር ኃይሎችና መደበኛ መሣሪያዎችን መቆጣጠር ፣ መወሰንና መቀነስን ፣ እንዲሁም የኑክሊየር መሣሪያዎችን መጠቀምን ፣ ማምረትንና ለሰው ልጅ መጥፊያ የሚሆኑ ሌሎች መሣሪያዎችን ሙሉ በሙሉ ማገድና ያለውን የኑክሊየር መሣሪያ ክምችትና ኃይል ለሰላማዊ ዓላማ ማዋል »[12] የሚሉ ሃሳቦች ይገበኙታል ።

የጦር መሣሪያ ክምችት ጉዳይ በ1970 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስለዓለም አቀፍ ሕግ መርሆዎች ባወጣው መግለጫ ላይ ስፍር ባይገኝም ፣ «ሁሉም መንግሥታት በቅን መንፈስ ድርድሮችን በማከናወን በዓለምአቀፍ ቁጥጥር ሥር የሚውል አጠቃላይና ሁለንተናዊ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ስምምነት ላይ ለመድረስ ይጥራሉ ፤ »[13] በማለት ተጠቃሎና ተሰባስቦ ዓይነተኛው ፍሬሐሳብ ተቀምጧል ። የጦር መሣሪያ ቅነሳን ወታደራዊ ይዘት ብቻ መመልከት አይበቃም ። ፖለቲካዊ ፣ ኤኮኖሚያዊ ፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ይዘቱንም አብሮ መመልከት አስፈላጊ ነው ። እንዲሁም የጦር መሣሪያ ቅነሳ ዓለምአቀፋዊ ባሕርይ እንዳለው መዘንጋት የለበትም ። የጦር መሣሪያ ቅነሳን ችግር የማያዳግም መፍትሔ ለመስጠት መርሁን በዓለምአቀፉ ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች ደረጃ ተቀባይነቱ የበለጠ እንዲጠናከርና ተግባራዊ እንዲሆን የማያቋርጥ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው ።

በዚህም መሠረት ፣

1. በዓለም አቀፍ ደረጃ መንግሥታት በሙሉ የጦር መሣሪያ ቅነሳን በሚመለከት ብዙ ሀገሮችን ያቀፈ (መልቲላተራል) ስምምነት ላይ መድረስ ፣
2. ዓለም አቀፍ ስምምነት ላይ ለመድረስ ድርድር በሚካሄድበት ወቅት የአንድን መንግሥት ወይንም የተወሰኑ መንግሥታትን ብሔራዊ ጸጥታ አደጋ ላይ ከመጣል መቆጠብ ያስፈልጋል ።

የጦር መሣሪያ ቅነሳን በሚመለከት ልዩ ልዩ ኮሚሽኖችና ኮሚቴዎች ያዘጋጁዋቸው ጥናቶች በልዩ ልዩ ወቅቶች ለተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ቀርበው የተለያዩ ውሳኔዎች ተላልፈውባቸዋል ። ከነዚህም መካከል አንዱ በታኅሣሥ 29 ቀን 1959 14ኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ «ፍጹምና አጠቃላይ የጦር መሣሪያ ቅነሳ» በሚል ርእስ ያስተላለፈው ውሳኔ ይገኝበታል ። ይኸ ውሳኔ «ፍጹምና አጠቃላይ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ዓለምን ከገጠሟት ችግሮች ዋንኛው መሆኑ አጠያያቂ አይደለም »[14] በማለት በትክክል አስቀምጦታል ።

የጦር መሣሪያ ቅነሳን በሚመለከት የተባበሩት መንግሥታት የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎችን መሠረት በማድረግ በተካሔዱት ውይይቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ብዙ መንግሥታትን ያቀፉ ውሎችና ስምምነቶች ላይ ሊደርስ ተችሏል ። ከነዚህም መካከል ፣—

—በሞስኮ ከተማ በ1963 ብዙ መንግሥታትን ያቀፈ በአየር ፣ በየብስና በባሕር ውስጥ የኑክሊየር መሣርያ ሙከራ እንዳይደረግ የተደረሰው ስምምነት ፤[15]

—የኑክሊየር መሣሪያ እንዳይባዛ በ1968 በብዙ መንግሥታት መካከል የተደረገው ስምምነት ፣[16] ይገኙበታል ።

እላይ በቅደም ተከተል ያስፈርናቸው ዓለም አቀፍ ሰነዶች ሙሉ በሙሉ የመሣሪያ ቅነሳን ችግር ለመፍታት የሚያስችል ሕጋዊ ችሎታ አላቸው ለማለት ባያስደፍርም ፣ የጦር መሣሪያዎችን ቅነሳ አስፈላጊነትና የጦር መሣሪያ ክምችት ችግሮችን የሚያ

Digitized by Google

መለከቱ ናቸው ። እነዚህ ውሳኔዎች የጦር መሣሪያ ቅነሳን መርህ ከዘመኑ የዓለም አቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርሆዎች መካከል አንዱ አድርጐ ለማዳበርና ወደተግባርም ለመለወጥ በሚደረገው ጥረት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንደሚያበረክቱ አይጠረጠርም ።

የአጠቃላይ ጦር መሣሪያ ቅነሳ አካል ለሆኑት ጉልህ ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችሉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን በተከታታይ ማድረግ እጅግ በጣም አንገብጋቢ ነው ። በተለይም ከዚህ በታች በተመለከቱት መስኮች ስምምነት ላይ መድረስ ለዓለም ሰላምና ለሰው ልጅ ሕልውና ወሳኝነት ያለው ነው ።

— የኑክሊየር ፣ የፀረ-ነፍሳትና የኬሚካል መሣሪያዎችን ለምን ጊዜም የሚያግድ ስምምነት ላይ መድረስ ፣

— በኃይል ላለመጠቀም የሚያስችል ዓለም አቀፍ ስምምነት ማድረግ ፣

— ለሰው ልጅና ተፈጥሮ ማጥፊያ የሚያገለግሉ አዳዲስ ዓይነት መሣሪያዎችን ከመሥራትና ከመፈልሰፍ የሚያግድ ስምምነት ማድረግ ፣

— ኃያላን መንግሥታት በመካከለኛው አውሮፓ ያላቸውን የጦር ኃይሎች ክምችት በተከታታይ የመቀነስ ስምምነት ላይ መድረስ ፣

— በአንድ በኩል በሶቭየት ኅብረት ፣ በሌላ በኩሉ በአሜሪካ ፤ በእንግሊዝና በፈረንሣይ መካከል ስትራቴጂያዊ የጦር መሣሪያ ቅነሳን በሚመለከት እስከአሁን የተደረጉ ስምምነቶችን ተግባራዊ ማድረግና ለአዳዲስ ስምምነቶች ሁኔታዎችን ማመቻቸት ፣

በእነዚህ ነጥቦች ከስምምነት ላይ መድረስ በጣም ወሳኝነት ያለው አንገብጋቢ የዘመኑ ችግር ሆኖ ሳለ ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት አጠቃላይና ፍጹም የመሣሪያ ቅነሳ ስምምነት ላይ መድረስ ቀርቶ በተቃራኒው የጦር መሣሪያ ክምችትንና እሽቅድድምን በማባባስና በማፋፋም ላይ ይገኛሉ ። የሶሻሊስትና የተራማጅ መንግሥታትን እንዲሁም የዓለምን ሰላም ወዳድ ሕዝብ ፣ የሰላም ጥያቄ ከምንም ባለመቁጠር የጦርነትን ሥጋት በማባባስ የሰውን ዘር እጅግ አስከፊ ለሆነ ዕልቂት ለመማገድ በመቅበዝበዝ ላይ ይገኛሉ ።

መንግሥታት ሰላማዊ ትብብርን የሚያጠናክሩባቸው መሠረታዊ መርሆዎች ፣

በሰዎች (ግለሰቦች ፣ ቡድኖች ወዘተ) መካከል ልዩ ልዩ ግንኙነቶች መኖራቸው አስፈላጊ የመሆኑን ያህል በመንግሥታትም መካከል ግንኙነቶች አስፈላጊ ናቸው።ሰዎች ለብቻቸው ተነጣጥለው ለመኖር እንደማይችሉ መንግሥታትም እንደዚሁ ብቻቸውን ያለአንዳች ግንኙነት ለመኖር ያዳግታቸዋል። የግንኙነቱ መስከ ይጥበብ ወይም ይስፋ እንጂ መንግሥታት ርስበርሳቸው መገናኘትና በልዩ ልዩ መስኮች መተባበር ከባህሪያቸው አንዱ ነው ። ግንኙነታቸው እየሰፋና ጥልቀት እያገኘ በሔደ ቁጥር በመንግሥታት መካከል ያለው ትብብር ይዳብራል ፤ የበለጸገ ይሆናል ። በየጊዜው ይኸንን መሠረታዊ የመንግሥታት ተግባር ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚያገለግሉ መርሆዎች ተቀርጸዋል ፤ እየተቀረጹም ነው ።

በመንግሥታት መካከል ሰላማዊ ትብብር እንዲዳብር ለማድረግ የሚያገለግሉ መሠረታዊ መርሆዎች ውስጥ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል ፦

— የአንድን አገር ልዕልናና ሕጋዊ (ሥልጣነ መንግሥት) እኩልነት ማክበር ፣

— የአንድን አገር የግዛት አንድነትና ድንበር አለመጣስ ፣

— ባንድ አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት ፣

— በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ትብብርን ማስፋፋት ፣

Digitized by Google

ከዚህ በላይ የሠፈሩት መርሆዎች ለሁሉም ነፃ መንግሥታት በእኩልነት እንዲያገለግሉ ተደርገዋል ። እነዚህ መርሆዎች በተባበሩት መንግሥታትና እንደ አፍሪካ አንድነት ድርጅት ባሉት አህጉራዊና ቀጠናዊ ድርጅቶች ቻርተሮች ፣ መግለጫዎች ፣ በ1970ው የተባበሩት መንግሥታት የዓለም አቀፍ ሕግና በ1975ቱ የሄልስንኪ መግለጫዎች ላይ በደንብ መልክ ሰፍረው ከመገኘታቸውም በላይ ፣ በሁለት ወይንም በብዙ መንግሥታት መካከል በተደረጉት አያሌ ስምምነቶችና ውሎች ውስጥም ተቀባይነት አግኝተዋል ።

<u>የልዕልናና (የሥልጣነ—መንግሥት) እኩልነት መርህ</u>

የመንግሥታት ልዕልናና የእኩልነት መርህ በነፃ መንግሥታት ዘንድ ተቀባይነት ያገኘና በብዙ ዓለምአቀፍ ሰነዶች ላይ ሰፍሮ የሚገኝ የዓለም አቀፍ ሕግ የማዕዘን ድንጋይ ነው ። የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር በአንቀጽ 2/1/ «የተባበሩት መንግሥታት የተመሠረተው በሁሉም አባሎች የልዕልና (የሥልጣነ—መንግሥት) እኩልነት መርሆ ላይ ነው» [17] በማለት ያረጋግጣል ። የ1970ው የተባበሩት መንግሥታት የዓለም አቀፍ ሕግ መግለጫ ለልዕልናና ለእኩልነት መርህ ግንዛቤ ሲሰጠው መንግሥታት ሁሉ ሕጋዊ እኩልነት ያላቸው መሆኑን ፣ ስለሆነም መንግሥታት ሁሉ በዓለም አቀፍ ሕግ ፊት ተመሳሳይ መብትና ግዴታም ሊኖራቸው እንደሚገባ ያረጋግጣል። ይህ መብትና ግዴታ መንግሥታት የሚከተሉትን ርዕዮተ ዓለም ፣ ፖለቲካ ፣ ኤኮኖሚ ፣ ማኅበራዊ ሥርዓትና አጠቃላይ የዕድገት ደረጃን ሳይመለከት ወይም ከእነዚህ ባሻገር እንጂ በእነዚህ ምክንያት ሊዛባ የሚችል አይሆንም ። የዓለም አቀፍ ሕግ ባለቤት የሆኑት መንግሥታት በዓለም አቀፍ ግንኙነት ውስጥ ካላቸው አበይት መብቶችና ግዴታዎች ውስጥ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል ፤

— መንግሥታት ነፃ በሆነ መንገድ የራሳቸውን ፖለቲካዊ ፣ ኤኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊ ወዘተ የዕድገት አቅጣጫ ለመምረጥ መቻል

— የሌሎችን መንግሥታት የግዛት አንድነትና ድንበር አለመጣስ ፣ (ማክበር)

— በዓለም አቀፍ ስብሰባዎች መካፈል ፣ ስምምነቶች ፣ ውሎች ፣ ወዘተ መዋዋል

— እያንዳንዱ መንግሥት ዓለም አቀፍ ግዴታውን በቅን መንፈስ ማሟላትና ከሌሎች መንግሥታት ጋር በሰላም አብሮ መኖር ፣

የልዕልናና የእኩልነት መርህ (The Principle of Sovereign Equality) በሁለት ላይ የሚከፈል ሲሆን ፣ ባንድ በኩል የአንድ ሀገር ልዕልና(ሥልጣነ—መንግሥት) በሌላ በኩል ደግሞ የእኩልነት መብት ይገኛሉ ።

የአንድ ሀገር ልዕልና ማለት ፣ አንድ መንግሥት በራሱ ግዛት ላይ ያለውን የበላይነት (supermacy) የሚያመለክት ወይም የሚያረጋግጥ ነው ። በግዛቱ ውስጥ የፈለገውን የማድረግንና የራሱ የሆነ የውጭ ፖሊሲ ማካሄድን ያጠቃልላል ። አንድ ነፃ መንግሥት ወይንም ሥልጣነ መንግሥት የራሱን ሥርዓት ይዘረጋል ። ይጠቅመኛል ያለውን አምኖ ሕግ ያወጣል ፤ የፈለገውን የእድገት ፈለግ ይከተላል ፤ ያልተቀበለውን የዓለምአቀፍ ደንብ ሌላ መንግሥት ወይንም የተወሰኑ መንግሥታት በግዴታ እንዲቀበልና ተግባራዊ እእዲያደርግ በሕግ ሊያስገድዱት አይችሉም ።

የመንግሥት እኩልነት መርህ መንግሥታት በዓለምአቀፍ ሕግ ፊት እኩል መብትና ግዴታ እንዳላቸው ያስገነዝባል ። መንግሥ

Digitized by Google

ታት ካላቸው የዓለምአቀፍ ግንኙነት አኳያ በሚያደርጉት ስምምነት ላይ መብታቸውንና ግዴታቸውን ይወስናሉ ።

የልዕልና (የሥልጣኑ መንግሥት) እኩልነት የሚያስገነዝበው መንግሥታት በዓለም አቀፍ ሕግ የእኩልነት መብት እንዳላቸው ለማረጋገጥ እንጂ ነፃ መንግሥታት በተጨባጭ ዕድገት ደረጃቸው ፣ በሕዝብ ብዛታቸው ፣ በሀገራቸው ስፋት ፣ ወዘተ ... አይበላለጡም ማለት አይደለም ። ከዚህም ሀቅ በመነሳት ኃያላን መንግሥታት ከአነስተኛ መንግሥታት ይልቅ የዓለምን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለባቸው ግልጽ ነው። ኃያላን መንግሥታት (ሶቭየት ኅብረት ፣ አሜሪካ ፣ እንግሊዝ ፣ ፈረንሣይና ቻይና) ከሌሎች የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል ሀገሮች ጋር ሲነፃፀሩ ቻርተሩ በደነገገው መሠረት በፀጥታው ምክር ቤት ውስጥ ልዩ መብት ተሰጥቷቸዋል ። ስለሆነም በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር የፀጥታው ምክር ቤት የዓለምን ሰላምና ፀጥታ በመጠበቅ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና እንዲጫወት የተለየ ኃላፊነት ተጥሎበታል ።

የግዛት አንድነትና የድንበር አለመጣስ መርህ ከልዕልና መርህ ጋር የተያያዘ ከመሆኑም በላይ አንድ መንግሥት በራሱ ግዛት ላይ ከአለው የበላይነት ጋር ይመሳሰላል ። የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር አንቀጽ 2/4 በኃይል መጠቀም የሀገር የግዛት አንድነትንና የፖለቲካ ነፃነትን የሚፃረር መሆኑን ይጠቁማል ። የ1970ው የዓለምአቀፍ ሕግ መግለጫ ይህንን መርህ ተቀብሎታል ። የ1975 የሄልሲንኪው መግለጫ ደግሞ በግዛት አንድነትና በድንበር መጣስ ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግና ይህንንም ከመንግሥታት ልዕልናና እኩልነት ጋር በማገናዘብ በመንግሥታት መካከል ጠቀሜታ ያላቸውን ግንኙነቶችና ትብብሮች ለማስፋፋትና ለማዳበር አስፈላጊነታቸውን አመልክቷል ።

በሌላ ሀገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት

የውስጥ ጉዳይ እና ጣልቃ መግባት የሚሉትን ሀረጐች በአጭሩ ማብራራት ያስፈልጋል ። ያንድ ፃ መንግሥት የውስጥ ጉዳይ ማለት ፃ መንግሥት በግዛቱ ውስጥ የሚያደርገውን ማናቸውንም ነገር እና የውጭ ግንኙነቱንም የሚመለከት ነው ። በሌላው መንግሥት ጉዳይ ጣልቃ እስከአልገባ ድረስ ወይም የሌላውን መንግሥት ጥቅም እስከአልጐዳ ወይም እስከ አልተፃረረ ድረስ ከሌሎች መንግሥታት ጋር የሚፈጥረው ግንኙነት እንደ ውስጥ ጉዳዩ ይቆጠራል ። ጣልቃ መግባት ያለፈቃድ ወይም በኃይል የሚከናወን ድርጊት ነው ። አንድ መንግሥት ፈቅዶና ፈልጐ ሌላ መንግሥት በዚያ መንግሥት ጉዳይ ውስጥ ቢገባ እንደ ጣልቃገብነት አይቆጠርም ።

ባንድ ነፃ መንግሥት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባት መርህ በአውሮፓ የቡርዧው አብዮት ከፈነዳ ወዲህ ተቀባይነትን እያገኘ መጣ። የዚህ መርህ ይዘት አንድ መንግሥትም ሆነ የተወሰኑ መንግሥታት በቡድን በሌላው መንግሥት የውስጥ ጉዳይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጣልቃ እንዳይገቡ የሚከለክልና የሚያግድ ነው ። መርሁ ከመንግሥታት ሕጋዊ እኩልነት መርሆ ጋር የተያያዘና ከእነዚህ የሚከተል ነው ። ባንድ መንግሥት የውስጥ ጉዳይ ያለፈቃድ ጣልቃ መግባት የዚህን መንግሥት ልዕልና መጻረር መሆኑ ግልፅነው ።

Digitized by Google

የኢምፔሪያሊዝም የውጭ ፖሊሲ በሽብር ፈጠራ ፥ በጣልቃ ገብነት ፥ የሀገሮችን ልዕልና በመጻረርና ድንበራቸውን በመጣስ ላይ የተመሠረተ ነው ።

(*New Times*) ከተሰኘ የሶቭየት ሳምንታዊ መጽሔት ላይ የተገኘ)

Digitized by Google

በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባት መርህ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር ውስጥ በአንቀጽ 2/7/ሰፍሮ ይገኛል ። በቻርተሩ መሠረት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እንኳን በአንድ መንግሥት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት እንደሌለበት በግልፅ የተቀመጠ ጉዳይ ነው ። «አሁን ያለው ቻርተር የተባበሩት መንግሥታት የአንድን ሀገር የውስጥ አስተዳደራዊ ሥልጣን በሚመለከቱ ጉዳዮች ጣልቃ እንዲገባ ሥልጣን አይሰጠውም። በመሆኑም እንዲህ ዓይነቶቹ ጥያቄዎች በቻርተሩ መፈታት አለባቸው ።»[18]

ባንድ መንግሥት የውስጥ ጉዳይ ያለፈቃዱና ፍላጐቱ ጣልቃ ያለመግባት መርህ ሰፋ ባለ መንገድ ሕጋዊ ግንዛቤ የተሰጠው በ1965 የተባበሩት መንግሥታት « በመንግሥታት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብነትን አለመፍቀድ» በሚለው መግለጫ ሲሆን ፣ ካቀፋቸው አበይት ቁምነገሮች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል ።

—በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሌላ መንግሥት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብነትን መቃወም ፣

—አንድ መንግሥት ለራሱ ጥቅም ከማግኘት አኳያ የሌላውን ሀገር ሥልጣነ መንግሥት መተናኰል የሌለበት መሆኑና ፣

—መንግሥታት ያለምንም ጣልቃገብነት የራሳቸውን ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ዕድገት የመምረጥ መብት ያላቸው መሆን ይገኙበታል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በ1970 ባወጣው የዓለምአቀፍ ሕግ መርሆች መግለጫ ላይ በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባት መርህ በሰፊው ተብራርቷል ። መግለጫው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሌላ መንግሥት ጉዳይ ጣልቃገብነትን ከመቃወም በላይ ይህን መርህ የሚጥሱ መንግሥታት ሕገወጥ ድርጊት መፈጸማቸውን ያረጋግጣል ። ጣልቃገብነት በተለያዩ መንገዶች ሊከሰት ይችላል ።

—በነፃ መንግሥታት የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚና የባህል ነፃነት ላይ ተፅእኖ ለማድረግ በወታደራዊና በተለያዩ መንገዶች ጣልቃ መግባት ፣

—በኢኮኖሚና በፖለቲካ መስኮች በሌላ ሀገር ላይ ተፅእኖ ማሳደር ፣ እንዲሁም አንድ ነፃ ሀገር በሥልጣነ መንግሥት መብቶቹ ከመጠቀም ይቆጠብ ዘንድ ማስፈራራት ፣

—ነፃ መንግሥትን ለመገልበጥ ቅጥረኞችና የሽብር ፈጣሪ ቡድኖች በማደራጀት ፣ በማስታጠቅና በመርዳት በተግባር ላይ ማስማራት ፣

—በአንድ ሀገር ውስጥ በሚካሄድ የርስ በርስ ትግል ካንዱ ወገን (ሕጋዊነት ከሌላው ጐን) መሰለፍ ፣

—ያንድ አገር ሕዝብ የራሱን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገት አቅጣጫ እንዳይወስንና እንዳይከተል እንቅፋት መሆንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል ።

በአንድ መንግሥት ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባት መርህ በተለያዩ መንግሥታት በተደረሱ ስምምነቶችና ውሎች ላይ ሰፍሮ የሚገኝ ሲሆን ይህ መርህ ዘወትር በአብሪተኞች በተለይም በቀንደኛ ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት እንደተጣሰ ነው ። ለምሳሌ ፣ የዩናይትድ ስቴትስ ኢምፔሪያሊዝም በቅርብ ጊዜ በግሬናዳ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት የዚህን አገር ህጋዊ መንግሥት ከመገልበጡም በላይ፣ ሕዝቡ የፈለገውንና የመረጠውን ዕድገት አቅጣጫ እንዳይከተል በማድረግ የራሱን አሻንጉሊት መንግሥት በማቋቋም አገሪቱን ወደ ጥገኛና እጅ አዙር ቅኝ ግዛትነት ለውጧታል ። ከዚህ በተቃራኒ ሶሻሊስት ሀገሮችና ተራማጅ መንግሥታት በሃገሮች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባት መርህ እንዲከበርና ተግባራዊ እንዲሆን የማያቋርጥ ትግል ያካሂዳሉ ።

የመንግሥታት የትብብር መርህ

በያዝነው ክፍለ ዘመን የሳይንስና የቴክኖሎጂ ፈጣን ግሥጋሴና የምርት ኃይሎች ከፍ

Digitized by Google

ተኛ ዕድገት የዓለምአቀፍ የሥራ ክፍፍልን ከመቺውም ጊዜ የበለጠ አስፋፍቶታል ። መንግሥታት በኢኮኖሚ መስክ የሚያደርጉት ትብብርና ልውውጥ እያዳበረና እያሰፋ ሊመጣ ችሏል።ስለሆነም በመንግሥታት መካከልም የሚደረገው ትብብር በዘመናችን ዓለምአቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርሆች ለመታቀፍ በቅቷል ።

የመንግሥታት የትብብር መርህ ማለት በሰላም አብሮ መኖርን መርህ በተጨባጭ ተግባራዊ ማድረግ ማለት ነው ። በሰላም አብሮ የመኖር መርህ የሚያስገነዝበው መንግሥታት የተለያዩ ማኅበራዊ ሥርዓቶችን ቢከተሉም ፣ ኃይልን ፣ ማስገደድን ፣ ጣልቃ መግባትን ፣ ወዘተ በመተው በመካከላቸው በተለያዩ መስኮች (በሳይንስ ፣ በኢኮኖሚ ፣ በንግድ ፣ በባህል) ትብብራቸውን እንዲያጠናክሩና እንዲያስፋፉ ነው ። በዚህ አንፃር የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር በአንቀጽ 1/3/ «የዓለምአቀፍ ትብርርን የሰመረ መልክ ለማስያዝ ዓለምአቀፋዊ የሆኑ የኢኮኖሚ ፣ የማኅበራዊ ፣ የባህላዊና የሰብአዊ ችግሮች መፈታት አለባቸው»[19] በማለት የትብብሩን መሠረትና አስፈላጊነት ደንግጓል ።

መንግሥታት እርስበርሳቸው ትብብር ፣ በሚፈጥሩበት ጊዜ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ነጥቦችን መቀበል እንዳለባቸው ይጠበቃል። እነሱም ፣

—በዓለምአቀፍ ትብብር መሠረት የሚካሄደው የመንግሥታት ግንኙነት በተናጠል ከገነቡት የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ሥርዓት ባሻገር መሆን ወይም የሚከተሉትን ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት መንካት እንደሌለበት ወይም የአንድ አገር የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ሥርዓት ለዓለምአቀፍ ትብብር እንቅፋት መሆን እንደማይችል ፣

—ዓለምአቀፋዊ ትብብር መጠናከር ያለበት የዓለምን ሰላምና ደህንነት ከመጠበቅና ከማረጋገጥ አንፃር እንደሆነ ፣

—መንግሥታት ትብብር ሲፈጥሩ የሥልጣን መንግሥት እኩልነትና በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለመግባትን መርሆች ተግባራዊ በማድረግ አንድ መንግሥት የሌላውን መንግሥት ነፃነት በማወቅ ያለምንም አድልዎ መጠናከርና መዳበር እንደሚገባው የሚዘረዘሩት መርሆዎች ናቸው ።

በ1970ው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዓለምአቀፍ ሕግ መግለጫ ትብብርን በሚመለከት በቀየሰው አቅጣጫ መንግሥታት ግንኙነታቸውን በተለያዩ መስኮች (በኢኮኖሚ ፣ በማኅበራዊ ኑሮ ፣ በባሕል ፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ) በማጠናከርና በማዳበር የዓለም ሰላምን በማስጠበቅ የሰው ልጅ መሠረታዊ መብትና ነፃነትን ማክበር እንዳለባቸው ያስገነዝባል ። የ1975 የሄልሲንኪው የአውሮፓ ፀጥታና የትብብር ስብሰባ ባወጣው መግለጫ ላይ በመንግሥታት መካከል የሚደረገው ትብብር አስተማማኝና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ መሆን እንዳለበት ያስገነዝባል ።

ዓለምአቀፍ ትብብር የተሳካ ሊሆን የሚችለው በመንግሥታት ግንኙነት ውስጥ አድልዎን በማስወገድና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ግንኙነት መፍጠር ሲቻል ነው ። እያሌ አከራሪ የቡርዧ መንግሥታት ዓለምአቀፍ ትብብርን በሚመለከት ሆን ብለው የተያያዙት የአድልዎ ፖሊሲን ግራመድ ነው ። አከራሪ ኢምፔሪያሊስት መንግሥት ሰበብ አስባብ እየፈለጉ ከሶሻሊስትና ተራማጅ መንግሥታት ጋር እንነግድም ፣ አንለዋወጥም በማለት ዘወትር ከመደንፋት አልተቆጠቡም ። ይሄንንም በተጨባጭ የምንረዳው ኢምፔሪያሊዝም በፈጠረው የተዛባ ዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍል በመጠቀም የሶሻሊስትንና የታዳጊ አገሮችን ዕድገትንና መጠናከርን ለመግታት ብዙ ጥረት ማድረጋቸውን አሁንም ካለመተዋቸው ነው ። ኢምፔሪያሊቶች ፍትሕና እኩልነት ላይ የተመሠረተ የኢኮኖሚ ትብብር እንዳይመሠረት በተለያዩ ዘዴዎች ይቃወማሉ ። የዓለም አ

Digitized by Google

ቀፍ ኢኮኖሚን በማስመልከት በ1974 በተባበሩት መንግሥታት በ6ኛው ልዩ ስብሰባና በ19ኛው መደበኛ ጉባዔ ላይ ስለአዲሱ የዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ግንባታ የድርጊት ፕሮግራም እንዲሁም የመንግሥታትን የኢኮኖሚ መብትና ግዴታ የሚያስረዳ ቻርተር አውጥቶ ነበር ። ይሁንና ኢምፔሪያሊስቶች በሌላ በኩል እንደሚያደርጉት ሁሉ ይህንንም የአዲስ ኤኮኖሚ ሥርዓት መመሥረትና የትብብርን መዳበር በተቻላቸው ሁሉ እያደናቀፉት ይገኛሉ ።

ግዴታን በቅን መንፈስ ተግባራዊ ማድረግ

በመንግሥታት መካከል የሚደረገውን ትብብር ሊያጠናክሩና ሊያስፋፉ ከሚችሉት ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ መንግሥታት ግዴታቸውን በወቅቱና በሚገባ መፈፀም ነው ። መንግሥታት በገዛ ፈቃዳቸው ፣ ሳይገደዱ ወድደው የተዋዋሉትን ውል ፣ የአደረጉትን ስምምነት ፣ የገቡትን ግዴታ ማክበር ይገባቸዋል ። ያለምንም ማስገደድና ተፅእኖ ይጠቅመናል ብለው የገቡትን ግዴታ ካልፈፀሙ ምንም ዓይነት ትብብር ወይም መግባባት ሊኖር አይችልም። ስለሆነም ለትብብር ብሉም ለሰላም መከበር መንግሥታት ግዴታቸውን በሚገባ መፈፀም አለባቸው ።

የዚህ መሠረታዊ መርሆ አስፈላጊነት ግልፅ ይሁን እንጂ ተግባራዊነቱን በሚመለከት በየጊዜው ችግሮች መፈጠራቸው አልቀረም ። ባብዛኛው የችግሮቹ ምንጭ ወይም መንስዔ ባንድ በኩል ከኃይልና ከማን አህሎኝነት የሚመጣና በኢምፔሪያሊስት አገሮች የሚፈጠር ችግር ነው ። በሌላ በኩል አድኃሪ የገዥ መደቦች በሕዝባዊ አብዮት ተገልብጠው ተራማጅ መንግሥት ሲመሠረት ለሕዝብ ጥቅም ያልዋለውን ግዴታ አልቀበልም ከማለት አንዳንድ የተዛቡ ውሎች ሊሰረዙ ይችላሉ ። ኢምፔሪያሊስትና አድኃሪ መንግሥታት ጥቅማችን ተነካብን በማለት አግባብ በሌለው መንገድና በኃይል በመመካት በተራማጅና አብዮታዊ መንግሥታት ላይ ቀድሞ የተደረገው ውል ያስገኝላቸውን የተዛባ ጥቅም እናስከብራለን በማለት በታላቁ የጥቅምት ሶሻሊስት አብዮት ማግሥት በአዲሱ በሶቪዬት መንግሥት ላይ ያደረጉት ተጽዕኖ ለዚህ ምሳሌ ሊሆን ይችላል ።

አሁን ባለንበት ሁኔታ ማለትም በሁለቱ ተፃራሪ ዓለምአቀፍ ሥርዓቶች (ሶሻሊዝምና ካፒታሊዝም) ውስጥ ባሉ መንግሥታት መካከል በህቅ፣ በእኩልነትና በፍትህ ላይ የተመሠረቱ ለጋራ ጥቅም የተደረጉ ውሎችና ስምምነቶች መከበራቸው አስፈላጊ ነው ። ይህ ካልሆነ አብሮ በሰላም የመኖር መርህና ማናቸውም ዓይነት ትብብር ሊሰፍን አይችልም ። ይህ ደግሞ ወደ ዓለም ሰላም መናጋትና ወደ ጦርነት ሊያመራ እንደሚችል አይጠረጠርም ።

የሕዝቦችንና የብሔሮችን ሰብአዊ መብት በማስጠበቅ በኩል የሚያገለግሉ መሠረታዊ መርህዎች

ዓለማችን ሰላምና ፀጥታ ለማግኘትና ወደፊት ለመራመድ የምትችለው ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች የተከበሩ እንደሆን ነው ። እነዚህ ሁኔታዎች ካልተሟሉ በየአካባቢው ችግሮች መፈጠራቸው ፣ ውዝግቦችና ብጥብጦች መነሳታቸው ፣ ግጭቶችና ጦርነቶችም መከተላቸው አይቀርም።

የሕዝቦችና የብሔሮች የራስን ዕድል በራስ መወሰን መርህ

የሕዝቦችና የብሔሮች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መርህ ከፖለቲካ መፈክር ወደ ማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲ ፕሮግራም ከዚያም ወደአጠቃላይ የዓለም አቀፍ ሕግ መሠረታዊ መርህ የተሸጋገረ ነው ። ታላቁ የጥቅምት አብዮት የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መርህ ሶሻሊስት መንግሥታት በውስጥና

Digitized by Google

በውጭ ፖሊሲያቸው ተግባራዊ ከሚያደር ጓቸው መርሆች አንዱ እንደሆነ ይታወቃል።

የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መርህ በተ ባበሩት መንግሥታት ቻርተር ላይ በአንቀጽ 1/2 «በሀገሮች ዘንድ የወዳጅነት ግንኙነ ትን ለማዳበር ግንኙነቱ በሕዝቦች እኩል ነት፣ መብትና የራስን ዕድል በራስ የመወ ሰን መብት በማክበር ላይ መመሥረት ይና ርበታል» በማለት ይገልፀዋል ።[20] ይህ መርህ ዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊና ማኅ በራዊ ትብብርን ለመፍጠር የሚኖረውን አስተዋጽኦ የተባበሩት መንግሥታት ቻር ተር በአንቀጽ 55 እንደሚከተለው አስ ቀምጦታል፣ «በአገሮች መካከል ሰላምና መልካም የወዳጅነት ግንኙነት በተረጋ ጋና በአስተማማኝ ሁኔታ ለመፍጠር የሕ ዝቦች የእኩልነት መብቶችና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት መሠረት በማድረግ የተባበሩት መንግሥታት ፤—

ሀ. የተሻለ የኑሮ ደረጃ፣ የሥራ አጥነት ችግሮችን ሙሉ በሙሉ መፍታት የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገትን ማዳ በር፣

ለ. ዓለምአቀፍ የኤኮኖሚ፣የማኅበራዊና የጤና ችግሮችን መፍታት፣ እንዲሁም የባሕልና የትምህርት ትብብርን ማጐ ልመስ፣

ሐ. ሰብዓዊ መብቶችና መሠረታዊ ነፃነ ቶችን ካላንዳች የቀለም፣ የጾታ፣ የቋ ንቋ ወይም የሃይማኖት ልዩነት ሁሉን ተናዊ በሆነ መንገድ ማክበር ።»[21]

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻር ተር ላይ የፀደቀው የራስን ዕድል በራስ የመ ወሰን መርህ በተለያዩ በርካታ ዓለምአቀፍ ሰነዶች ውስጥ ተቀባይነትን አግኝቷል ።

—እነሱም—በቅኝ ግዛት ሥር ለሚገኙ ሀገሮችና መንሥታት ነፃነታቸውን ስለ መስጠት የወጣው የ1960 የተባበሩት መንግሥታት መግለጫ (አንቀጽ 2)፣

—የ1966 ስለሰው ልጅ መብቶች የወጣው ቃልኪዳን (አንቀጽ 2)፣

—የ1970ው የዓለምአቀፍ ሕግ መርሆች

—የ1975ቱ የሄልሲንኪው የአውሮፓ መን ግሥታት የፀጥታና የትብብር ስብሰባ መግ ለጫ ናቸው ።

የዘመኑ ዓለምአቀፍ ሕግ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መርህን ይዞት በሚገባ ይተ ነትናል ። በተለይም የ1970ው የዓለም አቀፍ ሕግ መርሆች መግለጫ በሚከተሉት ሁኔ ታዎች ያሰፍረዋል፣

—ሕዝቦች በሙሉ ያለምንም የውጭ ጣልቃ ገብነት የየራሳቸውን የፖለቲካ አቅጣጫ በመወሰን የኢኮኖሚ ዕቅዳቸውን ተግባ ራዊ ያደርጋሉ፤ እንዲሁም ማኅበራዊ ኑ ሮና ባሕላቸው እንዲዳብር ጥረት ያደር ጋሉ፤

—እያንዳንዱ ሀገር የእኩልነት መብትና የራ ስን ዕድል በራስ የመወሰን መርህ ተግባ ራዊ ሲያደርግ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር ጋር በማጣጣም ነው፤

—አንድን ሕዝብ በውጭ ኃይል ተፅእኖ በ ቅኝ ግዛት ሥር ማድረግና መበዝበዝ፣ ሕገወጥ ድርጊት ነው፤

—እንዲሁም በቅኝ ግዛት ሥር ያሉ ሕዝቦች ለብሔራዊ ነፃነታቸው በሚያደርጉት ት ግል ተገቢ ነው ብለው በሚገመቱት መንገድ (በትጥቅ ትግልም ጭምር) መጠ ቀም ይችላሉ፣

—ሁሉም መንግሥታት የሕዝቦችን የራስ ዕድል በራስ የመወሰንና የእኩልነት መ ብት በግዴታ ከመጻረርና በኃይል ከመጠ ቀም ድርጊት መቆ ጠብ አለባቸው፤ የብሔ ሮች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብ ትና የብሔሮች የእኩልነት መብት የተያ ያዙና የማይነጣጠሉ ናቸው ። ሁሉም ብሔሮችና ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ሊጠቀሙ ይችላሉ ። የብሔሮችና የሕዝቦች የራስን ዕድል በ

Digitized by Google

ራስ የመወሰን መብት በሶሻሊስት አገሮች ተግባራዊ ሲሆን በካፒታሊስት አገሮች ግን ይህ መብት እንደተጣሰ ነው ። ኢምፔሪያሊዝምና አድኀሪት ስለዚህ መብት የሚያነሱት የተራማጅና የሶሻሊስት አገሮችን አንድነት ለማናጋትና ለፀረ ሶሻሊዝም ፕሮፓጋንዳ እንጂ ራሳቸው በፍጹም ተግባራዊ አያደርጉትም ፣ ሊያደርጉትም አይችሉም ።

ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር መርህ፣

በዓለምአቀፍ ደረጃ ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር መርህ እየታወቀ የመጣው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር ከወጣ ወዲህ ነው ። ከዚያ ጊዜ በኋላ ሰብአዊ መብት የማክበር መርህ ካሁኑ የዓለምአቀፍ ሕግ መርሆዎች አንዱ ሊሆን ችሏል ። ይህ መርህ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር መግቢያ ላይ «እኛ የተባበሩት መንግሥታት ሕዝቦች የሚቀጥለውን ትውልድ ከጦርነት ለማዳን ፣ መሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶች ክብርና ዋጋ ፣ የወንዶችና የሴቶች እንዲሁም የትልቅና የትንሽ መንግሥታት የእኩልነት መብቶች ልናረጋግጥ ያስፈልጋል ፤»[22] የሚል መሠረተ ሃሣብ ሰፍሮ ይገኛል። በተጨማሪ ከዚህ በላይ ከፍ ብሎ እንደተመለከተው በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር በአንቀጽ 1/3/ የተደነገገውም ከዚህ ጋር የተያያዘና የሰውን ልጅ መብት የሚመለከት ነው ።

የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ከፀደቀ በኋላ የሰውን ልጅ መብቶች የሚመለከቱ የተለያዩ ዓለምአቀፍ ሰነዶች ይፋ ወጥተዋል ።

—በ1948 የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ የሰውን ልጅ መብቶች በሚመለከት ያወጣው መግለጫ (Human Rights Declaration)

—በተለያዩ ጊዜያት የሴቶችንና የሕፃናትን መብት ለማስጠበቅ ፣ በዘር ልዩነት ላይ የተመሠረተ ግድያን ፣ አፓርታይድን የባሪያ ንግድን ፣ ወዘተ የሚያወግዙ ብዙ ዓለምአቀፍ ሰነዶች ወጥተዋል ። እነዚህ ሰነዶች ላይ በመመርኮዝ ዘረኝነትን ፣ አፓርታይድን ፣ በቀለም ፣ በጾታ ፣ ወዘተ ላይ የተመሠረቱ መድልዎችን ለማስወገድ ከፍተኛ ትግል እየተካሄደ ሲሆን ፣ እነዚህን ዓለምአቀፍ ድንጋጌዎቹን የሚጥሱና የማያከብሩ መንግሥታትና ፣ ድርጅቶች ከመወገዝና ከመኰነን አላመለ

የሶቭየት ኅብረት ዓለምአቀፍ ሕግ ተመራማሪ ቱንኪን የሰብአዊ መብቶችን መከበር ጉዳይ

«ሀ. መንግሥታት ሁሉ በግዛታቸው ውስጥ የሚገኙትን መሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች የማክበር ኃላፊነት አለባቸው ፣

ለ. መንግሥታት በግዛታቸው ውስጥ በጾታ ፣ በዘር ፣ በቋንቋ ወይንም በኃይማኖት ላይ የተመሠረተ አድልዎ እንዳይፈፀም የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፣ ጡም ።

ሐ. መንግሥታት የሰው ልጅ መብቶች ሁለንተናዊ ተቀባይነትን እንዲያገኙና ተግባራዊ እንዲሆኑ እርስ በርሳቸው መተባበር አለባቸው»[23] በማለት ጠቅለል አድርጐ አስቀምጦታል ።

በመሠረቱ እነዚህ ዓለምአቀፍ ሰነዶች በመንግሥታት የውስጥ ሕጐች እስካልተጠቃለሉ ድረስ በራሳቸው ለሰው ልጅ ምንም ዓይነት መብት አይሰጡም ወይንም አያስከብሩም ። ይሁንና መንግሥታት በውስጥ ሕጋቸው ሰብአዊ መብቶችን ካወቁና ካረጋገጡ ከዓለምአቀፍ ሕግ ጋር ይስማማሉ ። መንግሥታት በውስጥ ሕጋቸው ሰብአዊ መብቶችን እንዲያውቁና እንዲቀበሉ በዓለምአቀፍ ሕግ ላይ መደንገጉም ከፍተኛ ተፅእኖ ያደርጋል ። ለምሳሌ ያህል በተባበሩት መንግ

Digitized by Google

ምታት ድርጅት አማካይነት በዘረኛው የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ላይ በተደጋጋሚ ማዕቀብ ለማድረግ ተሞክሯል ። በዚህ አንፃር ሶሻሊስትና ተራማጅ አገሮች በግልና በወል በዘረኛው መንግሥት ላይ ማዕቀብ ማድረጋቸውን እንደቀጠሉ ሲሆን ፣ በአንፃሩ ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ግን ማዕቀቡን ይቃወማሉ ፤ አለያም በአፍ ብቻ ይቀበሉና ተግባራዊ አያደርጉትም ።

ለሰብአዊ መብቶች መከበር ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት በተለይም ቀንደኛው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና ግብረ አበሮቹ ብዙ ያላዝናሉ ፤ለሰብአዊ መብት እንታገላለን ይላሉ። ነገር ግን ለእነሱ ሰብአዊ መብት ማለት ለካፒታሊዝም የመበዝበዝ ወይም የመጨቆን መብት እንጂ እያንዳንዱ ግለሰብ ጭቆናና ብዝበዛ በሌለበት ሥርዓት ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች አግኝቶ የሚኖርበት ሁኔታ ማለት አይደለም ። ከዚህ የተዛባና የተጣመመ አመለካከት በመነሳት በሰብአዊ መብት «አለመከበር»ሽፋን በሶሻሊስትና ተራማጅ አገሮች ላይ የፕሮፓጋንዳ ውርጅብኝ ያስተጋባሉ፤ ይህ የፕሮፓጋንዳ ጦርነት ደግሞ በተለይም ባሁኑ ወቅት የዓለምን ሰላምና ፀጥታ ወደማቃወስ ደረጃ እየተሸጋገረ በመሄድ ላይ ይገኛል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. D. B. Levin, *Basic Problems of Present-day International Law* (Moscow: 1958), p. 101 (in Russian).
2. Charter of the United Nations and Statute of the International Court of Justice, (U.N. Charter and Status of ICJ), United Nations, New York, DTJ/511-175 M/2-80, P. 1.
3. See U.N. Charter and Statute of ICJ, P. 8.
4. Resolutions adopted by the General Assembly during its 15 Session No. 1,236, 15 December, 1960.
5. U.N. Charter of the United Nations and Statute, the International Court of Justice, United Nations, P. 4.
5. Charter of the United Nations ICJ, P. 4.
7. 2,625 (XXV) — Declaration on Principles of International Law Concerning Friendly Relations and Co-operation among states in accordance with the Charter of the United Nations, October 24, 1970.
8. U.N. Charter and Statute of ICJ, P. 4.
9. The Programme of the Communist Party of the Soviet Union.
10. See U.N. Charter and Statute of ICJ, P. 16.
11. Resolutions adopted by General Assembly on December 14, 1946/41/1.
12. Resolutions Adopted by General Assembly on November 4, 1954, Rso No. 809 (IX).
13. 2,625 (XXV) — Declaration on Principles of International Law Concerning Friendly Relations and Co-operation among states in accordance with the Charter of the United Nations, October 24, 1970.
14. Resolutions Adopted by General Assembly on December 20, 1959, Reso. No. 1,378, during XIV Session.
15. L. A. Modzhorian, *International Law*, 2nd edition (Moscow, 1979), P. 180 (in Russian).
16. G. I. Tunkin, *Theory of International Law*, (Harvard University Press, Cambridge, Massachusetes, 1974) P. 79.
17. U.N. Charter and Statute of ICJ, P. 4.
18. *Ibid.*, P. 15.
19. *Ibid*, p. 3.
20. *Ibid.*
21. *Ibid*, *p*. 30.
22. *Ibid*, p. 1.
23. G.I. Tunkin, P. 81.

Digitized by Google

ቢሮክራሲና ሕዝባዊ አስተዳደር

ወልደ ዮሐንስ ወርቅነህ

ቢሮክራሲ የሚለው ቃል በአንድ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ አገዛዝን (Officials rule) የሚያመለክት ነው ። ሰፋ ባለ ግንዛቤውም የባለሥልጣናት ማንኛውንም ሥልጣን ማጠቃለልን ያመለክታል። ይህ ቃል በ1715 አካባቢ በፈረን ሳይ ውስጥ በጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን «ቢሮክራሲ» የሚለው ቃል በወቅቱ ለነበረው የመንግሥት አሠራር የተሰጠ ስያሜ ነበር። ይኸው ቃል በ19ኛው ምዕተ ዓመት ላይ ወደ ጀርመን ፣ እያደርም በእንግሊዝኛ ቋንቋ ወደሚጠቀሙ አካባቢዎች ሊዛመት በቃ ።[1]

ቢሮክራሲ የሚለው ቃል የሁለት ቃላት ማለትም የቢሮና የክራሲ ቅንብር ነው ።ቢሮ (Bureau) ጽሕፈት ቤት ሲሆን ፣ ክራሲ (Cracy) አገዛዝ ማለት ነው ። የሁለቱ ቃሎች መገጣጠም ቢሮክራሲ (Bureaucracy) የሚለውን ቃል የሚያስገኝ ሲሆን ፣ ይኸም በመንግሥት ልዩ ልዩ ጽሕፈት ቤቶች ውስጥ በገኙው መደብ እየተከፈላቸው በሚሠሩ የገኙው መደብ አባላት ወይንም ተወካዮች ፣ ባለሥልጣናት ተሞልቶ የአንድን የገኙ መደብ አምባገነንነት ተግባራዊ የሚያደርግ የመንግሥት አውታር አካል ነው ።[2]

ቢሮክራሲ አንድ የተወሰነ ቅርጽ ያለው (የፖለቲካ ፣ የኤኮኖሚ ፣ የርዕዮተ ዓለምና የመሳሰሉት) ማኅበራዊ ድርጅት ሆኖ የሚከተሉትን ባሕሪያት የያዘ ነው ።

አንደኛ ፣ የሥራ አስፈፃሚው (ማዕከል) ሥልጣን ከአብዛኛው የድርጅቱ አባላት ፈቃድና ውሳኔ የሚለይ፣

ሁለተኛ ፣ በመዋቅራዊ ቅርጹ በማንኛውም ድርጅት የሥራ እንቅስቃሴ ይዘት ላይ የበላይነትን (ተፅዕኖን) የሚያሳይ ፣

ሦስተኛ ፣ የድርጅቱን ሕግና ሥነ ሥርዓት በማዛባት ህግን ለራስ መገልገያና በራስ ቁጥጥር ሥር የሚያደርግ ነው ።[3]

ማኅበራዊ እኩልነት በሌለበት ፣ የሰው በሰው መበዝበዝ በሰፈነበትና ሥልጣን በጥቂት ግለሰቦች እጅ በተማከለበት ኅብረተሰብ ውስጥ ቢሮክራሲ የበዝባዡን መደብ

Digitized by Google

ጥቅም ለማስከበር መቆሙ አያጠራጥርም። ለቢሮክራሲ መከሰት የተፈጠረው አመቺ ሁኔታም ይኸው የሥልጣን በጥቂት ግለሰቦች እጅ መግከል ነው።በዚህ አሠራር ሥልጣንን በሞኖፖል ለመያዝ የቻሉ ግለሰቦች ሥልጣናቸውን የግል መገልገያ በማድረግ በኅብረተሰቡ ላይ ጫና ይሆናሉ ።

ቢሮክራሲ በቅርጹ ኤኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ብዝበዛን ከለወጠው ማኅበራዊ ሥርዓት ጋር ሲለዋወጥ የኖረ ነው ። አመሠራረቱም በፊውዳል ሥርዓተ ማኅበር ማህጸን ውስጥ ካቆጠቆጠው ከፍጹማዊነት አገዛዝ ጋር የተያያዘ ነው ። የፍጹማዊነት አገዛዝ ባሕርይ በድርጅታዊ መልኩ ከባሪያ አሳዳሪው ሥርዓተ መንግሥት የጠነከረ ነው ። ማርክስ በፈረንሣይ ፍጹማዊ አገዛዝ ውስጥ የቢሮክራሲን አመጣጥ አስመልክቶ ሲጽፍ፣ « - - - እጅግ ቢሮክራሲያዊና ወታደራዊ ድርጅት ፣ ጥንካሬና ዕውቀት ያለው የመንግሥት የአገዛዝ አውታር ፣ - - - ግማሽ ሚሊዮን አባላት ያሉትን ጦር ያጠቃለለ አስፈሪ ኃይል በፍጹማዊ አገዛዝ ወቅት ብቅ አለ »[4] ብሏል ። ካፒታሊዝም ቀደም ብሎ የተመሠረተውን የመንግሥት ቢሮክራሲያዊ የአገዛዝ ተቋምን ለራሱ የመደብ ጥቅም ማስከበሪያና ማስፋፊያ መሣሪያ አደረገው። የፊውዳል ሥርዓተ ማኅበር ሙሉ በሙሉ ለካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር ሥፍራውን ለቆ የቡርዧው መደብ የበላይነት ከመስፈኑና የቡርዧው መንግሥት አውታር በተኋላ የቡርዧ መልኩ ከመከሰቱ ጋር ቢሮክራሲም ጠንካራ የአገዛዝ መሣሪያ መሆኑ ግልጽ እየሆነ መጣ ። በቡርዧ መንግሥት ቢሮክራሲ የሚጫወተው ሚና በቅርጽም ሆነ በይዘት እየተጠናከረ ሄደ ። « አዲሱ የቡርዧ ኅብረተሰብ የመንግሥትን ቢሮክራሲ የራሱ ፣ ማለትም የአዲሱ ገዥ መደብ መሣሪያ አደረገው ፣ - - - የቢሮክራቶች ወደ ቡርዧነት መለወጥም ቢሮክራሲው የቡርዧው መደብ የፖለቲካ መሣሪያ እንዲሆን አደረገው ። »[5] ካፒታሊዝም እየተስፋፋ ቡርዧዎች በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ሥልጣን ሲይዙ የቢሮክራሲ አገዛዝም በካፒታሊስት ኅብረተሰብ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ጽኑ መሠረት እየጣለ መጣ።

የካፒታሊዝም የምርት ግንኙነት እየዳበረ ፣ ከነፃ ውድድር ካፒታሊዝም ወደ ሞኖፖል ካፒታሊዝም ሲሸጋገር ፣ ቢሮክራሲም በቡርዧው መንግሥት ውስጥ የተስፋፋና የተንዛዛ ቅርጽ ያዘ ። በ20ኛው ምዕተ ዓመት ላይ በኢንዱስትሪ የበለጸጉ አገሮች በሁሉም መስክ ከፍተኛ እድገትን ማሳየት እንደጀመሩ የቡርዧው መንግሥት በማዕከላዊነት የሚመራው ኤኮኖሚ እየሰፋ መጣ ። ከመንግሥት መዋቅር መስፋፋት ጋር የቢሮክራሲው መዋቅር እድገት አሳየ ። በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም ቢሮክራሲ የቡርዧው መደብ በወዝአደሩ መደብ ላይ አምባገነንነቱን የሚያስፈጽምበት መሣሪያ ከመሆኑም በላይ ሞኖፖል ካፒታል ከአገሩ ድንበር አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚያደርገው ጭቆናና ብዝበዛ አስፈፃሚ ኃይል ሆኗል ።

ቢሮክራሲ የመዋቅር መጠሪያ ለመሆኑ ከላይ ተጠቅሷል ። በመሆኑም አሠራሩና ባሕርዩ ኅብረተሰቡን ከሚበዘብዘው መንግሥታዊ መዋቅር ጋር የተያያዘ ነው ። ሕልውናው ከዝርክርክነት ፣ ከሥራ ወዛፌነት፣ ከአባካኝነትና ከብኩንነት ወዘተ - - -ጋር የተሳሰረ ነው ።

በተለምዶ ቢሮክራሲ የሥራ መጓተትን ፣ የተዝረከረከ የወረቀት አሰራርን ፣ ባለ ጉዳይ ማጉላላትን ፣ ወዘተ - - - የመሳሰሉ ፀረ— ሕዝብና ፀረ — ዲሞክራሲ አሠራሮችን የሚያመለክት ነው ። ይሁን እንጂ እነዚህ የቢሮክራሲያዊ አሠራር ገፅታዎችን የሚያመለክቱ እንጂ ቢሮክራሲን እራሱን የሚተረጉሙ አይደሉም ።

ቢሮክራሲ ከሰፊው ሕዝብ የራቀና ሰፊውን ሕዝብ በመጨቆን የሚገዛ ፣ ከሕዝብ ቁጥጥርና ተጠሪነት ውጭ የሆነ የገዥ መደቡንና የአጋሮቹን ጥቅም የሚያራምድ በጠባብ ማኅበራዊ መሠረት ላይ የተዋቀረ ሲሆን ፣ መዋቅሩ የሚመራው ከበላይ በሚመጡ ትዕዛዞች ብቻ ነው ።[6] ይኸም ቢሮክራሲያዊ አሠራር ከሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ አሠራር በተፃራሪነት የቆመ መሆኑን ያመለክታል ።

የቢሮክራሲ ሳይንሳዊ ትርጓሜ ከላይ እንደተጠቀሰው በመንግሥት አውታር ውስጥ ላለው የአስተዳደር ዘርፍ አደረጃጀት፣ ተግባር ፣ ተጽእኖና የፖለቲካ ሥልጣን መሠረት የሆኑ የሲቪልና የሚሊታሪ ተቋሞች የሚንቀሳቀሱበትን የአገዛዝ መሣሪያ የሚያጠቃልል ነው ።

የካፒታሊዝም ዕድገትና ይኸው ሥርዓት ያስከተለው የተካረረ የመደብ ትግል ለቢሮክራሲ አሠራር ሥር መስደድ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል ። ይህም በመሆኑ የቡር

Digitized by Google

ኂው ጭቆና ፣ አምባገነንነትና ጣልቃገብነት በመዋቅሩ አግላይነት የበለጠ ለመጠናከር በቃ ። ቢሮክራሲ በካፒታሊስት ሥርዓት ከሚከሰት መንግሥት ጋር የተያያዘ የመበዝበዣና የመጨቆኛ መሣሪያ ነው ።

ቢሮክራሲ የመጨቆኛ መሣሪያነቱ በጉልህ የሚከሰተው በካፒታሊስቱ ሥርዐተ ማኅበር ውስጥ ነው። የሶሻሊስት አብዮት በፈነዳበትና ተራማጅና ሥርነቀል ርምጃዎች በተወሰዱበት አገር ከግል ሀብት መደምሰስ ጋር በመደብ ይዘቱና በባሕሪው ሊከሰት የሚችልበት መሠረት አይኖረውም ። ሆኖም አብዮት በተካሄደባቸው አገሮችም ቢሆን ቢሮክራሲያዊ አሠራር ሊያንሠራራ ስለመቻሉ ሌኒን በተለያዩ ሥራዎቹ አረጋግጧል። በእነዚህ አገሮች ቢሮክራሲ ቀደም ብሎ ከነበረው መንግሥት ጋር የተደመሰሰ ቢሆንም፣ በተለይ በሽግግር ወቅት የሚታየው ቢሮክራሲያዊ አሠራር ከሶስት መሠረታዊ ሁኔታዎች የሚመነጭ ነው ።

እነሱም ፣

—አንደኛው የቀድሞ ማኅበራዊ ቅንብር ውጤት የሆነው ርዕዮተዓለም የሚያሳድረው ተጽዕኖ ፣ በመንግባት ላይ ያለው መንግሥታዊ መዋቅር በአኗኗራቸውና በርዕዮተዓለማቸው የቀድሞው ሥርዓት ውጤት የሆኑ ባለሙያዎችን ማቀፉ ፣

—በወቅቱ የሚወሰዱት ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ርዕዮተዓለማዊ ርምጃዎች ኋላቀር ከሆኑ የምርት ኃይሎች ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ካለው ህብረተሰብ ባሕል ጋር የሚጣጣሙ አለመሆናቸው ፣

—የሶሻሊስቱን የእድገት ፈለግ በሚከተሉ አገሮች የቀድሞውን መንግሥታዊ መዋቅርና አሠራር አዲስና ሕዝባዊ በሆነ መልክ እንዲዋቀርና እንዲሠራ የማድረጉ ሂደት ጊዜን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው ።[7] በመሠረቱ የሶሻሊስትን የዕድገት ፈለግ የሚከተሉ አገሮች ያሏቸው ማኅበራዊ መዋቅሮች የተለያዩ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቅንብሮች ላይ ከተመሠረተው ቅይጥ ኢኮኖሚ የመነጩ በመሆናቸው የውስብስብነት ባሕሪ ላላቸው የመደብ ፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ አዝማሚያዎች መናር አመቺ ይሆናሉ ።

በተለይም በግል ሀብት ባለቤትነት ላይ በተመሠረተው የኢኮኖሚ ዘርፉ ኑሮአቸውን የመሠረቱ ግለሰቦች የአብዮታዊውን መንግሥት ርምጃዎችና ውሣኔዎችን ለማደናቀፍ በሚያደርጉት ሙከራ በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ሊኖሩ በሚችሉ ዋልጌዎችና የሕዝብ አደራን በሚዘነጉ ሹማምንት የመጠቀም ሙከራቸው ለቢሮክራሲያዊ አሠራር መሠረት ናቸው ። የእነዚህ አሠራሮች ዓይነተኛ ምልክቶች ደግሞ ፣

—በሥልጣን አላግባብ መጠቀም ፣

—ራስን ፣ ወዳጅንና ዘመድን አላግባብ መጥቀም ፣ ሌላውን ግን ሆን ብሎ ማጥቃት ፣

—ሥራን በፍጥነት አለማከናወንና ከአስፈላጊው በላይ ማዘግየት ፣

—የፎርማሊቲና የወረቀት ሥራን ከመጠን በላይ ማብዛት (ይህ በመሠረቱ ካለመተማመን ፣ በሀቅ ካለመሥራት ፣ ኃላፊነትን ከመፍራት) ፣ በሆነ ባልሆነው ምክንያት ሥራን ከማጓተት ጋር አብሮ የሚታይ ነው ፣

—አንድን ጉዳይ በወቅቱ ባለመወሰንና ባለመቁረጥ ፣ ተገልጋዩን ሕዝብ መበደል ፣

—ሥራን መበደል ፣ ለመልካም የሥራ ክንውን እንቅፋት መሆን ፣ ተገቢ ያልሆነ አመራር መስጠት ፣

—የሥራ አፈፃጸምን ማላላትና ግደለሽ መመሆን ፣

—ሥራን ለራስ እድገት ፣ ለራስ መሻሻል፣ ወዘተ… ብቻ አድርጎ መቁጠር ፣

—በተገልጋዩ ሕዝብ ላይ መመሳጠርና የአሠራር ሥርዓትን ከሕዝብ መደበቅ ፣

—ሥራን መደራረብና መዘበራረቅ ፣ [8] ወዘተ …

የመሳሰሉት ናቸው ። እነዚህ የእድገት መሰናክሎች የሶሻሊስት የዕድገት ፈለግን በሚከተሉ አገሮች መከሰታቸው የማይቀር ነው።

ይህ የእድገት መሰናክል የሆነው የቢሮክራሲያዊ አሠራር ሕዝባዊና ወገናዊነት ባለው አሠራር መተካት እንዳለበት የማሌ

Digitized by Google


ሠራተኛ ማኅበሩ
ለ5 ደቂቃ አቤቱታ 5 ቀን . . .
እስከ መቼ - -
አቤት ስብሰባ ስም . . . .
ስብሰባ ላይ ናቸው!
ሰፊውን ሕዝብ በታማኝነትና በቅንነት ማገልገል ተግባራችን ነው!!
እቴ ! ዛሬ ምንም ሥራ አልሠራም ! ሰውንም አላነጋግርም ! "ስብሰባ ላይ ናቸው" ብለሽ ለተላላኪው ንገሪ !

ሳይንስ ያስረዳል ፡፡ ይሁን እንጂ ለረጅም
ዘመናት የብዝበዛ መዋቅሩን ዘርግቶ በጥ
ቂት ቅምጥሎች አማካይነት አብዛኛውን
ኅብረተሰብ ሲጨቁን የነበረውን የአድኀሪ
መንግሥት አገዛዝ አውታር አፍርሶ በአዲ
ስና ሕዝባዊ አሠራር ባለው መዋቅር መተ
ካት ረጅም ጊዜና መራራ ትግልን የሚጠ
ይቅ ነው ፡፡ ይህንን ሕዝባዊ ባሕርይ የማይ
ታይበትን የአገዛዝ መዋቅር እስከ መጨ
ረሻው ድል መንግሉ መጣል ታሪካዊ ኃላ
ፊነት ያለበት በዚህ ጸረ ሕዝብ መዋቅር
ሲጨቆን የነበረው ሰፊው ሕዝብ ሲሆን ፣
ለትግሉም ግብ መምታት የማሌ ፓርቲ
የሚሰጠው ቆራጥ አመራር ወሳኝ ነው ፡፡

ቢሮክራሲን በሕዝባዊ አስተዳደር የመተካቱ አስፈላጊነት

ሌኒን ዲሞክራሲያዊ ሥልጣን ያለውን
የመንግሥት አውታር ለመመሥረት የሚ
ቻለው በአሮጌው ሥርዓት ውስጥ ብኩንነ
ትና ዝብርቅርቅ አሠራር የፈጠረውን ቢሮ
ክራሲያዊ የመንግሥት የአገዛዝ አውታርን
ማጥፋት አስፈላጊ መሆኑን አስገንዝቧል፡፡
ሌኒን ቢሮክራሲን መታገል ማለት አሮጌ
ውን ማኅበራዊ ሥርዓትን መታገል ብቻ ሳይ
ሆን በሶሻሊስት ሥርዓት ውስጥ ቢሮክራሲ
በተሰወረ መልኩ ገብቶ የሶሻሊስት ዲሞ
ክራሲን እንዳይበክል መዋጋትንም እንደሚ
ጨምር አበክሮ አስገንዝቧል ፡፡ ሌኒን ቢሮ
ክራሲያዊ አሠራር ለሶሻሊዝም ግንባታ
ጠንቅ መሆኑን በመግለጽ ይህን ለማስወገ
ይቻል ዘንድ አብዮታዊ የሆነ የአሠራር ዘዴ
መዘርጋት አስፈላጊ መሀ ኑን አስገንዝቧል፡፡

በሶሻሊስት ኅብረተሰብ ሕዝቡ የሚመራ
በት መርህ የቡርዧ ኅብረተሰብ ከሚመራ
በት መርህ ይለያል ፡፡ በሶሻሊስት የፖለቲካ
ሥርዓት አሠራር ውስጥ በተለይም በሕዝብ
አስተዳደር ውስጥ ሂስና ግለሂስ ከፍተኛ ሚና
ይጫወታል ፡፡ የሶሻሊስት መንግሥት በዲሞ
ክራሲያዊ ማዕከላዊነት መርህ የሚመራ በመ
ሆኑ ለቢሮክራሲያዊ አሠራር ማንሠራራት
አመቺ ሁኔታን አይፈጥርም ፡፡ [9] በሕዝብ
ኃይልና ድጋፍ ላይ ያልተመሠረተ የመንግ
ሥ ት የአገዛዝ አውታር ሕዝባዊ ወገናዊ
ነት እንደሌለው ይታወቃል ፡፡ ካርል ማር
ክስ ለአንድ የትግል ጓዱ ለሆነ ግሊሰብ
በጻፈው ደብዳቤ ፣ «<u>አሥራ ስምንተኛ ብሩ
ሚር</u> የተባለውን የመጽሐፌን የመጨረሻ
ክፍል ብትመለከት መገንዘብ እንደምት
ችለው ፣ ከእንግዲህ ወዲህ የፈረንሣይ አብ
ዮት እንደቀድሞው ቢሮክራሲያዊውን የመ
ንግሥታዊ መዋቅር ከቀድሞ ሥርዓተ ማኅ
በር መረከብ እንደሌለበትና ይህንን መዋ
ቅር መደምሰስ እንዳለበት ገልጫለሁ፡፡ በአ
ህጉሩ ውስጥ ማናቸውም በርግጥም ሕዝ
ባዊ የሆነ አብዮት ይህንን ማድረግ ይና
ርበታል ፤ » [10] በማለት አስገንዝቦት
ነበር ፡፡ ማርክስ ይህንን የተናገረው በፈረን
ሣይ የሠራተኛው መደብ በቡርዧው ላይ
አመፅ ያቀነባብር በነበረበት ወቅት ነበር ፡፡
ኤንግልስም <u>የሲቪል ጦርነት በፈረንሣይ</u>
በተባለው የማርክስ መጽሐፍ መግቢያ ላይ
ባሰፈረው ጽሑፍ «የሠራተኛው መደብ ሥል
ጣን እንደጨበጠ በአሮጌው መንግሥታዊ
መዋቅር ሊገለገል እንደማይችል የፓሪስ
ኮሚዩን ገና ከመጀመሪያው ማስተዋል ነበ
ረበት ፡፡ የተቀዳጀውን የበላይነት እንደገና
መልሶ እንዲያጣ — ቀደም ሲል ሲጨቁነው
የቆየውን አሮጌ የመጨቆኛ መዋቅር መግር
ሰስ ይገባዋል ፤ » [11] በማለት ገልጿል ፡፡

ሌኒን የአድኃሪ መንግሥት የአገዛዝ መሣ
ሪያ የነበረው መንግሥታዊ መዋቅር የሠራ
ተኛውን መደብ እንደማያገለግል አስገንዝ
ቧል ፡፡ «ገዥው መደብ የመሠረተው መን
ግሥታዊ መዋቅር እስካልተደመሰሰ ድረስ
...ጭቁኑ መደብ ነፃ ሊወጣ አይችልም» [12]
ሲል ሌኒን ፣ ሠራተኛው የቀድሞውን መንግ
ሥታዊ መዋቅር ሳይደመስስ የፖለቲካ የበ
ላይ ገዥነቱን ለማስፈን የማይችል መሆኑ

Digitized by Google

ለማመልከት ነው። እዚህ ላይ ግልጽ ሊሆን የሚገባው ካፒታሊዝምን ድል ማድረግ ማለት ቢሮክራሲያዊ አሠራሩን ጭምር ድል ማድረግ ማለት መሆኑን ነው ። ይህ ደግሞ የሠራተኛውን መደብ ጥቅም ከሚያስከብረው ከወዝአደሩ የበላይ ገዥነት መንግሥት ምሥረታ ተለይቶ የሚታይ አይደለም ።

ማርክስ 18ኛው ብሩሜር በተባለው መጽሐፉ ውስጥ የሶሻሊስት አብዮት ግቡን እንዲመታ የቡርዧው ቢሮክራሲ መደምሰስ እንዳለበት አብራርቷል ። ሌኒን ቢሮክራሲን የማጥፋት መርህን በሚመለከት ሲያብራራ የሶሻሊስት አብዮት የበላይነት ማግኘት ማለት አስተዳደራዊ አገልግሎትን ለሰፊው ሕዝብ ማስረከብ ማለት እንደሆነ በሚገባ ገልጾታል ። የአንድ ሕዝባዊ ሥርዓት የበላይነት የሚረጋገ ጠውም ቀድሞ የነበረውን የአድኃሪ መደ ቦች የመገልገያ እና የመጨቆኛ መሣሪያ በተራማጅና ወገናዊነት ባለው አሠራር ለመተካት ሲችል ብቻ ነው ።

የሠራተኛው መደብ የበዝባዡን መንግሥት የአገዛዝ አውታሮች በመረከብ ለራሱ እምባገነንነት ሊገለገልበት አለመቻሉን አብዮታውያን በተደጋጋሚ ገልጸውታል ። ሌኒን «ሠራተኛው መደብ ሥልጣን እንደጨበጠ አሮጌውን መዋቅር ሥራ ላይ በማዋል ሳይሆን አንኮታኩቶ ... አዲስ መንግሥታዊ መዋቅርን ከራሱ የበላይ ገዥነት ጋር ለሚካሄደው ትግል ጠንካራ መሣሪያ እንዲሆን ያደርጋል። አዲሱ መዋቅር የማንም ግለሰብ የሥራ ውጤት ሳይሆን የወዝአደሩ የመደብ ትግል እየሰፋና እየፋመ በሄደ ጊዜ ከትግሉ አብራክ የሚገኝ ፍሬ ነው ፤ » [13] ብሏል ።

ሌኒን ካቀረባቸው መሠረተ ሀሳቦች ሶስት ዕውነታዎችን መገንዘብ ይቻላል ። እነርሱም ፣ አንደኛ የሚገረሰሰው አድኃሪ መንግሥታዊ መዋቅር በአዲስ መተካት ያለበት መሆኑ ፣ ሁለተኛ ፣ አዲሱ መዋቅር ከሠራተኛው የበላይ ገዥነት ጋር የሚጣጣምና በቡርዧው የአሠራር ሥልቶች ላይ ተፅዕኖ የሚያደርግ መሆን እንዳለበት ፣ ሶስተኛ ፣ አዲሱ መንግሥት አመጣጡ ከሠራተኛው ትግል ስፋትና ጥንካሬ ጋር የተያያዘ መሆኑ ናቸው። ሌኒን የሠራተኛው መደብ ለዚህ ለዘላቂ ድል መታገል እንዳለበት ሲገልጽ ፣

ቢሮክራሲውን በአንድ አፍታ ፣ በሁሉም ሥፍራ ሙሉ በሙሉ ማጥፋት አይቻልም። ይህ ተምኔታዊነት ነው ። ነገር ግን አሮጌውን ቢሮክራሲያዊ መዋቅር መደምሰስና ወዲያውኑ በአዲስ መዋቅር መተካት አስፈላጊ ነው ። በዚህም አማካይነት ቢሮክራሲን በአጠቃላይ ደረጃ በደረጃ ማጥፋት ተምኔታዊ ሳይሆን የፓሪስ ኮሚዩን ልምድ ነው።[14]

ብሎ ነበር ።

አሮጌውን የመንግሥት መዋቅር የሚተካውን አዲስ አስተዳደር ሌኒን «አዲሱ መንግሥታዊ መዋቅር ፣ አዲሱ የመንግሥት ዓይነት ሕዝባዊ አስተዳደር ነው» [16] ይለዋል ። ይህ ሕዝባዊ አስተዳደር እየጐለበተና ሥር እየሰደደ ሊሄድ የሚችለው ደግሞ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትና በሶሻሊስት አብዮት አማካይነት ሶሻሊዝም በሚገነባበት ሂደት ውስጥ ነው ። በአጠቃላይ ቢሮክራሲውን ለማውደም መታገል ማለት ሕዝባዊ አስተዳደርን ለመገንባት መታገል ማለት ነው ። ቢሮክራሲውን ሙሉ በሙሉ መደምሰስ የረጅም ጊዜና የመራራ ትግል ውጤት ሲሆን ፣ ይህንኑ አድኃሪ መዋቅር የሚተካውን ሕዝባዊ አስተዳደር በተሟላ መልኩ ለመገንባት እንደዚሁ መራራ ትግልንና ጊዜን ይጠይቃል ። ሕዝባዊ አስተዳደርን ከሥረ መሠረቱ ማጠናከር አስፈላጊ መሆኑንና ከዚህም ጋራ ለሕዝባዊ አስተዳደር መታገል ማለት ምን እንደሆነ ሌኒን የሶቭየትን ልምድ መሠረት በማድረግ ሲገልጽ ፣

Digitized by Google

Digitized by Google

--- ሥልጣን ለሶቭዬቶች (ለሰፊው ሕዝብ
የአስተዳደር አካላት) ማለት ፥ ማናቸው
ንም የዲሞክራሲያዊ አሠራርን የሚያፍነው
ቢሮክራሲያዊ መዋቅር ፥ አሮጌውን መንግ
ስታዊ መዋቅር ሥርነቀል በሆነ መንገድ
መለወጥ ማለት ነው ። ይህን መዋቅር አስወ
ግዶ በአዲስና በሕዝባዊ መዋቅር መተካት
ማለት ነው ። ይህም በሐቀኛ ዲሞክራሲያዊ
የሶቭዬቶች መዋቅር ማለትም ፥ በተደራ
ጀና በታጠቀ ሰፊ ሕዝብ ፥ በሠራተኛው ፥
በገበሬውና በወታደሩ ተወካዮች አስተ
ዳደር መተካት ማለት ነው ። ብዙኃኑ ተወካ
ዮችን በመምረጥ ብቻ ሳይወሰኑ በአስተዳ
ደርና በሌሎች ልዩ ልዩ ለውጥን በሚመለ
ከቱ ተግባራት እንዲሳተፉ ማበረታታትና
ሕዝቡ ራሱን እንዲችል መርዳት ማለት
ነው ።[16] ብሎ ነበር ።

ጆሴፍ ስታሊን የዛሩ መንግሥት ተገርስሶ
ሕዝባዊ አሠራር በሩስያ እንደሰፈነ የወዝ
አደሩ የበላይ ገዥነት የትግል ውጤት የሆነ
ውን የሕዝባዊ አስተዳደር ገጽታ እንደሚከ
ተለው አስቀምጦታል ።
--- የሙያ ማኅበራት የሠራተኛው መደብ
ሕዝባዊ ድርጅቶች እንደመሆናቸው በተለ
ይም ምርትን በሚመለከት የወዝ አደሩን
መደብ ፓርቲ ከመላው የወዝአደር መደብ
ጋር ያገናኛሉ ። በሰፊው ሕዝብ የተመረ
ጡ የአስተዳደር አካላት የሰፊው ሠርቶ አደ
ር ሕዝብ ሕዝባዊ ድርጅቶች እንደመሆናቸው
በወዝአደሩ ፓርቲ መሪነት ሰፊው ሕዝብ
በመንግሥት ሥልጣን ላይ ለሚኖረው ተካ
ፋይነት መሣሪያ ይሆናል። የኅብረት ሥራ
ማኅበራት በተለይም የገበሬው ሕዝባዊ
ድርጅቶች እንደመሆናቸው በቀድሚያ በኢ
ኮኖሚ ረገድ ሰፊው ገበሬ ሶሻሊዝምን
በመገንባት ረገድ የሚኖረውን ተሳትፎ በሚ
መለከት የወዝ አደሩን ፓርቲ ከገበሬው
ጋር ያገናኛሉ ። የወጣት ማኅበራት የወጣት
ወዛደሮችና ገበሬዎች ሕዝባዊ ድርጅቶች
በመሆን የወዝአደሩ ግንባር ቀደም ፓርቲ
አዲሱን ትውልድ በሶሻሊስት ትምህርት
ለማነጽና ወጣት ጆገናችን ለማሠልጠን
የሚያደርገውን ጥረት ያግዛሉ ፥ ያጠናክራ
ሉም ። በመጨረሻም እነዚህን ሁሉ ሕዝባዊ
ድርጅቶች የመምራት ተልዕኮ ያለበት የወዝ
አደሩ መደብ ፓርቲ በወዝአደሩ መደብ የበ
ላይ ገዥነት ወቅት አመራርን የሚይዝ ኃይል
ይሆናል ። እንግዲህ በአጠቃላይ የበላይ ገዥ
ነት ሥልጣን - የወዝአደሩ መደብ የበላይ
ገዥነት አሠራር የሚኖረው መልክ ይህ
ነው ።[17]

ከላይ እንደተመለከተው ሕዝባዊ ድርጅ
ቶችና በአሠራር ከእነዚህ ጋራ የተያያዙ ሌ
ሎች ድርጅቶች ለአሮጌው መንግሥታዊ
መዋቅር መፈራረስ የሚያበረክቱት አስተ
ዋጽኦ ወሳኝ ነው ። በዚህም ቢሮክራሲው
በሕዝባዊ አስተዳደር እንደሚተካ ጥርጥር
የለውም ። ሕዝባዊ አስተዳደር የበለጠ ጥራ
ትና ጥንካሬን በማግኘት ደረጃ በደረጃ እያ
ደገ ሲሄድ የአድሃሪው መንግሥት ርዝራዥ
የሆነው ቢሮክራሲ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ወደ
መደምሰሱ ያመራል ። ይሁን እንጂ ሕዝ
ባዊ አስተዳደር መሠረት በተጣለ ማግስት
ይህ አስተዳደር በሚያካሂዳቸው የኢኮኖሚ ፥
የፖለቲካና የማኅበራዊ ጉዳይ ሥራዎች ላይ
በቀድሞው የመንግሥት መዋቅር ውስጥ
ተሰጥተው የነበሩ ቢሮክራቶች በየደረጃው
በሚዋቀሩት መንግሥታዊም ሆነ ሕዝባዊ
ድርጅቶች ውስጥ ሰርገው መግባታቸው
አይቀርም ። እነኝህ ቢሮክራቶች ወገናዊ
ነት የጐደለውን አሠራር የሚከተሉና
የአድሃሪውን የአሠራር ሥርዓት የሚናፍቁ
እንደመሆናቸው እንቅስቃሴያቸውን በቅ
ርብ መከታተሉ የአብዮታውያን ሁሉ ግዴታ
ነው ። ሌኒን ይህን እንደመሆናቸው በሚመ
ለከት ሲጽፍ ፦—

... ካፒታሊስቶች የወዝአደሩን መን
ግሥት ኃያልነት እንዲገነዘቡና ይህን
መንግሥት ፊት ለፊት ለመቃወምና
ለመቋቋም ያላቸውን ከንቱ ምኞት እን
ዲተው ማድረግ ብቻ በቂ አይደለም ።
በረቀቀ ሁኔታ ውስጥ ውስጡን የሚካሄ
ዱት ተቃውሞ መከሸፍ ይኖርበታል ።
የተለያዩ መልኮችን የያዙ ተቃውሞዎችን
በማክሸፍ ብቻም ውሉን መሆን የለብንም።
ካፒታሊስቶች በአዲሱ መንግሥታዊ መዋ
ቅር ውስጥ በጥንቃቄ እንዲያገለግሉ
ማስገደድ ጭምር መቻልም ይኖርብናል ።
ካፒታሊስቶችን (ከመንግሥት ሥልጣ
ን) አናባርራለን። ይሁንና የማያስፈልጉት
ንና የማይታረሙትን ክፍሎች ካስወገድን
በኋላ ሌሎቹ ለአዲሱ መንግሥት እንዲያ

Digitized by Google

ገለገሉ ልንቀጥራቸው ይገባል። ይህ ለሠ
ራር በካፒታሊስቶች ፣ በቡርዧ ምሁራን
በቢሮ ሠራተኞችና በመሳሰሉት ላይ ተፈ
ጻሚነት ይኖረዋል ።[18]

የካፒታሊስት ሥልተምርት በተሟላ መ
ልኩ ባልዳበረባቸው ፣ የሕዝቡ አብዛኛው
ክፍል ማንበብና መጻፍ በማይችልባቸው ፣
የባሕል እድገታቸው ዝቅተኛ በሆነና ከኢሳ
ይንሳዊ አስተሳሰቦች ጋር በተዳቀለባቸው ፣
የተማሩ ባለሙያዎች በአብዛኛው ከገዥ መደ
ቦች አካባቢ የተገኙ በሆኑባቸው አገሮች አብ
ዮት ተካሂዶ የአድሃሪው መንግሥት ቢሮክ
ራሲ ቢሰባበርም ፣ የዚህ አድኃሪ ሥርዓት
ርዝራዦች በቅጽበት አይወገዱም ። ነገር
ግን ካፒታሊዝም በሰፈነባቸውና የወዝአደሩ
መደብ ስፋት ፣ ድርጅትና ጥንካሬ ከፍተኛ
በሆነባቸው ኅብረተሰቦች ውስጥ የመንግሥ
ትን አውታር በሕዝባዊ አስተዳደር ለማጠ
ናከር የሚደረገው ትግል በከፊል ፊውዳልና
ከፊል ካፒታሊስት ኅብረተሰብ ውስጥ ከሚ
ደረገው ትግል ይልቅ ቀላል መሆኑ አይካ
ድም ። ምክንያቱም የሳይንስና የቴክኖሎጂ
የዕድገት ደረጃ ፣ የአስተዳደር ሳይንስ መስ
ፋፋት ፣ የወዝአደሮች የንቃትና የዕውቀት
ደረጃ አሮጌውን አውታር በአዲስ ለመተካት
ለሚደረገው ትግል አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠር
ስለሚያደርግ ነው ። ሌኒን ቢሮክራሲን የመ
ደምሰስ ተግባር በሚመለከትና በተለያዩ
የዕድገት ደረጃዎች የአሮጌው መንግሥት
አውታሮች ምን እንደሚመስሉ እንደሚ
ከተለው ገልጿል ።

ሥር የሰደደ ቢሮክራሲያዊና ጪቁኝ የቡ
ርዧ መዋቅር ከመሠረቱ እንዲገረሰስ አድ
ርገናል ። . . . ወንዶች ብቻ ሳይሆኑ እጅግ
ኋላቀር ከሆነው የኅብረተሰብ ክፍል የሚ
ገኙ ሴቶችም ካለምንም ልዩነት የሚሳተ
ፉባቸውን አካሎች መስርተናል ። ቢሆን
ም . . . በመንግሥታዊ ሥራዎች ከነበሩ
ሠራተኞች መካከል . . . አስቸጋሪ ቢሮክ
ራቶች ይገኛሉ ። እነዚህን ቢሮክራቶች
በታተንን ፣ ለዋወጥን ፣ በአዲስ ሥፍራ
ልናስቀምጣቸው ሞከርን ። ይሁን እንጂ
እነዚህ የዛሩ ቢሮክራቶች በሕዝባዊ አስተ
ዳደር አካላት ውስጥ ሾልከው መግባትና
ቢሮክራሲያዊ አሠራራቸውን ማራመድ ፣
የኮሚኒስት ካባ ማጥለቅ ፣ ለሹመትና ለደ
ረጃ ዕድገት የተሻለ ዕድል በማግኘት ተራ
ማጅ መምሰል ፣ እንዲሁም ደግሞ በሩሲያ
ኮሚኒስት ፓርቲ ውስጥ የአባልነት ካርድ
ለማግኘት በፓርቲው ውስጥ ሰርገው መ
ግባት. . . ጀመሩ ። ይህም በመሆኑ ፣ በበር
በኩል ተገፍትረው ከወጡ በኋላ እንደገና
ተመልሰው በመስኮት በኩል ሾልከው እየ
ገቡ ነው ። እንግዲህ ትልቁ ችግራችን ይ
ህን ለመቆጣጠርና ለማክሸፍ የሚያስችል
ብቃትና ልምድ ያለው ኃይል ሊኖረን አለ
መቻሉ ነው ። እነዚህ ቢሮክራቶች ከሥ
ፍራቸው ይነሱ ይሆናል ። ይሁን እንጂ በ
አንድ ጊዜ ሊገሩ አይችሉም ። እዚህ ላይ
በተለይም የድርጅት ፣ የባህልና የትምህ
ርት ችግሮች እንደገጠሙን ግልጽ ነው ።
ቢሮክራሲን እስከመጨረሻውና እስከወ
ሳኙ ድል ልንዋጋው የምንችለው ሠራተ
ኛው ሕዝብ በመንግሥታዊ አስተዳደር
ሲሳተፍ ብቻ ነው ። . . . እዚህ ላይ ደጋ
ግሚ እንዳመለከትኩት በመንግሥት ሥራ
ላይ የተሳተፈው የሠራተኛው መደብ ክፍ
ፍል በጣም አነስተኛ በመሆኑ ዛሬ በቢሮ
ክራሲው ላይ ወሳኝ ድልን የመጐናጸፉ
ተግባር አስቸጋሪ ነው ። የሠራተኛውን
መደብ በማስተማሩ ረገድ ዕድገት ማሳየት
የሚቻለው በትምህርት ቤቶች ውስጥ ብቻ
ባለው ትምህርት ሳይሆን ትምህርትን ሰፊ
በሆነ ትርጉሙ በመውሰድ ነው ። ... ግን
የሕዝቡ የንቃትና የባህል እድገት ደረ
ጃ ስላልዳበረ ቢሮክራቶች የቀድሞ ቦታቸ
ውን ይዘው ይታያሉ ። ይህን ማስቀረትና
ሙሉ ድልን መቀዳጀት የሚቻለው ወዝ
አደሩና ገበሬው አሁን ከሚገኙበት በ
ላይ ሲደራጁና ሠርቶ አደሮችን በመንግ
ሥት ሥራዎች ውስጥ በማሳተፍ ረገድ ቁ
ርጠኛ ርምጃዎች ሲወሰዱ ብቻ ነው ።[19]

Digitized by Google

ቢሮክራሲውን የመደምሰሱ ተግባር፣ አር
ጌውን የመንግሥት ጭቆና አውታር በአዲ
ስና ሕዝባዊ ወገናዊነት ባለው መዋቅር የመ
ተካቱ ትግል ፣ ሌኒን እንደአመለከተው በተ
ለይም ቀድሞውኑ ካፒታሊስት ዕድገታቸ
ውን ባላገባደዱ ኅብረተሰቦች ውስጥ እጅግ
አድካሚና መራራ ነው ። ይሁን እንጂ የአ
ድኃሪ ሥርዓት መገልገያ የነበረውን መንግ
ሥታዊ መዋቅር ከመሠረቱ ማፈራረስ የሶ
ሻሊስት አብዮት ዋንኛው የትግል መስክ
ነው ።

በማኅበራዊ አብዮት ወቅት አብዮታው
ያን በቢሮክራሲያዊ አሠራር የተገነባውን
የበዝባዥ መንግሥት መዋቅር ለመደምሰስ
እንዲችሉ ችኩልነትን ፣ «ግራ» ቀደምትነ
ትን ፣ ለመራራው ትግል ተገዥ አለመሆንን፣
በረጅሙና በአድካሚው የትግል ጉዳና ለመ
ጓዝ አለመቻልን መዋጋት አለባቸው። አር
ጌውን ሥርዓት አፍርሶ በአዲስ የመተካቱ
ተግባር ውስብስብ ቢሆንም፣ አሮጌ መዋቅር
ከተገረሰሰ አገር የማይኖር የሚመስላቸው፣
የሰፊው ሕዝብ ታሪክ ሠሪነት የማይዋጥላቸ
ውና የሕዝባዊ አስተዳደር አካሎችን ደካማ
ጎን አጋንነው የሚያዩትን ጭምር መዋጋት
ተግባራቸው ሊሆን ይገባል ።

በአብዮቱ ሂደት ው ስ ጥ በሕዝቡ ላይ
ማሾፍ ፣ የሚያደርጋቸውን ሁሉ ማንኳሰስ
የሚወዱ አስመሳዮችና ወላዋዮች ብቅ ማለ
ታቸው የማይቀር ነው ። ሌኒን ይህንን
ሁኔታ በማስመልከት ሲጽፍ ፣

ወላዋዮች ሁሉ ከታሪክ መማር ይኖርባ
ቸዋል። 'አሮጌውን የምንተካበት መዋቅር
የለንም' በማለት እየተንሸራተቱ ከቡር
ዧው ጉን የሚቆሙ ሁሉ ሀፍረት ሊሰማ
ቸው ይገባል ። አሮጌውን የምንተካበት
መዋቅር አለ ። አዲሱ መዋቅር ሕዝባዊ
መዋቅር ነው ። የሰፊውን ሕዝብ የመፍ
ጠር ችሎታና ራስን የመቻል ተሰጥኦ አተ
ፍሩ ። በአብዮታዊ ድርጅቶቻቸው ላይ
እምነት ብታሳድሩ ወዛደሮችና ገበሬዎች
ተባብረው በተነሱበት ወቅት ያሳዩትን ጥን
ካሬ ዛሬም ልትመለከቱት ትችላላችሁ ።
. . . በሕዝቡ እምነት ማጣት ፣ የሕዝቡን
የፈጠራ ችሎታና ራስን መቻል መፍራት ፣
በሕዝቡ አብዮታዊ ኃይል መደናገጥና
ይህን ኃይል አለመደገፍ የሶሻሊስት አብ
ዮታውያንና የሚንሼቪክ መሪዎች ኃጢአ
ት ነው ። አፋጣኝ ውሳኔዎችን ለመስጠት
አለመቻላቸው ፣ ወላዋይነታቸው ማስመሰ
ላቸውና ፍሬቢስ ሙከራቸው የሚመነጨ
ው ከዚሁ ነው ። [20] በማለት ገልጾታል ።

አንድ ማኅበራዊ አብዮት እንደፈነዳ ኅብ
ረተሰቡ ይጨቁነው የበረውን መዋቅር መ
ፈራረሱ የማይቀር ነው ። ሕዝባዊ አብ
ዮት እየጐለበተ ሄዶ በሁለት እግሩ እስ
ከቆመ ድረስ የአብዮቱ ወላፈን ያልነካቸው
ያረጀውና ከታዳጊ የምርት ግንኙነት ጋር
እኩል መራመድ የማይችለው የካፒታሊ
ስቱ ፣ የፊውዳሉ ወይንም የፊውዶ ቡርዧ
ው ቢሮክራሲ አባላት አድብተው ይቆ
ያሉ ። እነዚህ ለሕዝባዊ አብዮት ታማኝነት
የሌላቸው ግለሰቦች በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ
በመጠቀም አብዮቱ እንዲቀለበስ የማይሸር
ቡት አሻጥር የለም ። በዘመናችን የተቀለ
በሱ አብዮቶችና የአብዮቱ ደጋፊ በሆኑ ኃይ
ሎች ላይ የደረሰው አሰቃቂ ጭፍጨፋ የእ
ነዚህ አድኃሪ ኃይላት ሴራ ውጤት ለመሆኑ
የሚያጠያይቅ አይደለም ። በሌላ በኩል ከቀ
ድሞው ሥርዓት በተወረሰው ቢሮክራሲ
ውስጥ የነበሩ ግለሰቦች ከወደቀው አድ
ኃሪ የገዥ መደብ ጋር በጥቅምና በርዕዮተ
ዓ ለ ም የተሳሰሩ በመሆናቸው ለአብዮቱ
በታማኝነት ለመቆም ያላቸው ፍላጐት
እጅግ ዝቅተኛ ነው ።

የአንድ አድኃሪ የገዥ መደብ ቢሮክራሲ
ለአንድ ሕዝባዊ አብዮት ወደፊት መራመድ
ሊያበረክት የሚችለው ሕዝባዊ አሠራር

Digitized by Google

አይኖርውም ። የታሪካዊ ቁስአካልነት ጽንሰ ሀሳብ እንደሚያስገነዝበን፣መንግሥትና አውታሮቹ የተመሠረቱት በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ባሉ ሊቻቻሉ በማይችሉና በመደብ በተከፋፈሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል በሚመነጩ የማይታረቁ ቅራኔዎች ምክንያት ነው ። እነዚህን በመሳሰሉ በመደብ በተከፋፈሉ ኅብረተሰቦች በተለይ የገዥው መደብ የራሱን የፖለቲካ ፣ የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ጥቅሞች ለማስከበር የመንግሥትን አውታሮች ለመገንባት ይገደዳል ። በመሆኑም ተፃራሪ መደቦች ባሉባቸው ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ መንግሥትና የመንግሥት አውታሮች ተብለው የሚታወቁ መዋቅሮች የሰው ልጅ በመደብ ከተከፋፈለበት ጊዜ ጀምሮ የገዥውን መደብ ጥቅም በመጠበቅ ሕዝቡን ሲጨቁኑ ፣ ሰብአዊ መብቱን ሲረግጡና ሲያጕሳቁሉ ኖረዋል ። እነዚህ የበዝባዥ መንግሥት አውታሮች በአንድ ማኅበራዊ አብዮት ፍንዳታ ወቅት የሠራተኛውን መደብ ጥቅም የሚጠብቁና የበላይነቱንም የሚያረጋግጡ አይደሉም ። በመሆኑም ወገናዊነትና ሕዝባዊ አሠራር ባለው አውታር መተካታቸው አስፈላጊና አማራጭም የሌለው ነው ። ይህ ኅብረተሰቡን የሚጨቁነው አውታር ከፈራርሰና ወገናዊነት ባለው ሕዝባዊ አሠራር ከተተካ ኅብረተሰቡ የአዲስ ባሕል ባለቤት እንዲሆን አመቺ ሁኔታን ይፈጠርለታል ።

የግሌ ማይንስ እንደሚያስገነዝበው ቢሮክራሲያዊ አሠራርን ለማስወገድ የሰፊውን ሕዝብ ባሕል ማሳደግ፣የነቁ ሠራተኞችንና ገበሬዎችን በመንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ በተለያየ ደረጃ እንዲሳተፉ ማድረግ አማራጭ የለውም ። ከሁሉም በላይ ሰፊው ሠራተኛ በአስተዳደር ሥራ እንዲሳተፍ አመቺ መንገድ ሊቀየስበት ይገባል ። ወደዚህ ዘላቂ ግብ ለመድረስ እንዲቻልም አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር አስፈላጊ ነው። ከዚህ አንፃር ፣ ለመንግሥት አገልግሎት የሚመረጡ ኃላፊዎች ምልመላ በችሎታ ፣ በፖለቲካ ዝንባሌና ለአብዮቱ ባላቸው ታማኝነት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ፣ ለመንግሥት አገልግሎት የሚመጥኑ የሠርቶአደሩ ወገኖች ለአስተዳደር ብቁ ሆነው ሊሰለጥኑ የሚችሉበት ሁኔታ መመቻቸቱ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው ። የመንግሥት አውታር ሕዝባዊ መሠረት እንዲኖረው ማድረግ፣ የሕዝባዊ ድርጅቶችን አስተዳደራዊ ድርሻ ማሳደግ፣ እንደዚሁም የሕዝባዊና የመንግሥታዊ ድርጅቶች አሠራር የሚቀናጅበትን መንገድ በመቀየስ እንዲደጋገፉና እንዲተጋገዙ ማድረግ አስፈላጊ ነው ።

ሕዝባዊ አገልግሎት በሚሰጡ መንግሥታዊ ፣ ሕዝባዊ ተቋሞችና አካሎች ውስጥ የተሰገሰጉና ለግል ጥቅማቸው የቆሙ ፀረ አብዮት ኃይሎችን ስውር ደባ በየወቅቱ መከታተል ፣ ሥራና ሠራተኛን ማገናኘት ፣ የድርጅቶች አቋምና የሥራ አመራር እንዳይንዛዛ ቁጥጥር ማድረግ ፣ በመንግሥት አስተዳደር የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን የአሠራር ባሕል ማዳበር የሚተኰሩባቸው ጉዳዮች ናቸው ።

Digitized by Google

የግርጌ ማስታወሻ

1. Mohit Bhattachanya, Public Administration, St. Ructure, Process and Behaviour, (The World Press Private Ltd., New Delhi, 1981), p. 44.
2. Encyclopedia Britannica, Vol. 3, 1979, p. 485.
3. Great Soviet Encyclopedia, Vol. 4, (MacMillan, Inc., New York, 1974), p. 183.
4. Karl Marx and Frederic Engles, Selected Works, Vol. 1, p. 477.
5. Draper Hal. Karl Marx's Theory of Revolution, Volume I: State and Bureaucracy, (Monthly Review Press, New York, 1977), p. 497.
6. *Ibid.*, 485.
7. የቢሮክራሲያዊ አሠራር ምንጩና የማስወገጃ ዘዴው፣ ሠርቶ አደር፣ ቅጽ 4፣ ቁጥር 121፣ ታህሣሥ 14 ቀን 1975፣ ገጽ 3።
8. ከላይ የተጠቀሰው
9. Great Soviet Encyclopedia, Vol. 4, p. 184.
10. Karl Marx and Frederic Engles, Selected Correspondence, (Progress Publishers, Moscow, 1975), p. 247.
11. Karl Marx and Frederic Engles, Selected Works, Vol. 2, p. 187.
12. V.I. Lenin, Collected Works, Vol. 25, (Progress Publishers, Moscow, 1974), p. 393.
13. V.I. Lenin, Collected Works, Vol. 30, (Progress Publishers, Moscow, 1965), p. 237.
14. V.I. Lenin, Collected Works, Vol. 25, p. 430.
15. V.I. Lenin, Collected Works, Vol. 30, p. 264.
16. V.I. Lenin, Collected Works, Vol. 25, p. 372.
17. J. Stalin, On Opposition, (Foreign Languages Press, Peking, 1974), p. 291.
18. V.I. Lenin, Collected Works, Vol. 26, (Progress Publishers, Moscow, 1964), p. 109.
19. V.I. Lenin, Collected Works, Vol. 29, (Progress Publishers, Moscow, 1964), pp. 182-84.
20. V.I. Lenin, Collected Works, Vol. 25, p. 374.

Digitized by Google

ሕግ በሽግግር ወቅት

ግህሉ ወ/ጊዮርጊስ

የሕግ አመጣጥና ዕድገት

የኅብረተሰብን ታሪካዊ ዕድገት ሳይንሳዊ
በሆነ መንገድ ለመመርመር ፤ ለመተንተንና
ከትክክለኛ ማጠቃለያ ላይ ለመድረስ ማር
ክሲዝም ሌኒኒዝም አማራጭ የማይገኝለት
ዓይነተኛ መሣሪያ ሆኖ ከቀረበና ተቀባይነ
ቱም ከተረጋገጠ ዓመታት አልፈዋል ።

ይህ ትክክለኛና ዛሬ በቢሊዮን ለሚቆጠሩ
ሠርቶ አደሮች በመመሪያነት እያገለገለ የሚ
ገኝ የኅብረተሰብ ሳይንስ የሰው ልጅ ሕል
ውና መሠረት ለሆነው የማምረት ተግባርና
በዚሁ ምክንያት በሰዎች መካከል ለሚፈ
ጠረው ኢኮኖሚያዊ (የምርት) ግንኙነት
የተለየ ግምት ይሰጣል ። በኅብረተሰብ ሕይ
ወት ውስጥ በማምረትና በማከፋፈል ሂደት
ውስጥ የሚፈጠሩ ግንኙነቶችን ባሕርያት
ለይቶ ማወቅ ኅብረትሰብን በሚገባ ለመረ
ዳት መነሻ መሠረት መሆኑን የማሌ ሳይንስ
አበክሮ ያስገነዝባል ።

ሰዎች በማምረትና በማከፋፈል ሂደት
ውስጥ የሚፈጥሩአቸው ግንኙነቶች ደግሞ
ታቅደው ፣ ሆን ብለው የሚከናወኑ ሳይሆን
ከፍላጐት ውጭና በማይቀር ሁኔታ የሚፈጠ
ሩና የሚመጡ ግንኙነቶች ናቸው ። ይህ የም
ርት ግንኙነት ሰዎች በማምረቻ መሣሪያነት
ከሚጠቀሙባቸው የምርትና የማጓጓዣ መ
ሣሪያዎች የዕድገት ደረጃ ጋር በተገናዘበ
መልክ የአንድን ሥርዓተ ማኅበር ኢኮኖሚ
ያዊ አወቃቀር የሚገልጽ ድምር ሁኔታ ነው

በአንድ በተወሰነ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ
የሚገኝ ርዕዮተ ዓለም ፣ ፖለቲካ ፣ ባህል ፣
ሕግ ፣ ወዘተ … የዕድገት ደረጃ ፣ በዚህ የኢ
ኮኖሚ መዋቅር መሠረትነት ላይ የሚቀረጽ
ወይም የዚህ ነፀብራቅ ከመሆን አያልፍም።
ሕግ ከላዕላይ መዋቅር ፈርጆች አንዱ እንደ
መሆኑ አንፃራዊ ነፃነት ቢኖረውም ፣ በመጨ
ረሻ መሠረቱ በሆነው በኢኮኖሚው ላይ
ጥገኝነት እንዳለው የተረጋገጠ ነው ።

ለአንድን ኅብረተሰብ የሚፈጥረው ሕግ ሳይ
ሆን በተገላቢጦሽ ሕግን የሚፈጥረው ኅብ
ረተሰብ ነው ። የንብረት ግንኙነት

Digitized by Google

(property relations)የሚኖረው ኅብረትን የሚገልጽ ሕግ በመኖሩ አይደለም ። በተቃራኒው እነዚህ ደንቦች ከታሪካዊ ምንጫቸውና ከተከታታይ ዕድገታቸው በኢኮኖሚ ሥርዓቱ የተፈጠሩ ግንኙነቶች ነጸብራቅ ናቸው ። ሕግ ከኅብረተሰቡ ሶሽዮ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት የተገነጠለ ሊሆን ከተውንም አይችልም ።[1]

ይህ አባባል ሕግ በራሱ የተገነጠለ ታሪክ የሌለው መሆኑን የሚያበሥር ሲሆን ፣ የሕግ አፀናነስ ፣ አስተዳደግና አጠቃላይ ታሪካዊ ሂደቱ በየሥርዓተ ማኅበሩ ውስጥ ከሚገኙ የምርት ግንኙነቶች ዕድገት ታሪክ ጋር የተቆራኘ ነው ።

መንግሥትና ሕግ ሁለቱም ታሪካዊ መሠረት ያላቸውና ከአንድ ሶሽዮ ኢኮኖሚያዊ ሂደት ውስጥ የሚመነጩ ናቸው ። ማለትም ከሥራ መከፋፈል ፣ ከግል ሀብት መከሰትና ኅብረተሰብ በማይታረቁ መደቦች መካከል ከመከፋፈሉ የመነጩ ናቸው ።[2]

የሕግ ውስጣዊ ይዘት ፣ ዓላማው ፣ ሚናውና የአስፈጻሚ አካሎቹ በዚህ ባሕርይ ጥምር እንደ የሥርዓተ ማኅበሩ እንዲለወጥ የሚገደደውም ሌላ ተአምራዊ ምክንያት በመኖሩ ሳይሆን ሕግ ከራሱ ውጭ በሆነ ፣ ነገር ግን በሚመሠረትበትና ተፅዕኖም በሚያደርግበት በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት ላይ በሚደረጉ ለውጦች መሠረትነት የሚቀረፅ በመሆኑ ነው ።

ሕግ ከሁብረተሰብ እንቅስቃሴ ውጭ የሚፍጠር ተአምራዊ ጉዳይም አይደለም ። ሕግ በአንድ በተወሰነ መንግሥት ወይም በሕግ አውጭዎች በጐ ፈቃድ ላይ ብቻ የተመሠረተና ከዚህም የመነጨም አይደለም ። በማምረት ሒደት ውስጥ በሰዎች መካከል የሚፈጠሩ ግንኙነቶች በአንድ ቦታ ረግተው ወይም ቆመው የሚገኙ እንዳለመሆናቸው ሁሉ በነዚህ ውስጥ የሚታይ ለውጥ የሕግንም ይዘትና ቅርፅ የሚለውጠው ይሆናል ።

ዛሬ እንደየሥርዓተ ማኅበሩ ሁኔታ በይዘትና በቅርጽ ዳብሮ የሚታየው ሕግ ከላይ በተጠቀሰው መልክ ከመደቦች መከሰት ጀምሮ ከዝቅተኛ ደረጃ አንሥተው ከምርት ኃይሎች ጐን ለጐን እያደጉ የመጡት የምርት ግንኙነቶች የጋበዙትና በየዘርፉ ከተደረጉ የዕድገት ሒደቶች ጋር እየተገናዘበ የመጣ ነው ።

ይህም ማለት ሕግ ከሃይማኖትና ከሌሎች በተለምዶ በመታወቃቸው ሲከበሩ ከነበሩ ጉዳዮች ተገንጥሎ በሥርዓትነቱ የታወቀው ከመደብ መከፋፈል ጋር ሲሆን ፣ ዕድገቱም በባሪያ አሳዳሪ ዘመን በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ በማንፀባረቅ ፣ በፊውዳሉና በካፒታሊዝም ዘመንም የእነዚህ ሥርዓተ ማኅበራት መሠረት በሆኑት የምርት ግንኙነቶች ላይ በመመሥረት የተቀረፀ ነው ።

የሶሻሊዝም አሸናፊነት እውን ሆኖ ሥርዓቱን በመገንባት ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሱ አገሮችም ሕግ የጋራ ባለሀብትነትን ዕውን በአደረገው በኢኮኖሚው መሠረት ላይ የተመረኮዘ ዕድገትን በማንፀባረቅ ለሰው ልጆች እኩልነትና የጋራ ብልጽግና መስፈን የሚያገለግል መሣሪያ መሆኑን አረጋግጧል ።

ሕግና መንግሥት

ስለሕግ አመጣጥና ዕድገት በአጭሩ በሚያወሳው ከላይ በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ እንደተጠቀሰው መንግሥት በመባል የሚታወቀው ክስተትም ያለአንድ ምክንያት እንዲያው ከሰማይ ዱብ ያለ ነገር አይደለም ።

የምርት መገልገያዎች በጋራ ባለቤትነት ሥር በነበሩበትና የምርት ውጤትም የኅብረተሰቡ የጋራ ሀብት በነበረበት በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሰው ልጅ «መንግሥት» የሚባል አካል ሳያስፈልገው ኑሮውን መምራት ይችል እንደነበር በታሪክ ጥናት የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ፣ ዛሬም ቢሆን የዚህ ሥርዓት ቅሪቶች በሚገኙበት አካባቢ ይህ ሁኔታ በግልጽ የሚንፀባረቅ ነው ።

Digitized by Google

የምርት ኃይሎች ዕድገት ፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተፈጠረው የሥራ ክፍፍል ባለሀብቶችና ሀብት አልባ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች እንዲፈጠሩ መነሻ ምክንያት ሆነ ። በነዚህ ኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል የተፈጠረው ልዩነት ተፃራሪነት ያላቸውን ቅራኔዎች በማስከተሉ መንግሥት እነዚህን ቅራኔዎች ለማጥፋት ሳይሆን የባለሀብቶችን ጥቅም ለማስከበር በሚችል መልኩ ተከሰተ ። ይህም መንግሥት የገዥ መደብ መሣሪያ ሆኖ ተወለደ ማለት ነው ።

ፍሬደሪክ ኤንግልስ ስለመንግሥት አመጣጥ ሲገልጽ የሚከተለውን ብሎ ነበር፣—

በኢኮኖሚ ሁኔታዎች መናር አስገዳጅነት በነፃ ሰዎችና በባሪያዎች፣በበዝባዥ ሀብታሞችና በተበዝባዥ ደሀዎች መካከል የተከፈለ፣ እነዚህን ቀራኔዎች ለማስታረቅ የማይችል ብቻ ሳይሆን ቀራኔዎቹ ይበልጥ ሥር እየሰደዱ እንዲሔዱ ማድረግ የነበረበት ኅብረተሰብ ተፈጠረ። እንዲህ ዓይነቱ ኅብረተሰብ እነዚህ መደቦች እርስ በርስ በሚያደርጉት ግልጽና ያልተቋረጠ የመደብ ትግል ውስጥ ወይም ትግል ከሚያደርጉ መደቦች በላይ ሆኖ ግልጽ የሆነ ግጭታቸውን በመግታትና ሕጋዊ ቀርጽ ያለው የመደብ ትግል በኢኮኖሚ መስክ ብቻ እንዲካሔድ በመፍቀድ በሚያስተዳድር ሶስተኛ አካል ሥር መኖር ነበረበት ። የቤተሰባዊ አስተዳደር ጠቃሚነት አከተመ።የኅብረተሰብ በመደብ መከፋፈልን ባስከተለው የሥራ ክፍፍል ምክንያት ተበታተነ። የርሱም ቦታ በመንግሥት ተወሰደ።[3]

በዚህ መልክ ለመጀመሪያ ጊዜ መንግሥት ተከሰተ ሲባል ከኅብረተሰቡ ውስጥ በምርት መገልገያዎች ባለሀብትነት ምክንያት የበላይነት ሊቀዳጁ የበቁት ጥቂቶቹ የይዞታቸው ማስከበሪያ የሆኑትን ቋሚ ጦር ፣ የፖሊስ ኃይል ፣ የቤተ ክህነት አካላት ፣ የዳኝነት ተቋሞችና ሌሎች ልዩ ልዩ አውታሮችን መዘርጋት ጀመሩ ማለት ነው ።

የተጠቀሱት ልዩ ልዩ የመንግሥት አካላት አስፈላጊነት የመነጨው ከባለሀብቶች ጥቅም መከበር ጋር ተያይዞ በመሆኑ የአውታሮቹ የዕለት በዕለት ክንውን እነዚህኑ ጥቅሞች ከማስከበር ውጭ ሊሆን አልቻለም ነበር ። የሕግና የአስፈጻሚ አካሎች ተግባርም ገና ከአፀናነሱና በአለፈባቸው የዕድገት ሒደቶች ውስጥ ከዚህ ውጭ ሆኖ ሊታይ የሚችል አልነበረም ።

በመንግሥትና በሕግ መካከል የተሳሠረ ግንኙነት አለ ።

ሕግ. . . ከመደቦችና ከመንግሥት ጋር አብሮ ተከሰተ ። ሕግ የገዥውን መደብ ፍላጎት በሕግ ቀርጽ የሚገልጽ ነው ። በመሆኑም የገዥውን መደብ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶቸን የሚያንጸባርቅ ነው ።[4]

በተለያዩ ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ የሚኖሩ መንግሥታት ባሕርይ በሚኖሩበት የምርት ግንኙነት ላይ ተመሥርቶ የሚገለጽ የመሆኑን ያህል ሕግም በዚሁ ላይ የተመሠረተ ይዘትና ቅርጽ ኖሮት ለገዥ መደቦች እንደ አንድ ጥቅም ማስከበሪያ መሣሪያ የሚያገለግል ነው ።

ሕግ የሚገኝበትንና የተቀረፀበትን ሥርዓት ለመጠበቅ የሚቆም እንደመሆኑ የጥንታዊ ጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር ፈርሶ ቦታውን በመደቦች ለተከፋፈለ ኅብረተሰብ ከለቀቀበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር ድረስ ያለው ሕግ በይዘቱ በየሥርዓተ ማኅበሩ ውስጥ የነበረውን ያልተስተካከለ የንብረት ባለቤትነትን ሕጋዊነት ሲገልጽና ሲያጠናክር የቆየ ነው ።

በነዚህ ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ የነበሩትና ያሉት ሕጎች ሁሉ ለመንግሥታቱ መኖርና በኅብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ ሰፊ አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ ናቸው ። የመንግሥታትንም ፍላጎቶች ቀርፀው በመያዝ በኅብረተሰቡ በአጠቃላይ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ

Digitized by Google

ሲያገዙ የቆዩ ብርቱ የመንግሥት መሣሪያዎች ናቸው ። የሕግ ምንነት በገዥ መደቦች ቁሳዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጐት ላይ በመመስረቱና ለሁሉም ሕግ ሆኖ በመውጣቱ የሚገለጽ ነው [5] የሚባለውም ለዚሁ ነው ።

ሕግ በይዘቱ የገዥ መደቦችን ፍላጐት የሚያንፀባርቅ ፣ በተግባሩ የገዥ መደቦችን ጥቅም የሚያስከብርና የሚከላከል ፣ በባሕርዩ በሁሉም ላይ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ሆኖ የሚቀረጽ በመሆኑ ፣ በማንኛውም ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት አውታሮች ያለው መንግሥት ያወጣቸውን ሕጐችና ደንቦች የማክበርና የማስከበር ግዴታ ይኖርባቸዋል ። በአንፃሩም በሥርዓተ ማኅበሩ ውስጥ የሚገኙ የገዥ መደቦች ሕጉ ጥቅማቸውን የማያስጠብቅ መሆኑን ቢረዱም ለሕጉ ተገዥ እንዲሆኑ ይገደዳሉ።

የሕግ ምንነት በውል መታወቅ የሚችለው በዚህ ባሕርዩ በመሆኑ ለሕጉ መከበርና መፈጸም የሚቆሙ የተለያዩ አውታሮች መፈጠራቸው ግድ ይሆናል። የፍርድ ቤቶች፣ የፖሊስ ፣ የእሥር ቤቶች፣ወዘተ . . . አስፈላጊነት የሚመነጨውም በዚሁ ምክንያት ነው ። ሌኒን ይህን ሲያስገነዝብ ፣ «የሕግን ተፈጻሚነት ለማስከበር የሚችል ተቋም በሌለበት ሁኔታ ሕግ ምንም ማለት አይደለም » [6] ብሏል ።

በተወሰነ ኅብረተሰብ ውስጥ የበላይነትን የተቀዳጀው መደብ (የመንግሥትን ሥልጣን የጨበጠው) ጥቅሙን ለማስከበር የሚያስችል ሕግ እንዲወጣ የማድረጉን ያህል የወጣው ሕግ በሚገባ መፈጸሙንም ለማረጋገጥ በቂ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል ።

በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥትና በዚህም አማካይነት የወጣው ሕግ የጥቂት ባለሀብቶችን ጥቅም ለማስከበር የቆመ በሚሆንበት ሁኔታና የመደብ ትግሉ ይህን ለመለወጥ በሚካሔድ የሕዝብ ዓመፅ በሚከሰትበት ወቅት፣የነባሩ ሕግ ተፈጻሚነት እየላላ እንዲሔድ ይገደዳል ። በነባሩ መንግሥትና ሕግ መኖር ተጠቃሚ የነበሩ አስፈጻሚ አካሎች በሕዝብ ዓመፅና ግፊት እየላላ እንዲሔድ የሚገደደውን ሁኔታ ለማጥበቅ ሕጉንና ሌሎችንም የኃይል መሣሪያዎች ለመጠቀም ጥረት የሚያደርጉትን ያህል፣የሕዝብ ዓመጹ እንዲሠምር ትግል የሚያደርጉ ወገኖችም ለሕጉ መሻር ፣ ለነባሩ መንግሥት ኃይል መዳከም ይታገላሉ ። በሕግ አስፈጻሚ አካሎች ውስጥ ያሉ የሕዝብ ዓመፅ ደጋፊዎችም በሌላ ዘርፍ ከሚያደርጉት ተሳትፎ በተጨማሪ ነባሩን ሕግ ለዓመፅ በሚጠቅም መንገድ በመተርጐም ጭምር ወገናዊነታቸውን ያሳያሉ ፣ ለገዥው መደብ መውደቅ ሕጉንም ጭምር በመሣሪያነት እንዲያገለግል ያደርጋሉ ።

በሌሎች ዘርፎች ለሕዝባዊ ዓመፅ መቀስቀስ ምክንያት በሚሆኑ መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የሚደረገው ትግልና ውጤቱ በወቅቱ በሚኖረው ሕግ አፈጻጸም ላይ የተወሰነ ተፅዕኖ ማድረጉ የማይቀር በመሆኑ፣ የሕጉ አስፈጻሚዎችም ሚናቸውን ለይተው እንዲቆሙ የሚገደዱበት ሁኔታ ይፈጠራል ። ይህ በአጠቃላይ በማኅበራዊ ቀውስ መልክ የሚገለጽ ሁኔታ ነባሩንና አድኃሪ የሆነውን ሥርዓት በአዲስና በተራማጅ ሥርዓት ለመተካት የሚካሔድ ትግልን የሚገልጽ በመሆኑ የሕጉ መጣስ ፣ የአፈጻጸሙ መላላትና በሕዝባዊ ዓመጹ እየተሸፈነ መሔድ ወደ ተሻለው ለመራመድ የሚያስችል ሁኔታን የሚያሳይ በመሆኑ ከአብዮታዊው እንቅስቃሴ አንፃር በገንቢነት የሚወሰድ ችግር ይሆናል ።

> ሕግንና ሕጋዊ አሠራርን ተግባራዊ ለማድረግ እምቢተኛ መሆን ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ርዕዮተዓለማዊና ሥነ ልቡናዊ ባሕርይያለው ከፍተኛ ውጤትን የሚያቀፍ፣ ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣንን የሚያዳክምና ነባሩን ሥርዓት በአብዮታዊ ግፊት ለመጣል ከሚያስችሉ ቀድመ ሁኔታዎች አንዱን የሚፈጥር ይሆናል ፣ [7]

Digitized by Google

በማለት በሕግ አፈጻጸም ላይ የሚገጥም ቀውስን ጠቃሚነት ጃ ዊስች አል ኤስ የተባለው የሕግ ሊቅ ገልጾአል ።

እንዲህ ዓይነቱ የሕግ አፈጻጸም መላላት ሌላ ቅርፅና ይዘት ኖሮት በጐጂነት ባሕርዩ ሊከሰት ይችላል ። የመንግሥትን ሥልጣን የጨበጠው ወገን የአብዛኛውን ሠራተኛ ሕዝብ ጥቅም ለማስከበር የቆመ በሚሆንበት ጊዜ ፣ የሕግን ቅርጽ ይዘው የሚወጡ ወይም የሕግነት ጠባይ ያላቸው መመሪያዎች ሁሉ የሚነደፉት፣የሠራተኛውን ሕዝብ መብት ለማስከበርና ለዚህ ተግባራዊ መሆን የቆሙ ወገኖችን ከማናቸውም ጥቃት ለመከላከል ፣ መንግሥት የቆመለት የሩቅ ዓላማ ከግቡ እንዲደርስ ለማገዝ የሚወሰዱ መሠረታዊ ርምጃዎች እንዲከበሩ ለማድረግ የሚያስችሉ ይዘት እንዲኖራቸው እየተደረገ ነው ።

በአፈጻጸምም ቢሆን ይህ መሠረታዊ ጉዳይ ሊዘነጋ የሚችል መሆን የለበትም ። ሕግ በይዘቱ ለሠራተኛው ሕዝብ የቆመ በአፈጻጸሙ ግን የሠራተኛውን ሕዝብ ጥቅም የሚፃረር እንዲሆን ከተደረገ ይህ ሁኔታ በተከሰተባቸው የመንግሥት አካሎች ውስጥ ያሉት ይህንን ተግባር የሚያከናውኑት ግለሰቦች አውቀውት ሆነ ሳያውቁት ከአዲሱ ሥርዓት ተፃራሪ ኃይሎች ጋር የተሰለፉ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው ። ሕግና ከዚህ ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ አውታሮች እንደሁኔታው ለአብዮታዊ እንቅስቃሴ ዕድገት ወይም በተፃራሪው በእንቅፋትነት ሊቆሙ የሚችሉ በመሆናቸው ከላይ በተጠቀሰው መልክ የሚፈጠረው ችግር ፀረ አብዮትን የሚያግዝና ለአብዮቱ መራመድ የቆመውን መንግሥት ለማዳከም አስተዋጽኦ የሚያደርግ ይሆናል ።

በልዩ ልዩ የመንግሥት አውታሮች ውስጥ የሚገኙ አካላትና ባለሥልጣኖች ለሠራተኛው ሕዝብ መብት መከበርና ለዕድገቱ መፋጠን የሚረዱ ሕጎችን ራሳቸው እየፈጸሙት መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይና በሥራ መስካቸው በሚገባ መፈጸማቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል ። በሕጉ መፈጸም ተጠቃሚ የሚሆነው የኅብረተሰብ ክፍል በአመራር ሰጭው ክፍል ላይ ያለው እምነት እንዲጠነክር ለማድረግ ከሚያስችሉ ሁኔታዎች መካከል አንዱ የዚህ ሁኔታ ተሟልቶ መገኘት ነው ። በመንግሥትና በሕግ መካከል ያለው ተደጋጋፊነትም መንፀባረቅ ከሚችልባቸው መንገዶች መካከል አንዱ የመንግሥት አውታሮች ለሕጉ መከበር ቆመው መገኘታቸው መረጋገጡ ነው። ለመንግሥት ሕግ መከበር መቆም ማለት በሌላ ገጹ ለመንግሥት ፖሊሲዎች መፈጸምና መንግሥት ለቆመለት መደብ ጥቅም መከበር መቆም ማለት ነው ።

ሕግና መንግሥት ያንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች እንደመሆናቸው ያንዱ ህልውና መከበር ለሌላው መሠረት ነው ። « የመንግሥት እንቅስቃሴ ቀጥተኛ በሆነ መንገድ በሕጐች ይገለጻል ---ሕጐችና ድንጋጌዎች ከሁሉም ግልጽ በሆነ መንገድ የገዥ መደብችን ፍላጐቶች ያንፀባርቃሉ ። »[1] የመንግሥትና የሕግ ግንኙነት የተመሠረተው ሁለቱም የአንድ መደብን (የገዥ መደብ) ጥቅምና ፍላጐት የሚያራምዱ በመሆናቸው ነው ። በመሆኑም ሕግ የመንግሥትን ሕልውና ይጠይቃል ፣ መንግሥትም በበኩሉ ተግባሩን በሚገባ ለማከናወን የሕግን መኖር ይፈልጋል ፤ ሁለቱም ተደጋግፈው ይኖራሉ እንጂ አንዱ ከሌላው ተነጥሎ ሕልውናው ዘለቄታን ሊያገኝ አይችልም

የአብዮት ወቅት ፖለቲካና የሕግ ሚና

የሶሻሊስት ሥርዓተን በአንድ የተወሰነ አገር ለማስፈን የሚካሔድ አብዮታዊ እንቅስቃሴ በአንድ የተወሰነ ወቅት ተጀምሮ ወዲያውኑ የሚጠናቀቅ ተግባር አይደለም ። ትግሉ አጠቃላይ የዕድገት ሕግጋትን ተከትሎ የሚራመድ ቢሆንም እንቅ

Digitized by Google

ሲቃሴው በሚካሔድበት ወቅት በአገሪቱ ውስጥ ባሉት ነባራዊና ሕሊናዊ ሁኔታዎች፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው አጠቃላይ እንቅስቃሴ በሚያደርግበት ተፅዕኖ ላይ በመመሥረት የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎችን በየጊዜው በማለፍ የሚከናወን የረዥም ጊዜ ሂደት ነው ።

የአብዮታዊው እንቅስቃሴ መሠረታዊ ዓላማ ነባሩንና አድኃሪውን የምርት ግንኙነት ማፈራረስና በምትኩ የላቀውንና የሕዝቡን የጋራ ብልፅግና ለማስፈን የሚያስችለውን ሥርዓት ለመመሥረት እንደመሆኑ፣ በአብዛኛው ሠራተኛ ሕዝብ ድጋፍ ላይ የተመሠረተ ይሆናል ። ሆኖም አድኃሪውን የምርት ግንኙነት ለመጠበቅ የተዋቀሩት የመንግሥት ዘርፎችና በሥርዓቱ ዕድሜ መራዘም ተጠቃሚ የሚሆኑ ወገኖች ሁሉ ይህን ዓላማ በመፃረር መቆማቸው ሊቀር የማይችል እውነታ ነው ።

የሽግግሩ ወቅት ትግል ዓላማ ከላይ የተጠቀሰውን በረዥም ጊዜ ሂደት ሊደረስበት የሚችለውን ሥርዓት ለመገንባት ቢሆንም ትግሉ በይፋ የሚጀምርበት ታሪካዊ ሁኔታ ይኖረዋል ። የማሌ ሳይንስ እንደሚያስተምረው ማንኛውም አብዮታዊ እንቅስቃሴ የሚፀነሰው በነባሩ ሥርዓተ ማኅበር ማኅፀን ውስጥ ነው ። ለፅንሱ መነሻ ምክንያት የሚሆነውም በሥርዓተ ማኅበሩ ውስጥ በሚኖሩ ተፃራሪ መደቦች መካከል የሚፈጠረው ቅራኔ ነው ።

የተጠቀሰው ዓይነት ቅራኔ ባለበት ሁኔታ ሁሉ የመደብ ትግል እንዳይኖር ጨርሶ ማስወገድ የማይቻል ቢሆንም ፣ አዳኂው መደብ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በማደናቀፍ ፣ ተግባሩን «ሕገወጥ » አድርጐ በመቅጣት፣ የራሱን አስከፊ አሠራር «ጥሩና» «ትክክለኛ» አድርጐ ለማቅረብ በመሞከርና ከዚህም አልፎ ሲመጣ ቀጥተኛ የሆነ ኃይል በመጠቀም ትግሉን ለማለዘብ ጥረት መደረጉ የማይቀር ነው ። በአንድ አገር ውስጥ አንድን አብዮታዊ እንቅስቃሴ የሚመራ የኅብረተሰብ ክፍል ከዘላቂ ዓላማው ለማድረስ እንዲያስችለው የመንግሥትን ሥልጣን መጨበጥ ተቀዳሚ ተግባሩ ሊያደርገው ይገባል የሚባለውም ከላይ የተጠቀሰውን ዓይነት ጋሬጣ ለመፍጠር « ሕጋዊነትን » ይዞ የተቀመጠን መንግሥትና አውታሮቹን ለመለወጥና ለዓላማው የቆሙ ኃይሎችን በጉኑ ለማሰለፍ ካልቻለ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ከቶውንም የማይቻለው በመሆኑ ነው። አብዮታዊ የሽግግር ወቅት ታሪካዊ እንቅስቃሴ ጀመረ መባል የሚችለውም ለአሮጌው የምርት ግንኙነት መከበር የቆመው መንግሥት ተወግዶ በምትኩ አዲሱን የሶሻሊስት ሥርዓት ለመገንባት የቆመ መንግሥት አመራሩን ሲጨብጥ ነው ።

ከዚህ በመነሣት ነው ነባሩን የማፍረስ ትግል በጉላ መልኩ የሚታይበት ፣ የማፍረስና የመገንባቱ ትግል ጐን ለጐን የሚራመድበትና በአመዛኙ የመገንባቱ ትግል ጐልቶ የሚወጣበት ሁኔታ ደረጃ በደረጃ እየተፈጠረ ወደዘላቂ ዓላማ ለመረማመድ የሚቻለው ። የመንግሥትን ሥልጣን ለመጨበጥ የሚደረገው ትግል በአመዛኙ ነባሩን ሕግ በመጣስ የሚደረግ እንደመሆኑ ሁሉ ፣ የመንግሥትን ሥልጣን የጨበጠ አብዮታዊ ኃይል በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙ መሠረታዊ ግንኙነቶችን ለመለወጥ የሚወስዳቸው ርምጃዎች በአመዛኙ ነባሩን ሕግ በመሠረዝና በአዲስ እንዲተካ በማድረግ የሚከናወኑ ተግባሮች ናቸው ።

በጥቅሉ የሽግግር ወቅት የተቀየጠ ሁኔታ ጐልቶ የሚታይበት ፣ በነባሩና በአዲሱ መካከል የሞት ሽረት ትግል የሚካሔድበት ፣ ፈጣን የሆኑ ለውጦች በየጊዜው የሚታዩበት ፣ ያለፈው ሥርዓት ልዩ ልዩ ገጽታዎች የሚንፀባረቁበትና አዲሱም ሙሉ በሙሉ ያልተገነባበት ወቅት ነው ። በመሆኑም ጊዜያዊ የሆነ ፣ ያልተረጋጋ ሁኔታ ጐልቶ የሚታይበት ስለሚሆን ለሕግ ተገዥነት የሚላላበት ፣ የሥራ ምርታማነት ፣

Digitized by Google

ቁጥጥርና የአስተዳደር ተሰሚነት የሚቀንስበት ወቅት ነው ።

በመሆኑም የምርት ግንኙነቱን ደረጃ በደረጃ ለመለወጥ የሚወሰዱ ርምጃዎች ፣ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ በመወከል የመንግሥትን ሥልጣን የጨበጠውን ክፍል ኃይል ለማጠናከር በአንፃሩም ዓላማውን ለማደናቀፍ የቆሙ ወገኖችን ኃይል ለማዳከም የሚወሰዱ ርምጃዎች ፣ የሠራተኛውን ሕዝብ ባህልና አመለካከት ለማሳደግ የሚደረጉ ጥረቶች ሁሉ ከላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ውስጥ የሚካሔዱና በነዚህ ተፅዕኖ እየተደረገባቸው የሚከናወኑ ናቸው ።

እንደሌሎች የላዕላይ መዋቅር አካሎች ሁሉ ሕግና ለሕግ መከበር የቆሙ አውታሮች እንቅስቃሴም ከዚህ ተፅዕኖ ውጭ ሆነው ሊራመዱ አይችሉም ። እነዚህ ተፅዕኖዎች መኖራቸውን መቀበል ግን በሽግግር ወቅት ሕግ አያስፈልግም ወደሚለው የሚያመራ አይደለም ። ይልቁንም የሠራተኛውን ሕዝብ ጥቅም ለማስከበርና ለዚህ ዘላቂ ዓላማ እውን መሆን የሚታገልና ሕዝቡን የሚያታግል መንግሥት ነባሩን ሕግ የሚተካና ለአዲሱ ሥርዓት ግንባታ የሚቆም ፣ ለዚህም ዓላማ እውን መሆን እገዛ የሚያደርግ ሕግ እያወጣ መሥራት ያለበት መሆኑን አጥብቆ የሚያስገነዝብ ነው ። ምክንያቱም ሥልጣን የጨበጠው መንግሥት አብዮታዊም ቢሆን ለሠራተኛው ሕዝብ ዓላማዎች እውን መሆን ሕግን በመሣሪያነት መጠቀም ስለሚኖርበት ነው ።

በመንግሥትና በሕግ መካከል ያለውን የቅርብ ተዛምዶ ለማሳየት በተሞከረበት ክፍል ውስጥ ሕግ በሥልጣን ላይ ያለ መንግሥትና በርሱ የሚወከለውን የኅብረተሰብ ክፍል ስብስብ ፍላጐት የሚገልጽና ለፍላጐቱ ተፈጻሚነት የሚቆም መሆኑ ታይቷል። በሽግግር ወቅት የሚታይ ልዩ ሁኔታ ደግሞ የነበረውንና ለዕድገት እንቅፋት የሆነውን የማፍረስ ፣ በምትኩም አዲሱን የመገንባት ጥምር ትግል የሚካሔድበት እንደመሆኑ ፣ በሕግ መልክ የሚቀረፀውን ሥልጣን የጨበጠው መንግሥት ስብስብ ፍላጐት ይዘትም በዚሁ ክልል ውስጥ የሚወሰን ይሆናል ። ይህ ጥምር ትግል ፈጣን እንቅስቃሴና ለውጥ የሚታይበት እንደመሆኑ ፣ በሕጉ ላይ የሚንፀባረቀው የመንግሥት ፍላጐትም በዚሁ የዕድገት ፍጥነት የሚለወጥ ይሆናል።

እንደሚታወቀው ሁሉ የሽግግር ወቅት ትግል የነበረውን ሁሉ በማፍረስ የሚጀምር አይደለም ። መሠረታዊ የሆነውን የምርት ግንኙነት ለመለወጥና የአብዮታዊውን መንግሥት ሥልጣን ለማጠናከር የሚያስችሉ ዓቢይ ርምጃዎችን ደረጃ በደረጃ በመውሰድ የሚካሔድ ትግል ነው ። ሕግ ቅድሚያ ትኩረት የሚያደርግባቸው አካባቢዎችም እነዚህ እንዲሆኑ የሕግ መነሻ መሠረቶች ያስገድዳሉ ።

የሽግግር ወቅት የፖለቲካ እንቅስቃሴ ፈጣን በመሆኑ በዚህ ወቅት የሚወጡ ሕጎች ፈጣን ለውጥ እንዲያደርጉ ሊገደዱ የሚችሉ መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል ። ይህ ፈጣን ለውጥ ግን ዛሬ የሚወጣውን ሕግ ነገ የሚታወጀው የሚያፈርሰው ዓይነት እንዳይሆን የሕጐች ዓይነትና ደረጃ ሊያገለግሉ ከሚችሉበት ጊዜ ጋር በተጣጣመ መንገድ እየታዩ የሚቀረጹ መሆናቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ይሆናል ።

በነዚህና በሌሎችም ምክንያቶች የኅብረሰቡ መመሪያ ሊሆኑ የሚችሉ ሕጐች ሁሉ (ሕገ መንግሥት ፣ የንብረት ሕግ ፣ የወንጀል ሕግ . . . ወዘተ) በተጠናቀረና የሕግ ቅርጽ በያዘ መልካቸው በሽግግር ወቅት ተሟልተው ሊገኙ አይችሉም ።

በሽግግር ወቅት የሕጐች ተሟልቶ አለመገኘት ማለት ግን በኅብረተሰቡ ውስጥ ሕግና ሕጋዊነት የለም ወደሚለው የሚያመራ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም በዚህ ወቅት የሚወጣው ሕግ በደረጃም ይሁን በቅ

Digitized by Google

ርጹ ቀድሞ ከነበረውና ወደፊት በሰከነ ሁኔታ ከሚፈጠረው የተለየ ቢሆንም ፣ ሥልጣኑን የጨበጠው አብዮታዊ ኃይል ሕጋዊ ነው ብሎ የሚቀበለውና የሚያስፈጽመው ሁሉ ለተወሰነ ጊዜም እንደሕግ ሆኖ የሚያገለግል በመሆኑ ነው ።

ይህ ነባራዊ ሁኔታ እንዲኖር የሚያስገድደው ተጨባጭ እውነታ ነው ። አንድ አብዮታዊ መንግሥትም በዚህ ወቅት ሕጋዊ ነው የሚለው የሠራተኛውን ሕዝብ መብትና ጥቅም የሚጠብቀውን ተግባር ሁሉ ነው ። ሆኖም አብዮታዊው መንግሥት የሚደገፈው ሁሉ ከጅምሩ የሕግን ቅርጽ ይዞ መገኘት አለበት ለማለት አይቻልም ። በዚህ ዓይነቱ የሽግግር ወቅት እያንዳንዱ ጉዳይ በዓዋጅ ፣ በድንጋጌ ፣ በትእዛዝ ፣ ወዘተ .., መልክ ካልወጣና ለሚያስፈጽሙ አካሎች ካልተሰጠ ብሎ ማላዘን የሕግን ምንነት በአግባቡ ካለመረዳት ወይም «በሕግ አለመኖር» ሽፋን ጠቅላላውን እንቅስቃሴ ለመግረር ከመቆም የሚመነጭ አመለካከት ነው ።

ይህ የግንዛቤ ጉድለት ወይም የትግል ስልት በተለይ በሽግግር ወቅት በሚገኙ አስፈጻሚ አካሎች ዘንድ ጉልቶ ሊንፀባረቅ የሚችል ነው ። ይኸ የተሳሳተ አመለካከት ሕግ በሽግግር ወቅት ሊኖረው የሚገባውን ሚና የሚያለዝብ ይሆናል ።

አብዮታዊ እንቅስቃሴ በሚካሔድበት አገር የሚገኝ ሕዝብ በአጠቃላይና የመንግሥትን ልዩ ልዩ ፖሊሲዎች እንዲያስፈጽሙ ኃላፊነት የተጣለባቸው አውታሮች ውስጥ የሚገኙ ባለሥልጣኖች በተለይ የመንግሥትና የፓርቲውን ፖሊሲዎች የማወቅና የማሳወቅ ፣ ለነዚህም ተገዥዎች ሆኖ የመገኘት ግዴታ አለባቸው ። ይህ በተለይ በመንግሥት ባለሥልጣኖች ዘንድ በውል ተለይቶ መታወቅ ያለበት ነው ። ምክንያቱም ባለሥልጣን ከሥልጣኑ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሚያከናውነው ተግባር አገረ መንግሥቱን የመንግሥትን ሕግ የሚገልጽ በመሆኑ ነው ።

> የመንግሥት ባለሥልጣን ተግባር በይዘቱም ሆነ በባሕሪው የሕጉን አሠራር እንጂ ሌላ ምንም ነገር አይገልጽም ። በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚሠራ የሕግ ሥርዓትም መንግሥት ተግባሩን የሚያከናውንበት አንድ ልዩ ቅርጽ ነው ።[9]

በማለት ጃስዊች ከላይ በተጠቀሰው ሥራው ውስጥ ያንድ የመንግሥት ባለሥልጣን ተግባር ሕግን በሥራ ላይ ከማዋል ተነጥሎ የማይታይ መሆኑን በትክክል አስቀምጦታል ።

በሽግግር ወቅት የሚገኝ አብዮታዊ መንግሥት ፍላጐቶች በሙሉ በሕግ መልክ ተቀርፀው ለአስፈጻሚ አካሎች ሊሰጡ የማይችሉት መንግሥት ይህን ለማድረግ ባለመፈለጉ ሳይሆን ፣ ከፍ ብለው የተጠቀሱት ነባራዊ ሁኔታዎች ለዚህ ዓይነቱ ሁኔታ መፈጠር አመቺ ሆነው ስለማይገኙ ነው ። ሆኖም በወቅቱ የሚገኝ መንግሥት (ፓርቲ) ዘላቂ ዓላማዎች በልዩ ልዩ መንገዶች መገለጣቸው የማይቀር ነው ። ይህን በምሳሌ ለመግለጽ ፓርቲው እና መንግሥት ሶሻሊዝም ዓላማቸው መሆኑን ገልፀው ወደዚያ ለመድረስ የሚያስችላቸውን ፕሮግራም* በመቅረፅ ለዚህ ተግባራዊነት እንዲታገል ሕዝቡን ማሰለፍ ይችላሉ ። በዚህ ዓይነት ስፋት ካለው ፕሮግራም ላይ የሚመሠረቱና በኅብረተሰቡ ውስጥ እንዲከናወኑ የሚጠበቁ ልዩ ልዩ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ዘርፎችን የሚመለከቱ ዓዋጆች ፣ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎች ፣ ወዘተ.. በየጊዜው በመንግሥት ውሳኔ ይፋ ወጥተው ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚጠበቅበት ሁኔታ ይኖራል ።

በሽግግር ወቅት በሚገኝ የተወሰነ አገር ውስጥ ከመንግሥት በተጨማሪ የፖለቲካ ድርጅት በሚኖርበት ሁኔታ የፖለቲካ ድር

---

* በመሠረቱ ፕሮግራም ከሕገ መንግሥት ፣ ከንብረት ሕግ ፣ ከወንጀል ሕግና ከቤተሰብ ሕግ ወዘተ... በይዘትም ሆነ በቅርጽ ይለያል ። ፕሮግራም በአንድ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲከናወን የሚነደፍና የወደፊቱን ግብ የሚጠቁም ሰነድ ነው ። የተጠቀሱት የሕግ ዓይነቶች ግን በተደረሰበት የተወሰነ የዕድገት ደረጃ ላይ የመንግሥትና የሕዝብ፣የልዩ ልዩ የመንግሥት አካሎች ፣ የልዩ ልዩ ሕዝባዊ ድርጅቶችና የመንግሥት እንዲሁም የሕዝቡን የርስ በርስ ግንኙነቶች የሚወስኑና የሚመሩ ሕጎች ናቸው ። እነዚህም በአብዛኛው ገጽታቸው ከወደፊቱ ይልቅ በነባሩ የምርት ግንኙነት ላይ ተመሥርተው የሚቀረጹ ናቸው።ይህ ማለት ግን የፕሮግራም ይዘት በሚወጡ የሕግ ዓይነቶች ላይ ምንም ተጽዕኖ አያሳርፍም ማለት አይደለም ።

Digitized by Google

ጅቱ በጉባኤ ውሳኔዎች መልክ ፣ በማዕከላዊ ኮሚቴዎች ውሳኔዎች መልክና በሌሎችም ልዩ ልዩ ቅርጾች የአገሪቱ ሕዝብና የመንግሥት አካላት እንዲያከብሯቸውና እንዲያስፈጽሟቸው የሚጠበቁ መመሪያዎች ሊወጡ ይችላሉ ።

እነዚህ ሁሉ በቅርፃቸው ቀድሞ ከነበሩ ሕጐች የሚለዩ ቢሆኑም ፣ የመንግሥት ሥልጣን የጨበጠውንና የሚወክለውን መደብ ፍላጐቶች የሚያንፀባርቁ ናቸው ። በመሆኑም ተፈጻሚነትን በማግኘት ረገድ ቀድሞ የነበሩትን ሕጐች ቅርጽ አልያዙም በሚል በማንኛውም አስፈጻሚ አካል ወደ ጐን ሊተው የሚችሉ አይሆኑም ። ይልቁንም ነባሮቹና የሽግግር ወቅት በሚያስከትለው ችግር ምክንያት በሽግግሩ ወቅት እንዲሠራባቸው ከቀድሞው የሚሸጋገሩ ሕጎች ሁሉ ከነዚህ ጋር ተፃራሪ ወይም የሚጋጩ ሆነው በሚገኙበት ሁኔታ ነባሮቹ ለነዚህ ቦታቸውን መልቀቅ አለባቸው ።

ከሽግግሩ ወቅት ውስብስብ ሁኔታ በፍጥነት ለመውጣትና በሁሉም ዘርፍ የሰከነ የግንባታ ተግባር ለማከናወን እነዚህ አዳዲስ ሕጐች ተፈጻሚ ሆነው መገኘታቸውን ማረጋገጥ አማራጭ የማይገኝለት ግዴታ ነው ። ፍሬደሪክ ኤንግልስ ይህን ሁኔታ በማስመልከት ሲገልጽ ፣

ለብዮት የሚፈጥረው ለዲስ ሕጋዊነት ያለምንም ገደብ መታወቅና መከበር ያለበት መሆኑን ማረጋገጥ ሥልጣንን በለብዮታዊ እንቅስቃሴ የጨበጡ ፓርቲዎች ወይም መደቦች ሁሉ ባሕርይ ነው ፣[10] ብሏል ።

ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው በሽግግር ወቅት የሚወጡ ሕጐች የተለያየ ቅርጽ ኖሯቸው ፈጠን ባለ ሁኔታ እየተለወጡ የሚወጡ ቢሆኑምና በሥራ ላይ እንዲውሉ በተፈለገበት ወቅት ሁሉ ተፈጻሚነታቸው በመንግሥት አካላት ፣ በልዩ ልዩ ድርጅቶችና በሕዝቡም ላይ የሚጸና ነው ። ቀደም በአለው አሠራርና በሚታወቀው መንገድ ሕገ መንግሥት ወይም አዋጅ ወይም ትእዛዝ ወዘተ… ካልሆነ የሕግነት ደረጃውን ማሳነስና አፈጻጸሙንም ቸል ማለት ተገቢ አሠራር አይሆንም ። ተገቢ ያለመሆን ብቻ ሳይሆን የመንግሥትን ፍላጐቶች በመፃረር መቆምና የአብዮቱን ዕድገት ለማደናቀፍ የሚደረግ አሻጥር ይሆናል ።

በተለይም በልዩ ልዩ የመንግሥት አውታሮች ውስጥ የሚገኙ አስፈጻሚዎች በአሠራራቸው መንግሥትን ወክለው የሚገኙ መሆናቸውን በመገንዘብ መንግሥት (የፖለቲካ ድርጅት) የሚያወጣቸው ዓዋጆች ፣ መመሪያዎች ፣ ውሳኔዎች ፣ ወዘተ. . . ጋር የመተዋወቅና በተግባር እያዋሏቸው መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው ።

የመንግሥት ለካላት ሕግን በጥብቅ በማክበር መሥራት ለለባቸው ፤ ይህን ሳያደርጉ ሲቀሩ በኅብረተሰቡ ውስጥ ጤናማ ያልሆኑ ለዝማሚያዎች ለመኖራቸው ምልክት ነው ።[11]

በማለት ቴሬሊሾቭ የተባለው የሕግ አዋቂ ሁኔታውን ጠቅለል አድርጎ አስፍሮታል ።

ሕግ በመላ ኅብረተሰብ አባላትና ልዩ ልዩ ተቋሞች መከበር ያለበት መሆኑ ለሽግግር ወቅት ብቻ የተሰጠ የተለየ ባሕርይ አይደለም ። « … ሁሉም ሰው በእኩልነት የንብረት ባለቤት ሊሆን እንደሚችል በሚገልጸው ነገር ግን ብዙኃኑን ሠራተኞችን በምንም መንገድ የንብረት ባለቤት በማያደርጋቸው»[12] በቡርዧው ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሚወጣው ሕግም ለጥቂት በዝባዦች አድላዊ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም ፣ ቡርዧው ም ቢሆን በሕግ ፊት ሁሉም እኩል ነው እያለ የሚመጻደቅ መሆኑም የታወቀ ነው ።

በእንፃሩ በእርግጥ ከሕግ ፊት ሁሉም እኩል ሊሆን የሚችለው ማናቸውም ሠራተኛ እንደየችሎታው የመሥራት ፣ እያን

Digitized by Google

ዳንዱ ሠራተኛ ከምርት መገልገያዎች ጋር ያለው ግንኙነት በእውነተኛ እኩልነት ላይ የተመሠረተ መሆኑ በተግባር በተረጋገጠባ ቸው በሶሻሊስት አገሮች ውስጥ ብቻ ነው።

የመንግሥትን ሥልጣን የጨበጠው ኃይል እንደሚቆምለት የኅብረተሰብ ክፍል ፍላጐት የተለያየ ይዘት ያላቸው ሕጐች በተለያየ ቅርፅ ይወጣሉ ፤ በመንግሥት ማየ ስፈጸሚያ አውታሮች አማካይነት ይፈጸ ማሉ ። አለመፈጸማቸው በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ቀውስ የሚጠቁምና አለመ ፈጸማቸውን የሚፈልጉ ወገኖች የበላይነ ትን የሚጐናጸፉበትን ሁኔታ የሚያመቻች ሊሆን ይችላል ።

ይህን ሁኔታ ከመንግሥት አስፈጻሚ አካ ሎች አንዱ የሆነው ፍርድ ቤት ከሁሉም በላይ ሊያጤነው የሚገባ ዓቢይ ጉዳይ ነው ። የሽግግር ወቅት ነባሩን የመንግሥት አው ታርና አሠራሩን በአንድ ጊዜ የሚደመስ ስና በምትኩ አዲሱን በአንዴ የሚያዋቅር አለመሆኑ ተጠቅሷል ። ሌኒን ይኸንኑ ጉዳይ በማስመልከት ሲጽፍ ፦

> ቢሮክራሲውን በአንደ ከሁሉም ቦታና ሙሉ በሙሉ ማጥፋት የማይታለም ተም ኔታዊነት ነው ። ነገር ግን አሮጌውን ቢሮ ክራሲያዊ መዋቀር መምታት መጀመርና ሁሉን ቢሮክራሲ ቀስ በቀስ መደምሰስ የሚያስችለውን አዲሱን ወዲያውኑ መገ ንባት መጀመር ተምኔታዊነት አይደለም፤ ይህ ቀጥተኛና አጣዳፊ የሆነ የአብዮታዊ ወዛደር ተግባር ነው ፤ [13]

ማለቱ ይታወሳል ።

የሽግግር ወቅት ተጨባጭ እውነታ የሚ ፈቅደው አሠራር ይኸንኑ በመሆኑ ለአለፈ አድኃሪ ሥርዓት ሕጐች መከበርና በዚህም ለበዝባዥ መደብ ዕድሜ መራዘም ተዋቅር የቆየን ፍ/ ቤት ወይም አወቃቀርና አሠራር በአንዴ ሙሉ በሙሉ መለወጥ ወይም መደምሰስ የሚቻል ተግባር አይሆንም ። ሆኖም ከሌኒን የተወሰደው ጥቅስ እንደሚ ገልጸው አብዮታዊውን እንቅስቃሴ ለመግ ታት በግንባር በሚቆሙት በዚህ አካል ዘር ፎች ላይ አብዮታዊ በትር መሠንዘሩና በአ ንፃሩም ለሽግግሩ ወቅት ፖለቲካና ኢኮኖሚ ተግባራዊነት የሚቆሙ አካሎች መፈጠራ ቸው በመንግሥት ከሚወሰዱ ተቀዳሚ ተግባሮች አንዱ ነው ። በአጣዳፊነታቸው ምክንያት ለሽግግሩ ወቅት ፖለቲካና ኢኮ ኖሚ ተገዥ የሚሆኑ የፍርድ ቤት አካሎች መፈጠራቸው ግን ልዩ ልዩ ቅርጽ ይዘው የሚወጡ የመንግሥት ሕጎች ፣ መመሪያ ዎች ፣ ውሳኔዎች ፣ ወዘተ . . . በነዚህ ክፍ ሎች ተፈጻሚነት ሲኖራቸው ቀሪዎቹ የፍ ርድ ቤት አካሎች ለነዚህ ተገዥዎች አይሆ ኑም ማለት አይደለም ። ሌሎችም የመንግ ሥት አውታሮች ለልዩ ልዩ የሽግግር ወቅት የመንግሥት መመሪያዎች ተግባራዊነ ት እንዲቆሙ የሚጠበቅባቸውን ያህል ወይም ከዚያም በበለጠ ነባሮቹም ፍ/ ቤቶች ለነዚህ መመሪያዎች ተግባራዊነት መቆም ይጠበ ቅባቸዋል ።

> ፍርድ ቤት የሥልጣን መሣሪያ ነው።ለዘ ብተኞች አንዳንድ ጊዜ ይህን ይረሳሉ ። ነገር ግን ይህን መርሳት ለአንድ ማርክሲ ስት ኃጢአት ነው ፤ [14]

በማለት ሌኒን ስለፍርድ ቤት ምንነት በግ ልጽ ያስፈረውም፣ በሽግግር ወቅትም ቢሆን የፍርድ ቤቶች አሠራር የፓርቲና የመንግ ሥት ፖሊሲዎች ከማስፈጸም ውጭ ሊሆን እንደማይችል የሚያስገነዝብ ነው ።

ከዚህ ተጨባጭ ሁኔታ ውጭ ልዩ ሽፋን በመስጠት አንዳንድ የመንግሥት አካላት ለመንግሥት ፖሊሲዎች ተፈጻሚነት የቆሙ ሌሎቹ ደግሞ ከመንግሥት ፖሊሲዎች በላይ ሆነው የሚታዩበት ወይም ራሳቸውን በእንደዚህ ዓይነት መነጽር የሚመለከቱ በት ሁኔታ ከቶውንም ሊኖር አይችልም ።

የኢትዮጵያ አብዮት በማርክሲዝም ሌኒ

Digitized by Google

ኒዝም ንድፈ ሐሳብ በመመራት በየዘርፉ የሽ
ግግር ወቅት የሚጠይቃቸውን የትግል ዘዴ
ዎች ተግባራዊ በማድረግ እየተራመደ የሚ
ገኝ ለመሆኑ ከማንም የተሸሸገ ጉዳይ አይደ
ለም ። አብዮቱ በየዘርፉ እስከአሁን የወሰዳ
ቸውና እየወሰዳቸው የሚገኙ ርምጃዎችም
ከኢትዮጵያ ሠርቶአደር ሕዝብ ፍላጐትና
ለዓለለም ሰላም ወዳድና ተራማጅ ሕዝ
ቦች ከሚያደርገው አስተዋጽኦ አንፃር ሲገ
መገሙ ትክክለኛነታቸውና ሕጋዊነታቸው
የሚያጠያይቅ አይደለም ።

አብዮቱ የሚወስዳቸው ርምጃዎች ሕጋ
ዊነት የሠራተኛውን ሕዝብ ፍላጐት ለማር
ካት የሚያስችል ሁኔታ ከመፍጠሩ አንፃር
ብቻ የሚታይ ሳይሆን ፣ የእነዚህ ፍላጐቶች
መከበርና መጠበቅ የሕግን ድጋፍና የአስ
ፈጻሚ አካሎችን ትኩረት እንዲያገኙ በማ
ድረግም ጭምር ነው ።

አብዮቱ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብ
ዮት ፕሮግራም እየተመራ ባለፈባቸው
ወቅቶች ሁሉ የሚወጡ ሕጐች ይህን ፕሮ
ፕሮግራም የማይፃረሩና ለፕሮግራሙ ተግ
ባራዊነት እገዛ ሊያደርጉ የሚችሉ መሆና
ቸው እየተረጋገጠ የወጡ ሕጐች ናቸው ።
የኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባኤ እስከተካሔደበት
እስከ ታኅሣሥ 1975 ድረስ የጊዜያዊ ወታ
ደራዊ አስተዳደር ደርግ 227 ዓዋጆችን ፣
ሌሎች በርካታ ደንቦችንና መመሪያዎችን
አውጥቷል ።[15] በዚህ መስክ የተደረገው
እንቅስቃሴ በዚህ ደረጃው የጐላ ውጤት
ሊያስገኝ የቻለ ይሁን እንጂ እስካሁን የወ
ጡት ዓዋጆች ፣ ሕጎች በኅብረተሰቡ ውስጥ
የሚገኙትንና ሕግ ሊቀረጽላቸው የሚገቡ
ጉዳዮችን ሁሉ የሚሸፍኑ አይደሉም ፤ እን
ዲሆኑ መጠበቅም ነባራዊ ሁኔታን መካድ
ነው ።

ሁኔታው ይህ በመሆኑም በቀድሞው ሥር
ዓት የነበሩትን አንዳንድ ሕጐች አብዮቱ
ዛሬም ሊጠቀምባቸው ተገዷል ። ይህም
ሆኖ አስፈጻሚ አካሎችና የሕግ ተርጓሚ
ዎች ሕጉ ላይ የሰፈረው ይህ ነውና ይህንኑ
ካላስፈጸምን በሚል የወደፊቱን የዕድገት
ጉዞ ሊያደንቅፉ የሚችሉ ውሳኔዎችን እንዲ
ሰጡ አይጠበቅም ። በጽሑፉ ዓቢይ ክፍል
ውስጥ ለማሳየት እንደተሞከረው የሽግግር
ወቅትን ፖለቲካ ፣ የሕግን ሚና ፣ የሕጐችን
ደረጃና የአስፈጻሚ አካሎችን ሚና በሚገባ
በማጤን የሚሰጡ ውሳኔዎች ሁሉ ወደአብ
ዮቱ ዓላማዎች የሚያቀርቡ እንጂ ወደኋላ
ሊመልሱት የሚቃጡ መሆን አይኖርባቸ
ውም ።

ስለሕግ ያለ አመለካከትን ቀድሞ በተገኘ
ትምህርት ላይ ብቻ ወስኖ ሁኔታውን ላለማ
ወቅ ከመሻት የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ
አብዮት ፕሮግራምን ፣ የኢሠፓአኮ ጉባኤና
የማዕከላዊ ኮሚቴ ውሳኔዎችን ፣ ሌሎች የአ
ዋጅ ፣ የደንጋጌ ፣ የትእዛዝ ፣ ወዘተ ... ቅርፅ
የሌላቸውን የአብዮታዊ መንግሥትንም ሆነ
የኢሠፓአኮን መመሪያዎች በተፈጻሚነት
ደረጃ ከሕግ ያነሱ አድርጎ ለማየት መሞከር፣
ያሉበትን ሁኔታ በመርሳት ወይም አውቆ
በርምጃ አደናቃፊነት በመሰለፍ ሕግ በሽግ
ግር ወቅት ሊጫወተው የሚችለውን ለመን
ፈግ መሞከር ይሆናል ።

« ... ሕጋዊ ደንቦች ፍርድ ቤቶች ተጨ
ባጭ ጉዳዮችን እንዴት መወሰን እንዳለባ
ቸው አቅጣጫ የሚያሳዩ እንጂ ድርቅ ያሉ
መመሪያዎች አይደሉም ፣ »[16] በማለት
አንድ የሕግ ሊቅ የሰጠውን ማጠቃለያ በማ
ገናዘብ፣ የሕግ አስፈጻሚ አካሎች የሚሰጧ
ቸው ውሳኔዎችና አፈጻጸማቸው ያለንበትን
የሽግግር ወቅት ሁኔታ የተንተራሱ፣ ነገር ግን
ወደግባችን ሊያቃርቡን የሚያግዙ መሆና
ቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው ።

Digitized by Google

የግርጌማስታወሻ ፤

1. V.M. Chkhikvadze, *The Soviet State and Law*, (Moscow: Progress Publishers, 1969), p. 189.
2. *Ibid.*, p. 194.
3. Fredrick Engles, *The Origin of the Family, Private Property and the Sate*, (Moscow: Progress Publishers, 1977), p. 157.
4. V.G. Afanasyev, *Marxist Philosophy* 4th ed., (Moscow: Progress Publishers, 1980), p. 372.
5. L.S. Jawitsch, *The General Theory of Law: Social and Philosophical Problems*, H. Campbell Creighton tran., (Moscow: Progress Publishers, 1981), pp. 39-90.
6. V.I. Lenin, *Selected Works* Vol. 2, (Moscow: Progress Publishers, p. 310.
7. L.S. Jawitsch, p. 44.
8. *Ibid.*, p. 43.
9. *Ibid.*, pp. 54-55.
10. Vladimir Terebilov, *The Soviet Court*, (Moscow: Progress Publishers, 1973), p. 6.
11. V.M. Chkhikvadze, p. 195.
12. Tashukanis, *Selected Writings on Marxism and Law* (London: Academic Press, 1980), p. 86.
13. V.I. Lenin, p. 272.
14. *Ibid.*, p. 141.
15. የኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባኤ ሰነዶችና ውሳኔዎች ፣ ታኅሣሥ 1975 አዲስ አበባ ገጽ 109 ።
16. Thomas Glyn Wofkm, *The Nature of Law*, (Amsterdam: North-Holland Publishing Company, 1980), p. 6.

Digitized by Google

የ ጋ ብ ቻ ጽ ን ሰ ሐ ሳ ብ ግ ን ዛ ቤ

አጠቃላይ ነጥቦች

ኢሳይያስ ደምሴ

ኅብረተሰብ የቤተሰብ ታሪካዊ ዕድገት ውጤት ሲሆን ፤ ቤተሰብ ደግሞ የኅብረተሰብ ምንጭና መንስኤ ነው ። ኅብረተሰቡ የቤተሰቦች ድምር ሳይሆን የቤተሰቦች ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የግንኙነት አወቃቀር ያለው የሰዎች ቁርኝታዊ ማኅበርም ነው ።

በዚህም ማኅበር ውስጥ ሰዎች በየጾታቸውና በየዕድሜያቸው ከዚህም ባሻገር የሚያደርጉትን ግላዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ወይም በጥቅሉ ግላዊና ማኅበራዊ አኗኗራቸውን ማየት ከመቻል ባሻገር የማኅበራዊ ኑርአቸው መሠረት የሆነውን ጋብቻንና የጋብቻን ልዩ ልዩ ገጽታዎች መመልከት ያስፈልጋል ።

ጋብቻ እንደየኅብረተሰቡ መንፈሳዊ ልማድና ወግ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የተለያየ የዕድገት ደረጃ ሁለት ተቃራኒ ጾታዎችን የሚያገናኝ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ የአኗኗር ቅርጽ ነው ። በመሆኑም በአብዛኛው «ጋብቻ ኅብረተሰብ በታሪክ ሂደት ውስጥ የሚወሰነው ፣ የሚያጸድቀውና የሚደነገገው በአንድ ሴትና በአንድ ወንድ መካከል የሚፈጠር የግንኙነት ቅርጽ ነው ።»[1]

« . . . በአንዲት ሴትና በአንድ ወንድ ... » የሚለው አነጋገር መሠረተ ሐሳብ የዘመናዊው ኅብረተሰብ አጠቃላይ የጋብቻ ገለጻ ነው ። ይህም ማለት ከሥርዓተ ማኅበራት ሹም ሽር ፣ ከኅብረተሰብ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት ከፍተኛነት ኅብረተሰብ ከኋላቀር ሃይማኖታዊና ሥነ ልቡናዊ አመለካከትና አስተሳሰብ ነፃ እየሆነ መምጣት አኳያ በአብዛኛው የዓለም ኅብረተሰብ ዘንድ የተከሰተና እየተከሰተም ያለ በመሆኑ ነው ።

ከዚህ አጠቃላይ አነጋገር ባሻገር ፣ ዛሬ በዓለም ኅብረተሰብ ዘንድ የተለያየ የጋብቻ

Digitized by Google

ዓይነት ይታያል ። የልዩነቱ መንስኤና ምክንያቶች አያሌ ቢሆኑም ቅሉ ዓይነተኛው ምክንያት ግን የሕዝቦች ቁሳዊና መንፈሳዊ ዕድገት አለመመጣጠንና የመደቦች የጥቅም ቅራኔ መኖር ፣ የፖለቲካ ዘይቤአቸው መለያየት ፣ ግንኙነታቸው አንፃራዊ በሆነ መንገድ በቦታና በጊዜ መወሰንና በአንፃሩም የእምነታዊ አስተሳሰቦች ውስብስብነትና ዝብርቅርቅነት ጠንከር ያለ ተጽዕኖ ነው ።

ጋብቻ ተከታታይነት ያለው በማናቸውም የኢኮኖሚ ፣ የማኅበራዊና የፖለቲካ ዕድገት ደረጃ ላይ ባለ ኅብረተሰብ ዘንድ የሚታይ በሁለት ወይም ከዚያም በላይ በሆኑ ተቃራኒ ጾታዎች መካከል የሚፈጠር ማኅበራዊ ግንኙነት ቢሆንም ፣ የአንድን ኅብረተሰብ ገጸ ባሕርይ ከሚያሳዩትና የዕድገቱንም ደረጃ ከሚያመለክቱት የውስጥ ባሕርያቱም አንዱ ነው ። ጋብቻ የትውልድን ተከታታይነት የሚወስን እንደመሆኑ መጠን የቤተሰብም መሠረትና አስተሳሳሪ ድርም ነው ። ቤተሰብም አንድ ታሪካዊ ዘርፍ በመሆኑ ሕልውናውና ቅርጹ በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ባለ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓትና በአጠቃላይም በማኅበራዊ ግንኙነቱ ጠባይ ይወሰናል ። ጋብቻም የዚሁ ነጸብራቅ ነው ።

በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ የአንድ ኅብረተሰብ ቁሳዊ የዕድገት ደረጃ ርዕዮተዓለማዊና ስነ ልቡናዊ አመለካከትና አስተሳሰብ የእነዚህም ውጤት ያስከተለው እርካታ ወይም ችግር በጥቅል መልኩ ይንጸባረቃል ። ከዚህ አኳያ የጋብቻ ግንኙነት ባሕርይ የአንድን ሕዝብ ዕድገትና የተከታዩንም ትውልድ አካላዊና መንፈሳዊ ሁኔታ የመወሰን ክብደት አለው ። ባሕላዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች እየተለዋወጡ ሲሔዱ የሚተላለፈውን የቤተሰብ ባሕርይ አወራረስ ከሕዝብ ፍላጎት አንፃር በማጤን ሁኔታዎችን ያመቻቻል ። [2]

ጋብቻ ቁሳዊ መሠረት ያለው በመሆኑ ከቁሳዊ ጥቅም ፍላጎት ማስከበር አንፃር ቅርጹና ዘላቂነቱ እንደየኅብረተሰቡ ሕጋዊ ፣ ስነምግባራዊና መንፈሳዊ ድንጋጌዎች ይወሰናል ። ኅብረተሰብ በመደብ በተከፋፈለበት ተመሳሳይ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ያሉ ግን በቦታና ምንአልባትም በጊዜ ክልል ውስጥ የሚኖሩ የተለያዩ ኅብረተሰቦች ስለጋብቻ የሚኖራቸው ስነምግባራዊና መንፈሳዊ እንዲሁም ሕጋዊ አመለካከት ሊለያይ ይችላል ። አንድ ኅብረተሰብ ከጋብቻ ባለቤቶች ወይም ተጋቢዎች ላንዱ ጾታ የበለጠ ቁሳዊና ማኅበራዊ የበላይነት መብት ሲፈቅድለት አንዱ ደግሞ ይህንን በተቃራኒው ያስቀምጠዋል ። አንዱ ለወንዱ ተጋቢ በአንድ ወቅት ከአንድ ሴት በበላይ እንዲያገባ ሲፈቅድለት ሌላው ደግሞ ይህንን ይኮንናል ፤ እንዲሁም ጋብቻው ቢፈርስ አንዱ ወገን በጋራ ንብረት ላይ ብቸኛ የባለቤትነት መብት ሲኖረው ሌላው ግን ይህን መብት እንዲአጣ ይወስንበታል ።

ኅብረተሰብ በመደብ በተከፋፈለባቸው በታዳጊም ሆነ በበለጸጉ አገሮች ውስጥ በጋብቻ ተቋም ውስጥ ተጠቂዋ ሴት ናት ። «የአብዛኛዎቹ የቡርዧ አገሮች ሕግ ዓይነተኛ ገጽታም ሴቲቱን በቤተሰብ ውስጥ ዝቅ አድርጐ ማሳየት ፣ በንብረት ባለቤትነት ላይ ያላትን መብት ማሳነስና የወላጅነት መብቷን ዝቅ ማድረግ ነው።»[3] ይህም ከመደብ ጥቅም ጋር የተያያዘ ሲሆን የመደብ ሥርዓተ ማኅበራትም የወንድን የበላይነት አኩራርቶ የሴትን ዝቅተኛነት አብዝቶ ማሳየት ከባህሪያቸው አንዱ ገጽታ መሆኑን እንገነዘባለን ። ማለትም ሴትን ከቁሳዊ ጥቅሟ አንስቶ እስከ ስነምግባራዊ ሰብዕናዋ ድረስ የሚነካ የወንድን የበላይነት ጥቅም ፣ ከማስከበርና የሴትን ማኅበራዊ ድርሻ ዝቅ አድርጐ ከመመልከት የመነጨ የሥርዓተ ማኅበራቱ የፖለቲካ ፣ የሕግ ፣ የስነምግባር ፣ የሃይማኖት አቋም ነው ። በመሆኑም ሴትን በብዙ መልክ በወንድ ጥገኝነት ሥር ለማዋልና ለማቆየት እንዲቻል ጋብቻ ሲመሠረት የሴትን ዕድሜ አሳንሶ የወንድን ዕድሜ

Digitized by Google

አብልጦ የቤተሰብን መሪነት በአስተሳሰብ ዝቅተኛነት አስታኮ ፣ ለወንድ ለመስጠት መሆኑን ጠለቅ ብሎ መመልከት ያሻል ። ለምሳሌ በአያሌ የካፒታሊስት አገሮች ሕገ መንግሥቶች ጋብቻን በሚመለከት ረገድ የሴትን ዕድሜ ከወንድ በማሳነስ ተደንግጓል ። ይህም በኢጣሊያ የሴት የጋብቻ ዕድሜ 14 ሲሆን የወንድ 16 ፣ በፈረንሳይ የሴት የጋብቻ ዕድሜ 15 ሲሆን የወንድ 18 ፣ በጀርመን ፌዴራል ሪፐብሊክ የሴት የጋብቻ ዕድሜ 16 ሲሆን የወንድ 21 ሆኖ መደንገጉ[4] እንደምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል ።

ዛሬ የሰው ልጆች ቁሳዊና መንፈሳዊ አመለካከት እየሰፋ ፣ ከሃይማኖታዊ አስተሳሰብ በላይ እየመጠቀና ነገሮችን በትክክለኛ መልካቸው ለመረዳት አመቺ ሁኔታ እየተፈጠረ ባለበት ወቅት በተጋቢዎች መካከል የሚኖረው ግንኙነት የአንዱን መብት አብልጦ የሌላውን አሳንሶ የማየቱ ሁኔታ ተቀባይነት የለውም ። ትምክህተኛ የሆነ ወንድ በጋብቻ ውስጥ ሥርዓቱና እምነቱ ያሳደረበትን የበላይነት ስሜት ለማስከበር ሲሞክር፣የሥርዓቱንና የእምነቱን ተጽዕኖ እየተገነዘበች የመጣች ሴት ደግሞ በወንድ የበላይነት ስሜት የሚደርስውን ጭቆና ለመቋቋም በምታደርገው ጥረት ምክንያት የሚፈጠረው አለመግባባት የጋብቻን መፍረስ ይጋብዛል ። ይህ ሁኔታ በተፈጠረበት ኅብረተሰብ ውስጥም የጋብቻ ማኅበራዊ ባህርይ የበላይነት ባለው መደብ ይወሰናል ። በመሆኑም በጋብቻ ላይ የሚታየው ጉድለትና ሳንክ የሥርዓተ ማኅበሩ አጠቃላይ ችግር አካል ይሆናል ። ጋብቻንም ትክክለኛ አቅጣጫ ለማስያዝ የሚደረገው ጥረት የመደብ ትግሉን ባሕርይ ያንጸባርቃል ።

ጋብቻ ከሰዎች ፈቃድ ውጭ ነው ። የሰው ተፈጥሮ የጋብቻ ፈቃድ ያለበት በመሆኑ ከጋብቻ ውጭ መኖር አይችልም ። ማርክስና ኤንግልስ እንዳሉት ጋብቻ የቤተሰብ መሠረትና[5] ቤተሰብም ለኅብረተሰብ ተከታታይነት ዓይነተኛ ምንጭ በመሆኑ የጋብቻ አስፈላጊነት ከሰዎች መልካም ፈቃድና ውዴታም ውጭ ነው ። ሆኖም የጋብቻን ቅርጽና ሂደት ሰዎች እንደየማኅበረሰብ ልማዳቸውና ደንባቸው ፣ እንደ የፖለቲካ ዘይቤአቸው ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሥርዓታቸው ሊለዋውጡትና ሊገቱት ወይም ሊያራምዱት ይችላሉ ።

ኋላቀር የሆነው የጋብቻ ቅርጽ

አንድ በተወሰነ ኅብረተሰብ ዘንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነት ያለው መደብ ከቁሳዊና ከፖለቲካ ጥቅሙ አንፃር በጋብቻ ውስጥ የተጋቢዎችን ግንኙነት በሕግና በሌሎችም መንገዶች ይወስናል ። ይህም ጋብቻ ከተመሠረተ በኋላና ሲፈርስ የሚኖረውን የግንኙነት ቅርጽ የሚመለከት ብቻ ሳይሆን ለጋብቻ ግንኙነትም የሚያበቃውን ቅድመ ሁኔታም የሚወስን ይሆናል ። እነዚህ የጋብቻ ቅድመ ሁኔታዎችም የኢኮኖሚውን የበላይነት ከያዘው መደብ ጥቅም አንፃር ያላቸው ጠቀሜታ ተገምግሞ ሲታመንበት ለሰፊው የኅብረተሰብ ክፍል ማኅበራዊ ዕድገትና አንድነት ጉዳት ያላቸው መሆኑ ቢታወቅም «የሕዝቡን ዲሞክራሲያዊ መብት ለማስከበር» በሚል ሽፋን ሕጋዊ ድጋፍ ይሰጣቸዋል ። ለምሳሌ ያህል በየብሔረሰቡ የሚካሔደው ልማዳዊ የጋብቻ መተጫጨትና ለመተጫጨትም የሚያስፈልገው ቅድመና ድኅረ ዝግጅት ለኅብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ግንኙነት እንዲሁም ብሔራዊ አንድነት መዳበርና መጽናት ጠንቅ መሆኑ ቢታወቅም «ሁሉም እንደየባሕሉና እንደ የልማዱ» በሚል ሽፋን በሕግ የታወቀ የጋብቻ መተጫጨት ተደርጎ ይቆጠራል ። ከዚህም በቀር አንዱ ብሔረሰብ ከሌላው ብሔረሰብ ጋር እንዳይጋባ የአድህሮት ኃይላት ወይም አድኀሪ ግለሰቦች የሚያራምዱት አስተሳሰብና የሚያደርጉት ተጽዕኖ ሕጋዊ ቡራኬ ሆኖ ይገኛል ።

Digitized by Google

በአንድ ዓይነት ሙያ የተሰማራ የኅብረተሰብ ክፍል በሌላ ዓይነት ሙያ ከተሰማራው የኅብረተሰብ ክፍል ጋር የጋብቻ ግንኙነት እንዳይፈጥር አንዱ አንዱን ዝቅ አድርጐ የማየትና ወይም አንዱ ከአንዱ ራሱን ከፍ አድርጐ የመቁጠር አጉል ባሕል እንዲያድርበት ስለሚያደርግ ፣ በጋብቻ ግንኙነት ላይ ከፍ ያለ ችግር ይፈጥርበታል። በተለይም የቋንቋም ሆነ የብሔረሰብ ልዩነት ሳይኖር በአንድ ብሔረሰብ ውስጥ ከሙያ አንፃር ብቻ የጋብቻ ግንኙነት እንዳይፈጠር የማድረጉ ሁኔታ በጉልህ ጐልቶ የሚታየው በፊውዳል ኅብረተሰብ ውስጥ ነው። በሽመና ሥራ የተሰማራው ቤተሰብ በግብርና ከተሰማራው ፣ በሸክላ ሥራ የተሠማራው በንግድ ሥራ ከተሠማራው ቤተሰብ ጋር ፣ ወዘተ ... እንዳይጋባ ከፍተኛ የሆነ የመናናቅ ተጽዕኖ ያሳድርበታል። ይህም ለፊውዳሉ የገዥ መደብ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታ እንዲያስገኝ ሆኖ የተመሠረተ ኋላቀር ልማድ ነው።

ስለ ጋብቻ ያለው ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ

ኅብረተሰብ በመደብ በተከፋፈለባቸው በማንኛውም የዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ አገሮች ውስጥ የጋብቻ የተለያየ ገጽታ ሕጋዊ ድጋፍ እንዲኖረው ተደርጐ የሚኖርበት ዓይነተኛ ምክንያት የገዥው መደብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ጥቅም እስከአልተነካ ድረስ ነው። በተለይም በቡርዧ ኅብረተሰብ ዘንድ ጋብቻ እንደየባሕሉና እንደየእምነቱ የሚሉትም «ዲሞክራሲ የሰፈነበት አስተዳደር» አለ በማለት ሰፊውን ሕዝብ ለመሸንገል ነው።

ይሁን እንጂ ዲሞክራሲያዊ ጋብቻ ተብሎ ሊጠራ የሚገባው የተጋቢዎችን ጾታ ሳይመለከት አባላቱን በእኩልነት የሚመለከትና እኩል መብትና ግዴታን የሚያከብር ፣ ለኅብረተሰብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ዕድገት ምንም ዓይነት ተፃር የሌለው ሲሆን ነው። የአንድ እምነት ወይም ልማድ ዲሞክራሲያዊ ባሕርይ የሚለካው ደግሞ የሰዎችን መብት ሴትና ወንድ ሳይል እኩል ከማየትና ከማስከበር አንፃር ነው። የእምነቶችን ትክክለኛ ይዘት ብንመረምር መረዳት የምንችለው የኢኮኖሚ የበላይነት ያለውን መደብ ጥቅም የሚያስከብር ሆኖ ነው። ኅብረተሰብ በመደብ ከተከፋፈለበት ወቅት ጀምሮ እምነትም ሴትን የበታች አድርጐ በመመልከት በጋብቻ ውስጥ ሊኖራት የሚገባትን የእኩልነት መብት ስለማይቀበል ለጋብቻ ጾንሰ ሐሳብ ትክክለኛ ግንዛቤ ሰጥቶታል ማለት አይቻልም። እንዲያውም በአንድ ጋብቻ የተሳሰሩ ተጋቢዎችን በእኩልነት አይመለከታቸውም። በዋና ዋና ሃይማኖቶች ዘንድ በጋብቻ ውስጥ ሴትን የበታች ወንድን የበላይ አድርጐ በመመልከት ሴት የእኩልነት መብቷ ሳይጠበቅ የባሏ ተገዥና ፈቃድ ፈጻሚ አድርጐ ማቅረቡ ተቀባይነት አግኝቷል። በተለይም የሃይማኖትን አስተሳሰብ ትክክለኛ ገጽታ የምንረዳው ወንድ ብቻውን እንዳይኖር ለወንድ ተብላ ተፈጠረች የሚለውን አነጋገር ስንመረምር ነው።[6] ይህንን አመለካከት በጥሞና ስናጤነው መረዳት የሚቻለው በተፈጥሮ ሴትን ከወንድ ያነሰች ዝቅተኛ ፍጥረት አድርጐ በማቅረብ በጋብቻም ይህንን የዝቅተኛነቷን ደረጃ ይዛ የወንድን ቃል በመቀበል የራሷ ፈቃድና ፍላጐት ምንም ይሁን ምን ከባሏ ፈቃድ እንዳትወጣ ለማድረግ ነው። ይህም በሰው ልጅ ረጅም ታሪክ ውስጥ በጉልህ ታይቷል፤ ዛሬም በተግባር እየታየ ነው። ምንም እንኳ አንዳንድ ሃይማኖት «አንድ ወንድ ላንዲት ሴት» ቢልም ሌላው ደግሞ አንድ ወንድ ከአን

Digitized by Google

ዲት ሴት በላይ ባንድ ጊዜ እንዲያገባ ሲፈቅድለት ለሴቷ ግን ይህንን አይፈቅድም። ከዚህ አንፃር ማለት የሚቻለው ሃይማኖቶች ሴቶችን ከሞላ ጐደል በጋብቻ ው ውስጥ በእኩልነት እንደማይመለከቱ ነው ።

እምነት ምንጊዜም ቢሆን በኤኮኖሚ የበላይነት ያለውን መደብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ጥቅሞች ከሚያበስሩት የላዕላይ መዋቅር ዘርፎች አንዱ በመሆኑ በጋብቻ ውስጥ ወንድንና ሴትን እኩል አይመለከታቸውም። ሃይማኖቶች በአብዛኛው ጋብቻን የሚያጸኑት የተጋቢዎችን አብሮ ከመኖርና አንዱ ባንዱ ላይ የስርቆሽ ዝሙት እንዳይፈጸም ከሚለው አኳያ እንጂ ተጋቢዎችን አብረው እንዲኖሩ የሚያስችላቸውን የቁሳዊና ማኅበራዊ እኩልነታቸውን መብት ማስከበር ከሚለው አስተሳሰብ አንፃር አይደለም ።[7] ሃይማኖት ሴት ሁልጊዜ በቤተሰባዊና በማኅበራዊ ተሳትፎዋ ከወንድ በታች መሆኗ ተፈጥሮአዊ ጉዳይ ነው ይላል ። ይህም ሥርዓት በጋብቻ ውስጥ ተጠብቆ እንዲኖር ያስተምራል ።

ከዚህ አኳያ ፣ የአንድ ኅብረተሰብ ክፍል የሆነ ብሔረሰብ እምነቱና ልማዱ ጋብቻን በእኩልነት የማይመለከት መሆኑ እየታወቀ «ዲሞክራሲያዊ መብቱን ለመጠበቅ» በሚል ሰበብ የጋብቻን ሥርዓት እንደእየምነቱና ልማዱ እንዲፈጸም የሚለው የቡርዧ ዲሞክራሲ ምን ያህል ስሕተት እንደሆነና በተለይም የሴትን መብት የሚጥስ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል ። ዲሞክራሲው እንደእምነቱና ልማዱ እንዲያ፣ባ ሕጋዊ ፈቃድና ድጋፍ ከመስጠቱ ላይ ሳይሆን እምነቱና ልማዱ በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ የተጋቢዎችን እኩል መብት ከመቀበሉ ወይም በተግባር እንዲያውል ከማድረጉ ላይ ነው ። ይህን ሀቅ ግን ኅብረተሰብ በመደብ የተከፋፈለባቸው ሥርዓቶች አይቀበሉትም ።

የሴት የኢኮኖሚ ጥገኝነት በጋብቻ ውስጥ

በካፒታሊስትም ሆነ የካፒታሊስትን የዕድገት ፈለግ በተከተሉ አገሮች ውስጥ የሴቶች ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎ በጣም አነስተኛ ነው ። በመሆኑም ማኅበራዊና የፖለቲካ ንቃታቸው ያንኑ ያህል ዝቅተኛ ሆኖአል ። ይህ ደግሞ በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ የወንድን የበላይነትና ትምክህተኝነት ከፍ አድርጐት ይታያል ። እንደየአለበት የኅብረተሰብ ዕድገት ደረጃ ያለውን ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎ መጠቀሚያ በማድረግ ወንድ በሴቷ ላይ የአዋቂነት ከእርሱም ሕይወት አልፎ በእርሷ ሕይወት አመራርና በጋብቻ ግንኙነታቸው ውስጥ ያለውን ቀያሽነትና ወሳኝነት በሥጋዊ ስሜቷና ፍላጐቷ ላይ የሚኖረውን ተቆጣጣሪነት ፣ ወዘተ. . . በተፈጥሮ እንደተሰጠው አድርጐ በተግባር አውሎት ይታያል ። ይህ የበላይነት ጥያቄው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከፊል ማኅበራዊና ሕጋዊ መሠረት ያለው በመሆኑ ሴቷ የዚህ ዓይነቱን የወንድ የበላይነት ብትቃወም በኅብረተሰቡ ዘንድ የሚኖራት ተቀባይነት አስተማማኝ አይደለም ። እንዲያውም በኅብረተሰቡ ዘንድ ጸንቶ የኖረ የጋብቻ ሥርዓት አፍራሺና ባሕል አጉዳፊ ሆና ትቆጠራለች ። ለምሳሌ ያህል ሁለቱ ተጋቢዎች ማለትም ባልየው ብቻውን የትም እያመሸ ፣ ሚስትየዋ ብቻዋን የትም እያመሸች ቢገቡ በአካባቢው ኅብረተሰብ ዘንድ ሁለቱም እኩል መነቀፍ ሲገባቸው ፣ ቢያንስ ቢያንስ ተወቃሿና የጋብቻ ጠንቅ መስላ የምትቆጠረው ሚስትየዋ ናት ። ይህ በአብዛኛው በካፒታሊስትና በፊውዳል ኅብረተሰብ ዘንድ የሚንጸባረቅ ነው ። የዚህም ምንጩ የኢኮኖሚ ጥገኝነቷ ነው ።

በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ የሴቶች ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ ተሳትፎአቸው በጣም አነስተኛ ነው ። በመሆኑም ሴት በጋብቻ ግንኙነት ሂደት ውስጥ በቤተሰብ ገቢ ላይ ዝቅተኛ አስተዋጽኦ አላት ።

Digitized by Google

ይህ ሁኔታ ደግሞ ከወንድ ፈቃድ ሥር እንድትወል አድርጉታል ። ወንድ የቤተሰብ ገቢን በማስገኘት ላይ የበለጠ ድርሻ ስለአለው አንዳንድ ጊዜም ብቸኛ ገቢ አስገኝ ሆኖ ስለሚገኝ በጋራውና እኩልነት በሚያስፈልገው ኑሮ ላይ የበላይነቱን ተግባራዊ እያደረገ ይኖራል ። ይህም ቤተሰባዊ አስተያየቷንና ማኅበራዊ ተሳትፎዋንም እርሱ ከሚፈልገው ውጭ እንዳይሆን የመቆጣጠር መብት ሰጥቶት ይታያል ። የኅብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ነጸብራቅ የሆነውና በጋብቻ ውስጥ የሚታየው የሴት የኢኮኖሚ ጥገኝነቷም በቤተሰብ ውስጥ ሊኖራት የሚገባውን ግንኙነትም የእኩልነት ተሳትፎዋንና አኗኗሯን ይጠናወተዋል ።

ከዚህም በቀር ሴት በቤተሰብ ውስጥ የኢኮኖሚ ጥገኛ መሆኗ ብቻ ሳይሆን ወንድ በሚያስገኘው ገቢ ላይም በእኩልነት የማዘዝ መብት የማጣቷም ጉዳይ አለ ። ወንድ የገቢው ብቸኛ ምንጭ ከመሆኑም ባሻገር ከቤተሰብ ውጭ ባለው ማኅበራዊ ግንኙነት የተነሳ ከሚያገኘው ገቢ ከፊሉን ወይም አንዳንድ ጊዜም ይበልጡን ሴቷ በማታውቀው ሁኔታ የማጥፋቱ ተግባር በጋብቻ ግንኙነት ላይ ጠንቅ ሆኖ ይታያል። ይህ ሁኔታ ልማዳዊ ቢሆንም ቅሉ በቡርዧውም ሆነ በፊውዳሉ ኅብረተሰብ ዘንድ ማኅበራዊ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ይታያል ።.

የጋብቻ ግንኙነት ከሥርዓተ ማኅበሩ ገጽታዎች አንዱ በመሆኑ በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ የሚታዩት ችግሮች በሥርዓቱ አጠቃላይ ችግሮች ውስጥ ያሉና የሚኖሩ ናቸው ። ዓይነተኛ መፍትሔያቸውም የሥርዓቱ ሹም ሽር ነው ።

ጋብቻ በሶሻሊስት ሥርዓት

ሶሻሊዝም ሴትንና ወንድን በምርትና በጋብቻ ግንኙነት እኩል ያደረገ በመሆኑ ጋብቻ በጋራ መፈላለግና መፈቃቀድ፣በጋራ መከባበርና ልጅን ወልዶ በጋራ ኃላፊነት፣ በፍቅርና በጋራ በማሳደግ ላይ የተመሠረተ ነው ።[8] የሶሻሊስት ሕብረሰብ ተጋቢዎች በጋብቻ ግንኙነታቸው የሚኖራቸውን የእኩልነት መብት በሚመለከት የአንዱን ዝቅ የሌላውን ከፍ የሚያደርገውን ሃይማኖታዊ አስተሳሰብም ሆነ ድንጋጌ ወይም የብሔረሰብ ልማዳዊ እምነት ቦታ አይሰጠውም ። ተጋቢዎች በጋብቻ ውስጥ የሚኖራቸውን ቁሳዊ ጥቅምም በእኩልነት ደረጃ ይጠብቅላቸዋል ። በመሆኑም ሶሻሊዝም ይህን ዓይነቱ ግንኙነት በእኩልነትና ነፃ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ሆኖ እንዲኖር በሕጋዊና ስነምግባራዊ ድንጋጌዎች ያስከብረዋል ።

ጋብቻ የሁለት ተጋቢዎች ብቻ ነፃ ፈቃድና መፈላለግ ውጤት መሆኑን የአካባቢው ኅብረተሰብ እስከአልተቀበለው ድረስ የቤተሰብ ጽኑ መሠረትና ዝልቀት ሊኖር አይችልም ። በጋብቻ ውስጥ የሶስተኛ ሰው ተዋናይነት ማኅበራዊ መሠረት ሊያጣ ይገባዋል ። ይህ ዓይነቱ ተግባር የተጋቢዎችንም የነፃ አስተሳሰብና የራሳቸውንም ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብት ይጻረራል ። ይህም አሠራር ከመደብ ጥቅም ጋር የተያያዘ በመሆኑ ሶሻሊዝም አይቀበለውም ። ሕጋዊ ድጋፍም አያደርግለትም ። ምክንያቱም «በሶሻሊስት ሥርዓት ጋብቻ በፈቃደኝነትና በእኩልነት ላይ የተመሠረተና ከሶስተኛ ሰው ጣልቃ ገብነትና ለግል ጥቅም ብቻ ከማሰብ ነፃ የሆነ የወንድና የሴት ግንኙነት ነውና ።»[9]

በመደብ ኅብረተሰብ ዘንድ በጋብቻ ውስጥ የሴትን መብት ከሚቀንሱት ሁኔታዎች አንዱ ሴትን ከቁሳዊ ንብረት ጋር የማያያዙ ጉዳይ ነው ። ይህም ሁለት ገጽታ አለው ። አንደኛው ለጋብቻ ግንኙነት የሚያበቃ ቁሳዊ ንብረት ወይም ውርስ ያላትና የሌላት የመሆኑ ጉዳይ ሲሆን ፣ ሁለተኛው ደግሞ በወንዱ ቁሳዊ ሀብት ተዳዳሪ ሆኖ ለጋብቻ ግንኙነት መብቃቷ ነው። እነዚሁ ሁኔታዎች ሴትን በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ እንደዕቃ የመቆጠር ተግባርን

Digitized by Google

ያመለክታሉ ። ይሁንና እንዲህ ያለው ሁኔታ በሶሻሊዝም ምንም ዓይነት ሕጋዊም ሆነ ማኅበራዊ ፣ ሃይማኖታዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ መሠረት ስለሌለው ማኅበራዊ ችግር ሆኖ አይኖርም ።

በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ ሊኖር የሚገባው የእኩልነት መሠረት ባንድ ወገን የቁሳዊ ሀብት መኖርና የቤተሰብ ቁሳዊ ሀብት ምንጭ ደግሞ የሁለቱም ተጋቢዎች የጋራ ኃላፊነት ሲሆን ነው ። በሌላ ወገን ሁለቱም በኅብረተሰብ እንቅስቃሴ ውስጥ ለሚኖረው ማኅበራዊ ተሳትፎ እኩል መብት ያላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው ። ይህ ደግሞ የአንድ ሥርዓተ ማኅበር ጠባይ በመሆኑ እውን ሊሆን የሚችለው በሶሻሊዝም ብቻ ነው ።

ሶሻሊዝም በጋብቻ ቁሳዊና መንፈሳዊ ግንኙነት ውስጥ አንዱ ላንዱ የኢኮኖሚ ጥገኛ የመሆንንና በሕግ ፣ በስነምግባር በስነልቡናና በሃይማኖት አድልዎ አንዱን አንዱ የሚያጠቃበት ሁኔታ መኖርን ባለመፈቀዱ ፣ ጋብቻ በሁለቱም ጾታዎች እኩልነት ላይ የተመሠረተ ይሆናል ። የጋብቻ ጭቆናም የመደብ ኅብረተሰብ አጠቃላይ ጭቆና አካል በመሆኑ በሶሻሊስት ሥርዓት መክስትና እውን መሆን ያከትማል ።

የአዲሱ ኅብረተሰብ የጋብቻ ሥርዓት በእኩልነት ፣ በጋራ መተሳሰብና መፈቃቀር ፣ በጋራ የቤተሰብ ኃላፊነትና ማኅበራዊ ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ ይሆናል ። ከፊውዳላዊና ካፒታሊስታዊ የጋብቻ አመለካከት ነፃ የሆነ ኅብረተሰብ የሶሻሊስት ኅብረተሰብ በመሆኑ ለጋብቻ ግንኙነት ትክክለኛውን ግንዛቤ ይሰጠዋል ። ጋብቻ ከማንኛውም ማኅበራዊ ጠንቅ ሁሉ ነፃ የሆነ ግንኙነት ሊኖረው የሚችለው በሶሺያሊዝም ብቻ ነው ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. Great Soviet Encyclopedia, Vol. 3, p. 720.
2. *Ibid.*,
3. *Ibid.*, p. 72
4. *Ibid.*,
5. Marx, K. and Engles, F. Vol. 1, p. 162.
6. ፍትሐ ነገሥት ፣ ንባብና ትርጓሜው ፣ አዲስ አበባ ፣ 1958 ፣ ገጽ 294 ።
7. Marxism Communism and Western Society, (Vol. 3), (Herder and Herder, N.Y., 1972), p. 264.
8. Rosenthal M. and Yudin P., A Dictionary of Philosophy, p. 158.
9. Great Soviet Encyclopedia, Vol. 3, p. 720.

[illegible]

1/ [illegible] 1976 [illegible]
ሀ. [illegible] 22 [illegible] 1980 [illegible] 1981 [illegible]
ለ. [illegible] 40 [illegible] [illegible]

2/ [illegible] 1976 [illegible] 16 [illegible] 46 [illegible]
[illegible]

[illegible] 1960 [illegible] 1975 [illegible]

ተ.ቁ.	[illegible]	1960	1965	1966	1967	1969	1970	1972	1974	1975
		ብር	ብር	ብር	ብር	ብር	ብር	ብር	ብር	ብር
1	[illegible]	236,675	174,320	217,900	582,010	512,637	669,946	2,068,942	2,055,102	1,768,387
2	[illegible]	571,085	116,086	145,108	969,207	622,146	700,150	1,778,137	762,561	1,406,204
3	[illegible]	22,082	-		29,732	276,029	143,805	465,439	2,587,411	575,261
4	[illegible]	22,841	281,200	551,500	267,283	224,477	160,870	755,117	2,331,560	5,816,556
5	[illegible]	11,368	34,694	43,367	97,115	105,414	270,176	160,332	82,336	39,414
6	[illegible]	244,611	134,245	167,806	210,061	135,414	157,142	688,212	1,395,424	1,032,032
	ድምር	1,108,662	740,545	925,681	2,155,408	1,876,117	2,102,089	5,914,079	9,212,394	10,637,854

Digitized by Google

Digitized by Google

Digitized by Google

መስከረም

ቅጽ 4 ቁጥር 18

ሰኔ 1976

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተዓለም መጽሔት

ማውጫ

ገጽ

- የዝግጅት ገፅ 3
- የዜጐች መሰረታዊ መብቶች ፣ ነፃነቶችና ግዴታዎች—ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ገጽታዎች (ክፍል አንድ) 7

  — መዝገቡ ምትኬ
- የህብረት ሥራ ማህበር ታሪካዊ አመጣጥ 23

  — አሰፋ ሁብቴ
- የኢትዮጵያና የምዕራቡ ዓለም ግንኙነት—አንዳንድ ገጽታዎች (እስከ 1950ዎቹ) 45

  — ጠንክር ተረዳ
- የእምነት በዓላት ብዛት በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ኑሮና የሥራ ዕቅድ ላይ ያስከተለው ችግር 57

  — ኢሳይያስ ደምሴ
- የመስከረም መጽሔት ማውጫ 78

  — ደግፌ ገብረ ጻድቅ

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ

አድራሻ

የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001

የስልክ ቁጥር — 113000

Digitized by Google

ኢሠፓአኮ

ያለ አብዮታዊ ንድፈሐሳብ
አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊኖር አይችልም!

Digitized by Google

የዝግጅት ገፅ

ማሌ ርዕዮተዓለም – የአዝማች ፓርቲ የትግል መመሪያ

ርዕዮተዓለም የማኅበራዊ ንቃተሕሊና ዋንኛው ገጽታ እንደመሆኑ፣ የአንድን ኅብረተሰብ ልዩ ልዩ የኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጠባዮች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያንፀባርቅ፣ የተወሰኑ መደቦችን ጥቅምና ፍላጐት የሚገልጽ፣ ነባር የሆነ የምርት ግንኙነትንና በግንኙነቱም ላይ የተገነባውን የፖለቲካ ላዕላይ መዋቅር ለማቀየት ወይም ለማፍረስ የቆሙና የሚያልሙ አመለካከቶችንና አስተሳሰቦችን የሚያቅፍ የንድፈሐሳብ ቀንበር ነው።

ርዕዮተዓለም የተለያዩ የማኅበራዊ ንቃተኅሊና ቅርጾችን ማለትም ፖለቲካን፣ ሕግን፣ ፍልስፍናን የተለያዩ የማኅበራዊ ሳይንስ የትምህርት ዘርፎችን፣ ሥነ ምግባርን፣ ኪነጥበብን ሃይማኖትን፣ ወዘተ፣ የሚያጠቃልል ነው። በመደብ ሥርዓተ ማኅበራት እነዚህ ሁሉ ተጠቃለው በተቀናጀና ሥርዓት ባለው መልክ ሲከሰቱ የመደብ ርዕዮተዓለምን የሚገልፁ ይሆናሉ ።

በመደብ በተከፋፈሉ ኅብረተሰቦች የርዕዮተዓለም ትግልና ግጭት የማኅበራዊ ለብዮቶች መሠረታዊ መንስኤ ከሆነው ከምርት ኃይሎችና ከምርት ግንኙነቶች ቀራኔና ለለመጣጣም የሚመነጭ ነው ።

ማኅበራዊ ንቃተሕሊና መሠረቱ ማኅበራዊ ሕልውና የመሆኑን ያህል፣ የማኅበራዊ ንቃተሕሊና ከፍተኛና ዋንኛ ገጽታ የሆነው ርዕዮተዓለም ዕድገትና የለውጥ መሠረቱ በኅብተሰብ ውስጥ የመደቦች ቁሳዊ ሕይወትና ማኅበራዊ ግንኙነት መለወጥ ነው። ይሁንና የአንድ መደብ ርዕዮተዓለም ያ መደብ በኅብረተሰብ ውስጥ የበላይነቱን እንዳጣ ወዲያውኑ የሚከስም ሳይሆን፣ የአዲሱን መደብ ያላሰለሰ የርዕዮተዓለም ትግል የሚጠይቅ ነው።

በመደብ ሥርዓተ ማኅበራት ውስጥ የማናቸውም መደብ ርዕዮተዓለም ዓላማ በመደቡ ርዕዮተዓለም ንቃት ላይ በመመሥረት በተወሰነ ኅብረተሰብ ውስጥ በፖለቲካ፣ በኢኰኖሚና በማኅበራዊ መስኮች ጥቅሙን በሚገባ እንዲያራምድ ማስቻል ነው። ይኸንንም ለማድግ እያንዳንዱ መደብ በሚመራበት ርዕዮተዓለም ላይ በመመሥረት የመደብ ጥቅሙን ለማስበከርና ታሪካዊ ተልዕኮውን ለመወጣት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል። ተፃራሪ መደቦች ባሉበት ማናቸውም ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የበላይነት ያለው መደብ በርዕዮተዓለማዊና ፖለቲካዊ መሣሪያው ፣ ማቴሪያላዊ ጥቅሙን የሚጠብቅለትን ማኅበራዊ ግንኙነት እንዳለ ለማቀየትና ለማሻሻል ሲታገል፣ የተጨቀነው መደብ ደግሞ በራሱ ርዕዮተዓለም በመመራት በማኅበራዊ አብዮት አማካይነት አዲስ ኅብረተሰብ ለማዋቀር ይነሳል። በዚህም ሂደት ትግሉ በአዲሱ ኅብረተሰብ መሥራች መደብ ወይም መደቦች አሸናፊነት እልባት በማግኘት አዲስ የኢኖሚና ማኅበራዊ ግንኙነት ሲመሠረት ፣ ይህንኑ ሁኔታ የሚያንፀባርቀው ርዕዮተዓለም የቀድሞውን ርዕዮተዓለም በመተካት ይከሰታል። በዚህ መሠረት ለማናቸውም ማኅበራዊ አብ

Digitized by Google

ዮት ወደፊት መግፋትና ገበ መምታት ርዕዮተዓለም ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

ገቡ ሶሺያሊዝም መሆኑን ያወጀ አንድ ማኅበራዊ አብዮት በተለይም ይኸን አብዮት የሚመራው ፓርቲ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርዕዮተዓለም በሚገባ እስካልታጠቀ ድረስ፣ ትግሉን ከግብታዊነት በማላቀቅ እግቡ ለማድረስ የሚያስችለውን ሳይንሳዊ የሆነ ፕሮግራም ሊነድፍ፣ ትክክለኛ ስትራቴጂና ስልት ሊቀይስ አይችልም።

አንድ ማሌን መመሪያው አድርጐ የተነሳ አብዮታዊ ፓርቲ ለሚመራው ሰፊ ሕዝብ ትክክለኛ አመራር በመስጠት ታሪካዊ ተልዕኮውን በሚገባ ለመወጣት መቻሉ የሚወሰነው ፓርቲው በማሌ ርዕዮተዓለም የታነፀና በውስጣዊ አሠራሩም የሌኒን የአዲሱን ዓይነት ፓርቲ የአሠራር መርህ ለማዋሃድ ተገቢውን ጥረት ያደረገ እንደሆነ ብቻ ነው።

የኢትዮጵያ አብዮት ባለፉት አስር ዓመታት የመሪ ፓርቲን አመራር ለማቀዳጀት፣ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ አብዮታዊ አመራርና በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አማካይነት አሁን የምንገኝበት አስተማማኝ የሆነ ደረጃ ላይ ለመድረስ፣ በሌሎች ዘር ፎች እንደተደረገው ሁሉ በርዕዮተዓለሙም ዘርፍ ከፍተኛ ትግል ሲያካሂድ ቆይቷል።

በየካቲት 1966 የተቀጣጠለው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ከመጀመሪያው የፓርቲ አመራርን ለመቀዳጀት ባይታደልም፣ ጠላትና ወዳጅን በመለየት ወደፊት እንዲገፋና እመርታ እንዲያሳይ ለማድረግ ያስቻለው ሶሺያሊዝም የሀገሪቱ ይፋ መመሪያ ሆኖ መታ ወጁ፣ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መውጣቱ፣ በዚህም መሠረት የማሌ ርዕ ዮተዓለምን በስፋት በኅብረተሰቡ ውስጥ ለማስረጸጪትና የአብዮቱም ወገኖች የትግል መመ ሪያ እንዲሆን ለማድረግ በመቻሉ እንደሆነ የሚዘነጋ አይደለም።

በመጀመሪያዎቹ የአብዮት ዓመታት ለአብዮቱ በቀሙ መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍ ሎች ውስጥ የማሌን ርዕዮተዓለም በስፋት ለማሠራጨት በመቻሉ የአብዮቱን ዓላማዎችና ግቦች እንዲረዱ፣ ወቅቱ በጠየቀው የትግል ስልት ታክቲክ መሠረት ትግላቸውን እንዲያካ ሂዱ ለማድረግ ተችሏል። ከዚህ አንፃር በየደረጃው አብዮቱን ለመቀልበስ ተነሣሥተው የነበሩ ትን ፀረ አብዮት ኃይሎች ድል ለመምታትና የአብዮቱን ሕልውና ለማስከበር የተቻለው ለአ ብዮቱ ወደፊት መግፋት በግንባር ቀደምትነት ቆመው በነበሩ ኃይሎች ውስጥ የማሌን ርዕ ተዓለዮም ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ለማሠራጨት በተደረገው ጥረት ነው።

ከኢሠፓአኮ መከሰት በኋላም የማሌ ርዕዮተዓለምን ለማስራጨት በተደረገው ጥረት ከቀድሞው በተሻለ ሁኔታ በተቀናጀና ማዕከላዊነትን በተከተለ አኳኋን ለመምራት ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። አብዮቱ በወለዳቸው በተለያዩ መድረኮች በመጠቀም የማሌን ርዕዮተዓለም ለማሠራጨት በተደረገው ከፍተኛ ጥረት በአብዮቱ ሂደት በተለያየ ወቅት የተከሰቱ አድኃ መስመሮችን ለማጋለጥ፣ ትክክለኛውን መስመር ለሕዝቡ ለማስጨበጥና አብዮቱን ወደፊ ለማራመድ ተችሏል።

በዚህ መሠረት ባለፉት አሥር ዓመታት በኢትዮጵያ የማሌ ርዕዮተዓለም በስፋት እንዲሠራጭና የሕዝቡም የትግል መመሪያ እንዲሆን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደረጓል። ሆኖም በፖለቲካ ድርጅቱ አባላት በኩልም ሆነ በአጠቃላይ በሕዝቡ ዘንድ በርዕዮተ ዓለሙ ግንዛቤ በኩል የተደረሰበት ደረጃ አሁንም በበለጠ መዳበር ይኖርበታል።

በመሠረቱ የርዕዮተዓለም ስርጭት ሥራ ውጤታማነት የሚለካው በሕዝቡ የአደ

Digitized by Google

ረጃጀትና የሥራ እንቅስቃሴ ላይ በሚያስከትለው ፍሬያማ የሆነ ለውጥ ነው ። ይሁንና በሕሊናዊ መስክ የሚደረገ ለውጥ ዘለቄታዊነት ተጨባጭ በሆነው ማቴርያላዊ መስክ ለውጥ ላይ መመሥረት ያለበት በመሆኑ ፣ በዚህ ረገድ የወረስነውም ሆነ አሁን ያለንበት ዝቅተኛ ኤኮኖሚያዊ ፣ የማኅበራዊና ባህላዊ የዕድገት ደረጃ ለሰፊው ሕዝብ ማኅበራዊ ንቃተሕሊና እድገት እንቅፋት መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም ። በተለይም የማሌ ርዕዮተዓለም ማኅበራዊ መሠረት የሆነው የሠራተኛው መደብ ገና በበለጠ ማደግ ባለበት ፣ አነስተኛ የሸቀጥ ምርት በሰፈነበትና ከዚህም የአመራረት ዘይቤ የመነጩ ኋላቀር አመለካከቶች ፣ ልማዶችና ወጉች ወዘተ … ባልተወገዱበት ፣ የፖለቲካ ባህል በሚገባ ባልተስፋፋበት ኅብረተሰብ ይህን ሁኔታ መለወጥ የረዥም ጊዜ የተጠናከረ የርዕዮተዓለም ሥራ ማካሄድን ይጠይቃል ።

ከአስር ዓመታት መራራና ውስብስብ ትግል በኋላ አሁን አብዮቱ በደረሰበት የዕድገት ደረጃ በድርጅት ዘርፍ የመሪ ፓርቲው የኢሠፓ ሕልውና ሊከሰት የተቃረበበት ፣ በፖቲካውም ዘርፍ በኢሠፓ አመራር የኢትዮጵያን ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፖብሊክ በመመሥረት አዲሱን ሕዝባዊ የፖለቲካ ሥርዓት ለማዋቀር ዝግጅቱ የሚካሄድበት ወቅት ነው ። በኢኮኖሚው ዘርፍ ለምርት ኃይሎች መዳበርና ለሶሺያሊስት የምርት ግንኙነቱም በጥራት መስፋፋት ትኩረት የምንሰጥበት በፓርቲና በመንግሥት የውጭ ግንኙነት ዘርፍ የአብዮቱ አስተማማኝ አጋሮች ከሆኑት ከሶሺያሊስት አገሮች ጋር የሚኖረው ግንኙነት ይበልጥ ሥር እንዲሰድና እንዲጠናከር ለማድረግ ቀርጠን የተነሳንበት ወቅት ነው ። እነዚህ እርምጃዎች በአብዮቱ ዲሞክራሲያዊ ሂደት ለተከናወኑ አብዮታዊ ለውጦች ስፋትና ጥልቀት የሚሰጡ እንደመሆናቸው ፣ የእንግዲሁ የርዕዮተ ዓለም ሥራ እነዚህ ሥር ነቀል ክንውኖች በወቅቱ የመደብ አሰላላፍ ላይ የሚያስከትሉትን ለውጥ የሚያገናዝብና የወቅቱ የተካረረ የመደብ ትግል ከሚጠይቀው ሁኔታ ጋር የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል ። ከዚህ አንፃር በተለይ የወቅቱ የርዕዮተዓለም ሥራ የንዑስ ከበርቴው ርዕዮተዓለም ዓይነተኛ ገጽታ የሆነውን ብሔረተኝነትን ፣ የኢምፔሪያሊስቱን ዓለም በሃሰት ላይ የተመሰረተ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ለማከሸፍ የሚችል መሆን አለበት ።

እንደሚታወቀው ተራማጅና አዲስ ሥርዓት ለመገንባት በተነሳሳ ኅብረተሰብ ውስጥ የርዕዮተዓለም ሥራ ውጤት የሚለካው የአብዮቱ ወገኖች የመሪውን የፖለቲካ ድርጅት ወይም ፓርቲ ፖሊሲ በሚገባ በመገንዘብ ፣ ፖሊሲው የነሱን መሠረታዊ ጥቅም ለማራመድ የቆመ ፖሊሲ ስለመሆኑ ሙሉ እምነት ሊያሳድርባቸው በመቻሉ ነው ። በፓርቲ የርዕዮተዓለም ሥራ መስክ እጅግ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሠረታዊ ጉዳይ ቃል ከተግባር ጋር በሚገባ መጣጣሙን ፣ የነገሮች ይዘት በቀርጽ አለመተካቱን ማረጋገጥ ነው ።

በቀርቡ ሕልውናው የሚከሰተው ኢሠፓ የተያያዝነውን የሽግግር ወቅት በማገባደድ ሶሺያሊዝምን ለመገንባት የሚያስችለንን ሁኔታ በመፍጠር ታሪካዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት የተነሳው የማሌን ርዕዮተዓለም የትግል መመሪያው በማድረግ ነው ። ከዚህ አንፃር መሪ ፓርቲያችን በኅብረተሰቡ ውስጥ ወደፊት በስፋት የሚያካሂደው የርዕዮተዓለም ሥራ ለአብዮቱ የቆመው ሠርቶአደር ሕዝብ ሁሉን አቀፍ የሆነውን የፓርቲውን ፕሮግራም በሚገባ እንዲገነዘብ ፣ ግንዛቤውንም ወደ ተግባር እንዲተረጉም ፣ ወደተግባር በመተርጐሙም ሂደት እያንዳንዱ የአብዮቱ ወገን እራሱን እንዲለውጥ ለማድረግ የሚያስችል እንደሚሆን አይጠረጠርም ።

Digitized by Google

ለኢሠፓ ምሥረታ ወደፊት !

Digitized by Google

የዜጎች መሠረታዊ መብቶች፣ነፃነቶችና ግዴታዎች –

ብሔራዊና ዓለምአቀፋዊ ገጽታዎች

(ክፍል አንድ)

መዝገቡ ምትኬ

ይህ ጽሑፍ ስለዜጎች መሠረታዊ መብቶች ፣ ነፃነቶችና ግዴታዎች አጠቃላይ ገለጻ ያደርጋል። ዛሬ ስለመብት ፣ ነፃነትና ግዴታ በየቦታው ሲነገር ፣ ሲወራና ሲተች መስማት ለጆሮ እንግዳ ነገር አይደለም ። የእነዚህ ጽንሰሐሳቦች መደባዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ይዘት በግለሰብ ፣ በቤተሰብ ፣ በኅብረተሰብ ፣ በመንግሥትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር ውዝግብና አለመግባባትን ሲያስከትል ቆይቷል ። የዚህ ብሔራዊ ፣ ዓለም አቀፋዊ ውዝግቢና አለመግባባት መንስኤ ጽሑፉ ትኩረት የሚያደርግበት ዋና ነጥብ ነው ።

ስለመብት ፣ ነፃነትና ግዴታ በሚወሳበት ጊዜ መረሳት የሌለበትና ቅድሚያ ቦታ ማግኘት የሚገባው የነዚህ ጽንሰሐሳቦች ባለቤት የሆነው ሰው ነው ። እዚህ ላይ የምንጠቅሰው ሰው ሰብዓዊ ሕልውና ያለውን የተፈጥሮ ሰው እንጂ የሕግ ሰውነት ያለውን አካል አይደለም ። ከጥቂት የገዥ መደብ አባሎች በስተቀር መብትና ነፃነት ሳይኖረው ስፍር ቁጥር በሌለው ግዴታ በመተብተብ ታሥሮ የነበረውን ሰው መርሳት ሕያውነት ባለው የታሪክ ማኅደር ከመወገዝ አያድንም ። ዛሬም ቢሆን የሰው ልጅ የተሟላ መብትና ነፃነቱን ተጐናጽፏል ማለት አይደለም ። እንደየሥርዓተ ማኅበሩ የዕድገት ደረጃ ዓይነት የአንድ አገር ዜጋ ያልሆነ ሰው የሌለውን መብትና ነፃነት የዜግነት መብት ያለው ግለሰብ በተለይ ሊኖረው ይችላል ። ይህም ማለት ሰው በማለት የምንጠቅሰው ግለሰብ በስደተኝነት ፣ በአገር አልባነት ወይም በባዕድነት ተጠልሎ በሚኖርበት አገር ውስጥ ለሚኖሩት የሀገሪቱ ዜጎች ከሚሰጠው መብትና ነፃነት ሙሉ በሙሉ ተካፋይ ላይሆን ስለሚችል ነው ። ይህ ዓይነቱ ሰው የሚኖርበትም ግዴታ ውሱን ነው ። በሌላ አነጋገር የአንድ አገር ዜጋ በሀገሩ ውስጥ ከማንኛውም ሌላ የሀገሩ ዜጋ ካልሆነ ሰው የተሻለ መብትና ነፃነት ሲኖረው በአንጻሩ የሚኖርበት ግዴታም የበለጠ ከባድ ነው ።

Digitized by Google

ይህ ጽሑፍ በሁለት ክፍሎች ተከፍሏል። የመጀመሪያው ክፍል ስለ ዜግነት ፣ መብትና ነፃነት የሚመለከት ነው ። ስለዜጐች መብት ፣ ነፃነትና ግዴታ ለመጻፍ በሚሞከርበት ጊዜ በመጀመሪያ የመብት ፣ የነፃነትና ግዴታ ባለቤት ስለሆነው ዜጋ ወይም ስለዜግነት ጽንሰ ሐሳብ ምንነትና ታሪካዊ ዕድገት በአጭሩና በአጠቃላይ ማቅረብ ተገቢ በመሆኑ የጽሑፉ መጀመሪያ የሚያተኩረው በዚህ ርዕስ ላይ ነው ። ከዚያ ቀጥሎ የሚቀርበው ስለነፃነት ጽንሰ ሐሳብ ምንነት ፣ በየሥርዓተ ማኅበሩ ስላሳየው የይዘት ዕድገትና ስለርዕዮተዓለማዊ ባሕርይ ይሆናል ። በዚሁ ክፍል አንድ መጨረሻ ላይ ስለመብት ምንነት ፣ ከነፃነት ጋር ስላለው ግንኙነትና እንደነፃነት ሁሉ ጽንሰ ሐሳቡ ስላሳየው ታሪካዊ ዕድገት በአጠቃላይ ይቀርባል ።

በክፍል ሁለት ለመግለጽ የሚሞከረው የዜጐች መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ጥያቄ የብሔራዊ መንግሥታት ጉዳይ ብቻ መሆኑ ቀርቶ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለመታወቁ ፣ ስለአገር አቀፍ መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ከዚህም ጋር ተያይዞ ስለመብትና ነፃነት ዓይነቶች ፣ በኢምፔሪያሊስትና ሶሻሊስት አገሮች መካከል ስላለው መሠረታዊ የመብቶችና ነፃነቶች ሕጋዊና ቁሳዊ ዋስትና አሰጣጥ ልዩነቶችና ስለዜጐች ግዴታ ነው ።

ዜግነት ፣ መብትና ነፃነት

የዜግነት ጽንሰ ሐሳብ

በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኝ የማንኛውም ግለሰብ ሕጋዊ አቋም ከወቅቱ ስልተምርት ዓይነትና የዕድገት ደረጃ ተገኙነት ነፃ ሊሆን አይችልም ። በመደብ አልባው የጥንቱ ጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር የነበረው ግለሰብ ሕጋዊ አቋም በመደብ በተከፋፈለ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ከሚገኝ ግለሰብ ሕጋዊ አቋም የተለየ ነው ። በመደብ በተከፋፈለ ሥርዓተ ማኅበር የሚገኝ ግለሰብ ሕጋዊ አቋምም እንደመደቡ ግንኙነት ማለትም እንደመደቡ ተጻራሪ መሆንና አለመሆን ሊለያይ ይችላል ።

በመደብ አልባው የጥንቱ ጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የነበረው ግለሰብ ሕጋዊ አቋም ተወስኖ የነበረው በወቅቱ ሰፍኖ በነበረው የመላው ኅብረተሰብ ወግ ፣ ሥነ ምግባርና ደንቦች ነው ።

በሌላ በኩል በመደብ በተከፋፈለ ሥርዓተ ማኅበር ሁሉ መንግሥት የሚባል የመጨቆኛ መሣሪያ መኖር ግድ በመሆኑ ፣ በሚያወጣው ሕግ መሠረት የግለሰብን አቋም የሚወስነው ይኸው መንግሥት ሆነ ። እንዲህ ባለው ሥርዓት ውስጥም የግለሰብ አቋም በመደቦች መካከል ባለው ግንኙነት ማለትም በመደቦቹ መጣጣምና አለመጣጣም ፣ በቅራኔያቸው ተጻራሪነትና ተጻራሪ አለመሆን ይወሰናል ።

ዓይነተኛ የምርት መገልገያዎች በግል ይዞታ ሥር በሆኑበት ሥርዓተ ማኅበር ሁሉ የግለሰብ አቋም የሚለካው ባለው የሀብት መጠን እንጂ በሰብዕናው አይደለም ። የሰዎችም እኩል አለመሆን የሚመነጨው ከምርት መገልገያዎች በግል ይዞታ ሥር መሆን ነው ። የምርት መገልገያዎች ይዞታ በግል የጥቂቶች መሆንም የይዞታ መብት የሌለውን አብዛኛውን የኅብረተሰብ ክፍል ሠርቶ አደሩን ሕዝብ ለብዝበዛና ለጭቆና ዳርጐታል ። በዚህም ምክንያት የመደቦች ቅራኔ ተጻራሪና የማይታረቅ ይሆናል ።

በአንጻሩ በሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር የምርት መገልገያዎች በሕዝብ ይዞታ ሥር መሆን ብዝበዛን አስወግዶ በምትኩ እኩልነትንና ነፃነትን ለማስፈን በመቻሉ የዓለም ሠርቶአደር ሕዝብ ለዚህ ሥርዓት በመቆም ያላሰለሰ ትግል በማካሔድ ላይ ይገኛል ። በዚህ ሥርዓት ውስጥ መደቦች ቢኖሩም በመካከላቸው የሚኖረው ቅራኔ ሊታረቅ የሚችልና ከራሳቸው ከመደቦቹ መክሰም ጋር አብሮ የሚጠፋ ነው ።

Digitized by Google

ከዚህ በላይ በአጠቃላይ እንደተመለከተ
ው በመደብ የተከፋፈለ ኅብረተሰብ ካለ
ባቸው ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ የግለሰብ
አቋም በሕግ የተወሰነ ቢሆንም ፣ ግለሰቡ
መብቶቹን ለማረጋገጥ የሚያስችለው ቁሳ
ዊ መሠረት ካለማግኘቱም በላይ ሕጉም ቢ
ሆን የጭቁን መደቦችን ጥቅም በሚመለ
ከት ረገድ ላይስሙላ የታወጀ እንጂ በትክ
ክል በተግባር ሊተረጐም የሚችል አይደ
ለም ። ፀረ—ብዝበዛ በሆነው የሶሻሊስት
ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሚገኘው ግለሰብ
አቋምም ግልጽ ነው ። በቀደምቶቹ ሌሎች
ሦስት ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ ለሰዎች
እኩል አለመሆን መሠረታዊ ምክንያት የነ
በረው የምርት መገልገያዎች በግል ይዞታ
ሥር መሆን አክትሞ የሰው በሰው መበ
ዝበዝ ስለሚቀር ቁሳዊ መሠረት ያለው በ
ሕግ የተደገፈ እውነተኛ ነፃነትና እኩል
ነት የሚሰፍነው በዚህ ሥርዓተ ማኅበር ይ
ሆናል ።

እስካሁን ድረስ በአጠቃላይ ለመዳሰስ
የተሞከረው በተለያዩ ሥርዓተ ማኅበሮች
ውስጥ በአንድ ኅብረተሰብ ወይም መንግ
ሥት እና በግለሰብ መካከል የሚኖረውን
ሕጋዊ ግንኙነትና በዚህ ግንኙነት ሳቢያ
የግለሰቡ እኩልነትና ነፃነት እስከምን ድረ
ስ እንደሆነ ነበር ። ከመንግሥት ወይም ከኅ
ብረተሰብ ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት የተጠ
ቀሰውና እስካሁን ግለሰብ እየተባለ ይጠ
ራ የነበረው ሰው ደረጃ (አቋም) በሦስት
ተከፍሎ ሊታይ ይችላል ። ግለሰቡ ፣ 1/የአ
ንድ አገር ዜጋ ፣ 2/ የውጭ አገር ሰው ፣ ወ
ይም 3/ አገር የሌለው ሰው ሊሆን ይችላል።
ጣንድ ዜግነት ያላቸው (የሁለት አገሮች ዜ
ጐች የሆኑ) እና የፖለቲካ ስደተኞች ሆነው
ከሀገራቸው ወጥተው በሌላ አገር የሚኖሩ
ሌሎች ግለሰቦች ከላይ ከተጠቀሱት ሦስት
ክፍሎች አንደኛው ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ።[1]

ከዚህ በላይ በአንደኛው ተራ ቁጥር ስለ
ተመለከተው ስለዜጋ ወይም ስለዜግነት
ምንነት ፣ ጽንሰ ሐሳቡ በየሥርዓ ተ ማኅበሩ
እንዴት ይታይ እንደነበርና የሰው ልጅ
አሁን በደረሰበት የዕድገት ደረጃ ዜግነት
ስለሚያስከትለው መብት ፣ ነፃነትና ግዴታ
ዘርዘር አድርገን ለመመልከት እንሞክ
ራለን ።

የዜግነት ምንነት

ዜግነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቅ
ድሚያ መግለጽ የጽንሰ ሐሳቡን ይዘት ግ
ልጽ ለማድረግ ስለሚጠቅም ከትርጉም መ
ነሳት ተገቢ ይሆናል ። በተለመደው ተራ
አነጋገር ዜግነት ማለት ዜጋ መሆን ማለት
ነው ። ዜጋ ማለት ደግሞ ገባር ፣ ተገዥ ፣
የሌላ ሰው ቅኝ ማለት እንደሆነ በደስታ ተ
ክለወልድ መዝገበ ቃላት ተተርጉሟል ።
ተሰማ ሀ/ሚካኤል በከሳቴ ብርሃን ተሰማ
ላይ ዜጋ ማለት «ዜጋ» ከሚለው የግዕዝ
ቃል እንደመጣና ትርጉሙም «በርስቱ ፣
በመሬቱ ለመንግሥት ገበረ ፣ ወይም በአ
ንድ መንግሥት ውስጥ የሀገር ነዋሪ ዜጋ
ሆነ ፣ ባላገር ተባለ» ማለት እንደሆነ ገልጸ
ውታል ። በአጠቃላይ የመጀመሪያው መዝ
ገበ ቃላት ዜግነት ማለት «ተገዥነት ፣ ገባ
ርነት ፣ ዜጋ መሆን»ማለት ነው ሲል ፣ ሁለ
ተኛው መዝገበ ቃላት ደግሞ «በርስቱ ፣
በመልከኛነት ፣ በዜግነት መኖር» ማለት
ነው ብሏል ። የነዚህ መዝገበ ቃላት አተረ
ጓጐም በአንድ ታሪካዊ ወቅት ማንም ሰው
የሚያውቀውን ተራ አገላለጽ የሚያመለ
ክት ይመስላል ። ሁለቱም መዝገበ ቃላት
ዜግነትን ከመሬት ፣ ከርስት ጋር አያይዘው
ታል ።

በኅብረተሰብ ታሪክ ውስጥ በመሬት ላይ
የተመሠረተ የመደቦች ኢኮኖሚያዊ ግንኙ
ነት በይበልጥ የሚታወቀው በፊውዳል ሥ
ርዓተ ማኅበር በመሆኑ ይህ ትርጉም በተ
ሻለ ሁኔታ የሚጣጣመው ለዚሁ ሥርዓተ
ማኅበር ነው ።

ዜግነት በግለሰብና በመንግሥት ወይም
በኅብረተሰብ መካከል ሕጋዊ ግንኙነት ይ
ፈጥራል ። ይህም ግንኙነት በመንግሥት
በታወጀ ሕግ ወይም በኅብረተሰብ ዘንድ

Digitized by Google

በታወቀና ተቀባይነት ባገኘ ወግና ሥነ ም ግባር ፣ በአንድ በኩል የግለሰቦችን መብ ት ፣ ነፃነትና ግዴታ ፣ በሌላ በኩል የመንግ ሥትን ሥልጣንና ኃላፊነት (የኅብረተሰ ቡን ተጽዕኖ) ይወስናል ። ይህ ሕጋዊ ግን ኙነት በጊዜና በቦታ የተወሰነ ባለመሆኑ ማንኛውም ዜጋ ከልደት እስከሞት ድረስ በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በየትኛውም ሀ ገር ቢሆን የመንግሥትን ጥበቃ የሚያስገኝ መብት ይሰጣል ።

ዜግነት በቅርብ ጊዜ የተፈጠረ አዲስ ጽ ንሰ ሐሳብ አይደለም ። የባሪያ አሳዳሪው ሥርዓተ ማኅበር እንደተከሰተና መንግሥት የተባለ የፖለቲካ ድርጅት እንደተፈጠረ ኅብረተሰብ ዜጋና ነዋሪ (ዜጋ ያልሆነ) ተ ብሎ በመከፈል ይታወቅ ነበር ። ለምሳሌ በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የነበረው የጥንቱ የሮማ ኅብረተሰብ ዜጎች ከነዋሪዎች ተለይተው የተሟላ መብት ነበ ራቸው ፤ የተለየም ልብስ ይለብሱ ነበር ።

ዜግነት በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ውስ ጥ የነበረውን ነፃ ሕዝብ የሚያሰባስብና የ ግል ንብረት የማበጀት መብቱን የሚጠብ ቅለት ድንጋጌ ሆነ ። በዚህ ወቅት ዜግነት ነፃና እኩል የሆኑ ግለሰቦች ድንጋጌ በመ ሆኑ የተመሠረተው በብዙ ሺህ በሚቆጠሩ ባሮች የግል ይዞታና ብዝበዛ ላይ ነበር።ባሮ ች ንብረትም ሆነ መብት አልነበራቸውም፤ በመሆኑም እንደዜጋ ቀርቶ እንደሰብአዊ ፍጡር አይቆጠሩም ነበር ። የወቅቱ ታዋቂ ፈላስፋ አሪስቶትል አባል የሆነበትን የገዥ ውን መደብ ጥቅምና ፍላጐት በማራመድ ፖለቲክስ በተባለው መጽሐፉ ባርነት በተ ፈጥሮ ሕግ መሠረት መኖር ያለበት ነው ፤ ባሪያና ነፃ ሰው እኩል ሊሆኑ ከቶ አይቻላ ቸውም ፤ ሊሆኑም አይገባቸውም ፤ ባሪያ በ መንግሥት አመራር ሥራ ውስጥ መካፈል የለበትም ፤ አይቻልምም ብሏል ።

በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓተ ማኅበር የነ ጻው ሕዝብ ሁሉ የእኩልነት አቋም ዘላ ቂና ቋሚ አልነበረም ። በጥንት ጊዜ ተዋቂ ነት የነበረው የግሪኩ ዲሞክራሲ እንኳ እጅ ግ ብዛት የነበራቸውን ነፃ ሰዎች የፖለቲካ መብት ነፍጓቸው ነበር ። በወቅቱ ዜግነት የጥቂት ነፃ ሰዎች ብቻ የመብት ምንጭ ነ በር ። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ4045 4ሺህ የሚሆኑ ነፃ ሰዎች የዜግነት መብታ ቸውን በቅጣት መልክ ተነፍገዋል ። ይህን መብት ሲነፈጉ ንብረታቸው ከመወ ረሱም በላይ ወደባርነት ተለውጠው ተሸ ጠዋል ። የዜጎች ብዛት እንዳይጨምር ለ መወሰን የዜግነት መብት የሚገኝበትን ሁ ኔታ በመዘርዘር ልዩ ሕጎችም ወጥተው ነበር ። [2]

በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ዜግነት ሙሉ ጥቅምና መብት የሚያስገኝ በኅብረተሰቡ ም ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚያሰጥ ሲሆን ፣ ባሮች ግን ዜጎች ባለመሆናቸው ገደብ የሌ ለው ግዴታ እንጂ መብት አልነበራቸውም። ይህም በአጠቃላይ በባሪያውና በባሪያ አሳ ዳሪው መደቦች መካከል መራራ ትግል እን ዲካሔድ አድርጓል ። የትግሉም ውጤት የባሪያው መደብ ከባርነት ዓለም ወደተሻ ለው ወደ ገባርነት የግዴታ ቀንበር መሸጋገር ነበር ። ይህ የተከሰተው በፊውዳሊዝም መፈጠር ነው ።

በፊውዳሉ ሥርዓት ገባሩ በግል የመሬት ከበርቴው ጥገኛ መሆን እና ልዩ ልዩ ነፃ የ ጉልበት ሥራ አገልግሎት ማበርከት ግዴ ታ መሆን በመካከላቸው የኢኮኖሚ ብቻ ሳ ይሆን የፖለቲካ ግንኙነት እንዲፈጠር አደ ረገ ። የመሬት ከበርቴው በገባሩ የምርት ውጤትና ጉልበት ላይ ብቻ ሳይሆን በራሱ ከገባሩም ላይ የማዘዝ ሥልጣን ነበረው ። በዚህ ሥርዓት በመጀመሪያ የነበረው ሕጋ ዊ ግንኙነት በገባሩና በመንግሥት መካከ ል ሳይሆን በገባሩና በመሬት ከበርቴው መ ካከል ነበር ። ይህም ግንኙነት ገባርነት (Subject) እየተባለ የሚታወቀው ሆነ ። በሁለቱ መካከል በውል ላይ የተመሠረተ የመብትና ግዴታ ግንኙነት ተፈጠረ።እርሱእ

Digitized by Google

ድር ነዋሪው ሁሉ የገባርነት መብት አገኘ። መሬት ከበርቴውም ለገባሩ ወታደራዊ ጥበቃ ያደርግ ነበር ። የዘውድ አገዛዝ ቀስ በቀስ እየተጠናከረ መምጣት በገባርና በመሬት ከበርቴ መካከል የነበረው ግንኙነት (ገባርነት) መልኩን በመለወጥ በጢሰኛና በፊውዳሉ መንግሥት መካከል ሆነ ።

የፊውዳሉ ሥርዓት እየዳበረ መሔድ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍልን አስከተለ ። ይህም በበኩሉ የንግድና የዕደጥበባትን የኅብረተሰብ ክፍሎች መፈጠርና የከተሞችን መቆርቆር አስገኘ ። በገባርነት ላይ በማመጽ ወደ ከተማ የገቡት ሰዎች በከተሞች የራሳቸውን የፖለቲካ ተቋሞች በማቋቋም በመሬት ከበርቴው ሥርዓት ውስጥ ሰፍና ከነበረው ገባርነት የተለየ የከተማ ዜግነት ተቋም ቀስ በቀስ ሊመሠ ቻለ። ወደ ከተማ የሚገቡት ሰዎች ሁሉ ዜጎች በመሆናቸው አንዳንድ መብቶችን መጐናጸፍ ቻሉ ። ዜጋ ማለት አንዳንድ የፖለቲካና የንብረት መብት ያለው ነፃ «የከተማ ነዋሪ» ማለት ሆነ ። በእርግጥ የከተማ ዜግነት ባለሙሉ መብቶች የነበሩት ታላላቅ ነጋዴዎችና የምርት መገልገያዎች ባለይዞታዎች ነበሩ ።

የፊውዳሉን ሥርዓተ ማኅበር የተካው የካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር የተመሠረተው በምርት መገልገያዎች ይዞታ በግል የካፒታሊስቱ መሆን እና ምንም ዓይነት የምርት መገልገያዎች የይዞታ መብት በማጣታቸው ጉልበታቸውን ለካፒታሊስቶች ለመሸጥ የተገደዱትን ሠራተኞች በመበዝበዝ ላይ ነው ። ሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ ቡርዧው « እኩልነትና ነፃነት » እያለ ባስተጋባው ዲሞክራሲያዊ መፈክር በመሳብ የፊውዳሉን ሥርዓት ለማስወገድ በተደረገው የቡርዧ አብዮት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ተጫወቱ ። «ገባርነት ያከትማል ! » «ከእንግዲህ ማንም ሰው ገባር አይሆንም ! » የሚሉት የቡርዧው አብዮት መፈክሮች ሰፊውን ሕዝብ ወደ አብዮቱ ጋበዙት ። የፈረንሣዩ የ1789 * « የሰው ልጅ እና የዜጋ መብቶች አዋጅ» መውጣት የመብት መነፈጊያና የጭቆና ምንጭ ሆና የቆየውን የገባርነትን መወገድና በምትኩም ነፃ ሆና በፖለቲካ ሕይወት ውስጥ መሳተፍ የሚያስችል የዜግነትን ጽንሰ ሐሳብ መከሰትን አበሰረ ።

በወቅቱ የቡርዧ ዜግነት ንድፈ ሐሳብ እንደ ሩሶ በመሳሰሉት ታዋቂ የፈረንሣይ የፖለቲካ ፈላስፋና በሌሎችም አያሌ ምሁራን በሰፊው መተንተን ጀመረ ። ሩሶ በዘመኑ ዜግነት ማለት ግለሰቦችን በመንግሥት ሥልጣን ውስጥ ተካፋይ የሚያደርግ የአባልነት ስሜት መግለጫ መሆኑን በመጠቆም ዜጎች በከፍተኛው የመንግሥት አመራር መካፈል የሚችሉ ገባሮችን ግን የመንግሥት ሕጐችን የማክበር ግዴታ ያለባቸው ግለሰቦች እንደነበሩ አመልክቶ ስለ ሰዎች እኩልነት ተከራክሯል ።[3]

የሩሶና የተከታዮቹ ሐሳቦች በቡርዧው አብዮቶች ላይ ተጽዕኖ አሳድረዋል ። ቡርዧው በራሱ ማዕከላዊ መንግሥት የሚገኘውን የአገር አንድነት በይበልጥ ለማጠናከርና ለመጠበቅ እንዲሁም የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነቱን ዋስትና ባለው ሁኔታ ለማራዘም የዜግነትን መብት ለሁሉም የኅብረተሰቡ አባሎች በማዳረስ ከመሬት ከበርቴው የገዥ መደብ የተሻለ መሆኑን አስመሰከረ ።

የቡርዧውን ሥርዓተ ማኅበር የተካው የሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር ሰዎች በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚኖራቸውን ፖለቲካዊና ሕጋዊ ግንኙነቶች አዳብሯል ። ቀደም ሲል በፍጹም ይታወቅ ያልነበረ የመንግሥት (ኅብረተሰብ) እና የግለሰብ ግንኙነት በአዲስ መልክ ተገንብቷል ። አዲሱ ሕጋዊ የግለሰብ አቋም ሶሻሊስት ዜግነት ሆኗል ። ይህንም ከቀድሞዎቹ የዜግነት ዓይነቶች ልዩ የሚያደርገው የራሱ የሆነ ጠባዮች አሉት ።

* በመጽሔቱ ውስጥ የተጠቀሱት የዘመን አቆጣጠሮች በተለይ ካልተጠቀሱ በስተቀር እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ናቸው ።

Digitized by Google

የሶሻሊስት ዜግነት ልዩ ጠባዮች—የመንግሥት ሥልጣን የራሱ የሶሻሊስት ዜጋ (የሕዝብ) መሆን ፣ ሶሻሊስት ዜግነት በኅብረተሰቡ ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ውስጥ ሁሉ ግለሰቦች ሙሉ ተሳትፎ የሚያደርጉበት መብት መሆን፣ ሶሻሊስት ዜግነት ማለት ከብዝበዛና ከጭቆና ነፃ መውጣትና በአጠቃላይ የራስን ዕድል በራስ መወሰን መቻል ማለት ወዘተ ናቸው ።

በሶሻሊዝም ሠርቶ አደሩ ሕዝብ (ሶሻሊስት ዜጋ) ሁሉ ከብዝበዛ ነፃ ነው የምንለው የብዝበዛ ምንጭ የነበሩት የምርት መገልገያዎች የግል መሆን በማከተሙና በምትኩ የእኩልነት ፣ የነጻነት ፣ የፍትሕና የዲሞክራሲ መሠረት የሆነው የሶሻሊስት ንብረት ሥርዓት በመስፈኑ ነው ።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው የአንድ አገር ወይም መንግሥት ዜጋ የሆነ ግለሰብ ዜግነት ከሌለው ግለሰብ የበለጠ ጥቅም ይናረዋል ። ይህም ጥቅም እንደነገሩ ሁኔታ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካና የባህል ሕይወት ውስጥ ተካፋይ በመሆን የመብትና የነፃነት ባለቤት መሆን መቻል ነው ።

ዜግነት በዓለም አቀፍ ደረጃ

ዜግነት የሚያስከትለውን እነዚህን መሠረታዊ ጥቅሞች ለመቀዳጀት ሲል ሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ በየወቅቱ ባካሄደው መራራ ትግል በአሸናፊነት ሲወጣ ከተጐናጸፉቸው መብቶች መካከል የዜግነት መብት አንዱ ነበር ። ይህን መብት ለመጨበጥ ሲባል የተደረገው ትግል ካገር አቀፍ አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንኳን የታወቀ ሆኗል።ለምሳሌ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እንደተቋቋመ የሰብአዊ መብቶች ሁለንታዊመግለጫ (The Universal Declaration fo Human Rights) በድርጅቱ ጠቅላላ ጉባኤ በ1948 ታወጀ ። መግለጫውም ዜግነትን በሚመለከት በአንቀጽ 15 የሚከተለውን ደንግጓል ።

<u>አንቀጽ 15</u>

ሀ- ማንኛውም ሰው የዜግነት መብት አለው ።

ለ- ማንኛውም ሰው ያለፍርድ ዜግነቱ ሊሰረዝበት ወይም ዜግነት የመለወጥ መብቱን ሊከለከል አይችልም ።

ከዓለም አቀፍ ሸንጐ በመለስም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል አገሮች በብሔራዊ ሕገ መንግሥቶቻቸው ወይም ሕጐቻቸው አማካይነት ይህን መብት አውቀዋል ። ዜግነት የሚገኝበትንም ሆነ የሚታጣበትን ወይም የሚነፈግበትን ሁኔታዎች ደንግገዋል። በ1922 ዓ.ም.* ወጥቶ የነበረው የኢትዮጵያ የዜግነት ሕግም ዜግነት ስለሚታጣበትና ስለሚነፈግበት ሁኔታ** በሰፊው ባይዘረዝርም ፣ ዜግነት ስለሚገኝበት ሁኔታዎች አያሌ ድንጋጌዎች አሉት ።

---

* እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር

** ነገር ግን አንቀጽ 11 ስለዚሁ ሁኔታ በመጠኑ ያወሳል ። ይኸውም የሚከተለው ነው ፤

ሀ. አንዲት የኢትዮዮጵያ ዜጋ ከውጭ አገር ሰው ጋር በመጋባቷ ምክንያት የሌላ አገር ዜጋ ሆና ልትቆጠር የተገባት እንደሆነ ፣

ለ. አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ዜግነቱን ለውጦ የውጭ አገር ዜጋ የሆነ እንደሆነ የኢትዮጵያ ዜጋ መሆናቸው ይቀራል ።

Digitized by Google

በዚህ ሕግ መሠረት « በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም በውጭ አገር ከአንድ ኢትዮጵያዊ ወይም በአንዲት ኢትዮጵያዊት የተወለደ ሁሉ የኢትዮጵያ ዜጋ ነው ። »ከዚህም በላይ ከውጭ አገር ሴት ጋር በስርዓት የተጋባ የኢትዮጵያ ዜጋ ሚስቱ የኢትዮጵያ ዜጎ ትሆናለች ። የውጭ አገር ሰው ኢትዮጵያን ዜግነት ለማግኘት የሚችለው በሀገሩ ሕግ መሠረት በፈቃዱ አዳሪ እሚሆንበት ዕድሜ ሲደርስ ፥ ቢያንስ አምስት ዓመት በኢትዮጵያ የኖረ ፥ ለሕይወቱና ለራሱ ቤት ዘመዱም የሚያስፈልገውን ነገር ለማግኘት የሚችል እና ቀደም ሲል በወንጀል ተከሶ ያልተፈረደበት እንደሆነ ነው ።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል አገሮች በብሔራዊ ሕጎቻቸው እማካይነት ዜግነትን በመብትነት አውቀዋል ሲባል ሁሉም አገሮች ዜግነት ሊያስገኝ የሚባውን ሙሉ የኢኮኖሚ ፥ የሶሻል ፥ የባህል ብሔራዊና ፖለቲካዊ መብቶች በሕግ እንኳን አውቀዋል ማለት አይደለም ። ይህ እያንዳንዱ አገር በሚገኝበት የስልተ ምርት ዕድገት ደረጃ ዓይነት ውሱን ይሆናል ። ታላቁ የማርክሲስት ሌኒኒስት የፖለቲካ ኢኮኖሚ መሥራች ካርል ማርክስ ይህን የገለጸው «መብት ከኅብረተሰቡ የኢኮኖሚ መዋቅርና የባህል ዕድገት ደረጃ በምንም ዓይነት ሊበልጥ አይችልም» [4] በማለት ነበር ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የመብቶችና ነፃነቶች ዓይነቶች ሁሉ በቅድመ ሶሻሊስት ስልተምርት ይሰፍናሉ ብሎ መገመት ዘበት ነው ። በብዝበዛ ላይ የተመሠተረው የምርት ግንኙነቱ ይህን አይፈቅድም።ቢሆንም ለኅብረተሰቡ የዕድገት ደረጃ የሚጣጣምና ኅብረተሰቡ ከሚገኝበት የኢኮኖሚ ፥ የፖለቲካና የማኅበራዊ ኑሮ ሕግጋት ጋር የሚስማማ መብትና ነፃነትን የሚያስገኝ ይሆናል ።

በሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር የዜግነት መብት የሶሻል ፥ የኢኮኖሚ ፥ የፖለቲካና የባህል መብቶችን የሚያቀዳጅ የሕግ ዋስትና ብቻ ሳይሆን የብዝበዛ ምንጭ የነበሩት የምርት መገልገያዎች የሕዝብ ሀብት በመሆናቸው ቁሳዊ ዋስትናም አግኝቷል ።

ነፃነት

በማናቸውም የዕድገት ደረጃ ላይ ያለ የኅብረተሰብ ክፍል ወይም መደብ ለነፃነት ተመሳሳይ ግንዛቤ የለውም ። ቡርዧው የሚያውቀው ነፃነት የወዛደሩን ባርነት ነው ። ሳይንሳዊ አመለካከት ያላቸው ተንታኞች ለነፃነት የተሰጠ የተለያየ ትርጉምና መግለጫ ቢኖርም በየትኛው ሥርዓተ ማኅበር የየትኛው መደብ አባል እንደተረጎመውና እንደገለጠው መረዳት አያስቸግራቸውም። ይህ ሁኔታ የርዕዮተ ዓለም ትግል ከሚደረግባቸው የትግል መስኮች መካከል አንዱ በነፃነት ላይ የሚደረገው መሆኑን ያመለክታል ። የካፒታሊስቱ ሥርዓት ከሶሻሊዝም እንደሚበልጥና የበላይነት እንዳለው አድርጐ ለማቅረብ ከንቱ ጥረት ይደረጋል።ለምሳሌ በአንድ ወቅት የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበረው ጆን ኤፍ ኬኔዲ በዘመናችን በዓለም ውስጥ ሁለት ታላላቅ ኃይሎች አሉ ብሎ ፥ እነሱም «የኮሚኒስት ዓለምና የነፃው ዓለም » [5] እንደሆኑ ገልጿል ። ለኬኔዲ «ነፃው ዓለም» የካፒታሊስቱ የዓለም ክፍል ነው ። እንደሱ አባባል የሶሻሊስት ሥርዓት የተመሠረተባቸው አገሮች ነፃነት የላቸውም ። ሐቁ ግን የተገላቢጦሽ ነው ።

ስለነፃነት በምናወሳበት ጊዜ መረሳት የሌለበት ነገር « ነፃነት» በተለያየ ወቅት ታጋዮች የተጠቀሙበት መፈክር መሆኑን ነው ። በተለያዩ ሥርዓተ ማኅበሮች የተደረጉ የመደብ ትግሎች ሁሉ የነፃነት ትግል ባሕርይ የነበራቸው ናቸው ።

የቀድሞው የኢትዮጵያ ፊውዶ ቡርዣ መንግሥት ተጠሪ (ንጉሡ) እና ባለሟሎቹ ይሉት እንደነበረው ሁሉ ሕገ መንግሥታዊ መብቶችና ነፃነቶች በንጉሡ «መልካም ፈቃድ ለሚወዱትና ለሚወዳቸው ሕዝብ » የሚሰጡ ችሮታዎች አይደሉም ፤ በሰፊው

Digitized by Google

ሕዝብ መራራ ትግል የተገኙ ናቸው። የድል
ውጤቶች ቢሆኑም በዚህ ጽሑፍ ወደፊት
እንደምናየው የይስሙላ መብቶችና ነፃነቶች
እንጂ በተግባር የተተረጐሙ ዋስትናዎች
አልነበሩም ።

በመሆኑም ነፃነት ከማንም እንደስጦታ
የሚቀርብ ገጸበረከት አይደለም ፤ ወይም
እንግሊዛዊው ፈላስፋ ኩርንፎርዝ በትክ
ክል እንዳለው «እግዚአብሔር ወይም ተፈ
ጥሮ ለሰው ልጅ ያጐናጸፈው ጸጋ አይደለም፣
ነፃነት በትግል የሚገኝ የድል ፍሬ ነው፤
ትንሽ በትንሽ ፣ ቀስ በቀስ በትግል የሚገኝ
እና በሰው ልጅ የረዥም ዘመን ማኅበራዊ
እንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ ግባራዊ ሊሆን
የሚችል ነው ። »[6]

ሩሶ በአሥራ ስምንተኛው ምዕተ ዓመት
አጋማሽ ላይ የጻፈውን ዝነኛ መጽሐፍ የጀ
መረው «የሰው ልጅ የተወለደው ነፃ ሆኖ
ነው ፤ ይሁን እንጂ ቢያለበት ታሥሮ ይገ
ኛል »[7] በማለት ነበር ። ይህ የሩሶ አባባል
ለነፃነት ታጋዮች በመፈክርነት ያገለገለ እና
ከመጽሐፉ መታተም ጥቂት ዓመቶች በኋላ
ለፈነዳው የፈረንሣይ አብዮት አስተዋጽኦ
ያደረገ ቀስቃሽ ኃይል መሆኑ የሚዘነጋ አይ
ደለም ። ነገር ግን ሩሶ እንደሚለው የሰው
ልጅ ነፃ ሆኖ አልተወለደም ። እንዲያውም
ኩርንፎርዝ በትክክል እንዳስቀመጠው ፡—

> ሰው በምንም ዓይነት ከነፃነት ጋር አልተ
> ወለደም ። ከሱ ፍላጉትና ቁጥጥር ውጭ
> በሆኑት ሁኔታዎች ወሳኝነት የተወለደ
> ፍጡር ነው ። ይሁን እንጂ የሰው ልጅ ማ
> ኅበራዊ ኑሮ እና የዚሁ ማኅበራዊ ኑሮ
> ዕድገት ሕግጋት በማኅበራዊ ልምዱ ውስ
> ጥ ቀስ በቀስ ያዳበረው ችሎታው ራሱን
> ነፃ አደረገው ። ይህም የሆነው ከተፈጥሮ
> ጋር በገጠመው ትግል ፣ በመደብ ትግል
> እና በግል ትግል ነው ። ሰው የሚኖረው
> ነፃነትም ራሱ የፈጠረው እና ታግሎ ያገ
> ኘው እንጂ ራሱ ከፈጠረው እና ታግሎ
> ካገኘው የበለጠ ሊሆን አይችልም ።[8]

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው የሰው
ልጅ የተፈጠረው ነፃ ሆኖ አይደለም ። የሰ
ው ልጅ ባለፈባቸው ሥርዓተ ማኅበሮች
ሁሉ ነፃ ለመውጣት ያደረገውን መራራ ትግ
ል በአጠቃላይ ለመመርመር ብንሞክር የነፃ
ነት ጽንሰ ሐሳብ እንዴት ቀስ በቀስ እየዳበ
ረና እያደገ እንደመጣ ለመገንዘብ ይረዳናል።

በጥንቱ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር የሰ
ው ልጅ ነፃ ለመውጣት ይታገል የነበረው
በየጊዜው ተፈጥሮ ያደርስበት ከነበረው የ
አደጋ መቅሰፍትና ያልታሰበ የአካል ፣ የሕ
ይወትና የጤንነት ጉዳት ለመዳን ነበር ።
ይህን የተፈጥሮ አደጋና ጉዳት ለመቆጣጠ
ር የሚያስችለው ብቃት ፣ ዘዴና ብልሀት
አልነበረውም ። በአጠቃላይ በዝቅተኛ ደ
ረጃ እንኳን ተፈጥሮን መቆጣጠር እማይች
ልበት የዕውቀት ደረጃ ላይ ስለነበር በራስዋ
በተፈጥሮ ቁጥጥር ሥር ከመውደቅ ማም
ለጥ አልቻለም ። ከኑሮና ከልምድ ግንዛቤ
እየወሰደና እየተማረ ባከማቸው ዕውቀቱ
ቀስ በቀስ በተፈጥሮ ላይ የበላይነትን ማግ
ኘት በመቻሉ በየደረጃው ከተፈጥሮ ሙሉ
ቁጥጥር ነፃ የመውጣቱ ሂደት እየጨመረ
መጣ ።

ግርክስ አብዛኛውን የምርምር ጊዜውን
ባሳለፈበት ታላቅ ሥራው በካፒታል ውስ
ጥ በትክክል እንደገለጸው « . . . የጥንቱ(ያ
ልሰለጠነው) ሰው ፍላጐቶቹን ለማርካት
ለመራባት እና በሕይወት ለመኖር ከተፈ
ጥሮ ጋር መታገል የነበረበትን ያህል የሰለ
ጠነውም ሰው በማናቸውም ሥርዓተ ማኅ
በርና በየትኛውም ስልተምርት ይህን ማድ
ረግ ነበረበት። በዕድገቱም- - - ፍላጐቶቹን
የሚያረኩለት የምርት ኃይሎችም በበኩላ
ቸው ዳበሩ ። በዚህ ረገድ የተገኘው ነፃነት
በማኅበራዊው ሰው ፣ በአምራቾች መተባ
በር እና ከተፈጥሮ ጋር ያላቸውን ግንኙነት
(መስተጋብር) በመቆጣጠር ፣ በጭፍን የተ
ፈጥሮ ኃይሎች በመገዛት ፈንታ ተፈጥሮን
በጋራ ቁጥጥራቸው ሥር በማስገባት . . .
ለሰብአዊ ተፈጥሯቸው በይበልጥ ተስማሚ
በሆኑ ሁኔታዎች ብቻ ነው ። »[9]

ከዚህ በላይ የተመለከትነው የሰው ልጅ
በመጀመሪያ ከተፈጥሮ ቁጥጥር ነፃ ለመው
ጣት ያደረገውን ትግል እና በመጠኑም ቢ
ሆን በተፈጥሮ ላይ የበላይነትን በመቀዳ
ጀቱ ያገኘውን ድል ነው ። ከተፈጥሮ ጋር
ባደረገው ትግል በየወቅቱ የተጐናጸፈው
ድል እየጨመረ ቢሔድም ፣ የሰው ልጅ ያላ
ሰበው ሌላ የነፃነት መጣበብ ገጠመው ።
የነፃነቱ መጣበብ የተጣለበትና የተጫነው
ከለመደው ጠላቱ ከተፈጥሮ ኃይል ሳይሆን
ከሰው ልጅ ከራሱ ሆነ ። ይህም በኅብረተ

Digitized by Google

ሰብ ውስጥ ቀድሞ ያልነበረ ፣ ነገር ግን ከግል ንብረት ፣ ከመደቦች እና ከመንግሥት መፈጠር ጋር አብሮ የተከሰተው የሰው በሰው መበዝበዝ እና ጭቆና ነበር ። የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጭቆና በማያንሰው የመደብ ጭቆና እና ብዝበዛ ተሸጋገረ ። ይህም የመደቦችን ቅራኔ እና መራራ ትግልን አስከተለ ።

በመደብ በተከፋፈለ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ነፃነት ወይም ነፃነት ማጣት (ነፃነት አለመስጠት) መደባዊ ግንዛቤ እና ባህርይ እንዳለው ቀደም ሲል መጠቆማችን የሚታወስ ነው ። በዚህ መሠረተ ሐሳብ ላይ የኩርንፎርዝ አመለካከት ጠቃሚ ነው ። እንደ ኩርንፎርዝ አባባል በአንድ ታሪካዊ ወቅት የተገኘ ወይም የታጣ ነፃነት ስንል በአንድ የተወሰነ መደብ የተገኘ ወይም የታጣ ነፃነት ማለታችን ነው ። የአንድ መደብ ነፃነት ማግኘት ወይም ማጣት ከሌላ ተቃራኒው መደብ ነፃነት ማግኘትና ማጣት ፍጹም የተለየ ነው ፤ ስለሆነም ስለነፃነት ምንነት የተለያዩ መደቦች የተለያዩ አመለካከት እና ግንዛቤ አላቸው ። [10]

በየሥርዓተ ማኅበሩ የተደረጉት የመደብ ቅርጽ ያላቸው የነፃነት ትግሎች ሁሉ መደቦቹ እንደቆሙለት ዓላማ ዓይነት ነፃነትን ለማግኘት ፣ ነፃነትን ላለመስጠት ወይም ነፃነትን ለማጣበብ የተደረጉ የመደብ ትግሎች ናቸው ። በመደብ ትግሉ ውስጥ በመሳተፍ ላይ ያሉ የጭቁን መደቦች አባሎች የሚታገሉት በነፃነት ስሜት ስለነፃነት ነው። ይህን በማስመልከት ኩርንፎርዝ የሚከተለውን ብሏል ።

በዚህ ዓይነት ትግል ውስጥ ነው ሰዎች ነፃ ሆነው የፈለጉትን የሚያደርጉት ፤ ራሳቸውን ነፃ የሚያወጡት የሰብአዊ ነፃነትን አድማስ የሚያሰፉት ። የማያምጽ ባሪያ ያው በባርነት የሚታወቅ ባሪያ ነው ፤ በአመጽ ላይ ያለ ባሪያ ግን የባርነት ቀንበርን እንደተሸከመ ቢሆንም ነፃ ለመውጣት የሚያደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ እንደ ነፃ ሰው ሆኖ «በነፃነት ስሜት» ነው ። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ናቸው የሰብአዊ ነፃነት ጉህ ቀዳጆች ።» [11]

ኅብረተሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ በመደብ በተከፋፈለበት በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓተ ማኅበርም የነፃነት ግንዛቤ ከመደባዊ ጥቅም ተጽዕኖ ነፃ አልነበረም ። የባሪያው መደብ በታሪክ ተወዳዳሪ የሌለው ግዴታ እንጂ ነፃነት እና መብት አልነበረውም ። ለባሪያው መደብ ነፃነት ማለት ከባሪያ አሳዳሪው አሰቃቂ ብዝበዛ እና ጭቆና መላቀቅ ማለት ነበር ። የባሪያ አሳዳሪው መደብ ነፃነት ደግሞ ባሪያውን ያለአንዳች ገደብ መበዝበዝ እና መጨቆን መቻል ነው ። በኅብረተሰቡ ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ ማድረግ እና ወሳኝ ሚና የመጫወት ነፃነት ለባሪያ አሳዳሪው የገዥ መደብ ብቻ በመወሰን የሕግ ዋስትና አገኘ ።

የባሪያው መደብ ለነፃነት ያደረገው መራራ ትግል ለፊውዳሊዝም መከሰት እና ለሠርቶ አደሮች (ለባሮች ጭምር) ገባር ሆኖ ተሻለ ሕይወት ለመኖር የሚያስችል ዋስትና አስገኘላቸው ። የፊውዳሉ እና የገባሩ መደቦችም ቀደም ሲል የተገለጸው ዓይነት የየራሳቸው የነፃነት ግንዛቤ ነበራቸው ። በፊውዳሉ ሥርዓት ውስጥ ጭቁኑ ገበሬ ዲሞክራሲያዊና ፖለቲካዊ ነፃነቱን ገና አልተቀዳጀም ነበር ።

በቡርዥው ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ነፃነት ሲባል ለዋናዎቹ ሁለት ተጻራሪ መደቦች ለቡርዥውና ለሠራተኛው ምን ማለት እንደሆነ እንመልከት ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ነፃነትን በመፈክርነት አንግቦ የተነሳው ቡርዥ የራሱን መደባዊ ጥቅም የሚያንጸባርቅ የነፃነት ግንዛቤ ነበረው ። ቡርዥው ከፊውዳሉ የገዥ መደብ ጋር ባደረገው የሞት ሽረት ትግል ባሸናፊነት መውጣት ማለት ነፃነትን መጐናጸፍ አድርጐ ወሰደል ። ለአዲሱ ቡርዥ የካፒታሊስት ስልተ ምርት መመሥረት እና መጠናከር የነፃነት መስፈን ማለት ነበር ። ነፃነትም ለካፒታሊስቱ ርካሽ የሰው ጉልበት እና ጥሬ ዕቃ እንዲሁም ነፃ ገበያ ማግኘት ፣

Digitized by Google

የካፒታሊስት ነፃ ውድድር መስፈን ፣ በአ
ጠቃላይ ትርፉን በማጋበስ የመበዝበዝ መ
ብትን መቀዳጀት ማለት ሆነ ። ሌላው የቡ
ርዣ ነፃነት በብዝበዛ ላይ የተመሠረተውን
የካፒታሊስቱን ስልተምርት እንዳለ ጠብ
ቆ ለማኖር የሚያስችል ጠንካራ መንግሥ
ት በመመሥረት የሠራተኛውን መደብ ተ
ገዥ አድርጐ ማቆየት ነው ። ይህን ዓይነ
ቱን ነፃነት የሠራተኛው መደብ ባርነት እ
ንጂ ነፃነት አይለውም ።

የሠራተኛው መደብ ነፃነት የሚገኘው
የብዝበዛ እና የጭቆና ምንጭ የሆነው የካ
ፒታሊስቱ ስልተምርት ሲለወጥ ብቻ ነው ።
ምርት መገልገያዎች ከግል ይዞታ ወደ
ሕዝብ ይዞታ ሲለወጡ የኢኮኖሚ ፣ የሶሻ
ልና የባህል ነፃነቶችን ይቀዳጃል ። የመንግ
ሥት ሥልጣን በሠራተኛው መደብ እጅ
ሲገባ እውነተኛ ለብሔራዊ እና የፖለቲካ
ነፃነት ይጐናጸፋል ። በአጠቃላይ ለሠራተ
ኛው መደብ ነፃነት ማለት የካፒታሊስቱን
የብዝበዛ እና የጭቆና ቀንበር አሽቀንጥሮ
መጣል ማለት ነው ። በመሆኑም የካፒታ
ሊስቱ ነፃነት ማለት የሠርቶ አደሩ ሕዝብ
ባርነት በመሆኑ ሰፊው ሕዝብ አጥብቆ
ይታገላል ።

እምራቹን ሠራተኛ በማናቸውም ጊዜ
ማባረር የካፒታሊስቱ መብትና ነፃነት የመ
ሆኑን ያህል የመሥራት (ሥራ የማግኘት)
መብት ደግሞ የወዛደሩ ጥያቄ በመሆኑ የሁ
ለቱ መደቦች የመብትና የነፃነት ግንዛቤ የ
ተለያየ ነው ።

የነፃነት መጣበብንም ሁለቱም መደቦች
የሚያዩት በተለያየ ሁኔታ ነው ። ማናቸው
ም የብዝበዛ ሥርዓት በሠርቶ አደሩ ሕዝብ
ላይ የሚያደርሰው የጭቆና እና የተገዥነት
ቀንበር ከባድነት ከዕለት ወደዕለት እየከ
በደ በሔደ ቁጥር የመብት እና የነፃነት መ
ጣበብም ያንኑ ያህል ነው ።

በሌላ በኩል የገዥው መደብ ራሱ ያወ
ጣው ሕግ እንኳን እያደር እያደገ የሚሔደ
ውን የመበዝበዝ ፍላጐቱን የፈለገውን ያ
ህል ሊያሟላላት ባለመቻሉ የነፃነት መጣ
ቡብ የደረሰበት ይመስለዋል ።

ነፃነትና ሶሻሊዝም

በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ
የወዝአደሩ መደብ ነፃነት እና የቡር
ዣው መደብ ነፃነት ተጻራሪ እና አንዱ
የሌላውን ጥቅም የሚጐዳ በመሆኑ ሠራተ
ኛው ሕዝብ በአጠቃላይ ከብዝበዛ እና ከጭ
ቆና ነፃ ለመውጣት ፣ ካፒታሊስቱ ደግሞ
የመበዝበዝ እና የመጨቆን መብቱን ለማ
ስከበር መራራ የመደብ ትግል ይካሔዳል።
ሠርቶ አደሩ ሕዝብ ከብዝበዛ እና ከጭቆና
ነፃ ይወጣል ። ነፃም እየወጣ ነው ። ይህ ነፃ
ነት የተገኘው የሰው ልጅ በየደረጃው በተ
ፈጥሮ ላይ የበላይነትን ለመቀዳጀት እና በ
ይበልጥም በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል ካደረገ
ው ትግል እና ድል ባሻገር የምርት መገል
ገያዎችን የሕዝብ ሀብት በማድረግ የሶሻ
ሊስት ንብረት ተቋምን በመመሥረት ነው።
በአጭሩ ሶሻሊዝምን በመገንባት ነው ። በ
ሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር የሚሰፍነው ነ
ፃነት እንደ ካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር
ያልተሟላና የፖለቲካ ነፃነት ብቻ አይደ
ለም ። በሶሻሊስት ሥርዓተ ማኅበር ሰው
ሰውን አይበዘብዝም ፤ የምርት መገልገያ
ዎች የሕዝቡ የጋራ ንብረት ስለሚሆኑ የእ
ያንዳንዱን ፍላጐት ለማርካት በሚቻልበ
ት ዘዴ ምርት ፣ የምርት ክፍፍልና ስርጭት
በማዕከላዊ ዕቅድ ይከናወናል። በዚህን ጊዜ
«ሰዎች እንዴት በተሟላ ሁኔታ በነፃነታ
ቸው እንደሚጠቀሙ እንጂ ለነፃነት የሚ
ያደርጉት ትግል አነስተኛ ይሆናል ። » [12]

ራሱን«የነፃው ዓለም» አካል አድርጐ በመ
ቁጠር የሚመጻደቀው የአሜሪካ ገዥ መደብ
በገዛ አገሩ እጅግ አስከፊ የዘር አድልኦ በማ
ራመድ በቀይ ሕንዶች ፣ በፑርቶሪካኖች እና
20 ሚሊዮን በሚሆኑ ጥቁሮች ላይ የሚያደ
ርሰው ግፍና በደል አሁንም እንደቀጠለ ነው።
በአስከፊነቱ በዓለም ተወዳዳሪ የሌለውን
የደቡብ አፍሪካ የዘረኝነት ፖሊሲ (አፓር
ታይድ) በመደገፍ ቁሳዊና የሞራል ድጋፍ
የሚሰጠው ለነፃነት ቆምኩ የሚለው የቡ
ርዣው ዓለም በተለይም ኔቶ (የሰሜን አት

Digitized by Google

ፍንቲክ የታል ኪዳን ድርጅት) ነው ። በሌላ በኩል ግን የሶሻሊስት አብዮት አንዱ ዓላማ ዘረኝነትን ማጥፋት ስለሆነ በዘር አድልኦ የሚግቅተው የኅብረተሰብ ክፍል ነፃ የሚወጣው በሶሻሊዝም ነው ።

ቅኝ ግዛት ወይንም ካፒታሊስቶች ከሀገራቸው ድንበር በመውጣት በኃይል የሌላውን አገር በመያዝ ቅኝ የሆነውን አገር ብሔራዊ ሀብት መበዝበዝ የተስፋፋው በካፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር ነው ። ቅኝ ገዥዎች የሚበዘብዙት የቅኝ ተገዥውን ብሔራዊ ሀብት ብቻ ሳይሆን የሥራ ኃይሉን ጭምር ነው ። የራሱ ብሔራዊ መለያ የነበረውን ወጉንና የነፃነት ስሜቱን ሰልበውታል ። በብሔራዊ ነፃ አውጭ ድርጅቶች እና ግምባሮች አማካይነት ታግለው እውነተኛ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ነፃነት የተቀዳጁት ሶሻሊዝምን መገንባት የቻሉት ወይም በመገንባት ላይ ያሉት አገሮች ብቻ ናቸው ። ዛሬ አብዛኞቹ «ነፃ» የወጡ በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ከኢምፔሪያሊዝም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት መላቀቅ ባለመቻላቸው እውነተኛ ነፃነታቸውን ተቀዳጅተዋል ለማለት አይቻልም ። በአጠቃላይ የካፒታሊስቱ ሥርዓት የብዝበዛ ዓይነተኛ መሣሪያ ከነበረው ቅኝ አገዛዝና አሁንም ተንሰራፍቶ ከሚገኘው የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥርዓት ነፃ መውጣት የሚቻው በሶሻሊዝም ነው ።

ብሔሮች (ብሔረሰቦች) ፣ የኅብረተሰብ ክፍሎች እና አገሮች በካፒታሊስቱ ሥርዓት ከወደቀባቸው የባርነት ቀንበር ነፃ ሊወጡ የሚችሉት በሶሻሊስት አብዮት ነው። በሶሻሊዝም አንድ ብሔር ወይም ብሔረሰብ ሌላውን ብሔር ወይም ብሔረሰብ የማይጨቁንበት እና የማይበዘብዝበት ሥርዓት ነው ። በመሆኑም አናሳ (ሕዳጣን) ብሔረሰቦች ነፃ የሚወጡትና ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር እኩል የሚሆኑት በሶሻሊዝም ነው።

እዚህ ላይ የብሔሮችን ፣ የኅብረተሰብ ክፍሎችን እና የአገሮችን ነፃ መውጣት ከግለሰቦች ነፃ መውጣት ለይተን ማየት እንደሌለብን ልንገነዘብ ይገባል ። የግለሰቦች ነፃነት ሊገኝ የሚችለው ግለሰቦቹ የሚኖሩበት ብሔረሰብ ፣ ብሔር ፣ ኅብረተሰብ ፣ ወይም አገር ነፃ ሲሆን ብቻ ነው ። እውነተኛ ነፃነት የሚኖረው ግለሰብም አዲሱ የሶሻሊስት ሰው ነው ።

የምርት ኃይሎችን በጋራ ይዞታ ሥር የሚያደርግ ነፃነት የሌሎች የፖለቲካ ፣ የማኅበራዊ ፣ የኢኮኖሚ እና የባህል ነፃነቶች ምንጭ ነው ። ዛሬ በካፒታሊስት አገሮች ሕገ መንግሥቶች ሁሉ በሕግ ደረጃ እንኳን ያልታወቁ እንደመሥራት ፣ ትምህርት መማር ፣ የጤና እንክብካቤ ማግኘት ወዘተ ... የመሳሰሉት መብቶች በሶሻሊስት አገሮች ሕጋዊ እና ቁሳዊ ዋስትና አግኝተዋል።የሶሻሊስት አገሮች ሕገ መንግሥቶች የፖለቲካ ፣ የሶሻል ፣ የኢኮኖሚ እና የባህል ነፃነቶች እና መብቶች* ለዜጎች የተሰጡ መሆናቸውን ከማረጋገጣቸውም በላይ መብቶቹም ተግባራዊ የሚሆኑበትን ቁሳዊ መሠረት በሰፊው በመዘርጋት ላይ ናቸው ።

የሰው ልጅ በታሪኩ ውስጥ እንዲህ በሰፋትና ተግባራዊ በመሆን ረገድ ቀደም ሲል አይቶ የማያውቃቸውን እና በሶሻሊስት አብዮት ታግሎ የተጎናጸፋቸውን የነፃነት ዓይነቶች እዚህ ላይ ስንጠቅስ የሰው ልጅ ነፃነት በዚሁ የተወሰነ ነው ማለታችን አይደለም ። በሶሻሊስት ኢኮኖሚ መበልጸግ በሳይንስ እና በቴክኖሎጂ መዳበር «ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደ ፍላጎቱ» የሚለው ኮሚኒስታዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ መርህ ተግባራዊ በሚሆንበት በኮሚኒዝም እጅግ የላቀ እና የተሟላ የዜጎች ነፃነት ይሰፍናል ።

የሶሻሊስት ሥርዓት የፖለቲካ ኢኮኖሚ

---

* ስለዜጎች የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚ ፣ የሶሻል ፣ የባህል መብቶች እና ነፃነቶች በዝርዝር በዚሁ ጽሑፍ ክፍል ሁለት ውስጥ ይገለፃሉ ።

Digitized by Google

መርህ «ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደሥራው»እንደመሆኑ መጠን የሰው መሠረታዊ ፍላጐት በሶሻሊስት ሥርዓት ሊሟላ ቢችልም በይበልጥ የተሟላ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጐቱ የሚረካው በኮሚኒዝም ነው ። በመሆኑም የሰው ልጅ የተሟላ የኢኮኖሚ ነፃነቱን በመቀዳጀት በልዩ ልዩ መስኮች የመመራመር እና የመፍጠር ችሎታውን ከምንጊዜውም የበለጠ የሚያዳብረው ያኔ ነው ።

በኮሚኒዝም የመንግሥት መጨቆኛ መሣሪያነት በሕዝባዊ የራስ አስተዳደር ሲተካ እያንዳንዱ ዜጋ በሕዝባዊ አስተዳደር ውስጥ በሚያደርገው ተሳትፎ ለመጨረሻጊዜ ከመንግሥት ጭቆና ነፃ ይወጣል ።

በአጠቃላይ ሰው የተሟላ እና ከፍተኛውን የኢኮኖሚ ፣ የፖለቲካ ፣ የማኅበራዊ ፣ የባህል ፣ የሞራል ፣ (ኮሚኒስት ሞራል) ወዘተ . . . ነፃነት የሚቀዳጀው በኮሚኒዝም ነው ። [13]

መብት

መብት ማለት ምን ማለት ነው ? መብት ከነፃነት የተለየ ጽንሰ ሐሳብ ነው ወይ ? የመብትን ጽንሰ ሐሳብ ምንነት አሟልቶ ለመግለጽ መሞከር ራሱን የቻለና ሰፊ ሥራ ነው ። ለዚህ ጽሑፍ አግባብነት በሚኖረው ክልል ብቻ በመወሰን በጥቂት ቃላት አቀናብሮ የመብትን ትርጉም በአጠቃላይ ማስቀመጥ ይቻላል ። መብት በሕግ የታወቀ እና በሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋሞች አፈጻጸሙ ዋስትና ማግኘት የሚችል የዜጐች (የግለሰቦች)የይገባኛል ጥያቄ ነው ። ባለመብት ነኝ ባይ ግለሰብ ወይም ኅብረተሰብ በተለያየ ወቅት የተለያየ የይገባኛል ጥያቄዎች በማንሳት እንደነገሩ ሁኔታ ለኅብረተሰቡ ወይም ለመንግሥት ያቀርባል ። ይህም መብት ነፃ መሆን ፣ ሐሳብን መግለጽ ፣ በመንግሥት ሥራ ተካፋይ መሆን ፣ ሥራ ማግኘት ወዘተ . . . ሊሆን ይችላል ።

ብዙ ጊዜ መብት ማለት ነፃነት ማለት እንደሆነ ተደርጐ የሚወሰድበት ወቅት አለ ። አንድ የሕግ መዝገበ ቃላትም [14] የመብት አንዱ ትርጉም ነፃነት ፣ ግዴታ አለመኖር ነው ይላል ። ይህ አንዱን ቃል ለሌላው ተክቶ የአንድ ሐሳብ መግለጫ ማድረግ ሊመጣ የቻለው ሁለቱንም ቃላት በማጓደን አዘውትሮ ከመናገር ይመስላል ።

ነፃነት አንድን ነገር በግዳጅ (በመገደድ) ከማድረግ ወይም ካለማድረግ ፈር መውጣትን ፣ ከመከልከል ወይም ከመገደድ መላቀቅን የሚያመለክት ጽንሰ ሐሳብ ነው ። አንዱ ግለሰብ ፣ ኅብረተሰብ ፣ ብሔረሰብ ፣ ብሔር ወይም አገር የነፃነት መብት አለኝ ሲል ባሪያ ፣ ተገዥ ፣ ተበዝባዥ ሆኖ ከመኖር ግዴታ መላቀቅ ፣ ወይም ፈር መውጣት ይገባኛል ብሎ የሚያቀርበው ጥያቄ ነው ። በአጠቃላይ ኩርንፎርዝ እንዳለው «መብቶች ከነፃነቶች ጋር ይጐዳኛሉ—ማንም ሰው በመብቶቹ ለመገልገልና ለመደሰት ነፃ መሆን አለበት ። መብቶች በሕግ ይደነገጋሉ ። » [15]

ስለመብት ጽንሰሐሳብ አመጣጥ የተለያዩ የፖለቲካ ፈላስፎች የተለያየ አመለካከት አላቸው ። አመለካከታቸውም የሚከተሉትን ርዕዮተ ዓለም ሊያራምድ በሚችልበት ሁኔታ የተቀየሰ ነው ። የዚህን ጽንሰሐሳብ አመጣጥ እና ታሪካዊ ዕድገት መተንተን አስፈላጊነት የማያጠያይቅ ቢሆንም ፣ የጽሑፉን ይዘት ጠበብ ለማድረግ ሲባል የሕዝቦች የመብት ጥያቄ በተለይ ከገነነበት ጊዜ መጀመሩ አግባብነት ይኖረዋል ። ከዚህም በላይ የመብት ጽንሰ—ሐሳብ ታሪካዊ ዕድገት ቀደም ሲል ስለነፃነት ጽንሰሐሳብ ታሪካዊ ዕድገት ከተገለጸው የተለየ ባለመሆኑ የቀድሞው ገለጻ ለዚህም በተመሳሳይነት የሚያገለግል ነው ።

በፖለቲካ ፈላስፎች ጽሑፎች ውስጥ መብት የተለየ ትኩረት የተሰጠው ከ17ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ በኋላ ነው ። የእንግ

Digitized by Google

ሊዦ ጆን ሎክ (1632-1704)፥ የፈረንሣዩ ባሮን ደ ሞንተስኪ (1689-1755) እና ዣን ዣክ ሩሶ (1712-1778) በተለይ ስለመብት የነበራቸው አመለካከት በእንግሊዝ፥ በፈረንሣይ እና በአሜሪካ ለፈነዱት የቡርዣ አብዮቶች መካሔድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። የ1688 የእንግሊዝ፥ የ1789 የፈረንሣይ እና 1791 የአሜሪካ የሰብዓዊ መብቶች አዋጆች መታወጅ በየሀገሮቹ የፈነዱት የቡርዣ አብዮቶች ውጤቶች ናቸው።

በአዋጆቹ መሠረት የንግግር እና የጽሑፍ፥ የመሰብሰብ እና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፥ የመምረጥ እና የመመረጥ፥ የእኩልነት፥ የነፃነት፥ ወዘተ . . . መብቶች ታውቀዋል። ነገር ግን በመብቶቹ ዋናዎቹ ተጠቃሚዎች የቡርዣው የገዥ መደብ አባሎች ሲሆኑ፥ ለሠርቶ አደሩ ሕዝብ የይስሙላ ድንጋጌዎች ብቻ ቀሩት። ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በነዚህ መብቶች መገልገል ያልቻለው የምርት መገልገያዎች ይዞታ የግል በመሆኑ እና በነሱም ላይ የባለቤትነት መብት በማጣቱ ነው።ለምሳሌ ማተሚያ ቤቶች፥ ጋዜጦች እና የጋዜጦች ስርጭት በካፒታሊስቶች ይዞታና ቁጥጥር ሥር እስካለ ድረስ የጽሑፍ ነፃነት ሊከበር የሚችለው ለካፒታሊስቱ መደብ እንጂ ተጻራሪ አስተያየት እና አመለካከት ላለው ለሠራተኛው መደብ አይደለም።

በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ከሚታወቁት መብቶች መካከል ለፖለቲካ ተቋሞች አመራር ሰጭነት የመምረጥ እና የመመረጥ መብት ነው። ቡርዣው በመምረጥ እና በመመረጥ መብቱ ሲጠቀም፥ ለሠራተኛው ግን ይህ መብት የተሟላ አይደለም። በዚህ ሥርዓት በገዥው መደብ በተቀየሰው የምርጫ ሥርዓት መሠረት የሠራተኛው መብት በካፒታሊስቱ እና ከካፒታሊስቱ መደብ ከቀረቡለት ዕጩዎች (ገዥዎች) መካከል አንዱን መምረጥ ብቻ ነው። ሠራተኛው መመረጥ አይችልም—የተወሳሰቡ የሕግ፥ የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚ፥ የማኅበራዊና የባህል መሰናክሎች የትም ስለማያደርሱት ይህ መብት «ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ» ሆኖ የሚቀር ነው። ነገር ግን በዚህ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ሠራተኛው መደብ በትግሉ የተቀዳጃቸው እንደ መደራጀት እና ሥራ ማቆም የመሳሰሉት መብቶቹ ንቃተ ሕሊናውን እና ድርጅቱን በማጠናከር የራሱ አምባገነንነት እውን የሚሆንበት አዲስ፥ ትክክለኛ እና ተራማጅ ሥርዓት ለመመሥረት አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩለት መሆኑ አይካድም።

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ከእንግሊዙ፥ ከፈረንሣዩ እና ከአሜሪካው የሰብአዊ መብቶች አዋጆች መውጣት በኋላ በተለይ ከሐያኛው ምዕተ ዓመት መግቢያ ጀምሮ አያሌ አገሮች የዜጐቻቸውን መብቶች በሕግ አውቀዋል። የአብዛኞች አገሮች ዜጐች መብቶች በብሔራዊ እና በፖለቲካው መስክ ብቻ እንዲወሰኑ ተደርገዋል። የ1936 ቱ የሶቪዬት ሶሻሊስት ሪፐብሊኮች ኅብረት ሕገ መንግሥት የዜጐችን መብቶች እና ነፃነቶች በስፋት እና በዓይነት ሕጋዊ እና ቁሳዊ ዋስትና በመስጠት በዓለም የመጀመሪያ ሆነ። ሕገ መንግሥቱ ከብሔራዊ እና ከፖለቲካ መብቶች አልፎ የኢኮኖሚ፥ የሶሻል እና የባህል መብቶችንም ዜጐች እንዲገለገሉባቸው አደረገ። ሌሎች ሶሻሊስት አገሮችም የሶቪዬት ኅብረትን ፈለግ በመከተል እነዚህን መብቶች በሕገ መንግሥቶቻቸው ውስጥ በማስገባት የዜጐቻቸው መሠረታዊ መብቶች እንዲሆኑ አደረጉ።

በሌላ በኩል ዛሬ በኢምፔሪያሊዝም ቀንደኛ ተጠሪነት የሚታወቀው አሜሪካ ራሱን በዓለም የሰብአዊ መብቶች አስከባሪ ፖሊስ አድርጐ ሰይሟል። በዚሁ መሠረት የሶሻሊስት አገሮች ሰብአዊ መብቶችን እየጣሱ ናቸው እያለ በማናፈስ ላይ ይገኛል። የአሜሪካ መንግሥት የመጀመሪያው ሕገ መንግሥቱን ካወጀ እና በኋላም

Digitized by Google

በ1791 አንዳንድ የፖለቲካ እና ብሔራዊ መብቶችን በመጨመር ካሻሻለ እነሆ ዛሬ ሁለት መቶ ዓመት ሊሆነው ሰባት ዓመት ቀርቶታል ። የዜጐቹን መብቶችና ነፃነቶች በሚመለከት ረገድ በዚህ ረዥም ጊዜ ውስጥ ያደረገው መሠረታዊ መሻሻል ወይም ለውጥ የለም ። የአሜሪካ ሠርቶ አደር ሕዝብ የመደብ አቻዎች (በሶሻሊስት አገሮች) ግን የፖለቲካ እና ብሔራዊ መብቶች ብቻ ሳይሆን የሶሻል ፣ የኢኮኖሚ እና የባህል መብቶቹንም ከተቀዳጁ ዘመናት አልፈዋል ። ይህ ሐቅ ጐልቶ በማንጸባረቅ ላይ እያለ ነው የአሜሪካ የገዥ መደብ አባሎች ዓይን ያወጣ ውሸት የሚዋሹት ።

ስለሌሎች አገሮች «ሰብአዊ መብቶች መጣስ» ጉዳይ የሚለፍፈው የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በሕገ መንግሥቱ የዜጐች የመሰብሰብ እና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት የማይደፈር መሆኑን ደንግጓል ። ሐቁን እንመልከት ። በዚያው አገር ፣ አሜሪካ ውስጥ በ1969 ብቻ በልዩ ልዩ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ተገኝተዋል በማለት 127 ጊዜ የዩኒቨርሲቲ ገቢዎችን በመድፈር 4 ሺህ ተማሪዎችን ከትምህርት ገበታቸው ላይ አፈናቅሎ ማሠሩ ፣ በ1970 በአሃዮ አንድ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ አራት ተማሪዎችን በግፍ በመግደል ብዙዎችን ማቁሰሉ ፣ በግንቦት ወር 1971 አሜሪካ በኢንዶ ቻይና የምታካሂደውን ጦርነት በመቃወም በዋሽንግተን ከተማ ሰላማዊ ሰልፍ ካደረጉት መካከል በአንድ ቀን ብቻ 15 ሺህ ሰዎች ተይዘው መታሠራቸው ፣ በ1972 የሰላማዊ ሰልፈኛ ተቃዋሚ እና አሸባሪ ቡድኖች (ሥውር ወታደራዊ ድርጅት) በአሜሪካ ብሔራዊ የምርመራ ድርጅት (ኤፍ· ቢ· አይ ·) አማካይነት አቋቁሞ እና በፈንጅና በጦር መሣሪያዎች አስታጥቆ በተለይ የቬየትናምን ጦርነት የሚቃወሙ ሰልፈኞችን በግል ቤታቸው እና በቢሮአቸው በድንገት በመግባት እንዲያሸብሩ ፣ እንዲፈትሹ ፣ ሲያስፈልግም እንዲገድሉ በማድረግ ግፍ መፈጸሙ ፣ በግንቦት ወር 1977 የዘረኛው የደቡብ አፍሪካ ተማሪዎችን ወደ ስታን ፎርድ ዩኒቨርሲቲ መግባት ከተቃወሙት መካከል 200 ያህሉ ተማሪዎች በፖሊስ ተይዘው መታሠራቸው ፣ በሰኔ ወር 1977 በሺህ የሚቆጠሩ ፑርቶሪካኖች ችካጐ ውስጥ ተሰብስበው የፑርቶሪካንን ቀን በማሰብ እናት አገራቸው ከአሜሪካ ቅኝ ግዛት እንድትወጣ በመጠየቃቸው የአሜሪካ ፖሊሶች ሁለት ገድለው ፣ ሁለት አቁስለው ከመቶ በላይ ይዘው ማሠራቸው [16] ፣ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ሳያሳፍረው ፣ ስለሌላ አገር ሰብአዊ መብት መደፈር መናገሩ ያገጠጠ አስመሳይነት መሆኑን ለመረዳት እያዳግትም ። ይህ አሜሪካ በራሱ ዜጐች ላይ ከሚፈጽመው ግፍ እጅግ አነስተኛው እና በተለይ ሰላማዊ ሰልፍና ሰብሰባ የማይደፈር ሕገ መንግሥታዊ መብት ነው የሚለው የይስሙላ መብት የሚከበረው በጥይት ፣ በዱላ እና በግስር መሆኑን ለማመልከት ያህል ብቻ የተጠቀሰ ነው ።

አሜሪካ ሰብአዊ መብት ተጥሷል እያለ የሚወተውተው በተለይ በሶሻሊስት አገሮች ውስጥ ነው ። ኢትዮጵያም በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራሟ ፀረ— ኢምፔሪያሊስት አቋሟን ግልጽ በማድረጓ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በሚችለው የትግል መስክ ሁሉ እየተፈታተናት ነው።ሰብአዊ መብቶች ተጥሷል በማለት የወነጀላትም ገና በአብዮቱ ፍንዳታ ማግስት ነበር።

የሚገርመው ነገር ከአሜሪካ ርዳታ ከሚያገኙት 82 አገሮች መካከል 23 ብቻ ሰብአዊ መብትን አክብረዋል በመባል የኢምፔሪያሊስት አሜሪካን ውዳሴ እና ምስጋና ካገኙት አብዛኞቹ የምዕራብ አውሮፓ ኢምፔሪያሊስት አገሮች መሆናቸው ነው። [17] በተለይም በዓረብ ሕዝቦች ላይ በምትፈጽመው ጭፍጨፋ ፣ እሥራትና ድብደባ የዓለም ኅብረተሰብ በማውገዝ አንቅር የተፋት ጽዮናዊት እሥራኤል በአሜሪካ መንግሥት አመለ

ካኩት ሰብአዊ መብት አክባሪ ናት ። በደ
ቡብ አፍሪካ በ4 ሚሊዮን ነጮች እስከፊ
የዘር መድሎ ቀንበር ሥር ያሉትን 20 ሚሊ
ዮን የሚሆኑ ጥቁሮችን ፣ 2 ሚሊዮን ክል
ሶችን እና ከ700 ሺህ በላይ የሚሆኑ ሕንዶ
ችን [18] ለመጨፍጨፍያ ፣ የናሚቢያ ሕዝ
ብ በሰዋፖ መሪነት የሚያደርገውን የነፃ
ነት ትግል ለማኮላሸ የሚሆን ገደብ የለሽ
የጦር መሣሪያ በማስታጠቅ አድኃሪ ትብ
ብር የሚያደርጉት ምዕራብ ጀርመን እና
ፈረንሣይ በአሜሪካ መንግሥት እስተያየ
ት ለሰብአዊ መብቶች የቆሙ ናቸው ።

የእሥራኤል መንግሥት ደጋፊ የሆነች
ው አሜሪካ አብዮታዊት ኢትዮጵያን ሰብ
አዊ መብቶችን ደፍራለች በማለት የወነጀ
ለችው ለምን ይሆን ? በተለይ ለፊውዳሉ
ከሚሰጠው ነፃ የጉልበት አገልግሎት ሌላ
እስከ 75 በመቶ የእርሻ ምርት ውጤቱን
ለባለመሬቱ የመክፈል ሕጋዊ ግዴታ የነ
በረበት ጢሰኛ የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀ
ብት በማድረግ ነፃ በወጣበት ማግስት ፣
የሥራ ኃይሉን እንደሸቀጥ በመሸጥ ወደር
የሌለው ብዝበዛ ይደርስበት የነበረው
ወዝአደር ዓይነተኛ የማምረቻ መሣሪያዎች
የመንግሥት ሀብት በመሆናቸው የነፃነት
አየር መተንፈስ በጀመረበት ወቅት ፣ ሰፊ
ው ሠርቶ አደር ሕዝብ እውነተኛ የመደራ
ጀት መብቱ ተጠብቆለት በመኖሪያ አካባ
ቢው ፣ በየሥራ መስኩ በመደራጀት የራ
ሱን የአስተዳደር ፣ የዳኝነት እና የደህንነት
ጥበቃን ራሱ መምራት በጀመረበት እና በብ
ሔራዊ የኢኮኖሚ ዕቅድ ቅየሳ ተካፋይ በሆ
ነበት ጊዜ ሰብአዊ መብት ተጣሰ ሲል ምን
ማለቱ ይሆን ? በእርግጥ የአሜሪካ ኢምፔ
ሪያሊዝም ለጭቁኑ አርሶ አደርና ወዛደር
በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ጥቅ
ምና ደህንነት የሚበጁ ሰብአዊ መብት እን
ዳላለመ ይህ ሕዝብ በሚያካሂደው አብዮት
ላይ በወሰደው የጠላትነት አቋምና የራሱ
የኢምፔሪያሊዝም ባህርይ ያረጋግጣል ።

ከዚህ ላይ አንድ ነገር ግልጽ ሊሆን ይገ
ባል ። በመሠረቱ የሰብአዊ መብት ጽንሱ-
ሐሳብ መደባዊ ይዘት አለው ። የቡርዣ አብ
ዮት በተካሔደበት ወቅት አብዮቱን ለመ
ምራት ራሱን በግንባር ቀደም ያሰለፈው
አብዮታዊ ቡርዣው በጊዜው ከጐኑ ተሰ
ልፈው አብዮቱን ያራምዱ የነበሩትን የእ
ርሶ አደሩን እና በማደግ ላይ የነበረውን የወ
ዛደሩን መደብ ጥቅሞች ጭምር የሚያቅ
ፈው መፈክሩ ከፊውዳል መሣፍንት ጭቆ
ና እና ብዝበዛ ነፃ የመውጣት መብት ነበር።
በእርግጥም ቡርዣው በይበልጥ የራሱን ጥ
ቅሞች በማስከበር ተግባራዊ ቢያደርጋቸ
ውም ፣ የፊውዳል መሣፍንት ኢኮኖሚያዊ
ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ጥቅሞች ሲወገዱ
የፊውዳል እና የጢሰኛ ግንኙነቶች ተቋረ
ጡ ። ቀድሞ ጢሰኛ የነበረው በምንዳ ተቀ
ጥሮ ለመሥራት የሚያስችል ነፃነት ተቀ
ዳጀ ።

በአብዮቱ ወቅት የተነሳው የሰብአዊ መ
ብቶች ጥያቄ ከፊውዳል መሣፍንት አገዛዝ
እና ብዝበዛ ነፃ መውጣት በመሆኑ ከሞላ
ጐደል የቡርዣው እና የሌሎች ጭቁን መደ
ቦች የጋራ ጥያቄ ነበር ። ቢሆንም የፊውዳሉ
ን ልዩ ልዩ ጥቅሞችን ማስወገድ ቢቻልም
ቡርዣው በአዲሱ የምንዳ ተቀጣሪ ሠራተ
ኞች ላይ የነበረውን የበላይነት ጥቅሞች እ
ብሮ ማስቀረት አልቻለም ። በመሠረታዊ
የሰብአዊ መብቶች ጽንሰ—ሐሳብ ላይ በቡ
ርዣው እና በሠራተኛው መካከል ውዝግ
ቦች እና የተለያዩ አመለካከቶች የተጀመ
ረው በዚህ ጊዜ ነበር ። ቡርዣው የራሱን
መደብ ጥቅሞች ለማስከበር ግላዊ የምርት
መገልገያዎች ባለቤትነት መብት ሲያፈሩ
አይችሉም ሲል ፣ ወዛደሩ ደግሞ የግል ንብ
ረት ተቋም ብቻ ሳይሆን መደቦች ራሳቸው
መጥፋት አለባቸው በማለት ይታገላል ። [19]

እንዲያውም ቡርዣው የመበዝበዝ እና
መጨቆን መብቱን ለማራዘም ሲል በሚ
ያሰራጨው ፕሮፓጋንዳው መብትን መደ
ባዊ ይዘት የሌለው አድርጐ ያቀርበዋል ።

Digitized by Google

ሰብአዊ መብቶች ዘላለማዊ ፣ ከሰው ልጅ የማይለዩ እና የማይለወጡ «ጸጋዎች» በመሆናቸው «ማንም ሰው ፣ የትም ቦታ በማናቸውም ሁኔታ» በይገባኛልነት ሊጠይቅ እና ሊገለገልባቸው ይችላል ይባላል። ይህም ሠርቶ አደሩን ሕዝብ ለማወናበድ እና ትግሉን ለማኮላሸት በተሳሳተ ርዕዮተ ዓለም እምነቱን ለመግዛት እንጂ የሰብአዊ መብቶች ጽንሰ—ሐሳብ ከኅብረተሰብ ዕድገት ሕግጋት ጋር ግንኙነት ያለው ስለሆነ ታዳጊ እና ሊለወጥ የሚችል የመደብ ይዘት ያለው መሆኑን የማሌ ሳይንስ ያረጋግጣል ። [20]

በአጠቃላይ ለቡርዣው በምርት መገልገያዎች የግል ሀብትነት ሰውን መበዝበዝ እና በዚህም አማካይነት የሚገኘውን ገደብ የለሽ ትርፍ በማጋበስ አብዛኛውን ሕዝብ መጨቆን በሱ ግንዛቤ መሠረት የሰብአዊ መብቶች መከበር ሲሆን ፣ የምርት መገልገያዎች የሕዝብ ሀብት መሆን ግን የሰብአዊ መብቶች እና ነፃነቶች መደፈር ፣ ነው። የተደፈረው «መብት እና ነፃነት» ብዝበዛ ነው—የቡርዣው የመበዝበዝ መብት ።

በሌላ በኩል የምርት መገልገያዎች የሕዝብ ሀብት መሆን ለሠርቶ አደሩ ከብዝበዛ ነፃ መውጣት ማለት ነው ። ለዘመናት ሲታገል የኖረውም ያለ መበዝበዝ መብቱን ለማስከበር ነው ። ዛሬም ከብዝበዛና ጭቆና ነፃ በመውጣት እውነተኛ የኢኮኖሚ ፣ የማኅበራዊ እና የባህል መብቶቹን እና የነዚህ መብቶች ውጤት የሆነውን ብሔራዊና የፖለቲካ መብቶቹን ጭምር ሊቀዳጅ የቻለው በሶሻሊስት አገሮች ነው ። ይህንን እያወቁ ፣ ያልሆነውን ሆነ የሆነውን ደግሞ አልሆነም በማለት ከሠራተኛው ጥቅም ጋር ተጻራሪ ፕሮፓጋንዳ መንዛት በተለይ ከሶሻሊዝም መወለድ ጋር ኢምፔሪያሊዝምን ከተጠናወቱት ባሕሪያት አንዱና ርዕዮተ ዓለማዊ ክስረቱን በገሐድ የሚያሳይ ነው ።

(ይቀጥላል)

የግርጌ ማስታወሻ

1. V. Shevtov, *Citizenship of the USSR —A Legal Study* (Moscow: Progress Publishers, 1979), p. 20.
2. L. Grigoryan and Y. Dolgopolov, *Fundamentals of Soviet State Law* (Moscow: Progress Publishers, 1971), p. 132.
3. J.J. Rousseau, *The Social Contract, London*, 1974, p. 59ff.
4. K. Mark, *The Critique of the Gotha Programme* (Peking: Foreign Language Press, 1972), p. 126.
5. G. Shahanazarov, *Socialist Democracy* (Moscow: Progress Publishers, 1974), p. 126.
6. Maurice Cornforth, *Theory of Knowledge*, New York, 1975, p. 195.
7. J.J. Rousseau, p. 49.
8. M. Cornforth.
9. Karl Marx, Capital — *A Critique of Political Economy* Vol. III (Moscow: Progress Publishers, 1974), p. 820.
12. *Ibid.*, p. 200.
10. Maurice Cornforth, p. 198.
11. *Ibid.*
13. V. G. Afanasyev, *Fundamentals of Scientific Communism* (Moscow: Progress Publishers, 1974), p. 820.
14. Max Radin, *Law Dictionary, New* York, 1970, p. 300.
16. Maurice Cornforth, *The Open Philosophy and the Open Society* (New York: International Publishers, 1968), 302.
16. Igor Geevsky and Victor Smelev, *U.S. Documents Reveal Conspiracy to Stifle Dissent in America* (Moscow: Novosti Press Agency Publishing House, 1978), pp. 152-4.
17. "A Human Rights Scorecard", *Time*. March 28, 1977, pp. 9-10.
18 ወ/ዮሐንስ ወርቅነህ ፣ «አፓርታይድና የአርነት እንቅስቃሴ በደ.ቡብ አፍሪካ» መስከረም ቅጽ 2 ፣ ቁ. 9 ፣ ሰኔ 1974 ፣ ገጽ 67
19. Wolfgang Weichelt, "Some Remarks on the Concept of Human Rights", *Law and Legislation in the GDR*, 2/28, p. 37.
20. M. Crauston, *What are Human Rights?* London, 1973, p. 21

Digitized by Google

የኅብረት ሥራ ማኅበር ታሪካዊ አመጣጥ

አሰፋ ሀብቱ

በታሪክ ውስጥ የኅብረት ሥራ መስ
ፋፋት ሠርቶአደሮች የካፒታሊስት ሥርዓት
የሚነባቸውን የብዝበዛ ቀንበር ለማስወገድ
ካካሄዱት የትግል እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ
ነው ። ስለሆነም የኅብረት ሥራን አመጣ
ጥና ዕድገት በውል ለመገንዘብ በመጠኑም
ቢሆን የካፒታሊዝምን የመጀመሪያውን
ዕድገት ደረጃ ማጤኑ አስፈላጊ ነው ።

የካፒታሊስቱን ስልተምርት ሊከሰት ካስ
ቻሉት ምክንያቶች መካከል የፊውዳሉ ስል
ተምርት ቀውስና የመጀመሪያ ደረጃ የካፒ
ታል ክምችት ይገኙበታል ። የመጀ
መሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት አምራ
ቾች የምርት መገልገያቸውን እንዲያጡ
ያደረገ እንደመሆኑ ፣ ይኸ ሂደት በካፒታሊ
ስቱ ሥርዓት ውስጥ ሁለት ተፃራሪ መደ
ቦች ማለትም ቡርዧውና ወዝአደሩ እን
ዲከሰቱ አደረገ።አብዛኛው አምራች የኅብረ
ተሰብ ክፍል ከምርት መገልገያ መሣሪያዎች
መለየቱና የሥራ ኃይሉን ለጥቂት የምርት
መገልገያ ባለቤቶች እየሸጠ የሚያድርበት
ሁኔታ መፈጠሩ የካፒታሊስት ስልተምርት
መስፋፋትን የሚያንፀባርቅ ነበር ። የመጀ
መሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት የፊውዳሉን
ስልተምርት በማፈራረስ ወዝአደሮች የሥራ
ኃይላቸውን እንደሸቀጥ እንዲሸጡ በማድ
ረግ ለካፒታሊስት የምርት ግንኙነት መስ
ፋፋት ሁኔታዎችን አመቻቸ ። ለምንዳ ሥራ
መሠረቱና መነሻውም የመጀመሪያ ደረጃ
የካፒታል ክምችት ነው ። በአጠቃላይ በካ
ፒታሊስቱ ሥርዓተ ማኅበር የግል ይዞታ
መስፋፋት ፣ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል መዳ
በርና የሥራ ውጤት ወይም የምርታማነት
ማደግ የምርት መገልገያ ባለቤቶች በሌሎች
የሥራ ኃይል እንዲጠቀሙ ከማድረጉም ሌላ
ሥራ የበለጠ ማኅበራዊ ሲሆን የሥራ ውጤ
ትም ለካፒታሊስቱ የግል ጥቅም የሚውል
ሆነ ።

ቀደም ሲል በነበሩት ስልተምርቶች ይካ
ሄድ የነበረው ብዝበዛ በግልጽ የሚታይ

Digitized by Google

ሲሆን ፥ በካፒታሊስቱ ስልተምርት ውስጥ ግን ብዝበዛው የሚካሄደው በስውር ነው ። ምክንያቱም ካፒታሊስቱ የወዝአደሩን የሥራ ኃይል በሚገዛበት ወቅት እንደባርያ ሥርዓት ጊዜ በቀጥታ ሠራተኛውን የማስገደድ ሁኔታ አይጠቀምም ። ወዝአደሩም ለመኖር ሲል የሥራ ኃይሉን የሚሸጠው በግዴታ ውዴታ ነው ። ማለትም ወዝአደሩ ምንም ዓይነት የምርት መገልገያ የሌለው በመሆኑ ለመኖር የሥራ ኃይሉን ለምርት መገልገያ ባለቤት ለሆነው ለካፒታሊስቱ ለመሸጥ ይገደዳል ። በዚሁ መሠረት በዚህ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የሥራ ኃይል ወደ ሸቀጥነት ሊለወጥ በቃ ።

ወዝአደሮቹ መጀመሪያ በግብታዊ ሁኔታ እያደርም በተባበረና በተደራጀ መልክ በግመጽ በካፒታሊስቱ ላይ የመደብ ትግል ማካሄድ ጀመሩ ። ይህም ታሪካዊ ሂደት በሦስት ደረጃዎች ተከፍሎ ሊታይ ይችላል ። እነርሱም፥

ሀ/ከ 1760 ጀምሮ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን በማቋቋም ሠርቶ አደሮች ያካሄዱት የኢኮኖሚ ትግል ሂደት ፥

ለ/ከ1825 ጀምሮ ወዝአደሮች የሙያ ማኅበራትን በማቋቋም ያካሄዱት ፀረ ካፒታሊስት ብዝበዛ ትግልና

ሐ/ከ1848 ጀምሮ የወዝአደር መደብ በፖለቲካ ፓርቲ መሪነት ያካሄደው የፖለቲካ ትግል ናቸው ።

ወዝአደሩ መደባዊ ትግሉን ማካሄድ የጀመረው በኢንዱስትሪው አብዮት ዘመን በግብታዊነት ያካሂድ በነበረው የኤኮኖሚ ትግል አማካይነት ነው ። ኤንግሌስ እንዳለው የወዝአደሩ ኤኮኖሚያዊ ትግል የተጀመረው ወዝአደሩ ከገጠመው አስከፊ ሁኔታ ለመሸሽና የተሻለ ሰብዓዊ ሁኔታ ለማግኘት ነው።[1] የመጀመሪያው የትግል ስልት ከነባራዊ ሁኔታዎች በመነሳትና በግብታዊነት ከ1760 ጀምሮ የኅብረት ሥራ ማኅበራት በማቋቋም የኤኮኖሚ ትግል በማካሄድ ላይ ያተኮረ ነበር ።

በወዝአደሩ የትግል እንቅስቃሴ ታሪክ ውስጥ ከኅብረት ሥራ መቋቋም ቀጥሎ የተከሰተው የወዝአደሩ መደብ የትግል ቅርጽ ይኸው መደብ ከ1825 ጀምሮ በሙያ ማኅበራት በይፋ እየተደራጀ ያካሄደው የኤኮኖሚ ትግል ነው ። ከዚያ በፊት ግን ወዝአደሩ እንዳይደራጅና ለመብቱ እንዳይታገል በሕግ ታግዶ ይኖር እንደነበረ ታሪክ ይመሰክራል። የወዝአደሩ መደብ አባላት የካፒታሊስት ስልተምርት ማቆጥቆጥ ከጀመረበት ከ14ኛው ክፍለዘመን አንስቶ እስከ 1825 ድረስ ትግላቸውን በሕቡዕ ካልሆነ በቀር በይፋ ለማካሄድ ሕጋዊ መብት አልነበራቸውም። በተለይም በ1349 የታወጀውና ለብዙ ዘመናት ፀንቶ ከቆየ በኋላ በ1825 በተሻረው የሠራተኛ አዋጅ መሠረት ወዝአደሩ ስብሰባ ሲያካሄድ ቢገኝ ከባድ ወንጀል እንደፈጸመ ይቆጠርበት ነበር ።[2] እንዲሁም እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ገባሩ ከመሬቱ ተነቅሎ ፥ ከገጠር ተባሮ ፥ ሥራ ፍለጋ ከተማ ገብቶ ፥ ሥራአጥ ሆኖ ሲገኝ ከግንባሩ ላይም «ባሪያ» የሚል ምልክት በጋለ ብረት ይተኮሰበትና በባርነት እንዲያገለግል ለካፒታሊስቱ ይሸጥ እንደነበር ታሪክ መዝግቦታል ። ወዝአደሩ በተለይ ከኢንዱስትሪ አብዮት ጀምሮ ትግሉን ስላፋፋመ ከ1825 ወዲህ የመሰብሰብ፥ የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ ፥ የሥራ ማቆም የፓርላማ ምርጫ መብት ድል እየተቀዳጀ መጣ ።

በ18ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ የተጀመረው የኢንዱስትሪ አብዮት በአጠቃላይ ከዕደጥበብ የአመራረት ስልትና ደረጃ ወደፋብሪካ ፥ ማለትም ወደሞተር ኃይል የአመራረት ስልትና ደረጃ የተደረገውን የማምረቻ ኃይሎች የእድገት ሽግግር የሚያመለክት ነው ። ስለዚህ የኢንዱስትሪ አብዮት አብዛኛው ሸቀጥ በዕደጥበብ ባለሙያዎች መመረቱ እየቀነሰ ፥ ባለሙያዎቹ ሙያቸውን እንዲተውና ወዝአደሮች እንዲሆኑ የተገደዱበትን የለውጥ ዘመን የሚያመለክት ነው ።

Digitized by Google

የኢንዱስትሪው አብዮት በሠርቶ አደሩ ኑር ላይ ብዙ ችግርና ለውጥ ያስከተለ ነበር። የኢንዱስትሪ አብዮ ት እስከተከሰተበት ጊዜ ድረስ ፣ ሠራተኛው የዕደ ጥበብ ባለሙያ ብቻ ሆኖ ካፒታሊስቱን ሲያገለግል የሚከፈለው ደመወዝ ቢያንሰው እሱና ቤተሰቡ በአካባቢ እና በጓሮ እርሻ ጭምር እየተረዱ በመጠኑ ችግራቸውን ለመወጣት ይችሉ ነበር ። የኢንዱስትሪ አብዮት የመስፋፋት ሂደት የሠራተኞች የአካባቢ የእርሻ መሬት የተወሰደበትና የጓሮ እርሻ የቀረበት ፣ አርሶ አደሩ መሬቱን ተነጥቆ ከገጠር የተባረረበት፣ ቤተሰቡን ይዞ ከተማ ሲገባ ለሥራአጥነት የተዳረገበት ፣ ከነቤተሰቡ ለረሃብ ፣ ለበሽታ በመጋለጥ ብዙ የተሰቃየበት ፣ መሬት እየተወደደ የሄደበት ፣ ሥራ የታጣበት ፣ ወዝአደሩ ቀደም ሲል በቀን አሥር ሰዓት ይሠራ የነበረው በቀን እስከ 18 ሰዓት ድረስ እንዲሠራ የተገደደበት፣ ሕፃናት ያለዕድሜያቸ በፋብሪካ ውስጥ እንዲሠሩ የተገደዱበት፣ ጤናቸው እየተጐዳ ሕይወታቸው ያለፈበትና ከተሞች የተስፋፋበት ሂደት ነው ።

የኢንዱስትሪ አብዮት ባስከተለው የፋብሪካዎች መቋቋምና መስፋፋት ምክንያ ካፒታሊስቱ በፋብሪካው አካባቢ ሱቅ እየከፈተ በፋብሪካው የሚሠሩትን ወዝአደሮች ምግብና ሌላ ሸቀጥ ሁሉ ከሱቁ እንዲገዙ ያስገድድ ነበር ። የማስገደጃውም ዘዴ ወዝአደሮቹ ለዕለት ጉርሳቸው የሚያስፈልጋቸውን ሸቀጥ ከካፒታሊሱቱ ሱቅ በዱቤ እንዲገዙ በማድረግና ደመወዝ በመክፈል ፈንታ ደመወዛቸውን በዱቤ ከወሰዱት ሸቀጥ ጋር አወራርዶ ማስቀረትን የሚያጠቃልል ነበር። በዚህ ሁኔታ ወዝአደሮቹ ከካፒታሊስቱ ሱቅ በግድ በሚገዙት ሸቀጥ ተወስነውና ደመወዛቸውን ለቀጠራቸው ካፒታሊስት እያስረከቡ ለመኖር ይገደዱ ነበር ። ከዚህም ሌላ በሱቁ የሚሸጠው ሸቀጥ ፣ በተለይም ምግብ፣ ዋጋው ውድ ከመሆኑም በተጨማሪ ባዕድ ነገር የተቀላቀለበትና የተበላሸ ስለነበር ለጤና ተስማሚ አልነበረም ። ወዝአደሩ በሚሠራበት ፋብሪካ የሚደርስበት ብዝበዛና በደል አንገፍግፎት ሥራ ለመለወጥ ሲጠይቅ የካፒታሊስቱ ሱቅ ዕዳ ስላለበት እየታገደ የግድ እንዲሠራ ይደረግ ነበር። ከዚህ ወጥመድ ለመውጣት ወዝአደሩ ያካሄደው ትግልና አመጽ ብዙ ነው ። ደመወዙ በጥሬ ገንዘብ እንዲከፈለውና ካፒታሊስቱ በፋብሪካው አካባቢ ሱቅ እየከፈተ ሸቀጥ እንዲገዛ እንዳያስገድደው በሕግ እያገደ የራሱን የኅብረት ሥራ ማኅበር በማቋቋም መሥራት ጀመረ ።

የኅብረት ሥራ ማኅበራት ለመጀመሪያ ጊዜ በወዝአደሮች በግብታዊነት የተቋቋሙት በ1760 በእንግሊዝ አገር ውሊችና ቻሳም በተባሉ ከተሞች ነበር ። ማኅበራቱ የእህል ወፍጮና የዳቦ መጋገሪያ አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንደነበሩ ይታወቃል ።[3] ወዝአደሮቹ የእህል ወፍጮ በኅብረት ማቋቋም የተገደዱት የካፒታሊስቱ የእህል መሸጫ ዋጋ ውድና ከአቅም በላይ ስለሆነባቸው ነው።ካፒታሊስቶቹ የወዝአደሩን የኅብረት ሥራ ማቋቋም ክፉኛ ስለተቃወሙ በውሊች ከተማ የነበረውን የወዝአደሩን የኅብረት ሥራ ማኅበር ወፍጮ በእሳት አቃጥለውት ነበር ። ካፒታሊስቶቹ ለፈጸሙት ወንጀል ሕግ ፊት ቢቀርቡም ምንም ዓይነት ቅጣት ሳይፈጸምባቸው በነፃ ተለቀዋል ።

የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር የተቋቋመው በ1769 በስኮትላንድ ፌንስ በተባለው ቦታ ሲሆን የተቋቋመው ሸማኔዎች የሚያስፈልጋቸውን ሸቀጥ ለመግዛት እንዲያስችላቸው ነበር ። እንዲሁም በእንግሊዝ አገር በርሚንግሃም በተባለ ከተማ የልብስ ሰፊዎች አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር በ 1777 ተቋቋመ። ከዚያ በኋላ የኅብረት ሥራ ማኅበራት መቋቋም ቢቀጥልም በዚያን ጊዜ የተደራጀ እንቅስቃሴ ነበረ ለማለት አይቻልም ። ስለሆነም በተለይ የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንቅስቃሴ ተፋፍሞ የታየው

Digitized by Google

1820 እና ከ[illegible] አ[illegible]ባቢ ጀ[illegible]ር ነበር። ለም[illegible] [illegible]እንግሊዝ አገር በ1826 እና በ1835 መሐከል ብቻ 250 የኅብረት ሥራ ማኅበራት ተቋቁመው እንደነበረ ይታወቃል።

የኅብረት ሥራ ማኅበራት

በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር

የኅብረት ሥራ ማኅበር እንቅስቃሴ በአጠቃላይ ግንባር ቀደም በነበሩት የካፒታሊስት ሀገሮች ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ አንስቶ መስፋፋት የጀመረ ሲሆን፥ ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ማኅበሩ የወዝአደሩ መደብ ከብዝበዛ ለመዳን በማሰብ፥በትግሉ የፈጠረው ድርጅት ነው። የኅብረት ሥራ ማኅበር እንቅስቃሴ እንደ እንግሊዝ በመሰሉ አንጋፋ የካፒታሊስት ሀገሮች ተጀምሮ ካፒታሊዝም ወደተስፋፋባቸው ሀገሮች ሁሉ ተዛመተ። በወቅቱ የኅብረት ሥራ መስፋፋት በካፒታሊስት ሥርዓት ሥርና በተምኔታዊ መርሆዎች ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ዓላማው ውሱን ነበር። የኅብረት ሥራ ማኅበራት በካፒታሊስት ሥርዓት ሥር እስከሆኑ ድረስ የሠርቶአደሩን ችግር በዘላቂነት ለማስወገድ እንደማይችሉና እያደርም እንደካፒታሊስቱ ድርጅት የወዝአደር ጉልበት እየበዘበዙ ትርፍ ወደማካበት እያመሩ የሄዱና ብሉም የካፒታሊስት ተቋሞች እንደሆኑ ታሪክ ያስገነዝባል። ብዙ የወዝአደሩ ትግል ያስገኛቸው የኅብረት ሥራ ማኅበራት በቅርጽ የኅብረት ሥራ ማኅበር ስም ይዘው ይዘታቸው ግን የካፒታሊስት ተቋም ሊሆን በትቷል። ለዚህም የእድገታቸውን ታሪክ ማየት ይበቃል። ለምሳሌ በ1862 አንድ የእንግሊዝ አገር የኅብረት ሥራ ማኅበር ፋብሪካ 500 ሠራተኞች ነበሩት። ከእነዚሁ ውስጥ የኅብረት ሥራ ማኅበሩ አባላት 50 ብቻ ሲሆኑ የቀሩት 450 ተበዝባዥ ወዝአደሮች ነበሩ።[4] ከዚህ ሁኔታ አንፃር የኅብረት ሥራ ማኅበራትን እንቅስቃሴ ያየን እንደሆነ በግደግ ፈንታ እያሽቆለቆለ እንደመጣ ለመገንዘብ ይቻላል።[5]

[illegible]እንግሊዝ አገር የኅብረት ሥራ ማኅበር ታሪክ ላይ ብናተኩር፥ እስካሁን ድረስ የተከሰቱትን የኅብረት ሥራ ማኅበራት በሦስት ክፍሎ ማየት ይቻላል። እነሱም ፦

1/ የቀድሞ የሠራተኞች ማኅበራትና የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት የመጀመሪያዎቹ ሆነው፥ እነዚህም በአብዛኛው ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በፊት የተመሠረቱ ነበሩ። ከእነዚህም በአሁኑ ወቅት የተረፉ ቢኖሩ ከአሥር አይበልጡም።

2/ ቀጥሎ ያሉት ከኢንዱስትሪ የጋራ ንብረት እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ ንግድ ቤቶች ናቸው። እነዚህም የካፒታሊስት ድርጅቶች ሆነው የተነሱ፥ ዲሞክራሲያዊ ገጽታ ያላቸውና በአብዛኛው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የተመሠረቱ ሲሆኑ በ1970 ዓመታት መጨረሻ ገደማ ቁጥራቸው ከአሥር የማይበልጥ ሆና ይገኛል።

3/ የቀሩት በቅርብ ዓመታት የተከሰቱ ናቸው። እነዚህም በተለይ በ1970ዎቹ ዓመታት ካፒታሊዝም ባጋጠመው ውጥረትና ውድቀት ምክንያት ብዙ ፋብሪካዎች እየተዘጉ ወዝአደሩ ሥራ አጥ እየሆነ ሲባረር፥ ይኸንን ሁኔታ አልቀበልም እያለ ካካሄደው ትግል የተነሳ የካፒታሊስት ሥርዓት የጥገና መፍትሔ ለመሻት በሚያደርገው ጥረት የተከሰቱ ናቸው። በተዘጉት ፋብሪካዎች ላይ ካፒታሊስቱ ወዝአደሮቹን በኅብረት ሥራ ማኅበር እያሰባሰበ ፋብሪካዎቹን በማቆየት የዘለቄታ ሳይሆን የወቅቱን ችግር ለመፍታት በመሞከር ላይ ይገኛል። እነዚህም የኅብረት ሥራ ማኅበራት ቁጥራቸው ባይታወቅም ግባቸውን ለመምታት የተሳናቸው መሆኑ ይታወቃል።[6]

Digitized by Google

ከዚሁ አንፃር እስቲ የአንድን ማኅበር ታሪክ ለምሳሌ ያህል በአጭሩ እንመልከት ። ከፍ ሲል እንደተመለከተው በእንግሊዝ አገር የሮሽዴል መሥራቾች በመባል የታወቁት በ1854 አንድ መቶ ሠራተኞችንና ጥቂት ባለአክሲዮኖች (ባለመዋጮ አባላት) ያሉት የሮሽዴል ፋብሪካ የኅብረት ሥራ ማኅበር የተባለ አቋቋሙ ። ቆየት ብሎ በ1859 ማኅበሩ ለካፒታሊስቶች ዕጣ (አክስዮን) በመሸጥ ገንዘብ ሰብስቦ የጥጥ ፋብሪካ አቋቋመ ። ከአንድ ዓመት በኋላ በ1860 ይኸው ማኅበር 1,400 ባለአክስዮን አባላት ሲኖሩት ከእነዚሁ አባላት በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ውስጥ የሚሠሩ 200 ብቻ ነበሩ ። የቀሩት 1,200 አባላት ወዝአደሩ ለፍቶ ባስገኘው ትርፍ የሚጠቀሙ ነበሩ ። ይኸም ማለት ማኅበሩ በአንድ ዓመት ውስጥ የካፒታሊስት ድርጅት ሆነ ማለት ነው ።[7] ይህ ሁኔታ የአንድን የኅብረት ሥራ ማኅበር ለውጥ የሚያሳይ ሲሆን ፣ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተው አሐዛዊ መረጃ ከ1881—1973 በእንግሊዝ አገር የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራትን አጠቃላይ አዝማሚያ ይጠቁማል ።[8]

የዘመን አቆጣጠር	የኅብረት ሥራ ማኅበራት ብዛት	የዘመን አቆጣጠር	የኅብረት ሥራ ማኅበራት ብዛት
1881	13	1924	64
1890	74	1936	50
1893	113	1950	44
1900	105	1960	37
1905	105	1970	26
1913	71	1973	16

በካፒታሊስት አገሮች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ታሪክ የአምራች አባላት ቁጥር እየቀነሰ ሳያመርቱ በወዝአደሩ ጉልበት የሚጠቀሙ አባላት ቁጥር እየጨመረ ሄዷል ። ለምሳሌ በእንግሊዝ አገር የበዝባዥ አባላት ብዛት በ1948 76% የነበረው በ1970 ወደ 84% ከፍ ብሎ ይገኛል ።[9] በመሠረቱ ግን የኅብረት ሥራ ማኅበር ማለት አባላቱ ሁሉ አምራቾች ሆነው የሚሳተፉበትና ክፍያም ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደሥራው መጠን የሚከፈልበት ተቋም ነው ።

በፈረንሳይ አገር ከ1880 ጀምሮ እስከ 1960 ድረስ 2,250 የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት መቋቋማቸው ይታወቃል ። ከእነዚሁ መካከል በ1960፣ 520 ማኅበራት ብቻ ሲቀሩ በእነዚህም ውስጥ የሚገኙት አባላት ይበልጡን ካፒታሊስት ባለአክስዮኖች እንጂ አምራች አባላት አይደሉም ። በዚህ ሁኔታ በሀገር አቀፍ ደረጃ የወዝአደሩ ቁጥር ማለትም የኅብረት ሥራ ማኅበር አባል ሳይሆን ጉልበቱን ለማኅበራት እየሸጠ የሚበዘበዘው አምራች ቁጥር ከጠቅላላው የኅበረት ሥራ ማኅበራት አምራች ኃይል ከሦስት እጅ ሁለት እጅ ወይም 67% ሆኗል። እንዲያውም በአንዳንድ የሥራ ዘርፍ ከዚህ ቁጥር በላይ ሆኖ ይታያል ። ለምሳሌ ፣ በሕንፃ ኮንስትራክሽን ዘርፍ የኅብረት ሥራ ማኅበራት አምራች ኃይል እስከ 90% ወዝአደር ነው ።[10] ይህም የሚያመለክተው ማኅበራቱ፣ በኅብረት ሥራ ማኅበር መጠሪያ ቢሸፈኑም ቅሉ የካፒታሊስት ድርጅቶች መሆናቸውን ነው። ለዚህም ነው ሌኒን፣በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ፣ ወደ ንግድ ማኅበርነት እያዘቀጡ የመሬድ ዘን ባሌ አላቸው ፤ በመሆኑም ጥርጥር የሌለው የካፒታሊስት ተቋማት ናቸው ያለው ።

Digitized by Google

ተምኔታዊ ሶሻሊስቶችና የኅብረት ሥራ ማኅበር

በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ምርት የሚመረተው የሰውን ፍላጐት ለማርካት ሳይሆን ባለካፒታሉን ያለማቋረጥ ከፍተኛ ትርፍ እንዲያካብት ለማስቻል ነው ። ባለካፒታሉ ከፍተኛ ትርፍ የሚያካብተውም ጥሬ ዕቃዎችን በአነስተኛ ዋጋ በመግዛት ፣ አንድን ሸቀጥ ለማምረት የሚጠፋውን ጊዜ በማሳነስና የማምረት ዘዴዎችንና መሣሪያዎችን በማሻሻል ፣ የተገኘውን የምርት ውጤት በከፍተኛ ዋጋ በመሸጥ ፣ በተለይም እንደሸቀጥ የሚሸጠው የወዝ አደሩ ጉልበት ዝቅተኛ ምንዳ እየተከፈለው ብዙ እንዲያመርት ነው ።

የካፒታሊስት የጭቆናና የብዝበዛ ቀንበር የሚወገድበትን ዘዴ በማስመልከት አንዳንድ ምሁራን በየጊዜው የተለያዩ መፍትሔዎችን ቢተልሙም በካፒታሊስቱና በወዝ አደሩ መካከል ያለውን መደባዊ ቅራኔ ግን ለመረዳት አልቻሉም ነበር ። ከእነዚህ ምሁራን ውስጥ ሳን ሲሞን፣ቻርልስ ፉርየር የተባሉት የፈረንሳይ ተወላጆችና ሮበርት ኦወን[11] የተባለው እንግሊዛዊ በይበልጥ የታወቁ ናቸው። እያንዳንዱ ምሁር ያቀረበው ሐሳብ በዝርዝር ሲታይ የሚለያይ ቢሆንም ፣ በአጠቃላይ ሲታይ በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ ያለው ጭቆናና ብዝበዛ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን በማቋቋምና በማስፋፋት ያለመደብ ትግል በጥገና ሊወገድና ሊጠፋ ይችላል ፤ በምትኩም የሶሻሊስት ሥርዓት እያደር ይፈጠራል የሚል ነው ። ይህ አመለካከት በተጨባጭ ታሪካዊ ሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ የመደብ ትግልን አስፈላጊነትና ሂደት ያልተገነዘበ፣ ተግባራዊ ሊሆን የማይችልና በተምኔታዊ ሃሳብ የተመላ በመሆኑ ተምኔታዊ አመለካከት ተብሎ ይታወቃል ። እነዚህ ምሁራንና ተከታዮቻቸውም ተምኔታዊ ሶሻሊስቶች ይባላሉ ። የተምኔታዊ ሶሻሊስት ምሁራን የተለሙትም መመሪያ በተግባር ሲተረጐም የከበርቴውና የወዝአደሩ መደቦች በእርቅና በሰላም በአንድነት ሊኖሩ ይችላሉ ከሚለው የዋህ አመለካከት የሚነሳና በኅብረት ሥራ ማኅበራት የአባልነት መብት ለከበርቴውም ለወዝአደሩም እኩል የተጠበቀ ነው የሚል ነበር ። ሠራተኛው የመደብ ጠላቶችን የመደብ አጋሮች አድርጐ ብዝበዛንና የመደብ ቅራኔን ማጥፋት የማይቻል መሆኑ በታሪክ የተረጋገጠ ጉዳይ ስለሆነ የእነዚህ «ሶሻሊስቶች» ሃሳብ ተምኔታዊ ሆኖ ቀርቶአል ።

ይሁን እንጂ በተለይ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ፣ ብዙ የተምኔታውያን ተከታዮች የኅብረት ሥራ ማኅበራትን አቋቁመው ነበር። የሮበርት ኦወን ተከታዮች ያቋቋሙትን ማኅበር ለምሳሌ እንጥቀስ ። በ1844 በእንግሊዝ አገር ሮሽዴል በተባለ ከተማ « የሮሽዴል መሥራቾች » በሚል መጠሪያ በታወቁት የሸመና ባለሙያ ወዝአደሮች የተቋቋመው የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር በታሪክ የታወቀ ነው ። ይህ ማኅበር ታዋቂነት ሊያተርፍ የቻለው ከግብታዊነት ተላቆ የሮሽዴል መሠረተ ሐሳቦች በመባል የሚታወቅ የኅብረት ሥራ ማኅበርን መሠረተ ሃሳቦች ነድፎ ለመጀመሪያ ጊዜ በተግባር ለማዋል በመሞከሩ ነው ። እነዚህም መመሪያዎች፣

- —አባልነት በፈቃደኝነት መሆኑ ፣
- —የማኅበሩ የሥራ አመራር አባላት በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ተመርጠው ሥራውን የሚመሩ መሆኑን ፣
- —የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት እንደካፒታሊስቱ ሥርዓት እያንዳንዱ አባል ለማኅበሩ ባዋጣው የመዋጮ ገንዘብ መጠን ሳይሆን ፣ አንድ አባል በነፍስ ወከፍ አንድ ድምጽ ብቻ የሚኖረው መሆኑን ፣
- —የማኅበሩ ሸቀጥ በገቢያ ዋጋ እጅ በእጅ ገንዘብ ከፍሎ እንጂ በዱቤ የማይሸጥ መሆኑን ፣

Digitized by Google

—ከማኅበሩ የተጣራ ትርፍ ለአባላት የሚከፈለው ድርሻ እያንዳንዱ አባል ከማኅበሩ ሱቅ በገዛው ሸቀጥ መጠን መሆኑን ፣

—ከማኅበሩ ትርፍ ውስጥ የአባላትን የዕውቀት ደረጃ ከፍ ለማድረግ በሚያስችል ተግባር ላይ የሚውል ገንዘብ ማስቀመጥና ለዚሁም ግብ ትምህርት ቤት ፣ ቤተ መጻሕፍት ፣ የንባብ ቤት ፣ ወዘተ . . . መሥራት ማስፈለጉን የሚያመለክቱ ነበሩ ። [12]

እነዚህ መሠረተ ሃሳቦች የኅብረት ሥራ ማኅበር እንቅስቃሴ በተካሄደበት የካፒታሊስት አገር ሁሉ ከመስፋፋታቸውም በላይ፣ በ1895 በእንግሊዝ አገር በለንደን ከተማ የተቋቋመው ዓለም አቀፍ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ድርጅት (International Cooperative Alliance) ተቀበሎአቸዋል ። [13] በአሁኑ ወቅት የሶሻሊስት ሀገሮችም የዚህ ዓለም አቀፋዊ ድርጅት አባላት ስለሆኑ የድርጅቱ ደንብና መሠረተ ሐሳቦች በካፒታሊስትና በሶሻሊስት ሀገሮች ያሉትን ሁሉ ሊያቅፉ በሚያስችል ሁኔታ ተሻሽሏል ። ለማንኛውም በተምኔታውያን ሶሻሊስቶችና በተከታዮቻቸው አነሳሽነት ከ19ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ አንስቶ የተቋቋሙት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ለብዙ ጊዜ ሳይቆዩ ፈርሰዋል ። [14] ስለሆነም በካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሊያብቡ ስለማይችሉ በተለይ ከ1950 ዓመታት ጀምሮ ሕልውናቸው እየመነመነ የቀሩትም ወደካፒታሊስት የንግድ ድርጅት እየተለወጡ እንደመጡ ለመገንዘብ ይቻላል።

የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መሥራቾችና የኅብረት ሥራ ማኅበር

በኅብረት ማምረት የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ባህርይ ነው ። ማርክስ ከካፒታሊስት ስልተምርት መስፋፋት ጋር የበለጠ እየተጠናከረ የመጣውን በኅብረት የመሥራትን ሁኔታ በመግለጽ ሲጽፍ እንደሚ ከተለው ብሏል ፦

> አንድ ካፒታሊስት በአንድ ጊዜና ቦታ በርካታ ሠራተኞችን ቀጥሮ ሲያሠራ ያኔ የካፒታል አመራረት ስልት በእርግጥ ይጀምራል ። ከዚሁም በመነሳት የሥራው ሂደት በሠራተኛ ብዛት ስለሚከናወን በርካታ ምርት ይገኛል ። ስለሆነም በርካታ ሠራተኞች አብረው አንድ ዓይነት ሥራ ከሠሩ ተባበሩ ወይም በኅብረት ሠሩ ማለት ነው ። በኅብረት መሥራት የየግለሰቡን የማምረት ችሎታ ከመጨመሩም አልፎ አዲስ ኃይል ይፈጥራል ። በዚህም ሁኔታ የሚፈጠረው አዲስ ኃይል፣ የተባበረው የሰፊው ሕዝብ ኃይል ይሆ ይሆናል ። ብዙ ሰዎችን አዋህዶ አንድ ላይ በማስተባበር ከሚገኘው አዲስ ኃይልም ሌላ ፣ ሰዎች አብረው አንድ ላይ በመሥራታቸው ብቻ ማለትም የሚከሰተው ማኅበራዊ ግንኙነት ራሱ የእያንዳንዱን ሠራተኛ የሥራ መንፈስ ከፍ አድርጎ የሚያጐለብት ነው ።

የሥራ ለምሳሌ 12 ሰዎች በቀን 12 ሰዓት በኅብረት እየሠሩ በአንድነት 144 ሰዓት ሠርተው የሚያመርቱት ውጤት 12 ሰዎች በተናጠል እያንዳንዱ 12 ሰዓት ሠርተው ከሚያመርቱት ፣ ወይም አንዱ ሰው ብቻውን በቀን 12 ሰዓት እየሠራ በ12 ቀን ከሚያመርተው የበለጠ ነው ። እንዲሁም ፣ ለምሳሌ ፣ አንድ ሥራ በተወሰነ ወቅት 1,200 ሰዓት የሚፈጅ ቢሆን፣ ለአንድ ሰው በቀን 12 ሰዓት እየሠራ 100 ቀን ይፈጅበታል ። ለአንድ መቶ ሰዎች ግን 12 ሰዓት ሠርተው አንድ ቀን ብቻ ይፈጅባቸዋል ። የዚህም አሠራር ውጤት በግብርና ፣ በዕደ ጥበብ ሆነ ወይም በኢንዱስትሪ መስክ ያው ነው ። [15] በዚህም ማኅበራዊ የአሠራር ስልት የሚጠቀመው ካፒታሊስቱ ነው ።

Digitized by Google

በካፒታሊስት ስልተምርት ውስጥ የሥራ
ምርታማነትን የሚያሳድጉ ሶስት ተከታታይ
የዕድገት ደረጃዎች እንደነበሩ ማርክስ ይተ
ነትናል ። እነዚህም የኅብረት ሥራ ፣ የሥራ
ክፍፍልና የፋብሪካ ሥራ ሲሆኑ ፣ ሥራ ለካ
ፒታል ተገዥ የሆነበትንና የካፒታሊስት
ብዝበዛ የተፋፋመበትን ሂደት የሚያንፀባ
ርቁ ናቸው ። የኅብረት ሥራም በአንድ በኩል
የሥራ ጊዜን ሲቀንስ በሌላ በኩል ካፒታ
ሊስቱ የሚያካብተውን የተረፈ እሴት መጠን
ይጨምርለታል ። በዚህ ሁኔታ ፣ ማኅበራዊ
ሥራ ለአምራቾች ጥቅም የሚውል ኃይል
መሆኑ ቀርቶ ለካፒታሊስቱ ትርፍ ማካበቻ
የካፒታል አምራች ኃይል ይሆናል።[16] ማለ
ትም የሥራ ውጤት ለብዙኃን ሠርቶአደሮች
ጥቅም መዋሉ ቀርቶ ጥቂት ካፒታሊስቶች
የሚበዘብዙት ይሆናል ።

ማርክስና ኤንግልስ ከተጨባጭ ሳይንሳ
ዊና ቁስአካላዊ ትንተና ተነስተው የወዝአ
ደሩን መደብ ታሪካዊና አብዮታዊ ተልዕኮ
በሰፊው አብራርተዋል።በካፒታሊስቱና በወ
ዝአደሩ መሐከል ያለው መደባዊ ቅራኔ በመ
ራራ የመደብ ትግል እንጂ በእርቅ ፣ በድር
ድር ወይም በበጐ ፈቃድ እንደማይፈታ አረ
ጋግጠዋል ። ከእነዚህ ሁለት ተፃራሪ መደ
ቦች መሐከል የካፒታሊስቱ መደብ በወዝ
አደሩ አብዮታዊ የትግል ሂደት ተደምስሶ
እኩልነትና ፍትሕ የተመላበት የሠራተኛው
የበላይነት የሰፈነበት አብዮታዊ መን
ግሥት ተቋቁሞ ወደ ሶሻሊዝም እንደሚሸ
ጋገርና ከዚያም የኮሚኒስት ሥርዓት እንደ
ሚገነባ ሳይንሳዊ አቅጣጫ ቀይሰዋል ።

ከዚህም በመነሳት በ 1848 ባወጡት የኮ
ሚኒስት ማኒፌስቶ በሚባለው ጽሑፋቸው፣
ብዝበዛን ለማስቀረት የምርት መገልገያዎች
ሁሉ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ፣ የሠር
ቶ አደሩ ሕዝብ ንብረት መሆንእንዳለባ
ቸው አስገነዘቡ ። በተጨማሪም በማኒፌ
ስቶው በገጠር የሚኖረው ጭቁን ሕዝብ
በኅብረት ሥራ ማኅበራት እየተደራጀ
በሩፊ የወል እርሻዎችን በማቋቋምና በማ
ልማት የጋራ ጥቅሙን ማስከበር እንዲ
ችል መሬት የሕዝብ ንብረት መሆን
እንዳለበት በፕሮግራማቸው አመልክተ
ዋል ።[17] እዚህ ላይ ማርክስ የገበሬ
ውን አሰቃቂ የኑሮ ሁኔታ በማስመል
ከት ስለፈረንሳይ ገበሬ በወቅቱ የጻፈውን
መጥቀስ ተገቢ ይሆናል ። ይኸውም ፣ « ቁ
ጥሩ እንደአሸን የበዛ ትንሽ የመሬት ይዞታ
ያለው ገበሬ ፣ አንዱ ከሌላው ጋር ሳይተሳ
ሰር በቆረቆዘ ሁኔታ የሚኖር ፣ ትንሽ የመ
ሬት ይዞታው ከሚያቀራርበው ይልቅ ነጥሎ
የሚያኖረው ፣ ዕውቀት አልባና ጉስቋላ ፣ የማ
ኅበራዊ ኑሮ ሕግ የራቀው ነው ፤ »[18] የሚ
ለው ፣ የተበታተነና የተበጣጠሰ ብቸኛ የእ
ርሻ ይዞታ ከቶ እንደማይበለጽግ ያመለክ
ታል ።

የማርክስ ወዳጅ የነበረ ኤርነስት ጆንስ
የተባለ በወቅቱ በእንግሊዝ አገር የነበረ ቻር
ቲስት የተባለ ድርጅት ተጠሪ ስለኅብረት
ሥራ ማኅበራት ሲጽፍ ፣

> በካፒታሊስት ሥርዓት ውስጥ የኅብረት
> ሥራ ማኅበራት ከካፒታሊስቱ ጋር
> ተወዳድረው ሊዘልቁ አይችሉም ። ስለ
> ሆነም ፣ ግባቸውን ለመምታት በሀገር
> አቀፍ ደረጃ አንድ ማዕከላዊ ድርጅት
> አቋቁመው በአገሩ ያሉት ማኅበራት
> ሁሉ የዚህ ማዕከል ቅርንጫፎች ሆነው
> መመራት አለባቸው ። ለዚህም ግብ
> ማዕከላዊ ሂሳብ ተቋቁሞ ቅርንጫፎቹ
> ሁሉ ከተወሰነ መጠን በላይ የሚያገ
> ኙትን ትርፍ ለማዕከሉ ሂሳብ እንዲል
> ኩና ይህም የሚሰበሰብ ገንዘብ ለኅብ
> ረት ሥራ ማኅበራት ማስፋፊያ እንዲ
> ውሉ [19]

ብሎ ነበር።ነገር ግን የኤርነስት ጆንስ ሐሳብ
ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም ።

ማርክስ በካፒታሊስት ሥርዓት ሥር የኅ
ብረት ሥራ ማኅበራትን መቋቋም አልተቃ
ወመም ። እንዲያውም ፣ ያለካፒታሊስት
ተሳትፎ ፣ ወዝአደሩ የኅብረት ሥራ ማኅበ

Digitized by Google

ራትን እያቋቋመ ተደራጅቶ ቢያመርት ፣ በራሱ እምነት እንዲያድርበትና የአመራረት ስልት እንዲቀስም ይረዳዋል ብሎ ነበር ። ነገር ግን በማርክስ አስተያየት የኅብረት ሥራ ማኅበራት በካፒታሊስት ሥርዓት ሥር እስከ ሆኑ ድረስ ፣ እንኳንስ በሥርዓቱ ላይ ተጽ እኖ ኖሮአቸው የሥርዓት ለውጥ ሊያስከትሉ ይቅርና ማኅበራቱ ራሳቸው የሥርዓቱ ተገ ዥና ጥገኛ ሆነው እንደሚቀሩ አስገንዝቧል። በማርክስ አስተያየት የኅብረት ሥራ ማኅ ር ግቡን ሊመታ የሚችለው የወዛደሩ መደብ የፖለቲካ ሥልጣን ጨብጦ ኅብረተሰብን በአዲስ ሥርዓት ለመምራት ሲችል ብቻ ነው ። የኅብረት ሥራ ማኅበር በካፒታሊ ስት ሥርዓት ሥር ሆኖ ግቡን ይመታል ማለት ዘበት ነው ። ማርክስ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን አስመልክቶ በ1866 በመስከ ረም ወር ጄኔቫ ተሰብስቦ ለነበረው የሠራ ተኞች የመጀመሪያው ዓለምአቀፍ ጉባኤ በላከው ጽሑፍ እንደገለጸው ፣ ጉባኤው መፈ ክሮችን በማስተጋባት ፈንታ የሠራተኞችን እንቅስቃሴዎች ማዋሃድና ማቀነባበር እን ዳለበት አስገንዝቦ፣የሚከተሉት እርምጃዎች መወሰድ እንደሚገባቸው አመልክቷል ።

—በመደብ ቅራኔ ላይ የተመሠረተውን ያሁኑን ኅብረተሰብ ሊለውጡት ከሚ ችሉ ኃይሎች አንዱ የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንቅስቃሴ መሆኑ መታ ወቅ አለበት ። የዚህም እንቅስቃሴ ቁም ነገሩ ፣ የሰውን ጉልበት የካፒታል ተገዥ ያደረገውን ያሁኑን አቆርቋዥ አራቋችና ጨቋኝ ሥርዓት ነፃና በአ ምራቾች መካከል እኩልነት በሰፈነበት ሥርዓት ለመተካት መቻሉን በተግባር ከማሳየቱ ላይ ነው ።

—ነገር ግን የኅብረት ሥራ ማኅበር ስልት ብቻውን የካፒታሊስት ኅብረተሰብን ሊለውጥ እንደማይችል መታወቅ አለ በት ። ምክንያቱም ወዝአደሮች በየግል ጥረታቸውም እንደሚገልጹት ሁሉ እንቅስቃሴው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ተወስኖ ስለሚገኝ ነው ። ማኅበራዊ ምርትን ወደ አንድ ትልቅና የሰመረ ነፃ የኅብረት ሥራ ሥርዓት ለመለወጥ አጠቃላይ ኅብረተሰባዊ ለውጦች ያስ ፈልጋሉ ።እነዚህም ጠቅላላ የኅብረተ ሰቡን ሁኔታ የሚለውጡ ሆነው የተ ደራጁ የኅብረተሰቡ ኃይሎችን ፣ በማ ንቀሳቀስ ብቻ ነው ሊከናወኑ የሚች ሉት ፤ ማለትም አምራቾች ራሳቸው የመንግሥትን ሥልጣን ከካፒታሊስ ቶችና ከመሬት ከበርቴዎች እጅ መን ጥቀው መውሰድ አለባቸው ።

—ሠርቶአደሩም በኅብረት ሥራ ሱቆች ላይ ብቻ ሳይወሰን በኅብረት የማም ረት ሥራ ላይ እንዲሰማራ ያስፈል ጋል ።

—የኅብረት ሥራ ማኅበራት ከጋራ ገቢ አቸው ከፊሉን ገንዘብ ለፕሮፖጋንዳ ሥራ እንዲያውሉ ያስፈልጋል።ይኸም አዲስ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማቋቋምና ለማስተማር ይረዳል ።

—የኅብረት ሥራማኅበራት የካፒታሊስት የአክስዮን ማኅበራት እንዳይሆኑ ለማ ድረግ ባለአክስዮኖች ሆኑ ወይም አክስ ዮን የሌላቸው የቅጥር ሠራተኞችሁሉ ገቢውን እኩል ሊካፈሉ ይገባል ። [20]

ኤንግልስ በ1894 የፈረንሳይና የጀ ርመን ገበሬዎችን አስመልክቶ ባቀረ በው ጽሑፍ ውስጥ በኅብረት ሥራ ማኅበር ተደራጅቶ የማምረትን ጥቅም ሲያብራሩ የመንግሥት ሥልጣን ስን ይዝ የሰፋፊ እርሻ ባለርስቶችን እንደ ምንወርስ ሁሉ የገበሬዎችን ትናንሽ ይዞታዎች አንወርስም ። ትንሽ ይዞታ ያለውን ገበሬ በሚመለከት ከሁሉ አስቀድሞ ተግባራችን የግል ይዞታ ውን ወደኅብረት ሥራ ማኅበርማሸ ጋገር ነው።ይኸንንም ስናደርግ በማ ስገደድ ሳይሆን መልካም አርአያ በማሳየትና ለዚሁም ግብ ማኅበራዊ ድጋፍ በመስጠት ነው ። እያደር

Digitized by Google

> የሚገኙትን ጥቅሞች በተግባር ለማሳየት እንችላለን ። እነዚህም ጥቅሞች ከአሁኑ ለገበሬው ጉልህ ሊሆኑ ይገባል ፤

በማለት የጻፈው ነው። ኤንግልስ በዴንማርክ የአንድ መንደር ገበሬዎች የእርሻ ይዞታቸውን አዋህደው በኅብረት ሥራ ማህበር ተደራጅተው የተገኘውን የምርት ውጤት ባዋጡት ገንዘብ፣ መሬትና ጉልበት መጠን እንዲከፋፈሉ ቀደም ሲል የዴንማርክ ሶሻሊስቶች ያቀዱትን ጠቅሶ ፣

> በአንድ አካባቢ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች ይዞታቸውን አዋህደው ሰፋፊ እርሻዎችን እያቋቋሙ ቢያመርቱ ማኅበራቱን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለማድረስና የአባላትንም የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ያስችላል። ሌላ የሰፋፊ እርሻዎች ምርታማነት የሚገኘውን ትርፍና በነዚህ እርሻዎች ላይ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ምክንያት የሚፈጠረውን ትርፍ የሰው ኃይል በኢንዱስትሪ መስክ ማሰማራት መቻሉን ያመለክታል ። የቀረውንም የሰው ኃይልን ለማኅበራቱ ከአካባቢው መሬት ጨምር በመስጠት በግልማት ላይ ማሰማራት እንደሚቻል ይጠቁማል ።

ኤንግልስ፣ ይህ በተግባር ላይ ሊውል የሚችለው ሠርቶ አደሩ የመንግሥት ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ መሆኑን ጠቅሞ ፣ የሚቋቋመው አብዮታዊ የሠራተኛ መንግሥት ለኅብረት ሥራ ማኅበራት አንዳንድ ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባው ያመለክታል ። ከእነዚህም ድጋፎች መካከል ፣

—ማኅበራት ብድር ሲወስዱ ወለዱ ዝቅተኛ መሆን አለበት ፣

—ዘመናዊ መሣሪያዎችን ማዳበሪያና የመሳሰሉትን ሁሉ ማኅበራት ከመንግሥት በረዥም ጊዜ ክፍያ ሊያገኙ የሚችሉበት ሁኔታ መፈጠር የሚሉ ይገኙበታል ። የዚህም ግብ ፣ እርሶ አደሩ በኅብረት ሥራ ማኅበር ተደራጅቶ መሬቱ ፣ ሀብቱ ፣ ቤቱ ፣ የራሱ ሆኖ ለራሱ ጥቅም መዋሉን አውቆ እንዲያመርት ነው ። በአንፃሩም የግል የመሬት ይዞታና በግል ማረስ ይዞታውን እያጣበበና እያሽቆለቆለ የሚጥለው መሆኑን እርሶ አደሩ መገንዘብ እንዳለበት ኤንግልስ አጥብቆ ያሳስባል ። [21]

የኅብረት ሥራ ማኅበራት በሶሻሊስት ሥርዓት

በሶሻሊስት ሥርዓት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ምሥረታና ግንባታ እስካሁን ድረስ ለረዥም ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ የተካሄደውና ግቡንም ሊመታ የቻለው በሶቪዬት ኅብረት ነው ። ይህን ሐቅ በበለጠ ለመገንዘብ ከ1917 የጥቅምት አብዮት ጀምሮ እስከ 1937 ያለውን የሃያ ዓመታት የሶሻሊስት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ዕድገት ታሪክ በአጭሩ እንመለከት ።

ከ1917 የጥቅምት አብዮት በፊት ሩሲያ በንጉሣዊ አገዛዝ ጨቋኝ ሥርዓት እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው ። እንዲያውም ከ1861 በፊት የገጠሩ የሩሲያ ሕዝብ ከመሬት ጋር ተቆራኝቶ የሚሸጥና የሚለወጥ ገባር ጭሰኛ እንደነበረ የታወቀ ነው። በ1861 በሰፊው የሩሲያ ሕዝብ ትግል የመሬትን ይዞታ ከፊውዳል ወደካፒታሊስት ይዞታ የለወጠው ሕግ ሲታወጅ 23 ሚሊዮን ያህል ከመሬት ጋር የተቆራኙ ገባሮች እንደነበሩ ታሪክ መዝግቦታል ። ይኸም ማለት አንድ ቤተሰብ በአማካይ አምስት አባላት ነበሩት ቢባል በአጠቃላይ 115 ሚሊዮን ሕዝብ ከባርነት ባላነሰ በገባርነት ሥር ይማቅቅ እንደነበረ ያመለክታል ። ከፊውዳል ይዞታ ወደ ካፒታሊስት ይዞታ ባሸጋገረው አዋጅ መሠረት ገባሩ ከመሬት ጋር የመቆራኘቱ ቀንበር ተነስቶ

Digitized by Google

ለት ይዞታውን ለመግዛት ይችላል በሚል
ሳቢያ ፣ መሬቱን እንዲገዛ ይገደድ ነበር ።
በዚህ ሁኔታ ፊውዳል ባለርስቱ ምርጥ መሬ
ቱን ለራሱ እያስቀረ የቀረውን መሬት ለገ
ባሩ በከፍተኛ ዋጋ እየሸጠ እስከ 1917
የጥቅምት አብዮት ድረስ ገበሬውን በከ
ፍተኛ ደረጃ እየበዘበዘ አራቁቶታል ።

በዓለም ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ፣ በወዝ
አደሩ ፓርቲ አመራር ፣ በወዝአደሩ መደ
ብና በአርሶአደሩ ሕዝብ አጋርነት ፣ ሠርቶ
አደሩ ሕዝብ የመንግሥትን ሥልጣን ከጨ
ቋኝ የፊውዶ ቡርዧ መንግሥት እጅ በአብ
ዮታዊ ኃይል መንጥቆ የወሰደበትና ሶሻሊ
ዝምን ለመገንባት የፖለቲካና የኤኮኖሚ
መሠረት የጣለበት የጥቅምት 1917
የሩሲያ ሶሻሊስት አብዮት ነው ። ከዚህም
በመነሳት አብዮታዊውን ለውጥ በተግባር
ለመተርጐም መሪው አብዮታዊ ኃይል ማለ
ትም የኮሚኒስት ፓርቲው በአገሪቱ የኤኮኖ
ሚና ማኅበራዊ ኑሮ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ
ተመርኩዞ ሳይንሳዊ እቅድ ዘርግቷል።ይኸም
በእቅድ መሥራት የሶሻሊስት ግንባታ ዓይ
ነተኛ ባሕርይ መሆኑን ያመለክታል ።

በሶቭየት ኅብረት ታሪክ ውስጥ ከ1917
እስከ 1927 የነበረው ጊዜ የመረረ ትግል፣
የጦርነት ፣ የልማት ቅድመ ሁኔታዎች ዝግ
ጅትና ግንባታ ወቅት ነበረ ለማለት ይቻ
ላል ። ምንም እንኳ የሶሻሊስት አብዮቱ ገና
ከ1917 ጀምሮ በእቅድ የመሥራትን ስልት
ጨብጦ የሽግግሩንና የግንባታውን ሂደት
ከሞላ ጐደል ቢጀምርም የውጭና የውስጥ
ፀረ አብዮት ኃይሎች አብዮቱን ገና ሳያን
ሰራራ ለመቅጨት ያላከናወኑት ተግባርና
ሴራ አልነበረም ። ከውጭ የአሜሪካ ፣ የእን
ግሊዝ ፣ የፈረንሳይ ፣ የጀርመን ፣ የኢጣሊያ
የጃፓን ኢምፔሪያሊስት ወራሪዎች ኃይላ
ቸውን በማስተባበር ከ1918 እስከ 1920
ድረስ ለጋውን የወዝአደር አብዮት ለመቅ
ጨት ተፍጨርጭረዋል ። በተጨማሪም ያ
ወቅት በውስጥም የርስ በርስ ጦርነት ከፉኛ
ተፋፍሞ የነበረበት ወቅት ነው ። ይኸም
ሆኖ ከዚያ ወረራ ፣ ከበባና የርስበርስ ጦርነት
አብዮቱ ድል ተቀዳጅቶ በአሸናፊነት ለመ
ውጣት ችሎአል ።

ከውጭና ከውስጥ ፀረ አብዮተኞች ጦር
ነትም ሌላ በሶቭዬት ኅብረት የኮሚኒስት
ፓርቲ ውስጥ የአንጃኞች ሴራ ነበር ።ይኸም
በተለይ የመደቦችን አሰላለፍ ያልተገነዘበ ፣
የወቅቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያልተረዳ ፣ የሶ
ሻሊስት ግንባታን የሚያደናቅፍ የእነ ትሮት
ስኪ፣የቡካሪንና ተከታዮቻቸው ኢሳይንሳዊ
አመለካከት ነበር። በአጭሩ የእነ ትሮትስኪ
አንጃኛ ቡድን የወዝአደሩን መደብና የአርሶ
አደሩን ሕዝብ አጋርነት የማይበቀል ሆኖ
ወዝአደሩ ፣ ያለ አርሶአደሩ ፣ ብቻውን ሶሻ
ሊዝምን ሊገነባ ይችላል የሚል ነበር ። የእ
ቡከሃሪን አንጃኛ ቡድን ሶሻሊዝምን
መገንባት የሚቻለው ከበርቴ ገበሬውን (ኩላ
ኩን) አጋር አድርጐ ነው የሚል ለካፒታ
ሊዝም ማቆጥቆጥ አመቺ የሆነ አመለካከት
ነበር ። በአጠቃላይ ትሮትስኪ ፣ ቡካሃሪንና
ተከታዮቻቸው የሶቭዬት የኅብረት ሥራ ማኅ
በራት ከካፒታሊስት የንግድ ድርጅት አይ
ለዩም ፣ ሶሻሊዝምን በአንድ አገር መገንባት
አያስችሉም ፤ የሠራተኛው መደብና የአርሶ
አደሩን ሕዝብ የፖለቲካ አጋርነት የፀና ለማ
ድረግ አይችሉም [22] የሚል ከተጨባጭ
ሁኔታ የራቀ ሃሳቦችን ያናፍሱ ነበር ።

በአጭሩ ከዚህ በላይ በተመለከተው ትግል
ነበር በሶቭዬት ኅብረት የሶሻሊስት ግን
ባታና የኅብረት ሥራ ማኅበራት ምሥረታ
ሂደት የተጀመረው ። ማርክስና ኤንግልስ
የሶሻሊዝምን ግንባታ አስመልክተው ስለ
ኅብረት ሥራ ማኅበራት የተለሙትን ንድ
ፈ ሃሳብ ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር ለማገናዘብ
ከ1917 የጥቅምት አብዮት ጀምሮ ተግባራዊ
ስልት ለመቀየስ የቻለው ሌኒን ነው ። የኅ
ብረት ሥራ ማኅበራት የሚመሩባቸውን
ሌኒናዊ መሠረተ ሃሳቦች በጥር ወር 1923
ሌኒን በጻፈው መመሪያ ተብራርተው ይገ
ኛሉ ። እነዚህም በአጭሩ ፣

Digitized by Google

— አባልነት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ፣

— ማኅበራት በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትና በዕቅድ የሚመሩ መሆናቸውን ፣

— ማኅበራት ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደሥራው በሚለው መርህ መሠረት ክፍያ ማድረጋቸውንና መተዳደራቸውን ፣

— ማኅበራት መሃይምነትን ለማጥፋትና ቴክኖሎጂን ለማስፋፋት አባላትን የሚያስተምሩ መሆናቸውን ፣

የሚያረጋግጡ ናቸው ። ሌኒን ፣ በሶሻሊስት ሥርዓት ሥርየኅብረት ሥራ ማኅበርን ዕድገት የተለያየ መልክ አብራርቷል ። ለምሳሌ የኅብረት ሥራ ማኅበር ፣ በማኅበራዊ ይዞታ ላይ የተመሠረተ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ አካል ሆኖ ፣ በግብርና ዘርፍ አዲስ የምርት ግንኙነት የሚገነባና አርሶ አደሩን አዲስ የሥራ ሥነ ሥርዓት የሚያስተምር መሆኑን ልክ የሠራተኞች ማኅበር የሠራተኛውን መደብ አባላት እንደሚያንፃ ሁሉ የኅብረት ሥራ ማኅበር መላ አርሶ አደሩን የሚያስተባብር ሕዝባዊ ድርጅት መሆኑን ይገልጻል። በመሆንም የኅብረት ሥራ ማኅበር በገጠር ምርት ኃይሎችን የሚያዳብርና የአርሶ አደሩን ቁሳዊ ሕይወት የሚያሻሽል አዲስ የገጠር ማኅበራዊ ሥርዓት መሆኑን ሌኒን ያመለክታል ። [23]

የሌኒንን የኅብረት ሥራ ማኅበር ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የሶቭዬት መንግሥት በመጀመሪያ ደረጃ ከወሰዳቸው እርምጃዎች ውስጥ ከላይ እስከታች ድረስ በመንግሥት አሠራር መሠረታዊ ለውጥ በማካሄድ ማሻሻልን ያጠቃለለ ነበር ። ይኸም ማሻሻል በተለይ ዋልጌነትን ፣ የቢሮክራሲ አሠራርን የማስወገድ ተግባርን ያካተተ ነበር። ቀጥሎም አርሶአደሩን በኅብረት ሥራ ማኅበር ለማደራጀትና ብሎም ግንዛቤውን ከፍ ለማድረግ በቅድሚያ የባህል አብዮት ማካሄድ ነበር ።

የሌኒን ኅብረት ሥራ ማኅበር ዕቅድ ዋና መነሻዎች ፣

— የመንግሥት ሥልጣን በሠርቶ አደሩ ሕዝብ እጅ መሆኑን ፣

— በኮሚኒስት ፓርቲው አመራር ሥር የሠራተኛው መደብና የአርሶ አደሩ ሕዝብ የፖለቲካ አጋርነት መጠናከር ሆኖ ፣ በዚሁም ላይ ፣ ለኢኮኖሚው ሶሻሊስታዊ ዕድገት ሶሻሊስት ኢንዱስትሪን ፣ በተለይም ከባድ ኢንዱስትሪን፣ መገንባት እንደሚያስፈልግ የሚተይስ ነው ። ከዚሁ በመነሳት ነው ከሁሉ አስቀድሞ ሶቭዬት ኅብረት በኤሌክትሪክ ኃይል እንድትገነባ ማድረግ ለኢንዱስትሪ ብሎም ለኮሚኒዝም ግንባታ ወሳኝ ነው በሚል መርህ ታዋቂውን የኤሌክትሪፊኬሽን ዕቅድ ለመጀመሪያ ጊዜ ሌኒን የዘረጋው ። ይኸም ሆኖ የየሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታ በሚወስነው መሠረት ፣ የኢንዱስትሪውንና የግብርናው ዘርፍ በተደጋጋፊነት ማደግ እንዳለባቸው ሌኒን ደጋግሞ አሳስቧል ።

በመሆኑም የሌኒንን መመሪያ በመከተል ፣

— የፓርቲው 14ኛው ጉባኤ በ1925 ኢንዱስትሪ የሚገነባበትን መመሪያ ፣ እንዲሁም

— 15ኛው የፓርቲው ጉባኤ በ1927 የግብርናው ኢኮኖሚ የሚለማበትንና የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚደራጁበትን መመሪያ ተይሰጥል ። [24]

አብዮቱ መጀመሪያ ከወሰዳቸው ዓበይት እርምጃዎች ውስጥ አንዱ የመሬት አዋጅ ነበር ። ይኸም አብዮቱ ድል በመታ በሁለተኛው ቀን መሬትን የሕዝብ ያደረገው አ

Digitized by Google

ዋጅ ነው ። ኋላም ሌኒን በታኅሣሥ ወር 1918 ለገበሬዎች ጉባኤ ባደረገው ንግግር፥ «ተግባራችንና ግባችን ወደሶሻሊስት እርሻ ለመሸጋገር ሆኖ ይህም ተግባራዊ የሚሆነው ገበሬዎች የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት እያቋቋሙ በማምረት ነው » ብሏል ። ሌኒን የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሥራ ምርታማነት እጥፍ ድርብ የሚጨምሩ መሆናቸውን አስገንዝቦ ፥ የሥራ ምርታማነት በበኩሉ የሰው ኃይል ለመቆጠብና የተቆጠበውንም የሰው ኃይል በሌላ የኢንዱስትሪ ወይም የግብርና ሥራ ላይ ማሰማራት የሚያስችል መሆኑን ገልጾአል ። ስለሆነም ምንም እንኳ አርሶአደሩን በኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲደራጅ መቀስቀስና ማንቃት ተገቢ ቢሆንም ቅሉ በፈቃደኝነት [25] እንጂ በግፊት እንዳይደራጅ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ሌኒን አሳስቧል ። የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማስፋፋት የሶቭዬት መንግሥት ዕርዳታውን በሰፊው ዘርግቷል ። ለምሳሌ ፥ በኅዳር 1918 የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማደራጀት የተወሰነ ገንዘብ መድቦ እንደነበር ይታወቃል ። [26] የተመደበው ገንዘብ ያለ ወለድ ለማኅበራቱ በብድር እየተሰጠ ማኅበራቱም ብድሩን በዓይነት (በእህል) እንዲከፍሉ ይደረግ ነበር ።

የሶቭዬት ኅብረት መንግሥት በየካቲት ወር 1919 ያወጣው ድንጋጌ መሬትን በግል ከማረስ ይልቅ በኅብረት ወደማረስ መሸጋገር ማስፈለጉን አስገንዝቧል ። በጥር ወር 1923 ሌኒን በጻፈው መመሪያ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚደራጁበትን መሠረተ ሀሳብ ቀይሷል ። [27] ሌኒን የወዝአደሩ መደብ ከአርሶአደሩ ጋር የሚመሠርተው አጋርነት ሶሻሊዝምን ለመገንባት ዋስትና መሆኑን ብዙ ጊዜ ደጋግሞ አስገንዝቧል ። እንዲሁም በአርሶአደሩ ውስጥ ደኃ ገበሬ ፥ መለስተኛ ገበሬና ሃብታም ገበሬ (ኩላክ) መኖራቸውን ተንትኖ ድኃውና መለስተኛው ገበሬ በሽግግሩና በሶሻሊስት ግንባታው ሂደት ውስጥ አጋርና ተባባሪዎች መሆናቸውን ገልጿል ። በመሆኑም ምንም እንኳ የድኃ ገበሬው አጋርነት የማያጠራጥር ቢሆንም ፓርቲው በተለይ መለስተኛ ገበሬውን አጋር አድርጎ መያዝ እንዳለበት አሳስቧል ። ሃብታም ገበሬው (ኩላኩ) ግን የመደብ ጠላት በመሆኑ አብዮቱ የሚታገለው እንጂ የሚታረቀው አለመሆኑን አስገንዝቧል ።

የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሲደራጁ የሃብታም ገበሬው መደብና ፀረ አብዮተኞች አደጋ እየጣሉ ማኅበራቱን ይዘርፉና አባላቱን ይገድሉ ስለነበረ የማደራጀቱ ተግባር የተካሄደው የመደብ ትግል ፍልሚያ ከፉኛ በተፋፋመበት ሁኔታ እንደነበረ የሚዘነጋ አይደለም ። ይኸም ሆኖ አምራች ማኅበራት በተደራጁ ቁጥር በየግል ተበታትትኖ ከሚያመርተው ገበሬ የበለጠ ምርት እንደሚያመርቱ በተግባር ከመታየቱም ሌላ ከሰበሰቡት ምርት ለፍጆታ የሚበቃ እያስቀሩ ትርፉን ለአከፋፋይ የመንግሥት ድርጅቶች ይሸጡ ነበር።እርግጥ በመጀመሪያው ወቅት የአምራች የኅብረት ሥራ ማኅበራት በአብዛኛው ለፍጆታ ያህል እንጂ ለገበያ የሚተርፍ ለማምረት እንዳልቻሉ ይታወቃል ። ያም ሆኖ ለፍጆታም ቢሆን በቂ በማምረት ከረሃብ ለመዳን በመቻላቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ።

ግብርናን በሶሻሊስት ፈር ለማደራጀት የመንግሥት እርሻዎች መቋቋምና መስፋፋት ወሳኝ ነው ። በመሆኑም ከአብዮቱ ድል ጀምሮ ሰፋፊ የመንግሥት እርሻዎች ከኅብረት ሥራ ማኅበራት ጐን ተቋቁመው ቴክኒካዊና የዘመናዊ እርሻ አመራር ድጋፍ ይሰጡ ነበር ። ለምሳሌ በ1920 ከመሬት ከበርቴዎች የተወረሰ 2,868,000 ሄክታር መሬት የሚያርሱ 3,988 የመንግሥት እርሻዎች ነበሩ ። [28]

በ1921 ሌኒን አዲስ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ነደፈ ። ከዚህም ፖሊሲ መሠረታዊ ዓላማ መካከል በእርስ በርስ ጦርነትና በውጭ ወረራ የወደቀው የሶቭዬት ኢኮኖሚ እንዲ

Digitized by Google

ያገግምና በገጠር ለሶሻሊስት የኢኮኖሚ
ግንባታ አመች ፖሊቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና
ማኅበራዊ ሁኔታ መፍጠር ይገኙበታል ።
አዲሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በተግባር በዋለ
በት ጊዜ ማለትም ከ1921 እስከ 1927
ድረስ በነበረው ጊዜ ውስጥ ኩላክ በመ
ባል የሚታወቁት የገጠር ሃብታም ገበሬ
ዎች እንሠራሩ ። ምክንያቱም አዲሱ የኢ
ኮኖሚ መመሪያ ከበርቴ ገበሬዎች ትርፍ
እህላቸውን ገበያ ወስደው እንዲሸጡ ፣ በገ
ጠር የሰው ኃይል ቀጥረው እንዲያሠሩ ፣
የእርሻ መሬት እንዲከራዩ ስለፈቀደላቸው ፣
ለካፒታሊዝም ማቆጥቆጥ አመቺ ሁኔታ
በመፈጠሩ ነው ።

በእርግጥም የአዲሱ ኢኮኖሚ መመሪያ
በተግባር መዋል የሶቭዬት ኅብረት ብሔ
ራዊ ኢኮኖሚ ከደረሰበት ውድቀት እንዲያ
ገግም ለማድረግ ትልቅ ሚና ተጫውቷል ።
በገጠሩ አያሌ የገበሬዎች ፣ የሸማቾች
የአገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበራት
ተመሥርተዋል ። እነኚህ ማኅበራት መመ
ሥረታቸው በአንድ ፊት አርሶ አደሩን ከነ
ጋዴዎች ብዝበዛ ነፃ ያወጣው ሲሆን በሌላ
በኩል በቀጥታ ከሶሻሊስቱ ኢንዱስትሪ
ምርት ጋር እንዲተዋወቅ አደረጉት ። ከአ
ገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚ
ገኘው ከፍተኛ ትርፍ ለተጨማሪ የኅብረት
ሥራ ማኅበራት ማስፋፊያ እንዲውል
ተደረገ ። [29] በአጠቃላይ በገጠሩ የአዲሱ
የኢኮኖሚ ፖሊሲ በሥራ ላይ መዋል የ[illegible]
ዝአደሩንና የአርሶአደሩን አንድነት የበ
ለጠ አጠናከረው ፣ በገጠር የንግድ ካፒ
ታልን ብዝበዛን ገታው ፣ እንዲሁም ገበ
ሬው የሶሻሊዝም ኢኮኖሚን ጠቃሚነትና
የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማስፋፋትን አስ
ፈላጊነት ግልጽ አደረገለት ።

የአዲሱ ኢኮኖሚ ፖሊሲ በገጠር በተግ
ባር መተርጐም በአንድ ፊት ለሶሻሊስት
የኢኮኖሚ ግንባታ አመች ሁኔታና መሸጋ
ገሪያ ድልድይ የፈጠረ ቢሆንም በሌላ በኩ
ል ፀረ ሶሻሊዝም አቋም ያላቸውን የገጠር
ከበርቴዎች (ኩላኮች) ፈጥሮ ነበር ። የኩላ
ኮች መበራከት የገጠሩን አብዮት ከሚያ
ስጋ ደረጃ ላይ ስላደረሰው በ1927 የፓርቲው
15ኛ ጉባኤ አርሶአደሩን በኅብረት ሥራ
ማኅበራት እያደራጁ ሶሻሊዝምን መገንባት
ያስፈልጋል ሲል ታሪካዊ ውሳኔውን አሳ
ለፈ ። በ15ኛው ጉባኤ ውሳኔ መሠረት በሶ
ቪዬት ኅብረት የኅብረት ሥራ ማኅበራት
እንዲስፋፉና እንዲያብቡ አስፈላጊው እር
ምጃ ሁሉ ስለተወሰደ አያሌ የኅብረት ሥራ
ማኅበራት ተመሠረቱ ። እስከ 1927 ድረስ
የነበረውን የኅብረት ሥራ ማኅበራትንና
የአርሶ አደሩን ሁኔታ ከዚህ በታች ከተመ
ለከተው አኃዛዊ መረጃ መረዳት ይቻላል ።

የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራት [30]

የዘመን አቆጣጠር	የኅብረት ሥራ ማኅበራ ብዛት	በኅብረት ሥራ ማኅበራት የአርሶ አደሮች ቁጥር ብዛት	የኅብረት ሥራ ማኅበራት የመሬት ስፋት በሄክታር
1918	1,579	16,400	202,000
1919	6,188	81,300	925,000
1920	10,600	131,000	1,777,000

Digitized by Google

አርሶአደሩን በሚመለከት በ1925 [31]

ገበሬዎች	የቤተሰብ ኃላፊዎች ብዛት	የሕዝብ ብዛት	የአንድ ቤተሰብ አማካይ ብዛት
ደኃ ገበሬዎች	5,200,000	22,400,000	4.
መለስተኛ ገበሬዎች	13,900,000	26,700,000	5.5
ሃብታም ገበሬዎች	780,000	5,000,000	6.3

እዚህ ላይ የመለስተኛ ገበሬው ቁጥር በ ዝቶ መገኘቱ ከመሬት አዋጅ በኋላ መሬት የሕዝብ ሆኖ ለአርሶአደሩ በመከፋፈሉ አርሶአደሩ ከነበረበት ድህነት እየተላቀቀ መለስተኛ ገበሬ ለመሆን መብቃቱን ያመለክታል ። በዚሁ ወቅት የገጠር ወዝአደሩ ማለትም ለሃብታም ገበሬው /ኩላክ/ ተቀጥሮ የሚሠራው የእርሻ ሠራተኛ ብዛት ከሁለት ሚሊዮን በላይ ደርሶ ነበር ።

በሶቭዬት የኅብረት ሥራ ማኅበር ሶሻሊስታዊ ግንባታ ግቡን ሊመታ የቻለው ከ1927 እስከ 1937 በነበረው ጊዜ ውስጥ ነው ። ከፍ ሲል እንደተመለከተው በታኅሣሥ ወር 1927 የተሰበሰበው የፓርቲው 15ኛው ጉባኤ የሶሻሊስት ኢንዱትሪን መገንባት የሚቻለው ከግብርናው ክፍለ— ኤኮኖሚ ከሚገኘው ክምችት ነው የሚለውን ቀደም ሲል የነበረውን እቅድ ከገመገመ በኋላ ከግብርናው ዘርፍ የተጠበቀው ክምችት አልተገኘም ። በመሆኑም ጉባኤው አርሶ አደሩን ሕዝብ በአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት አደራጅቶ ፣ የተበበታተነውን እርሻ ወደሰፋፊ እርሻ ለውጠ በትራክተር መጠቀም የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው ሲል ከመወሰኑም ሌላ በሃብታም ገበሬው /ኩላክ/ መደብ ላይ መራራ ትግል ለማካሄድ ቆርጦ ተነሳ ። በዚህ ወቅት በገጠር በጠቅላላው ኩላክ የተባሉት ሃብታም ገበሬዎች ቁጥር አንድ ሚሊዮን ያህል ደርሶ ነበር ። የጭቁኑ አርሶ አደር ቁጥር ግን ከሃያ ሦስት ሚሊዮን በላይ ነበር ። ከላይ በተጠቀሰው ውሳኔ መሠረት በመጀመሪያው የአምስት ዓመት የኤኮኖሚ እቅድ ፣ ማለትም ከ1928 ጀምሮ ፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የማደራጀቱና የማቋቋሙ ሂደት በአብዮታዊ ግፊት በአፋጣኝ ተከናወነ ።

የመደብ ፍልሚያውም በአንድ ሚሊዮን ሃብታም ገበሬዎችና በ23 ሚሊዮን አርሶ አደሮች መካከል እጅግ ተፋፋመ ። ውጤቱም የሃብታም ገበሬው መደብ ከመደብ አንፃር መደምሰስ ሆኖ አርሶአደሩ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ለመደራጀት ቻለ ። በመሆኑም በ1929 38,000 አምራች ኅብረት ሥራ ማኅበራት እንዲደራጁ ታቅዶ የነበረው ፣ በእቅዱ ጊዜ ውስጥ ከዚያ አልፎ 57ሺህ ማኅበራት ሊቋቋሙ ቻሉ ። እንደዚሁም በ1930 የመጀመሪያው

Digitized by Google

ሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ብቻ አስር ሚሊዮን ቤተሰብ የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላት ሆኑ። በእርግጥ ሂደቱ እጅግ የተፋጠነ ነበረ። ከዚሁም የተነሳ አንዳንድ ጉድለቶች መከሰታቸው አልቀረም ። ለምሳሌ እንደ ዶሮ የመሰለውን የቤት እንስሳ የማኅበር ንብረት እንዲሆን የማድረግ አዝማሚያ ነበር ። ፓርቲው ይኸን ሁኔታ በማጤን ብዙ የማረሚያ መመሪያዎች በአፋጣኝ በማውጣት በተለይም በ1930 በ16ኛው የፓርቲ ጉባኤ የሌኒን የኅብረት ሥራ ማኅበር መመሪያ በትክክል በተግባር እንዲተርጉም ወቅታዊ ውሳኔ አሳለፈ ። በመሆኑም የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የማደራጀቱና የማጸጸሙ ተግባር በመጀመሪያውና በሁለተኛው የአምስት ዓመት እቅዶች ጊዜ ውስጥ ግቡን ሊመታ ችሏል ። በ1936 ከዘጠና ሚሊዮን ሄክታር መሬት በላይ በኅብረት ሥራ ማኅበራት ሲታረስ በግል የታረሰው መሬት ስፋት አንድ ሚሊዮን ሄክታር ብቻ ነበር ። እስከ 1939 ድረስ በገጠር ከሚገኘው የአርሶ አደር ቤተሰብ 97% የሚሆነው የኅብረት ሥራ ማኅበር አባል ነበር ።

ከዚህ በታች የተመለከተው ዝርዝር በሶቭዬት ኅብረት የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ዕድገት ያመለክታል ።[32]

	1929	1930		1937
የኅብረት ሥራ ማኅበራት ብዛት	57,000	85,000	233,300	243,700
በኅብረት ሥራ ማኅበራት የታቀፉ እርሻዎች ብዛት (በሚሊዮን)	1.0	6.0	15.7	18.5
<u>የኅብረት ሥራ ማኅበራት እድገት በመቶኛ አንፃር ሲታይ</u>				
ሀ /የእርሻ መጠን	3.9	23.6	71.4	93
ለ/ የታረሰው መሬት መጠን	4.9	33.6	87.4	99.1

ከዚህ በላይ ያለው አሃዛዊ ሠንጠረዥ የሚያሳየው ከአገሩ አጠቃላይ የእርሻ ይዞታ አንፃር ነው ።

የአምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት እቅድ ሊሳካ የቻለው የኅብረት ሥራ ማኅበር እንቅስቃሴ በፈቃደኝነት ላይ በመመሥረቱና ብዙሃኑ አርሶ አደሮች የሚደግፉት ከመሆኑም ሌላ የቴክኒክ ሰዎችና የምርትና የፖለቲካ ካድሬዎችን በብዛት ለማሠልጠን በመቻሉ ነው ። በሶቭዬት ኅብረት የኅብረት ሥራ ማኅበራት የእድገት ታሪክን ስንመረምር ከምንገዘባቸው ዋና ዋና ነጥቦች መካከል በዚች አገር የኅብረት ሥራ ማኅበራት እቅድ ግቡን ሊመታ የቻለው፥

— ፓርቲውና መንግሥት የሶሻሊስት ስልተምርትን ለመመሥረት ባሳዩት ያላሰለሰ የአመራር ስልትና ቆራጥነት፥

—ፓርቲው ሁኔታዎችን እየገመገመ በእቅድ ላይ የተመሠረተ ወቅታዊ ርምጃዎችን በመውሰዱ፥

—ፓርቲውና መንግሥት ለኅብረት ሥራ ማኅበራት መደራጀት፥ መቋቋምና እድገት ባበረከቱት ቁሳዊ ድጋፍ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ። በተለይም ዘመናዊ የማምረቻ መሣሪያዎችን በማቅረብና የሠለጠነ የሰው

Digitized by Google

ኃይል በመመደብ በሶሻሊስት መንግሥት የተከናወኑት ተግባሮች ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል ።

ከዚህም በላይ እንደተመለከተው የኅብረት ሥራ ማኅበራት በካፒታሊስት ሥርዓት ሥር ሊስፋፉና ሊዳብሩ እንደማይችሉና ከነአካቴው ወደካፒታሊስት የንግድ ድርጅትነት እያዘቀጡ እንደሚወርዱ መረዳት ይቻላል ። በአንፃሩ ግን በሶሻሊስት ሥርዓት የኅብረት ሥራ ማኅበራት እንደሚያብቡና ግባቸውን እንደሚመቱ በተግባር የተረጋገጠ ነው ። ለዚህም የሶቪየት ኅብረት መላ አርሶ አደር በአሥር ዓመት ውስጥ ፣ ማለትም ከ1927 እስከ 1937 በነበረው ጊዜ በኅብረት ሥራ ማኅበራት ለመደራጀት መቻሉና በሶሻሊስት ሥርዓት ግንባታ ላይ በቀጥታ መሳተፉ ጉልህ ማስረጃ ነው ። ሌሎችም የሶሻሊስት ግንባታ ጎዳና የተከተሉ ሀገሮች ሁሉ መሰል ድል የተቀዳጁ መሆናቸው የታወቀ ነው ።

በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት በኤኮኖሚ ፣ በፖለቲካና በማኅበራዊ ጉዳይ አያሌ የግንባታ ርምጃዎች ተወስደዋል ። (እ. ኢ. አ.) ከ1971 ጀምሮ የሶሻሊስት ኤኮኖሚ ግንባታ ዓይነተኛ ስልት በሆነው በእቅድ መሥራት ተጀምሯል። በተለይም አርሶ አደሩና የዕደ ጥበብ ባለሙያው በኅብረት ሥራ ማኅበራት እየተደራጁ እንዲያመርቱ (እ. ኢ. አ.) 1970 በቁጥር 138 በወጣው አዋጅ መሠረት አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ በሰኔና ሐምሌ ወር (እ. ኢ. አ.) 1971 በተከታታይ የገበሬዎችና የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበራት መመሪያዎች ወጥተው ተግባራዊ በመሆን ላይ ናቸው ።

የኢትዮጵያ ጭቁን ገበሬዎች በአምራቾችና በአገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበራት እራሳቸውን ለማደራጀት ያደረጉት ትግልና መንግሥትም የሚሰጠው ድጋፍ ውጤት እያስገኘ ነው ። ከዚህ በታች የቀረበው ሠንጠረዥ ይህንኑ የሚያመለክት ነው ።

Digitized by Google

እስከ የካቲት 30/1976 በክፍለ ሀገር የተቋቋሙ
የገበሬዎች የአምራቾች የሕብረት ሥራ ማኅበራት ዝርዝር

ክፍለ ሀገር	ማኅበራት ያሉበት		የአባላት ብዛት			የአባል ቤተሰብ ብዛት			የማኅበራት ብዛት		
	አውራጃ	ወረዳ	ወንድ	ሴት	ጠቅላላ	ወንድ	ሴት	ጠቅላላ	የተመዘገበ	ያልተመዘገበ	ድምር
አርሲ	3	21	12,789	1,372	14,161	24,435	35,316	59,751	32	136	168
ባሌ	3	10	4,172	577	4,749	6,927	10,203	17,130	7	87	94
ኤርትራ	5	7	244	53	297	535	694	1,229	—	8	8
ጋሞጎፋ	4	10	2,730	223	2,953	6,188	8,756	14,944	3	15	18
ጎጃም	7	31	10,153	715	10,868	12,877	18,846	31,723	20+9	142—9	162
ጎንደር	7	18	2,532	112	2,644	3,471	4,913	8,384	13+4	43—4	56
ሐረርጌ	7	26	6,889	242	7,131	8,251	11,074	19,325	21	90	111
ኢሉባቦር	4	25	3,604	199	3,863	5,691	7,538	13,229	6+2	79—2	85
ከፋ	6	21	2,607	120	2,727	3,638	5,755	9,393	3	60	63
ሸዋ	11	64	9,443	745	10,388	14,802	20,056	35,107	13+1	209—1	222
ሲዳሞ	5	22	10,063	908	10,971	21,567	25,985	47,552	4	84	88
ትግራይ	3	3	99	54	153	198	,249	447	—	4	4
ወለጋ	5	35	6,751	868	7,619	11,275	16,641	27,946	15+4	95—4	110
ወሎ	9	22	4,227	228	4,455	5,479	8,699	14,178	4	82	86
ድ ም ር	79	315	76,360	6,416	82,979	29,334	174,727	300,338	161	1,144	1,275

ምንጭ፡ በግብርና ሚኒስቴር፡ የኅብረት ሥራ መምሪያ

የአምራቾች የሕብረት ሥራ ማኅበራት ዝርዝር

ክፍለ ሀገር	የዕድገት ደረጃ		ካፒታል	የመሬት መጠን በሄክታር		የእርሻ መሣሪያዎች		
	ማልባ	ወልባ		ጠ/መሬት	የለማ	በሬዎች በነጠላ	ፈረስ	ትራክተር
አርሲ	51	117	7,519,266	64,946	23,411	16,934	13	20
ባሌ	33	61	2,357,076	26,452	7,550	5,649	—	2
ኤርትራ	3	5	55,750	317	205	23	—	1
ጋሞጎፋ	14	4	546,840	7,824	2,332	894	—	4
ጎጃም	144	18	5,771,154	43,335	27,003	13,599	371	5
ጎንደር	54	2	777,433	9,670	5,076	2,382	177	7
ሐረርጌ	36	75	4,567,585	8,115	5,872	3,048	5	3
ኢሉባቦር	79	6	703,084	14,279	4,841	2,527	7	—
ከፋ	61	2	811,990	7,012	3,166	1,547	19	—
ሸዋ	157	65	7,130,990	34,819	26,147	8,764	17	12
ሲዳሞ	87	1	2,184,626	35,774	22,327	1,232	28	4
ትግራይ	4	—	27,622	235	213	56	1	—
ወለጋ	87	23	2,222,002	30,194	14,168	5,467	—	2
ወሎ	60	26	761,624	6,130	5,067	3,273	23	6
ድ ም ር	870	405	35,437,042	289,102	147,378	65,395	661	66

ምንጭ ፡ በግብርና ሚኒስቴር የኅብረት ሥራ መምሪያ

Digitized by Google

ከሐምሌ 1 ቀን 1975 እስከ የካቲት 30 ቀን 1976
የአገልግሎት የህብረት ሥራ ማኅበራት ዝርዝር

ክፍለ ሀገር	የአገልግሎት ኅ/ሥ/ማኅ ብዛት	የተጠቃሚ ገበሬዎች ብዛት			የአባል ቀ/ ገ/ማህበራት	የማኅበሩ ካፒታል	የተመዘገቡ	ያልተመዘገቡ	ቋሚ ቅጥር ሠራተኛ	
		ወንድ	ሴት	ጠ/ድምር					የሂሣብ	ሌሎች
አርሲ	143	231,335	16,577	247,912	1,068	14,153,574	76	67	153	459
ባሌ	131	60,569	2,755	63,324	247	3,107,276	31	100	45	96
ኤርትራ	41	21,879	5,840	27,737	138	339,565	—	41	—	9
ጋሞ ጎፋ	98	108,837	1,412	110,249	408	3,534,971	4	94	29	129
ጎጃም	401	328,408	25,239	353,647	1,623	10,791,137	156	245	175	—
ጎንደር	242	144,232	12,565	156,797	634	3,221,350	38	204	163	160
ወሎ	270	405,788	32,096	441,884	993	5,835,138	57	213	127	483
ሐረር	261	283,065	11,846	294,911	1,104	13,166,412	69	192	217	178
ኢሉባቦር	194	140,520	2,376	142,896	896	4,908,981	51	143	30	277
ከፋ	283	320,351	5,363	325,714	1,370	14,664,406	61	222	157	565
ሸዋ	1,068	1,120,643	111,268	1,231,911	5,134	29,421,126	160	908	726	1,570
ሲዳሞ	235	512,064	28,047	540,111	1,135	22,068,789	148	87	131	1,178
ትግራይ	57	38,253	17,735	55,988	130	1,547,059	—	57	24	30
ወለጋ	391	314,706	12,363	327,069	1,965	93,717,820	116	275	203	462
ድምር	3,815	4,030,668	289,482	4,320,150	16,845	140,467,638	967	2,848	2,180	5,596

ምንጭ ፦ በግብርና ሚኒስቴር የህብረት ሥራ መምሪያ

Digitized by Google

የዕደ ጥበባት ባለሙያዎች አ. የኅ. ሥ. ማ.			ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው			ሕጋዊ ሰውነት የሌላቸው			ጠ ቅ ላ ላ		
ብዛት	የአባላት ቁጥር	ካፒታል	ብዛት	የአባላት ቁጥር	ካፒታል	ብዛት	የአባላት ቁጥር	ካፒታል	ብዛት	የአባላት ቁጥር	ካፒታል
66	3,524	9,035,025.89	64	5,153	2,634,239.79	702	35,773	23,167,251.32	832	44,450	34,836.517=

<u>ምንጭ ፦</u> በግብርና ሚኒስቴር የሕብረት ሥራ መምሪያ ።

Digitized by Google

አብዮታዊው መንግሥት አቅም በፈቀደ መጠን ለኅብረት ሥራ ማኅበራት ግንባታ የተቻለውን ርዳታና ድጋፍ እያበረከተ ነው ። አርሶ አደሩና የዕደጥበብ ባለሙያው በዘመናዊ የማምረቻ መሣሪያዎች እየተጠቀሙ ምርታማነታቸውን ከፍ ለማድረግ እንዲችሉ በባሌ ክፍለ ሀገር የአጋርፋ ማሠልጠኛ ማዕከል ተቋቁሞ ገበሬዎችን በማሠልጠን አስተማማኝ ውጤት እያሳየ ነው ። በአርሲ ክፍለ ሀገርም አርዳኢታ በተባለ ቦታ የኅብረት ሥራ ማኅበር ማሠልጠኛ ተቋም ሥራው ተጠናቆ በቅርቡ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል ። እንደዚሁም በናዝሬት ከተማ አካባቢ በመሠራት ላይ ያለው የትራክተር መገጣጠሚያ ፋብሪካ ሲጠናቀቅ አርሶ አደሩ በዘመናዊ መሣሪያ እየተጠቀመ ምርታማነቱን እጥፍ ድርብ እንዲያሳድግ ያስችለዋል ። በተጨማሪም ሰፊው ሕዝብ አብዮቱ ባስገኘለት ድል ተጠቃሚ እንዲሆንና በግንባታውም ቀጥታ ተሳታፊ እንዲሆን ከ1971 (እ.ኢ.አ.) ጀምሮ የባሕል አብዮት ዘመቻ በመካሄድ ላይ በመሆኑ እስካሁን ድረስ ከሕዝቡ 62.4 % በላይ የሚሆን ከመሐይምነት ተላቋል።ዘመቻው ሲጀምር ግን ከመሃይምነት ነፃ የነበረው ከሕዝቡ 7% ብቻ እንደ ነበር የሚታወስ ነው ። በአጠቃላይ የኅብረት ሥራ ማኅበር የሶሻሊስት ሥርዓት ዓይነተኛ ገፅታ በመሆኑ በአብዮታዊት ኢትዮጵያም እየሰፋና እየዳበረ የሚሄድ ነው ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. Karl Marx & Fredric Engels, *Collected Works* (Moscow: Progress Publishers), p. 501.
2. Karl Marx, Capital Vol. I, pp. 686-693.
3. G.M. Trevelyan, *British History in the 19th Century & After* (1782-1919) (London: Longman, Green & Co., 1922), pp. 278-279.
   — G.D.H. Cole, *A Century of Co-operation*. (London: George Allen & Urwin Ltd., 1944), pp. 13-17.
4. G.D.H. Cole, p. 90.
5. Robert Oakeshott, *The Case for Workers' Co-ops*. (London: Routledge & Kegan Paul, 1978), pp. 36, 52-53.
6. *Ibid.*, pp. 114-120.
7. *Ibid.*, pp. 55-56.
8. *Ibid.*, pp. 59-65.
9. *Ibid.*, pp. 68.
10. *Ibid.*, pp. 65, 128, 142.
11. G.D.H. Cole, pp. 14-16.
12. *Great Soviet Encyclopaedia*. Volume 13, MacMillan Inc., (New York: 1977), p. 122.
13. *Ibid.*, Vol. 15, p. 54.
14. G.D.H. Cole, p. 89.
15. Karl Marx, *Capital*. Vol. 1, pp. 305-317.
16. MEGA — Marx, Engels, Gesamtausgabe, Berlin, p. 234, as quoted by V. Vygodsky, *The Economic Substantiation of the Theory of Socialism* (Moscow: Progress Publishers, 1981), p. 107.
    D. Ryazanoff, *The Communist Manifesto of Marx & Engels* (New York: International Publishers, 1930), pp. 26 - 39.
17. *Ibid.*, p. 52.
18. Hal Draper, *Karl Marx's Theory of Revolution*. Vol. 2, (New York: Monthly Review, 1978), p. 348.
19. Marx & Engels, *Collected Works*. Vol. II (Moscow: Progress Publishers) pp. 580-581.
20. K. Marx & F. Engels, *Selected Works*. Vol. 2. (Moscow: Progress Publishers, 1969), pp. 81-82.
21. *Ibid.*, Vol. 3, pp. 470-471.
22. S.P. Trapeznikov, *Leninism & the Agrarian & Peasant Question*. Vol. 2, (Moscow: Progress Publishers, 1981), p. 14.
23. *Ibid.*, pp. 14-15.
24. *Ibid.*, pp. 24-25.
25. J. William, edt., *The Soviet Peasantry' An Outline History* (1917-1970), (Moscow: Progress Publishers, 1975), pp. 131-136.
26. V.I. Lenin, *Collected Works*. Vol. 28, (Moscow: Progress Publishers, 1965), p. 177.
27. *Ibid.*, Vol. 33, pp. 467-475.
28. J. William, pp. 49.
29. *Great Soviet Encyclopaedia*. Vol. 13. p. 127.
30. *Ibid.*, p. 46.
31. E.H. Carr & R.W. Davies, *Foundation of a Planned Economy*. Vol. 1, Penguin Books, 1969, p. 121.
32. T. Yakovlev, S. Geguzin, *What the October Revolution Gave the Peasants* (Moscow: Foreign Languages Publishing House, 1957), p. 33.

Digitized by Google

የኢትዮጵያና የምዕራቡ ዓለም ግንኙነት

— አንዳንድ ነጥቦች (እስከ 1950ዎቹ)

ጠንክር ተረዳ

የሰው ልጅ ከእንስሳቱ ኑሮ በማይለይ ደረጃ የተፈጥሮ ተገዥ ሆኖ ከቆየበት ዓለም ወጥቶ የተፈጥሮን ተጽእኖ በመቋቋም ለሕልውናው መቀጠል አመቺ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የበቃው ከመሰሉ ጋር (ተፈጥሮ አስገድዶት) የመሠረተውን ትብብር ተመርኩዞ ነው ። ይህ ማኅበራዊ ኑሮ ለሰው ልጅ ዘላቂ ሕይወት መረጋገጥ ዋና ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ማኅበራዊው ኑሮም ያደገው በሰው ልጅ ብቻ ነው ። ስለዚህም የአንዱ ዕድገት ከሌላው ዕድገት ጋር የተቆራኘ ብቻ ሳይሆን አንዱ ለሌላው ምንነት መለኪያም ነው ። ማኅበራዊ ኑሮ በሰው ልጆች መካከል ብቻ ያለ ግንኙነት ሲሆን የሰው ማንነት መግለጫ ከሆኑት መካከል አንዱ በማኅበር መኖሩ ነው ። በሌላ አነጋገር ማኅበራዊ ኑሮ ካለ ሰው ፥ ሰው ደግሞ ከማኅበራዊ ኑሮ ውጭ የማይታሰብ ነው ።

የጥንቱ ማኅበራዊ ኑሮ የሰው ልጅ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮውን ለመግፋት የሚያችል በጎሣ ክልል የተገታና በተወሰኑ አካቢዎች የተወሰነ ነበር ። ይሁን እንጂ በተፈጥሮ ላይ የተቀዳጀውን የበላይነኑ እያሳገደ በመጣ ቁጥር ማኅበራዊ ግንኙነቱንም እያሰፋ መጥቷል ። ዛሬ ደግሞ ስለማኅበራዊ ኑሮ ስናወሳ በጥንቱ ዘመን እንደነበረው በአንድ አካባቢ ያሉትን ሰዎች ግንኙነት ብቻ ሳይሆን ከዘመን ዘመን እየሰፋ መጥቶ በጠቅላላው የዓለም ሕዝቦች መካከል የተመሠረተውን ግንኙነት ጭምር ይመለከታል ። ያለ ዕድገት ሕልውናን ለዘለቄታው ማረጋገጥ አይቻልምና ዕድገት ራሱ የሕልውና ጥያቄ ከመሆን አልወጣም። በመሆኑም ሕልውና ከዕድገት ጋር የሚተሳሰረውን ያህል ማኅበራዊ ኑሮም ከዕድገት ጋር የተቆራኘ ነው ። ሰዎች ማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ መግባታቸው ነባራዊው ሁኔታ ያቀረበላቸውን ግዴታ ማሟላታቸውን እንጂ ፈቃዳቸው ሆኖ አይደለም የሚባለውም ለዚህ ነው ።

Digitized by Google

በተለያዩ አካባቢዎች ለሚኖሩ ሕዝቦች መገናኘት ምክንያድ የሚሆኑ የተለያዩ ጉዳዮች ሊሆኑ ይችላሉ ። ግን ከጥንት ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ላሉት ግንኙነቶች ዋንኛውና መሠረታዊው ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ነው ። ኢትዮጵያውያን ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ጥንት የነበራቸውም ግንኙነት ሆነ የዛሬው ከዚህ ውጭ አይደለም ። ቀይ ባሕርና የሕንድ ውቅያኖስ በዓለም ንግድ ከጥንት ጀምሮ ከፍተኛ ሚና የነበራቸው ስለመሆኑ ፣ የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ከመጀመሪያዎቹ የዓለም ሥልጣኔዎች ጋር ግንኙነት እንደነበረው ቀይ ባሕር የሩቅ ምሥራቅንና የሜዲቴራኒያን አካባቢን ንግድ አገኝና መስመር እንደነበረ ፣ ከ3400—2900 ዓመተ ዓለም ጀምሮ ግብጽ ከአፍሪካ ቀንድ ጋር ግንኙነት የነበራት ስለመሆኑ [1] የተለያዩ የታሪክ መረጃዎች ያረጋግጣሉ ። እነዚህም የሚያሳዩን የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ረጅም ዕድሜ ያለው መሆኑን ብቻ ሳይሆን የግንኙነቱም ዋንኛ ገጽታ የኢኮኖሚ ግንኙነት መሆኑንም ጭምር ነው ።

የአፍሪካ ቀንድ በግብጽ ፣ በሜዲቴሪኒያን፣ በግሪክና በሮማ በነበሩ ሕዝቦች ዘንድ ተፈላጊ የነበሩ የአንዳንድ ምርቶች ምንጭ ከመሆኑም በላይ የሩቅ ምሥራቅ ምርቶችንም ወደዚሁ አካባቢዎች በማሻገር ያገለግል ነበር ። በተጨማሪም ከኢትዮጵያ የሚነሳው የአባይ ወንዝ ለግብጽ እርሻ የሚሰጠው ጥቅም ከፍተኛ ነው ። እነዚህን ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች በመረዳት የጥንቶቹ የግብጽ ፣ የግሪክና የሮማ ነገሥታት አባይ ወንዝ የሚፈልቅበትን ቦታ ለማግኘትና አካባቢውንም ለመቆጣጠር ባይቻል ግንኙነቱ እንዳይቋረጥ የሚያስችል ወዳጅነት ለመመሥረት ነጋዴዎችን፣ አጥኚና አሳሽ ቡድኖችን ወዘተ - - - መላካቸው [2] ኢትዮጵያ ከጥንቱ ዓለም ጋር የነበራትን ግንኙነት ይመሰክራል ።

ይህ ግንኙነት ግን እንደአጀማመሩ እያደገ አልመጣም ፤ የሚቀዘቅዝበት ጊዜም ነበር ። ከምዕራቡ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ከምሥራቅም ጋር የነበራት ግንኙነት በ7ኛው ክፍለ ዘመን ቀዝቅዞ እናያለን ፤ የዚህም ምክንያቱ የእስልምና ሃይማኖት መነሳት ነበር ። የሃይማኖቱ መሥራች በነበረው በነቢዩ መሐመድ ዘመን በኢትዮጵያውያንና በእስልምና ተከታዮች መካከል ነበረው የሰመረ ግንኙነድ በዚሁ መልክ አልቀጠለም ። የእስልምና ማደግና መስፋፋት የቀይ ባሕርን አካባቢ በመቆጣጠር የአክሱም መንግሥት ከውጭ ዓለም ጋር ነበረው ግንኙነት እንዲቀዘቅዝና ንግዱም እንዲዳከም ምክንያት ሆነ ። [3]

የእስልምና መስፋፋት የምዕራቡንና የምሥራቁን ዓለም ግንኙነት በማቋረጡ በአክሱማውያን ላይ ብቻ ሳይሆን በምዕራቡም ዓለም ከፍተኛ ተጽእኖ አሳደረ ፤ ምዕራባውያን ከሩቅ ምሥራቅና ከቀይ ባሕር አካባቢ መሥርተውት የነበረው ግንኙነት መቋረጥ ኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸውን አስቀረ ። ይህ በዚህ እንዳለ በ12ኛው ክፍለ ዘመን ፕሬስተር ጆን የሚባል የክርስቲያን ንጉሥ (የኢትዮጵያ ንጉሥ መሆን አለመሆኑ መጀመሪያ አውሮፓውያን አያውቁም) በምሥራቅ መኖሩ በአውሮፓ ሲሰማ በሜዲትራኒያንና በቀይ ባሕር አካባቢ የኦቶማን ቱርኮችን ኃይል ለመስበር ከፍተኛ ድጋፍ እንደሚሆን ተገመተ ። ከምሥራቁ ንጉሥ ጋር መተባበር ለአውሮፓውያን ከምሥራቅ የሚፈልጉትን ግንኙነት ለመቀጠል የሚያስችል ሌላ አማራጭ ነበር ። ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ከክርስትና እምነት ተከታዮች ጋር ግንኙነት የሚፈልጉበት ወቅት ነበር ። [4] ይህ የጋራ ፍላጐት በሁለቱም በኩል መፈላለግን አስከተለ ። የኢኮኖሚው ግንኙነት ወደ ፖለቲካ ተሸጋገረ ፤ በ14ኛውና በ15ኛው ምዕተ ዓመታት ላይ የሁለቱ ግንኙነት እያደገ መጣ ። በዚህ ወቅት የአውሮፓውያን ኢኮኖሚያዊ ፍላጐት በኢትዮጵያ ላይ እንዲያተኩሩ አስገደዳቸው ። [5] ፓርቱጋል ከኢ

Digitized by Google

ትዮጵያ ጋር ግንኙነት የምትጀምረውና በቀይ ባሕር አካባቢ ከቱርኮች ጋር ትራኔ የምትገባው በዚህ ጊዜ ነው ። ግራኝ መሐመድ በሰሜን ኢትዮጵያ ለነበሩት የክርስቲያን ነገሥታት አልገብርም በማለት ጦርነት የከፈተው ከቱርኮች ባገኘው ዘመናዊ ጦር መሣሪያ አማካይነት ሲሆን ለመሸነፉም ለክርስቲያኑ ነገሥታት ፖርቱጋል የሰጠችው ድጋፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ። በሁለቱ ኃይሎች መካከል የታየው ትብብር በሃይማኖት አንድነት ስም ይደረግ እንጂ ትብብሩ ፖለቲካዊ አንድነትን ማጠናከሪያ መንገድ እንደነበረም አይዘነጋም ።

በጸረ—ግራኝ ጦርነት ሰበብ ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ፖርቱጋሎች የራሳቸውን ሃይማኖት ማስፋፋት ጀመሩ ። ስፓኒሾችም የፖርቱጋሎችን ፈለግ በመከተል የካቶሊክ እምነታቸውን የሚያስፋፉበት ት/ቤት ከፍተው ሰበካቸውን ተያያዙት ፤ የስፔን ጀስዊቶች በጊዜው የነበረውን ንጉሥ ዘድንግል (አጥናፍ ሰገድ) የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ ማድረግ ቻሉ ። ዘድንግል የተቀበለውን ሃይማኖት ለማስፋፋት የሚረዱት ተጨማሪ ቀሳውስትና ወታደር ለማግኘት ከስፔን ንጉሥ ጋር መጻጻፉ እንደተሰማ የተነሳው ሕዝባዊ ተቃውሞ ጦር አማዝዞ ንጉሡም በጦርነቱ ሊሞት በቃ ። ዙፋኑን የወረሰው ንጉሥ ሱስንዮስም የተከተለ አመራር ከዘድንግል ያልተለየ ስለነበረ «የውጪውን» ሃይማኖት በመቃወም የተቀሰቀሰው ጦርነት ከፍተኛ የሕዝብ እልቂትን በማስከተሉ በ1632 ጀስዊቶችን ከኢትዮጵያ በማባረር ሕዝቡ ወደቀድሞ ሃይማኖቱ እንዲመለስ አዋጅ አስነገረ ፤ ዙፋኑንም ለልጁ (ፋሲለደስ) አስረከበ ። ንጉሥ ፋሲለደስም አውሮፓውያኑ ዳግመኛ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ ለማድረግ ከቱርክ ገዥዎች ጋር ተደራደረ ።[6] ፖርቱጋሎችም በቀይ ባሕር ላይ በማተኮር በምሥራ አፍሪካና በእስያ መካከል የባርነት ንግድ ወደማስፋፋት ተሸጋገሩ ።

የባሕር በሮቿን በመዝጋትና በእስልምና ሃይማኖት ማስፋፋት ሰበብ የግዛት ጥማቸውን ለማርካት በኢትዮጵያ ላይ ተደጋጋሚ ወረራ በመፈጸም በተለይም ግራኝን በማስታጠቅ የክርስቲያን ነገሥታትን ሕልውና አደጋ ላይ ጥለው የነበሩና በኢትዮጵያና በጀስዊቶቹ መካከል በመጀመሪያ ለታየው የሰመረ ግንኙነት ምክንያት ከነበሩት ቱርኮች ጋር እንደገና መደራደር ደረጃ ላይ ለመድረስ ምክንያት የሆነው የጀስዊቶቹ ፖሊሲ እንደመሆኑ ፣ ፖሊሲያቸው ምን ያህል ፀረ—ኢትዮጵያ እንደነበረ ያስገነዝባል ። ኢትዮጵያውያን ከዚህ ጊዜ በኋላ የሚመጡትን አውሮፓውያን በጥርጣሬ ዓይን ሊመለከቷቸው የቻሉት ጀስዊቶቹ ጥለውት ከሔዱት ቅርስ ጋር የተያያዘ ነው ።

በሁለቱ የክርስትና እምነት ተከታዮች መካከል ግጭት መነሳት ፣ የኢትዮጵያ የባሕር በሮች በቱርኮች ቁጥጥር ሥር መዋል በጎንደር ዋና ከተማ ተመስርቶ የነበረው የመንግሥት ኃይል ተዳክሞ የ«ዘመነ መሣፍንት» መንሰራራት ፣ በ19ኛው ክፍለ ዘመን በሚከሰተው ታሪካዊ ሁኔታ መሠረት እንደገና እስከሚቀጥል ድረስ ኢትዮጵያ ከምዕራብ አገሮች ጋር መሥርታው የነበረው ግንኙነት እንዲቋረጥ ምክንያት ሆኑ ። በዚህ ወቅትም ቢሆን ኢትዮጵያ ከአሌክሳንደሪያ ፣ ከኢየሩሳሌምና ከመካ መዲና ጋር የነበራት ግንኙነትና አልፎ አልፎም የውጭ ዜጎች ጉብኝት በመኖሩ እነዚህም ግንኙነቶች በአብዛኛው የቀይ ባሕር ወደቦችን መጠቀም ስለሚያስገድዱ በ17ኛውና በ18ኛው ምዕተ ዓመታት የኢትዮጵያ ከውጭ ዓለም መገለልና ቱርኮች በኢትዮጵያ የባሕር ብሮች ላይ የነበራቸው ቁጥጥር ፍጹም ነበር ለማለት አያስደፍርም ።[7]

ከ19ኛው እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት

በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በኢትዮጵያና በአውሮፓ መካከል የተጀ

Digitized by Google

መረው ግንኙነት በኢትዮጵያ አነሳሽነት ሳይሆን በአውሮፓውያን የመነጨ ግፊቶች ውጤት ነው ። [8] በ1798 የናፖሊዮን ግብጽን መውረር ፈረንሣይ ፣ ታላቋ ብሪታንያና ሩሲያ የቅርብና የመካከለኛው ምሥራቅ እስትራቴጂካዊ ጠቃሚነት እንዲረዱ አስቻላቸው ። ወረራው የቀይ ባሕር አካባቢን በቁጥጥር ሥር ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አጉልቶ የሚያሳይ ነበር ። ሚስዮናያን ፣ ተማራማሪዎች ፣ ቆንስሎች ፣ የንግድና የፖለቲካ አስፋፊዎች መንግሥታቸውን በመወከል የቅኝ ግዛትን ጥርጊያ ጐዳና ለማዘጋጀት አካባቢውን በማጥለቅለቅ የጦር አውድማ አስመሰሉት ። ኢትዮጵያም ከዚህ እንቅስቃሴ ነፃ አልነበረችም ። በ1841 ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት የፈረንሣይ ተጓዦችና ወደ ሸዋ ግዛት ብቻ የገባው የእንግሊዙ ቡድን እያንዳንዳቸው ከ30 አባላት በላይ እንደነበራቸው [9] መጥቀሱ የአውሮፓውያኑ ትኩረት ከፍተኛ እንደነበር የሚያሳይ ነው ። በሃይማኖት ፣ በንግድ ፣ በጥናትና ምርምር ስም ወደ ኢትዮጵያ የገቡት አውሮፓውያን የየአካባቢውን ገዥ መስፍን በእጅ ለማድረግ በመጠጋት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ጣልቃ መግባቱን ተያያዙት ። የኢትዮጵያ መሪዎች አውሮፓውያኑ ከኢትዮጵያ ጥቅም ፈላጊ መሆናቸውን ግንኙነቱ በተጀመረ አካባቢ የተገነዘቡ አይመስልም ። በ1820 የሱዳን በግብጽ መወረር ኢትዮጵያን ስጋት ላይ የሚጥል እርምጃ መሆኑንና ይህም በእንግሊዝ የተቀናበረ መሆኑን ለኢትዮጵያውያን የሚከሰተው እየቆየ ነበር ። [10]

የአውሮፓ ወኪሎች ከመሣፍንቱ ጋር በየፊናቸው ጠንካራ ግንኙነት ለመመሥረት የሚያደርጉትን ግፊት በጸረ ቱርክና እስልምና አቋም እንዲመሠረትና የአውሮፓም መንግሥታት የኢትዮጵያ ተባባሪዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ በማስመልከት የሚያደርጉት ጥረት በኢትዮጵያውያን በኩል እጅግም ተቀባይነት አላገኘም ። የዚህም ምክንያት የመሣፍንቱ ዋና ትኩረት በነበረው የሥልጣን ሽኩቻ ላይ እንጂ በውጪ ግንኙነት ላይ አለመሆኑንና ከጀስዊቶች ጋር የተደረገው የሃይማኖት ግጭት ትርሱ ሙሉ በሙሉ ባለመፋቁ መሣፍንቱ ስለ አውሮፓውያን የነበራቸው አመለካከት በጥርጣሬ ላይ መመሥረቱ ነው ። ኢትዮጵያውያን ስለ ግንኙነቱ የነበራቸውን ቀዝቃዛ ስሜት ለመቀስቀስ የአውሮፓ ወኪሎች በግንኙነቱ መጀመሪያ ላይ የኢትዮጵያን መሣፍንት በተለያዩ ጥቅሞች ለመያዝ ሲሞክሩ ይታያሉ ። በጦር መሣሪያ ፣ በእደ ጥበብ ባለሙያዎችና በባሕር በር በኩል መሣፍንቱ የነበሩባቸውን ችግርችና የአውሮፓ መንግሥታት ሊያቃልሉ እንደሚችሉ መሣፍንቱን በማባበል የተለያዩ ስምምነቶችን እንዲደራደሩ መገፋፋት ጀመሩ ።

በዚህም ውትወታ መሠረት በ1827 ደጃዝማች ሰባጋድስ ወልዱ ለእንግሊዙ ንጉሥ ጆርጅ አራተኛ በጻፈው የወዳጅነት ደብዳቤ በመሠራት ላይ የነበሩትን አብያተ ክርስቲያናት ለመጨረስ የሚረዱት ቁሳቁሶችና ባለሙያዎች እንዲላክለት ይጠይቃል ። ደብዳቤውን እንዲያደርስ የተወከለው ሚስዮናዊ ኮፊን የጦር መሣሪያ ሽያጭንና የምጽዋን ወደብ እንግሊዞች ከቱርክ በመንጠቅ እንዲያስረክቡት ወይም ራሳቸው እንዲያስተዳድሩት ደጃዝማች የጠየቀ መሆኑን የሚገልጹ በአማርኛው ጽሑፍ የሌሉ ሐሳቦች በእንግሊዝኛው አስፍሮ ይገኛል። [11] በኢትዮጵያ በኩል የነበሩት ጥያቄዎች በእስላም ግዛቶች አካባቢ የሚኖሩትንና ወደ እነዚሁ ሥፍራዎች የሚጓዙ ክርስቲያኖችን ደህንነት ለመጠበቅና ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት የሚያስችሉ ትብብሮችን የሚጠይቁ ሆነው ሳለ ፣ [12] የጦር መሣሪያንና የግዛቶችን አስተዳደር በሚመለከት የተነሱት ሐሳቦች የሚስዮናውያኑ እንጂ የኢትዮጵያውያን ፍላጐት አለመሆናቸው የአውሮፓውያን ቃለ አባ

Digitized by Google

ይንትገና የግንኙነቱ ገፊት ከየት እንደመ
ነዉ ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ የሚፈል
ጉትንም ጥቅም ያጋልጣል ። በእንግሊዝ
መንግሥት በኩል ተፈላጊ የነበሩትን የትኛ
ገዛት መሬትና የጦር መግሪያ ሽያጭ ለግ
ኋላት ሚስዮናዊው ያደረገው ጥረት የሚ
ያሳየው የእንግሊዝ መንግሥት ወኪልነ
ቱን ነው ። ሚስዮናውያን በኢትዮጵያ
በኩል ያልተጠየቁትን ኢትዮጵያውያንን
መስለው መጠየቃቸው በወቅቱ በኢትዮ
ጵያ በኩል የነበሩትን ችግሮች በመገምገ
ምና መፍትሔ ብለው ያቀረቧቸውንም
ሐሳቦች ኢትዮጵያውያን እንደሚቀበሏ
ቸው በመገመት በሁለቱም መንግሥታት
በኩል ተወዳጅነትን ለማትረፍ የቀየሱት
ዘዴ ነው ። ሚስዮናውያን እንደገመቱት
ኢትዮጵያውያን ገዛታቸውን ከአንዱ ወደ
ሌላው ጠላት የሚያሳልፉበት ምክንያት
አልነበራቸውም ። ይህ ዓይነት የማጭበር
ዘበር ዘዴያቸው ግንኙነቱን ማጠናከር በሚ
ፈልጉ መሣፍንት ዘንድ እንኳ አውሮፓው
ያንን በመጠራጠርና የመጥላት አመለካከት
እንዲኖር በማስገደዱ በሁለቱ መካከል
ከመነሻው ጤናማ ግንኙነት እንዳይመ
ሠረት እንቅፋት ሆኗል ። በመጨረሻም
የተከፈቱ ጦርነቶች የማይቀሩ መሆናቸ
ውን የሚጠቁሙ አዝማሚያዎች በመሆ
ናቸው ኢትዮጵያውያን ጥርጣሬያቸውን
በማሳደግ አውሮፓውያኑን በይበልጥ እን
ዲገመግሙ የረዳቸው ሁኔታ መሆኑ ነው።
በ1850ደጃዝማች ውቤ ከእንግሊዝ መንግ
ሥት ሊያገኝ የሚችለውን ትብብር በአካ
ቢው ከነበሩት እንግሊዛውያን በተነገ
ረው መሠረት አለመፈጸሙን ከእንግሊዝ
ንግሥት ቱርኮችን በሚመለከት የተጻፈ
ለትን መልስ አስመልክቶ ፥

ንግሥት ቪክቶሪያ የጻፈችው ደብዳቤ
አክብሮት ያለው ቢሆንም የመልእክቱ
ቁም ነገር በአጭሩ አንረዳህም የሚል ነው።
እኛንና ሃይማኖታችንን እንወዳለን ትላላ
ችሁ ፤ እስካሁን ግን አላየሁትም ፤ ከቱር
ኮች ይበልጥ ኃያል ነን ትላላችሁ፤ አታስ
መለክሩትም ። የአገሬን ነጋደዎች ደኅን
ነትና . . . ምጽዋን በሚመለከት ቃልየተ
ገባልኝን ዕርዳታ ለማገኘት ከብዙዎቹ
የአውሮፓ አገሮች ጋር ግንኙነት ከጀመ
ርኩ ብዙ ዓመታት አልፈዋል ። ምጽዋ
በክርስቲያናች እጅ እንድትሆን እፈልጋ
ለሁ፤ ለጊዜው መድፍንና የጦር መርከብን
መከላከል አልችልምና እናንተ እንግሊ
ዞች ከሌሎቹ መሻል አለመሻላችሁን ለ
ማወቅ ጊዜ ይፈጃል እንጂ አይቀርም [13]

በማለት መናገሩ ኢትዮጵያውያን በመጀ
መሪያ የተነሱበትን ጥርጣሬ ማረጋገጥ ደረጃ
ላይ መድረሳቸውን ያሳያል ። ስለ ኢትዮጵ
ያውያን ግንዛቤ ከፍተኛነትና ስለ አውሮ
ፓውያን ቃለ አባይነት ሚስዮናዊው መን
ዚንጀር የሚከተለውን ጽፏል ።

ወደ ባዕድ ገዛቶች ስንደርስ ለመጀመ
ሪያ ጊዜ የወዳጅነት አቀባበል ሊደረገ
ልን ይችላል ፤ ከሶስት ቀናት መስተንግዶ
በኋላ እንግዳውና አስተናጋጁ እርስበርስ
መጠናናት ይጀምራሉ ፤ ማንነታችንን
ካወቁ በኋላ ተመልሰን እንድንጐበኛቸው
የሚፈልጉ ሰዎች ቁጥር በጣም አነስተኛ
እንደሚሆን ማንም እርግጠኛ መሆን
ይችላል ። [14]

የአውሮፓውያንን ማንነት በሚመለከት
ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ግንዛቤ ማግኘት
ቢችሉም በመሣፍንቱ መካከል የነበረው
የስልጣን ሽሚያ የውጭ ግንኙነቱን በአ
ንድ አመራር ሥር ማድረግ የሚያስችል
አልነበረም ። የማዕከላዊ አመራር አለመ
ኖር አንዱ መስፍን የአሰረውን ሌላው
እንዲፈታው ያመች ነበር ። ከፍ ብሎ ከተ
ጠቀሱት ሐሳቦች እንደምናየው በምጽዋ
ጉዳይ የሰባጋድስና የውቤ አስተሳሰብ
መለያየት ኢትዮጵያ ውስጥ ከነበረው የአ
መራር ችግር ጋር ይያያዛል ። ግንኙነቱ በተ
ጀመረ ሃያ አምስት ዓመታት ውስጥ ከታ
ዩት በአውሮፓውያንና በቱርኮች ፥ በእን
ግሊዝና በፈረንሣይ እንዲሁም በመሳፍ
ንቱ መካከል ከነበሩት ውድድሮችና ትግል

Digitized by Google

እንዱም በድል አድራጊነት ሊወጣ አልቻለም ። በዓፄ ቴዎድሮስ አመራር የኢትዮጵያ የውስጥ አስተዳደር መለወጡ ተደጋ በነበረው ዝብርቅርቁ በወጣው የውጪ ግንኙነት ላይም ለውጥ አስከተለ ።

የውጭ ግንኙነቱን በሚመለከት ዓፄ ቴዎድሮስ ከመሳፍንቱ በተሻለ ሁኔታ ላይ እንዲሆን ያስቻሏቸው ሁለት ቁም ነገሮች በመኖራቸው ነው ።[15]

እነሱም ፦

1. ኢትዮጵያውያን ስለ አውሮፓና አውሮፓውያን የነበራቸው ግንዛቤ ከፍ ማለቱና ፣
2. ዓፄ ቴዎድሮስ ከቀደሙት መሳፍንት ሁሉ በተሻለ ሁኔታ ጠቅላላ ኢትዮጵያን ወክለው መናገር መቻላቸው ነው ።

የኢትዮጵያ የወቅቱ የውጪ ግንኙነት በሚመለከት ዓፄ ቴዎድሮስ ከዘመነ መሳፍንት የተረከቧቸው ዋናዎቹ ጉዳዮች በሚከተሉት ነጥቦች የሚጠቃለሉ ናቸው ።[16]

—የአውሮፓውያንን ፍላጎት በሚመለከት መወሰድ የነበረበት እርምጃ ፣ በእንግሊዝና በፈረንሣይ መካከል የነበረው ውድድር የሚያስከትለው ውጤት ፣

—ለካቶሊክ ፣ ለፕሮቴስታንት ወይስ ሁለቱም ሃይማኖት አስፋፊዎች ተከታዮቻቸውን እንዲያበዙ መፍቀድ የሚኖረው ጥቅምና ጉዳቱ ፣ [illegible] ጋር ከሁለቱም መንግሥታት ጋር የሠመረ ግንኙነት መፍጠር ይቻላል ወይስ አንዱን መምረጥ ያስፈልጋል የሚለው ጥያቄ ፣

—ወደፊት ከግብጽ ጋር በሚደረገው ጦርነት አውሮፓውያን የኢትዮጵያ ወዳጆች መሆን አለመሆናቸውን እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል ? የሚለው ጥያቄ ነበር ።

አውሮፓውያን ዓፄ ቴዎድሮስ ዘንድ የሚቀርቡት በዘመነ መሳፍንት የጀመሯቸውን እቅዶች እንዲፈጽሙላቸው በመጠየቅ ነበር ፤ ከእነዚህም አንዱ የአውሮፓ ቆንስሎች ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡበትን ሁኔታ ይመለከታል ። በዚህም መሠረት የቴዎድሮስ አማካሪ የነበረው እንግሊዛዊው ፕላውድን ቀደም ሲል በእንግሊዝ መንግሥት የተሰጠውን መመሪያ አስመልክቶ ለእንግሊዝ መንግሥት በጻፈው ደብዳቤ ምንም እንኳ ቴዎድሮስ የእንግሊዝን ቆንሲል ለመቀበል ፈቃደኛ ባይሆንም ፣ ጥሩ የእንግሊዝ ወዳጅ ሊሆን እንደሚችል ለዚሁም ጊዜ መስጠት እንደሚያስፈልግና ግብጽንና ምጽዋን የሚመለከቱ ሐሳቦች ጨምሮ ነበር ። የእንግሊዝ መንግሥት ለፕላውድን በጻፈው የመልስ ደብዳቤ ቴዎድሮስ ግብጽንና ምጽዋን መውረር እንደሌለበት ይገልጻል ። ግብጽንና ምጽዋን በሚመለከት ከዚህ በፊት በሌሎች ሃይማኖት አስፋፊዎች እንዳየነው ፕላውድን በራሱ አነሳሽነት የጠቀሰው እንጂ በኢትዮጵያ በኩል በጊዜው የተነሣ ጉዳይ ስላልነበረ ቴዎድሮስን አስቆጣ ። በዚህም ምክንያት አፄ ቴዎድሮስ ከእንግሊዝ ጋር ግንኙነት የፈለጉት ግብጽንና ቱርክን ከመፍራት አለመሆኑን ለማረጋገጥ ተገደዱ ።[17]

ዓፄ ቴዎድሮስ ከአውሮፓውያን ጋር ግንኙነት ለመመሥረት የፈለጉት በዐረ ግብጽ አደጋ አለመሆኑን ገና ከመጀመሪያው ለማሳየት ሞክረዋል ። ከግብጽ ጋር በሰላም ተደራድሮ መኖር ካልተቻለ በአገር ውስጥ የነበረውን ሁኔታ ካረጋጉ በኋላ በጦርነት ሊፈቱት እንደሚችሉ ይተማመኑ ነበርና ግንኙነቱን የፈለጉት ኢትዮጵያ ውስጥ ዘመናዊ አስተዳደር ለመመሥረት የተነሱበትን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የአውሮፓውያን ትብብር አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ በመገመት ነበር ። ፕላውድን ኢትዮጵያ ከግብጽ ጋር ጠብ እንዳትጭር ፣ ለኢትዮጵያ ግዛት መከበር ዋስትና እንግሊዝ መሆኗን መቀበልና ባለውለታነቷን ለማረጋገጥ ሌሎች ተርካካሪዎችን በማስ

Digitized by Google

ገፀድ የእንግሊዝን ጥቅም እንድታራምድ ይፈልጋል ። [18]

ከዚህም የምንረዳው ግንኙነቱ በዓፄ ቴዎድሮስና በፕላውደን አመለካከት በእኩልነት ላይ አለመመሥረቱን ነው ። ሁለቱም ግንኙነቱን ይፈልጉ እንጂ በመቅደላ እንዲፈታ የሆነው ቅራኔ የተጀመረው ገና በመነሻው እንደነበር ነው ። በዓፄ ቴዎድሮስና በእንግሊዝ መሐል ለተፈጠረው ቅራኔ መሠረትም ይህ በእኩልነት ላይ ያልተመሠረተ ግንኙነት መሆኑ ነው ። በመቅደላ ዘመቻ ዋዜማ ላይ ቴዎድሮስ «ጥቁርና ድሀ በመሆኔ ነወይ እንዲህ የሚቀለድብኝ» [19] ማለታቸው የአውሮፓውያንን ትምክህት መቃወማቸውን ያሳያል ።

እዚህ ላይ ወደ መቅደላ ባስገባችው ሠራዊት አማካይነት እንግሊዝ ኢትዮጵያን ለመያዝ የነበራትን የቆየ ፍላጐት ሰርዛ እንዴት ልትወጣ ቻለች ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል ። የትጥቅ ፣ የስንቅ ፣ የመሳፍንት ክሕደት ፣ - - - ወዘተ ችግሮች የነበሩበትን በ3,000—8,000 መሐል የነበረውን የቴዎድሮስ ሠራዊት ለመውረር እንግሊዝ ብዛቱ 42,000 የሚደርስ ሠራዊት ማዝመቷ [20] ፣ የዘመቻው መሪ ናፒር በዙላ ወደብ ከማረፉ አምስት ቀናት ቀደም ብሎ ለኢትዮጵያ ፖለቲካና ሃይማኖት መሪዎች እንዲሁም ለጠቅላላው ሕዝብ ባስተላለፈው አዋጅ እንግሊዝ የታሠሩባትን ዜጎቿን ለማስፈታት እንጂ ሀገሪቱን የመያዝ ዓላማ የሌላት መሆኑን ገለጸ ። [21] በተለያዩ አካባቢዎች የነበሩ የኢትዮጵያ መሳፍንት ከእንግሊዝ ጋር ባይተባበሩ ቢያንስ ከቴዎድሮስ ጋር እንዳይቆሙ ለማድረግ እንግሊዞች ያደረጉት ጥረት ኢትዮጵያን ለመያዝ ሳይፈልጉ ቀርተው ሳይሆን የሀገሪቱን ኃይል ከመፍራት የተነሳ መሆኑን ያሳያል ። ኢትዮጵያን በመናቅና መልስ በማዘግየት በደብዳቤ ልውውጥና በመሳሰለው በቴዎድሮስ ጊዜ ያሳዩትን ዓይነት ትምክህተኝነት ከቴዎድሮስ በኋላ በነገሡት ነገሥታት ላይ አለመድገማቸው በዓፄ ቴዎድሮስ ምክንያት የኢትዮጵያን ሁኔታ ለመረዳት መቻላቸውንና ትምህርት መውሰዳቸውን ያረጋግጣል ።

ዓፄ ቴዎድሮስ ከምዕራቡ ዓለም ጋር ለመመሥረት ያቀዱት ግንኙነት ከእርሳቸው በፊት ከነበረው ሁኔታ በተቃራኒ በራሳቸው አነሳሽነት መሆኑና ለአውሮፓውያን ተልዕኮ አለመበገራቸው አውሮፓውያን ስለ ኢትዮጵያ የነበራቸውን አመለካከት እንዲያጤኑ በማስገደድ ብቻ ሳይወሰን ከዚህ በኋላ ለመጡት የኢትዮጵያ መሪዎች ትምህርት በመሆን በኢትዮጵያ ለጠንካራ የውጭ ግንኙነት መጀመር መሠረት የጣለ ፖሊሲ ነው ።

የፈረንሣይና የእንግሊዝ ሚስዮናውያን ከመሳፍንቱ ጋር የተደራደርነው ስምምነት (ከመሳፍንቱም ጋር ቢሆን ስምምነት ደረጃ አልደረሱም) ሥራ ላይ ይዋልልን ባሉት መሠረት ቢፈጸምላቸው ኖሮ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በፈረንሣይ፣ ደቡብና ሰሜን ኢትዮጵያ ደግሞ በእንግሊዝ ተጽእኖ ሥር ሆኖ ነበር ማለት ነው። በዚህም መሠረት በኋላ በጣሊያን ተግባራዊ የሆነው «የኤርትራ» ግዛት ከቴዎድሮስ መነሳት በፊት በእንግሊዝ የተጠነሰሰ እንደነበረ ለመገንዘብ ይቻላል ። [22] ይህም የሚያሳየን በ1906 ጣሊያን ፣ ፈረንሣይና እንግሊዝ ኢትዮጵያን ለመከፋፈል ባደረጉት ስምምነት እንደታየው ኢትዮጵያን ለመቃረጥ የነበራቸው ፍላጐት የቆየ መሆኑንና በሃይማኖት ሰባኪነት ወደ ሀገራችን የጐረፉት ሚስዮናውያን ዋንኛ ተልዕኮ የቅኝ ግዛትን ፖሊሲ ለማስፈጸም እንደነበር ነው ። በካቶሊኮችና በፕሮቴስታንቶች መካከል የነበረው ውድድር የሃይማኖቶቹን ቅራኔ ሳይሆን የሚያሳየው የፈረንሣይንና የእንግሊዝን ቅኝ ግዛት ፉክክር ነበር ። ሃይማኖት የገዥ መደቦችን ፍላጐት ለማራመድ በመሣሪያነት ሲያገለግል የምናየው በተለያዩ ወቅቶችና በታዎች ለመሆኑ አያሌ ምሳሌ

Digitized by Google

ዎችን መጥቀስ ይቻላል ። በ19ኛው ክፍለ
ዘመን ሁለተኛው አጋማሽ ላይ ግብጽ በኢ
ትዮጵያ ላይ ያደረገቻቸው ተደጋጋሚ
ወረራ በሃይማኖት ሽፋን መሆኑን የሚያ
ረጋግጥ ሲሆን ፣ የእንግሊዝ መሣሪያ በመ
ሆናቸው ደግሞ አውሮፓውያን የቅኝ ግዛት
ጥማቸውን ለማርካት የተጠቀሙባቸው
ስልቶች የተለያዩ መሆናቸውን ነው ። በአ
ንድ በኩል በኢትዮጵያ ላይ ለማድረግ እን
ደሞከሩት በሃይማኖት አንድነት ስም ለመ
ቀራረብ የሚፈልጉ ሲመስሉ በሌላ በኩል
በተቃራኒነት እናያቸዋለን የሚሏቸውን
ክርስትናንና እስልምናን ለአንድ ዓላማ
ሲጠቀሙባቸው ይታያሉ ።

ፈረንሣይና እንግሊዝ እስልምና ተከታይ
ከሆነችው ቱርክ ጋር ተባብረው ኦርቶዶክስ
ሩሲያን መውረራቸው (በክሬሚያን ጦር
ነት) ቴዎድሮስ ሲሰሙ ከሩስያ ጋር ወዳጅ
ነት ለመፍጠር ጥረት አድርገዋል ። [23] ከፈ
ረንሣይና ከእንግሊዝ ጋር መተባበር ማለት
በቱርክ ላይ መተባበር መሆኑን የአውሮፓ
ወኪሎች ኢትዮጵያውያንን ለማሳመን ያደ
ረጉትን ጥረት ውሸትነት በማረጋገጣቸው
ነው ከሩስያ ትብብር የፈለጉት ። ይህም ቴ
ዎድሮስ በመነሻቸው አካባቢ ግብጽን በሚ
መለከት የነበረውን ጥያቄ የአውሮፓውያ
ንን አቋም ግልጽ በማድረጉ የሁለቱን ኃይ
ሎች ተጽዕኖ መቋቋሚያ አማራጭ መፈለ
ጋቸውን ያሳያል ። ቴዎድሮስ ጠንካራ ማዕ
ከላዊ መንግሥት ለመመሥረት የተነሱበት
ዓላማ አስተዋጽኦው ለውጭ ግንኙነት መ
ጠናከር ብቻ ሳይሆን ለውስጥም አስተዳደር
ጭምር ነበር ። በቴዎድሮስ መሠረቱ የተጣ
ለው የማዕከላዊ አስተዳደር መጠናከር ቅኝ
አገዛዝ በተጧጧፈበት ዘመን የውጭ ተጽ
ዕኖን ለመቋቋምና ኢትዮጵያን በነፃነት
ለማቆየት ያስቻለ ዋና ጉዳይ ነው ። ምኒ
ልክ የዚህን መሠረታዊ ጉዳይ አስፈላጊ
ነት ለመረዳት መነሻ የሆናቸው በቴዎ
ድሮስ ሥር ሆነው የቀሰሙት ትምህርት
ጭምር ነው ። አጼ ምኒልክ የቴዎድሮስን
ሞት በሰሙ ጊዜ « . . . ግልጽ ፍቅሩንና
ልባዊ እንክብካቤውን ምን ጊዜም ያልነፈ
ገኝንና ያስተማረኝን ሰው ዛሬ አጣሁ... » [24]
በማለት የአጼ ቴዎድሮስ ደቀ መዝሙርነ
ታቸውን አረጋግጠዋል ። ለሕይወታቸው
መጨረሻ ምክንያት የሆነው በአውሮፓው
ያን ላይ የወሰዱት እርምጃ የአጼ ቴዎድሮስ
የውጭ ፖሊሲ ብቻ ሳይሆን በአገር ውስጥ
ም የተከተሉት አመራር አሸባሪ እንደነበር
በአንዳንድ ደራሲያን ዘንድ ይንጸባረቃል።
ይህ ግን በሕይወታቸው መጨረሻ አካባቢ
ያሳዩትን ብቻ በቁንጽል የተመለከተ እንጂ
የአስተዳደራቸውን ጠቅላላ ዘመን የሚወ
ክል አይደለም ። በመጨረሻም ያሳዩት ጸባ
ይ በዓላማ አለመሳካት በብዙ ሰው ዘንድ
ሊታይ የሚችል ለውጥ በመሆኑ አስተያየ
ቱ ሚዛን የጐደለው ነው ። የፍርዱ ሚዛን
እንዳይዛባ የፖሊሲው መለወጥ ምክንያት ፣
ይህንንም ያስከተለው ግፊትና የነበሩት ች
ግሮች በዘመኑ ከነበረው ዕድገትና በዚህም
ወቅት ሊኖር ከሚችል የመንግሥት ባሕሪ
ጋር መገናዘብ ይኖርበታል ።

ከመቅደላ ዘመቻ በኋላ የኢትዮጵያና የም
ዕራቡ ዓለም ግንኙነት በአጼ ዮሐንስ አመ
ራር ሲቀጥል ፣ እንግሊዝና ፈረንሣይ የተ
ጽዕኖ ክልል የማስፋፋት ዓላማቸውን ተግ
ባራዊ ለማድረግ ከዚህ በፊት ይጠቀሙባ
ቸው የነበሩትንና ሌሎችንም ስልቶች በማ
ከል አባባሱት ። በእንግሊዝ አበረታችነት
«ታላቋን ግብጽ» ለመመሥረት የተቀየሰ
ው ፖሊሲ በተደጋጋሚ ወረራዎች ተደገፈ፤
እንግሊዝ የግብጽንና የሱዳንን ኃይል በኢ
ትዮጵያ ላይ ከማስማራቷም በላይ ጣሊያ
ንን በመሣሪያነት መጠቀም ጀመረች።ከመ
ካከለኛው ምሥራቅ ፣ ከአውሮፓ ፣ ከሜክ
ሲኮና ከዩናይትድ ስቴትስ በተውጣጡና በ
እነዚሁ አገሮች በተካሔዱ ጦርነቶች ልም
ድ ባገኙ የጦር መኰንኖች መሪነት የተካ
ሔዱት የጉንደትና የጉራዕ ጦርነቶች [25]
(ግብጽ በእንግሊዝ አስተዳደር ሥር የነበ
ረች በመሆኗ) የእንግሊዝ ወረራዎች ናቸው
ለማለት ይቻላል ። እንግሊዝ እነዚህን ጦር

Digitized by Google

ነቶች ማቀነባበሯ በግብጽ አማካይነት ሱዳ
ንን ለመያዝ የተጠቀመችበትን ዘዴ በኢት
ዮጵያ ላይ ለመድገም ያደረገችው ሙከራ
መሆኑን ያሳያል ። በተጨማሪም ሱዳን ው
ስጥ የገጠማትን ፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል ለማ
ክሸፍ በሂወት ስምምነት* አማካይነት ኢት
ዮጵያን በመሣሪያነት ተጠቅማ ፍላጐቷን
ካሟላች በኋላ ስምምነቱን በማፍረስ ምጽ
ዋን ለጣሊያን አሳልፋ መስጠቷ ጣሊያንን
በመሣሪያነት ማሰለፍ ብቻ ሳይሆ ፣ ኢት
ዮጵያንም አዳክማ ለመያዝ የነበራትን
ዕቅድ ያረጋግጣል ። እንግሊዝ ለጣሊያን
የሰጠችውን ድጋፍ በማስመልከት ሲል
ቪያ ፓንክረስት «ለጣሊያን በጐና አስከፊ
ምኞት እንግሊዝ የሰጠችው ድጋፍ» በሚል
ርዕስ የሚከተለውን ጽሑፍ አስፍረዋል 1

የምሥራቅ አፍሪካ ብሪታንያ ካምፓኒ (The British East African Company)

ከሡልጣኑ የተረከባቸውን የቤናድር (የጣ
ልያን ሶማሊያ) ወደቦች ለጣልያን መን
ግሥት ማስረከቡን ፣ የብሪታንያ መንግ
ሥት እንዲያጸድቅ በተጠየቀው መሠረት
ነሐሴ 12 ቀን 1892 የሁለቱ መንግሥ
ታት ወኪሎች እንደተስማሙት ተፈረመ ።
በፋሽዝም ዘመንና ከፋሽዝም በኋላ እን
ግሊዝ «ጥንትም የጣልያን ጠላት» እንደ
ነበረች ለማሳመን ቀይቶ የተጀመረውን
ፕሮፓጋንዳ በማክሸፍ ጣልያን ለብሔ
ራዊ አንድነቷ ትታገል በነበረችበት ወቀ
ት ግላድስቶን፣ጆን ሩሲልና ሌሎች ብሪታ
ንያ ውስጥ አነስ ያለ ታዋቂነት የነበራቸ
ው በዛ ያሉ ሰዎችና የብሪታንያ ሕዝብ
የጣልያንን ነፃነት ወክሎ የሰጠው ሞቀ
ያለ ድጋፍና ያደረገው ቅስቀሳ የጣልያንን
ዓላማ ማራመዱን በመረጃነት ለመጥቀስ
ወደኋላ መመለስ አያስፈልገንም ። ይህም
ብሪታንያና ጣልያን በኩራት ማስታወስ
ያለባቸው ድጋፍ ነው ። ብሪታንያ ለጣል
ያን ቀኝ አገዛዝ የሰጠችው ድጋፍ አነስ
ባለ ደረጃ የሚታይ ጉዳይ ነው ። በሕንድ
ውቀያኖስ ጠረፎች እንዳደረገችው ሁሉ
በቀይ ባሕር ጣልያን ልትይዘው ለቻለች
ው ቀኝ ግዛት በብሪታንያ ድጋፍ ብቻ መ
ሆኑ ይበልጥ የሚያሳዝን ነው ። በምሥ
ራቅ አፍሪካ ያውሮፓውያንን መስፋፋት
መደገፍ ማለት ከፍተኛ የሆነ ሥልጣኔ በ
ማደራጀት የባሕር ማዶ በርካታ ወረራዎ
ችን ተቃቁሞ ነፃነቱን ለዘመናት ጠብቀ
የኖረውን ጥንታዊና ታዳጊ አስተዳደርን
ሕልውና አሳልፎ የሚሰጥ አቋም በመሆኑ
የቀኝ አገዛዝ ዕድሜ ማክተሚያ ወቀት
ላይ ብንሆንም በዚህ አካባቢ ተደጋፊ
ነት ያልነበረውን የቀኝ ግዛት አስተዳደር
አስከፊ ገጽታ በተለይ በምሥራቅ አፍሪካ
በመዘርጋት ብሪታንያ ለፈጸመችው ወን
ጀል መፀፀት ይኖርብናል ። 26

ከዚህም የምንረዳው ለጣሊያን የውስጥና
የውጭ ፖሊሲ እውን መሆን እንግሊዝ የሰ
ጠችው ድጋፍ ባውሮፓ ውስጥ ለካፒታሊ
ዝም ዕድገትና ለዚህም ዋስትና የሰጠውን
ቅኝ ግዛት ተፈጻሚነት በእንግሊዝ ቅንብር
እንደተመራ ነው ። ይህም ላውሮፓ ማደ
ግና ለተቀሩት አኅጉራት ኋላቀርነት እንግ
ሊዝ በኢትዮጵያ ላይ ብቻ ሳይሆን በጠቅላ
ላው ታዳጊ ሕዝቦች ዕድገት ላይ ባስተባባ
ሪነት ለፈጸመችው ደባ ማረጋገጫ ነው።

በዚህ ወቅት በኢትዮጵያውያንና ባውሮ
ፓውያን መካከል የነበረው ግንኙነት አን
ደኛው መልኩ በስምምነቶች አማካይነት
የሚታይ ነበር ። ከነዚህም ውስጥ ጣሊያን
የውጫሌን ውል ትርጉም በማዛባት የኢት
ዮጵያ «የበላይ ጠባቂ» መሆኗ እንዲታወቅ
ላት ያደረገችው ሙከራ እንግሊዝ በሂወት
ስምምነት የተጠቀመችበትን ስልት መድ
ገሟ ነው ። በስምምነቶቹ አማካይነት በመ

* የሂወት ስምምነት የዓድዋ ስምምነትም በመባል ይታወቃል ። ስምምነቱ ሰኔ 3 ቀን 1884 በአጼ ዮሐንስና በእንግሊዛዊው አድሚራል ሂወት መካከል የተፈረመ ነው ። በዚህ ስምምነት እንግሊዝ በምጽዋ ወደብ የበላይ ጠባቂ ሆና ኢትዮጵያ በወደቡ እንድትጠቀም ፣ በዚሁ ወደብ ዕቃ ስታስወጣና ስታስገባም ከቀረጥ ነፃ እንደምትሆን ተገልጿል ።

Digitized by Google

ማፍንቱ መካከል የነበረውን ቅራኔ በመጠ
ቀም ያገሪቱን ኃይል ለማዳከም የዘረጉት
መረብ ነው ። በከፋፍለህ ግዛ ዘይቤአቸው
ዮሐንስን ከቴዎድሮስ ፣ ምኒልክን ከዮሐንስ
ለመነጠል ያደረጉት ሴራ ይህንኑ የሚያመ
ለክት ነው ።

ከመቅደላ ጦርነት እስከ ዓድዋ ጦርነት
በነበረው ጊዜ ውስጥ ግንኙነቱ ወደ
ጦርነት እንደተሸጋገረ ይታወሳል ።
በተለያዩ ዘዴዎች የኢትዮጵያን ኃይል
ማዳከማቸው በሰላማዊ መንገድ ያጡ
ትን ቅኝ ግዛት በጦርነት መሟላት ያለ
በት ጉዳይ በመሆኑ ያገሪቱ ኃይል መዳከም
ከማይቀረው ጦርነት ባሸናፊነት ለመው
ጣት ያዘጋጁት ቅድመ ሁኔታ ግልጽ ነበር ።
በዓድዋ ጦርነት የጣሊያን መቀጣት በፋሽ
ስት ወረራ እስከ አገረሸ ጊዜ ድረስ ወደ ጦር
ነት ያሸጋገሩትን ግንኙነት ጋብ በማድረግ
ወደ«ሰላማዊው » ግንኙነት እንዲመለሱ
አስገደዳቸው ። በዚህ ወቅት የታየው ሌላ
ው ለውጥ ካድዋ በፊት እንግሊዝ ፣ ፈረን
ሣይና ጣሊያን ኢትዮጵያን የየግላቸው ለማ
ድረግ በየበኩላቸው ያደርጉት የነበረውን
አጼ ምኒልክም የተጠቀሙበትን ፉክክር
አቻችለው ኢትዮጵያን ለመቋረስ ሽርክና
መግባታቸው ነው ። በ1906 የተዋዋሉት
የሶስቱ ወገኖች ስምምነት ይህንኑ ይመሰ
ክራል ። ፈረንሣይ ካኢትዮጵያ ጋር የመሠ
ረተችው ግንኙነት በዲፕሎማሲ ግንኙነት
ብቻ እንዲያተኩር ማድረጓ የእንግሊዝንና
የጣሊያንን ሽርክና ከመፍራት የመነጨ ነው።
ባንድ ወቅት ፈረንሣይ ቤልጂግን ከጐኗ ማ
ሰለፏ የሚያሳየው የኃይል ሚዛኑን ለመጠ
በቅ የሚያስችላትን ዘዴ መቀየስዋ እንደነ
በር ነው ። እንግሊዝ ዲፕሎማሲን ከጦር
ነት ጋር በማቀናጀት ስትጠቀም በተለይ ሌ
ሎችን መሣሪያ ማድረጓ ከሁሉም የረቀቀ
ዘዴዋን የሚያሳይ ነው ። ከሌሎቹ ጋር ሲ
ወዳደር የጣሊያኑ ዲፕሎማሲ ኋላቀር በመ
ሆኑ ብዙም ሳይቆይ በግንፍልነት ወደ ጦር
ነት የሚያመራ ግንኙነትን አስከተለ ። ለከ
ፈተቻቸው ጦርነቶች መነሻ ያደረገቻቸው
ምክንያቶች ለሩቅ ተመልካች እንኳ ፊት
ለፊት የተጋለጡ የሰከነ ዲፕሎማሲን መጠ
ቀም የማያስችሉ ስልቶች ሆነው እናያለን ።
በመሆኑም ኢትዮጵያውያን ዕድገታችንን
ያፋጥንልናል በማለት ካውሮፓውያን ጋር
የጀመሩት ግንኙነት በተቃራኒው ዕድገታ
ቸውን የሚያደናቅፍ ሆኖ አገኙት ። ሕል
ውናቸውንም ሥጋት ላይ የሚጥል ግንኙ
ነት መሆኑን ሲገነዘቡ ተጽዕኖውን በመከ
ላከል ላይ እንዲያተኩሩ ተገደዱ ። ስለ ግን
ኙነቱ ተጽዕኖ ከፍተኛ ግንዛቤ የተገኘው
በተለይ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ
ነው ።

ከ2ኛው የዓለም ጦርነት እስከ 1950ዎች መባቻ

አውሮፓውያን በኢትዮጵያ ላይ ከከፈ
ቷቸው ጦርነቶች በዓይነትም ሆነ በብዛት
አይለው የሚታዩት የጣሊያን ወረራዎች
ናቸው ። በተለይ አምስት ዓመታት የፈጀ
ው የጣሊያን ፋሽስት ወረራ ከዚህ በፊት
በኢትዮጵያ ላይ ከተካሔዱት ጦርነቶች
የከፋና የኢትዮጵያን ነፃነት በጦርነት ለመ
ግፈፍ በምዕራቡ ዓለም የተደረገ ሙከራ
ነው ። በዚህ ጦርነት በኢትዮጵያ ሕዝ
ቦች ላይ ለደረሰው ጥፋት ተጠያቂው የጣ
ሊያን ፋሽዝም ብቻ ሳይሆን ፣ (አሜሪካንን
ጨምሮ) መላው የኢምፔሪያሊስቱ ዓለም
ነው ። ኢትዮጵያ ለመከላከያ የሚሆናትን
መሣሪያ እንዳታገኝ በማገድ የወረራውን
«ሕጋዊነት» በይፋ አውጀው በወቅቱ የነ
በረውን የዓለም ማኅበር (The League
of Nations) ያሳለፈውን ውሳኔ ሥራ ላይ
እንዳይውል በማደናቀፍ የኢትዮጵያን ሕ
ዝብ ለፋሽስቶች ጭፍጨፋ የዳረጉት እንግ
ሊዝና ፈረንሣይ ናቸው ። አሜሪካም በጣ
ሊያንና በኢትዮጵያ መካከል በተከፈተው
ጦርነት «ገለልተኝነትን» በማወጅ [27] ካው
ሮፓ ኃያላን ያልተለየ አቋም ያዘች ።

. . . ይህ (የፋሽስት ጣልያን ወረራ)
ከ1939—45 ባውሮፓ ለተካሔደው
ጦርነት መነሻ ነበር ። በመጀመሪያ ኢት

Digitized by Google

የሕዝቦቻቸውን ፍላጎት የምዕራቡ ባለሟል ቢሆን ጦርነቱ ላይከሰት ይችል ነበር ። በፋሽስቶችና በናዚስቶች ላይ የተቀዳጀው ጦርነት ድል ካደረገ በኋላ የቀድሞ ቅኝ ገዥዎችን እንደገና ለማምጣት (የጠላቶችን) ዕማሲ ጨለማ ዋነኛው ዕቅድ እርምጃ ነው ።[28]

ይህ ዋናው የምዕራቡ ኃያላን በጦርነቱ ላይ የወሰዱት አቋም ምንነት ብቻ ሳይሆን ከጦርነቱም በኋላ ያራመዱትን የተለያዩትን ፖሊሲ በግልጽ የሚያሳይ ነው ። በኢትዮጵያ አካባቢ የነበሩትን ቅኝ ግዛቶች ኢትዮጵያ ውስጥ ከነበረው የጣሊያን ሠራዊት ወረራ ለማዳንና ንጉሡን በማጀብ ወደ ኢትዮጵያ ባስገባቸው ወታደር አማካይነት እንግሊዝ በኢትዮጵያ የተጽዕኖ ክልል የማስፋፋት ፍላጎቷን ተግባራዊ ለማድረግ ምክራ ነበር ። ገና ጦርነቱ ሳያበቃ ኃይለ ሥላሴ ወደ ዙፋኑ እንዳይመለስ ይታገሉ የነበሩትን ኢትዮጵያውያን በመምታት ኃይላቸውን ያዳከመችውና ንጉሡ ተመልሶ ዙፋኑ ላይ እንዲቀናጠጥ ያደረገችው እንግሊዝ ናት ። ወደ ሥልጣን እንደተመለሰም በተለያዩ አካባቢዎች የተነሱት ሕዝባዊ አመጾች የተመቱት ንጉሡን አጅቦ በገባው በእንግሊዝ ወታደር አማካይነት ነበር ። እንግሊዝ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበራትን ተጽዕኖ ለአሜሪካ በማስረከብ ከኢትዮጵያ እስከወጣች ጊዜ ድረስ ያተከረችው የንጉሡን ተቀናቃኞች በመምታትና ሥልጣኑን በማጠናከር ላይ ነበር ።

በሁለተኛው የኢምፔሪያሊስቶች ጦርነት ወቅት በተቀሰቀሰው ፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል ምክንያት የምዕራቡ ዓለም የውጭ ፖሊሲ ከቀጥተኛው ቅኝ አገዛዝ ወደ እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ እንዲሸጋገር ሆነ ። ከጦርነቱ በኋላ የተጠናከረው የአሜሪካና የኢትዮጵያ ግንኙነትም በዚሁ ፖሊሲ ሥር የሚጠቃለል ነው ። ኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ሲል ያውሮፓ መንግሥታት ይዘውት የነበረውን የበላይነት አሜሪካ ልትረከብ የቻለችው በወቅቱ ከምዕራቡ ዓለም ኃያል ሆና ለመውጣት በመቻሏ ነው ። ከጦርነቱ በፊትና በኋላ አሜሪካ ከአፍሪካ አገሮች ጋር የነበራትን ግንኙነት በማነጻጸር የምናገኘው ልዩነት የኢምፔሪያሊስቱ ዓለም መሪ ሆና መውጣቷን ከሚያሳዩት ሁኔታዎች አንዱ ብቻ ነው ። ለምሳሌ በ1939 አሜሪካ ከጠቅላላው አፍሪካ ጋር የነበራት ግንኙነት በ5 ሌጋሲዮኖች ፣ በ3 ቆንሲል ጀኔራሎች ፣ በ8 ቆንሲሎችና በአንድ የቆንሲል ወኪል አማካይነት ብቻ ሲካሄድ ቆይቶ በ1966 37 ኤምባሲዎች ፣ 9 ቆንሲል ጀኔራሎች 13 ቆንሲሎች ፤ በ3 የኤምባሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና አንድ የቆንሲል መኖሪያ በመክፈት አጠናከረችው ።[29] ከዚህም በላይ መጀመሪያው የዓለም ጦርነት ወቅት ከአፍሪካ ጋር በ150 ሚሊዮን ዶላር ታካሂደው የነበረው ንግድ በሁለተኛው ያለም ጦርነት ወቅት ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ማሳደጓና በ1943 አፍሪካ ውስጥ የነበራት የ104 ሚሊዮን ዶላር መዋዕለ ንዋይ ፣ በ1963 ወደ 1,423 ሚሊዮን ዶላር ማሻቀቡ[30] አሜሪካ በነዚሁ ዓመታት ውስጥ በአፍሪካ ለተጽዕኖዋ መስፋፋት የተፈጠረላትን ምቹ ሁኔታ የሚያረጋግጥ ነው ።

የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ይህን መሰል ተጽዕኖን ዘላቂ ለማድረግ የተጠቀመበት (ዛሬም የሚጠቀምበት) ዘዴ በታዳጊ አገሮች ውስጥ የሚገኙትን አድኃሪ መደቦች መሣሪያ ማድረግ ነው ። እነዚህም መደቦች በፀኩላቸው ሥልጣናቸውን የሚያጠናክሩበት የውጭ ዕርዳታ ይሻሉ ። ይህ የሁለቱ መፈላለግ ሲጋራ ትብብራቸው ጠንካራ በመሆን ያስገኛል ፤ ከፋሽስት ጣሊያን መባረር በኋላ የኢትዮጵያ ንጉሥ ከአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ጋር የተሻረከው ፀረ ፊውዳል እንቅስቃሴዎችን በመምታት ሥልጣኑን የሚያጠናክሩለት ቁሳዊና ፖለቲካዊ ድጋፎችን ለማግኘት እንዲችል ነው ። በእንግሊዝ እግር የተተካው የአሜሪካ ፖሊሲ እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ የንጉሡን ሥልጣን በማጠናከር የኢም

Digitized by Google

ፔሪያሊዝም ፖሊሲ አራማጅ ኃይል ሆና እንዲያገለግል በማድረግ ላይ አተኩሯል። በአምስቱ ዓመታት ፀረ ፋሽስት ትግል ወቅት ተናግቶ የነበረው ፊውዳል መንግሥት ኃይል እንደገና እንዲጠናከር ያበቃው ኢምፔሪያሊዝም በታዳጊ አገሮች ውስጥ በጣልቃ ገብነት ለሚጫወተው ሚና በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ነው።

የብሔራዊ አርነት ጥያቄ ኢምፔሪያሊዝም ከሚያስከትለው ችግር ጋር እጅግ የተሳሰረ ነው። ዓለምን በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል ዘደ የቀየሰውና ወታደራዊ ኃይሉን በከፍተኛ ደረጃ አዳብር የሚገኘው ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ባሁኑ ወቅት የብሔራዊ አርነት ትግሎች ቀንደኛ ጠላት ነው። ኢምፔሪያሊዝም ባይናር ናር በብዙ አገሮች ኢትዮጵያንም ጨምር (ቀድሞ አብዮት) የሚገኙ አሻንጉሊት መንግሥታት ዕድሜ በጣም አጭር ይሆን ነበር። . . .[31] ይህም በታዳጊው ዓለም የአድኃሪ መንግሥታት ዕድሜ መርዘም በኢምፔሪያሊዝም ጋሻ ጃግሬነት መሆኑን ያሳያል፤ የታዳጊው ዓለም ሕዝቦች ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግልም ከዚሁ ይመነጫል።

የግርጌ ማስታወሻ

1. Richard Pankhurst, *An Introduction to the Economic History of Ethiopia from early times to* 1800 (Lalibela House, London, 1961), p. 3.
2. Sergew H. Selassie, *Ancient and Medieval Ethiopian History to* 1270 (H.S.I.U., Addis Ababa, 1972), pp. 46-7.
3. R. Pankhurst, *Ibid*., pp. 55-7.
4. *Ibid*., p. 68
5. *Ibid*., pp. 70-1.
6. *Ibid*., pp. 81-6.
7. Seven Rubenson, *The Survival of Ethiopian Independence* (Addis Ababa University Press, 1976), p. 29.
8. *Ibid*.
9. *Ibid*., pp. 56-7.
10. *Ibid*., p. 57.
11. *Ibid*., pp. 59-64.
12. *Ibid*., p. 168.
13. *Ibid*., p. 128.
14. *Ibid*. p. 171.
15. *Ibid*., p. 173.
16. *Ibid*., p. 174.
17. *Ibid*., pp. 184-6.
18. *Ibid*., p. 223.
19. *Ibid*., p. 238.
20. *Ibid*., pp. 256-7.
21. *Ibid*., p. 259.
22. *Ibid*., p. 206.
23. *Ibid*., p. 183.
24. H.G. Marcus, *The Life and Times of Menilik II*: *Ethiopia* 1844-1913 (Clarendon Press, Oxford, 1975), p. 30.
25. S. Rubenson, *Ibid*. pp. 364-5.
26. Silvia Pankhurst, Ex-Italian Somaliland ("The benadir"), (Johnson's Court London, 1961), pp. 17-8.
27. JR., Harris Bruce, The United States and the Italo—Ethiopian Crisis (Stanford University (Press, California, 1964), p. 25.
28. Peter Freeman, M.P., In Sylvia Pankhurst, *Ibid*. p. 7.
29. Vernon Mckayed, Africa in the United States (Macfadden-Bartell Corporation, USA, 1967), p. 10.
30. *Ibid*., *p*. 32.

31 መስከረም ፣ ቅጽ 2 ቁጥር 6 ፣ 1974 (እ.ኢ.አ.) ገጽ 45።

Digitized by Google

የእምነት በዓላት ብዛት

በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ኑሮና የሥራ ዕቅድ ላይ ያስከተለው ችግር

ኢሳይያስ ደምሴ

ስለእምነት መንስዔና ዕድገት አጠቃላይ ሐሳቦች

ሰው ማኅበራዊ ነው ። ይህም በመሆኑ ቁሳዊ፣ መንፈሳዊ አስተሳሰቦቹና አመለካከቶቹ ሁሉ ማኅበራዊ ይዘት አላቸው ። ሰው ራሱ የኅብረተሰብ ውጤት እንደመሆኑ መጠን ገሳዊ አስተሳሰቡና አመለካከቱም የኅብረተሰብ አስተሳሰብና አመለካከት ነጸብራቅ ነው ። በየደረጃው ባለፈባቸው የታሪክ ዕድገት ወቅቶች የነበረው የአስተሳሰብ ስፋትና አወቃቀር በቁሳዊ ፍላጐት ምንጭነት ላይ የተመረኮዘ ነው ። ኅብረተሰብ በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ በነበረበት ወቅት ሰው ቁሳዊ ፍላጐቶቹን ለማሟላት የሚጠቀምባቸውን ነገሮች ምንነት ለመረዳት ፣ ተፈጥሮ ያደረሰበትን ችግር ለመወጣትና ለመከላከል ሞከሯል ።

ኤንግልስ « ሥራ ሰውን ራሱን ፈጠረው ማለት አለብን » እንዳለው ሥራ ሰው በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃውም ቢሆን ተፈጥሮን በጥንቃቄ እንዲያጠናና ሕልውናውም ከተፈጥሮ ጋር ያለውን ግንኙነት ለመመርመር እንዲሞክር ተጽእና አድርጐበታል ። ሆኖም ሰው ተፈጥሮን የመረዳትና የተፈጥሮንም ሕግጋት መርምሮ የማወቅም አቅሙ በቂ አልነበረም ። በመሆኑም የተፈጥሮ ክስተቶች በሰው ልጅ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕልውና ላይ ያላቸውን ተከታታይ ተጽዕኖና ውጤት በነበረው ዝቅተኛ የልምድ ክበት እየተረዳ መርምሮ ውጤት ሊጨብጥ አልቻለም ። በዚህ ውስንነቱ የተነሣ ብዙዎች የተፈጥሮ ክስተቶችም (መብረቅ ፣ ድርቅ ፣ በጐርፍ መጥመቅለቅ ፣ እሳተ ገሞራ ፣ ሞትና ልደት ወዘተ - - -) የአንዳንድ ሊመረመሩ የማይቻሉ ረቂቅ ወይም ግዙፍ ኃይላት ሥራዎች ናቸው የሚል የአምልኮት አስተሳሰብ አደረበት ።

እንግዲህ የሰው ልጅ የተፈጥሮ ክስተቶች የሚገዙበትን የተፈጥሮ ሕግጋት በትክክል ከተረዳበት ደረጃ ላይ ገና ባለመድረሱ ሊረ

Digitized by Google

ዳቸው ካልቻለው ከስተቶች ጋር ግንኙነት ያላቸው ነገሮችን ማምለክ ጀመረ ። እነዚህም የብዙ ነገሮች አስገኝዎችና ዘላለማዊ ጠባቂዎችም ናቸው ብሎ ማመንም ጀመረ። ሕልውናውንም ከእነዚህ ኃይላት ጋር አያያዘ ። ይህም የእምነት ጽንሰ ሀሳብ ጅማሬ ነበር ። የእምነት ጽንሰ ሀሳብ ከክርስቶስ ልደት በፊት (ከ5000—4000 ዓመታት በፊት) እንዳልነበረ የጥንተ ነገር ተመራማሪዎች ይናገራሉ ።[1]

ሰው በእምነት ታሪኩ መጀመሪያ ደረጃ ላይ ያመልክ የነበረው በዓይን የማይታዩ ፣ በእጅ የማይዳሰሱ ረቂቅ ሳይሆን ግዙፍ የሆኑ ነገሮችን ነበር ።

የኅብረተሰብ የዕድገት ታሪክ እንደሚያስተምረን ፣ የሰው የመጀመሪያ ቁሳዊ ኑሮው በአደን ላይ የተመሠረተ ነበር ። ለአደንም በሚሠማራበት ጊዜ ታላላቅ አራዊት ለቁሳዊ ፍላጐቱም ሆነ ለአጠቃላይ ሕልውናው አደገኛ ናቸው ብሎ ገመተ ። እነርሱንም ለመቋቋም ያለውን ደካማነት በመገንዘቡ ኃያልነታቸውን ተቀብሎ በማምለኩ ለሕይወቱም ሆነ ለቁሳዊ ፍላጐቱ ጠባቂውና ምንጮች ፣ እንዲሁም ተፈጥሮን ለመቆጣጠር የሚረዱትና ተፈጥሮም የምታስከትል በትን አደጋ የሚከላከሉለት አማልዕክት ናቸው ብሎ አመነባቸው ። በየዕድገት ደረጃውም በአንድ የተወሰነ የታሪክ ወቅትና ቦታ ዛፎችን ፣ ተራሮችን ሌሎችንም ግዙፋን ነገሮች ከሌሎች በመለየት መናፍስት የተዋሕዳቸው አማልዕክት አድርጐ በመቁጠር ፣ እርሱን ራሱንም ያስገኙ እነርሱ እንደሆኑ በመቀበል ፣ የሕይወትና የሞት ምሥጢርን የያዙ እነዚህ አማልክት ናቸው ብሎ አመነ ።

በወቅቱ በነበረው ንቃተኅሊና አመጣጡንና ድኅረ ሞት ሕልውናውን ሲመረምር ፣ ሰውና እንስሳት የአንድ ቅድመ አያት ልጆች እንደሆኑና ሰዎችም ከሞቱ በኋላ እንደገና ነፍስ ዘርተው በምድር ላይ እንደሚኖሩ ይገምት ፣ አልፎም ያምን ነበር ።

ከዚህም በቀር ለቁሳዊ ፍላጐቱ መሟላትም ሆነ አለመሟላት ምክንያት የሆኑትን ነገሮች ጠለቅ ብሎ የመመርመር ችሎታውና ዕውቀቱ ውስን በመሆኑ መገንዘብ አልቻለምና አማልክት የቁሳዊ ፍላጐቱ ወሳኞች ናቸው ብሎ እምነቱን አጸና ። ቁሳዊ ፍላጐቱ እንኳ ሳይሟላ ቢቀር ከእርሱ ጉድለት ወይም የአማልክት ፈቃድ አለመሆን እንጂ ሌሎች ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች መኖራቸውን መገንዘብ አልቻለም ። ተፈጥሮ የምትሰጠውን ደስታ ሳይቀር የአማልክት ቡራኬና ፀጋ አድርጐ ቆጠረ ።

ኅብረተሰብ በመደብ ሲከፋፈል በሰዎች ማኅበራዊ ሕልውና ውስጥ እንጸራዊ የሆነ ጭቆና ፣ ፍትሕ ርትዕ ማጣትና የሰው በሰው ብዝበዛ ተከሰቱ ። የተፈጥሮ ንብረትም ሆነ የብዙኃኑ ሕዝብ የሥራ ኃይል በጥቂቶች ቁጥጥር ሥር እየዋለ በመምጣቱ የኅብረተሰብ አብዛኛው ክፍል ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጐት መሟላት አልቻለም ። የዚህም ውጤት በሰፊው የኅብረተሰብ ክፍል ዘንድ ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ችንና የኅሊና ውጥረትን አስከተለ ። ስለዚህም ቁሳዊ ብሶቱንና የኅሊና ጭንቀቱን ሊያቃልልለት የሚችል ከእርሱ ውጭ የሆነ አንድ ኃይል ፈለጐ እርሱን መማጸን ጀመረ። የቁሳዊ ፍላጐቱ ምንጮች የሆኑት የምርት መገልገያ መሣሪያዎች የግል ባለቤትነትና የሥራ ኃይሉ ለጥቂቶች ጥቅም እንዲውል የሚያስገድደው የፖለቲካ ሥልጣን በጥቂቶች በመያዙ የሚደርስበት ጭቆናና ድኅነት አማልክት ናቸው ብሎ ካመነባቸው አራዊት ፣ ዛፎች ፣ ወንዞች ፣ ጨረቃ ፣ ፀሐይ ወዘተ - - - ቁጣና መኀሪነት ጋር አዛምዶ ይመለከት ጀመር ። በመሆኑም ጭቆናን ፣ ድኅነትን ፣ ተገዥነትን ፣ ወዘተ - - - በፀጋ በመቀበል የምርት መገልገያ መሣሪያዎች በግል ባለቤትነት መያዝና የሥራ ኃይሉ ለጥቂቶች መዋል የቁሳዊና መንፈሳዊ ችግሮቹ ምንጮች መሆናቸው በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ በነበረበት ጊዜ ሊከሰቱለት

Digitized by Google

አልቻለም ። ከችግሩ ለመወጣት በመደብ ጠላቶቹ ላይ ከመነሳሳት ይልቅ ምንም የማይሳናቸው ነገር የለምና ምፅናዩን ይሰሙኛል ፣ ይፈጽሙልኛልም ብሎ ባመናቸው የተፈጥሮ ነገሮች ላይ አምልኮቱን አደረገ ።

የሰው የአስተሳሰብና የአመለካከት ዕድገት እንፃራዊ በሆነ መንገድ ቀስ በቀስ ዕድገት እያሳየ ሲሄድ ያመልካቸው የነበሩትን ግዙፉን ነገሮች (ዛፎች ፣ አራዊት ፣ ወንዞች፣ ፀሐይ ፣ ከዋክብት ፣ ወዘተ . . .) ውሱንነትና ጠፊነት ወይም ሟችነት ፣ አቅመ ቢስነት ፣ ወዘተ . . ተገነዘበ ፤ ስለዚህም ሰው በዓይን ከሚታዩና በእጅ ከሚዳሰሱ ነገሮች አምልኮት ወደማይታዩና ወደማይዳሰሱ ረቂቃን መናፍስት አምልኮት ተሸጋገረ ። ይህ የሰው ልጅ የአስተሳሰቡ አድማስ እየሰፋ መሄዱን ያሳያል ። እነዚህ መናፍስትም ከቁሳዊው ዓለም በፊት የነበሩ ፣ ያሉና ከቁሳዊው ዓለም በኋላም የሚኖሩ ዘላለማዊነት ያላቸው ናቸው የሚል አስተሳሰብ አደረበት ። በማኅበራዊ ተግባሩ ሂደት ውስጥ ለሚገጥሙትና ለተፈጥሮአዊ ልዩ ልዩ ክስተቶች ምንጭነትና እንቅስቃሴ ኃላፊነት ያላቸው መናፍስት ማለትም ርኩስ መንፈስ ፣ ቅዱስ መንፈስ ፣ ወዘተ . . . ከግዙፍ ዓለም ውጭ እንደሚኖሩና የደስታና የሀዘንም ምንጭ እነርሱ እንደሆኑ ማመን ጀመረ ። ማግኘትና ማጣትም የእነዚህ መናፍስት ስጦታና ቅሬታ ነው ብሎ አመነ ። ይህ የተፈጥሮ ክስተቶችን ምንጭና ባሕርይ ጠለቅ ብሎ የመመርመር ብቃት ያላገኘው ሰው እርሱ ራሱ እንኳ የአንድ ረቂቅ ኃይል ወይም መንፈስ ሥራ እንደሆነና ቅርጽና ውስጣዊ ባሕርዩም (ነፍሱ) የዚሁ መንፈስ ተመሳሌት መሆናቸውን እምነቱ አድርጐ ያዘ ።

እንግዲህ ሰው ከዚህ አስተሳሰብና አመለካከት ተነስቶ ለእምነቱ ቅርጽና ይዘት እየሰጠ በሚዳሰስና በሚታይ ነገር ላይ የነበረውን እምነት ለቆ በማይዳሰስና በማይታይ፣ ማለትም ሕልውና በሌለው ረቂቅ መንፈስ በማመን ራሱን የሃይማኖት ተገዥ አደረገ ።

በዚህ ዓይነቱ የኅብረተሰብ የአምልኮ ታሪካዊ ዕድገት ውስጥ በእምነት ላይ የተመሠረተ አመለካከት ብቅ ማለት የሚያሳየው የሰው ልጅ ተፈጥሮን ለመቋቋምና ቁሳዊ ፍላጐትን ለማሟላት ባደረገው ጥረት አኳያ የነበረውን ደካማነት ነው ። ደካማነቱና በአምልኮ መሸፈኑ ደግሞ ሰው ቁሳዊውን ዓለም ጠለቅ ብሎ እነዳይመረምር እንቅፋት ከመሆኑም በላይ የተፈጥሮና የማኅበራዊ ክስተቶችን ምንጭና ምንነት እንዳያጤንና እንዳያውቅ ፣ ቁሳዊና መንፈሳዊ ዕድገቱም እንዲገታ አድርጐታል ።[2]

የበዓላት ታሪካዊ አመጣጥ

በመጠኑም ቢሆን ከዚህ በላይ ለመጠቆም እንደተሞከረው የሰዎች የአምልኮት ፍላጐት ወይም የሃይማኖት ጅማሬ የሰዎችን ቁሳዊ ፍላጐት ለማሟላት ከተደረገ ጥረት የመነጨ ነው ።

በሃይማኖት አስተሳሰብ በዓልም ሲባል አንድ ጻድቅ ወይም ሰማዕት የተወለደበት ፣ የሞተበት ወይም ከፍተኛ የሆነ ተአምር ሥራ የሚባልበት ወይም ስለሃይማኖቱ በመቆም ከፍተኛ መስዋዕት የከፈለበትና መላክም የሆነ እንደሆነ ትልቅ ተዓምር ሥራ የሚባልበት ዕለት ነው ። በዚሁ መሠረት በዓል ማክበርም ስንል ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጐቱ የተሟላለት ወይም እንዲሟላለት የሚፈልግ አንድ ሰው « አሟላልኝ ወይም ያሟላልኛል» ብሎ ለሚያመልከው ግዙፍም ሆነ ረቂቅ ነገር ደስታውን ፣ አክብሮቱን ወይም ምኞቱን የሚገልጥበት ሁኔታ ነው ።

የበዓል አክብሮት በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ከረጅሙ የአምልኮት ታሪክ የተያያዘና ከእርሱም ተነጥሎ የማይታይ ነው ። በየታሪካዊ ወቅቱና በየቦታው የነበሩ ማኅበረሰቦች በአንድ ላይ ተሰብስበው የማኅበረሰቡ የእርሻ አምላክ ፣ የሞት አምላክ ፣ የልደት አምላክ ፣ የዝናም አምላክ፣ ወዘተ... እያሉ ለሚጠሯቸውና እርካታቸውን ፣ ፍር

Digitized by Google

ሀታቸውን ፣ ቁጣቸውን በአጠቃላይ ግን ሥጋዊና መንፈሳዊ ጭንቀታቸውን እንዲሁም ደስታቸውን ይገልጡ እንደነበረ ከታሪክ መገንዘብ ይቻላል ። በዘመናችን የሚታየው የእምነት በዓላት አከባበር በቅርጹ ይለይ እንደሆነ እንጂ ቀደም ያለ ታሪካዊ ሂደት ያለው መሆኑን በቀላሉ መረዳት አያዳግትም ።

ሆኖም ብዙዎች የሃይማኖት ሰዎች የእምነት በዓልና አከባበር በምንም ዓይነት ከሰዎች ቁሳዊ ፍላጐትና እርካታ ጋር እንደ አልተያያዘ አድርገው የሚያስተምሩት ትምህርት በሳይንሳዊ ምርምር የተደገፈ ነው ለማለት አያስደፍርም ፤ ትክክለኛም አይደለም ።

ሰዎች የተፈጥሮን ልግስና በትክክል ባለመገንዘብና ከምርት ኃይሎች ዕድገትና ኋላቀርነት የተነሳ የሚያገኙትን ቁሳዊ እርካታና የሚገጥማቸውን ቁሳዊ ችግር በሚገባ ባለመረዳት እንደነዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ከእነርሱ አስተሳሰብ ውጭ የሆኑ የአንዳንድ ኃይላት ሥራዎች አድርገው በመቁጠራቸው ምስጋናቸውንም ሆነ ልመናቸውን ለእነርሱ ይገልፃሉ ። የአገላለጹ ሁኔታ ግን ግላዊነት ቢኖረውም በአብዛኛው ማኅበራዊነት አለው ። ይህ ተግባር በአንድ በተወሰነ ቦታና የተወሰነ ዕምነት በተከተለ ማኅበረሰብ ወይም ብሔረሰብ እየተደጋገመና ጊዜ እየወሰደ ሲመጣ ታሪካዊ ክስተት ይሆናል ። ይህም የዚያ ማኅበረሰብ ወይም ብሔረሰብ የእምነቱ መለያ ውጫዊ ባሕርይ መስሎ ከመቅረቡም በላይ በታሪካዊ ሂደቱ ርዝማኔ ውስጥ የቦታና የብሔረሰብ ድንበርን አልፎ ይሄዳል። እንግዲህ የአንድ ኅብረተሰብ የዕምነት አስተሳሰብና አመለካከት በፈጠረው ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ግንኙነት መሰላልነት በሌላው ኅብረተሰብ ላይ እየተዛመተና እየተስፋፋ ሲሄድ ከእምነቱ ጋር የተያያዘው የበዓሉም አከባበር ልምድ እንዲሁ አብሮ በመተላለፍ ይስፋፋና የእምነቱ ባህል አካል ሆኖ ይቀራል ።

ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያ ውስጥ ለአያሌ መቶ ዓመታት ሥር ሰዶ የቆየው የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እምነት የበዓል አከባበር አመጣጥና አጀማመርም ይህን ሂደት የተከተለ ነው ለማለት ይቻላል ።

በኢትዮጵያ ገዥ መደቦችና በክርስቲያኑ ኅብረተሰብ ክፍል ዘንድ ለአያሌ ዘመናት ሰፍኖና ያተለመደ ተግባር ሆኖ የቆየው የበዓላት አከባበር መቼ እንደተጀመረና ከየትኛው አገር ኅብረተሰብ የእምነት ልማድ ተቀድቶ እንደመጣ በግልጽ አይታወቅም ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሊቃውንትም የሰጡትና የሚሰጡት አስተያየት ፣ ተለያየ ነው ።

ሆኖም የበዓላትን አከባበር ይዘትና ቅርጽ ስንመረምር የኦሪት ቅጅነት ያለበት በመሆኑ የአይሁድ የበዓል አከባበር ልምድና ሥነ ሥርዓት በቅይጥ ይታይበታል ።

የበዓሉም አከባበር ሥርዓትና ልማድ ከኦሪት የመጣ እንደሆነ ለማጠያየቅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ የሆነው ኅብረተሰብ ከብሉይ ኪዳን በወረሰው መሠረት ቅዳሜንና እሁድን ብቻ ሳይሆን በሌሎችም በዓላት ውኃ አይቀዳም፤ ቡና አይወቀጥም ፤ ወንዝ አይሻገርም፣ ሥር አይምስም ፤ ቅጠል አይበጥስም፤ ልብስአ ያጥብም፤ ፈትል አይፈትልም ። [3] በጣም ኋላቀር የሆነው ይህ ዓይነቱ የበዓል አከባበር የደረጃ ጉዳይ ቢኖርበትም ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ከከተማ እስከ ገጠር ባለው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ ኅብረተሰብ ዘንድ በተግባር ሲንጸባረቅ ይታያል ።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ስለበዓላት አከባበርና ድንጋጌ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ ምንጭና መመሪያዋ አድርጋ የምትቀበለው ፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ ፣ የበዓላት አከባበር በሐዋርያት የተደነገገ ፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣና ክርስትናን በተቀበሉ ሕዝቦች ዘንድም እምነታዊ ባህል ሆኖ የቆየ መሆኑ ይናገራል። [4] በኋላም ሶስት መቶ አሥራ ስምንት ሊቃ

Digitized by Google

ውንት በኒቂያ ተሰብስበውና የክርስቶስ የሐዋርያት ፥ የመላዕክት ፥ የሰማዕታት፥ ወዘተ . . . በዓላት መታሰብ እንዳለባቸው መወሰናቸውን ይኸው መጽሐፍ ይተርካል ።

ሆኖም ፍትሐ ነገሥት ይህን ይበል እንጂ በኢትዮጵያ ውስጥ ከየትኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ የሐዋርያት ፥ የጻድቃን ፥ የክርስቶስ የመላእክት ፥ ወዘተ - - - በዓላት መከበር እንደተጀመረ አይናገርም ። ግን ቅዳሜን ምንአልባት ሌሎችን የአይሁድ በዓላት ከክርስትና መግባት በፊት ኢትዮጵያ ታከብር እንደነበረ አንዳንድ ጥቆማዎች ይገኛሉ ። [5] የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የእምነት ባህል የአሪትና የእስክንድርያ ፥ የሶሪያና የግሪክ አብያተ ክርስቲያናት ልማዳዊ የበዓል አከባበር ቅይጥ ያለበት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል ።

በ6ኛው ምዕተ ዓመት ገደማ ፥ ከሶሪያና ከግሪክ የመጡት ዘጠኙ ቅዱሳን እንዲሁም በየጊዜው እስከ ሃያኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አጋማሽ ድረስ በተከታታይ እየመጡ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን በበላይነት ሲያስተዳድሩት የነበሩት ግብፃውያን ጳጳሳት የበዓላት አከባበር በኢትዮጵያ ውስጥ እየተስፋፋ እንዲሄድና ምናልባትም እንዲንዛዛ በማድረጉ ረገድ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው አልቀረም ።

በሌላም በኩል የእስልምና እምነት በኢትዮጵያ ውስጥ እየተስፋፋ ሲመጣና የጣኦት አምልኮትም እያገረሸ ሲሄድ ይህንን ሁኔታ ለመከላከል የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በዓላትን ማብዛትና በጥብቅም እንዲከበሩ ማድረጓ ከአንዳንድ የታሪክ ማስረጃዎችና ከተለያዩ ሁኔታዎች መገንዘብ ይቻላል ።

ይሁንና የቤተ ክርስቲያን በዓላት ዛሬ በሚታዩበት ቅርጽና ይዘታቸው እንዲከበሩ በአዋጅ መልክ ያስገደደው አፄ ዘርዐ ያዕቆብ (1434—1468) እንደሆኑ ታሪክ ያስረዳል ። [6] አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ካህናት ስለ በዓላትና ስለትሩፋት መጻሕፍት ጽፈው ሕዝቡን እንዲያስተምሩ ሲያስገድዱ ሕዝቡም የጣኦት አምልኮን ትቶ በክርስትና እንዲያምን በመቅጣትና በመግረፍ አስገድደውታል ። ይህንም ያደረጉት ከእምነት ቀናኢነት የተነሳ ብቻ ሳይሆን ለአገዛዝ እንዲመችና ግዛታቸውንም እያስፋፉ ለመሄት እንዲያግዛቸው አስበው እንደነበረ ይገመታል ። [7] በዚህም መንፈስ ሕዝቡ በበዓላት ቀን በየቤተክርስቲያኑ እየተሰበሰበ በዓላትን በደመቀ ሁኔታ አጥብቆ እንዲያከብር ከማዘዛቸውም በላይ ተጨማሪ በዓላትም ወስነው እንዲከበሩ አድርገዋል ። በተለይም ሠላሳ ሶስት የማርያም በዓላት ወስነው እንዲከበሩ ያደረጉት አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ናቸው ይባላል ። [8]

እንዲሁም መጽሐፈ ብርሃን የተባለው መጽሐፋቸው ቅዳሜና እሁድ በእኩልነት ደረጃ መከበር እንዳለባቸው ያሳስባል ። [9]

ከዚህም በቀር በአንድ በተወሰነ ጊዜና ወቅት በአንድ አካባቢ የነበረ መስፍን ወይም ተሰሚነት የነበረው ምስለኔ « ሕልም አየሁ ፥ እንዲህ ያለ ታምር ሠራልኝ» ብሎ ያከብረው የነበረው በዓል ቀስ በቀስ በእርሱ አካባቢ ኗሪ በሆነው የኅብረተሰብ ክፍል ዘንድ ተዘውትሮ የሚከበር እየሆነ እንደመጣ ወይም ደግሞ በአንድ ወቅት በአንድ አካባቢ አንድ ባሕታዊ ወይም ከዋሻ ወጣሁ ያለ መነኩሴ « እገሌ የሚባለውን ጻድቅ ወይም ሰማዕት ወዘተ - - - በዓሉን በየወሩ እንድታከብሩና እንድትዘከሩ ንገር ተብዬ ታዝዣለሁ » ብሎ በመስበኩ በየአካባቢው ኗሪ ሕዝብ ማክበር እንደተጀመረ « የጻድቃንና የሰማዕታትን ገድሎችን » ስንመረምር እንረዳለን ። እንደዚሁም አንድ ጻድቅ ወይም ሰማዕት በአንድ አካባቢ ላይ ከደረሰው ሁኔታ ጋር ይያያዝና ይህን ታምር የሠራ እገሌ ነውና በዓሉን ማክበር ይገባናል ብለው የአካባቢው ቄሶች ስለሚያስተምሩ በዚያ አካባቢና ቀስ በቀስም በሌላው አካባቢ የወሩንም ይሁን የዓመት በዓሉን ማክበር የተለመደ ሆኖ እንደቀረ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ይጠቁማሉ ። ለም

Digitized by Google

ሳሌ ፡ በሸዋ ተክለሃይማኖት ፡ ዜና ማርቆስ ፤ በጐጃም ገብረ መንፈስ ቅዱስ ፡ ተክለ አልፋ ፡ በትግራይ አቡነ አረጋዊ ወዘተ . . . ተዘውትረው የሚከበሩና ከፍተኛ ክብር የሚሰጣቸው ናቸው ።

ይሁንና ምንም እንኳ «የቅዱሳንና የሌሎ ችም በዓላት ከእግዚአብሔር ሕግጋት በአ ንዱ እንኳን እንዲከበሩ የታዘዘ አይደለም ፤ በራሷ በቤተ ክርስቲያን የተደነገጉ ናቸው እንጂ ፤ አንዳንዶቹ በዓላትም ከሐዋርያት ዘመን ጀምረው የሚከበሩ ሲሆን አንዳንዶቹ ግን ከዚያ ወዲህ መከበር የጀመሩ ናቸው» ቢባልም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሲ ኖዶስ ታሪክ ውስጥ ይኸ በዓል በዚህ ደ ረጃ ይከበር ወይም አይከበር ተብሎ በየወ ቅቱ የተደነገገ መመሪያ የለም ። የበዓላትን አከባበር ድንጋጌ የሚናገሩት ፍትሐ ነገሥ ት መንፈሳዊና ስንክሳርም ቢሆኑ በአንድ የተወሰነ ወቅት የተጻፉ ከመሆናቸው በላይ ምላት ያለው መመሪያ አይሰጡም ።

ከዚህ በመነሳት የበዓላትን አከባበር ወይ ም የእምነት ልምዶችን ግንኙነት ጥያቄ አ ንስቶ ባጭሩ መመልከቱ የዚህን ጽሑፍ ዓ ይነተኛ ዓላማ ይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል ። አንድ የቤተ ክርስቲያን ምሁር ፡ «የአንድ ሀ ገር ሕገ መንግሥት የዚያ ሀገር ሕጐች ፡ አዋ ጆች ፡ መግለጫዎች ወዘተ . . . ሁሉ መሠ ረት እንደሆነ እምነትም አንድ ቤተ ክር ስቲያን ለምታከብራቸው በዓላት ለደነገ ገቻቸው አጽዋማትና ለሌሎችም ሥርዓቶች ምንጭ ነው ፤» እንዳሉት ሁሉ ፡ በዓላት የማከበሩ ልማድም ሆነ እምነታዊ ባህሎ ችና ልምዶች በመሠረቱ የእምነቱ ነጸብራ ቆች ናቸው ። ይህም በመሆኑ በኅብረተሰብ ታሪክ ውስጥ የተለያዩ እምነቶች የነበሩና ያሉ ሲሆን ፡ እያንዳንዳቸው የተለያዩ እም ነታዊ ልማዶችና ባህሎች አሏቸው ። የባህሉ ምንጭና መሠረትም እምነቱ ነው ። ለምሳሌ የአንዱ እምነት ጾምን መ ጾም መንግሥተ ሰማያትን የሚያወርስ አድ ርጐ ሲያዝ ፡ ሌላው እምነት ደግሞ ፋይዳ የለሽ ተግባር አድርጐ ይመለከተዋል ፤ ወ ይም አንዱ እምነት የጻድቃን ፡ የሰማዕ ታትን ወዘተ . . . በዓላት ማክበር ጽድቅን የሚያስገኝ ዐቢይ ተግባር አድርጐ ሲቆጥ ረው ሌላው እምነት ግን ፍጹም የስንፍና ሥራ አርድጐ ይቀበለዋል ።

ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ዘን ድ ለዘመናት ሰፍኖ የነበረውንና አሁንም በአብዛኛው የሚታየውን የበዓላትን አከ ባበር ዘርዘር አድርጐ መመልከቱ የበለጠ ግንዛቤ ያስገኛል ።

የበዓላት ብዛትና አመዳደብ

የኢትዮጵያን ኅብረተሰብ ታሪካዊ የኢ ኮኖሚ ሕይወት ወደኋላ መለስ ብለን በጥን ቃቄ ብንመረምር ገዥ መደቦች በዚህ ኅብ ረተሰብ ላይ ካደረሱት ጭቆናና ምዝበራ በ ተጨማሪ የበዓላት ብዛት የፈጠሯቸው ማኅ በራዊ ችግሮች በቀላሉ የሚገመቱ አይደ ሉም ። አምራች የሆነው ኅብረተሰብ በተ ለይ አርሶ አደሩ ቁሳዊ ፍላጐቱን ለማሟ ላት ይታገል የነበረው ከማኅበራዊ ችግሮች ብቻ ሳይሆን ከተፈጥሮም ጋር ስለነበር በወ ቅቱ አርሶ በወቅቱ እንዳይዘራ እንዲሁም መከር ሲደርስ በወቅቱ አጭዶ በወቅቱ እንዳይወቃ የበዓላት ብዛት እንቅፋት ሆኖ ውበት ኖረዋል ። ዛሬ የእገሌ በዓል ፡ ከነገ ወዲያ ሌላው በዓል ወዘተ . . . እየተባለ የሥራ ጊዜው ስለሚባክንበት በዘር ጊዜ ዘግ ይቶ ይዘራና የዝናም እጥረት ስለሚገጥ መው ቡቃያው ጫጭቶ ፡ በመከርም ጊዜ በወቅቱ ማጨድ ስለማይችል እህሉ ከሐሩር ብዛት ረግፎ ያለበለዚያም በዝናም ተበላ ሽቶ ይቀራል ። ከምሩም ቢሆን በወቅቱ ስለ ማይወቃ በዝናም ይበሰብሳል ወይም ከብት በልቶ ይጨርሰዋል ።

የዕደ ጥበብ ባለሙያዎችንም በሚመለ ከት ረገድ እያንዳንዱ ባለሙያ ማለትም ሸ ማኔው የሸመናን ፡ ቆዳ ፋቂው የቆዳን ፡ ብረ ት ሠሪው የብረትን ፡ ሸክላ ሠሪው የሸክላን

Digitized by Google

ወዘተ - - - ሥራ እንዳይሠራ በበዓላት ብዛት ተተብትቦ በመያዙ መሠረታዊ ፍላጐቱን ማሟላት ስለሚቸገረው ፣ ለረሀብ ከመጋለጡም በላይ በአራጣ አበዳሪዎች ፣ በሀብታም ገበሬዎችና በጉልተ ገዥዎች የአራጣ ብድር ውስጥ ገብቶ እንዲዘፈቅ ይሆናል ። በአንድ ወቅትም ጨርሶ መክፈል ከማይችልበት ደረጃ ላይ ስለሚደርስ ያለ የሌለ ንብረቱን አስረክቦ ከአገር እንዲሰደድ ያለበለዚያም እርሱም ሆነ ቤተሰቡ ለሰው ተገዥ ሆኖ እንዲኖር ይገደዳል ።

ይህ ሁኔታ የሚከሰተው በዕደ ጥበባት ባለሙያዎች ብቻ ሳይሆን በአርሶ አደሮቹም ዘንድ ነው ። ለምሳሌ አንድ የቤተሰብ ኃላፊነት ያለበት ገበሬ ጥሮ ግሮ በወቅቱ አርሶ ዘርቶ ፣ አርሞ ፣ አጭዶና ወቅቶ የተደላደለ ኑሮ እንዳይኖር ፣ ዘጠኙ የጌታ፣ ሠላሳ ሦስቱ የማርያም ፣ አሥራ ሁለቱ የሐዋርያት ፣ አሥራ ሁለቱ የወሩ ገብርኤል ፣ አሥራ ሁለቱ የወሩ ሚካኤል ፣ አሥራ ሁለቱ የወሩ መድኃኔ ዓለም ፣ አሥራ ሁለቱ የባለእግዚአብሔር ፣ በዓመት ውስጥ የሚውሉት መቶ አራት የቅዳሜውና የእሁድ ወዘተ - - - የተባሉት በዓላት የየለት ሥራውን ያሰናክሉታል ።[10]

በዚህም ምክንያት « አነስ ሲሉት ተቀነሰ » የተባለው ተረት ይደርስበትና በሚቀጥለው ዓመት እንኳን ለዘር የሚሆነው እህል ሊኖረው ይቅርና ገና ሰኔ ሳያቆለቁል ይልሰው ይቀምሰው ያጣና ከነቤተሰቡ ስልቻውን ይዞ ልመና ይገባል ፤ በትውልድ መንደሬ ላይ አልዋረደም ካለም ይሰደዳል ። በወለድ ቁና እህል አበዳሪው ከተገኘም በየጊዜው እየቆነጠረ መክፈል ከሚያዳግተው ዕዳ ውስጥ ገብቶ ይዘፈቅና « እየየ » ሲል ይኖራል ። የዚህ ምክንያትስ ምንድነው ? መልሱ የእምነት በዓላት መንዛዛትና ከሰፊው ሕዝብ ቁሳዊና ማኅበራዊ ኑሮ ጋር ሳይገናዘቡ መደንገግ ወይም ለሰው ልጅ ቁሳዊ ሕይወት ምንነት የተሳሳተ ግንዛቤ መኖርን ያመለክታል ።

ስለእምነት በዓላት መንዛዛት ምክንያትና በኃላፊነት ተጠያቂነት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዘንድ የተለያዩ አስተያየቶች አሉ ። በዓላት ለሥራና ለሰፊው ሕዝብ የዕለት ኑሮ በአጠቃላይ ግን ለቁሳዊ ዕድገቱ እንቅፋት በመሆን በዝተው እንዲከበሩ ያደረገችው ቤተ ክርስቲያን ሳትሆን ቀሳውስቱና ራሱ ሕዝቡ እንደሆነ አንድ የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣን የነበሩ በሚከተለው አኳኋን ይገልጹታል ። ይህም « ለጻድቁ ስለት ተስዬ ስለደረሰልኝ አከብረዋለሁ ፣ ክርስትና ተነስቼበታለሁ ፣ ጠበል ተጠምቄ ተፈውሼበታለሁ፣ ወይም ጠጥቼበታለሁ ፣ በዚህ ቀን ከእንደዚህ ያለ መዓት አድኖኛል ፣ ቄሱም ሆነ ባህታዊው ይህንን በዓል ብትሽር አዝመራሀን በረዶ ይመታብሀል ፣ አይጥ ይበላብሀል ፣ መዓት ይወርድብሀል ፣ ይሉታል »[11] የሚለው ነው ። ይህ አባባል እውነታ ቢኖረውም ቤተ ክርስቲያንን ከቀሳውስቱና እንዲሁም ከምዕመናኑ ለይቶ መመልከት አይቻልም ። ያለበለዚያማ ራሷ ቤተ ክርስቲያን «ቤተ ክርስቲያን ማለት ካህናቱ ፣ ምዕመናኑና ሕንፃውም ነው »[12] ብላ የምትሰጠውን ገለጻ መቃረን ይሆናል ። ከዚህም በላይ የቀሳውስቱን ችሎታና ብቃት መርምራና መዝና ሥልጣነ ክህነት የምትሰጠውና የሚሰብኩትንም ስብከት የምትቆጣጠር ራሷ እንደመሆኗ መጠን ቄሱም ሆነ ባህታዊው ይህንን በዓል አክብር እያለ የሥራውን ቀን የበዓል ቀን ሲያደርገው ቤተ ክርስቲያን አታውቅም ፤ የቤተ ክርስቲያን ትምህርትም አይደለም ፤ ማለት ሁኔታዎችን በትክክል አለመገንዘብ ከመሆኑም በላይ ከሀቅ ውጭ ይሆናል ።

እንዲሁም አንድ የቤተክርስቲያን ሊቅ « በኢትዮጵያ ውስጥ ወደ ሦስት መቶ የሚጠጉ ገድል የተጻፈላቸው ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን አሉ ። የእነዚህ ቅዱሳን በየአካባቢያቸው ቢያንስ ቢያንስ ከዓመት ውስጥ ዕለተ ልደታቸውና ዕለተ ዕረፍታቸው ክብረ በዓል ሆኖ ይከበራል ። ከዚህም በቀር በየ

Digitized by Google

ጦሩ ተክለ ሃይማኖት ፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገብርኤል ፣ ኪዳነ ምሕረት ፣ ሥላሴ ፣ አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ፣ ሩፋኤል ፣ ሐና ፣ ቂርቆስ ፣ አቡነ አረጋይ ፣ አቡነ ገሪማ ፣ ዮስጣቴዎስ ፣ መርቆርዮስ ፣ መድኃኔ ዓለም ፣ አማኑኤል ፣ ማርቆስ ፣ በዓታ ፣ ልደታ ፣ በአብዛኛው ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ዘንድ ይከበራሉ ። ነገር ግን እነዚህን በዓላት ማንኛውም ክርስቲያን እንዲያከብር መገደድ አልነበረበትም ። በተግባር የሚታየው ግን ገበሬው በዓላቱን ሻርክ እየተባለ ሲወገዝ ፣ ንስሐ ግባ ተብሎም አርባ ቀን ሲጾምና ሌት ተቀን ሲሰግድ ነው ። እንደ ቤተ ክርስቲያን አባባል ከሆነ ይህ መሆን አልነበረበትም ፤ ምክንያቱም የግዝት በዓላት አይደሉም ። ይሁንና በገጠር ያሉ ቄሶች የግዝት በዓላትን ለይተው ስለማያውቁ ገበሬውን ግራ በማጋባት በኑሮው ላይ ከፍተኛ ችግር ይፈጥሩበታል በማለት ለየት ያለ ሃሳብ ሰንዝረዋል። ይህም ሃሳብ በመሠረቱ ይህን በዓል አክብር እያሉ ገበሬውን ሥራ የሚያስፈቱ ቄሶች ናቸው እንጂ ቤተክርስቲያን አይደለችም የሚለውን አስተያየት ለማጠናከር ነው ። በመቀጠልም እንደገለጹት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ፣ በሦስት መቶ ስምንቱ ሊቃውንትና በፍትሐ ነገሥት እንዲከበሩ በውግዘት የታዘዙትን በዓላት አክብሩ ብላ ከማስገደድ በስተቀር ውግዘት የሌላቸው በዓላት እንዲከበሩ የማታስገድድ ግን ትሩፋት ሠርተው ፣ ሰማትዕነት ተቀብለው የእግዚአብሔር ወዳጆችና የሰው ልጅ አማላጆች የሆኑትን የጻድቃን የሰማዕታት በዓላት ቢያንስ ቢያንስ በአካባቢያቸው እንዲከበሩ የምታስተምር መሆኗን ጠቁመዋል ።

ከዚሁ አንፃር ሌላው የቤተ ክርስቲያን ሊቅም በሰጡት አስተያየት መሠረት «በዓላት የዕረፍት ቀናት ናቸው ። ይህ ሲባል ግን ሥራ አይሠራባቸውም ማለት አይደለም ። በእነዚህ ቀናት ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ጸሎት መጸለይ ፣ ጾም መጾም ፤ ምፅዋት መስጠት፣ ወዘተ - - የመሳሰሉትን ሥራዎች ያከናውናል እንጂ እጅ እግሩን አጣጥፎ መቀመጥ የለበትም ፤ በወር በወር የሚከበሩትም በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ አንድ ጀግና ከፍተኛ የጀግንነት ሙያ ሠርቶ እንደሚታሰብ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም እገሌ የሚባል ጻድቅ ወይም ሰማዕት በዚህ ቀን እንዲህ ያለ ተአምር ሠራ ፣ በዚህ ቀን ደግሞ ሞተ እያለች ዝናውን ታነባለች እንጂ እንደግዝት በዓል መላው ክርስቲያን በግድ ያክብር ብላ አታስገድድም ። ሆኖም ሕዝብ በልማድ ዝም ብሎ የግዝት በዓላት አድርጎ ያከብራቸዋል ። መከበር ያለበት ግን የየዓመቱ ክብረ በዓልና የግዝት በዓላት የሆኑት ብቻ ነበሩ ። ይሁንና በዓል ማክበር ዣት (ሀብት) የሚሰጥ ፣ እህል የሚያበረክት መሆኑን ነው ፤ » ይላሉ ።

የቤተ ክርስቲያን በዓላትን ማክበር እንደ ዕረፍት ቀንና በበዓላት ቤተ ክርስቲያን እየሄዱ ጸሎት መጸለይና ምጽዋት መስጠት እንደሥራ መቆጠር የለበትም ፤ ሊሆንም አይችልም ። ዕረፍት ሲባል አንድ ሰው የራሱንና በአጠቃላይም የሚኖርበትን ኅብረተሰብ ቁሳዊ ፍላጎት ለማሟላት የሚያስፈልገውን ድካምና ልፋት ከአደረገ በኋላ ምርታማነቱና የፈጠራ ችሎታው እንዳይቀንስ የሚያደርገው የአእምሮና የአካል መዝናናት ነው። ሥራም ሲባል የሰው ልጅ የሥራ ኃይሉን በመጠቀም ምርትን ለማስገኘት የሚያደርገው አእምሮአዊና አካላዊ እንቅስቃሴ ነው ። ከዚህ ውጭ ሌላ ማለት ሊሆን ችልም ።

ይህንን ሐቅ በትክክል ባለማጤን ከታወቁት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አንዱ የሆኑትም ሊቅ አስተያየታቸውን በማራዘም በአሁኑ ጊዜ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በዓል እየሻረ በመሥራቱ በቤቱ ውስጥ ያለው እህል የሚነቅዝ ፣ አዝመራውን በረዶ የሚመታውና አንበጣም የሚባለው ከመሆኑም በላይ እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለተጣላው በድርቅ የሚቀጣው መሁኑን አብራርተዋል ። ከዚህ

Digitized by Google

ዓይነቱም መዓት ለመዳን እንድሰው በዓልን እየሻረ ከመሥራት ይልቅ ከሳምንት አንዱን ቀን እንኳን ቢሠራ ምርቱን እግዚአብሔር እንደሚያበረክትለት ተናግረዋል ።

እየተደጋገሙ የሚታዩትን ነገሮችና ሁኔታዎች በጥሞና የመመልከትና የማስተዋል ዓይነተኛ ችሎታ ያለው ማንም ሰው መገመት እንደሚችለው የእህል አለመበርከትና በነቀዝ መበላት ፣ የዝናም መቅረትና ያአዝመራው በበረዶ መመታት ፣ ወዘተ--- የመሳሰሉትን ድርጊቶችና ክስተቶች ከእግዚአብሔር ቁጣ ጋር መያያዛቸው አንድም ነገሮችን ጠለቅ ብሎ የመመራመርና የማስተዋል ችሎታ ማነስ ሲሆን ፣ አለያም እውነትን ለመሸሸግ የሚደረግ ሙከራ ከመሆኑም በላይ ምንእልባትም በዚህ ዓይነት እምነት ላይ ያለውን ኢሳይንሳዊ የሆነ አመለካከት የሚያሳይ ይሆናል ። ለመሆኑ የእህሉ አለመበርከትና በተባይ መበላት ከኢያያዝ ጉድለትና ጥንቃቄ አለማድረግ መሆኑ እንዴት ሊረሳ ይቻላል ? የዝናም አመጣጥና ምንጭም ከእምነት የሚመነጭ አመለካከት እንደሚለው ሳይሆን ሳይንስ እንዳረጋገጠው ነው ። የድርቅም ምክንያቶች ምን እንደሆኑ ሳይንስ በተጨባጭ ያስቀመጣቸው በመሆኑ የማስተዋል ችሎታ ያላቸው አርሶ አደሮች እንኳ ከማስተዋል ልምዳቸው በመነሳት « ዘንድሮ ድርቅ ይሆናል » እያሉ የሚናገሩትን ማገናዘብ አለመቻል መሆኑን ያስረዳል ።

ይህ በዚህ እንዳለ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በምትቀበለውና በየዕለቱም በየቤተ ክርስቲያኑ በምታስነብበው «ስንክሳር» በተባለው መጽሐፍ መሠረት የዓመቱ ቀናት በሙላ ወይም በእእያንዳንዱ ወር ውስጥ ያሉት ሠላሳ ቀናት በአማካይ በእያንዳንዱ ቀን ሁለት ሁለት በዓላት ይውላሉ ማለት ይቻላል።ይህንን በግልጽ ለማሳየት እንደምሳሌ አድርገን የመጋቢትን ወር ወስደን መመልከት እንችላለን ።

መ ጋ ቢ ት[13]

ቀን 1	ቀን 2	ቀን 3	ቀን 4	ቀን 5
በርኪኮስ እስክንድሮስ	መከራዊ ጉርጉርዮስ	ቀዝሞስ በርፎንዮስ	—ማኅበረ ጉባኤ ዘደሴተ ደቂቀ ኤሞር —ሀኑልያስ —ሀይመተ ስላሴ (ቅ/ት)	—ሰርባሞን —አውዶክርስቲያን (ቅ) —ገርማኖስ —ገ/መንፈስ ቅዱስ —ቴዎድሮስ

ቀን 6	ቀን 7	ቀን 8	ቀን 9	ቀን 10
—ዲዮስቆሮስ —ቴዎድስዮስ —እንጦንዮስ	—ፊሊሞን —አብላንዮስ —ቴዎዶስዮስ	—አርያኖስ —ማቴያስ —ዩልያኖስ	—እንድርያስ —አውሳቢዮስ —አርማ —40 ሰማዕታት —200 —ኖብ —ብንጣንያስ	—መስቀለ ክርስቶስ

Digitized by Google

ቀን 11	ቀን 12	ቀን 13	ቀን 14	ቀን 15
—ቴዎጢኪኖስ —ባስላኒክስ —አሴፍ —አውሳብዮስ —ኤፍሬም	—ሚካኤል —ዲሜጥርስ —መላዚ —ተሰፋ ጽዮን	—40 ሐራ (ቅዱሳን) —መርቆሪዮስ —መቃሪዮስ እስክንድራዊ —ዋልጢኖስ —ይሁዳ መቃብ ያዊ	—ቂርቆስ —በጥል —ቢኖዳ —አውጋንዮስ —አውጋንዮርስ —አንልብድዮስ —አፍጼ —ገርሲሞስ —ድምራ (ቅድስት —ቶማስ ሐዋርያ	—ሳራ(ቅድስት) —ስልፋኮስ —ሀልያስ —ቂርቆስ

ቀን 16	ቀን 17	ቀን 18	ቀን 19	ቀን 20
—ሚካኤል ጳጳስ	—አላዛር —ቴዎቅራጦስ —ጊዮርጊስ (መስ ተጋድል) —ተለሰስ —ዮሴፍ —ኒቆር አባ ገሪማ	—ኤስድሮስ	—አርዕፍርስ —እስክንድሮስ ግብጻዊ —አጋብዮስ —ኒሚጦስ —ቡኒዮስ —ዲዮስቆርስ —ተላስዮስ —አስከናፍር —ማርታ (ቅድ ስት) —አርቃድዮስ —ዮሐንስ	—ሚካኤል (ጳጳስ) —ክርስቶስ —አላዛርዕን —ያነሳበት —ጽጌ ሥላሴ —(ቅድስት) —አስጠራጠኒቃ —አስቃራን

Digitized by Google

ቀን 21	ቀን 22	ቀን 23	ቀን 24	ቀን 25
—ማርያም —ላሜህ —ቴዎድሮስ —ጢሞቴዎስ —በአልአዛር ቤት ክርስቶስ ተማሪዎቹን የሰበከበት —ሊቃነ ካህናት አላዛርን ለመ ግደል የመከ ሩበት	—ክርስቶስ ኢየ ሩሳሌም የገባ በት ቄርሎስ	—ዳንኤል (ነቢይ) —አይሁድ በቀያ ት ቤት በክርስ ቶስ ላይ የመከ ሩበት	—መቃርዮስ —አይሁድ በክር ስቶስ ላይ ምክ ራቸውን ያፀኑበት	—አኒፍኖስ

ቀን 26	ቀን 27	ቀን 28	ቀን 29	ቀን 30
—ኢዮጲራቅስ (ቅድስት) —ፍርፍርዮስ —ክርስቶስ የተማሪዎቹን እግር ያጠበበት —ይሁዳ ክርስቶ ስን የሸጠበት	—መቃርዮስ —እስጢፋኖስ —ስቅለት —ሕዝቅያስ —ገላውዲዎስ —አባ ዮሐንስ	—ቆስጠንጢኖስ	—የገብርኤል ብስራት —የጳውሎስ ስብከት በዋርቆ ሀገር	—ስምን (መስፍን) —ያዕቆብ ገሙድ —ገብርኤል ከክርስቶስ ወደማርያም የተላከበት

Digitized by Google

ከዚህ ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው በሠላሳዎቹ ቀናት የሚውሉት በዓላት ጠቅላላ ድምር አንድ መቶ ሠላሳ ሲሆን በመጋቢት የሚውሉት በዓላት አማካይ የበዓላት ቁጥር በቀን አራት ይሆናል ማለት ነው ። ይህ ሲሆን ግን በአብዛኛው የክርስቲያን አካባቢዎች የሚከበሩት በቤተ ክርስቲያንም ዘንድ በየወሩ እስከ ሠላሳ ባሉት ቀናት እንደመደበኛ የሚቆጠሩት በዓላት ከመቶ ዘጠናው ያህል እንኳ በሠንጠረዥ ላይ አል ተመለከቱም ። እነዚህን መደበኛ በዓላት ከሚከተለው ሠንጠረዥ መረዳት ይቻላል ።

መደበኛ የወር በዓላት

ቀን 1	ቀን 2	ቀን 3	ቀን 4	ቀን 5	ቀን 6	ቀን 7	ቀን 8	ቀን 9	ቀን 10
ልደታ ዮሐንስ	ታዲዮስ	በዓታ	ዮሐንስ ወ/ነጐ ድጓድ	አቦ	ቁስቋም	ስላሴ	ኪሮስ	ቶማስ	መስቀል አርባእቱ እንስሳት

ቀን 11	ቀን 12	ቀን 13	ቀን 14	ቀን 15
ሐና	ሚካኤል	ራጉኤል ዘር ብሩክ እግዚአብሔር አብ ገ/ክርስቶስ ሩፋኤል	ገ/ክርስቶስ አረጋዊ	ቂርቆስ

ቀን 16	ቀን 17	ቀን 18	ቀን 19	ቀን 20
ኪዳነ ምህረት	እስጢፋኖስ	ዮስጣቴዎስ	ገብርኤል	ህንፀታ

ቀን 21	ቀን 22	ቀን 23	ቀን 24	ቀን 25
ማርያም	ደቁስዮስ	ጊዮርጊስ	ተ/ሃይማኖት	አቡነ አቢብ

ቀን 26	ቀን 27	ቀን 28	ቀን 29	ቀን 30
ቶማስ ዘህንደኬ	መድኃኒ ዓለም	አማኑኤል አብርሃም ያዕቆብ	በዓለ እግዚአብሔር	ማርቆስ

Digitized by Google

እነዚህ በዓላት በአሥራ ሁለቱም ወራት በተመሳሳይ ቀን እየተደጋገሙ የሚውሉ ናቸው ። በአንዳንድ አካባቢዎች ብዙዎችን ምንም ሥራ ሳይሠሩ ሲያከብሩ አንዳንዶቹን ደግሞ ቀለል ያለ ሥራ እየሠሩ ማለትም ማረስ ፣ ማጨድ ፣ ወዘተ . . . የመሳሰሉትን ትተው የታጨደውን በመሰብሰብ ፣ እውድማ በመለቅለቅ ወዘተ . . . ያከብራሉ ።

ይህም ዓይነት አጋጣሚ የሚገኘው ግን አንድም የቁሶች ግዴለሽነት ሲኖር አለያም ቁሶች ራሳቸው በግብርና ላይ የተሰማሩ ሲሆኑ ነው ።

ከዚህም በቀር ፣ ዐአብዛኛው ክርስቲያን አካባቢ እንደማረስ፣ማረም ፣ ማጨድ ፣ መውቃት የመሳሰሉት ሥራዎች በእያንዳንዱ ወር ውስጥ የማይካሄድባቸው በዓላት ከሞላ ጐደል የሚከተሉት ናቸው ።[14]

ቀን 1	ቀን 5	ቀን 7	ቀን 12	ቀን 16
ልደታ	አቦ	ሥላሴ	ሚካኤል	ኪዳነ ምህረት

ቀን 19	ቀን 21	ቀን 23	ቀን 24	ቀን 27
ገብርኤል	ማርያም	ጊዮርጊስ	ተ/ሃይማኖት	መድኃኔ ዓለም

ቀን 28	ቀን 29
አማኑኤል	በዓለ እግዚአብሔር

በዚህ ሠንጠረዥ መሠረት ፣ አንድ ክርስቲያን ገበሬ ወይም የዕደ ጥበብ ባለሙያ በእያንዳንዱ ወር ውስጥ ማለትም ከሠላሳው ቀናት መካከል ሥራ የማይሠራባቸው ቀናት በወር ውስጥ የሚውሉትን ቅዳሜንና እሑድን ጨምሮ ሃያ ገደማ ይሆናሉ ፤ ስለዚህ በእንደዚህ ያለ አካባቢ በወር ውስጥ የሚሠራው አሥር ቀኖች ብቻ ነው ። በዓመትም ውስጥ ሌሎችን የዓመት ክብረ በዓላትና የገዝት በዓላት የሚባሉትን ሳንጨምር የማይሠራባቸው ቀናት ሁለት መቶ አርባ ስምንት (ስድሳ ሰባት በመቶ) ናቸው ።

ቤተክርስቲያን የገዝት በዓላት ብላ የምትጠራቸውና ማንኛውም የእምነቱ ተከታይ የሆነ ሰው በግድ ማክበር ያለበት የበዓላት ቁጥር ዘጠኝ የክርስቶስ አበይት በዓላት ፣ አሥራ ሁለት የሐዋርያት በዓላት ፣ ሠላሳ ሶስት የማርያም በዓላት ፣ ሃምሳ ሁለቱ የሰንበት በዓላትና የመሳሰሉት ናቸው ። የእነዚህም ድምር መቶ ስድሳ ቀናት ይሆናል ። እነዚህን ቀናት ሽሮ ማንኛውንም ሥራ የሠራ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን በነፍስ በሥጋ የሚቀጣና እንደአርዮስ የተወገዘ እንደሚሆን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አብዛኞቹ ቀሳውስት አጥብቀው ያስተምራሉ ።

ከዚህም በቀር የገዝት በዓላት ባይሆኑም እንደነርሱ በመቆጠር በተመሳሳይነት ደረጃ የሚከበሩ ከፋሲካ በፊት አምስት ቀናት (ሰኞ—ዓርብ) ፣ ከፋሲካ በኋላ (ከሰኞ—ዓርብ) አምስት ቀናት ፣ የጰራቅሊጦስ በዓላት አምስት ቀናት ፣ ከነሐሴ 16 ጀምሮ አምስት ቀናት ፣ ደብረ ምጥማቅ አምስት ቀናት፣ በድምሩ በዓመት ውስጥ ሃያ አምስት ቀናት

Digitized by Google

ሉ ። እንዚህም ቢሆን በብዙ አካባቢዎች ግዝት በዓላትን ያህል የሚከበሩና የሚታዩ ናቸው ። እንዲያውም በብዙዎች በዓላት ቀን ሥራ በመተው ብቻ ሳይሆን ድግስ ተደግሶ እየተዘከረ እንደሚከበሩ የታወቀ ነው ።

የግዝት በዓላት ተብለው ከሚጠሩት መካከል አብዛኞቹ ለምሳሌ አምሳ ሁለቱ የሰንበት በዓላት ፣ አሥራ ሁለቱ የማርያም የወር በዓላት ከሁለት መቶ አርባ ስምንቱ በዓላት ጋር አብረው እንደሚቆጠሩ መገንዘብ ያስፈልጋል ።

ባጭሩ ግን በማንኛውም ወር ውስጥ በዓል የማይውልበት ቀን አለ ወይ ? ለሚለው ጥያቄ መልሱ የለም ነው ። በዓመት ውስጥ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ የሚያከብራቸው በዓላት ሁለት መቶ አርባ ስምንት ገደማ ናቸው ብንልም ማንኛውም ክርስቲያን የሚያከብረው እነዚህን ብቻ ነው ማለት አይደለም ። ከቀሩት በዓላት መካከል እንደአካባቢው ሁኔታና እንደግለሰቡ ፍቅርና እምልኮ የሚያከብራቸው ተጨማሪ በዓላትም መኖራቸውን ማስታወስ ያሻል ። ከዚህም በቀር በአብዛኛው አካባቢ በወር በዓልነቱ የማይከበረው ታቦት በክብረ በዓሉ(በዓመት በዓሉ) ዕለት ይከበራል ። ለምሳሌ እስጢፋኖስ በወር በዓልነቱ በብዙ አካባቢ አይከበርም ፤ ግን በክብረ በዓሉ ዕለት አብዛኛው ክርስቲያን የዕለት ሥራውን ትቶ ያከብረዋል ።

ይህ እንግዲህ ምንም እንኳ እንደየአካባቢው ሁኔታና እንደግለሰቡ ፍቅር ብንልም ፣ ካህናት ስለበዓላት መከበር ከሚያስተምሩት አጠቃላይ መርህና በእያንዳንዱ አግኝ ላይም ከሚያሳድሩት ከባድ ተጽእኖ የተነሳ መሆኑ መካድ የለበትም ። በየተአምሩ ፣ በየድርሳኑ ፣ በስንክሳሩ ፣ በውዳሴው ፣ በመልክመልኩ ፣ በቅዳሴው ፣ በየጸሎት መጽሐፉ ፣ ወዘተ . . . የጻድቁን ወይም የመላኩን በዓል ያከበረ ፣ በእርሱም ስም ጠበል ጠዲቅ የዘከረ የጻድቁን ዋጋ ያገኛል ፤ ለጻድቁ ዝክር አሻር ሲቆላ የሸተተው ሁሉ እስከ ሶስት ትውልድ ይማራል ፣ ወዘተ . . . እየተባለ ነጋ ጠባ ስለሚሰበክለት አብዛኛው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ይህን ዓለም ንቶ ለወዲያኛው ዓለም ሲጓጓ ይኖራል ። ከሞት በኋላም መንግሥተ ሰማያትን እወርሳለሁ በሚል እምነት የዕለት ልብሱንና የዕለት ጉርሱን የሚያስገኝለትን ሥራ ትቶ በዓል አከብራለሁ በማለት እንደሰነፍ ወይም መሥራት እንደማይችል በሽተኛ ሰው ቁጭ ብሉ ይውላል ። በሀሳቡ ግን « የዘሩ ጊዜ አለፈብኝ ፣ ቡቃያውን ዓረም አጠለቀብኝ ፣ ጤፉ ሳይታጨድ ጊዜው ስለአለፈ ረገፈብኝ . . . ወዘተ » እያለ ያወጣል ፤ ያወርዳል፤ መንፈሱም ይጨነቃል ። በዓሉን ሽር እንዳይሠራም በቁሱ ግዝት ይደርሱበሃል የተባለውን መቅሰፍት ወይም ከሞት በኋላ ኩነኔን ይፈራል ። በዚህም የተነሣ የተንዛዙትን በዓላት ወዶ ሳይሆን ተገዶ ሰባኪዎች «እሳቱ የማይጠፋ ፣ ትሉ የማያንቀላፋ ገሃነመ እሳት » ብለው የአስተማሩትን በመፍራት ሲያከብር ይኖራል ።

የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ስለሥራ ያላቸው አመለካከት

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በምትቀበላቸው በተለይ ስንክሳርና መጽሐፈ ምዕላድ መሠረት በአንድ ዓመት ውስጥ በሚገኙት በ365/6 ቀናት ሁሉ በየቀኑ ቢያንስ ቢያንስ ሁለት በዓላት እንደሚውል ቀደም ብለን ከተመለከትነው ገለጻና እንዲሁም ሠንጠረዦች መገንዘብ ችለናል ።

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት አስተሳሰብ መሠረት በቅዳሜና በእሁድም ሆነ በሌሎች በዓላት ቀናት ሥራ መሥራት ቀደም ሲል የተጠቀሰውን መከራና ችግር የሚያደርስ ከሆነ ቤተክርስቲያን ሥራን የምንምንጭ አድርጋ ትመለከተዋለች ? በተከታዮችዋ ዘንድ ስለሥራ ያለው አመለካከት ምንድነው ? ብለን መጠየቅ ተገቢ ይመስላል ።

Digitized by Google

ለክርስቲያኑ ዓለም የእምነት ምንጭ ነው የሚባለው መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ቁሳዊ ፍላጐት ለማርካት የሚሠራው ሥራ በእርግማን የተሰጠው ወይም የሚኖርባት ምድር የእርግማን መኖሪያው እንደሆነች ሲያመለክት « አዳምን አለው ፤ - - - ምድር ካንተ የተነሳ የተረገመች ትሁን ፤ በሕይወት ዘመንህ ሁሉ በድካም ከእርሷ ትበላለህ ፤ - - - ወደ መጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ - - - » [15] ይላል ። የዚህ ጥቅስ መሠረተ ሀሳቡ የሚያስረዳው አዳምና ሄዋን በገነት ምንም ሥራ ሳይሠሩ በዚያ የሚገኘውን ሁሉ ከበለስ በስተቀር ቁጭ ብለው እንዲበሉ ተፈቅዶላቸው ሳለ ፤ ሄዋን አዳምን አሳስታ የተከለከለችዋን በለስን ስለአበላችው እግዚአብሔር አዳምን እየሠራ እንዲበላ የረገመው መሆኑን ነው ።

ከዚህ ጽንሰሃሳብ ስንነሳ በእምነት አተረጓጐም የሰው ልጅ ቁሳዊ ፍላጐቱን ለማርካት የሚሠራው ሥራ ሁሉ የእርግማን እንቅስቃሴ እንደሆነ ነው ። ከዚህ በመነሳት ይሆናል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቀሳውስት ውሀ እንኳ በሰንበትም ሆነ በበዓላት ቀናት ከጉድጓድም ሆነ ከወንዝ ቀድቶ መጠጣት በዓል እንደመሻር ማለትም ኃጢአት እንደመሥራት ቆጥረው ይህንን ያደረጉትን ሰዎች የሚያወግዙዋቸው ። [16]

በሌላም አነጋገር ፤ ሥራ መሥራት የኃጢያት አንደኛው ገጽታ ነው ፤ ወይም ኃጢአት ማለት በአንድ ጐኑ ሥራ መሥራት ነው። ይህንን አባባል ምንአልባት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሊያስተባብሉ ይሞክሩ ይሆናል ። ሐቁ ግን ለምሳሌ አንድ ሰው የእሑድንም ሆነ የማርያምን በዓላት ሽሮ እርሻ ቢያርስ ፤ ጤፍ ቢያጭድ ፤ ዛፍ ቢቆርጥ ፤ ኃጢአት በመሥራቱ በነፍስ በሥጋው እንደሚቀጣ ከፍትሐ ነገሥት እስከ መጽሐፈ ብርሃን ድረስ ያሉ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ይናገራሉ ። ግልጽ በሆነ አነጋገር በበዓላት ቀናት ሥራ አለመሥራት ጽድቅ የሚያስገኝ ከሆነ በእነዚሁ በዓላት ሥራ መሥራት ደግሞ የሚያስኰንን ነው ማለት መሆኑን ማንም ሰው የሚረዳው ነው ። ከዚህ ውጭ ሌላ ምን ትርጉም ሊሰጠው ይችላል ? ይህ ግልጽ የሆነ እውነት ነው ። ሥራ መሥራት የኃጢአት ምንጭ እንደሆነ ባይቆጠር ኖሮ በማርያም ፤ በባለእግዚአብሔር ፤ በሰንበት ፤ በሚካኤል ፤ በመድኃኔ ዓለም ፤ በጥምቀት - - - ወዘተ ክምር ስትከምር ፤ ስታርስ ፤ ስታጭድ ፤ ማረሻና ወገል ቀጥቅጠህ ስትሠራ ፤ ቆዳ ፍቀህ አትማዳ ስትሰፋ ፤ ሸማ ስትሠራ ፤ ግንብ ስትገነባ ፤ ቤት ስትሠራ ፤ ውኃ ስትቀዳ - - - ውለሀልና ኃጢአተኛ በመሆንህ «ውጉዝ ከመ አርዮስ» እየተባለ አርሶአደሩ ፤ ብረት ቀጥቃጩ ፤ ቆዳ ፋቂው ፤ ሸማ ሠሪው ፤ ግንበኛው ፤ ቤተ ሠሪው ፤ ውኃ ቀጂዋ ፤ ባልተገዘቱም ፤ አርባ፤ ሰማንያ ፤ ወዘተ - - - ቀን ጾም ፤ ለአርባ ቀናት - - - በቀን ሦስት ጊዜ 120 ስግደት ስገድ፤ አሥራት በኩራት ለቤተ ክርስቲያን ስጥ ፤ እገሌ ለሚባል ታቦት ዝክር ዝክር ባልተባለም ነበር ። ነፍስህ እንድትማር ፤ ኃጢአትህ እንዲሰረዝልህ ምፅዋት ለነዳያን ስጥ፤ ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች (ካህናት) እምኃ አቅርብ ፤ የንስሐ አባትህን አልብስ አብላ ፤ ወዘተ — እየተባለ እንደቅጣት ባልተጣለበትም ነበር ።

ቄሶች አማኞችን ዝክር እንዲዘክሩ ፤ እንዲመጸውቱ ፤ ንስሐ አባቶቻቸውን እንዲያለብሱና እንዲያጉርሱ የሚያስተምሩ ከሆነ በዓል ሽሮ ሥራ መሥራት የኃጢአት አንደኛው ገጽታ አድርገው መቁጠር እንዴት ይችላሉ ? ምክንያቱም የሀብት ምንጭ ሥራ ነውና ፤ መዘከርም ሆነ መመጽወት የሚቻለውም ምርት ሲኖር ነው ።

ይህ ዓይነቱ ድርጊት እጅግ አድርጐ ያስገረመው ጸሐፊ « ገበሬው የግብርና ሥራውን ትቶ በቤተክርስቲያን ውስጥ በዓል ሲያከብር እንዲውል ከፈለጉ ካህናቱ ገበሬው ምግብና መጠጥ እንዲሰጣቸው እን

Digitized by Google

ዴት ይሻሉ ? » [17] በማለት ጥያቄ አቅርቧል ። ትክክለኛና ተገቢ ጥያቄ ነው ። ሰው ሲሞት የሳልስቱ፥ የሰባቱ ፥ የአሥራ ሁለቱ፥ የሠላሳው ፥ የአርባው (የተዝካሩ) የዓመቱ፥ ወዘተ - - - ድግስ ደግሰህ ፍታት አስፈታ ፥ ለማርያም ፥ ለመድኃኔ ዓለም ፥ ለጥምቀት ፥ ለፋሲካ ፥ ለፍልሰታ ደግሰህ ዝከር ፤ ይህንን ካላደረግህ ግን ፍታት አንፈታም ፥ የንስሐ አባት አንሆንም ፥ እየተባለ ያለች የሌለችውን እህሉን አራግፎ ደግሶ በማብላት ከችግርም ሆነ ከረሀብ ላይ የሚወድቅ ስንቱ ነው ? ይህስ ሥራ ሳይሠራ ይገኛልን ? ኧይ ገኝም ፥ የሀብት ሁሉ ምንጭ ሥራ ነውና ።

በሌላ በኩል ፥ ይኸው ጸሐፊ እንዳለው እውነተኛ የቤተክርስቲያን ተከታዮች ናቸው የተባሉት በዓመት ውስጥ ማክበር ያለባቸው 364 የበዓላት ቀናት ናቸው ቢባልም ፥ እንኳ የሥራ ቀን የምትባለዋም ጥር 10 ቀን የጥምቀት ዋዜማ በመሆኗ ከሰዓት በኋላ ታቦት ስለሚወርድባት አማኒያኑ ሥራቸውን ትተው ታቦት ማውረድ እንዳለባቸውና ይህም ከሆነ በዓመት ውስጥ በመሠረተ ሀሳቡ ሥራ መሥራት የሚቻለው የዚችኑ ቀን ግማሽ ብቻ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል ። [18] በመሠረቱ ግን ጥር 10 ቀንም ብትሆን የሥራ ቀን አይደለችም ። ምክንያቱም በየወሩ ጥር 10 ቀን የሚከበረው የመስቀል በዓል አለና ነው ።

እርግጥ ይህ አባባል በተግባር የታየ ባይሆንም፥ በመሠረተ ሀሳቡ ግን ከእውነት የመነጨ ነው ። በዓመት ውስጥ የሥራ ቀን አንዲት ቀን ብቻ ናት (ጥር 10) የሚሉና ለዚህም ጥብቅና የቆሙ ካህናት እንዳሉም የማይታበል ሐቅ ነው ። እንዲያውም በኢየሩሳሌም የሚሠራው ከዓመት ውስጥ አንድ ቀን ብቻ እንደሆነና ይህንንም ፈጣሪ ስለባረከው ለዓመት ቀለብ እንደሚበቃ ፥ የሚባረከተውም ከኢየሩሳሌም ውጭ ያሉ ክርስቲያን ሠርቶአደሮች በዓልሽረው ሥራ ስለሚሠሩ ረድኤት እነርሱን እየራቃቸው የኢየሩሳሌምን ሰዎች ግን እየቀረባቸው እንደሚበረክትላቸው እየተረኩ ሥራ በማስተውና በማሳነፍ በረሀብ እንዲቀጣ የሚገዝቱ የግል ጥቅም ያጠቃቸው ቄሶችም ሆኑ ቄስ ቆሞሶች አሁንም ይገኛሉ ።

ከዚህ ላይ ጠለቅ ብለን ልናስብና ልንገነዘብ የሚገባን ፥ እንደቤተ ክህነት አመለካከት ፥

ሀ- በመሠረቱ በዓመት ውስጥ በዓል የማይውልበት አንድም ቀን አለመኖሩን

ለ- የግዝት በዓላት የሚባሉትን ብቻ ሳይሆን በዓልን ማክበር ጽድቅ የሚያስገኝና እንዲሁም የማንኛውም ምዕመን ግዴታ መሆኑን ፥

ሐ- ሥራ መሥራት ኃጢአት መሥራት መሆኑን ነው ።

እነዚህ እውነታዎች ረዘም ላለ ጊዜ በተለይም ከ15ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አጋማሽ ጀምሮ በኢትዮጵያ ክርስቲያኑ ኅብረተሰብ ክፍል ላይ ከፍተኛ ተጽዕና ያሳደሩ፥ አስተሳሰቡንና አመለካከቱንም የጎሩና ርዕዮ ተዓለሙንም የሰረጹ ናቸው ማለት ይቻላል ።

አንድ አማኒ በዓላትን የሚያከብረው ከሞት በኋላ መንግሥተ ሰማያትን እወርሳለሁ በማለት ብቻ ሳይሆን በዓላትን መሻር፥

ሀ- በሚኖርበት ኅብረተሰብ ዘንድ የተጠላና የተወገዘ የሚሆን መሆኑን ከመገንዘቡም በላይ በማኅበራዊ ኑሮውና ግንኙነቱም ከፍተኛ ችግር እንደሚያደርስበት ፥

ለ- እርሱ ወይም ከቤተሰቡ አንዱ ያለዚያም መላ ቤተሰቡ ያለዕድሜው እንደሚቀሰፍ ፥ በዓል መሻሩም እንደኃጢአት ተቆጥሮበት ኃጢአቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንደሚተላለፍ ፥

ሐ- ሀብቱ ንብረቱ እንደሚወድምበት፥ ያዘመረው አዝመራ በበረዶና በውርጭ እንደሚጠፋበትና ፥ ወቅቶ ያገባው እህልም እንደማይበረክትለት ከልጅነት እስከ ዕውቀት ባለው ዘመኑ ወላጅ ቤተሰቡና የአካባቢው ኅብረተ

Digitized by Google

ሰብ በይበልጥም የቀበሌው ቄሶች ያሳ
ደሩበት አጉል እምነትና ልማድ ነው።
በመሆኑም ፍርሀትና ጭንቀት በአስተ
ሳሰቡ ውስጥ ስርጸው የኀሊና ዕረፍት
ያሳጡታል ።

ይህም ማለት አንድ ገበሬ ፣ ለምሳሌ ዝና
ም ያለወቅቱ መጥቶ የጤፍን አዝመራ የሚ
ያጠፋበት ስለሆነ የታኅሣሥ በዓታ በምት
ውልበት ቀን ጤፍ ሲያጭድ ቢውል ሲሞት
ገሀነም እሳት ውስጥ ገብቶ መኰነኑ ብቻ ሳይ
ሆን በሕይወቱ ሳለም በዓታ ተቆጥታ ያለ
ዕድሜው እንደምትቀስፈው ፣ ወይም የነጣ
ያጣ ድሀ እንደምታደርገው ወይም ያገኘ
ውን ሁሉ እንደማታበረክትለት በማመኑ
አጨዳውን ትቶ ቁጭ ብሎ ይውላል ማለት
ነው ። ዓመት የለፋበት የደከመበት የጤፍ
አዝመራ ግን በዝናም ይወድማል ። አንገብ
ጋቢ ሥራውን ትቶ በዓታን ሲያከብር የዋ
ለው ገበሬም በቤተ ክርስቲያን ዘንድ እውነ
ተኛው ፤ ጻድቁና የእግዚአብሔር ሰው መ
ሆኑ ይመዘገብለታል ። በዚህም መሠረት
በታኅሣሥ አዝመራው በዝናም ሲጠፋበት
እያየ ታኅሣሥ በዓታን ፣ የታኅሣሥ አቦን ፣
የታኅሣሥ ሥላሴን ፣ የታኅሣሥ ሚካኤልን፣
የታኅሣሥ ገብርኤልን ፣ የታኅሣሥ ባለእግ
ዚአብሔርንና በታኅሣሥ ውስጥ የሚውሉ
ትን ስምንቱን የቅዳሜና የእሁድ ቀናትን
ያከበረ ፣ ጻድቅ ሰው ሲባል አላከብርም ብሎ
የደከመበትን ሰብል ከጥፋት ለማዳን ጤፉን
ያጨደ ሰው ግን ኃጢአተኛ ሆኖ ይቆጠራል
ማለት ነው ። ኃጢአተኛ መሆን ደግሞ በወ
ዲያኛው ዓለም ተፈጻሚት ለሌለው ዘመን
በእሳት ሲቃጠሉ መኖር መሆኑን ተነግሮ
ታልና የስቃይ ስሜት ይሰማዋል ።

«ይህ ዓለም የስቃይ የመከራ ዓለም በመ
ሆኑ ለወዲያኛው ዓለም አስብ ፤ ከሞ
ትህ በኋላ ከ—እስከ በማይባል መጨረሻ
በሌለው ዝንተዓለም የምትኖረው ኑሮ ምን
ዓይነት እንደሆነ የሚወስነው በመሬት
ሳለህ በምትሠራው ተግባር ነው ።
ማለትም እርሻን ፣ አጨዳን ፣ እህል መውቃ
ትን ፣ የዕደ ጥበብ ሥራ መሥራትን ወዘተ..
ትቶ በዓላትን ማክበር፣ ጾም መጾም፣ ወዘተ»
ተብሎ ከልጅነት እስከ እውቀት የተሰበከ
ለት ገበሬ ወይም ሠራተኛ እውነተኛውንና
ትክክለኛውን የሥራ ጽንሰሐሳብ ግንዛቤ
ተምሮ እስከጨበጠ ድረስ ይሽ ዓይነት ስብ
ከት ያሳደረበትን የተሳሳተ ግንዛቤና መን
ፈሳዊ ተፅእኖ በራሱ አነስተኛ ግንዛቤ ረዳ
ትነት ሰብሮ መውጣት ያዳግተዋል ። ለመ
ሆኑ ሠርቶ መብላትን ኃጢአት አድርጎ
መመልከት ትክክል ነው ? ብሎ እንዳይጠ
ይቅና እንዳይመራመር የመመርመርና የመ
ጠየቅ ችሎታው በጣም ዝቅተኛ ነው ። ያለ
ፈበትም የፊውዳል ሥርዐተ ማኅበር ይህ
ን አይፈቅድለትም ። ነገሮችን ተመራምሮ
እንዲያውቅ ሰፊውን ሕዝብ ከማገዝና ሁኔ
ታዎችንም ከማመቻቸት ይልቅ ለነገሮች
ባዳና እንግዳ ሆኖ መቀመጡ ለሥርዐቱ
ሕልውና አብነት ሆኖ በመቆጠሩ ይበል
ብሎ ይቀበለዋል ።

የሕይወቱና የማኅበራዊ ዕድገቱ፣ የሳይን
ሳዊ እውቀቱና የትክክለኛ አመለካከቱ፣በአጠ
ቃላይ አነጋገርም የቁሳዊና የመንፈሳዊ ሕል
ውናው ምንጭና ዋስትና የሆነውን ሥራ
ከበዓል ማክበርና መሻር እንዲሁም ከኢ
ሳይንሳዊ እምነት ጋር አያይዞ «በዚህ በዓል
ቀን ብታርስ ፣ ብታጭድ ፣ እህል ብትወቃ ፣
ወዘተ . . . በወዲያኛው ዓለም ትኰነናለህ
ባትሠራ ግን ትጸድቃለህ» እያሉ ቁሳዊ አመ
ለካከቱን በሀሳባዊ አመለካከት እንዲዋጥ
አድርገው ለእነሱ ፍላጐት ተገዥ ያደርጉ
ታል ። በእርሱ ቁሳዊ ድካም ውጤትም የእ
ነርሱን ቁሳዊ ፍላጐት ያረኩበታል ። በመ
ሆኑም ቤተ ክርስቲያን ፣

ሀ. ስለሥራ ያለውን በጎና ትክክለኛ አመ
ለካከት ወደተሳሳተ ትርጉም እንዲለ
ውጥ ፣

ለ. ‘በዓል ሽሮ የከበረ ፣ ጦም ገድፎ የወ
ፈረ የለም ’ በሚል የተሳሳተ ተረት
ለድህነት እንዲዳረግ ፣

ሐ. የሥራን ጽንሰ ሃሳብ አጣሞና አዛብቶ

Digitized by Google

የኢኮኖሚ ሕይወቱ ዕድገት እንዳያሳይና ምርታማነቱ እንዳይዳብር ፥

መ. በስንፍና ወቀመድ እንዲገባና የስንፍና ውጤቶች የሆኑትን ልመናንና ፥ ልዩ ልዩ ማኀበራዊ ጠንቆችን እንዲያካሂድ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች የሚፈጥሩ በትን ካህናት ከዚህ ተግባራቸው እንዲቆጠቡ የማድረግ ኃላፊነት አለባት።

ሰው በተፈጥሮው ከሥራ ጋር የተያያዘና ያለ ሥራም መኖር የማይችል ፥ ይልቁንም በዓለም ላይ የኀብረተሰብ ሕልውና ሥራ መሆኑ በተግባር የታየ ነው ። ሥራ የኅብረተሰብ ዕድገት ወሳኝ መሆኑ ዛሬ በሥልጣኔ የገፉና በሥልጣኔ ወደ ኋላ የቀሩ አገሮችንም የምንገመግመው ከዚህ መሠረታዊ እውነታ ተነስተን ነው ።

ሰው ካልሠራ ለሕልውናው መሠረታዊ የሆነትን ምግብንና መጠለያን እንዲሁም ልብስን ማግኘት በምንም መንገድ አይችልም ። እነዚህ ካልኖሩ ደግሞ ሰው የሚባል ፍጥረት በመሬት ላይ ሕልውና ሊኖረው አይችልም ። ራሳቸው ቁሶቹ « የሰው የሕይወቱ መጀመሪያ እህልና ውኃ ነው (ቀዳሚ ሕይወቱ ለሰብዕ እክል ወማይ) » እንዳሉት ሁሉ ሰው መንቀሳቀስም ሆነ ማሰብ የሚችለው ሲበላና ሲጠጣ ነው ። በሌላ አነጋገር «ያለሥጋ ነፍስ (ሕይወት) አትቆምም (ዘእንበለ ሥጋ ኢትቀውም ነፍስ)» ሲባል በሚያስብ አእምሮና በሚንቀሳቀስ ሥጋዊ አካሉ ውስጥ የሚዘዋወረው ደሙ ተፈጥሮአዊ ተግባራቸውን ማከናወን የሚችሉት ምግብና መጠጥ ፥ መጠለያ እና ልብስ ሲያገኙ ብቻ ነው ። እነዚህ ነገሮች ደግሞ የሚገኙት ሰው የሥራ ኃይሉን ከተፈጥሮ ጋር ሲያቀናጅ ነው ። የእነዚህ ነገሮች ማለትም ምግብ ፥ ልብስና መጠለያ በብቃትም ሆነ በዝቅተኛ ደረጃ በሰው ጉልበት አማካኝነት መገኘት እስካልተቻሉ ድረስ እምነትና አምልኮት ፥ ትሩፋትና ሌሎችም የአእምሮና የአካል እንቅስቃሴ ውጤቶች ሰው በተባለው ፍጥረት ውስጥ በተግባር መታየት ቀርቶ መሠረተ ሕልውና የላቸውም ። ያለምግብ ሰው የሚባል ነገር መኖር አይችልምምና ።

እንግዲህ ሥራ የሰው ቀዳሚ ሕይወቱ ከመሆኑም በላይ የማሰብ ችሎታውና የአካላዊ እንቅስቃሴው መሠረተ ሕልውና ዕድገትም ምክንያቱና ውጤቱ ነው ። በዚህ አንፃር ፥ እምነት ከሰው አስተሳሰብና አመለካከት ጋር የተያያዘ ነው ። ይህንንም ቀደም ብለን ተመልክተናል ። የአስተሳሰብና የአመለካከት ምንጭና ዕድገትም ሥራ ነው ። ሰውን እንዲያስብና እንዲንቀሳቀስ በአጠቃላይ ሕይወት እንዲኖረውና እንዳይኖረው የሚያደርገው ሥራ መሆኑ እየታወቀ በእንደዚህ ያሉ በዓላት መሥራት የለበትም የሚለው አመለካከት የሰውን መሠረታዊ ሕልውና የሚቃረን በመሆኑ ትክክል አይደለም ። « ጽድቅና ኩነኔ » የተባሉትም ጽንሰ ሀሳቦች ከሥራ ጽንሰሀሳብ ጋር ተያይዘው መቅረባቸው አግባብ አይኖረውም ።

በመሠረቱ የጽድቅና የኩነኔ ጽንሰ ሀሳቦች አመጣጥ ከሥራ ጋር የተያያዘ አልነበረም ። የአምልኮት ሰዎች ለሚያመልኳቸው ነገሮች ማለትም በዓይን የሚታዩ በእጅ የሚዳሰሱ ይሁኑ አይሁንም ለእነርሱ መስዋዕት ማቅረብና እነርሱን ያስደስታል ብለው የአመኑበትን መሥራት ከሕመምና ከደዌ የሚፈውስና የሚያጸድቅ እንደሆነና ይህንን አለመፈጸም ግን ለሕመምና ለደዌ የሚዳርግና የሚያስኮንን አድርገው ያምኑ ነበር ። የሰው ልጅ ሕልውና መሠረት የሆነው ሥራ ግን የጽድቅና የኩነኔ ምክንያት ውጤት ነው የሚለው እምነት የእምነት ጥንተ ባሕሪይም አልነበረም ። ይህም ማለት « በማርያም በዓል አንድ ገበሬ አርሶ አርሞና አጭዶ ምግቡን ስለአገኘ ፥ ዛፍ ቆርጦ ፈልጦ መጠሊያውን ስለሠራ ይኮነናል ፥ ይህን ካላደረገ ግን ይጸድቃል» የሚል አስተሳሰብ የእምነት ጥንታዊ ፈርጅ አይደለም ። ከዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባ «ሰንበት ለሰው ተፈጠረች እንጂ ሰው ለሰን

Digitized by Google

በት አልተፈጠረም ፤» የተባለውን አባባል
ነው ። ይህም ማለት ስለሰንበት ምንነት የሚ
ኖረን ግንዛቤ የዕረፍት ቀን በመሆኑ በሰን
በት ሥራ ያልሠራ ጽድቅ ያገኛል በሚለው
አንገር ሳይሆን ሲሠራ የሰነበተ አእምሮና
አካል ምርታማነቱ እንዳይቀንስ ጤንነቱ
እንዳይቃወስ ከሰባት አንድ ቀን ዕረፍት
ማድረግ ያለበት መሆኑን ነው ።

ሥራ በጥንትም ኅብረተሰብ ሆነ በዘመና
ዊ ኅብረተሰብ ዘንድ ከሞት በኋላ ይኖራል
ተብሎ ለሚታለም ጽድቅና ኩነኔ ምንጭ
ነው ተብሎ አይታመንም ። ምንጭነቱ ግን
ኤንግልስ «የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሊቃውንት
እንደሚሉት ሥራ የማንኛውም ሀብት ምን
ጭ ነው ። በእርግጥም ወደ ሀብት የሚለወ
ጠውን ቁስ ከምታስገኘው ተፈጥሮ ቀጥሎ
የሀብት ምንጭ ሥራ ነው ። ሥራ ለማንኛ
ውም ለሰው ልጆች ሕልውና ዋና መሠረታ
ዊ ሁኔታ ነው ። እንዲያውም ከዚህ አል
ፈን ተርፈን ሰውን ራሱን የፈጠረው ሥራ
ነው ማለት አለብን »[19] እንዳለው ነው ።

እንግዲህ ስለ ኩነኔና ጽቅቅ የሚያምኑት
ና የሚያስተምሩት ቄሶች በማርያም፣ በሰን
በት ፣ በሚካኤል ፣ በመድኃኒዓለም በዓላት
ሥራ ሠርቶ መብላት ያስኮንናል ብለው ከሚ
ያስተምሩ ይልቅ እነዚህንና ሌሎችን በዓ
ላት «ሥራ በመሥራት አስቧቸው» ብለው
ቢያስተምሩ በረሀብ ላይ በአጠቃላይም
የሰውን ልጅ ቁሳዊና መንፈሳዊ ዕድገት
በሚያቀረቅዘው ድህነት ላይ በሚደረገው
ዘመቻ ከፍተኛ ሚና በተጫወቱ ነበር ።
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የም
ትቀበላቸው ከታምረ ማርያም እስከ ስንክ
ሳር ድረስ ያሉት መጻሕፍት ፀረ—ምርት
የሆነው ይዞታቸው ሁሉ የኢትዮጵያ ሠርቶ
አደር በተለይም ገበሬው ካለው ሌት ተቀን
የመሥራትና ከፍተኛ ምርት የማስገኘት ፍላ
ጐት አኳያ እንደገና መመርመርና መስተካ
ከል ይኖርባቸዋል ። በአሁኑ ወቅት «በዓል
ሽረህ ሠራህ» እያለ የሚያወግዝ መነኩሴ ፣
ቄስ ፣ ወዘተ . . . ከስህተቱ ሊታረም የሚያ
ስችል ተገቢ ትምህርት ሊሰጠው “ይህን
በዓል ሽሮ የሠራ ገበሬ ወይም ሌላ ሠርቶ
አደር በነፍስ በሥጋው ይቀጣል ፣» እያለ
የሚተርክ የቤተክርስቲያን መጽሐፍ ይዘቱ
ሊሻሻል ይገባል ።

በዚህ አኳያ ፣ አንድ የቤተ ክርስቲያን
ባለሥልጣን ሥራን በሚመለከት ቤተክ
ርስቲያን ያላት አመለካከት ምንድን ነው ?
ብለን ለጠየቅናቸው ጥያቄ ሲመልሱ «እግ
ዚአብሔር የፈጠረው ዓለም በሥራ ፈቶች
እጅ እንዲያዝ ፈቃዱ አለመሆኑን ያስረዳል።
በክርስትና እምነት ስንፍና ወይም ሥራ
ፈትነት የተወገዘ ከመሆኑም በላይ የኃጢ
አት ምንጭ ነው ። . . . ቤተ ክርስቲያናችን
ምዕመናንን አዘውትራ ሥራን ለነገ አት
በሉ ፤ ለነገ ማለት ይቅር ፤ ሰውነታችሁን
ዘወትር በአዲስ ዕቅድ ፣ በአዲስ መንፈስ
በሥራ አድሱት ፣ እያለች ታስተምራለ
ች»[20] በማለት ተናግረዋል ። በወር ውስጥ
ካሉት ቀናት መካከል በትንሹ ከመቶ ስድሳ
ሰባት እጅ የሚሆኑት ቀናት በዓላት መሆ
ቸውን ቀደም ብለን ተመልክተናል ። ታዲ
ያ ቄሶች በእነዚህ ቀናት ሥራ አይሠራም
እያሉ ሠርቶ አደሩን ሕዝብ በግዝት እያስ
ስፈራሩ ቁጭ አድርጐ ማዋል ሥራ ማስፈ
ታት ወይም ስንፍናን ማስተማር ነውና ሊቁ
የሰጡት አስተያየት በተግባር ሊውል ይገ
ባል ።

ከዚህ በላይ አንድ ጸሐፊ በቤተክርስቲ
ያን በዓላት ምክንያት የኢትዮጵያን ገበሬ
ሥራ ፈት መሆን በጥሞና ተመልክቶ
«የኢትዮጵያ ገበሬ በዓመት ውስጥ እርሻ
ላይ የአዝመራውን ወቅት ጨምሮ የሚገ
ኘው 136 ቀናት ብቻ ነው»[21] ብሎአል ።
እርሱ እንዳለው በመሠረቱ በዓመት
ውስጥ ካሉት በዓላት መካከል አንድ
ገበሬ የሚያከብረውን አክብሮ ፣ የሚሽረ
ውን ሽሮ ሥራ የሚሠራባቸው ቀናት ከ125
እስከ 136 ቀናት ናቸው ቢባል ከእውነት
የራቀ አይደለም ። ይህም ማለት ሥራ ፈት
ሆኖ የሚውልባቸው ቀናት ከ229 እስከ 240
ይሆናሉ ማለት ነው ።

Digitized by Google

ሥራ ፈትነት የሚያስከትን ከሆነ የኦርቶዶክስ እምነት ያላቸው ሠርቶ አደሮች ከ229 እስከ 249 በሚሆሆኑ ቀናት ሥራቸውን ትተው ሲውሉ ስታይ ፣ ቤተ ክርስቲያን ይኸን ድርጊት መቃወምና ባላት የሕዝብ መገናኛ ዘዴ ማለትም በጋዜጦች ፣ መጽሔቶች ፣ በየቤተክርስቲያኑ አደባባይ በምታደርገው ስብከት ሕዝቡን ሚካኤል ገብርኤል ፣ ወዘተ . . . እያለ ሥራ ፈትቶ እንዳይውል ማስተማር ይኖርበታል ። ይህንን የተሳሳተ አቋም መገንዘብ የጀመሩ አንድ የቤተ ክርስቲያን ሊቅም« የእምነት መሠረቱ ሰው ነው ፣ የሰው የሕልውናው መሠረት ደግሞ ሥራ ነው ፤ ሰው ያለሥራ መኖር አይችልም ፤ ሰው ካልኖረ ደግሞ እምነት የለም ፤ እምነት ከሰው ፍጥረት በኋላ የመጣ እንጂ ሰው ከእምነት በኋላ የተገኘ አይደለም ፤ ለዚህ አንድ ጥሩ ምሳሌ አለ ። « ሰንበት ስለሰው ተፈጠረች እንጂ ሰው ስለ ሰንበት አልተፈጠረም (ሰንበትስ ተፈጥረት በእንተ ሰብእ ወአኮ ሰብእ በእንተ ሰንበት)» ያለውን በትክክል ስናጤነው ሥራ ለሰው ልጅ በፀጋ የተሰጠው እንጂ በርግማን የተሰጠው አይደለም ። ይልቁንም ሥራ መፍታት ራሱ የኃጢያትና የወንጀል ምንጭ ነው ። ሰው ሥራ ከፈታ ይሠርቃል ፣ ይቀማል ፣ ይለምናል ፣ ይጣላል ፤ ነፍስም ከማጥፋት ደረጃ ይደርሳል ። ለምን ቢሉ ካልሠራ ለሕልውና መሠረታዊ የሆነውን ምግብ ፣ ልብስና መጠለያ አያገኝምና ፤ ግዴታ ወደዚህ መጥፎ ተግባር ይሠማራል ። ይህን ደግሞ እምነት ራሱ የሚቃወመው ነው ። ስለዚህ አንድ ሰው እየራበውና እየጠማው ገብረኤልን ፣ ማርያምን ፣ መድኃኒዓለምን . . . አከብራለሁ ብሎ ሥራውን ቢተውና በረሀብም ምክንያት ቢሞት ራሱ ሰውየው ኃጢያተኛ ነው ። ምክንያቱም ሠርቶ መብላት ሲገባው ባለመሥራቱ የራሱን ነፍስ አጥፍቶአልና ፤ . . . » በማለት ሰፋ ያለ አስተያየት ሰጥተዋል ።

በእውነቱ በእነዚህ ሊቅ የተጠቀሱት አያሌ መሠረታዊ ቁም ነገሮችን ቤተክርስቲያን ተቀበላ በተግባር ልታውለው ይገባል ።

ስለበዓላት አከባበርም ያላትን ድንጋጌና አመለካከት እንደገና መመርምር ይኖርባታል ። የሰው ልጅ ከረሀብ ፣ ከጉስቁልናና ከማይምነት በአጠቃላይ ከድህነትና መሰል ጠንቆች ለመላቀቅ የሚችለው በሥራው ወይም በሥራ ምርታማነቱና በሥራ የፈጠራ ችሎታው መሆኑን ተገንዝባ ሥራን ትቶ በዓል ማክበር ራሱ ኃጢአትና ወንጀልም እንደሆነ በይፋ ማወጅና ማስተማር አለባት ። መሥራት የሚችሉ እጆችና መፍጠር የሚችል አእምሮ በበዓላት ሰበብ እንዳይሠሩ ከልክሎ ምርትን መቀነስ ኅብረተሰቡን ከችግር ለማላቀቅ የሚያደርገውን ጥረት የሚጻረር በመሆኑ ይህ ድርጊት በእምነት አስተሳሰብ ከፍተኛ ኃጢአት ሆኖ ሊታይ ይገባል ። ያለመሥራት ውጤት ድህነት ፣ የድህነት ውጤት ደግሞ ረሀብና በረሀብ መሞት ነውና ።

ይህንን በመገንዘብ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከአማኞችዋ ሥራ ወዳድነትና የምርታማነት መንፈስ አንፃር ስለበዓላት አከባበር አሁን ያላትን አስተያየትና አመለካከት በመለወጥ ፣

— መንግሥት ብሔራዊ በዓላትን በአዋጅ ሲደነግግ ዓበይት ናቸው የተባሉት የእምነት በዓላትም አብረው እንዲከበሩ ያደረገ መሆኑ የሚታወስ ነው ። ይህንን እንደበቂ በመቁጠር በሌሎች የእምነት በዓላት ቀናት ሕዝቡ ሥራ ፈትቶ እንዳይውል ግልጽ መመሪያና መግለጫ ማውጣት ፣

— ሥራ ክቡርና ቅዱስ ነው፤ የሰውን ልጅ በሕይወት እንዲኖርም የሚያደርገው የሥራ ውጤት ነው ። በመሆኑም ለምሳሌ አንድ ገበሬ ሚካኤል ፣ ገብርኤል ማርያም ፣ ወዘተ . . . ሳይል እርሻ ማረሱ ፣ መከሩን መሰብሰቡ ፣ ጤፉን መውቃቱ ኃጢአት አለመሆኑን በግልጽ ማስተማር ፣

Digitized by Google

— በከተማም ሆነ በገጠር ያለውን ሠርቶ አደር ሕዝብ «ሥራ ሠርተህ በዓል ሻርክ ፣ ጾም ገደፍክ፣ ወዘተ . . . እያሉ ከንቃተ ኅሊናቸው ዝቅተኛነትና ከግል ጊዜያዊ ጥቅምም የተነሳ በመገዘት ሥራ አስፈትተው የሚያውሉትን ቄሶችም ሆነ 'ባህታውያን ' ነን ባዮች በማስተማርና በመቆጣጠር ከዚህ ዓይነት አድራጐታቸው እንዲቆጠቡ ማድረግ ፣

— በየመንደሩና በየቤቱ እየዞሩ ፀረ ሥራና ፀረ-ምርታማነት የሆነ አጉል ትምህርት የሚሰጡትን አንዳንድ «የንስሐ አባቶች» ስለ ሥራ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግና ከምዕመናኑ ጋርም የሚኖራቸውን የግንኙነት መስመር መወሰንና መቆጣጠር ኃላፊነቷ እንደሆነ መገንዘብ ፣

— መንፈሳዊውን ዓለም በማጋነን ፣ ምድራዊውን ዓለም በማንቋሸሽና በማጥላላት በሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብ ላይ ፍርሀትን ፣ ጭንቀትንና የመንፈስ መሸበርን የሚያሳድሩትን፣ ቁሳዊ ዕድገቱን እንዲንቅ የሚገፋፉትን መጻሕፍትንና ሌሎችንና ጽሑፎች የሰፊውን ሕዝብ የሥራ መንፈስና ምርታማነት በማይፃረር ሁኔታ ማስተካከል፣

— በሌላ በኩል ቤተክርስቲያን የሰፊውን ሕዝብ ኑሮ የተስተካከለ ለማድረግ ከሚደረገው ጥረት አኳያ በዓል ለማክበር ተብሎ በሚደረግ ድግስ አማካይነት ብኩንነት እንዳይሰፍን ምዕመናንን በማስተማር የበኩሏን አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅባታል ።

የግርጌ ማስታወሻ

1. An Outline of Social Development — Precapitalist Society, Part I (Moscow: Progress Publishers, 1969 E.C.) (Duplicated Sheet), p. 28.
2. *Ibid.*, pp. 29-30.
3. ጐርጐርዮስ (አባ) ፤ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ፤ አ.አ. ፤ 1974 ገጽ 127
4. ፍትሐ ነገሥት ፣ ንባብና ትርጓሜው አ-አ- ፣ 1958 ገጽ 266
5. የሐዋርያት ሥራ ፣ ም- 8 ፣ ቁ-26—36
6. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ፣ የኢትዮጵ ታሪክ ፣ ከአፄ ይኩኖ አምላክ እስከ አፄ ልብነ ድንግል ፤ አ-አ- ፣ 1966 ፣ ገጽ 193
7. ከዚሁ መጽሐፍ ገጽ
8. Ulendroff. E., The Ethiopians, pp. 120-121.
9. Hyatt, H.M. The Church of Ethiopia, p. 176.
10. Aymro Wondmagegnhu and Motuvu, J. (ed), The Ethiopian Orthodox Church, pp. 127-128.
11. ሀብተማርያም ወርቅነህ ፣ የበዓላት ብዛት የቤተክርስቲያን ትምህርት አይደለም ፣ አዲስ ዘመን (ቅ-30 ፣ ቁ-127 ግንቦት 26 ቀን 1962 ፣ ገጽ 2
12. ከዚሁ ጽሑፍ ፣ ገጽ 2
13. ስንክሳር ፣(የመጋቢት ወርን ይመልከቱ ፣)
14. የብዙ ሰዎችን አስተያየት በመውሰድ ነው
15. ኦሪት ዘፍጥረት ፣ ም- 3 ፣ ቁ-17—19
16. ዘርዓ ያዕቆብ ፣ መጽሐፈ ብርሃን ፣ ገጽ 13
17. Workaferahu Kebede, All Play and no Work, *Addis Reporter,* Vol. I, No. 41, p. 7.
18. *Ibid.*, p. 7.
19. Engles, F., The Part Played by Labour in the Transition from Ape to Man, Progress, Moscow, 1949, p. 3.
20. ገብረማርያም ፈለቀ(ሊቀሥልጣናት)፣ የቤተክህነት መንፈሳዊ ፍርድ ቤት ሰብሳቢ
21. Workaferahu Kebede, *All Play and no Work, Addis* Reporter, Vol. I, No. 41, 1969, p. 6.

Digitized by Google

የመስከረም መጽሔት

ማውጫ*

ከቁጥር 1 – 18

በኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወሩ የሚወጣው መስከረም መጽሔት ፣ ከመስከረም 1973 እስከ ሰኔ 1976 ድረስ በአራት ቅጾች አሥራ ስምንት ተከታታይ ቁጥሮችን አውጥቷል ። መጽሔቱ ብዙ ትምህርታዊ ጽሑፎች ፣ አስተያየቶችና የምርምር ውጤቶችን ያዘለ ነው ። በእነዚህ የአራት ዓመታት ጊዜ ውስጥ በመጽሔቱ የወጡትን ጽሑፎች ወደኋላ መለስ ብሎ ለመመራመር ፣ በጽሑፉ ለመጠቀም ፣ አስተያየቶቹን ለማገናዘብና እንዲሁም ለሌሎች ጥናቶች መነሻ በመሆን ይረዳ ዘንድ የስምና የአርዕስት ማውጫ ተዘጋጅቶለታል ። ይህ ማውጫ ተገልጋዮች እያንዳንዱን ቁጥር ከማገላበጥና ጊዜ ከማጥፋት ሊድኑ ይችላሉ በሚል እምነት የተዘጋጀ ነው ።

---

* ጓድ ደገፉ ገብረ ፃዲቅ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ቤተመጽሐፍት ኃላፊ በራሳቸው አነሳሽነት ይህንን ማውጫ አዘጋጅተው ስለላኩልን የመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል ምሥጋና ያቀርባል ።

ለአንባቢያን

መስከረም መጽሔት የመጀመሪያው እትም ስርጭት 17,000 ሲሆን ባሁኑ ጊዜ የስርጭቱ መጠን 112,000 ደርሷል ።

—የመጽሔቱ የአማርኛ እትም ከቅጽ 1 ቁጥር 1 መስከረም 1973 እስከ ቅጽ 4 ቁጥር 18 ሰኔ 1976 ድረስ በ1,541,610 ቅጂ ተባዝቶ ተሰራጭቷል ።
—የእንግሊዘኛው እትምም በ54,000 ቅጂ ተሰራጭቷል ።

Digitized by Google

የስም ማውጫ

ለማ ጉተማ	ቁጥር 10	ገጽ	35—47
ለገሠ ለማ	ቁጥር 3	ገጽ	55—69
	6	ገጽ	28—52
	10	ገጽ	11—34
ላቀው አለሙ	ቁጥር 10	ገጽ	64—79
	12	ገጽ	74—88
ሊሳነወርቅ ደመ	ቁጥር 5	ገጽ	20—31
መሐመድ ሳላሀ	ቁጥር 7	ገጽ	64—81
	8	ገጽ	52—63
መስፍን ገብረ መድህን	ቁጥር 4	ገጽ	36—44
መዝገቡ ምትኬ	ቁጥር 18	ገጽ	7—22
ሞገስ ተ/ ሚካኤል	ቁጥር 12	ገጽ	15—30
ማህሉ ወ/ ጊዮርጊስ	ቁጥር 17	ገጽ	62—73
ሮቤርቶ ችጋና	ቁጥር 7	ገጽ	6—30
ሰለሞን ብርሃኔ	ቁጥር 8	ገጽ	13—23
ሰለሞን ዲባባ	ቁጥር 7	ገጽ	50—63
ሰለሞን ገብሬ	ቁጥር 4	ገጽ	9—19
ብርሃኑ ዘሪሁን	ቁጥር 3	ገጽ	70—83
	4	ገጽ	45—64
ተስፉ ገብረ ሥላሴ	ቁጥር 4	ገጽ	20—35
ተስፋዬ ለማ	ቁጥር 5	ገጽ	32—37
	6	ገጽ	53—67
ተስፋዬ ሸዋዬ	ቁጥር 15	ገጽ	13—20
ተስፋዬ አብዲ	ቁጥር 8	ገጽ	21—36
ተሾመ ከበደ	ቁጥር 5	ገጽ	6—19
	7	ገጽ	85—96
ተክለብርሃን ገ/ ሚካኤል	ቁጥር 14	ገጽ	34—57
ታምሩ ወንድም አገኘሁ	ቁጥር 16	ገጽ	9—20
ታረቀኝ አዴቦ	ቁጥር 14	ገጽ	15—33
ንሲብሆ ይፍሩ	ቁጥር 12	ገጽ	31—49
ንጉሤ አየለ	ቁጥር 9	ገጽ	14—34
እምሃ መለሰ	ቁጥር 10	ገጽ	48—63
እምሃ ዳኘው	ቁጥር 2	ገጽ	35—46
	3	ገጽ	27—35
እምሃ ማርቆስ	ቁጥር 13	ገጽ	68—84
አሰፋ ሀብቴ	ቁጥር 12	ገጽ	15—30
	18	ገጽ	23—44
አስፋው ማሞ	ቁጥር 16	ገጽ	38—52

Digitized by Google

አበበ ወርቁ	ቁጥር	13	ገጽ	68—84
		15	ገጽ	21—43
		16	ገጽ	53—69
አብዱልሀፊዝ የሱፍ	ቁጥር	2	ገጽ	11—20
		7	ገጽ	31—49
አየለ ዘውገ	ቁጥር	3	ገጽ	84—96
		5	ገጽ	38—63
አያሌው ከበደ	ቁጥር	8	ገጽ	37—51
አያልነህ ሙላት	ቁጥር	10	ገጽ	80—89
ኢሳይያስ ደምሴ	ቁጥር	9	ገጽ	46—65
		14	ገጽ	58—80
		17	ገጽ	74—84
		18	ገጽ	57—77
ከበደ ቅኩ	ቁጥር	12	ገጽ	50—73
ከበደ ገብረ መድኅን	ቁጥር	15	ገጽ	44—58
ክብሩ ገ/ መድህን	ቁጥር	12	ገጽ	74—88
ወልዴ ዮሐንስ ወርቅነህ	ቁጥር	9	ገጽ	66—90
		15	ገጽ	72—88
		17	ገጽ	50—61
ወርቁ ፈረደ	ቁጥር	13	ገጽ	13—40
ዘውዴ ስርባሮ	ቁጥር	12	ገጽ	50—73
የቆየ መንገሻ	ቁጥር	16	ገጽ	21—37
ደምሴ ኃይሌ	ቁጥር	9	ገጽ	35—45
ዳንኤል ገብረ ኪዳን	ቁጥር	2	ገጽ	21—34
		6	ገጽ	7—27
ገዛኸኝ ገብሬ	ቁጥር	3	ገጽ	7—25
ጌታቸው ሮበሌ	ቁጥር	15	ገጽ	59—71
ግርማቸው መኮንን	ቁጥር	17	ገጽ	29—49
ግርማዬ ገብረ ሄሩስ	ቁጥር	5	ገጽ	64—75
		6	ገጽ	68—95
ጠንክር ተረዳ	ቁጥር	18	ገጽ	45—56
ጥሩወርቅ ጥቀየ	ቁጥር	17	ገጽ	7—28
ጳውሎስ ደኪን	ቁጥር	10	ገጽ	90—96
		13	ገጽ	85—96
ፋሲል ተፈራ	ቁጥር	12	ገጽ	50—73
		14	ገጽ	34—57

Digitized by Google

የአርዕስት ማውጫ

የኅብረት ሥራ ማኅበራት	ቁጥር	5	ገጽ	20—31
	ቁጥር	18	ገጽ	23—44
ላቲን አሜሪካ	ቁጥር	3	ገጽ	70—83
ሌኒኒዝም	ቁጥር	3	ገጽ	85—96
ሌኒናዊ የውጭ ፖሊሲ	ቁጥር	15	ገጽ	59—71
የሐሳብ ሥርጭት ቁጥጥር	ቁጥር	15	ገጽ	13—20
የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች ተግባርና በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ውስጥ የተጫወቱት ሚና	ቁጥር	11	ገጽ	15—32
ሕግ በሽግግር ወቅት	ቁጥር	17	ገጽ	67—73
ሕግ፣ ኢንተርናሽናል	ቁጥር	16	ገጽ	9—19
ሕግ፣ ዓለም አቀፍ	ቁጥር	17	ገጽ	29—49
ሕጋዊ ምርምርችና አመለካከቶች	ቁጥር	10	ገጽ	35—47
መብት/ሰብአዊ	ቁጥር	16	ገጽ	70—80
መብትና ግዴታ	ቁጥር	18	ገጽ	7—22
መንዝሊ ሪቪው	ቁጥር	10	ገጽ	46—63
መገናኛ ዘዴዎች	ቁጥር	11	ገጽ	15—32
መገንጠል	ቁጥር	5	ገጽ	64—75
	ቁጥር	6	ገጽ	68—95
	ቁጥር	15	ገጽ	3—12
ማሌ ፓርቲ	ቁጥር	18	ገጽ	3— 5
የማሌ ፓርቲ ንድፈሐሳባዊ መሠረት፣ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ አሠራር	ቁጥር	11	ገጽ	3—14
የማሌ ፓርቲ፣ አማራጭ የማይገኝለት የትግል መሣሪያ	ቁጥር	15	ገጽ	3—12
ማርክሲዝም ሌኒኒዝም በጦርነትና በሰላም ጥያቄ ላይ	ቁጥር	13	ገጽ	85—96
ማርክሲዝምና የወቅታችን የሕዝቦች ትግል	ቁጥር	18	ገጽ	13—40
ማርክሳዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ግንዛቤ	ቁጥር	3	ገጽ	27—35
ማኅበራዊ ችግሮችና መፍትሔያቸው በአብዮቱ ሂደት	ቁጥር	12	ገጽ	89—105
ምዕራብ ሰሐራና የኢንተርናሽናል ሕግ	ቁርጥ	16	ገጽ	9—20
ምዕራቡ ዓለም	ቁጥር	18	ገጽ	45—56

Digitized by Google

ማዕከላዊ አሜሪካ	ቁጥር	9	ገጽ	3—13
የማዕከላዊ አሜሪካና የካሪቢያን ሕዝቦች				
ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል	ቁጥር	9	ገጽ	3—13
ሜይ ዴይ	ቁጥር	4	ገጽ	9—19
የሜይ ዴይ ታሪካዊ አመጣጥ	ቁጥር	4	ገጽ	32—37
ምሁር	ቁጥር	5	ገጽ	32—37
	ቁጥር	6	ገጽ	53—67
ምሁርና አብዮታዊ ሚናው	ቁጥር	5	ገጽ	32—37
ምርታማነት	ቁጥር	4	ገጽ	36—44
የምርት ግንኙነት	ቁጥር	12	ገጽ	15—30
ሥራ	ቁጥር	18	ገጽ	23—44
ሠራተኛ መደብ	ቁጥር	13	ገጽ	5—11
	ቁጥር	10	ገጽ	41—67
የሠራተኞች የትግል ታሪክ	ቁጥር	4	ገጽ	20—35
ሠርቶአደር	ቁጥር	13	ገጽ	41—67
የሥራ ምርታማነት	ቁጥር	4	ገጽ	36—44
ሥርዓተ ትምህርት	ቁጥር	11	ገጽ	54—79
የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ዕውነታ	ቁጥር	8	ገጽ	24—36
ርዕዮተ ዓለማዊ ትግል	ቁጥር	2	ገጽ	5—10
ርዕዮተ ዓለም	ቁጥር	10	ገጽ	3—10
	ቁጥር	18	ገጽ	3— 5
	ቁጥር	11	ገጽ	33—53
የርዕዮተ ዓለም ትግል አንዳንድ አጠቃላይ ገጽታዎች	ቁጥር	2	ገጽ	5—11
	ቁጥር	10	ገጽ	3—10
የርዕዮተ ዓለም ይዘት ፣ ዕድገትና ስርጭት	ቁጥር	6	ገጽ	3— 6
የሰላም ጥያቄ	ቁጥር	13	ገጽ	85—96
የሰላም ጥያቄና ዴታንት	ቁጥር	8	ገጽ	13—23
ሰብአዊ መብት	ቁጥር	16	ገጽ	70—80
ሶማሌ	ቁጥር	7	ገጽ	50—63
የሴቶች ጥያቄ	ቁጥር	17	ገጽ	7—28
ሶሻሊስታዊ ትምህርት	ቁጥር	11	ገጽ	54—79
ሶሻሊስታዊ አርበኝነት	ቁጥር	1	ገጽ	40—56
ሶሻሊስታዊ የምርት ግንኙነትን የማስፋ				
ፋት ሂደት በኢትዮጵያ	ቁጥር	12	ገጽ	15—30
በሶሻሊስት አገሮች ላይ የሚካሄድ የኢም				
ፔሪያሊዝም ደባ አንዳንድ ገጽታዎች	ቁጥር	10	ገጽ	90—96
በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ግንባታ የመንግሥ				
ትና የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሚና	ቁርጥ	5	ገጽ	20—31
የሶሻሊስት ዕድገት ፈለግና ችግሮች	ቁጥር	14	ገጽ	15—33
ሽብር ፈጣሪነት	ቁጥር	15	ገጽ	72—88
ሽግግር	ቁጥር	17	ገጽ	62—73

Digitized by Google

በሽግግር ወቅት በኢኮኖሚና በፖለቲካ
መካከል መኖር ስለሚገባው ግንኙነት ቁጥር 12 ገጽ 3—14
በቀይ ካባ ሽፋን የሚከናወን ፀረ ማርክሲስት ደባ ቁጥር 10 ገጽ 48—63
ቁጥጥር ቁጥር 7 ገጽ 3— 5
9 ገጽ 35—45
15 ገጽ 13—20
ቁጥጥርና ሶሻሊዝም ቁጥር 7 ገጽ 3—5
9 ገጽ 35—45
ቅኝ አገዛዝ ቁጥር 9 ገጽ 91—96
የቅኝ አገዛዝ የመጨረሻዎቹ ቅሪቶች ቁጥር 9 ገጽ 91--96
በረከት ሀብተ ሥላሴ ቁጥር 10 ገጽ 48—63
ቢሮክራሲና ሕዝባዊ አስተዳደር ቁጥር 17 ገጽ 50—61
ባህል ቁጥር 7 ገጽ 64—84
8 ገጽ 52—63
10 ገጽ 80—89
12 ገጽ 50—73
የባህልና የቴክኒክ መሠረተ ግንባታ በአብዮቱ ሂደት ቁጥር 12 ገጽ 50—73
ባህልና ንድፈ ሐሳባዊ ግንዛቤው ቁጥር 7 ገጽ 64—84
ቁጥር 8 ገጽ 52—63
ባህልና አብዮታችን ቁጥር 10 ገጽ 80—89
በዓላት (እምነት) ቁጥር 18 ገጽ 58—78
የብሔረሰብ ጥያቄ በኢትዮጵያ ቁጥር 11 ገጽ 80—91
የብሔራዊ ሀብት ቁጥጥር መሠረታዊ ሐሳቦች ቁጥር 9 ገጽ 35—45
ብሔራዊ አርነት ንቅናቄ ቁጥር 3 ገጽ 70—83
የብሔራዊ ኢኮኖሚ ግንዛቤና የኋላ ቀር አገ
ሮች ዕውነታ ቁጥር 15 ገጽ 44—58
ቦልሺቪክ ፓርቲ ቁጥር 2 ገጽ 21—34
የቦልሼቪክ ፓርቲ ታሪካዊ ልምድና ዓለም
አቀፋዊ አስተዋጽኦ ቁጥር 2 ገጽ 21—34
ተስፋፊ ቁጥር 7 ገጽ 50—63
ተስፋፊነትና ጠባብነት የሱማሌ ገዥ መደብ
ዓይነተኛ ገጽታ ቁጥር 7 ገጽ 50—63

Digitized by Google

ቴክኒክ	ቁጥር	12	ገጽ	50—73
ትምህርት	ቁጥር	11	ገጽ	54—79
ትግል	ቁጥር	1	ገጽ	18—27
	ቁጥር	3	ገጽ	36—54
	ቁጥር	4	ገጽ	45—64
	ቁጥር	7	ገጽ	31—49
	ቁጥር	13	ገጽ	13—40
	ቁጥር	14	ገጽ	58—80
የትግል መሣሪያ	ቁጥር	15	ገጽ	3—12
ችግር ፣ ማኅበራዊ	ቁጥር	12	ገጽ	89—104
ኋላ ቀር አገሮች	ቁጥር	15	ገጽ	44—58
ኋላ ቀር አገሮች ሁኔታ	ቁጥር	10	ገጽ	64—79
የኋላ ቀር አገሮች የውጭ ዕዳ ሸክምና የኢምፔ ሪያሊዝም የፋይናንስ ስትራተጂ	ቁጥር	14	ገጽ	81—96
	ቁጥር	1	ገጽ	28—39
ኋላ ቀርነት	ቁጥር	8	ገጽ	37—51
ኋላ ቀርነትና መፍትሔው በኢትዮጵያ				
የኢኮኖሚ ግንባታ ግንዛቤ	ቁጥር	1	ገጽ	28—39
ነፃነት	ቁጥር	18	ገጽ	7—22
የነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ የፖለ ቲካ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ	ቁጥር	3	ገጽ	84—96
ንድፈ ሐሳብ	ቁጥር	1	ገጽ	4— 6
የንግዱን ክፍለ ኢኮኖሚ ሶሻሊስታዊ ፈር ለማስያዝ	ቁጥር	12	ገጽ	31—49
አርበኝነት (ሶሻሊስታዊ)	ቁጥር	1	ገጽ	40—56
አርነት ንቅናቄ	ቁጥር	3	ገጽ	70—83
አርነት እንቅስቃሴ	ቁጥር	9	ገጽ	66—90
የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም	ቁጥር	3	ገጽ	55—69
	ቁጥር	15	ገጽ	21—43
	ቁጥር	16	ገጽ	3—7
	ቁጥር	16	ገጽ	21—37
	ቁጥር	16	ገጽ	53—69
የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ	ቁጥር	3	ገጽ	55—69
	ቁጥር	6	ገጽ	28—52
አስተዳደር ፣ ሕዝባዊ	ቁጥር	17	ገጽ	50—61
አብዮታዊ ንድፈሐሳብ	ቁጥር	1	ገጽ	4—5
አብዮት (የኢትዮጵያ) በዓለምአቀፍ ደረጃ	ቁጥር	2	ገጽ	11—20

Digitized by Google

አብዮታዊት ኢትዮጵያ	ቁጥር	7	ገጽ	6—30
	ቁጥር	7	ገጽ	31—49
	ቁጥር	9	ገጽ	14—34
	ቁጥር	10	ገጽ	3—10
በአዲሱ የትግል ምዕራፍ የሠራተኛው መደብ ሚና	ቁጥር	4	ገጽ	3— 7
አዲሱ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት በጽንሰሐሳቡ ይዘት ላይ አንዳንድ አመለካከቶች	ቁጥር	14	ገጽ	3—14
አዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት	ቁጥር	17	ገጽ	3— 6
አድህሮት/ፀረ	ቁጥር	1	ገጽ	18—27
አፓርታይድና የአርነት እንቅስቃሴ በደቡብ አፍሪካ	ቁጥር	9	ገጽ	66—90
ኢምፔሪያሊስት/ፀረ	ቁጥር	1	ገጽ	18—27
ኢምፔሪያሊዝም	ቁጥር	3	ገጽ	55—69
	ቁጥር	6	ገጽ	28—52
	ቁጥር	9	ገጽ	14—34
	ቁጥር	9	ገጽ	46—65
	ቁጥር	10	ገጽ	48—63
	ቁጥር	10	ገጽ	90—96
	ቁጥር	10	ገጽ	81—96
	ቁጥር	15	ገጽ	21—43
የኢምፔሪያሊዝም የጠብ አጫሪነት ባህሪ መባባስ	ቁጥር	8	ገጽ	3—11
የኢምፔሪያሊዝም ጦረኝነትና የሰላም ጥያቄ	ቁጥር	11	ገጽ	92—96
ኢሠፓአኮና የድርጅት ጥያቄ	ቁጥር	1	ገጽ	6—17
ኢንተርናሽናል ሞነተሪ ፈንድ	ቁጥር	10	ገጽ	11—34
ኢኮኖሚ ሥርዓት	ቁጥር	14	ገጽ	3—14
ኢኮኖሚ ዕቅድ	ቁጥር	14	ገጽ	34—57
ኢኮኖሚ ግንባታ	ቁጥር	1	ገጽ	28—39
ኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ግንኙነት	ቁጥር	12	ገጽ	3—14
ኢኮኖሚያዊ የወጪ ግንኙነት ከምንከተለው የዕድገት ፈለግ አንጻር	ቁጥር	12	ገጽ	74—88
ኢትዮጵያ/ቅድመ አብዮት	ቁጥር	3	ገጽ	55—69
		6	ገጽ	28—52
የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ትግልና የጣሊያን ፋሽስት ወረራ	ቁጥር	3	ገጽ	36—54
የኢትዮጵያ ሠራተኛ መደብ ከትላንት እስከዛሬ	ቁጥር	13	ገጽ	41—67
የኢትዮጵያ ሠራተኞች የትግል ታሪክ	ቁጥር	4	ገጽ	20—35
ኢትዮጵያ አብዮት በዓለም አቀፍ ደረጃ	ቁጥር	2	ገጽ	11—20
የኢትዮጵያ አብዮት ከዓለም አቀፍ አዮብታዊ ትግል አንጻር	ቁጥር	7	ገጽ	31—49
የኢትዮጵያ አብዮት የዓለም ሶሻሊስት አብዮት አካል ነው	ቁጥር	2	ገጽ	35—46
በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት የርዕዮተዓለም ሚና	ቁጥር	10	ገጽ	3—14

Digitized by Google

የኢትዮጵያ አብዮት ሂደትና የኢምፔሪያሊዝም ደባ	ቁጥር	9	ገጽ	4—34
የኢትዮጵያ አብዮትና የቤቶች ጥያቄ	ቁጥር	17	ገጽ	7—28
የኢትዮጵያ አብዮት የዕድገት ደረጃ	ቁጥር	7	ገጽ	6—30
የኢትዮጵያ አብዮት ከግብታዊነት ወደ				
ተቀናጀ አመራር	ቁጥር	5	ገጽ	3— 5
የኢትዮጵያ አንድነት ታሪክ ፣ በኤርትራ				
ክፍለ ሀገር የመገንጠል እንቅስቃሴ አነሳስና				
የደረሰበት ደረጃ	ቁጥር	5	ገጽ	64—75
	ቁጥር	6	ገጽ	68—95
ኢትዮጵያ ከእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ጋር				
ያደረገችው ታሪካዊ ትግል	ቁጥር	9	ገጽ	46—65
	ቁጥር	14	ገጽ	58—80
በኢትዮጵያ የድርጅት ጥያቄ እስከ ኢሠፓአኮ	ቁጥር	1	ገጽ	6—17
ኤርትራ	ቁጥር	5	ገጽ	64—75
	ቁጥር	6	ገጽ	68—95
የአብሪተኞች ባዶ ጩኸትና የራስን ዕድል				
በራስ የመወሰን ዕውነታ	ቁጥር	8	ገጽ	24—36
እንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም	ቁጥር	9	ገጽ	46—65
	ቁጥር	14	ገጽ	58—80
እድገት	ቁጥር	14	ገጽ	15—33
ካሪቢያን	ቁጥር	9	ገጽ	3—13
ካርል ማርክስና የሠራተኛው መደብ ተልዕኮ	ቁጥር	13	ገጽ	5—11
ካፒታሊስት	ቁጥር	8	ገጽ	37—51
ካፒታሊዝም	ቁጥር	13	ገጽ	68—84
የካፒታሊዝም ቀውስና የወዝ አደሩ መደብ				
የኑሮ ሁኔታ	ቁጥር	13	ገጽ	68—84
ካፒታል	ቁጥር	8	ገጽ	24—36
ኪነጥበብ	ቁጥር	11	ገጽ	33—53
ኪነጥበባትና ርዕዮተ ዓለም	ቁጥር	11	ገጽ	33—53
ኮምኒስት ማለት ምን ማለት ነው ?	ቁጥር	3	ገጽ	7—25
ኮንትሮባንድ	ቁጥር	16	ገጽ	38—52
ኮንትሮባንድ በአብዮታዊት ኢትዮጵያ				
ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ላይ ያስከ				
ተለው ችግር	ቁጥር	16	ገጽ	38—52
የወቅቱ የኢምፔሪያሊዝም ፀረ ሰላም አቋምና				
የዓለም ሰላም ኃይሎች ሚና	ቁጥር	16	ገጽ	21—37
የወቅቱ የወዝ አደር ዓለም አቀፋዊ ትግል	ቁጥር	4	ገጽ	45—64
ወዝ አደር	ቁጥር	4	ገጽ	45—64
	ቁጥር	13	ገጽ	68—84
ውጭ ግንኙነት	ቁጥር	12	ገጽ	74—88
	ቁጥር	14	ገጽ	58—80

Digitized by Google

	ቁጥር	16	ገጽ	3— 7
	ቁጥር	16	ገጽ	53—69
	ቁጥር	18	ገጽ	7—22
የውጭ ፖሊሲ	ቁጥር	15	ገጽ	59—71
	ቁጥር	18	ገጽ	7—22
የዓለም ሰላም ኃይሎች ሚና	ቁጥር	16	ገጽ	21—37
ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት	ቁጥር	10	ገጽ	11—34
ዕቅድ አዘገጃጀትና አፈጻጸም	ቁጥር	14	ገጽ	34—57
ዕውቀት	ቁጥር	2	ገጽ	47—71
የዕውቀት ንድፈ ሃሳብ	ቁጥር	2	ገጽ	47—71
ዕዳ	ቁጥር	14	ገጽ	81—96
ዕድገት	ቁጥር	12	ገጽ	74—88
ሊዘላቂው ድል አስተማማኝ መሠረት	ቁጥር	3	ገጽ	3— 6
የዘመኑ ዓለም አቀፍ ሕግ	ቁጥር	17	ገጽ	29—49
የዘመናችን የአሜሪካ ኢምፔሪሊዝም የውጭ ፖሊሲ	ቁጥር	15	ገጽ	21—34
	ቁጥር	16	ገጽ	53—69
ያለ አብዮታዊ ንድፈ ሃሣብ አብዮት አይኖርም	ቁጥር	1	ገጽ	4— 5
ደቡብ አፍሪካ	ቁጥር	9	ገጽ	66—90
ዲሞክራሲ	ቁጥር	11	ገጽ	80—91
ዲሞክራሲና የብሔረሰብ ጥያቄ በኢትዮጵያ አብዮት	ቁጥር	11	ገጽ	80—91
ከዳበሩ ካፒታሊስት አገሮች ወደ ኋላ ቀር				
አገሮች ካፒታል የሚዘምትበቸው መልኮች	ቁጥር	8	ገጽ	37—51
ዶታንት	ቁጥር	8	ገጽ	13—23
ለዘላቂው ድል አስተማማኝ መሠረት	ቁጥር	3	ገጽ	3— 6
ድርጅታዊ ጥያቄ	ቁጥር	1	ገጽ	6—17
ድንበር ዘለል የገንዘብ ድርጅቶችና /ባንኮች/				
የኋላ ቀር አገሮች ሁኔታ	ቁጥር	10	ገጽ	64—79
ገንዘብ ድርጅቶች	ቁጥር	10	ገጽ	64—79
ገንጣይ	ቁጥር	5	ገጽ	64—75
ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ	ቁጥር	3	ገጽ	84—96
የጊዜው ፀረ ኮምኒዝም ዋነኛው	ቁጥር	6	ገጽ	7—27
የጊዜያችን ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል	ቁጥር	3	ገጽ	70—83
ጋብቻ	ቁጥር	17	ገጽ	74—80
የጋብቻ ጽንሰ ሐሳብ ግንዛቤ	ቁጥር	17	ገጽ	74—80
ጦረኛነት	ቁጥር	16	ገጽ	3— 7
ጦረኛነት—የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም የውጪ ፖሊሲ				
ዓይነተኛ ገጽታ	ቁጥር	16	ገጽ	3— 7

Digitized by Google

ጠባብነት	ቁጥር	7	ገጽ	50—63
ፀረ ማርክሲስት ደባ	ቁጥር	10	ገጽ	48—63
ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል	ቁጥር	1	ገጽ	18—27
	ቁጥር	3	ገጽ	70—83
ፀረ ኮሚኒዝም	ቁጥር	6	ገጽ	7—27
ፋሽስት ወረራ	ቁጥር	3	ገጽ	36—54
ፊውዳሊዝም በኢትዮጵያ	ቁጥር	5	ገጽ	6—19
ፊውዳሊዝም ገፅታዎች በኢትዮጵያ	ቁጥር	5	ገጽ	6—19
	ቁጥር	7	ገጽ	85—96
ፋይናንስ ስትራተጂ	ቁጥር	14	ገጽ	81—96
ፓርቲ	ቁጥር	11	ገጽ	3—14
	ቁጥር	18	ገጽ	3— 5
ፖለቲካ ሥርዓት	ቁጥር	17	ገጽ	3— 6
ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ	ቁጥር	3	ገጽ	27—35
ፖሊሲ	ቁጥር	16	ገጽ	3— 7
	ቁጥር	16	ገጽ	53—69

Digitized by Google

Hoover Institution Library
3 6105 071 108 950
Digitized by Google

ዋጋው ብር 1.25

Digitized by Google